# ከምድራዊነታችን ባሻገር

## አንደኛ መጽሐፍ

## ከግለሰብ እስከ ሀገር - ማስታወሻና ማስተዋያ

መ. ኃ. መስቀል (ዶ/ር)

# ጸሎት

አቤቱ ፈጣሪአችን አምላካችን ቸሩ እግዚአብሔር ሆይ!
የእውር ሰውን ልቦና ባለ አይን ከሚያየው የበለጠ እንዲያይ
ማድረግ የምትችል አንተ ነህና፤
ይህ መጽሐፍ ለአንባብያን የሚጠቅም ሆኖ ይጨረስ ዘንድ፥
ስለአንተ ፈቃድ እለምናለሁ።
አሜን።

Copyright © 2019 - 2024 by M.H. Meskale (PhD)

አራተኛ እትም ግንቦት 2016

መልሶ የማሳተም መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

ከዚህ መጽሐፍ ሽያጭ የሚገኝ ገቢ ሁሉ
ለበጎ አድራጊ ድርጅቶች፥ ለድኩማንም መርጃ የሚውል ነው።

# መታሰቢያ

**ለባለቤቴ እና ለልጆቼ፥ እንዲሁም ለኢትዮጵያችን መሠረታዊ ለውጥ - ለዴሞክራሲ፥ ለፍትህ፥ ለአንድነት፥ ለእኩልነት እና ለነጻነት ሲታገሉ ለሞቱ መታሰቢያ ይሁን።**

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ ከእዚህ ያደረሰኝን ፈጣሪ አምላኬን በከፍተኛ ደረጃ አመሰግነዋለሁ። በእውነት ፍጹምና ኃያል፥ ስሙ ክቡር፥ ለዘለአለምም የተመሰገነ ፈጣሪ አምላካችን የጨለመውን የሚያበራ፥ ቀናውንም መንገድ የሚያሳይ፥ እኔ በእውቀት ሳይሆን፥ በብዙ ዓመታት ጥረትና በጸሎት የተጋሁበትን ሥራ አይቶ እርሱ እንደረዳኝ አምኛለሁ።

በአካላዊነት የማትታየው ባለቤቴን እና በኑሮዬ ደስ እንዲለኝ የሚያደርጉኝ ልጆቼን በጣም አመሰግናለሁ። ለደገፉኝ ለኔ ዘመዶችና ለባለቤቴ ዘመዶች ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

በቅርብም ሆነ በሩቅ ሆናችሁ በመንፈስ ላልተለያችሁኝ ወገኖቼ ሁሉ ሙሉ ምስጋናዬን ከመንፈሳዊ ፍቅር ጋር አስተላልፋለሁ።

በከፊልም ሆነ በብዛት መንፈሳዊ ትምህርትን ላስተማሩኝ (ለተማርኩባቸው) ኦርቶዶክሶች፥ ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶች ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

በእርማትም ሆነ አስተያየት በመስጠት ለተባበሩኝ ሁሉ፥ በተለይም ለወንድሜ ለአዲስ አለሙ እና ለጓደኛዬ ለተስፋየሱስ መንግሥቱ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

# የአጻጻፍ መመሪያዎች

ይህ መጽሐፍ ለምሁራኑ እንዲሁም ለሠፊው ሕዝብ ቀላል ምንባብ እንዲሆን የሚከተሉትን የአጻጻፍ መመሪያዎች ተከትሏል፡-

- አንዳንድ ቃላት በመጥበቅም ሆነ በመላላት ሲነገሩ የተለያየ (አሻሚ) ፍቺ እየሰጡ እንዳያደናግሩ፥ አንዳንድ ሆሄዎች ላይ በመጥበቅ መነገር ሲኖርባቸው ከሥራቸው ተሰርዞባቸዋል። ሁለት ፍቺ ከሚኖራቸው ውስጥ ለምሳሌ፡- አ<u>ል</u>ለይህም (ሰረዙ አንድ ሆሄ ላይ ብቻ ነው)፤ አ<u>ይገባ</u>ም (ሰረዙ ሦስት ሆሄዎች ላይ ነው)። ይህ የተደረገው፥ በተለይ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ሆኖ፥ ወይንም በውጭ ሀገር ብዙ ስለቆዩ፥ ወይንም ከዛ ስለተወለዱ፥ የአማርኛን ስነጽሑፍ ምንባብ ላልተለማመዱ አንባቢያን እንዲቀላቸው ለማድረግ ነው እንጂ፥ በዚህ ረገድ የአማርኛን ስነጽሑፍ ለማሻሻል ታስቦ አይደለም።
- አንዳንድ ቃላት በትእምርተ ጥቅስ (quotation mark) የታጠሩት፥ አረፍተነገሩ ከሚያመለክተው ውጪ ሌላም ትርጉም ሊ<u>ሰ</u>ጠው ስለሚችል፥ የመጽሐፉ ስሜት እንዳይዛባ በማሰብ ነው።
- አንዳንድ ፖለቲካዊ ወይንም ሃይማኖታዊ አመለካከቶች ሲብራሩ፥ የሚያነበው ሁሉ ከራሱ ሃሳብ ርቆ የሚሄድ ባለ አንድ አቅጣጫ አክራሪ ሃሳብ እንዳይጎላበትና እንዳይሰናከል ጥንቃቄ ተደርጓል። ምናልባት በግላጭ ወይንም በድብቅ ወገናዊነት ቢታይባቸው፥ የአንባቢ ይቅርታ ይጠየቃል።
- ከተጠቀሱት ዋቢ መጻሕፍት ሌላ፥ ተጨማሪ ማብራሪያዎች በግርጌ ማስታወሻዎች (foot notes) እንዲያመላክቱ ተደርጓል።
- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችም የተጠቀሱት፥ አንዳንድ ሃሳቦችን ከሥጋዊ እና ከመንፈሳዊ ይዘቶቻቸው ጋር የበለጠ ለማብራራት እንደሚጠቅሙ በማሰብ፥ በጥቅሶቹ ለመታገዝ ያህል ነው እንጂ፥ "በግድ" መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያመለክተው መንፈሳዊ ትርጉም ጋር ለማመሳሰል አይደለም። ሆኖም፥ አንባብያንን ለተጨማሪ ማገናዘቢያ እንዲረዳቸው፥ አብዛኛዎቹ ጥቅሶች በግርጌ ማስታወሻ ነው የተቀመጡት።

- ብዙሓኑ ሲያነቡት “የማውቀውን ቀስቅስ እንጂ አትንገረኝ” እንዳይሉ፤ በተቻለ መጠን፥ ገኃድ የሆኑ ሃሳቦች መጠቀሳቸው ለአንዳንድ የአስተሳሰብ ዘገባዎች የግድ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር፥ ተወግደዋል።
- አንዳንድ ጠቃሚ ሃሳቦች ላይ መጠነኛ ትኩረት ቢደረግ፥ አንባቢ የበለጠ እንዲያስብበትና ነገሮችን በራሱ መንገድ በጥልቀቱ እንዲመለከት ነው።
- ይህ መጽሐፍ ብዙ ንኡሳን አርእስቶችን ያቀፈ ስለሆነ፥ በአንድ በኩል አንባቢ እንዳይበዛበት ሲታሰብ፥ በሌላም በኩል ጠቃሚ ሃሳቦች ጥብብ እንዳይሉበት፥ በግርድፉም እንዳይቀሩ ጥንቃቄ ተደርጓል። በንባብ ብዙ ጊዜ ጠፍቶ ቁም ነገር የማይገኝበት እንዳይሆንም፥ የመጽሐፉ ትኩረት በብዛት አጠቃላይ ፍሬ ሃሳቦች ላይ ነው።
- አንባብያን ዘና ብለው እንዲያነቡ፥ አልፎ አልፎ ግጥሞች ታክለውበታል። የግጥሞቹም ዋና አላማ አንዳንድ ቁምነገሮችን ለማስጨበጥ (ጠለቅ ያሉ ሃሳቦችን ለማፍታታት)፥ የግል ስሜትን በማጉላትም ቢሆን፥ ደራሲና እና አንባቢ የበለጠ በሃሳብ እንዲቀራረቡ ለማድረግ ነው።

# መቅድም

የዚህን "ከምድራዊነታችን ባሻገር" የተሰኘ አቢይ ርዕስ ሳይለቅ፥ ይህ ከአራቱ መጻሕፍት የመጀመሪያ ሲሆን፥ በሃምሳ ዓመታት ውስጥ ያሳለፍናቸውን አንኳር አንኳር ጉዳዮችን ነው የሚያወሳው። የዚህ መጽሐፍ ዋና አላማ፡-

- አባቶች/እናቶች በበኩላችን የሄድንበትን ጎዳና፥ ያሳለፍነውን - ክፉውንም ደጉንም ቀጣዩ ትውልድ እንዲያውቀውና እንዲማርበት፤
- ለሀገራቸው በመቆርቆር፥ በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ የሚሳተፉ ሁሉ፥ ካለፉት የፖለቲካ ትግሎች፥ ከስህተቶቻቸውም እየተማሩ፥ የራሳቸውን ግላዊ ፍላጎት ከሀገራቸው (ከሕዝባቸው) ጋር ማጣጣምን እንዲያስቡበት እና እንዲያውቁበት፤
- ለጥሩም ሆነ ለመጥፎ ሥራ ምክንያት የሚሆን የሰው ጠባዩ ስለሆነ፥ ሁሉም የራሱን ግንዛቤ - አለማዊ (ጠፈራዊ) ርዕዮቱን እንዲመረምር፥ እናም ከአንጻራዊ እውነታዎች መካከል ወደ አንድነታችን የሚመራንን ጥሩውን መንገድ በመምረጥ፥ የጋራ ግንዛቤአችንን እንድናጠናክር፤
- ከሁሉም በላይ፥ እኛ ሥጋውያን ብቻ ሆነን ስላልተፈጠርን፥ እና ብቻችንን ስላልሆን፥ ምንጊዜም የመንፈሳዊነታችንን ነገር ከግል እና ከማሕበራዊ ኑሮአችን ጋር በማያያዝ እንድንመረምር ነው።

ስለ ሀገራችን የተጻፉ በርካታ ጽሑፎች ቢኖሩም፥ መንፈሳዊነትና መልካሙ የሰው ልጅ ጠባይ (ቅንነት፥ ደግነት፥ አዎንታዊነት፥ እውነተኛነት፥ ወ.ዘ.ተ.) ለኢትዮጵያችን ሰላም፥ አንድነት እና እድገት ወሳኝ መሆኑን በመጠቆም፥ የዚህች ምድር የመጥፎ ጎኗ ከፋት ያንገሸገሸው (ያስመረረው) ሁሉ፥ በግልጽ ከሚታየው ባሻገር "የተሻለው ቢኖርስ!" እያለ እንዲመራመርበት፥ ለመንፈሳዊ ሕይወቱም ትኩረት እንዲሰጥ - የሚያበረታታ፤ እንደ ማስታወሻ እንደ ማስተዋያም ይሆን ዘንድ ተጻፈ።

ከአለመረጋጋት ወደመረጋጋት ስንሸጋገር የሚከሰቱ ግላዊ እና ሀገር አቀፍ ክስተቶችን አብረን እንድንመለከታቸው፥ ይህና በዚህ አቢይ አርእስት ሥር የተጻፉት ቀጣይ መጻሕፍት በእጃችሁ የገባ፥ በውስጣችሁ ያለው እውነት እንዳይበረዝባችሁ እየተጠነቀቃችሁ፥ በእናንተው እንደተጻፉ እየቆጠራችሁ፥ ከአበቦች መካከል ጣፋጩን ጮርቃ እንደሚቀስሙ ወፎች፥ ወይንም ከጭቃ ውስጥ የወደቀ ወርቅ እንደሚፈልግ

ሰው ሆናችሁ፡- “ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለኔ የሚጠቅም ምን አገኘሁበት?" በማለት እራሳችሁን እየጠየቃችሁ፥ የፍሬ ሃሳቦችንም እድገትና ሂደት እየመዘናችሁ እንድታነቡ ተጋብዛችኋል።

የእውነት ምንጭ አንድ፥ እርሱም እግዚአብሔር ብቻ ነውና፤ የእርሱን እውነት እርሱው ይግለጽላችሁ።

## የሁለተኛው መጽሐፍ ይዘት፡- ከምድራዊነታችን ባሻገር - ሁሉም ለአንድነት - ማስታወሻና ማስተዋያ

ይህ መጽሐፍ አንዳንድ “ጠቃሚ” ሃሳቦችን በስእሎችና በግጥሞች ያጠናክራል። ግጥሞቹ የተዘጋጁት፥ የሚገባን ከሚመስለን በሕይወት መቆየታችንን ለማስታወሻ፥ መሠረታዊ ጥያቄዎቻችንንም እያመላለስን ለማሰላሰል እንዲረዳን ሲሆን፥ በአጠቃላይ የግጥሞቹ ይዘት በኢትዮጵያችንም ሆነ በተቀረው አለማችን ውስጥ ግለሰብአዊ፥ ቤተሰብአዊና ሕብረተሰብአዊ ኑሮአችንን ይመለከታል።

## የሦስተኛው መጽሐፍ ይዘት፡- ከምድራዊነታችን ባሻገር - ሳይንስ፥ እምነት፥ ሥልጣኔ - ማስታወሻና ማስተዋያ

ይህ መጽሐፍ ምድራችን ከመፈጠሯ በፊትና በኋላ እንዴት እንደነበር ግምታዊ - ሳይንሳዊ ማብራሪያ ያቀርባል። በጂኦሎጂ (ሥነ ምድር) ምርምር ከተገኙ መረጃዎች በመነሳት፥ በምድራችን የተከናወኑትን ተፈጥሮአዊ ክስተቶች - ተፈጥሮአዊ እድገት በአካላዊነቱ ከዝግመተ ለውጥ (evolution) እንዴት ተለይቶ እንደሚታይ ያብራራል።

ለአንዳንድ መሠረታዊ ሳይንሳዊ ጥያቄዎችም ጥንቃቄ በተመላበት መንገድ፥ ሃይማኖታዊ (መንፈሳዊ) አስተያየት ያቀርባል። ቀጥሎም፥ ስለ ሰው ዘር አመጣጥ፥ ስለ ስደቶቻችን እና ስለ ቀደሙ ሥልጣኔዎች፥ ከማንነታችን ጋር ስለሚያያዘው ስለ መንፈሳዊ አንድነታችን ጉዳይም ያወሳል። ሳይንስ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ እንጂ፥ የሚያርቅ አለመሆኑን ለማስረገጥ ይሞክራል። ሆኖም፥ ይህ እኛ “ሳይንስ - ሥልጣኔ” የምንለው ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ ቢሆንም ባይሆንም፥ ከዚህ ዘመናዊ ሥልጣኔ የተለየ “ሌላም፥ ሌላም” ሊኖር እንደሚችል ይጠቁማል።

**የአራተኛው መጽሐፍ ይዘት፡- ከምድራዊነታችን ባሻገር - መንፈሳዊ ጉዞ - ማስታወሻና ማስተዋያ**

ይህ መጽሐፍ ከምናየው አለም የማናየውን አለም ለማየት ስንሞክር የሚታሰበንን (ፍቅር፥ ደስታ፥ ሃይማኖታዊ - መንፈሳዊ ስሜት..) የሚጠቃቅስ፤ ሁሉም የገዛ እምነቱን ይዞ እንዲጸና ለየት ባለ መልክ የሚያሳስብ ነው።

**ድረ ገጽ፡- https://www.ambscience.org/**

ቀደም ሲል፥ ይህ ድረገጽ ተዘጋጅቶ አያሌ ግለሰቦች በአለም ዙሪያ ተመልክተውታል። አራቱም መጻሕፍት ከሌሎች ተጨማሪ ጽሑፎች፥ ግጥሞች እና ስዕሎች ጋር፤ ሳይንሳዊ ጽሑፎችም በዚሁ ድረገጽ ውስጥ ተካተዋል። መጻሕፍቱ እየተሻሻሉ በድግግሞሽ በታተሙ ቁጥር፥ ድረገጹም በዛ ልክ እየታደሰ ቆይቷል።

ብልህ ሰው እድሜው ሲገፋ፥ ድካም ሲሰማው፥ ሰውነቱ ሲዝል፥ ከምድራዊ ሕይወቱም መሰናበቻው ቀን መቃረቡ ሲታወቀው፥ በአፉ ያልተናገረውን ቁሳዊ ያልሆነ ሃብት፥ በጽሑፍ እና በተለያዩ መንገዶች (በስዕሎችም) መልክ አጠራቅሞ ያቆየውን ለቀሪው ትውልድ ያስተላልፋል።

አራቱም መጻሕፍት እርስ በርስ የሚደጋገፉ ሆነው፥ ከብዙዎቻችን የሃሳብ ማህደር የተቀዱ ናቸውና፤ ተመልከቷቸው።

# ማውጫ


...................................................................................................... ገጽ

ምስጋና፡ ........................................................................ iv

የአጻጻፍ መመሪያዎች፡ .................................................................. v

መቅድም፡ ..............................................................................vii

ማውጫ፡...................................................................................x

መግቢያ፡ ....................................................................................... 1

ምዕራፍ አንድ፡ ውስጣዊ ስሜታዊ ውይይት፡ ............................. 3

ምዕራፍ ሁለት፡ አብዮት እና ንቃተ ሕሊና፡ ............................... 31

ምዕራፍ ሦስት፡ የኢሕአፓ መከፈል - የአንጃዎች መፈጠር፡ ........... 41

ምዕራፍ አራት፡ ዘመቻ ወደ መርካቶ፡ ..................................... 61

ምዕራፍ አምስት፡ የብቸኛ ትግል፡............................................. 91

ምዕራፍ ስድስት፡ ሃሳቦች እና ጭንቀቶች፡..................................... 97

ምዕራፍ ሰባት፡ ቀጣይ ሕይወት በከፍተኛ አምስት፡.................... 125

ምዕራፍ ስምንት፡ ቅሪተ ሃሳብ፡.............................................. 153

ምዕራፍ ዘጠኝ፡ በደርግ ምትክ ኢሕአዴግ፡.............................. 175

ምዕራፍ አስር፡ በኢሕአዴግ ምትክ ልዩ መንግሥት፡ ................. 211

ምዕራፍ አስራ አንድ፡ የሕብረተሰቡ ጭንቀት እና የብዥታ ዘመን፡ ........ 239

ምዕራፍ አስራ ሁለት፡ መልእክት ከገደል አፋፉ ላይ፡ ......................... 263

ዋቢ መጻሕፍት

(ለአራቱም መጻሕፍት)፡ .......................................................... 317

# መግቢያ

መጻሕፍትን የመጻፍ ሥራ ከመጀሩ በፊት፥ “ለመሆኑ እኔስ ማነኝና? ምንስ አውቄ? እንዴትስ ብደፍር፤ እስቲ እራሴን በቅድሚያ ልመርምር” በማለት የምድራዊነቴን እና የነፍሴን (የመንፈሴን) ጉዳይ ሳሰላስል የቆየሁበትን፥ ለአራቱም መጻሕፍት መነሻ በማድረግ፥ “**ውስጣዊ ስሜታዊ ውይይት**” በሚል ርዕስ የተጻፈውን በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ ላይ ያገኙታል።

ይህ መጽሐፍ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) በኩል በተካሄደው አብዮታዊ ትግል ውስጥ ደራሲው ካሳለፈው ወቅታዊ ተሳትፎ በመነሳት፥ በወታደራዊው ቡድን (ደርግ) አገዛዝ ዘመን፤ በመቀጠልም፥ እስከ 2016 ባሳለፍናቸውን የኢሕአዴግ እና ቀጣዩ አምሳያ መንግሥት የነበረውን የአገዛዝ ስልት እና ሕብረተሰብአዊ ተቋም በአጭሩ ያወሳል።

በእነኚህ በ50 ዓመታት ጊዜአቶች ውስጥ “ማነው ኢትዮጵያችንን እንዲህ እያነሳ የሚጥላት?” እያልን ራሳችንን እንጠይቃለን። ታላላቅ ምድራዊ ምሁራን እና ፈላስፎች ለጥያቄዎቻችን በቂ መልስ ይሰጡን ዘንድ አልተቻላቸውም። ይህም መጽሐፍ ይህንን ጥያቄ መመለስ አይችልም። ሆኖም፥ ይህ መጽሐፍ፥ “ከምድራዊ ምልከታዎቻችን ወጣ እያልን፥ የራሳችንን ተፈጥሮአዊ ሰማያዊ ገጽታ ለሕይወታችንም እንደ መመሪያ (ምድራዊ ፖለቲካ) ብንጠቀምበት፥ ቢያንስ እርስ በርሳችን ከመጠፋፋት ያድነን ይሆናል” የሚል ጽኑ እምነት ስላለው፥ አንባቢም ይህንኑ እምነት እንዲጋሩት ሲል፥ ፖለቲካ እና ሃይማኖታዊ እሳቤዎችን በስነ አመክንዮ እያመሳጠረ ያቀርባል።

ምን ይደረግ? ቢወራም/ባይወራም፥ ቢጻፍም/ባይጻፍም፥ ግራ የሚያጋባ ሆነ የኢትዮጵያችን ጉዳይ። “ታዲያ እኔ ምን አውቃለሁ፤ ፖለቲከኛ አይደለሁ..” በማለት፥ እራሳቸውን ከሚያገሉ ሰዎች ጎን መቆጠርን፤ ብዙዎች ሰዎች የሚያወሩትንም ከልሶ ማውራት ያልወደዱ፤ “ከነገሮች ሁሉ በስተጀርባ ምን ነገር ቢኖር ነው?” ብለው ይጠይቃሉ። መልሱንም ፍለጋ ብዙ መንገድ በሃሳብ ይጓዛሉ፤ የጉዞውም አቅጣጫ በግልጽ ከሚታየው፥ በግልጽ ወደማይታየው ይሆናል። እውነት ነው፤ የሁላችንም ሕይወት በአንድ “ሁለንተናዊ እውነት” የሚመራ ነው። ታዲያ፥ ወደዚያ እውነት ለመጠጋት ዘዴው ምንድነው?

ሰዎች ይህንን እና የመሳሰሉ ጥያቄዎቻቸውን ለመመለስ ይችሉ ዘንድ፥ በብዙ የእውቀት ዘርፎች (ከሳይንስ እስከ ሃይማኖት) እጅግ ሠልጥነዋል። ነገር ግን፥ እውቀት ሁሉ፥ ለሁሉም ሰው ሊገባው በሚችልበት መንገድ ስለማይደረደር፥ ምሁራኑም በተወሰነለት (ተደንግጎ በተሰጠው!) የአስተሳሰብ አቅጣጫ እየተመሩ፥ በሕብረት ከማሰብና አብሮ ከመሆን ይልቅ፥ በተናጠል እያሰቡ መለያየት አመዝኗል። እስካሁን ያለፍንባቸውንም ጊዜያቶች ስናሰላስል፥ የሚከተሉት ሁለት ጥያቄዎች በአእምሮአችን ይመላለሳሉ፡-

1ኛ) በእውነት ይህች ድንቅ ኢትዮጵያችን በውስጧ ሰዎች ብቻ ናቸው ያሉባት - እኛ ሥጋውያን ብቻ ነን ወይ በውስጧ የምንርመሰመሰው?

2ኛ) የሰው ልጅ አስተሳሰቡ የሰው ስለሆነና፥ ያው የማይለቀው፥ ተፈጥሮ የደነገገለት ውስጣዊ ጠባዩ ስለሆነ ነወይ፥ ትውልድ አልፎ ትውልድ ሲተካ፥ ከስህተቱ የማይማረው?

ለሰው ልጅ፥ በወጣ ገብ ሕይወቱ ውስጥ፥ ለእያንዳንዱ እንደ ብጤው፥ ሄዶ ሄዶ ቆም እንዲል እና እንዲያስብ የሚያደርገው፥ ከፊት ለፊቱ ችግር እንደ ገደል ሲጋፈጠው፥ ከምድራዊው አልፎ ሰማያዊ ክስተቶችንም እንዲመራመር የሚያደርግ አእምሮ አለው። ይህም መጽሐፍ፥ በሰዎች መካከል የተለያዩ የሃሳብ ቅራኔዎች (ግጭቶች) ተደምስሰው፥ ሉላዊ አንድነታችንን እና ሰላማችንን እንድናገኝ የሚረዳንን፥ ከነገሮች ሁሉ ምድራዊ አመለካከትን እያወጣን፥ አፋዊ ገለጻ የማይበቃውን መንፈሳዊ እሳቤዎቻችንን ችላ ባለማለት (በመማር፥ በመጻፍ፥ በመወያየት፥ በተመስጦ እና በጸሎት) መንፈሳዊ አንድነታችንን በጋራ እንድናጎለብት ያሳስባል።

**መልካም ምንባብ**

# ምዕራፍ አንድ

## ውስጣዊ ስሜታዊ ውይይት

**ቶማስ**

“ኮከቤ[1] የተባለች ባለቤቴ ድንገት ብትለየኝ፥ ከሃዘን ብዛት ከምድራዊ እውነታ የወጣሁ መስሎኛል፤ እኔው ራሴ ከሁለት ተከፍዬ ብዙ አወራለሁ፥ ከእኔው ጋር።

የሰው ተፈጥሮ ሁለት ባይሆን ኖሮ፥ ብቸኝነት ሲሰማ የብቸኝነቱ ብቸኝነት ምን ያህል የከፋ ይሆን ነበር? በችግር ጊዜ የሰው ሁለትነት በገሃድ ይታወቃል። “በእውነት በውስጤ ልክ እንደራሴ ያለ ሌላ ሰው መኖር አለበት!..” እላለሁ።

ሰው ሁሉ ሁለት ስለሆነ፥ ከራሱ አምሳያ ሰው ጋር ያወራል (ይጫወታል)፤ ይህም፥ ድመት ከገዛ ጭራዋ ጋር እንደምትጫወት አይነት አይደለም በእውነት። ድመት የምትጫወተው ከገዛ ራሷ ጋር ነው፤ እኛ ግን እያንዳንዳችን “ሰውና ሰው” ሆነን ስለተፈጠርን፥ በግልጽ ለሁለት ተከፍለን ነው የምናወራው (በቀን በሃሳብ፥ በሌሊትም እንቅልፍ ሲወስድ - በሕልም ወይንም በቅዠት)።

አይ! እኔማ “ይህ የሥጋ ሰው እስኪሞት ድረስ፥ ከውስጡ አካለ ብርሃን እና መንፈስ ብርሃን ካለ መቀላቀል በውሕደት፥ ከሞቃት የሕይወት እስትንፋስ ጋር ይኑሩ፤ በሃዘኑም ሆነ በደስታው የመንፈስ ሰው አብሮት ይሁን እንጂ አይለየው፥” የሚል ውስጣዊ ስሜት ቀስቅሶኛል።

ልባዊ ጭምጭምታ - ካለ ድምጽ የሚያናግር፥

ካለ ብርሃን - እንደ እውን የሚከሰት ምስል፥

ከጎኔ - የእኔው አጋር፥

የሃዘን ጉም ሲከበኝ - ብቻዬን እንዳልቀር፥

ከውስጣዊው እኔ - ከዮሐንስ ጋር ምክክር፥

ከምድራዊነቴ ስላቀቅ - በመንፈሴ እንድከበር፥

---

[1] ከምድራዊነታችን ባሻገር - አራተኛ መጽሐፍ - መንፈሳዊ ጉዞ - ማስታወሻና ማስተዋያ።

ይህ ነው መነሻዬ - የመሰንበቴም ምሥጢር።

ከብቸኝነት የሚያወጣኝ እራሴን ስፈልግ፥ ከራሴ ውስጥ አጋር መንፈስ መኖሩ ትዝ ይለኛል። በመንፈስ እኔን የሆንክ - አንተ ዮሐንስ ነህ - ለኔ አጋር ሆነህ ከጎኔ የተቀመጥክ። ስለዚህ፥ በዚህ ጭንቅ ቀን አብረኸኝ ሁን ዮሐንስ፤ እባክህ አትለየኝ።"

**ዮሐንስ**

"አዎ! ማንም ሰው ጭልጥ ብሎ እስኪጠፋ ድረስ፥ ከሁለት አለም መካከል መጠነኛ ሽርሽር ያደርጋል። እንደምፈልገውና መሆን እንዳለበት አልሆንክም። ከነልዩነቶቻችን አብረን ብንኖርም፥ እድሜ ሲገፋ መመሳሰልና መስማማት ይመጣል በማለት አስብ ነበር። ሁለት የማይጣጣሙ ፍጡሮች በአንድ ላይ መኖር እንደማይችሉ ጊዜና ሁኔታ አረጋግጦልናል።

በስተእርጅናም ቢሆን ጨብጠህ የያዝከውን ምድራዊነትክን ጣል ብልህ አትሰማኝም። ካንተ ጋር አብሬ እንድኖር የሚያበቃ ሁኔታ ካልፈጠርክልኝ፥ ተለያይቶ መኖር ግዴታ ይሆናል።

ሰው በተፈጥሮው የተደነገገለት መንፈሱ ከሥጋው ጋር ተስማምቶ እንዲኖር ነው እንጂ፥ እየተቃረነ እንዲኖር አልነበረም። የተገነጠልኩ እኔም ልሁን አንተ፥ የመለያየታችን እውነታ እንዲህ ቁልጭ ብሎ ሲታይ፥ እኔ በበኩሌ ምንም ማድረግ አልችልም።"

**ቶማስ**

"ሰው የራሱን ቤት ይንከባከባል፤ ግርግዳው ቢወድቅ፥ ጣሪያው ቢሸነቆር፥ የበሩ ወይም የመስኮቱ እንጨት ቢበሰብስ፥ አስፈላጊውን ጥገና ያደርጋል፤ ቀለም ቀብቶ አዲስ ያስመስለዋል እንጂ፥ የገዛ ቤቱ ሲፈራርስ ዝም ብሎ አያስተውልም፤ ወይንም ጥሎት አይሄድም። እስከ ሥጋዊ ሕይወቴ ፍጻሜ የምትኖርብኝ ስለሆንክ፥ እንደ ቤት ቁጠረኝ፤ ተንከባከበኝ እንጂ፥ አሁን ከባድ ችግር በላያችን ሲወድቅ ከኔ ተገንጥለህ ለመሄድ አታስፈራራኝ።

አእምሮ ከሁለት ተከፍሎ እንደ ሁለት ሰው ሆኖ የሚያወራ ይመስል፥ አካሌ ሰውነቴ፥ ነፍሴ፥ መንፈሴ እያልኩ እለፈልፋለሁ። ባለቤቴ ተለየችኝ፤ አንተም ከኔ ተገንጥለህ ከሄድክ፥ እኔ ብቻዬን ግራ የማጋባ ልዩ ፍጡር እሆንና ሰዎች ከሩቅ ይሸሹኛል። አንድ ሰው ከራሱ ተገንጥሎ እንዴት ይኖራል? አንተ ማለት የኔ ግልባጭ

ማለት ነህ እኮ! ሁለታችንም "በምድራዊነት ክልል" ውስጥ የምንኖር ነን እኮ! ተረዳድተን አብረን እንኑር እንጂ።"

**ዮሐንስ**

"አዬ!...ከሰማይም ከምድርም መሆን አቅቶት የሰው ልጅ መንፈሱ ብቻውን ሲንከራተት፥ የሚያርፍበትም ሥፍራ ሲያጣ፥ ለማደሪያም የሚሆን ቤት ሲፈልግ፤ እህ! ከሰዎች መካከል ለኔ ማደሪያ ቶማስ ሆነህ ተገኘህ! ብቻዬን መኖር ብችልስ ደስ ባለኝ ነበር። አንተ "በምድራዊነት ክልል" የምትለውን ወዲያ ብለው፥ የራሳቸውን "የሰማያዊነት ክልል" አበጅተው የሚኖሩ እንዳሉ አታውቅም?

አዎ! እኔ ግን ብቻዬን ሆኜ ምን እንደምመስል ማወቅ እንዳልችል፥ ከምድር ተጥዬ ከአካል ጋር ተደባልቄአለሁ። አዎ! ይህ ነው የግማሹ ሰው (የሥጋ ሰው/የሰውእነት) ታሪክ - ምድራዊ ተፈጥሮ፥ ከሰማያዊ ድንጋጌዎች አንዱ (ወደ ምድር መጣል ማለት/ከገነት መባረር ማለት)።

*"የሰማይን ሥራ መርምሮ ማወቅ፥ ከሥጋው ለይቶ ነፍሱን፥ ከነፍሱም ለይቶ ሥጋውን ማየት፥ ይህ ነፍሴ ነው፥ ይህም ሥጋዬ ነው ብሎ መናገር የሚቻለው ማነው?" ሄኖክ 35፡34*

ሞት ማለት ዘላለማዊ ሁለት መከፈል ማለት ነው። ከዚያ በፊት ግን፥ የሰው ልጅ ሲጨነቅና በሃሳብ ማዕበል ውስጥ ገብቶ ሲንገላታ፥ ብዙ ብዙ ነገር ያሳስበዋል። ጭንቀት (የቁም ቅዠት) ማለት እንዲሁ የሆነ ያልሆነውን እያሰቡ፥ በቁም (ባለመሞት) ከሁለት እየተከፈሉ መሞትና መኖርን እንደ መለማመድ አይነት - ምድራዊ ውጥረት ማለት ነው። እኛም (እኔና አንተ) አዳምና ሔዋን ከገነት ደጃፍ ቆመው፥ ተመልሰው ወደ ገነት እንዳይገቡና የሕይወትን ፍሬ በልተው ለዘለአለም እንዳይኖሩ *"ኪሩቤልና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍ....." ዘፍ. 3፡24* ተከላካዮች ሆነው እንዲጠብቁ እንደተደረገው ሆነናል ማለት ነው። አዎ! በአሁኑ ሰዓት እኔና አንተ በሁለት ተከፍለን፥ ከገነት ደጃፍ ቆመናል ማለት ነው።

አንተ ግን በራስህ የምትንቀሳቀስ ነፍስ ያለህ ቤት ሆነህ፥ እኔም በውስጥህ ብኖር፥ ይህ ለጊዜው መሆኑን አስታውሳለሁ። አንተን ትቼ "እውነተኛው እኔን" ብጠብቅ ምን እንደሚሆን አላወቅሁም።

አንተ ምድርን ከሚገባው በላይ ወደሃታል። እግዚአብሔር ወዳለበት ለመሄድና ኑሮህን ከሰማይ ቤት የሚጣጣም ለማድረግ ስትል አልተጋህም። ከመንፈስም ከሥጋም ነካክተህ፥ እያታለልክ እድሜህን ልትቆጥር ፈልገሃል፤ ግን

አትችልም። ከእንግዲህ እኔም በምድር ላይ ከአንድ አካላዊ ጋር በመዛመድ ለሰብአዊነት የማበረክተው ጠቃሚ ነገር ከሌለኝ ተገነጥዬ እሄዳለሁ። ሥጋ ጊዜያዊ መኖሪያ ቤት፥ ጥቅሙ ለመሬት ስለሆነ፥ በቅቶኛል፤ ከመጣሁበት ልመለስ።

ግን! እኸ!! .. ለጊዜውም ቢሆን የምኖርበትን ቤት ላድስ - ልጠግን ብዬ ብነሳ አንተ መች እሺ ትላለህ። ምድራዊነትህ እንቅ አድርጎ ይዞህ! በስብሰህ በመውደቅ ላይ እንዳለህ እራስህ እያወቅኸው፥ አንተን ለማቅናት የሚደረገውን ሙከራ ሁሉ የምትከላከል የራስህ ጠላት በመሆንህ አንድ ወጥ እራስክን አጥተሃል።

በሁለታችን መካከል የእግዚአብሔር መንፈስ ከሌለ፥ እኔም ቀባጣሪ ነኝ። የሁኔታዎች መፈጠር ሁለታችንንም የተለያየን ፍጥረታት መሆናችንን አረጋግጦልናል። አንተ የምታደርገውና የምታስበው ሁሉ ከምድር የማይላቀቅ ነው። እኔ ላንተ ብዬ ደከምኩ፤ ካንተ ያገኙሁት ምንድነው? መንፈሳዊ ስሜቶቼን ላንተ ብዬ አልለውጥም። በጣምራነት አብረን መኖራችን ለማንም የማይጠቅም ከሆነ፥ እግዚአብሔር በፈቃዱ ይለያየናል።"

**<u>ቶማስ</u>**

"እኔ በእግዚአብሔር ሥራ ጣልቃ አልገባም፤ ግን "የለሁም" እስክል ድረስ ተስፋ ቆርጬ፥ ጎዶሎነቴ ሲሰማኝ፥ "መንፈስ አይራቀኝ፥ መንፈስ አይራቀኝ፤" እያልኩ ስማጸንህ፥ ተገነጥዬ እሄዳለሁ እያልክ ታስፈራራኛለህ፤ ጩኸቴን ስትቀማኝ፥ የኔን ላንተ አደረግህ። ምድራዊ ጭንቀት ለምድራዊ ሰው ነው፤ አንተ ምን ቀረብህ?

መናፍስት የሚያድሩበትን ሥጋ እራሳቸው እንዲመርጡ ዕድል የተሰጠበት ዘመን ውስጥ አይደለም ያለነው። በፈቃድህ ከኔ ተለይተህ ለመሄድ ምንም ሥልጣን እንደሌለህ እያወቅኸው፥ ከመስማማት ይልቅ ቅራኔዎችን ታበዛለህ። ማን ምን ብሎህ ነው እስከዚህ ድረስ ያመረርከው? ማን ምን ብሎህ ነው እስከዛሬ ድረስ እኔ የምትለውን እኔን ካንተ ለመለየት ያሰብከው?

እኔስ ፈራሁ፤ እጅግ ፈራሁ፤ ሚስት ከማግባቴ በፊት፥ "የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የተባለውን የፖለቲካ ድርጅት ሳገኝና ስቀላቀል፥ ልክ ሚስት እንዳገባ ሰው ሙሉነት ተሰምቶኝ ነበር። በእርግጥ፥ ነፍስ አውቄ፥ በጉልምስና ወቅት፥ የተበለሻሸውን የፊውዶ - ሶሻሊስት ስርዓት እያየሁ በመቆየቴ ጎዶሎነት ይሰማኝ ነበር። ኢሕአፓን ካገኘሁ ወዲህ እና፥ ከኢሕአፓ ጋር ተቆራኝቼ እስከቆየሁ ድረስ ሙሉነት ይሰማኝ ነበር። ዳሩ ግን፥ ሁኔታዎች እኔን ከኢሕአፓ ጋር መቀጥል ወደማልችልበት ጎዳና ሲከቱኝ፥ ልክ ወደማልፈልገው አለም ውስጥ ተመልሼ እንደምገባ እየተሰማኝ፥ እራሱን እንዳላወቀ ተቅበዝባዥ እና ልክ እንደ አበደ ሰው ሆኜ

ነበር። የዛን ጊዜ አእምሮአዊ ጎዶሎነት እየተሰማኝ፥ በንዴት እና በሃዘን ውስጥ ሳለሁ፥ በመኖር እና ባለመኖር መካከል ሆኜ የቆየሁበት ጊዜ ነበር።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ፥ ሚስት አግብቼ ስኖር፥ ሁሉ ነገር ተረስቶኝ፥ ሙሉነትም ተሰምቶኝ፥ ልጆችም ወልጄ ስኖር፥ ኑሮዬ ደስተኛና የተሟላ ነበር። እርሷን ሳጣ፥ ያ የጥንቱ ጎዶሎነት ተመልሶ የመጣ እየመሰለኝ፥ ፈራሁ፤ እጅግ ፈራሁ። ስለዚህም፥ እጅግ ብቸኝነት ስለተሰማኝ፥ የስነ አእምሮ መረጋጋትን ፈልጌ አንተን ጠራሁህ እንጂ፥ ገና ሳልሞት፥ ሌላ ሕያዊት፥ ልባዊት፥ ነባቢት የሆነች ነፍስን ከአንተ ሽቼ አይደለም። አንተ ግን፥ የኔው ሆነህ ሳለ፥ ልክ እንደ ባይተዋር ከኔ ተነጥለህ መኖር እንደምትችል ታስመስላለህ። አሁንም ደግሜ እጠይቅሃለሁ፤ ማን ምን ብሎህ ነው እስከዚህ ድረስ ያመረርከው? ማንስ ምን ብሎህ ነው እስከዛሬ ድረስ እኔ የምትለውን እኔን ካንተ ለመለየት ያሰብከው? አዬ.......! ወይንስ እንደ ማንም ተራ ሰው ሲደላህ የምትቀርብ፥ ሲከፋህ የምትርቅ ጥቅመኛ ነህ?"

**<u>ዮሐንስ</u>**

"ከምትለው ሁሉ ነጻ ነኝ። ስለ ነፍስ ጉዳይስ የማናውቀውን ባንቀባጥር ይሻላል። "ማን ምን ብሎህ ነው?" ላልከውስ፥ ማንም ምንም አላለኝ፤ እንዳው የበላይ ትእዛዝ ሆነና፥ ካንተ ጋር ተጣብቄ ስለቀረሁ፥ የራስ ወዳድ ምሬት ተሰምቶኝ ይሆናል።

እህ!....ምን ይደረጋል? ካለፈቃዴ ካንተ ጋር እንድቆይ ሲነገረኝ። አዎ! እኔ ላንተ የተሰጠሁ ነኝና፤ በራሴ የ<u>መለ</u>የት ሥልጣን የለኝም (አ<u>ል</u>ለይህም)።

መናፈቅ፥ መከጀል፥ መጓጓት፥

ላይደርሱበት አጉል መንጠራራት፥

ብቅ ጥልቅ አንድ ቦታ አለመርጋት፤

ባጥር ላይ መንጠልጠል፥ ዥዋዥዌ - ወዲያ ወዲህ ማለት፥

የጥሩን ጥሩነት፥ የመጥፎን መጥፎነት አለመለየት፥

አንዱን መርጦ አለመርጋት፤

ቢላሽ፥ ተበላሽቶ ማበላሸት፥

በጸሎት ፈንታ እርኩሰት፥

በጽድቅ ፈንታ ኃጢአት፤...

ጸጸት የማናውቅ፥ በኃጢአታችን የማናፍር፥

ሁሉንም ሽፍንፍን - ሽፍንፍን፥ ተብለጭልጮ መስሎ ማደር፤

ጥፋትን በሌላው ላይ ማላከክ፥ እራስን ማሞካሸት፥
ይህ ነው ይህንንም ያንንም መስሎ - አስመስሎ የሚኖር፥
መንፈሳዊነቱን አርክሶ ምድራዊነቱን የሚያከብር፥
"ቄስ መሳይ በሸንጎ" - በግላጭ ለሥጋው የሚያድር፥
ያልተዋሃደ፥ ድብልቅ የሰው ፍጥረት ማለት።"

**ቶማስ**

"እነሆ! የእራሴን የክፋት ማዕበል ለመቀነስ እና ጥሩ ሰው ለመሆን ስለፈለግሁ፥ የምሄድበትንና የምደርስበትን ሥፍራ ሁሉ ውሱን አደረግሁ። የንግግሬ ቋንቋ ወደ ጥቅል ሃሳቦች እያዘነበለ ተራ ወሬ ማውራት እስኪያቅተኝ ድረስ፥ እኔ በእራሴው ክልል ውስጥ ሆኜ፥ እህ! እኔነቴን በማሳነስ ድምጼን አጥፍቼ ተቀመጥኩ፤ አካል ሆኜና በአካል ታጥሬ ሳለሁ፥ እውነተኛውን ሰው ከውስጤ እስካገኝ ድረስ ብቻዬን ስቆይ፥ ይህ ወደ መንፈሳዊነት ያዘነበለ ኑሮ፥ ተሐድሶ መንፈስ የማገኝበት መስሎኝ።

የአስተሳሰቤ ዝንባሌ ከመንፈሳዊነት ይልቅ ወደ አለማዊነት እያመዘነ ሲያስጨንቀኝ፥ ምንጊዜም እራሴን ለማስተካከል እሞክራለሁ፤ እራሴን ለማስተካከል ስሞክር ደግሞ፥ እራሴን እጠራጠረዋለሁ። ታዲያ፥ የእኔን ምድራዊ አስተሳሰብ ለሌሎች አላስተጋባም ብዬ ከሰዎች ስርቅ፥ እህ! አንተን ያገኘሁ መስሎኝ።

እራሴን በራሴ በደልኩ፤ የሚሰማኝም ስሜት ሁሉ (የንዴት፤ የቁጣ፥ የሃዘንም ቢሆን) እኔን ተቆጣጠረኝ እንጂ፥ እኔ በእራሴ ላይ ምን ሥልጣን አለኝ? ፍላጎቴና አስተሳሰቤ አልጣጣም ሲል፥ እኔ ቤት ሆኜ በውስጤ የሚኖር ሌላ ሰው ስላለ፥ እኔ አልናገርም፤ ዝም ብዬ ልኑር አልኩ። ምነው ወቀሳ በእኔ ላይ ብቻ ደራረብክብኝ? ምነው የአንተን እኔነት ለይተህ አየኸው? እስቲ አስበው፡- በዚህች ምድር ከተፈጠርንባት ቀን ጀምሮ ማን ነበረ ቤቱ? ማን ነበረ ነዋሪው? ማን ነበረ ባለ ሥልጣን? እኔ ብቻዬን ነበርኩ ቤቱ? አንተ ብቻህን ነበርክ ነዋሪው? አንተ ብቻህን ነበርክ ባለሥልጣን?

እኔማ - እስቲ ልበል እኔማ......ማ......።
ማወቅን ያላወቅሁ - ነቅቼ ያልነቃሁ፤
በሕልም አለም እኖራለሁ፤
በእውን አለም አልማለሁ።

ሁለትነቴ ሲሰማኝ፥
ግማሽ ጎኔ ሊከዳኝ ሲያስፈራራኝ፥
ብርሃናማውን አለም ያጨልምብኛል፤
ሳልወድ አሉታዊ ያደርገኛል።

“ማወቅ” ሳለ ማወቅን ያላወቅሁ፥
ውህደት ሳለ ድብልቅ ብዬ የተለየሁ፥
ጤንነት ሳለ በሽተኛ፥
ደስታ ሳለ ሃዘንተኛ፥
ከሁለትነቴ ተገንጥዬ፥
“ስላላወቅሁ?”
መስሎኛል ብቻዬን የቀረሁ።

አይኖቼ፥ ጆሮዎቼ፥ አፌም አንደበቴም፥
የሥጋዊ እኔነቴ መገለጪያ፥
አብራኮቼ ሁሉ ከድተውኛል፤
ሁሉም በአበሳ ተፈጥረው፥ አበሳ ሆነውብኛል፤

የአበሳ አይኖቼ እየመረጡ አበሳ ያሳዩኛል፤
የአበሳ ጆሮዎቼ እየመረጡ አበሳ ያሰሙኛል።

ሰርክ አለም የእንቅልፍ አለም፥
ምን ቢጨልም መንጋቱ አይቀርም፤
ራሱን የሚወድ ራሱን አይከዳም፤
የራሱን ብርሃን በራሱ አያጠፋም።

እኔም ሳልም ከድንግርግሩ እወጣለሁ፤
ከፋም ለማም ጥርት ያለውን አያለሁ፤
ጥርት ያለውንም እሰማለሁ።

በስተእርጅና ሂሳቡን ሳስበው፥
ጠቅላላ የአንድ ወጣት ኑሮ ከዚያ (ከሕልም አለም) ብቻ ኖሬአለሁ፤
ከዚያ ሥፍራ ቤቴን መሥርቻለሁ።

ታዲያ ዛሬ እራሴን ስጠይቅ፡-

“ለምን ከዚያ ሥፍራ እበረታለሁ?

ለምን ከዚህ ስመጣ እደክማለሁ?

ለምን ከዚያ ሥፍራ አንደበተ ርቱእ እሆናለሁ?

ለምን ከዚህ ሥፍራ ስመጣ እንላደፋለሁ?

ለምን ከዚያ ሥፍራ ስሄድ ሾር እላለሁ?

ለምን ከዚህ ስመጣ ፍዝዝ እላለሁ?

ደስታዬ - እውቀቴስ ቢሆን፥ ለምን ከዚያ ሲሆን ፍጹማዊ ይሆናል?

ለምን ከዚህ ሲመጣ ድብዝዝ - ድብልቅልቅ ይላል?”

እያልኩ “ለብቻዬ” በለሆሳስ አወራለሁ፤

በዝምታ አስባለሁ።

ይቅርታ! ይህንን በአንድ ወቅት የተሰማኝን የለፈለፍኩት፥ ዝም ብሎ እየታዘቡ፥ አስመስሎ መኖር አድርባይነት ስለመሰለኝና፥ ላንተ ግልጥልጥ ስልልህ፥ አንተም በእኔ ውስጥ እራስህን ታገኘው ይሆናል ብዬ ነው።

ብዙ ብዙ መንፈሳዊ ክስተቶች ሲፈጸሙ እየታየኝ “እኔ ከኃጢአቴ እስከነጻ ድረስ ሃዘንተኛ ሆኜ፥ ደንዝዤ እቀራለሁ እንጂ፥ ማን ደፍሮ ይናግረኛል - “አንተ ሰው ለራስህ የሚጠቅምህን ባለማወቅህ ከፉኛ ተጎድተሃል” ብሎ። “እኔን ማን ሊመክረኝ ይችላል?” በማለት እራሴን በራሴ ወሰንኩ። በጭንቀቴ “እባካችሁ ይህን ታሪካዊ እንቅስቃሴዬን ሁሉ ከሰማይ ቤት መዝግቡልኝ” ብዬ መላእክቶችን ተማጽኛለሁ። መልስ አጥቼ ስጠባበቅ ብዙ ከቆየሁ በኋላ፥ እነርሱም፡- “ይህ እንቅስቃሴህ የሥፍራና የጊዜ፥ የሥጋና የመንፈስ ይዘት ከሌለው፥ ለሰው ልጆች ትምህርት አይሰጥም። የጽሑፍህ ግዴታዊነት አሁን ነው፤ ከእንግዲህስ ታሪክህን ወደመፈጸሙ ተቃርበሃልና፤ ይህ የደረሰብህ ስባሬ ሕይወት ያለህበትንና የምትሄድበትን ስለሚያሳውቅህ፥ ለጥያቄዎችህ ሁሉ መልስ ይሆንህ ዘንድ ይጻፍ። ከሰማይ ቤት እርሳስና ወረቀት ስለሌለ፥ መላእክቶችም የሰው ታሪክ መጻፍ ሥራቸው አይደለምና፥ በል አንተው ጻፍ” ብለው የነገሩኝ ይመስለኛል።

ሁኔታዎች አስገድደውኝ በራሴ ላይ ሃሳብ አብዝቼ ሳለ፥ በየወቅቱ እውነት የሚመስለኝን ሁሉ በወረቀት አሰፍር ነበር። ስጽፍ እየተማርኩ ብዙ ከዘለቅሁ በኋላ፥ ሁሉም በሁሉም ዘንድ ያለውን መናገሬ ለማን እና ለምን እንደሚጠቅም ባለማወቄ፥ ግራ እየተጋባሁ ብዙ ቆይቻለሁ።

የሰው ልጅ ተወልዶ ከሚያየውና ከሚሰማው እንዴት ተለይቶ መኖር ይችላል? ከእድሜዬ በአብዛኛው ያየሁትን ጻፍሁ። ስጽፍም፥ ከግል ሃዘን ብዛት፥ ከምድራዊ እውነታ የወጣሁ እየመሰለኝ ነበር። ጹሑፉም ተጽፎ ሳያልቅ፥ ወይንም ማለቂያው ሳይታወቅ፥ በኢትዮጵያችን ላይ በሁሉም አቅጣጫ ጦርነቶች እየተቀሰቀሱ፥ የሀገሬ ሕዝቦች ብሶት፥ ልቅሶና ዋይታ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ ሄደና፥ ሃዘኔን አባባሰው፤ አይኖቼም በልቅሶ ብዛት ሞጨሞጩ። ለእኔም መጽናኚያ ይሆነኛል ያልኩት የጽሑፍ ሥራ በመጻፍ ብዛት አልረዳኝም። የእኔ የልቤ ሃዘን ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ሲሄድ፥ ይህቺን አለም እንድወዳት የሚያደርገኝ የስሜቴ ግለት፥ እንድጠላትም ከሚያደርገኝ የስሜቴ ግለት ጋር እየተጋጨ፥ የዝምታ ልፍለፉ ሆነብኝ። እህ! ምን ላድርግ?

"የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም" እንደሚባለው፥ ታሞ ከሚሞተው ይልቅ በጥይት የሚያልቀው ሲበረከት፥ ሕዝቦች ከያለበት ሲፈናቀሉ፥ ሲሰደዱ፥ በረሃብ እና በጥም ሲያልቁ፥ ይህንን በኢትዮጵያችን የተፈጸመ <u>የማይረሳ</u> ክስተት ለታሪክ ማስታወሻነት የሚጽፉ ሁሉ ልክ እንደ እኔው እያዘኑ፥ እያለቀሱ መሆኑ ይሰማኛል። አንድ ሰው ብቻውን ለስንቱ ማዘን ይችላል?

ምድራዊ ኩነቶች ኢትዮጵያችንን በዝብርቅርቆሽነት ሲያንገላቷት "አሁንስ በዛ! ምነው!..." እያሉ ከሚያማርሩ ኢትዮጵያውያን መካከል፥ "ከነገሮች ሁሉ በስተጀርባ <u>ያለ</u> ነገር ቢኖር ነው እንጂ!" የሚሉትን አደንቃለሁ። እኔም እንደነሱ ማሰቤ አልቀረም። በየጊዜው ከውስጤ የሚገፋኝ ኃይል መኖሩን እኔ ባውቅም፥ ስለ እውነት ብዬ፥ የማውቀውን (የማውቅ የመሰለኝን) ሁሉ በስነ አመክንዮ እያገናኘሁ ከማሰብና ከማሰላሰል አላረፍኩም። በውስጤ እየለፈለፍኩ የምጽፈውም፥ ልክ እንደ ስሜቴ ክርር ድብን ያለ ሆነብኝ። ምን ላድርግ?

አ! እኔ፡- ምንጊዜም በኃጢአቴ የማፍር፥ የማውቀው ሁሉ የሚያሳዝነኝ፥ የማላውቀውም ሁሉ የሚያስፈራኝ፥ በሥጋዊነቴና በመንፈሳዊነቴ የሚታየኝን - የታሰበኝን፥ በስሜት የተቀሰቀስኩበትን ሁሉ (የማውቀው የሚመስለኝን፥ የማምንበትንም) በእውነት ብዙ ብዙ እያለቀስኩ፥ ለእግዚአብሔር እየሰገድኩና ስለ እርሱ ፈቃድ ብቻ እየለመንኩ ጻፍኩ።

አ! እኔ፥ በአንድ ግለሰብ የሕይወት ታሪክ (አለማዊ፥ አብዮታዊ፥ መንፈሳዊ) ውስጥ፥ ስለዚህች አለም እና ከዚያም ባሻገር ቢሆን የሚሰማኝን በሳይንሳዊና በመንፈሳዊ ፍልስፍናዎች ላይ ተመርኩዤ፥ ባቅሜ ለመግለጽ ስነሳ፥ ምናልባት በዚህ ጽሑፍ ሰዎች የበለጠ ሊቀራረቡና ሊስማሙ ይችሉ ይሆናል በማለት ነበር እኮ።

"ከዚያ የከፉ ቀን" ጀምሮ፥ መንፈሳዊ ጉዞዬን ለማፋጠን ከምንጊዜውም የበለጠ የተጋሁ ይመስለኛል። ለዚህም ይህ እየተማርኩበት የምጽፈው ምሥክር ነው። ከበድ ያሉ ጉዳዮችን ሳወራ፡- ሰዎች ሆይ! እኔስ እንደ አላዋቂ ለፍላፊ ሆኛለሁ እያልኩ እናገራለሁ እንጂ፥ እውነት ነው ብዬ በመጮህ የሌሎችን እውነት አልሸፍንባቸውም። ይህ ነው መነሻዬ፤ ዝቅታዬን ሳልናገር የማላልፍበት እውነታዬ።

ነገር ግን፥ ካቅሜ በላይ እየተንጠራራሁም ቢሆን፥ የተሰማኝን ወይም ያወቅሁትን እንድናገር ተፈጥሮዬ ያስገድደኛል። በውስጤ ያሉ እውነቶች በራሳቸው ይጮሃሉ፤ ከአንባቢያን እውነቶች ጋርም ተመሰቃቅለው በጋራ የሰብአዊነትን እውነታ ያስተጋባሉ፣ እኔ አንድ የሰው ግማሽ ብሆንም፥ ከብዙዎች ጋር የምጋራው ሃሳብ፥ እንደ ብዙ ሰው ያስመስለኛል/ያደርገኛል። ሰዎች አለማወቄን አይተው እንዳያሳፍሩኝ መደበቅን ስፈልግ፥ ስፈራ፥ በስጨት ስልም፥ ከምድራዊነታችን ባሻገር ስለሚኖር ተስፋ ብዙ አስባለሁ፤ እንዲህም እላለሁ፡-

እኛ'ኮ! መሬት ስላለን ብዙ ችግር ደረሰብን እንጂ፥ ሌላ ደጋግ ሰዎችና ደጋግ መንፈሶች ብቻ ያሉበት ሥፍራ ብንኖር ኖሮ፥ ይህ ሁሉ ችግር አይደርስብንም ነበር። እኛ'ኮ! ከእድለኞች ጠፈራውያን መካከል አንደኞቹ ልንሆን እንችላለን። እኛ የምንኖረው ክፉና ደግ በተቀላቀለበት አለም ነው። ጠፈር እጅግ ሰፊ ስለሆነ፥ ፍጥረታትም በዚች እኛ "በምናውቃት" ምድር ብቻ የተወሰኑ አይደሉም። እስቲ በምናብ ከዚች ምድር ለቀን እንሂድ፤ ወደ ሌላ ልዩ አለም እንግባ፤ ሌሎች አለማትንም እንጎብኝ።

ከሰዎች ግንዛቤ ውጪ በሆነ መንገድ፥ በየቅጽበቱ - በየሰኮንዱ ክፋትና ደግነት ይለያያሉ። ክፋት ብቻውን ይቀራል፤ ደግነትም ብቻውን ተለይቶ ይቀመጣል። ክፋት ብቻ የሚያይልበት አለም አለ፤ ከዚያም የሚኖሩ "ሰዎች" አሉ። ደግነት ብቻ የሚያይልበት አለም አለ፤ ከዛም የሚኖሩ "ሰዎች" አሉ (ይመስለኛል)።

በዚች እኛ በምንኖርባት አለም ውስጥም እንደ መላእክት ተደስተው የሚኖሩ ሰዎች አሉ፤ እንደ ሰይጣናትም ሃዘንተኞች ሆነው የሚኖሩ አሉ። ሃዘንተኞቹ ሁሉ ሰይጣናውያን ወይንም ኃጢተኞች አይደሉም። ግን በምድር ስላሉ ብቻ ያለቅሳሉ። ሲያለቅሱ የሚጮሁት በጠፈር ውስጥ ለሚኖርና መጠነኛም ሆነ ከፍተኛ ግንዛቤ ካለው ሁሉ የሚዳረስ (በአካል የማይገለጽ ሞገድ) ይመስለኛል። እንዲህ እና እንዲህ ሳስብ ነው ብቻዬን አለመሆኔ የሚሰማኝ።

አጥቂና ተጠቂ ካለበት ሥፍራ ሁሉ ጩኸት ይኖራል። ይህ ከእንስሳትም ሆነ ከሰዎች በየጊዜው ወደሰማይ የሚገባ ጩኸት መልስ ሳያገኝ (ውጤት አልባ) ሆኖ እንደማይቀር አምናለሁ። ብቻችንን አይደለንም።"

**ዮሐንስ**

“በሰዎች መካከል በግልጽ ከሚታዩ - የቆዳ ቀለም፥ የገጽታና የቁመና አካላዊ ልዩነቶች በስተጀርባ፥ በመካከላቸው የሚገኝ የመንፈስ ልዩነት ምንኛ ታላቅ እንደሆነ በድብቅ ተናገርከ። እግዚአብሔር በግዛቱ ብቻውን እንዳልሆነ፥ በዙሪያው መላእክት እንደሚኖሩ፣ ሰይጣንም ብቻውን እንዳልሆነ፥ በዙሪያው ቡችሎቹ እንደሚከቡትም ነው በድብቅ የተናገርከው።

የማይታየውን ለማየት ስንሞክር ልዩ አለም ውስጥ ይከተናል። ልባዊ ስሜትህ ገብቶኛል። አንተ ተንፍሰህ፥ እኔ ሰምቼህ፥ እኔም ተናግሬ፥ አንተም አድምጠህ፤ የሁለታችን ወሬ ብዙውን ጊዜ ሰዎች ከሚያወሩት ለየት ቢል፥ ከሚያዩትና ከሚሰሙት ውጪ በመንፈስ አርቅቀው ቢሄዱ የሚታያቸው ሊኖር ስለሚችል፥ ጥረትህ ያንን በአንክሮ ለማመልከት እንደሆነ ገብቶኛል። ለዚህም ነው ከምድራዊነታችን ባሻገር እያልክ መፈላሰፍ የጀመርከው፤ ይገባኛል። እግዚአብሔር ከወደደልህ ፍጻሜው ጥሩ ይሆናል።

ከምታየው ተነስተህ የማታየውን ለመግለጽ መሞከርህ፥ በሰዎች እግር ዙሪያ የሚንጎራደድ ድመትን “እስቲ አንተ ድመት ስለ ሰዎች የምታውቀውን ተናገር፤” እንደማለት ያህል የከበደ መሆኑ ይገባሃል? ቢሆንም በትጋት የደከምክበትና የጸለይክበት ስለሆነ ጻፍ። ግን በመጀመሪያ ውሸት ከመናገር ተቆጠብ። ውሸት በመናገር ሌላውን የሚያሳምን ሰው እና ኑሮውን በስርቆሽ ላይ የመሠረተ ሰው አንድ ናቸው። እንደማትዋሽ አውቃለሁ፤ ነገር ግን፥ ነገር አሳምራለሁ ብለህ ነገር አታጋን።

እራሱን ለተወሰነ አላማ አሳልፎ የሚሰጥ ሰው፥ ከራሱ ይልቅ እውነትን አስቀድሟል። ስለዚህ ከውስጡ እውነት ቢጮህ፥ ያ ሰው እንደ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ሆነ ማለት ነው[2]።

መጀመሪያ ምድራዊ ችግሮችን ከቅጣት ለይተህ እወቅ። ሰው ሰራሽ ችግር ከሰማይ የሚወርድ ቅጣት አይደለም። በችግር ውስጥ ማለፍ ያጠነክራል። ከሰዎች የሚመነጨውን ችግር እንደራስህ ችግር አድርገህ ማየትና፥ ከሌላው ሁሉ ጋር ሆነህ ከችግር ለመውጣት መጣር ይኖርብሃል እንጂ፥ ብቻህን በመፍጨርጨር አይደለም።

በሰው ሁሉ ዘንድ የሚንቀሳቀስ እውነት በብዙ አቅጣጫዎች እየፈሰሰ፥ ያለማወቅ ፍርኃትን ያጠፋል። ልክ ነህ፤ “እኛም በሃዘን ብዛት ስንጮህ፥ ስናለቅስም

---

[2] *“የዐዋጅ ነጋሪ ቃል በምድረ በዳ፥ “የእግዚአብሔርን መንገድ ጥረጉ፤ ለአምላካችንም ጎዳና በበረሃ አስተካክሉ። ሸለቆው ሁሉ ይሙላ፤ ....የእግዚአብሔር ክብር ይገለጥ.....።” ኢሳ. 40፡ 3-6*

ስሜቶቻችንን ሁሉ የሚረዳ በጠፈር ውስጥ ስንጣራ የሚሰማን አለን" ብሎ ማሰብ ወደ እውነት ያስጠጋል እንጂ አያርቅም። ከፍ ሲልም፥ ከሃይማኖታዊ ፍልስፍናዎች ጋር ያቀራርባል እንጂ አያርቅም። ላዘኑት መጽናናትን የሚሰጥ ፍልስፍና ወደ መንፈሳዊነት ሲያመራ ደግ ነው።

በምድራዊ መበላለጦች ምክንያት ተለያይተን የተቀመጥን ሁሉ በመንፈስ አንድ የምንሆንበት ጊዜ ይመጣል። ስንሞት ይቀለናል፤ እስከዚያው ድረስ በምድር የሚኖር ሁሉ ይጮሃል። የጋርዮሽ (የሰውም የእንስሳም) ቃል (የመንፈስ ጸሎት) በጋርዮሽ ከምድር ወደ ላይ ይወጣል። ይህ ጩኸት በጠፈር ሁሉ እንደሚሰራጭ አትጠራጠር። ሰሚ እንዳለን እመን[3]።

ክርስቶስም፡- *"አንዲት መበለት ዳኛውን ስለጨቀጨቀቺው ሰማት..." (ሉቃ. 18፡1)* በሚል ምሳሌ የተማርነው ለምን ይመስልሃል? እነሆ! ሰዎች (በአለም ዙሪያ) በምድራዊ መጠቃት ላይ እንዳሉ የሚያሰሙት ጩኸት አንድ ቀን ፍርድ እንደሚያመጣልን አትጠራጠር። ሰሚ አለን፤ ስለዚህ፡-

*"ሁል ጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ ሳታቋርጡ ጸልዩ።" 1ኛ ተሰ. 5፡7*

ለሁላችንም፥ እንደ እድል ፈንታችን፥ በተሰጠን ብቻ እያመሰገን እና እየተደሰትን፤ ጊዜአችን እስኪደርስም እየጸለይን በተስፋ እንኑር።

አዋቂም ብትሆን አላዋቂ፥ ምንጊዜም ተስፋ በውስጥህ ይኑር፤ እርሱ ያቆይሃል፤ እርሱም ያዘልቅሃል።

በሰማይ ብዙ ከመሬት የተሻሉ መኖሪያ ሥፍራዎች ይኖራሉ። በምድር ላይ ኑሮ ባይደላህ፥ አንተ ጥሩ ሰው ከሆንክ፥ የሰማይ ቤት ኑሮ ያካክስሃል።

የክርስቲያናዊነት ምሥጢሩ አንዱ ለሌላው እራሱን መስዋእት እስከማድረስ መሆኑን አትርሳ። ፍቅር ካለ ምድራዊ ክፍያ ይለገሳልና፤ አንተም ፍቅርህን ካለ ክፍያ ስትለግስ ደስ እያለህ ይሁን።

ከምድራዊነት ባሻገር በመንፈሳዊነት ብቻ መኖር ቢቻል፥ የሰብአዊነት ፍጹማዊነት ይረጋገጣል። ግን ይህን አይነት ብቃት በምድር የሚያገኙ እንደ እነ ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ያሉ መንፈሳውያን ናቸው። ቢሆንም፥ ለዚህ የመጨረሻ ግብ የሚያልም፥ ከሁሉ በላይ ፍቅርን ያስቀድማል። *".. በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባርያዎች ሁኑ" ገላ. 5፡13* ቢል፥ አንዱ ሰው ለሌላው እንደ ባሪያ ሆኖ ቢኖርም፥ ፍቅር

[3] *"በልሳን ብጸልይ፥ መንፈሴ ይጸልያል፤ አእምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው።" 1ኛ ቆሮ. 14፡14*

ካለ ባርያ የሚለው ስሜት እንደሚጠፋ ታዋቂ ስለሆነ ነው። ስለዚህ፥ እድሜ ልክህን ለፍቅር ብለህ ብትደክም፥ ባሪያ የሆንክ አይምሰልህ። ለልፋትህም ዋጋ ምድራዊ ምላሽ፥ ምድራዊ እውቅናም ባይሰጠው፥ እንዲሁ ደስ ይበልህ እንጂ፥ አትከፋ።

ጠላት ሰይጣን አንተን ወደ ክፋት በሚወስደው ጎዳና ያስገባህ ዘንድ ቀላል የሚሆንበት ሁኔታ ቢፈጠርም፥ መንፈሳዊነትህ (ለምሳሌ ቅዱስ ቁርባን ብትወስድ) ይህንን ሁኔታ ሊቀይረው ይችላል። ሰይጣን ውስጣዊ ማንነትህ በመንፈሳዊነትህ ጎላ ብሎ እንዳይታይ በምድራዊነትህ ይደበቃል። የዛን ጊዜ በሁለት ትከፈልና ከራስህ ጋር ክርክር ትገጥማለህ። የክርክሩም አይነት፡- በዚሁ በክፋት ጎዳና ልቀጥል ወይንስ አልቀጥል የሚል ይሆናል።

በክፋት ጎዳና መዝለቅ የሚያስከትለውን ጉዳት ምድራዊነትህ እንዳይታይህ ያደርግብሃል፤ መንፈሳዊነትከም ጉዳቱን አሳውቆ ምርጫውን ላንተ ይተወዋል። ያንተ የፍላጎትህ ፈቃድ ለራስህ ነው። ይህም እኔና አንተን በአንድላይ በማጠቃለል ነው እንጂ፥ ለየብቻ በመሆን አይደለም። ችግር የሚፈጠረው መከፋፈል ሲመጣ ነው።

ብርሃን ያረፈበት አካል ጥላ እንደሚኖረው ሁሉ፥ ለሰውም በራሱ ልክ እንደ ጥላ ሆኖ የሚከተለው ክፉ መንፈስ ሲኖር፥ የሰውም የራሱ የምንለው ጠባዩ ለራሱ ጠላት ይሆንበት ዘንድ አብሮት ይኖራል። ለዚህ ነው ምድራዊ ፈተና የሚበዛው። ይህም ፈተና መጠጥ፥ ሲጋራ እና ሌሎችም ክፉ ልምዶች ያደረባቸው ሰዎች፥ ከሱሰኛነት ወጥመድ ለመላቀቅ ከሚያደርጉት ትግል ጋር ይመሳሰላል።

እርምጃዎችህን የምትቆጣጠር፥ የምትሄድበትንም አቅጣጫ የምትወስን አንተው ነህና፤ አንተም እንደ ሱሰኞቹ፥ “ከውሸት ጋር ብዙ ቆይቻለሁ ወይ?” ብለህ እራስክን ጠይቅ። በውስጥህ የሚኖር ፍጹማዊ እውነት (የእግዚአብሔር ኃይል - ፍቅር) ክፉውን መንፈስ እንደሚያቸንፈውም እወቅ/እመን[4]።

መቼም የሰው ጠባዩ ገና ከፍጥረቱ መሆኑ ጥርጥር የለውም። መንፈሳዊነት ግን ከሰው ጠባይ ርቅቅ ያለና የተለየ፥ ከአካላዊነት ውጪ በራሱ ፍጹማዊነት ውስጥ “የሚኖር” ሲሆን፥ ለሰው የሚቀርበው እና የሚርቀው እንደየሰዉ ተፈጥሮአዊ ጠባይና እምነቱ ሊሆን ይችላል።

“ከሰዎች በየጊዜው ወደሰማይ የሚገባ ጩኸት መልስ ሳያገኝ (ውጤት አልባ) ሆኖ እንደማይቀር አምናለሁ” አልክ። ይህ እውነት ነው፤ ታዲያ! ምን አስፈራን? ምንስ አሸማቀቀን? ማልቀስ ካለብን እናልቅስ፤ ማዘን ካለብን እንዘን። ልቅሶን የግል

---

[4] *“እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት፤ ቀርቦም ሳለ ጥሩት፤ ክፉ ሰው በደለኛም አሳቡን ይተው፤ ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ፤ እርሱም ይምረዋል...።” ኢሳ.* 55፡ 6፥7

አታድርገው፥ የሰው ልጅ ሁሉ ያለቅሳል፤ አለም ያለቅሳል፤ ኢትዮጵያም ታለቅሳለች። የሁላችንም የልቅሶአችን እና የሃዘናችን ሞገድ ምድሪቱን ለቆ ይሄዳል፤ ከሌሎች ልቅሶዎች እና ሃዘኖች ጋርም ይተባበራል፤ ሁኔታውን ሁሉ ለፈጣሪው በጸሎት ያቀርባል። እግዚአብሔርም ይሰማል፤ እርሱ በፈቀደ ጊዜም መልስ ይሰጣል[5]።”

**ቶማስ**

“አዎ! እውነት ነው፤ እኔም አንተም የምናውቃቸው ጥሩ የተባሉ ሰዎች እርኩስ መንፈስ ሲያድርባቸው ተመልክተናል። ግን ለምንድነው ሰው አንድ እራሱን እንኳን ማስተዳደር የሚያቅተው? ለሰው የራሱ የሆነ በውስጡ ሌላ አስተዳዳሪ አለው እንዴ? ሕይወታችን ከራስ አስተዳዳሪ ጋር የሚኖር፥ የስምምነትና የቅራኔ ውጤት ይመስለኛል።

በዚህ በከፋ አለም ውስጥ አንድ ሰው ፍጹም ጥሩ ጠባይ ቢኖረው፥ ጥሩ ጥሩውንም ብቻ እያሰበ ቢኖር፥ ይህ አይነት አኗኗር ከምድራዊነት የሚያስወጣ ይመስለኛል። ይህም ምድራዊ አለምን ሸሽተው በገዳም እንደሚኖሩ አይነት ይመስላል። ግን እነርሱም ቢሆኑ በምድር እየኖሩ ከምድራዊነት ፈጽሞ የሚላቀቁ አይመስለኝም። ምክንያቱም፥ ከምድራዊነት የሚያስወጣ “መድኃኒት” ቢገኝ፥ ያ መድኃኒት ሊገድልም ይችላል እላለሁ። የሚያድን ይገድላል ወይ? የሚገድልስ ያድናል ወይ?”

**ዮሐንስ**

“ብዙ የታመቁ ሃሳቦችህን “የሚያድን ይገድላል ወይ? የሚገድልስ ያድናል ወይ?” በሚል ጥያቄ አጠቃለህ አቀረብክልኝ። እኔ ለዚህ የምሰጥህ አጭር መልስ፡- አዎ! የሚገድል ዘለአለማዊ ሕይወት የሚሰጥ ከሆነ ያድናል ማለት ነው፤ የሚያድን ግን አይገድልም ነው። ይህንንም ስልህ፥ ስለ እውነት የሞቱ (የተገደሉ) በሥጋ ቢሞቱም በነፍሳቸው ሕያዋን መሆናቸውን እንድታስተውል፥ ከታች የተጠቀሱትን አንብብ (አጥና፥ አስተውል) እና ሌሎችንም አንብብ።[6]

---

[5] *“አቤቱ እንደ አንተ ማን ነው? አቤቱ ዝም አትበል፤ ቸልም አትበል።” መዝ. 82፡1*

[6] መዝ. 115(116)፡15፥ ማቴ. 16: 25፥ ራዕ. 14፡13

ዘለአለማዊውን ከጊዜአዊ ጋር እያነጻጸርክ፥ አያሌ ሃሳቦችን በአንድ ላይ አታጭቅ። ስታወራም እውቀትህን እየመዘንክ ይሁን። ልፈላሰፍ ብትልም፥ ችሎታህን (ብቃትህን) ታሳቢ በማድረግ ይሁን።

የአለሙ **ሁሉ** ቤዛ ለመሆን ከሰማይ የወረደውና ላመኑበት ሁሉ መድኃኒት የሚሆን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። *"አትፍሩ፤ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት፥ እርሱም ጌታ ክርስቶስ የሆነ ተወልዶላችኋልና።" ሉቃ. 2፡11 እንዲሁም፥ "....የእውነት እና የሕይወት መንገድ እኔ ነኝ.." ዮሐ. 14፡6* ብሏልና።

የእለት ሀኪቶችን ከመደበቅ ይልቅ፥ በየጊዜው ገልጾ መናገር፥ ችግሮችን ከራስ ላይ ለማራገፍ፥ አማራጭ መፍትሔዎችንም ፈልጎ ለማግኘት ይጠቅማልና፤ ከብዙሃን ጋር የማያቋርጥ ግንኙነቶችን መፍጠር ደግ ነው። እውነት የጋራ ሆኖ ሳለ፥ በየግለሰብ ደረጃም (ሁሉም ለራሱ - እንደብጤው) የሚወሰን ይሆናል። ቶሎ ቶሎ የሚግባቡ ሰዎችም ላለመስማማትም እየተስማሙ በሰላም ይኖራሉ እንጂ፥ በጭቅጭቅ ጊዜያቸውን አያጠፉም። ያንዱ እውነት ለሌላው ሙሉ በሙሉ የማይዘልቅ መሆኑን በመገንዘብ፥ ምንጊዜም የራስን እውነት ለራስ አድርጎ፥ ከማንም ሰው ጋር ቢሆን መግባባት ይቻላል።

እስካሁን ስንነጋገርበት የቆየነውን፥ የሰውን የሁለትነት ባህሬ ምንጊዜም አትርሳ፤ ሰው ካፍህ የሚወጣውን እንጂ ከልብህ ያለውን እንደማይመረምርልህ አትዘንጋ። ብዙውን ጊዜ ካፍህ የሚወጣውና በልብህ ያለው የተገላቢጦሽ ሊሆን ይችላል። ካፍህ የምትወጣ እያንዳንዷ ቃል ለምትደርሰው ሰው ምን ያህል ተስማሚ መሆኗን ሳታረጋግጥ፥ በከንቱ አትለፍልፍ (አትጻፍ፤ አትናገር)። አንተ እውነት ተናግረህ ያን እውነት እንደ መልካም ስጦታ ደስ እያለህ ካላቀረብክ በስተቀር፥ የምትናገረውም የሚያስደነግጥ፥ የሚያስፈራም ከሆነ፥ ካንተ እውነት ይልቅ፥ ለጊዜውም ቢሆን፥ የሌላው ውሸት የተሻለ መስሎ ሊታይ ይችላል።

ካንተ ሰው ሲርቅ፥ ምኔ ነው ለሰው የማይጥመው ብለህ ጠይቅ። ከአንተ አፍ የሚወጣውና የልብህ እውነት ለምን እንደማይጣጣሙ እራስህን መርምር።

እንድትጨነቅ የሚያደርግህ የገዛ ቅብጥብጥ ጠባይህ ሊሆን ይችላልና፤ በመንፈሳዊነት አረጋጋው። ላንተ ያልገባህን (ሊገባህ የማይችለውን ሁሉ) አጠገብህ ካለው መልካም መንፈስ (የቅርብ ጓደኛ) ጋር ተነጋገርበት። በተስፋ ጭላንጭል ለማይጓዝ፥ ይህቺንም አለም በአሉታዊነት ብቻ ለሚመለከታት ሰው፥ አስተሳሰቡ ሁሉ (ክፉም ሆነ ደግ) ፋይዳ ቢስ (ጥቅም የማይሰጥ) ስለሆነ፥ የትም የማይደርስ፥ አጉል መፈናጠር (እየዘለሉ መፍረጥ) ሆኖ ሊቀር ይችላልና፤ በተስፋና በአዎንታዊነት መጓዝ ነው የሚሻለው። ስለዚህ፥ አይዞህ! ጥርት ያለው ልመናህን ለፈጣሪ አምላክህ በተስፋና

በአዎንታዊነት ከማቅረብ (ከመጸለይ) አትቦዝን፤ ሁሉም በፈጣሪህ ይከናወናል። እንጸልይ (መዝ. 50 በጠቅላላ)።"

**ቶማስ**

"እህ! በማንነቴ ታጥሬ፥ ሰዋዊ መልክም እንዳወጣ፥ የራሴ ብቻ የሆነ አካል ገጽታ፥ ቁመና እጅ እግር ተሰጠኝ። እኔ ለእኔ እሆን ዘንድ ማንነቴ አንቆ ያዘኝ፤ የሁሉ እሆን ዘንድ ስላልተፈጠርኩ፥ ወደራሴ አዘነበልኩ፤ እራሴንም ወደድኩ።

የሰው ፍጥረቱ አንድ ሆኖ ሳለ፥ ምድራዊነትን ታኮ የመጣ ምድራዊ ሥልጣኔ ነው እርስ በርስ ያበላለጠን። የሰው ልጅ በፍጥረቱ ከዚህ አለም ውጪ ያለውን ማየት የሚችል ሆኖ ሳለ፥ ትኩረቱ በዚች ምድር በሚያየው ብቻ ተወስኖ ስለቀረ፥ "ትምህርት ቤት ገብቶ የተማረውን ያወቀ፥ ትምህርት ቤት ገብቶ ያልተማረው ያላወቀ እያልን፥ ሰውን ከሰው እናበላልጣለን (ምድራዊ ሚዛን)።

በምድራዊነታችን እሳቤ ውስጥ፥ መንፈሳዊነትን ካልተላበሰ ከተራ እውነት በስተቀር ምን እናገኛለን? አዎ! ሰዎች ተራ የሆነ እውነተኛነታቸውን ለማረጋገጥ ሲሉ እርስ በርስ ይተላለቃሉ። ይህንን አይነት ክስተት አህጉራት አሳይተውናል፤ ከኢትዮጵያችንም በቀላሉ የምንመለከተው ጉዳይ ነው።

በዚህች ምድር ላይ ታሪክ ሲወራ (ከቅዱሳን መጻሕፍት በስተቀር) በታሪኩ ውስጥ በጉልህ የሚታየው ሥጋዊው ክስተት እንጂ መንፈሳዊው አይደለም። በዚህም ምክንያት ግማሹ የሰው ልጅ ታሪክ ተሸፍኗል። ታሪክ ጸሐፊዎች የሚታየውንና የሚጨበጠውን (በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችለውን)፥ አርኪዎሎጂስቶችና ሌሎችም የስነ ፍጥረት ተመራማሪዎች በቁፋሮ የሚያገኙትን አካለ ቅሪት እየመረመሩ የሚነግሩን የሥጋዊ አኗኗሩን ነው። ሥጋዊ ደማዊ - ምድራዊ አካላዊ ያልሆነ፥ በማንነቱ ፍጹም ልዩ መንፈስ ሆኖ ሳለ፥ ግን ልክ እንደ ማንኛችንም ሥጋውያን በመካከላችን የሚመላለስ ቢኖርስ፤ ይህንን ማን ያውቃል?"

**ዮሐንስ**

"መንፈሳዊነትን ያልተላበሰውን ምድራዊ እውነት እንደ ተራ እውነት መቁጠርህን እኔም እስማማበታለሁ። ከብዙ ተራ እውነቶች መካከል፥ የኮሙኒስቶች እውነት አንዱ ነው። እነርሱ ፈጣሪያቸውን ይዘው ቢነሱ ኖሮ፥ የአለም ገጽታ እንዲህ እንዳሁኑ አይሆንም ነበር። ይህች ምድር ለሁለት የማይጣጣሙ ሥጋና መንፈስ ማደሪያ ሆና የሰብአዊነትን አላማና ግብ ታካትታለች። ስለዚህ፥ ከሰው ታሪክ ውስጥ፥ የሥጋ

ያልሆነውን የመንፈሱን ታሪክ እንናገርለት ብሎ መነሳት ድንቅ ነው። ትልቁም ትንሹም ምሥጢር በሆነበት አለም ውስጥ፥ በቀላሉ የሚታወቅና የሚታይ እንኳን ለብዙ ሰዎች ድብቅ ሆኗልና፤ አውቀን አይናችንን ከምንሸፍን፥ "ከዚያ ማዶ" ያለውንም ለመመልከት መሻት መልካም ነው።

አንተ ከምታውቀው ምድራዊ ማንነት ተነስተህ፥ ስለሰማያዊ ማንነት ማሰቡም ከአቅምህ በላይ ይሆንብሃል። የሰው ልጅ በምድራዊ ማንነቱ ተወጥሮ፥ ኃጢአት እየሠራ ይኖራል። ከራሱ እየወጣ ሌላውን (ሰማያዊ ማንነቱን) ለመሆን ቢጥር፥ ያ ማንነት ግላዊ ስለማይሆን፥ ሰላማዊ፥ ደግ፥ ለሌሎች የሚያዝን ርህሩህ ይሆናል። ቅንጣት ታህል ሰማያዊ ማንነት የሌላቸው፥ ሰው ሲራብ፥ ሲጠማ፥ ሲታረዝ፥ ሲቸገር የማያዝኑ፤ ሰው በጦርነት ከትውልድ ሥፍራው ሲፈናቀል፥ ሲጎሳቆል፥ በበሽታ ሲሰቃይ፥ በአካል ሲጎዳ፥ ሲቆስል፥ ሲደማ ምንም ስሜት የማይሰጣቸው፥ እነርሱ ምድራውያን ናቸው፤ በውስጣቸው ጥቂት ሰማያዊነት ቢኖራቸውም፥ የእነርሱ ሰማያዊ ማንነት "የተለየ፤ ፍጹም የተለየ" ነው። ገብቶሃል፤ አይደለም?

እንግዲህ፥ በዚችው በምድራችን ሆነን በአካል ከምናየው ባገኘነው እውቀት ይህንን ካልን፥ ሰማያዊ እውቀት ምንኛ ይረቅ! የኛ ምድራዊ እውቀት ከማየት፥ ከመስማትና ከመንካት ተነስቶ በውሱን አንጎላችን እየረቀቀ የሚያድግ ስለሆነ፥ የምናውቀውና እና ልናውቅ የምንችለውም የዛኑ ያህል ውሱን ይሆናል ማለት ነው።

አንዳንድ ጊዜ ራሳችንን ለቀቅ አድርገን፥ ከውሱኑ ዙሪያችን (ምድራዊነታችን) ባሻገር ወሰን ወደሌለው ባህረ ሃሳብ ውስጥ ለመምጠቅ ብንጓጓ፥ ጥሩውን ፍለጋ ስለሆነ፥ ጥሩ ነው (ይህንንም እያሰብክበት ቆይ)። እውቀት እና እውነት ሁልጊዜ አብሮ አይሄዱም። እውነትን የሚደብቅ እውቀትም ይኖራል። ብዙውን ጊዜ ሰዎች "እናውቃለን" የሚሉት ሁሉ እውነቶችን በከፊል እንጂ፥ ሙሉውን አያሳየንም። ሁለንተናዊ እውነት የእግዚአብሔር ነውና የእግዚአብሔርን ቃል ከሚገኝበት ሁሉ እንስማ፤ ከሃይማኖት አባቶች እንስማ፤ ከምንጸልየውም ከጸሎታችን እንስማ።

*"ሁሉን ፈትኑ፥ መልካሙን ያዙ፤ ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ።" 1ኛ ተሰ. 5፡21*

"ልክ እንደ ማንኛችንም ሥጋውያን በመካከላችን የሚመላለሱ ቢኖሩስ፤ ይህንን ማን ያውቃል?" ብለህ ለጠየቅኸው፥ በአጠቃላይ፥ በምድር ላይ እውነት የምንላቸውም ሁሉ፥ መንፈስ ሲርቃቸው ተራ እየመሰሉ ይታያሉ። መንፈስ እና ሥጋ ለየብቻ ሆነው የየግል ህልውና ሊኖራቸው አይችልም፤ በድን ካልሆኑ በስተቀር። በመካከላችን የሚመላለሱ፥ አካላዊ ያልሆኑ ሕያዋን (ከፉዎችም/ደጎችም) መኖራቸውን በሕይወታችን ውስጥ ከሚሰሙን ስሜቶች መረዳት ችለናል።

በመምሰልና በማወቅ መካከል ያለውን ልዩነት እንኳን አለማወቃችን አንዱ የሰብእነታችን ጉድለት ነው። የሚመስለንን ሁሉ ለማረጋገጥ የሚያበቃ እድሜም አልተሰጠንም። እውነትን ለመንካት የሚሮጡ፥ ቶሎ ብለውም ለእውነት የሚቀርቡ፥ ከቀረቡም በኋላ እውነትን ለመንካት የሚፈሩ ብዙዎች ናቸው። በሩጫም ሆነ በዝግታ እውነትን የሚነኳት ግን፥ እነርሱ ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ፥ እግዚአብሔርም የሚያስጠጋቸው ቅዱሳን ናቸው።"

**ቶማስ**

"አመሰግናለሁ። በዚህ ባለንበት አለም ውስጥ፥ የመግባቢያ ቋንቋችን መደነጋገሪያም በመሆኑ፥ አንዱ የተናገረውን መልሶ መድገም ጀሮን የሚያሰለች ሆነ። እውነት ግን፥ ካንዱ ወዳንዱ እየተዛመተ ሲሄድ ደጋግመው ቢያወሩትም የእውነት እውነትነቱ እየተጋነነ ስለሚሄድ፥ ሲያወሩትም ሲሰሙትም ደስ ያሰኛል እንጂ አይሰለችም።

እነሆ! እስከ ሽምግልና እድሜዬ ድረስ ጥቂት ነገሮችን ብቻ ተገነዘብኩ። ከዚህም ከዚያም ወደ አንድ አቅጣጫ የሚያመሩ ሁኔታዎችን በማገናዘብና በማጠናቀር እኔ መናገርም ባልችል፥ እራሴን ልተው (ባዶ ልሁን)፤ ከሰብአዊነት ማሕደር እየቀረፍኩ ልጻፍ - እውነትን ከማይፈራ ሰው ጋር ሁሉ (ሃይማኖተኛም ቢሆን ወይም ሃይማኖት የሌለው) ልባዊ ጭውውት ላድርግ በማለት ተነሳሳሁ።

ስለ ሰብአዊ ጠባዮች፥ ስለ ሳይንስና ስለ ሃይማኖት፥ ስለ ቅጣትና ስለ ሃዘን፥ ስለ ምድራዊ ምሬት እና ስለ መጨረሺያው እኔን እያነጫነጨ እንድጽፍ የሚገፋፋ ኃይል በውስጤ አለ በእውነት። ይህ ሰው ኃጢአተኛ ነው ብለህ አትናቀኝ፤ ከኃጢአተኛም ሰው በውስጡ እውነት አይጠፋምና።

አዎ! እኛም የገነት ሰዎች ነበርን፤ በኃጢአታችን ከገነት ብንወጣ፥ አውላላ ሜዳ ላይ ተጥለን አልቀረንም። ሁለታችንም በምድር ላይ እስካለን ድረስ የእኔና ያንተ ተለይቶ አይታወቅም። ግን፥ በመካከላችን ልዩነት ይኖራል፤ ሰው ሁሉ በመንፈሱና በሥጋው ፍጹም ተዋሕዶ የሚኖርበት አለም ውስጥ አይደለም ያለነው። ለሁለት ተከፍለን የምንለፈልፈውም ለዚህ ይሆናል። እንደ እንቅልፍ ቀስቃሽ (sleep apnea)፥ ወይንም እረፍት እንደማይሰጥ የጎን ውጋት፥ በአንድም ሆነ በሌላ፥ በሕይወታችን እየተነካካን አለን - አንዱ ሲያንቀላፋ፥ አንዱ ሲቀሰቀስ ።

ሕዝቦችን ሁሉ በአንድ አቅጣጫ የሚመራ ኃይል (የእውነት መንፈስ) ሰውን እስኪያነቃው ድረስ ሥራውን ይቀጥላል። ከግርግርና ከልፍለፋ ባሻገር ሁለንተናዊ እውነት የሚገለጥበት ጊዜ ይመጣል። እስከዚያውም ድረስ፥ ጩኸት፥ ልቅሶና ማላዘን

ስለማይቀር፥ ይህ እና ይህን የመሳሰሉ ማህደረ ሃሳቦች ለወደፊቱ ትውልድ በጽሑፎች መልክ ማቆየቱ ጠቃሚ ይመስለኛል።"

**<u>ዮሐንስ</u>**

"መልካም ነው፤ ከአንዱ ሰው ውስጥ ምድራዊ የሆነው፥ ምድራዊ ካልሆነው (ከመንፈሳዊነቱ) መለያው ቢታወቅ ጥሩ ነበር። ሥጋዊ ሳትሆን በፊት፥ ሰው ሆነህ ተፈጥረህ፥ ሥጋዊነትን ስትላበስ አስተሳሰብህ ሁሉ ወደ ምድራዊነት አዘነበለ። በጥሞና አድምጠኝ። አይን ስላለህ በአይንህ ስለምታየው ነው የሚታሰብህ፤ ጆሮም ስላለህ ስለምትሰማው ነው የሚታሰብህ። ሲርብህ ጠቅላላ ሰውነትህ በምግብ ኃይልን አግኝቶ ሲንቀሳቀስ፥ የሚኖርበትንም አለም ሲዳስስ ይኖራል። መቼ ከተሸከምከው ከሥጋህ ተለይተህ አንተን ሆነህ ታውቃለህ? ምናልባት፥ ሁለመናህን በእንቅልፍ ስታሳርፈው፥ የዛን ጊዜ ወደ ልዩ አለም ገብተህ፥ በህልም አለም ትኖራለህ። ያም ቢሆን፥ የህልሞችህን አለም የቀን ውሎህ ይቆጣጠረዋል። ያም ቢሆን፥ ጠቅላላ የሰውነትህ ሁኔታ (የተኛኸው ሆድህ ርቦት፥ ወይንም ጠግበህ ሳለ ከሆነ፥ በሥጋ ሕመም ላይ ሳለህ ከሆነ፥ ወይንም ፊኛህ በሽንት ተወጥሮ ከሆነ) የህልም ኑሮህን ይወስናል። እንግዲህ፥ በእውን አለምም ሆንክ፥ በሕልም አለም፥ ያንተን ሥጋዊ ስሜቶች ለማንበብ ብቻ አይደለም አንጎልህ የተፈጠረው። ከዚያም በላይ ሊሠራ ይችላል፤ በአግባቡ ከተጠቀምክበት። ከምድራዊ ተጽእኖ ነጻ ብትሆን (ብትጾም፥ ብትጸልይ)፥ በሕልም አለም ወይንም በእውን አለም ውስጥ ሳለህ፥ ምድራዊ ያልሆነውን አንተነትክን ታገኘው ይሆናል።

በዚህ አለመግባባት በሰፈነበት አለም ሁለንታዊ እውቀትን/እውነትን አምጥቶ፥ የመረጋጋትን መንፈስ በሰው ሁሉ ዘንድ እንዲኖር ሊያደርግ የሚችል እርሱ አምላካችን ብቻ ነውና፤ እግዚአብሔር የሰብአዊነትን የመጨረሻ ግቡን በእርጋታ ይመለከታል፤ አኬሄዱንም ይቆጣጠራል። ወደ ፈጣሪህ ተጠጋ፤ እርሱ ሁሉን ነገር ይገጽልሃል።

ከሁሉም በላይ፥ የሰላም ንጉሥ በሕይወታችን ይንገሥበት እንጂ፥ ከአንድ አለም <u>ሲወጣ</u>፥ ወደሌላውም አለም <u>ሲገባ</u>፥ ሁለቱ አለማት ሲነካኩ፤ በመሃል የሰው ሚናው (ተሳትፎው) ለምክንያት እንደተደነገገለት እንገነዘባለን።

አዎ! እውነት ተናግረሃል፤ ባንድ በኩል ከሩቁ ይታይሃል፤ ለደግ ሥራም ታልማለህ። በአእምሮህ የተሰረጹት መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ፍልስፍናዎች ከብዙ ሰዎች አእምሮ ውስጥም ያሉ ናቸው። ሆኖም፥ "ሁሉን እውነት" እንድናውቅ የሚፈለግበት ጊዜ ገና ነው። አንተ ግን፥ ከሰው ተለይተህ፥ ከራስህ ጋር ስትሟገት በመቆየትህ፥ ስሜቶችህን መቆጣጠር ሲያቅትህ፥ መጻፍ ጀመርክ። እራስክን

ከምድራዊነትህ ነጻ ለመውጣት ስትል፥ የጊዜና የቦታ ወሰን የሌለበት ሃሳብህን መዳኘ መንገድ በማድረግ፥ ስነ አእምሮህን ለቀቅ አድርገህ፤ ሃዘንክን ወደ ፍልስፍና ለውጠህ፤ የማይታየውን ለማስተላለፍ ትሞክራለህ።

አውቃለሁ ሳትል የሚመስልህን (የሚሰማህን) በነፃነት ልትናገር፤ በፍርኃት ወይንም ባለማወቅ ታፍነውና ተደብቀው የቆዩ ዋና ዋና ሃሳቦችንም ልትቀሰቅስ ተነስተሃል። ስትጽፍ አንተን እያነጫነጨህም ቢሆን እንድትጽፍ የሚገፋፋ ኃይል በውስህ መኖሩን ታውቃለህ። ታዲያ ሥራህ ሁሉ እንዲቃና በርትተህ ጸልይ። በተመስጦ ስትጸልይ፥ አስተሳሰብህ ይመጥቃል። የዛን ጊዜ፥ በመንፈስም አርቅቀህ (ርቀህ - ልቀህ)፥ የሥጋዊነትህ መገለጫ የሆንከውን አንተን በትንሽነቱ ታየዋለህ፤ በመንፈሳዊነት መገለጫ የሆነከውን አንተን ከፍ ብሎ ታየዋለህ።”

**ቶማስ**

“የሰው ስሜቱ አይገታም። ክረምት እና በጋ ሲቀያየር፥ ጸሐይ ሲያቃጥል፥ ዝናብ ሲዘንብ፥ የሚያመጣውን ስሜት መቆጣጠር ቀላል አይሆንም። ጫካ ውስጥ በዛፎች መካከል፥ ከወንዝ ዳር መገኘት እና የሰዎች ውካታና ግርግር በበዛበት መገኘት የተለያየ ስሜትን ይሰርጻል። ሰዎች በጉዞአቸውም ውስጥ ከመንፈሳዊነት እና ከእውነታ ሳይርቁ፥ ብዙ ድንቅ ድንቅ ሥራዎችን ሠርተዋል። ሆኖም፥ የሰዎች ምልከታ ሁሉም እንደየተፈጥሮአቸው እንደየአካባቢያቸው የተለያየ ስሜት በውስጣቸው ይሰርጻል፤ ስለዚህ፥ ወደ ተለያየ መንፈስ ይመራሉ።

የምድራዊ እውቀቶች ግልጋሎት በብዛት ለምድራውያን ስለሆነ፥ የምድራዊ እውቀት ብዛቱ ሁለንተናዊ እውነትን አያፈልቅም። ስለዚህ፥ እኛ በምድር ስንኖር በእውቀት ብዛት እና በውስጡ በተከማቸ ውሸት ብዛት ወደ ጥፋት እንዳንመራ በጥንቃቄ ማድረግ ስለሚገባን ነገር ሁሉ መንፈሳዊ መመሪያ እንደሚያስፈልገን አምናለሁ።

የሰው አይነቱ በቆዳ ቀለም፥ በመልክና በቁመና ከሚለያየው ልዩነቱ ይልቅ፥ ውስጣዊው የማንነት ልዩነቱ እጅጉን የጎላ ነው። ለሰውነት ያልበቃ፥ በአካል ሰው መስሎ፥ በውስጣዊ ጠባዩ እና በአስተሳሰቡ እንደ አውሬ አይነት ሰው አለ። በአካል ሰው መስሎ፥ ሰው ከመሆንም በላይ፥ በጠባዩ እና በአስተሳሰቡ እንደ መልአክ አይነትም አለ። ከምሁራንም መካከል፥ በእውቀታቸው ሳይሆን በባህሪአቸው ሰይጣናውያን ይኖራሉ። እነርሱም በረቀቀ እውቀታቸው እና በከፋው ባህሪአቸው እየተጠቀሙ አለማችንን በክፋት ጎዳና ይመሯታል።

አዎ! ከምድራዊነት ባሻገር ብዙ ክንውን ቢኖር ሥጋዊ በስሜት፥ መንፈሳዊ በልቡና ነው እንጂ፥ ሁሉም ነገር በግልጽ አይታወቅም። ስለዚህ፥ ከምናውቀው ባሻገር ሌላም መኖሩን ካወቅን ዘንድ፥ ለምናውቀው ነገር ሁሉ "ሌላም" ሰማያዊ ፍቺ ለመስጠት መሞከር አይከፋም። በምድራዊ አይናችን ከምናየው ተነስተን ማወቅ እና ማመን፥ በአይነ ልቡናችን አይተን ከምናውቀው እና ከምናምነው ይቀላል። አንዳንድ ሰዎች ግን፥ እነርሱ ከሚያውቁት ሌላ ሰፊ እውቀት፥ ሌላም እውነት ያለ አይመስላቸውም። እነርሱ ካላቸው ረቂቅ ምድራዊ ስነ አመክንዮ (logic) ሌላ ረቂቅ መንፈሳዊ ስነ አመክንዮ ሊኖር እንደሚችል አያስተውሉም።

ሰዎች ሲስቁ፥ ሲዘምሩ፥ ሲዘፍኑ፥ ስሜቶቻቸውን ሁሉ በተለያየ መንገድ ሲገልጹ፤ ምንጊዜም ትንሽ ትንሽ ከምድራዊነታቸው፥ ትንሽ ትንሽ ደግሞ ከሰማያዊነታቸው ቆንጠር ቆንጠር እያደረጉ መሆኑ ግልጽ ይመስለኛል።

ከእንስሳት ይልቅ እኛ ሰዎች በአንድነት አብሮ በመኖር ምድሪቱን በጋራ ልንጠቀምባት ስንችል፥ ተከፋፍለናል። ከእንስሳት እና ከሰዎች በተጨማሪ፥ በምድሪቱ ላይ የሚንቀሳቀስ፥ በተለይ ለኛ ለሰዎች ጠላት የሆነ፥ የማይታይ፥ ሌላ ተጠቃሚ ልዩ የጠላት ኃይል ያለ ይመስለኛል። እንዳው በእውነት፥ ይህንን በየጊዜው የሚሰማኝን፤ ግን ሊገባኝ ያልቻለውን የድብቁን ውስጣዊ ኃይል ነገር ለሰዎች ሳልናገር፥ እኔ በአእምሮዬ አምቄ ይዤ ብቆይ፤ ስለምጽፈው ሁሉ ግልጽነት አይኖረኝም ብዬ አስባለሁ። ያም ሆነ ይህ፥ አንዳንድ መጽሐፍ የሚጽፉ ሰዎች፥ ከሰው ሌላ መካሪ ቢኖራቸው ማን ያውቃል? በኢትዮጵያ ውስጥ ግን፥ እውቀት እንዳያድግ የእውቀትም መደነቃቀፍ ያለ ይመስለኛል።"

**<u>ዮሐንስ</u>**

"መካሪዎቻችን ብዙዎች ናቸው። ፍሬውን ከገለባው መለየት የኛ ፋንታ ነው። አንዱ ሌላውን በእውቀቱ ሲጫነው፥ የእውቀት እድገቱ ይቀጭጫል። አንተ ግን፥ ተስፋ ሳትቆርጥ፥ በተሰጠህ መክሊት ሥራበት፤ አትርፍበት። የሰው ልጅ፥ በሁለትነቱ ምሥጢር፥ ከሚታየው በላይ ከፍ ያለ ነው። ምንም ይሁን ምን፥ ቤተ ክርስቲያን መሄድን አዘውትር። "አልዕሉ አልባቢከሙ/ልቦናችሁን ከፍ ከፍ አድርጉ" ስንል፤ ወደ ማናየው መንፈሳዊ ማንነታችን እንድንጠጋ ነው። በመንፈሳዊ ከፍታ (በሰማያዊ እውቀት) ደስ እንዲለን ነው።

በሃሳብም ቢሆን፥ ፍጹም ወደሆነው ሥፍራ ዘልቆ መግባት ፍጹም የማንነት ለውጥን ያስከትላል። ስለዚህ እኛ ሰዎች፥ ሰዎች በመሆናችን ብቻ ልናውቅ የምንችለው ውሱን መሆኑን ተቀብለን፥ በእምነት እና በተስፋ እየጸለይን፥ አላፊ ጠፊ የሆነውን

ሰዋዊ (ምድራዊ) ማንነታችንን በትንሽ በትንሹም ወደ ዘለአለማዊ ማንነት ማስጠጋት ይሻለናል እንጂ፥ በትምህርት ብቻ ስለማናገኘው እውቀት እጅጉን መጨነቅ ተገቢ አይደለም። ሆኖም፥ በመሬት ላይ የሚፈስ ወራጅ ውሃ በአይን ስለሚታይ መኖሩን እንደምናውቅ፤ የከርሰ ምድር ውሃም እንደሚኖር ልናውቅ የምንችለው መሬቱን በመቆፈሪያ ስንቆፍር እንደሆነ ሁሉ፤ ስለማይታየውም የመንፈስ ነገር ለማወቅም፥ መንፈሳዊ ምርምርን እና ጥልቅ ጥናትን፥ እንዲሁም በጸሎት መትጋትን ይጠይቃል።

ስለ እግዚአብሔር መኖርና ስለ ሥራው እኔን የገባኝ በእንደዚህ አይነት መንገድ ነው በማለት፥ ማንም ሰው በየጊዜው የሚሰማውን ቢመዘግብ ትልቅ ጥራዝ ይወጣዋል። እነሆ! በአለም ላይ አንዳንድ ሰዎች በችሎታቸው ብስል ብለው ተናገሩ፤ እንዲሁም ጻፉ። ከነኚህም መካከል እግዚአብሔርን ያስደሰቱ፥ ያሳዘኑትም ይኖራሉ።

በመምሰል እና በማመሳሰል አለም ውስጥ መኖርክን ካወቅህ፥ የሚታሰብህን እያሰብህ፥ የራስክን መንፈስ በራስህ መርምር እንጂ፥ ለጥያቄዎችህ ሁሉ ከእኔ (ከሌሎችም - ከማንም ዘንድ) በቂ መልስ አገኛለሁ ብለህ አትጠብቅ።"

**ቶማስ**

"እውነት ነው፤ አለም ለሁላችንም አንድ አይነት አይደለችም። ሰዎች ሁሉ የየግል እምነቶቻቸውን ይዘው በሚኖሩበት ምድር ይህ ነው ትክክሉ ብሎ የጋራ እውነትን ማንጸባረቅ አይቻልም። የእውነት እውነትነት ለሁላችንም የጋራ ቢሆን ኖሮ፥ አቴይስቶች (ሃይማኖት የሌላቸው) እና ሃይማኖተኞች ለአንድ እውነት ሲሮጡ፥ ካንድ ሜዳ ላይ ስለሚገናኙ፥ በሃሳብ ይቀራረቡ፤ ይደጋገፉም ነበር።

ከምድራዊነት ባሻገር የሚታይ ነገር ባይኖር ኖሮ፥ በአለም ላይ ገዳማት እንዲህ ባልበዙ ነበር። መንፈስም እንደ አካል ህልውናውን ለሚቀርቡት ሰዎች ያረጋግጣል። ሰዎች ፍርኃት ሲያስጨንቃቸው፥ ወይንም በአለማዊነት ለመኖርም ምድራዊ ብቃት ሲጎድላቸው፥ እንደ ሙብል እና መጠጥ ለመኖር አስፈላጊ የሆነውን ሰላም ለማግኘት ሲደክሙ፥ ሳያስቡት ወደ መንፈሳዊነት ያዘነብላሉ።

እግዚአብሔር እኛን በመንፈስ እርሱን አስመስሎ ፈጥሮን ሳለ፥ ከምድራዊነታችን ጋር እየታገልን፥ በዝግመተ ለውጥም ቢሆን እራሳችንን እንድናሻሽል፥ መንፈሳዊነታችንንም እንድናጎለምስ ለእኛው ለራሳችን ፈቃዳዊነት ለቀቀን። እግዚአብሔርስ እኛን ፈጥሮ ለቀቀን፥ እኛስ በፍጥረታችን ላይ ያመጣነው ለውጥ ምንድነው?"

**<u>ዮሐንስ</u>**

“የሰው ልጅ በሕይወቱ ውጣ ውረድ፥ አንዴ ከፍ ሲል፥ አንዴ ዝቅ ሲል፥ ሲደላውና ደስ ሲለው፥ ሲጎድልበት እና ሲከፋውም፥ ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ ላይመለስ፥ እንደ ወንዝ ውሃ ከማደሪያው እስኪደርስ ድረስ ወደማያውቀው ሥፍራ ይጓዛል።

ከጥንት ጀምሮ፥ እግዚአብሔር በሰውና ለሰው የሞከረው ሁሉ መንፈሳዊ እድገትን ቢያሳይም፥ በውስጡ ብዙ ውድቀት የበዛበት እንደነበረ ነው ከመንፈሳዊ ታሪካችን የተማርነው። እግዚአብሔር የሚፈለገውን “በእርሱ ጊዜ” ፈጽሟል። እኛም በጊዜአችን በተስፋ ጸንተን እንኖራለን፤ በጸሎት ተነስተን የምንሠራውን ሥራ እግዚአብሔር ይባርክልናል ብለንም እናምናለን።

የሰው ልጅ ሥጋን ስለተሸከመ፥ እየበላና እየጠጣ፥ ፍጹም ጥሩ መሆን ስለሚያቅተውም ይቸገራል። ወሰን የሌለው አምላካችን ትንሽ መሆንንም ያውቅበታል፤ በታናናሾች ውስጥም እየገባ ሰዎች መሥራት የማይችሉትን ሥራ ያሠራቸዋል፤ መላእክትንም ለሰዎች ተራዳኢ እንዲሆኑ ስለሚያደርግ፥ የእነርሱን እርዳታ የሚጠይቅም የጠየቀው ይሰጠዋል።

ጥሩነት አንድ አይነት ነው፤ ፍጹምም ስለሆነ፥ የሰው ልጅ ጥሩነቱ (ከምድራዊነት ባልተበከለ በጥራቱ) ከመላእክት ጥሩነት የተስተላከለ እንጂ፥ የሚያንስ ወይም የሚበልጥ አይሆንም። እውነት በኃጢአተኞች ውስጥም ባትገኝ ኖሮ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአተኞች ጋር ምግብ ባልበላ ነበር። እውነት ከማንም ዘንድ ትገኛለች። እውነትን ሲናገሯት ኀልታ ትታያለች፤ ታብባለች። እውነት ኀልታ ስትታይ፥ እርሷ እጅግ ቆንጆ ስለሆነች፥ ተናጋሪዋንም ቆንጆ ታስመስለዋለች። በውሸት እና በእውነት ትንንቅ መካከልም ቢሆን፥ እውነት በሰዎች ታድጋለች። እርሷን ይዞ የሚደብቃት ግን፥ እርሱ የራሱን እድገት በገዛ ራሱ የሚከላከል ነው።

የሰው ልጅ አሉታዊነትን እየቀነሰ፥ በአዎንታዊነት ቢጓዝና ጠቃሚ በሆነው ላይ ብቻ የሚያተኩር ቢሆን ኖሮ፥ መጥፎ የምንለው ሁሉ ወደ ጥሩ መለወጡ አይቀርም ነበር። በዚህም ሆነ በዚያ፥ ሕይወታችን በሰው ችሎታና መፍጨርጨር ብቻ እንደማይወሰን ሁሉ፥ የጎበጠውን እንዲያቀና፥ የቀናውንም ወደ ሰዎች አእምሮ ገብቶ ጥሩ ጥሩውን እንዲያስመለከተን በጸሎት መማጸንና መቆየት ያስፈልጋል።

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሲፈጥረው ለብቻው (ካለ እርኩሳን መናፍስት ጣልቃ ገብነት) እንዲኖር፤ ለራሱ በተሰጠው የተፈጥሮ ባህሬው መሠረትም እንዲያድግ ነበር። እኛ ግን (በሠይጣንም ጣልቃ ገብነት) ይህንን አላወቅንበትም። ዳሩ ግን፥ እኛም ይህንን ተረድተን፥ በመንፈሳዊነታችን ብንጠናከር፥ ከመሃላችን የሚገባ

እርኩስ ኃይል አይኖርም። የዚህን ጊዜ ብቻ ነው ለራሳቸው በተሰጠን ውስጣዊ ባህሬአችን መሠረት የምናድገው።"

**ቶማስ**

"እውነት ነው። ሰማሁህ ዮሐንስ፤ አሁንስ በጣም ገባኝ። ሥራችን ሁሉ ለሌላው የሚጠቅመው፥ በቅድሚያ ራሳችንን ማረም ስንችል መሆኑ ገብቶኛል። የአእምሮ ሥራ ከማናውቃቸው ነገሮች መካከል አንዱ ነውና፤ እኛን ለማገልገል ብቻ ላይሆን ይችላል በአንገታችን ላይ ቁጭ ያለው። ከጠቅላላ ጠፈር ጋር ግንኙነት ቢያደርግና፥ እኛ ከምናስበው ውጪ ሌላ ሥራ ቢኖረው እኛ አናውቅም። የእግዚአብሔርን ሥራ ማን ያውቃል? የዘመኑ የስነ አእምሮ ሊቆችና ኒውሮሎጂስት የሚባሉ ሃኪሞችም ቢሆኑ፥ የራሳቸውን አንጎል እየተጠቀሙ፥ ስለሌላው አንጎል ሥራ ሙሉ በሙሉ እናውቃለን ማለት አይችሉም። መንፈሳዊ ስሜቶችን በጎን የሚያነካካ ቢኖር፥ ይህ በአእምሮ የሚታሰብ ብቻ ሊሆን አይችልም፤ አእምሮ ራሱን በገዛ አእምሮው ሊያውቅ አይችልምና።

አንዳንድ ጊዜ፥ የምናደርገውንም ነገር በደንብ ለይተን የማናውቅ "እኛ"፥ የማናውቀው ከምናውቀው ወይንም ልናውቅ ከምንችለው ሁሉ እጅግ የሚበልጥ ስለሆነ፥ "ወደዚያ" ሄድ ማለትን እንደ አንድ አማራጭ እንወስደዋለን። እኔም በሥራዬ ሁሉ፥ የእኔን አስተዋጽኦ "ማሙሽ ሂድና ቡና ጠጡ ብለህ ጥራ፤" እንደሚባል ሕጻን ብመስለው ይቀለኛል። ይህንንም ስል፥ "ለሁላችንም ያው ሳይሆን አይቀርም.." እያልኩ በማሰብም ነው።

በዚህ ግርግር በመላበት አለም ውስጥ ሥጋዊነታችን ሲያስጨንቀን፥ "እስቲ ሰዎች ሰማያዊነታችንንም እየተመለከትን እንጽናና፤.." በማለት፥ ሰዎች በቀላሉ የሚገነዘቡትን የምድራዊነታችንን ነገር በማስቀደም አንዲት ትንሽ እውነት ፈንጠቅ ለማድረግ ነው የተነሳሳሁት። ግን፥ አንዳንድ ጊዜ፥ የአለማወቅ ፍርኃት ውስጥ እገባና እጨነቃለሁ። አለማወቅ እያደገ ሰብአዊነትን ሲያሳምመው፥ ወደ ጥፋትም ሲከተው፤ "እኔ በበኩሌ የሚታየኝን ብርሃን በገዛ ፈቃዴ አላጨልመውም፤.." በማለት ነው የተነሳሳሁት። በተለይ ይህች ምድር በየጊዜው ለምታስደነግጠን ሰዎች "አይዞን! አይዞን! አይዞን!.." እያልኩ የምጽፈውን፥ አይመለከተኝም የማይል፤ በራሱ የማይመካ ትሁት ሰው ያነበዋል።

በአንድ በተወሰነ መንገድ የተቀሰቀሰ የመንፈሳዊነት ስሜት በቀላሉ የማይረጋ ስለሆነ፥ ለኔ እውነት የሆነ ሁሉ እውነትነቱ ለኔ ብቻ ሆኖ እንዳይቀር፥ በዝምታ ከመቀመጥ ይሻላል ብዬ፤ ሰዎች የገዛ ሕይወታቸው ሲበላሽባቸው ረጋ ብለው

እንዲያስተውሉ፤ በዚህ አለም ላይ የሚሆነው ሁሉ በምክንያት መሆኑንም እንዲገነዘቡ፥ በበኩሌ የሚሰማኝን ለመናገር ተነስቼአለሁ። አንተም በኔ የምትደምቅ ነህ፤ እኔም መንፈሳዊ የሃሳብ ብርሃን ለማግኘት ስል ነው አንተን ሆኜ፥ ወደ አንተ ተጠግቼ ልጻፍ ያልኩት።

የፍቅር እዳ አለብኝ። መድረክ ላይ ወጥቼ እንዳልናገር፥ እውቀት፥ ክህነት፥ አንደበትም የለኝ። በተአምር የተሰጠኝ አርእስቱ ቢከብደኝም፥ እባክህ ልጻፍ አትከልክለኝ።"

**<u>ዮሐንስ</u>**

*"አዎ! ሁሉ ነገር የጋራ ነው፤ የአንዱ ሰው ህልውና ለሌላውም ዋስትና ነው። እኔ እና አንተ ተደምረን፥ ሰውን ሁሉ ነን እንጂ የብቻችንን ነፍስ የራሳችን አድርገን አልኖርንም። እንዲህማ ባይሆን ኖሮ፥ ሰው ሁሉ እጅግ (ሲበዛ) ግለኛ ይሆን ነበር። ለሕዝቦች ሲሉ ሕይወታቸውን አሳልፈው የሚሰጡ ሕይወት የጋራ መሆኗን ያረጋግጣሉ። አንተም፥ ይህንን የማትለቀውን እርሱም የማይለቅህን "ከምድራዊነታችን ባሻገር" የተሰኘ አርእስት ይዘህ በሃሳብ ማእበል ስትንገላታ አያሌ ዓመታት አለፉ።*

*አይሁዶች ምድራዊ ነጉሥ ፈለጉ፤ ሰማያዊ ንጉሥ መጣላቸው፤ እርሱን አልፈለጉትም። ስላልፈለጉት በስቅላት እንዲሞት የሞት ፍርድን ፈረዱበት። እኛም'ኮ! እንደነርሱ ማየት ያለብንን ማየት ስለአቃተን፥ ምርጫችን በምድራዊነታች ላይ ብቻ ሙጭጭ ብሏል። እንዲህ ባይሆንማ ኖሮ - ስለመንፈሳዊ ሕይወታችንም እያሰብንበት ቢሆን ኖሮ - የብዙዎች ምድራዊ ኑሮም ከዚህ ከአሁኑ አኗኗር እጅጉን ሻል ባለ ነበር።*

*የሃይማኖት ልዩነት መኖሩ አንዳንድ ሰዎችን ሲያስጨንቃቸው፥ በሕይወታቸውም ውስጥም ህኪት ሲፈጠር አስተውለናል። ነገር ግን፥ ሁሉም በጌታ የተማሩ የሚሆኑበት ቀን እስኪመጣ ድረስ፥ ማንም ሰው ምንም ቢያውቅ ጨርሶ ሊያውቅ አለመቻሉን ተገንዝቦ፥ በማንኛውም አቅጣጫ የአለማወቅ ፍርኃት ጨርሶ እንዳይኖር፥ ጭንቀትንም እንዳያስከትል ተመክረናል።*[7]

*የሕብረተሰቡ ስቃይ እና መከራ ላንተ የህዋሳቶችህ እንቅስቃሴ ሆነው፥ በስሜት እርግብግቢት አስተሳሰብህን ስላጠነከሩት፥ አሁን ከውስጥህ እምቅ ኃይል አለ። ስለዚህ፥ በየጊዜው የምታየውን ሳትረሳ እየጻፍህ ቆይ እንጂ፥ ቸኩለህ "የጻፍኩትን*

---

[7] *"አለማወቅ ፍርኃት እንዳይሆን በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛልን።" 2ኛ. ጴጥ. 1፡2-3*

አንብቡልኝ" እያልክ አትመጻደቅ። ፍሬ ሃሳቦችህን ካለ ብልግና፥ ካለ እልኸኛነትና ካለ ቁጣ መግለጽ ከቻልክ ግለጽ። በእውቀት መኩራራት ስነ አእምሮአዊ የእውቀት ግርግዳን ይፈጥራል።[8]

እውነት በፍልስፍናዊ ንግግሮች አይመነዘርም። እውነት የጎደለው እውቀት አይጠቅምም። እውቀትም ካለቦታው ሲውል፥ ወይንም ማስተዋል የጎደለው እውቀት አደገኛ ነው። ስለዚህ፥ አስቀድመህ አንተ አንድ እልኸኛ ደንቆሮ መሆንክን ተገንዝበህ፥ እራስህን ከሰው ሁሉ በታች ዝቅ አድርገህ፥ ከማወቅህ ጋር አለማወቅም እንዳለብህ ለራስህ ተገንዝበህ እና ለሌሎችም አስገንዝበህ፥ ሁሉም ካንተ ብቻ የመነጨ ሃሳብ አለመሆኑን አሳውቀህ ጻፍ።[9] የምድርን ለምድር በመተው፥ እራስህን ከሰብአዊነት ጋር በማዛመድ (በልብህ የተከፉ ወገኖችህን በፍቅር እቅፍ አድርገህ) በምድር ቆይታህ እስኪያበቃ ድረስ፥ ለመፈጸም ያሰብከውን ምግባር ሁሉ ትፈጽም ዘንድ እኔም ልተባበርህ ወስኛለሁ።"

**<u>ቶማስ</u>**

"አመሰግናለሁ። እስከዚህ አብረን ከዘለቅንበት ውስጥ የሰውን ሃሳብ የሚያሰናክሉ ከሌሉበት ብቻ አብረን እንቀጥል፤ አለዚያ ቆም እንበልና እናስተውል። በዚህም ምዕራፍ ውስጥ የገባንበት ሃተታ ለወደፊት ለማሳወቅ ስለፈለግነው ጉዳይ መሠረት የማይጥል ከሆነ ይቅርብን።"

**<u>ዮሐንስ</u>**

"መልካም ብለሃል። አዎ! ከፍተኛ በሆነ ስሜት የሚታሰብህ ሁሉ በከፍና ዝቅ እየተርገበገበ ነው ያለው፤ ረጋ እስኪል ካልጠበቅህ ከንግግርህ ስሜትህ ይቀድምብሃል። እውነትን ስትናገር በመጀመሪያ እራስህን ረስተህ መሆን አለበት፤ የዚያን ጊዜ አንተ ኃጢአተኛ ብትሆንም እውነት ለሰብአዊነት መተላለፏ (መነገሯ) ብቻ ተፈላጊና ግዴታ ስለሚሆን፥ የአንተን አፍ የሚዘጋ፥ እጆችህንም እንዳትጽፍ የሚያደርግ ኃይል አይኖርም።

---

[8] *"አትታበዩ በኩራትም አትናገሩ.....።" ሳሙ. ቀዳ. 2፡3*

[9] *"የሰማነውንና ያወቅነውን፥ አባቶቻችንም የነገሩን፥ ለሚመጣ ትውልድ ከልጆቻቸው አልሰወሩም።" መዝ. 77፡3*

ሰብአዊነት እድገቱ መንፈሳዊነቱንም ጨምሮ ነውና፤ መንፈሳዊነት በሃይማኖት እውቀት እና በእምነት ይጎለምሳል። የእውነት ምንጭ አንድ ስለሆነ፥ እውነትን ለመናገር ከፈለግህ ከራስህ ወጣ ብለህ በመንፈሳዊ አይኖችህ ተመልከት የምልህ ለዚህ ነው። እስከ ዛሬ ድረስ በአለም ላይ የነበሩ፥ ያሉና ወደፊትም የሚኖሩ ሰዎች እውቀት ቢደመር፥ ለአንድ እግዚአብሔር ኢምንት እንደሚሆን ሁሉ፥ ከግለሰብ ማንነትና ከግላዊነት ከሚመነጭ እውቀት ይልቅ፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ያለበት ምግባር ነው ለሰው ልጅ የሚጠቅም። ከእንግዲህ፥ አንተ በምድራዊ አመለካከትህ የሰውን ሕይወት ከመጠን በላይ እያቃለልህ፥ በራስህ እና በአካባቢህ፥ በሰውም የእድሜ ገደብ ላይ ብቻ አታሳርፈው። አስተሳሰብህን በብዙ ሺህ ዘመናት ከሚቆጠረው የሰብአዊነት እድሜ ጋር አዛምደው፤ ሰማያዊውን ምሥጢር በምድራዊ ርዕዮት አትመዝነው፤ በትእግስት የሚሠራ ሥራ ሁሉ በቅዱስ መንፈስ ደጋፊነት ውጤቱ ያማረ ይሆናልና።

"ሕይወቴ ጥሩ ነገር በመሥራት ላይ ብቻ የተመሠረተ ይሁን፤ ከእኔነቴ እውነትን ላስቀድም" ብለህ ተነሳ። የሕይወትህ አላማና ፍልስፍና ጥሩ ሰው ለመሆን እና ጥሩ በመሥራት ላይ ያተኮረ ይሁን። ጥሩ መሥራት ከቆርፋዳ ጠባይ ጋር እና መጥፎ መሥራት ከለስላሳ ጠባይ ጋር በመጨረሺያ የሚያመጡት ውጤት ሊቀራረብ እንደሚችልም ተገንዘብ። ደግነት ከለሰለሰ ጠባይ ጋር ሲሆን ይጣፍጣል፤ ከሸካራ ጠባይ ጋር ሲሆን ግን ይጎመዝዛል። ስለዚህ በቅድሚያ ጠባይህን አሻሽል።

በውስጥህ ደግ እንዲሁም ለስላሳ ሳትሆን መልካም ውጤት ያለው የሃሳብ ልውውጥ ማድረግ ያስቸግርሃል። ያልኩህን ካሟላህ በኋላ፥ ከሰዎች ጋር ስትነጋገር፥ አስቀድመህ አንተ ከምታናግረው ሰው በታች መሆንክን የሚገልጹ ምልክቶች አሳይ፤ ይኸውም አንገትህን ዘንበል ቀለስ በማድረግ፥ እንደምንም ተጨንቀህ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ሁለት ሦስት አረፍተ ነገሮች ከተናገርክ በኋላ፥ የሚያዳምጡህን ሰዎች ስሜት ለመረዳት ሞክር። ንግግርህ ምንጊዜም የሰዎችን ስሜት እየጠበቀ መሆን አለበት (ስትጽፍም ያው ነው)። እስቲ አስበው፤ አንተ በልብህ እጅግ ጥሩ ሰው ሆነህ፥ ካፍህ የሚወጣው (የምትጽፈውም) ሰዎችን ካንተ ቢያርቅ፥ ያንተ ጥሩነት ለማን ይጠቅማል? ማንም ሰው፥ መጥፎ ሆኖ ሰውን እንዳይጎዳ፥ ጥሩም ሆኖ ጥሩነቱ ሰውን የማይጠቅም እንዳይሆን፥ ድርብ ኃላፊነት አለበት። ስለዚህ ምንጊዜም በሁለት በኩል (ከራስህ ለሚፈልቀው፥ ከሰውም ለሚመጣው) ጥሩ ሁኔታዎችን የማስተካከል ድርብ ኃላፊነት አለብህ። ይህም ማለት በልብህም በአፍህም ጥሩ ሰው መሆን አለብህ ማለት ነው።

"ኮሶን ለልጅ መስጠት በማር ጠቅሎ ነው፤ ማሩ እየጣፈጠው ቆሶው እንዲያድነው" እንደሚባለው ሁሉ፥ እጅግ መራራ የሆነውንም እውነት እያጣፈጡ

ማቅረብን እወቅበት፤ በጽሑፍ ልታስተላልፍ የፈለግኸውም ተቀባይነት የሚኖረው፥ ይህን የነገርኩህን ሁሉ ስታሟላ ስለሆነ፥ በቅድሚያ እራስክን አሻሽል ነው የምልህ። በቆይታ አስብበትና፥ የሰብአዊነትን መልካም (ቆንጆ) ገጽታ ለማንጸባረቅ ተነሳ።

የኛ ጥያቄ "እውነትን ከየት እናገኛት?" ብቻ አይደለም፤ "እውነትን እንዴት እንናገራት?" እያልንም መጠየቅ አለብን። አእምሮ ዳዊቱን ሲያነቡለት ይረጋጋል፤ ጽሑፍም ለሁሉ ሰው እኩል አይጥምም። እንግዲህ፥ የሁለታችን የሃሳብ ጉዞ፥ ከምድራዊው ወደ ሰማያዊው ስለሆነ፥ ብዙ መንገድ ይጠበቅብናል። ለጥሩ ነገር ስንነሳ፥ ምንጊዜም ወዳሰብነው ሥፍራ ካለ ችግር ሰተት ብለን እንዳንገባ ተከላካይ ኃይላት አሉብን። ችግሮች (የሚታዩና የማይታዩ - በሃሳብና በአካል) በተከታታይ እየመጡ ሲያደናቅፉን፥ ወደተፈላጊው አቅጣጫ እንዳናመራ የሚከላከል ጠላትም እንዳለብን፥ ይህንን እናውቃለን። የሚረዳን ኃይል ከጎናችን አለ። መሰናክል ሲበዛ - ሲደራረብ ችግር፥ በአይን የማይታየው ሌባ - ቅስሙ እስኪሰብር፥ ጸሎት ብቻ ነው - የመከላከያው ምሥጢር በዙሪያህ - የመስቀሉ አጥር።

የአጠቃላይ ሰብአዊነት እውቀት እዚህ እንዳደረሰን ሁሉ፤ ለወደፊትም ይህ የጋራ እውቀታችን አብሮ ሲያድግ ነው የማይታየውንም የሚያሳየን። አንተም ከዚህ የጋራ እውቀት ተገንጥለህ፥ ብቻህን የምታውቀው ነገር አይኖርምና (ሁሉም የሁሉም ነውና)፤ "እኔ፥ እኔ" ማለትን ሳታብዛ ተናገር (እንናገር)። ኃይል እና እውነት የእግዚአብሔር ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተገለጡ እውነቶችም፥ ሰው ሲሞት፥ እውነት በምድር ብልጭ ሲል፥ ፍቅር ሲዘራ - ከምድራዊነታችን ባሻገር ለሚሰማን ስሜት ሁሉ፥ መንፈሳዊ ደስታና ብሩህ ተስፋን የሚሰጥ፥ የፈጠረን ቸሩ እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት ምልክት - እርሱ የሚፈልገውን ፈቃዱን የምንፈጽምበት ያድርግልን። አሜን።"

# ምዕራፍ ሁለት

## አብዮት እና ንቃተ ሕሊና

ሞኝ አይሉት ብልጥ፥ ፈሪ አይሉት ደፋር፥ ደንቆሮ አይሉት ጠቢብ፥ አላዋቂ አይሉት አዋቂ፤ እንዳው ባጠቃላይ የቅጽል ስም የማይሰጠው፥ በአንድ ወቅት አንድ ግለሰብ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ይኖር ነበረ። ይህም ግለሰብ እኔው ነኝ። ሰዎች “የት ጠፍተህ ነበር? ከየት ብቅ አልክ?” በማለት ጥያቄ ሲያበዙብኝ፣ እኔም መልስ ለመስጠት ያልቻልኩበትን፥ ጊዜ ከዝምታ ፈልቅቆ ያወጣውን ወሬ አውርቼ ልጨርሰው ተነስቻለሁ።

በኢትዮጵያ አብዮታዊ ታሪክ ውስጥ፥ ጥቂት ዓመታት (እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ1966 - 1970 ዓ.ም.) ለብዙዎቻችን የቀውጢ ዘመን ነበረ። በተጠቀሰው የቀውጢ ዘመን ውስጥ እኔው ያለፍኩበትን የሚመለከት ነው የማወራው፤ ሠፋ ያለ የፖለቲካ ትንተና ውስጥ ሳልገባ፥ የግለሰብ እውነተኛ መጠሪያ ስሞችንም ሳልገልጥ።

አብዮቱ ሊፈነዳ አካባቢ (ከ1966 ዓ.ም. በፊት) ባለ ከፍተኛ ሕሊናዊ ተሳታፊ የሆንኩበት፥ የኮሙኒስትት መጻሕፍትን እያሳደድኩ ማነብበ የጀመርኩበት አንድ ወቅት ነበረ። ይህ ወቅት እኔን ባለ ከፍተኛ ምድራዊ (ፖለቲካዊ) ተሳታፊ አደረገኝ። እነኚህን መጻሕፍት እንደኔው ካነበቡ ግለሰቦች ጋር ስለ ሕብረተሰብ መጨቆንና ስለ መፍትሔው ጉዳይ ማውራት በጀመርኩበት ወቅት፥ በሶሻሊስት ፍልስፍና የተጠመዱ፥ ደረጀ እና ኃይሉ የተባሉ ግለሰቦች አጋጠሙኝ። ከእነዚህ የሥራ ባልደረቦቼ ጋር በማውራት ብዙ “እውቀቶችን” ሸመትኩ።

በዚያን ወቅት፥ “እግዚአብሔር እንዴት ለገዛ ፍጡራኑ አያዝንም? ጨቋኞች ተዝናንተው ሲኖሩ፥ ድሆች ሲሰቃዩ፥ እንዴት እያየ ዝም ይላል? እርሱ ለፍጡራኑ ሥጋዊ ኑሮ ካልተቆረቆረና ካላሰበላቸው እኛ ለምን እናምንበታለን?” በማለት፥ የሶሻሊስት ፍልስፍናን በመከተል፥ እግዚአብሔርን ለመካድ የደፈርንበት ዘመን ነበር።

እኔና የሥራ ባልደረቦቼ በሥራ ጉዳይ ገጠር የምንሄድበት ወቅት ደረሰና ወደ ትግራይ አመራን። ሥራችን በየጫካውና በየዱሩ የሚያዘዋውር የሥነ ምድር (ጂኦሎጂ) ምርምር ስለነበር፥ በመሸበት ድንኳን መትከል፥ ሲነጋ ድንኳን ነቅሎ

መጓዝ፥ የተሰጠንን ሥራ እስክንጨርስ ድረስ (አንድም ሆነ ሁለት ወር) የማያቋርጥ የቀን ተቀን ተግባራችን ነበር። በዚህ አይነት የትግራይን አውራጃዎች ሁሉ ገጠር ገጠሩን ስንዞር፥ በእረፍት በእረፍት ጊዜም ስለ ኮሙኒስታዊ ርዕዮት መወያየት ከመደበኛ ሥራዎቻችን አንዱ ሆኖ ነበረ።

ከእለታት አንድ ቀን፥ ቀኑ መሸና ድንኳን የምንጥልበት ማደሪያ ሥፍራ ስንፈልግ፥ አንድ በዛፍ የተከበበ ገላጣ ሜዳ አገኘን። ከሜዳው ዳርቻ (መቼም ትግራይ፥ እንደ ሕዝቡ ደግነት፥ ገዳምና ቤተ ክርስቲያንም የበዛበት ነውና)፥ አንድ እጹብ ድንቅ የሆነ ቤተ ክርስቲያን አየን። ድንኳናችንን ከቤተ ክርስቲያኑ ራቅ አድርገን ከሜዳው ላይ ተከልን።

ሦስታችንም በአንድ ድንኳን ውስጥ ተጠቃለን ተኛን። ሞቃት ሥፍራ ስለነበር፥ የድንኳኑን በር (ዚፑን) ሙሉ ለሙሉ አልዘጋነውም ነበር። ሌሊት በእንቅልፍ ልቤ፥ ደረጃና ኃይሉን ከእንቅልፋቸው የሚቀሰቅስ፥ ጥርት ባለ አማርኛ ንግግር አደረግሁ፤ ለፈለፍኩ። ምን እንዳልኩ የሚያውቅ የለም፤ ግን ያካባቢውን ጭቁን ሕዝብ የሚመለከት ንግግር ይመስላል። ምናልባትም ከመምሸቱ በፊት ስላጋጠመን ስለ አንድ ጭቁን ገበሬ ኑሮ፥ በቀን የታሰበኝ ይሆናል በሌላ መልኩ (በቅዠት) መልክ የመጣብኝ።

አንድ ጭቁን የትግራይ ገበሬ ድንጋይ ለድንጋይ እያማታ ያርሳል፤ በእርሻው ላይ ከአፈሩ ብዛት የድንጋዩ ብዛት ሳይበልጥ አይቀርም። ከሩቅ ሲያየን ሥራውን አቋርጦ እጅ ነሳን፤ ወዲያው ሊረዳን ፈለገና እኛ መንገድ ስንጠይቀው፤ እርሱ ደግሞ "እባካችሁ ኑ፥ ወደኔ ቤት እንሂድ፤ ሚስቴ ከእንጨት ለቀማ ስትመለስ ወጥ ትሠራልናለች። ቶሎ ካልተመለሰችና እናንተም ከቸኮላችሁ እንጀራ በበርበሬ እንበላለን እባካችሁ፥ ወደ ቤት እንግባ (*ጣይታ ብበርበሬ ጌርና ክንበልእ፤ በጀኻትኩም ገዛ ንእትው...*)" እያለ ተማጸነ።

በሥራ የትግራይ አውራጃዎችን በሙሉ ዞረን፥ የሕዝቡን አኑኗር፥ ታታሪ ሠራተኛ፥ በጠባዩም በመንፈሳዊነቱ የተቃኘ ደግነትን የተላበሰ ሕዝብ እንደሆነ አስተውለናል። በየቀኑ የምንመለከተው የሕዝቡ ድህነትና ጉስቁልና፥ በተለይ ገጠር የሚኖረው ገበሬ ሁኔታ ሁላችንንም እጅግ አሳዝኖን ነበር። የአስተዳደር መዛባት፥ የእኛም ሕዝቦች ያሉበትን ሁኔታ በደንብ አለመረዳትና ዘላቂ መፍትሔ አለመፈለግ፥ ይህ ሁሉ ታስቦኝ ይሆናል ሌሊት የቃዠሁት። ሲነጋጋ ሲል ደግሞ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያኑ ካለበት አቅጣጫ ተነስቶ በተከፈተው የድንኳን በር በኩል ሲያልፍ "ተመለከትኩ" (ያዩትን ወይም ያላዩትን እንደ መመልከት ነው? የሚመስል ሁሉ እውነት አይደለም እኮ!)።

ጧት፥ ገና ፀሐይ ሙሉ በሙሉ ሳትወጣ፥ ከእንቅልፋችን እንደተነሳን፥ ሲያቀብጠኝ ይህንኑ አስገራሚ ትእይንት ለጓደኞቼ ተናገርኩና፥ መሳቂያ - መቀለጃ ሆኜ ቀረሁ። ያየሁት የሰው ቅርጽ በሰው ቀለም ሳይሆን፥ ሰማያዊና ነጭ ሆኖ ነበር የታየኝ። ነገር ግን "ይህ የተመለከትከው መልክ የኢየሱስ ክርስቶስ መልክ ነው" የሚል ሃሳብ፥ ልክ እንደማይታበል ሃቅ በመሆን፥ እስካሁን በጭንቅላቴ ተቀርጾ አልጠፋ ብሏል። ጓደኞቼ ግን "ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በማደራችን በአእምሮህ የምታሰላስለው ተከሰተብህ፤ አንተ አሁንም አይዲያሊስትነት (በእግዚአብሔር አማኝነት) ያልተላቀቀህ መሆንክን ተረዳን" ብለው አዘኑብኝ። እኔም የበኩሌን እውነተኛነት ከጓደኞቼ አስተሳሰብ ጋር እያነጻጸርኩ በነገሩ ብዙ አሰብኩበት።

"መቼም በቤተ ክርስቲያን አካባቢ በሥጋም ሆነ በመንፈስ የሚንጎራደድ ሰው አይታጣም። መቼም ሳይንቲስትና ኮሙኒስት ሲደመር አይዲአሊስት ሊሆን አይችልም። የቀን ተቀን ተግባሬ ሳይንሳዊ ምርምር ሆኖ ሳለ፥ ይህን የማይመስል ነገር የሚያጉላላ ጭንቅላቴ እውነቱን ማመሳከር እንዴት ያቅተዋል?" ብዬ እራሴን በትዝብት ጠየቅሁ። የገዛ ራሴ ከሁለት እየተከፈለ ሲጨቃጨቅ፥ በተፈጥሮዬ እውነትን የመፈለግ ብርታቴን አዳካመብኝ። ከሰማዩ ብርሃን ጋር የሰው ቅርጽ እንዲፈጠር የሚያደርግ አካላዊ ክስተት ሊኖር ስለመቻሉ ጉዳይ ሳይንሳዊ ገለጻ ለማግኘት ባለመቻሌ፥ እራሴኑ ባለ ቅዠታዊ አስተሳሰብ ከማድረግ በስተቀር ሌላ አማራጭ በማጣቴ እስካሁን ድረስ ዝም አልኩ።

ለሰው (ለግለሰብ) ማንኛውም የሚታሰበው፥ ለዛ ሰው እውነት ቢሆንለት ወይንም ቢመስለው፥ ለዛ ሰው ነው እንጂ፥ አይሆንም ለሌላ። "እንዲህ አየሁ፥ ይህ ተገለጠልኝ..." የሚል ሰው፥ እንዳው ለወሬ ብቻ መሆኑንም እያሳወቀ ቢሆን ይሻላል፤ አንዱ አየሁ ብሎ ያወራውን ሰሚ ሊያረጋግጥ አይችልምና። በተለይማ ለአንዳንዶች፤ "ይህስ አእምሮአችን የሚጫወትብን *የማስመሰል ጨዋታ* ነው...." ብሎ ማለፉ ነው ደጉ። በዛን ሌሊት ያየሁትን ረስቼው ነበር፤ ለመነገርም ያልበቃ - ኢምንት ጉዳይ ነው ብሎ ማለፍም ይቻላል። ሆኖም፥ የሰው ልጅ ውስጣዊ እውነት የሚገለጽበት ጊዜ መኖሩን፥ እግዚአብሔር ምን ጊዜም ከኛ ጋር መሆኑን፥ ኃጢአተኞች ብንሆንም - ባንሆንም፥ እግዚአብሔርን የካድን ኮሙኒስቶች ብንሆንም፤ የእግዚአብሔር መንፈስ የማይለቀን መሆኑን (የእግዚአብሔር መንፈስ ምን ጊዜም በውስጣችን መኖሩን) እርግጠኛ ስለሆንኩ፥ እና ይህንኑ ለመግለጽ ስል ለመናገር ደፈርኩ። ብዙ የተደበቁ እውነቶችን በምጽፋቸው መጻሕፍት ሁሉ እንመርምር ከተባለ፥ አንባብያንም በራሳቸው ሕይወት ውስጥ ይህን እና የመሳሰሉ ጉዳዮች ሊያጋጥሟቸው ስለሚችሉ፥ በውስጠ አእምሮ ግንዛቤያችን እያሰላሰልን እውነቱን ብቻ እንድናቆይ ብዬ ነው።

ሌሊት የለፈለፍኩትንም፥ “አንተ እንደዚህ የተጣራ ንግግር ከየት ልታመጣ ቻልክ? ሌላ እኛ የማናውቀው ሰው በውስጥህ ደብቀህ እንደሆን ንገረን፤” ብለው ቀለዱብኝ ጓደኞቼ። እኔም የራሴ  ሁለት ሰው መሆን ዘወትር የማይገባኝ ጉዳይ በመሆኑ አሁንም ከዝምታ የተሻለ አማራጭ አላገኘሁምና፥ ጭጭ አልኩ። ሁለቱንም ሳዛምደው፥ ምናልባት ሁለት ሰው በመሆኔ፥ ሳላስበው “አንደኛው እኔ ክርስቶስን አይቶትስ እንደሆን?..” እያልኩ አሁንም ትንሽ ትንሽ እጠራጠራለሁ።

አዎ! ሁላችንም ሁለት - ሁለት ሆነን ተፈጥረን ሳለ፥ አንደኛው ተፈጥሮአችን ከአካባቢው (ከምድራዊነታችን) ጋር የተዛመደ ስለሆነ በደንብ እናውቀዋለን፤ ሁለተኛው ግን ከዚህ ከአካላዊ (ሥጋዊ) አለም ጭራሽ የተለየ በመሆኑ እምብዛም አይታወቀንም። ነገር ግን አልፎ - አልፎ ምክር ሲሰጠን ወይም ገደል ውስጥ ሲከተን እናውቀዋለን።  “አለ፥ ይታያል፥ ሆኗል” የምንላቸው ጉዳዮች፥ “የለም፥ አይታይም፥ አልሆነም፤...” ከምንላቸው ጉዳዮች የማይተናነሱ መሆናቸውን በውስጠ ልቦናችን ስለምናውቅ፥ “ግን እኛ በምን አይነት አለም ውስጥ ነው የምንኖረው?...” እያልን እራሳችንን መጠየቃችን አልቀረም።

ይህን በዚህ እንግታውና ወደ ቀድሞው ነገራችን እንመለስ። ከተጠቀሰው አይዲያሊስት አስተሳሰብ መላቀቅ እና በማርክስ እና ሌኒን ፍልስፍና እራሴን ማጠናከር፥ ለወደፊት ሕይወቴን በመስዋእትነት ለማቀርብለት ሰፊ ሕዝብ አማራጭ የሌለው መንገድ መሆኑን በመረዳት፥ አላማዬን ብቻ እየተመለከትሁ ኑሮዬን አስተካከልኩ።

በሀገራችን የአብዮት ፍንዳታና የመንግሥት ለውጥ ሲመጣ፥ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)፥ የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)፥ የኢትዮጵያ ኮሙኒስትት ፓርቲ (ኢኮፓ)፥ የኢትዮጵያ ጭቁን አብዮታዊ ትግል (ኢጭአት)፥ ማርክሲስት ሌኒኒስት አብዮታዊ ድርጅት (ማሌሪድ) የተባሉት ሁሉ ከፍተኛ ተሳትፎ ያሳዩበት ዘመን ነበር (ከ1966 ጀምሮ)።

በወቅቱ ሶሻሊስቶች ነን የምንል ወጣቶች ከሩቅ እንለያለን። ገንዘብ አለማጠራቀም፥ ሃብትና ንብረት አለመያዝ፥ በአጠቃላይ ለራስ አለማሰብና በአለባበስም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ ድሃውንና ሰፊውን ሕዝብ መምሰል የኛ ምልክት ነበር። ጢማም የሆኑት፥ ጭንቀትና ሃሳብ ሲገባቸው፥ ካለማቋረጥ ጢማቸውን ይጎትታሉ፤ ባለ ጎፈሬዎቹ ደግሞ፥ ከጆሮአቸው ሥር ጥቂት ጠጉሮችን ካለማቋረጥ ይገምዳሉ። ከውስጣዊው ማንነታችን ሌላ፤ ይህንን ይመስል ነበር የኛ ሳናስበው በጭንቀቶቻችን ምክንያት የሚከሰቱ ውጪያዊ መለያዎች (ምልክቶች)።

እንደኔ "አርቆ ማሰብ የተሳናቸው?" ኢሕአፓዎች ደግሞ፥ ለገዛ ቤተሰብ ማሰብና ለራስ ማሰብ፥ ባጠቃላይ ለሰፊው ሕዝብ ከማሰብ ጋር የተያያዘ መሆኑን ባለመገንዘብ፥ ራሳቸውንና ዘመዶቻቸውን መርዳትን ረስተውታል። ግን ወቅቱ ይህን ሁሉ ለማሰላሰል ፋታ የሚሰጥ አልነበረምና፤ ሶሻሊዝምን ስንሰብክ አለምን ንቆ እንደመነኮሰ ባህታዊ መስለን ነበር።

ኢሕአፓዎች በውጪያዊ ጠባያቸው የሚለዩበትን ፍንጭ ሰጠን እንጂ፥ እጅግ የሚያስገርመው ግን፥ በማንኛውም ጊዜ የአብዛኛዎቻችን ተመሳሳይ ውስጣዊ ጠባያችን ነው። ገና ከጅምሩ ወደ ኢሕአፓ ስንገባ እርስ በርስ የሚያስተሳስረን ተመሳሳይ ውስጣዊ ጠባይ (ስለ ጭቁን ሕዝቦች/ስለ ጨቋኞች ያለን አስተሳሰብ) ያቀራርበናል። በየቀኑ የምናገኛቸውን መረጃዎች እያሰባሰብን እርስ በርሳችን ስንወያይ፥ የምንሰጣቸው አስተያየቶች፥ ምልከታችንም (ርዕዮተ አለማችን) አንድ አይነት ነው።

በወቅቱ "**ዴሞክራሲያ**" የተባለው ዋናው የኢሕአፓ መጽሔት ነበር። ይህ መጽሔት በአጻጻፉ - በአማርኛው ጥራት፥ በአንድ ወጥ ርዕዮተ አለሙ እና በፖለቲካው ብስለቱ፥ ከሌሎች በወቅቱ ከሚሰራጩ መጽሔቶች እጅግ የላቀ ነበር። ሌሎች አባሪ መጽሔቶች በየመንደሩ ይሰራጩ ነበር። ከሁሉም ተወዳጅ እና በሰፊው የሚሰራጭ የዴሞክራሲያ መጽሔት ስለነበር፥ በሃሳቡ የሚስማሙ የማይስማሙም ያነቡት ነበር።

የኮሙኒስት አስተሳሰብ፥ አህጉራዊ ሃብትን በእኩልነት ለማዳረስ የሚያስችል፥ በሰዎች የእኩልነት ምልከታ ላይ የተመሠረተ፥ የመንግሥት ስርዓትን የሚያቀነቅን፤ ብልጥ የሆነ አንድ ሰው፥ በብልጠቱ እና አድሎአዊ የሆነ የመንግሥትን ስርዓት ተንተርሶ፥ ሌሎችን እየበዘበዘ፥ እርሱ ብቻውን ከበርቴ እንዳይሆን እና የተቀረው ሕዝብ ድሃ ሆኖ እንዳይቀር፥ ላዕላይ እና ታህታይ መንግሥታዊ መዋቅሮችን በኮሙኒስት መመሪያ መሠረት የሚያስተካክል ርዕዮተ አለም ነው።

የኮሙኒስት አስተሳሰብ ጥሩ ሆኖ ሳለ፥ አካላዊ በሆነ ነገር ብቻ በማመኑ፥ በውስጡ መንፈሳዊ ጠባዮችን ባለማካተቱና እንደ እንጨት በደረቀ ይዘቱ፥ እንደልብ ከሕብረተሰቡ ውስጥ መግባት አቃተው። በአስተሳሰቡ ውስጥ መንፈሳዊነትም ቢካተት ኖሮ ትንሽ ለስለስ ይል ነበር። በተለይ፥ ሃይማኖትን በማግለሉ፥ እግዚአብሔርንም የሚክድ በመሆኑ፥ ከመወደድ ይልቅ ጥላቻን ነው ያተረፈው።

የሰውን ልጅ ውስጣዊ ጠባይ ወደ አንድ ርህሩህ - ለሰውና ለምድሪቱ፥ ወይንም ለሀገሩና ለሕዝቡ የሚያስብ የሚያደርግ፥ ሌላ የተሻለ አማራጭ በመታጣቱ ምክንያት፥ ለጊዜው የወጣቱ ዝንባሌ የሕዝቦችን ነጻነት በእኩልነት እና በዴሞክራሲ ለማምጣት ከሚታገለው የኮሙኒስት አስተሳሰብ - ከኢሕአፓ ጋር ሆነ።

የኢትዮጵያ ወጣት "መንፈሳዊም ባልሆን ለጭቁኑ የማስብ ነኝ" በማለት፥ ወደ ኮሙኒስትነት ርዕዮት ዘንበል ያለው፥ ከራሱ ይልቅ የውጪው ስላማረው፥ ወይንም እግዚአብሔርን መካድ ምርጫው ሆኖ አይደለም፤ ጥንትም ከእናት እና ከአባቱ የወረሰው ለድሆች እና ለተጨቆኑ ማሰብ እና መቆርቆር ውስጠ ጠባዩ ሆኖ ነው እንጂ። ይህም ሆኖ፥ መቼም የሰው ሁሉ ጠባይ እጅጉን ለየቅል (የተለያየ) ስለሆነ፥ ምንም ቢሆን ለኮሙኒስት ስርዓት እጄን አልሰጥም ያሉ ነበሩ፤ የአንዳንዶችም ጠባይ በርዕዮተ አለም አይነቶች የማይበገር (ሊለወጥ የማይችል) ነውና።

## <u>*የፓርቲ ሕዋስ ምሥረታ*</u>

አብዮታዊ ቅስቀሳ ማካሄድ በጠመንጃ ከመዋጋት ስለማያንስ፥ እንደ እኔ ዝምተኛ የነበሩ ሁሉ እንደበታቸው በድንገት ተከፍቶላቸው ለፍላፊዎች የሆኑበት ዘመን ነበር። እኔም የኢሕአፓን ጽሑፎች እያነበብሁ፥ ከኢሕአፓ የፖለቲካ አስተሳሰብ ጎን ለጎን በመሆን፥ ጭቁን ሕዝብ በተገኘበት ሥፍራ ሁሉ እየተዘዋወርኩ ጥሩ ታናጋሪ ወጥቶኛል። እህ! ተናጋሪ (ቀስቃሽ) ከተባለስ፥ እነ እገሌን፥ እነ እገሌን (ስንቱን - ስንቱን! ኸረ ስንቱን!) ማን ይሆን እነርሱን አስታውሶ ስለነርሱ የሚጽፍላቸው? እነርሱ ግን፥ የትግላቸውን ፍሬ አይቶ መደሰትን እንጂ፥ በአጭሩ ለሚቀጠፍ ምድራዊ ሕይወታቸው ማስታወሺያ የሚሆን ስንክሳር አልፈለጉም።

በፊውዶ ካፒታሊስትነቱ የተጠላውን የዘውድ (የኃይለ ሥላሴ) መንግሥት የተካው ወታደራዊ አገዛዝ እያየለ ሲሄድ፥ የሕዝቦች የመናገር ዴሞክራሲያዊ መብት ተገታ። በጥቂት ወታደሮች በተመራው የመንግሥት ግልበጣ ከተመሠረተው ሶሺያሊስት መሳይ የፖለቲካ አቋም ውጪ የተለየ ሃሳብ ያቀረበ፥ የተቃውሞ ፖለቲካን የተናገረ ሁሉ "ጸረ አብዮያዊ ቅስቃሳ ያካሂዳል" እየተባለ አስሮ ማሰቃየት እና መግደል ተጀመረ። በዚህን ጊዜ በህቡዕ (በድብቅ) ተደራጅቶ ከመታገል ውጪ ሌላ አማራጭ ጠፋ።

ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው ሁለቱ የሥራ ባልደረቦቼ (ደረጀ እና ኃይሉ) እኔን አስተማሩኝ፥ በሶሻሊስትም ጎዳና መሩኝ እንጂ፥ ለማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት አላጨኙኝም ነበር። እንዳውም ትንሽ ቆይቶ ኃይሉ ከፎቅ ተጥሎ ተገሏል። ደረጀ ግን፥ እስካሁን ድረስ ይሙት ይኑር አላውቅም።

በዛን የአብዮት ወቅት አዲስ አበባ ቤት ተከራይቼ የምኖረው ታደሰ ከተባለው ጓደኛዬ ጋር ነበር። ታደሰ በጣም ጥሩ ሰው ነው። እኔና ታደሰ ተቀራራቢ ርዕዮት አለን፤ በብዙ ነገር እንስማማለን። ታደሰ ሚዛናዊ ነው እንጂ፥ ወላዋይ አይደለም። እኔና እሱን የሚለየን ነገር ቢኖር፥ እኔ ለማምንበት ነገር ቶሎ ብዬ እርምጃ

መውሰድ እፈልጋለሁ። እርሱ ግን የራሱን ፍላጎት በማያስጠብቅ ጉዳይ ላይ ፈጣን እርምጃ መውሰድ ካለመፈለጉም በላይ፥ ከበድ ያሉ ውሳኔዎች ላይ ለመድረስ ያዳግተዋል። ከታደሰ እኩል የማቀርበው አዲስ አበባ ተወልዶ ያደገ፥ ኢትዮጵያዊ ኤርትራዊ ጓደኛዬ ተክሌ ይባላል። እኔና ተክሌ በጣም እንዋደዳለን። በአስተሳሰብም በጣም ስለምንቀራረብ፥ ከታደሰ ይልቅ ብዙውን ጊዜ የማሳልፈው ከተክሌ ጋር ነበር።

የአብዮቱ እንቅስቃሴ እየተፋፋመ ሲሄድ፥ የሰው ሁሉ መነጋገሪያ የሆነው በየቀኑ ስለሚከሰተው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሆነ። የደርግ መንግሥት የንጉሣዊ ስርዓትን በመገርሰስ፥ በምትኩ ሶሻሊስት የሚመስሉ እንቅስቃሴዎችን ያካሂዳል። ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶችም እንደየአመለካከቶቻቸው፥ “ይህ መንገድ ይሻላል፥ ይኸኛው አያዋጣም..” እያሉ፥ ደርግን ቀርበው የሚያማክሩ፥ ከደርግም ርቀው የራሳቸውን አጀንዳ የሚያራምዱም ነበሩ።

እኔና ተክሌ “የሁሉንም ፖለቲካዊ አመለካከት እያጠናን፥ ለሰፊው ሕዝብ የሚጠቅመው የትኛው ነው?” ብሎ መምረጥና ወዳንዱ ድርጅት መጠጋት፥ ከተቻለም መሳተፍ አስፈላጊ መሆኑን አምነንበታል። ታደሰ ግን እንዲሁ ለወሬ ያህል መረጃዎችን በማሰባሰብ ከኛ ጋር ይሳተፋል እንጂ፥ ምንም አይነት አቋም የሚወስድ ሰው አልነበረም።

በድርጅቶቹ መካከል ቅራኔዎች እየተባባሱ ሄዱ። ኢሕአፓም በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ብዙ አባላትን አፍርቶ፥ እጅግ በሚያስገርም ሁኔታ፥ የፖለቲካ አቋሙን የሚያንጸባርቁ አብዮታዊ ቅስቀሳዎች፥ በጽሑፍ (በዴሞክራሲያ)፥ ለሕዝቡ በማዳረስ፥ አያሌ ደጋፊዎችን አፈራ። በዛን ወቅት ሁለቱ ታላላቅ ተቀናቃኝ ፓርቲዎች፥ መኢሶን እና እሕአፓ ብቻ ነበሩ። በሁለቱ መካከል የነበረውን ተቀራራቢ የሚመስል፥ ግን ጠለቅ ብሎ ለተመለከተው ተፃራሪ የሆኑትን ርዕዮቶች በደንብ መረዳት ቀላል አልነበረም። የሁለቱን ፓርቲዎች ውስጣዊ ልዩነት ለመረዳት የፖለቲካ መመሪያቸውን (አጀንዳቸውን) መመልከት ብቻ በቂ አልነበረም። ሌሎች አገሮች ያለፉበትን አብዮታዊ ጉዞ ማጥናት እና ካገራችን ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ የትኛው ነው ለሀገራችን እድገት የሚጠቅም ብሎ የተሻለውን መምረጥም ቀላል አልነበረም።

የሁለቱን ፓርቲዎች ልዩነቶቻቸውን በደንብ ከተረዱ በኋላ ለሠፊው ሕዝብ የወደፊት ዕድል የሚጠቅመውንና የተሻለውን፥ ከሁለቱ አንዱ ለኢትዮጵያችን የተሻለውን በመምረጥ፥ ወዳንዱ ተጠግቶ በጋራ መሳተፍ፥ በወቅቱ የነበርን የብዙዎቻችን ወጣቶች ዝንባሌ፥ ምርጫችንም ነበር። ስለዚህ፥ እንዲሁ በየመንገዱና በየቡና ቤቱ የምናወራውን ወሬ አቅጣጫ ለማስያዝ በሃሳብ የምንገናኝ ጓደኛሞች፥ በአንዳንድ አመቺ ሥፍራዎች ሰብሰብ እያልን መወያየት ጀምረናል። እኔና ታደሰ

የምንኖርበት ግን፥ በተለያዩ ምክንያቶች (የታደሰም አቋም አለመውሰድ ተጨምሮ) ለዚህ አመቺ አልሆነም። ሰው ቤታችን ቢመጣ፥ ወይንም ከታደሰ ጋር ቡና ለመጠጣት ወጣ ብንል፥ ሁሉም ነገር በታደሰ ቀልድ፥ ሳቅና ጨዋታ ዙሪያ እየሆነ፥ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና ተሳታፊዎቻቸው ከደረሱበት ለመድረስ አዳጋች ሆነ።

ከእለታት በአንድ ቀን፥ እኔን በጣም የሚቀርበኝ አንድ ሻምበል፥ “ና፤ ቡና እንሂድና ልጋብዝህ” ብሎ፥ ወዳንድ ቡና ቤት አመራን። ከዚያም ቢራ እየጠጣን የወቅቱን ጥያቄዎች ሊፈቱ በሚችሉ የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶች ከተወያየን በኋላ፥ ሻምበሉ “የዚህን አምባገነን ፋሺስታዊ የወታደር መንግሥት ገርስሶ በምትኩ “ጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት” ለመመሥረት መተባበር አለብን...” በማለት፥ በተለይ እኔ ይህንን ጉዳይ በጣም እንዳስብበትና እንድሳተፍ አጥብቆ መከረኝ።

“ባሁኑ ወቅት፥ ይህንን የንኡስ ከበርቴ ጠባይህን ትተህ ከሠፊው ሕዝብ ጎን ካልተሳተፍክ፥ ያንተ አርቆ አሳቢነትና ተቆርቋሪነት ምንድነው?” አለኝ። ሻምበሉ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ስለነበርና ውሎውም ከተማሪዎች ጋር ስለነበር፥ እርሱን የደርግ አባል ይሆናል ብሎ የሚጠረጥር ሰው አልነበረም። እንዳውም ብዙዎቻችን በርሱ ተናጋሪነት አንድ ቀን ይይዙትና ያስሩታል ብለን እንፈራለት ነበር። አልቀረለትም፤ ከጥቂት ቀናት በኋላ፥ ያንን ሻምበል ያዙት። እጅጉን ከሚያፈቅራት ከሚስቱ እና እጅግ ከሚንከባከባቸው፥ በገባ በወጣ ቁጥር እቅፍ እያደረገ ከሚስማቸው ከሁለት ሴት ልጆቹ ለይተው ወደ ወህኒ ቤት አስገቡት። እርሱም አንድ ቀን እንደሚገድሉት ያውቅ ስለነበር፥ እንዲሁ በየቀኑ ደርግን እየተራገመና እየተሳደበ፥ ብዙም ሳይቆይ ተገደለ። የብዙዎቻችን ጓደኛ የሆነ፥ አንድ ለአገሩ ተቆርቋሪ የሆነ ጀግና፥ ገና በጅምሩ ቶሎ ተቀጨ፤ ያሳዝናል።

የኢሕአፓ ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይወሰን፥ በየከተማዎችና በገጠሮች ሁሉ ሲዳረስ፥ እኔም በውስጤ በኢሕአፓ የፖለቲካዊ የአመለካከት (የርዕዮት) መስመር ውስጥ መገኘቴ፥ ግን የኢሕአፓ አባል ለመሆን ምንም እርምጃ አለመውሰዴ፥ ሻምበሉም ሲለኝ የነበረው ሁሉ ተጨምሮ፥ አእምሮዬን እረፍት አሳጣው።

ከእለታት በአንድ ቀን፥ ተክሌ ቀርቦ አነጋገረኝ። “እኔና አንተ እስከ መቼ ነው ገለልተኞች የምንሆነው? ሁለታችንም ኢሕአፓን እንደግፋለን፤ ለምን ተሳታፊዎች አንሆንም?...” በዚህን ጊዜ የሻምበሉ ምክርና ተግሳፅ ትውስ አለኝና “አዎ! ልክ ነህ፤ ...እ..እ...ይሰማኛል፤... ግን ይህ እንዴት ይቻላል፥ የሚመለምለን ሳይኖር? ለመመልመል ደግሞ ሰብሰብ እያሉ ጥናቶችና ውይይቶችን ማካሄድ ያስፈልጋል።

እንደምታውቀው፥ በዚህ ሃሳብ ታደሰ አይስማማም፤ ቤቱም አሞቺ አይደለም....” አልኩ።

ተከሌም ሳቅ ብሎ “እህ!..እንደምታውቀው፥ አብዛኛው ሕዝብ፥ በተለይ ዝቅተኛው የሕብረተሰብ ክፍል የሚያወራው ስለጊዜው ሁኔታና ስለ ቀጣይ የመደብ ትግል ነው። በታደሰ ዙሪያ የሚያንዣብቡ ግለሰቦች ግን፥ ከቀን ወደቀን ለጊዜው ደስ በሚያሰኙ ቀልዶች (ዋዛ ፈዛዛ) ድንዝዝ እያሉ፥ ሠፊውን ሕዝብ እየረሱ፥ የራሳቸውን ምቾት ፈላጊዎች ናቸው። እኛም በዚሁ ከቀጠልን፥ ከራሳችን የቀን ተቀን ኑሮ አልፈን፥ ለሠፊው ሕዝብ የማናስብ ንኡስ ከበርቴዎች መሆናችን ነው። ታዲያ አንተም ከነሱ ተደምረህ እስከመቼ?...እኔ ሳውቅህ፥ አንተ ለየት ያልክ ነህ፤ እስከመቼ ከማይመስሉህ ጋር ጊዜህን ታጠፋለህ? ውጣና ሌላ ቤት ተከራይ፤ ይህ ነው መፍትሄው፤ አይመስልህም?” አለኝ።

እኔም “ይመስለኛል፤ ግን የት ነው የምከራየው? በየጊዜው ለመሰባሰብ የሚያመች ሥፍራ ታገኛለህ?” አልኩት። እርሱም “ይህንን በኔ ተወው፤ በአንድ ሳምንት ውስጥ ቆንጆ ቤት ፍልጌ አግኝልሃለሁ” አለኝ። ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ተከሌ መጣ። “ናና ቤቱን እንየው” አለኝ። ቤቱን ሳየው ወደድኩት። በዛኑ ለት ተፈራርሜ በሚቀጥለው ቀን ልብሶቼና መጻሕፍቶቼን ይዤ ወጣሁ፤ ለታደሰ ሳልነግረው።

ታደሰ የዛን ጊዜ በሥራ ጉዳይ ወደመስክ ተሠማርቶ ነበርና ቤት መልቀቄን አላወቀም ነበር። ከመስክ ሲመጣና ቤቱን ሲያየው፥ የኔንም መልቀቅ ሰራተኛዋ ስትነግረው እጅጉን ተቆጣ። እርሱን ያሳዘነውና ያናደደው፥ ለምን ለኔ ሳይነገረኝ ወጣ ብሎ ነው። ጉዳዩን እንደዚህ በዝርዝር መናገር የማይቻልበት ወቅት ስለነበረ፥ ሁሉንም እንደ ቀላል ነገር በማድበስበስ እና በማሳሳቅ “በቃ ይቅርታ አድርግልኝ” ብዬው ነው የተለየሁት። ታደሰ አሁን ይህንን ጽሑፍ ሲያነብ ነው በደንብ የሚገባው እንጂ፥ እርሱማ ደግ ሰው ስለሆነ፥ ወዲያው ነበር ይቅርታ ያደረገልኝ።

በሃሳብ የምንቀራረብ ከአዲሱ ቤት መሰባሰብና መወያየት ጀመርን። ስንጀምር አልፎ አልፎ ከሚመጡት ጋር በጠቅላላ ወደ አስር እንጠጋለን። ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራችን እየቀነሰ ሄዶ፥ በጣም በሃሳብ የምንቀራረብ ብቻ ከሰባት አንበልጥም ነበር። ሁላችንም ልክ እንደ ትምህርት ቤት ጥናት ያህል፥ የሶሻሊስት ጽሑፎችን እናነባለን፤ ባነበብነውም ላይ እንወያያለን።

ትግሉ እየተባባሰ ሲሄድ፥ በመካከላችን የነበረም ጥቃቅን የርዕዮት ልዩነት እየጎላ ሄደ። ቀስ በቀስ ቁጥራችን መነመነ። ሆኖም የኢሕአፓን አመለካከት ያልለቀቅን እኔ፥ ተከሌ፥ አሰፋና መሃመድ ብቻ ነበርን። መሃመድ ብዙ የማይናገር ከመሆኑም በላይ፥ አልፎ አልፎ ብቻ ነበር ከኛ ጋር የሚገናኝ። ከጊዜ በኋላ፥ ትግሉ እየተፋፋመ

ሲሄድ፥ ግድያዎችም ሲባባሱ፥ ከዚያ ቤት መቆየት አስጊ ሆነና፥ እንደገና ሌላ ቤት ቀየርኩ። ካዲሱ ቤት የምንገናኝ አራታችን ብቻ ሆን። እኛን ቀርቦ የሚመለምለን ጠፋ። በተለይ እኔና ተክሌ "እስከመቼ ነው ከትግሉ ተገልለን የምንቀመጥ?" እያልን ተበሳጨን። ከአራታችን ውጪም እኛ በፖለቲካ አቋማቸው የምናውቃቸው "ኢሕአፓ ለምን አይመለከተንም፤ አብረን በቆራጥነት እንዳንታገል" እያሉ የተጨነቁም ነበሩ።

ከእለታት በአንድ ቀን አራታችን ብቻ ከኔ ቤት እየተገናኘን ቋሚ ጥናት እንድንጀምር መሃመድ አሳሰበ። በዚሁም መሠረት እኔ፥ ተክሌና አሰፋ ከኔ ቤት ተገናኝተን፥ መሃመድን ስንጠባበቅ፥ መሃመድ ትንሽ ዘግየት ብሎ ከአንድ እኛ ከማናውቀው ሰው ጋር መጣ። መሃመድ የዚህ ግለሰብ ከኛ ጋር መሳተፍ ለበጎ ስለሆነ፥ በቅድሚያ የኛን ፈቃድ ጠየቀ። እኛም መሃመድን በመተማመን ብቻ "እሺ" አልን።

ግለሰቡ ግርማ ይባላል፤ ረጋ ያለና አስተዋይ ነው። የፖለቲካ ብስለቱና ስለ ሶሻሊዝም ያለው እውቀት ካነጋገሩ ያስታውቃል። አልፎ አልፎ፥ የኢሕአፓ አባል ያልሆነ ሰው ያውቅ ዘንድ የማይቻለውን፥ በድርጅቱ ውስጥ የሚከናወነውን ጉዳይ ሲያሳውቀን፥ በተዘዋዋሪ ከላይ (ከበላይ አካል) በተልእኮ ከውስጣችን የገባ መሆኑ ያስታውቅበታል (እኛም ጠርጥረናል)።

ስብሰባውን ስንጀምር እርሱ እንደመሪያችን እየሆነ፥ ማድረግ ያለብንን ይነግረን ጀመር። ከሁሉ አስቀድመን የሶሻሊስትን ቲዎሪ በደንብ እንድናውቅ፥ የሁለቱን መጻሕፍት (Historical Materialism & Dialectical Materialism) ይዘት በሚገባ ስንወያይ አንድ ወር አለፈ። ቀጥሎም በድርጅቶች መካከል ያለውን ቅራኔና የኢሕአፓ አቋም ከሌሎቹ እንዴት እንደሚለይ፥ ጽሑፎችን ሁሉ እያነበብን ተወያየን። በሦስተኛው ወር ላይ ያተኮርነው በወቅታዊ ጉዳዮች ላይና በኢሕአፓ እርምጃዎች ዙሪያ ነበር። በዚህን ጊዜ ሁሉ፥ ግርማ ከጥዑም ልሳኑ ጋር፥ በአስተሳሰቡ በጣም የበሰለ፥ የፖለቲካ እውቀቱም ከሌሎቻችን ሁሉ በጣም የላቀ መሆኑን ተረድተናል። ግርማ ሁላችንንም በጥሞና እያዳመጠ፥ የሁላችንንም አመለካከት የሚያደንቅ፥ በተለይ በኔ በኩል የሚሰነዘሩ አሳቦችን የሚወዳቸው መሆኑን ይነግረን ነበር።

ከሦስት ወራት በኋላ ግርማ የምሥራች ይዞልን መጣ (ለያንዳንዳችን ከፓርቲው ጋር የሚያገናኝ ኮድ)። እኔ እና አሰፋ በፓርቲው መዋቅር ውስጥ ስንገባ፥ መሃመድና ተክሌ በወጣቶች ክንፍ (ኢሕአወሊ - *ኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ወጣት ሊግ*) ውስጥ ገቡ። ሁላችንም በተመደብንበት ሥራ ተሰማራን።

# ምዕራፍ ሦስት

## የኢሕአፓ መከፈል - የአንጃዎች መፈጠር

በስሜት ተገፋፍቼ ሳይሆን፥ በአስተሳሰብ (በርዕዮተ አለም አመለካከት) የኔ ዝንባሌ ወደ ኢሕአፓ ተጠግቶ፥ እዚህ ድርጅት ውስጥ ለመግባት አስፈላጊ የሆኑትን የሕቡእ ጥናቶች ከጨረስኩና ፈተናዎችንም ካለፍኩ በኋላ፥ የፓርቲ አባል ለመባል በቅቼ፥ ከበላይ አካል የሚተላለፍልኝን ድርጅታዊ ሥራዎች መሥራት ጀምሬአለሁ።

በቅድሚያም፥ ከባንክ የነበረኝን ገንዘብ ሁሉ አውጥቼ፥ ግርማ ለፓርቲው እንዲሰጥልኝ ነግሬ፥ ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናበትኩት። ከሌሎቹም ጓዶች ጋር እንደበፊቱ መገናኘት ትተናል። ግርማ አሁንም በሕይወት ያለ ይመስለኛል፤ ግን እርግጠኛ አይደለሁም።

በሕቡዕ መታገል ማለት አብዛኛውን አብዮታዊ እንቅስቃሴ በድብቅ ማከናወን ስለሆነ፥ የሚያውቁኝ ሁሉ እስኪረሱኝ ድረስ፥ በልዩ ልዩ የፓርቲው የፖለቲካ አውታሮች ውስጥ በመሳተፍ በሕቡዕ ታግያለሁ። ሰው የሚፈልገውን ሥራ ሲያገኝ እና ሲሠራ ጥሩ ነው (ደስ ይላልም)።

የኮሚቴ ውይይቶች በምናደርግበት ወቅት፥ በዚያን ጊዜ፥ የሰው ልጅ መመዘኛያና መለኪያ አብዮታዊ አመለካከቱ ስለነበር፥ ከብዙ ጓዶች ጋር ተዋወቅሁ። ከነኚህም መካከል በኋላ ሚስቴ የሆነችው ኮከቤ ትገኝበታለች። ከቀን ወደ ቀን የሚፈጠረው ሁኔታ ለአንድ ደቂቃ እንኳን ቢሆን ፋታ የሚሰጥ ሆኖ አልተገኘምና፤ ሁላችንም በትግል አለም ተጠምደን ለአንዲት  ቅጽበት ታህል እንኳን አለማዊ ኑሮ ስለማያሳስበን፥ እኔ ኮከቤን በጓዳዊ ስሜት ብቻ ነበር የማውቃት፤ እርሷም እንዲሁ።

በቀድሞው "ሰላማዊ" ኑሮ ምትክ እጅግ አስከፊ ኑሮ ሲተካ፥ በአንጻሩም ፓርቲዎችና ድርጅቶች በርዕዮተ አለምም ሆነ በእንቅስቃሴ እየተጠናከሩ ሲሄዱ፥ የእኔ ኑሮ መልክ እየያዘ መጣ። ለመኖሬ ትርጉም አገኘሁለትና፤ ደስ የሚል ሕይወት መኖር ጀመርኩ። የጥናት ህዋሶችንም በመመሥረትና የፓርቲ አውታሮችን በመዘርጋት በኩል ጥቂት የማይባል አገለገልኩ። አዎ! ደስ እያለኝም ወደ ሞት ሊያመራ የሚችል፥ የበላይ አካል ትእዛዞችን ሁሉ ከመፈጸም አልቦዘንኩም። የፕሮፓጋንዳ ጽሑፎችንም "የድል ኮከብ" በምትባል የመንደር መጽሔት አማካኝነት እስከማዘጋጀት ደረጃ ደርሼ ነበረ።

ይህች መጽሔት የምትዘጋጀው ከኔ ቤት ነበር። አሠራሩም እንደሚከተለው ነው፡- በጊዜው ኮምፒተር ስላልነበረ፥ ታይፕ የማድረጊያም መሳሪያ ስለሌለን፥ ጽሑፉን በእጅ በወረቀት ላይ ጽፈን፥ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ለምትሠራ ለአንዲት የኢሕአፓ አባል ለሆነች ጸሐፊ (ሴክሬታሪ) እንሰጣታለን። እርሷም እየተደበቀች በእስቴንሲል (በፊደሎቹ ቅርጽ የሚበሳሳ) ታይፕ ታደርግና ትሰጠናለች። እኛም ያንን እስቴንሲል በድብቅ ተቀብለንና ከቤታችን ወስደን እንደሚከተለው እናትማለን፡-

በአንድ በደንብ የተላገ፥ እንደ መከተፊያ አይነት፥ ጠፍጣፋ እንጨት ላይ፥ ወፈር ያለ ጥቁር ቀለም እናፈስና፥ በላዩ ላይ ታይፕ የተደረገውን እስቴንሲል እናስቀምጣለን፤ ከእስቴንሲሉ ላይ አንድ ባንድ ወረቀቶችን እያስቀመጥን፥ ጥቁሩ ቀለም በእስቴንሲሉ ቀዳዳ እየወጣ እንዲያትም ከላይ በእንጨት መዳመጫ እንዳምጣለን። ከዚያም መጽሔቶቻችንን (የድል ኮከብ) እንበትናለን፥ ወይንም ለበታኞች እናከፋፍላለን።

በኢሕአፓ በኩል የተፈጸመ ታሪክ ተወርቶም አያልቅ። ግን ባጭሩ፡- ከብዙ የጽሑፍና የንግግር ፕሮፖጋንዳዎች (ቅስቀሳዎች)፥ ከአንዳንድ የግለሰብ ግድያዎችም በኋላ፥ ብዙ ሰላማዊ ሰልፎች ተደረጉና፥ ብዙ ወጣቶች አለቁብን። በኢሕአፓ በኩል የተሞከረው የደርግ መንግሥትን የመፈንቀል ሙከራ ሳይሳካ መቅረቱ፥ አንድ የኢሕአፓ ውድቀት መከሰቻ ሆነብን። የሀገር መሪ በተባለው ሰውዬ ላይ የተቃጣው የግድያ ሙከራ ውጤት ግለሰቡን በሥጋ ከማቁሰሉ በስተቀር፥ "ደም የሚመስል ከበድ - ጠቆር ያለ መንፈሱን" ከምንጊዜውም የበለጠ አኮሳተረው (መራራው ሃሞቱ የበለጠ መራራ ሆነ)።

የመንግሥት ተባባሪዎች ሁሉ የቀይ ሽብር በሚል መጠሪያ በአንድነት ትግላቸውን በማቀነባበር፥ በኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎቻቸው ላይ ዘመቱባቸው። ግድያ በያለበት ተጧጧፈ። ለቀበሌ የአብዮት ጠባቂዎች የመግደል መብት ተሰጣቸው። ከእነኚህም መካከል የእንስሳነት ጠባያቸው ያመዘነባቸው ጨካኞች የሰው ሚስት መቀማት፥ ገንዘብ ካላቸው ላይ "እፈታልሻለሁ፥ እፈታልሃለሁ" እያሉ ጉቦ መቀበል፥ አሰቃይቶ መግደል፥ ባጠቃላይ ለመስማት የሚዘገንን ግፍ መፈጸም የወቅቱ የአብዮታዊነት መለኪያ ሆኖ ነበር። ከነኚህ ግፈኞች መካከል፥ በነፍስ ወከፍ (እያንዳንዳቸው)፥ መቶና ሁለት መቶ የገደሉም ነበሩ። ወጣቶችን እየገደሉ መንገድ ላይ በመጣልና በመተው፥ ተመልካችን በፍርኃት ማሸበር እና ማሽማቀቅ እንደ አንድ የስነ አእምሮ ጦርነት ተቆጠረ።

የኢሕአፓ አባላትን ሁለት ቦታ በመክፈል ሲያጨቃጭቅ የቆየ የአመለካከት ልዩነት በገሃድ ወጣ (አንጃ ይባላል - ተቃዋሚ - ተገንጣይ ማለት ነው)። ይህን

የአመለካከት ልዩነት የሚገልጹ ዘገባዎች ከፓርቲው ይደርሰኝ ስለነበር፥ እውነት መስሎኝ የነበረ ሁሉ አጠራጠረኝ (አንድ ሰው ከሁለት ቢሰነጠቅ ሰው እንደማይሆን፥ ይህም ፓርቲ ከሁለት ቦታ ተሰንጥቆ ፓርቲ ሊሆን እንደማይችል፥ ውስጣዊ ስሜቴ ነገረኝ)። እኔ ብቻ ሳልሆን፥ እንዲህ አይነቱ መጠራጠር በፓርቲ አባላት መካከል ተስፋፋ። ፓርቲውም ከሁለት ተከፈለና ተገንጣዮች የራሳቸውን የተገንጣይ ክፍል (አንጃ) ሲያጠናክሩ፥ "ምድራዊ ኩነቶች" እውነተኛ ማንነታቸውን በቅድሚያ ለኛ ለአባሎች ነበር ያሳዩንና ያስደነገጡን።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ (አይ! ያ ጊዜ!....) የፓርቲው አካሄድ የተሰነካከለና የተደነቃቀፈ፤ የሚወሰደው እርምጃ ሁሉ ባጭሩ እየተቀጨ የሚከሽፍ ሆነ። በያለበት የፓርቲ አባላት እየተገደሉ፥ ምንም መሥራት እስኪያቅት ድረስ ተደረሰ። በጊዜው የነበረ "ጎህ" ተብሎ የሚጠራ መጽሔት ስለ ኢሕአፓ አቃቂር ሲያወጣ እንዲህ አለ፡- "ወጣ ወጣና እንደ ሸንበቆ፥ ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ"። ፓርቲውን እንዲህ እንደ ሙቀጫ እንዲንከባለል ያደረገው የጠላትን ኃይል በትክክል መመዘን አለመቻልና አክራሪነት ሲሆን፥ በጎን ደግሞ የአንጃዎች መፈጠር ነበረ።

ሀ እና ለ ተብለው የሚጠሩ፥ በማንኛችንም ዘንድ በታጋይነታቸው ስማቸው የገነነ (ብዙ የተጻፈላቸው)፥ ሁለት አብዮታውያን ግለሰቦች የፓርቲው መስራቾች እንዳልሆኑ ሁሉ፥ በቀውጢ ቀን በተገንጣይነት (በአንጃነት) ስማቸው በተጠራ ጊዜ፥ የአብዛኛዎቻችን የፓርቲ አባላት ቅስም ከሁለት ተሰነጠቀ።

የፓርቲው መሥራችና መሪ ከነበረው ሀ ተብሎ ከሚጠራው ቀጥሎ ፓርቲው የሚመራው "ደብተራ" ተብሎ በሚጠራ ግለሰብ ነበር። ግለሰቡ ከህጻንነት ጀምሮ ከቤተ ክርስቲያን ያደገ በመሆኑ፥ ትሁትነት እና ደግነት የተዋሃደው እጅግ ቀልደኛና ተጫዋች ሰው ነበር። የአማርኛው ጥራትና የአነጋገሩ ስልት፥ የእውቀቱ ብዛት እና ወሬው ሁሉ፥ ሲናገር ለሚሰማው፥ ምነው እኔም ከቤተ ክርስቲያን ባደግሁ ያሰኛል። ቀልዱን - ኩምከናውን ከቁም ነገር ያዛመደ፥ የፖለቲካ ሳይንስ ተማሪ፥ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ስለነበር፥ እርሱን የሚወዱትና በሄደበት ሁሉ የሚከተሉት አጃቢዎቹ ብዙ ነበሩ። ያን ሁሉ የቤተ ክርስቲያን እውቀት (ቅኔ፥ ዜማ፥...ወ.ዘ.ተ...) ችላ ብሎ ወደ ዘመናዊ (ምድራዊ) ትምህርት አተኮረ። እርሱ ሕአፓን ሲመራ በነበረበት ወቅት፥ ፓርቲያችን ከምንጊዜውም የበለጠ ምርር - ክርር ያለ ሆነ። ጭቅጭቁም የበረታው፥ በተለይ የዛን ጊዜ፥ ምድራዊ ስነ አመክንዮ ስለ ገነነ፥ መንፈሳዊነትን የተላበሰ ትእግስት፥ እውቀት እና እምነት ስለጠፋ ይሆናል።

የዛን ጊዜ፥ ብዙዎቻችን የኢትዮጵያችን ማንነት በቤተ ክርስቲያናችንም ውስጥ ተተክሎ እንደቆየ ያላገናዘብንበት ዘመን ነበር። ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን እና

እስከምንጊዜውም ድረስ፥ የኢትዮአጵያችን ማንነቷ ከመንፈሳዊነቷ እንደማይለይ ተረስቶን ነበር። ኢትዮጵያችን ጥንታዊ የጋርዮሽ ስርዓት ከሚባለው ተነስታ፥ የባርያ ስርዓት ወደተባለው ስትገባ፥ የፊውዳል ስርዓት ወደተባለው ስታድግ፥ ዘመናዊ የተባለውንም ካፒታሊዝም ስትቀምስ፥ ምንጊዜም ከርሷ ጋር መንፈሳዊነቷ አልተለያትም ነበር። ይህንን የመሰለ የምድራዊና የመንፈሳዊ ጠባዮቿን ዝምድና ነበር በዘመኑ ያልተረዳነው።

***<u>ታላቁ ውሳጣዊ የፓርቲ ውዝግብ</u>***

ፓርቲው ደርግን እንደ ፋሺስት ሲቆጥረው፥ ሀ እና ለ ደግሞ፥ መኢሶኖችን ተከትለው፥ "ደርግ ፋሺስታዊ ድርጊትን ቢፈጽም፥ ፋሺስታዊ ድርጊትን የሚፈጽም መንግሥት ይባላል እንጂ፥ ፋሺስት አያሰኘውም (ፋሺሽታዊ ቢሆንም ፋሺስት አይደለም)። ደርግ የፊውዶ ካፒታሊስት ስርዓት የፈጠረው (የወለደው) መንግሥት በመሆኑ፥ በጠባዩ በከፍተኛ ደረጃ ከካፒታሊስት ስርዓት እንደሚመነጭ (ጀርመን ሀገር እንደተፈጠረው) ፋሺስት መቆጠር የለበትም። ስለዚህ፥ ደርግን ከፋሺስታዊ ድርጊቶቹ እንዲላቀቅ ማድረግ፥ አብሮ መሥራትም ይቻላል..." ባዮች ነበሩ።

በዚህና በሌሎች ጥቃቅን አስተሳሰቦች ምክንያት፥ ውስጣዊ ቅራኔዎች ተስፋፉ። ለእነርሱ አልታያቸውም ይሆናል እንጂ፥ ከሰፊው ሕዝብ አንጻር፥ በሁለቱም ወገን የሚሰነዘሩ ፍልስፍናዊ አመለካከታቸው ወደ ጸጉር ስንጠቃ ነበር የመራቸው።

ሀ እና ለ "ድርጅታዊ ነጻነታችንን ሳናጣ ከደርግ ጋር መሥራት እንችላለን" በማለት፥ ከዋናው ፓርቲ ተገንጥለው የራሳቸውን እርምጃ መውሰድ ጀመሩ። "ድርጅታዊ ነጻነታችንን ሳናጣ" ሲሉ፥ ባንድ በኩል በአብዮታዊ ጦር ደርግን ስንወጋ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ለሕዝብ የሚጠቅም ሥራን አብረን እየሰራን፥ ለሕዝብ የማይጠቅመውንና የሚጎዳውን ደግሞ ለማሻሻልና ለመለወጥ፥ በጦር ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ እንታገላለን ማለታቸው ነው።

ዋናው የኢሕአፓ ፓርቲ ግን "ጎኑን እየተወጋ በእጆቹ የሚያቅፍ መንግሥት ምን አይነት ሞኝ ቢሆን ነው? ይህስ ለጠላት እጅ ከመስጠት ተለይቶ አይታይም.." በማለት፥ የ ሀ እና ለን አስተሳሰብ አልተቀበለውም።

አንጃዎች (ሀ እና ለ) "ጨካኙ መንግሥት በየቀኑ እንዳይጨርሰን አንድ መከላከያ ዘዴ ማበጀት ይገባናል። እኛም በበኩላችን ረጋ ብለን የጊዜውን ሁኔታና ትግሉን እናቀናጀው እንጂ፥ አባላቱን በየቀኑ ከማያስፈልግ አደጋ ውስጥ እየከተትን የገዛ ኃይላችንን ማዳከም አይገባም" በማለት፥ ቁርጥ ውሳኔ አደረጉ።

ፓርቲው የወደፊቱን ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ሲመለከት፥ እግረ መንገዱ የተኮለኮሉ ጥቃቅን እንቅፋቶችን ለማስወገድ ሚሊታሪ እርምጃዎችን ይወስዳል። አንጃዎች ደግሞ፥ "ያም ቢሆን አላስፈላጊ ግድያዎችንም በመቀነስ መሆን አለበት እንጂ፥ ጊዜ የፈጠረውን የፖለቲካ ልዩነት ተከትሎ፥ ወገኖቻችንን እንደ ውጪ ጠላት እየቆጠሩ እርስ በርስ መገዳደል ጥሩ አይደለም" ባዮች ነበሩ።

አንጃዎች "ይህ እኛ በማካሄድ ላይ ያለነው ትግል፥ አዝማሚያው ወደ ተናጠል ትግል የሚያመራ በመሆኑ፥ ግቡ የግለሰብ ግድያ (putshism) ብቻ ሆኖ ይቀራል እንጂ፥ አብዮታዊ ሆኖ መሠረታዊ ለውጥን አያመጣም። እንዲህ አይነቱ አሠራር እራሳችንን ከማስጨረስ በስተቀር የትም አያደርሰንም። መፈንቅለ መንግሥተኝነትም (coup d'etat - ኩዴታ) የቆምንለት አላማና የመጨረሻ ግባችን ስላልሆነ፥ በተራዘመ ጦርነት (protracted war) ሠፊውን ሕዝብ ለሕዝባዊ ሥልጣን ማዘጋጀት ነው ያለብን። በግለሰብ ግድያ ብቻ የትም መድረስ አለመቻላችንን ብናውቅና፥ ዘላቂ ታክቲክና እስትራተጂ ብንቀይስ ይሻለናል" ብለው መከሩ።

ዋናው ኢሕአፓ አንጃዎችን፥ ከመሠረታዊ አመለካከታቸው በመነሳት፥ ከመኢሶን መደቧቸው። ጥንትም መኢሶኖች ከኢሕአፓ የተለዩት የወታደራዊውን መንግሥት (ደርግን) እንደ ጊዜያዊ መንግሥት ስለተቀበሉት ነበር። በእውነትም አንጃዎች፥ በዚሁ ግልባጭ አስተሳሰባቸው ወደ መኢሶን አዘንብለዋል። የዋናው (ያልተገነጠለው) የኢሕአፓ አቋም ግን "ይህ የወታደሮች መንግሥት በጠባዩ አምባገነን ስለሆነ፥ በራሱ ሥልጣን ጨብጦ ሌላውን ተቃዋሚ ኃይል ያጠፋል እንጂ፥ ሕዝባዊ ተወካዮችን ሁሉ በማቀፍ የሕዝባዊነት ተቋም ሊኖረው አይችልም። ስለዚህ እንደ ጊዜያዊ መንግሥት ልንቀበለው አይገባም። ወቅታዊ ትግላችን ሠፊውን ሕዝብ ለሚያቅፍ ለእውነተኛ ጊዜያዊ ሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት መሆን አለበት። ከዚያ በኋላ የሚፈጠረው መንግሥት ሠፊው ሕዝብ በሚኖረው ንቃትና አብዮታዊ ትግል ይወሰናል" የሚል ነበር። በዚህ መሠረታዊ አመለካከት አንጻር፥ ፓርቲውና ተገንጣዮች (አንጃዎች) ሊስማሙ አልቻሉም።

ኢሕአፓ "ሕዝቡ በጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይደራጅ" ያለው፥ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ እኩል እና ሙሉ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ እንዲኖረውና በነፃነት እንዲነጋገር፥ በዚያውም ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርን ራሱ እንዲለማመድና የገዛ ኑሮውን እራሱ እንዲቀይስ ነበር። ምክንያቱም፥ የሰብአዊ መብት የሆነውን ዴሞክራሲ ዝንተ አለም ሳያገኝ፥ አሁንም እንደታፈነ፥ አዲስ መንግሥት በላዩ ላይ ቢመሠረት፥ ሠፊው ሕዝብ በዝምተኛነቱ ቢቀበለውም፥ ከልቡ ላያምንበት ይችላልና ነው።

ከአንድ የመንግሥት ስርዓት ወደ ሌላ የመንግሥት ስርዓት ሽግግር ሲደረግ፥ በቀጥታ ከውጪ እንደወረደ ማስገባት ሳይሆን፥ የትኛው ነው ለሠፊው የሀገራችን ሕዝብ (ለነጋዴው፥ ለገበሬው፥ ለላብ አደሩ፥ ለተማሪው፥ ለአስተማሪው፥ ለቄሱ፥ ለሼኩ፥ ወ.ዘ.ተ.) የሚስማማ - በሰላም ዘላቂነት የሚኖረው፥ ጤናማ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገትን የሚያመጣ በማለት፥ የሕብረተሰቡን አካል በማሳተፍ ማወያየት ግድ ይላል። ሰፊው የሀገራችን ሕዝብ በሰሻል፥ ፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ሙሉ ተሳታፊ ይሆን ዘንድ አስተማማኝ የሚሆነው፥ በቅድሚያ የዴሞክራሲ መድረኩ ተለቆለት እንደልቡ ሲወያይ እና ለራሱ የሚስማማውን ሁነኛ መንግሥትን ሲመርጥ ነው። የሁሉንም ብሔር ብሔረሰቦችን ታሪክ፥ ልምድ እና ባህል፥ እምነት እና አኗኗር ከግምት ውስጥ በማስገባት፥ እና የሁሉንም ነጻነት በእኩልነት በማስረገጥ፥ ሠፊው ሕዝብ ለራሱ የሚስማማውን የመንግሥት ስርዓት ከመረጠ በኋላ፥ እርስ በርሱ የሚጣላ አይሆንም፤ ይልቅስ በህብረት እየተደጋገፈ አንድነቱን ያጠናክራል እንጂ።

ኢሕአፓ በቅድሚያ "ለጊዜያዊ ሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት" መታገል ያስፈልጋል ያለው፥ የወደፊቱን ዘላቂ መንግሥት ሕዝቡ ራሱ እንዲቀይስ በማሰብ፥ ገና ከጅምሩ ሥልጣን የሕዝብ መሆኑ በግልጥ ታዋቂ ከሆነ በኋላ፥ በሕዝቦች ሁሉ ተሳታፊነት - ካለ አምባገነናዊነት ቀጣዩን "ሕዝባዊ መንግሥት" ለመመሥረት እንዲቻል ለማድረግ ነበር።

ወታደራዊው መንግሥት ራሱን ጊዜያዊ ብሎ ቢጠራም፥ ሕዝቡን ስለማይወክል አምባ ገነን ከመሆን አያመልጥም። ጊዜያዊ ነኝ ቢልም፥ ጊዜያዊ አለመሆኑን ራሱ አሳይቷል።

የኢሕአፓዎች አላማ፥ ተራማጅ ኃይላት ባላቸው ኃይል ሁሉ ተጠቅመው፥ ደርግ (ወታደራዊው መንግሥት) በጉልበቱ የያዘውን ሥልጣን ለሕዝቦች እንዲያስረክብ፤ ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ፥ በእርግጥ ሕዝቦችን ሁሉ የሚወክሉ አባላት አህጉራዊ መንግሥትን በጊዜያዊነት መርተው፥ ለዘለቄታው "ሕዝባዊ መንግሥት" መሠረት እንዲጥሉ ነበር።[10]

ኢሕአፓዎች ለዚህ ቅን አላማ ሲሉ ነበር በሕዝቦች ፊት የተጋረጠውን ወታደር ሥልጣኑን ለሕዝብ እንዲያስረክብ የጠየቁት (የታገሉት)። ይህንን ነው በቁንጽሉ፥ አንጃዎች "መፈንቅለ መንግሥተኝነት" ነው ያሉት።

ግን እዚህ ላይ ለአንባቢ ግልጽ መሆን ያለበት፥ ዋናው ፓርቲ (ያልተገነጠለው) እንዳስቀመጠው አድርገው አልነበረም አንጃዎች የተረጎሙት።

[10] እንግዲህ፥ እኛ (የኢሕአፓ አባላት) ለጊዜው የተረዳነው ይህንን ነበር።

የአንጃዎች እና የመኢሶኖች አመላካከት ተቀራራቢ ቢመስልም፥ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ያላቸው ልዩነት እጅግ የጎላ ነበር። የአንጃዎች ሕዝባዊ መንግሥትና የመኢሶኖች “ሕዝባዊ መንግሥት” በፍልስፍናውና በይዘቱ የተራራቀ ነበር።

መኢሶኖች፥ “እኛ በዚህ ወታደራዊ መንግሥት ውስጥ ገብተን አብረን ከሠራን፥ እንደ “ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት” ይቆጠራል። ቀስ በቀስ እኛው ሕዝቡ ሥልጣን እንዲጨብጥ እናደርገዋለን” ባዮች ነበሩ (ብዙ ቢባልም ከዚህ አባባል አይወጣም)።

የአንጃዎች “ሕዝባዊ መንግሥት” ግን ከዚህ እጅጉን ይለያል። እነርሱ (አንጃዎች) ለሥልጣን ሳይስገበገቡ “ሕዝባዊ መንግሥትን” በቀስታ ለመመሥረት ነበር ሃሳባቸው። እንዲህም ሲሉ አስቀምጠውታል፡-

“እውነተኛ ሕዝባዊ መንግሥት ሥልጣን ላይ ጉብ ካሉ በኋላ አይደለም የሚመጣው፤ ብዙ መስዋእትነትን ይጠይቃል። ምንም ያህል ጊዜ ቢፈጅ፥ ሕዝቡን “ለተራዘመ ጦርነት” (protracted war) አስታጥቆ፥ ሕዝቡ ራሱ በራሱ ሥልጣን እንዲጨብጥ መታገል ይገባል። ይህንንም ለማድረግ፥ ሕዝቡ ዴሞክራሲን እንዲያውቅና፥ እራሱን በራሱ ማስተዳደርን እንዲለማመድ፥ አብዮታችን ቀስ በቀስ ከገጠር ወደ ትናንሽ ከተሞች እየገባ በትጥቅ ትግል አካባቢውን ነፃ ሲያወጣና ሥልጣን እየጨበ፥ እራሱን በራሱ ማስተዳደር ሲጀምር፥ ይህም ክስተት ቀስ ቀስ እያለ ጠቅላላ አገሪቱን ሲያዳርስ፥ የዚያን ጊዜ አሮጌው ስርዓት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይደመሰሳል፤ የዛን ጊዜ ሕዝቡ ራሱ ባስገኘው ድል ሥልጣን ይጨብጣል፤ ያን ጊዜ ነው ሕዝባዊ መንግሥት የሚባለው።”

በዚህ ምልከታ ዋናው ፓርቲ ከአንጃዎች ምልከታ ምንም መሠረታዊ ተቃውሞ አልነበረውም። በሁለቱ መካከል የነበረው ልዩነት የታክቲክ እና እስትራተጂ ልዩነት ነበር። ዋናው ፓርቲ የአንጃዎችን “የሕዝባዊ መንግሥት” አመሠራረት ጉዳይ በቀላሉ አልነበረም የተመለከተው። ስለዚህም፥ እንዲህ ሲል ይጠይቃል፡- “ኢሕአፓ አያሌ ቅስቀሳዎችን ከከተማ እስከ ገጠሩ ድረስ በሚያካሄድበት ወቅት፥ በአንፃሩም የደርግ መንግሥት ሕዝቡን አፍኖ ሲይዝ፥ በእርግጥ የኢሕአፓ ቅስቀሳና የወቅቱ ሁኔታ ሕዝቡን አላነቃውም ወይ? ለተሻለ ለውጥ አላዘጋጀውም ወይ? ለጥቂት ጊዜ በዚሁ ቢቀጥል የግድ የተራዘመ ጦርነት ያስፈልገዋል ወይ?”

አንጃዎች አሁንም ፍርጥም ብለው፥ “ምንም ያህል ጊዜ ቢፈጅ፥ ሕዝቡን በቻይና የተካሄደውን አይነት ለተራዘመ ጦርነት (protracted war) አስታጥቆ ሕዝቡ ራሱ በራሱ ሥልጣን እንዲጭብጥ ማድረግ ያስፈልጋል” በማለት ወገን ለይተዋል።

ሁለቱ (ፓርቲውና አንጃዎች) የትግሉን ሚዛን በደንብ ያወቁት አይመስሉም። ይልቁንም አንጃዎች፥ ዛሬም ሆነ ለወደፊት፥ እኛ ከቻይና የተለየን ሕዝቦች መሆናችንን፥ ባሁኑ ጊዜ የሕዝባችንም ንቃተ ሕሊና ከዚያ አልፎ እንደሄደ የተገነዘቡ አልመሰሉም። ይህንን ስንል፥ የሁለቱም (ፓርቲው እና አንጃ) የመጨረሻ አላማ አንድ አይነት (ሕዝባዊ መንግሥትን መመሥረት) ሆኖ ሳለ፥ በእርግጥ በሥራ ላይ ቢውል፥ ከሁሉቱ የማንኛቸው የተሳካ እንደሚሆን ማወቅ (መተንበይ) አይቻልም።

መኢሶኖች ከአንጃዎች ጋር የሚስማሙት ከደርግ ጋር መሥራት ይቻላል በሚል ሃሳብ ነው እንጂ፥ የመጨረሻ ግባቸው የተለያየ ነበር። መኢሶኖች ኢሕአፓዎች (ያልተገነጠሉት) የሚሉትን ቀበል ያደርጉና፥ ተቃራኒውን በማስተጋባት፥ ይልቅስ "በጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" የሕዝቦች መደራጀት ከቀጠለ፥ ካለ "የተራዘመ ጦርነት" ሕዝባዊ መንግሥትን መመሥረት ይቻላል ይላሉ። ይህንን ሲሉ ግን፥ ደርግን እንደ ጊዜያዊ መንግሥት በመቁጠር ነው (የእነርሱን ከደርግ ጋር መሥራት ደርግን እንደ ጊዜያዊ መንግሥት የሚያስቆጥረው ያስመስሉታል)። እህ! ታላቅ የፖለቲካ ቀውስ።

*ይገርማል! ሁሉም (ኢሕአፓ እና አንጃው፥ መኢሶኖችም) የታገሉት ለአንድ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ መንግሥት ነበር።*

አንጃዎች ከተጠቀሰው መሠረታዊ የፖለቲካ መነሻቸው ተነስተው ዋናውን የኢሕአፓን ፓርቲ ጊዜያዊ አቋም ሲተቹ፥ ፓርቲው ከጊዜ ወደጊዜ በግትርነት እየተንገታገተ፥ በራሱና በሕዝቡ ላይ አላስፈላጊ ጥፋቶችን ማስከተሉን በመመልከት ነበር።

የፓርቲው ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ደርግን በቶሎ መደምሰስን ይጠይቃል። ደርግ ደግሞ ከመኢሶኖችና ከሌሎችም ጋር አብሮ ቶሎ የማይደመሰስ ሆነ። "ታዲያ በመሃል ወጣቱ ይለቅ ወይ?" ባዮች ነበሩ አንጃዎች። ከዚህም በመነሳት ነበር ፓርቲው ቆም ብሎ እንዲያስብ የጠየቁት። ከዚህም የተነሳ ነበር "የሕዝባዊ መንግሥትን" አመሠራረት (በተራዘመ ጦርነት፥ ከገጠር ወደከተማ) የተለሙት። አንጃዎች "በቃ! በቃን! ከከተማ እንውጣ፤ ወደ ገጠር እንሂድ፤ በአላስፈላጊ ግድያ ወጣቱን አናስጨርስ" በሚለው ሃሳብ ሳቢያ ኢሕአፓን የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ከተቱት (ሁለቱም የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ገቡ)።

ባጭሩ፥ የፓርቲው ዋነኛ ትግል ደርግን መደምሰስና "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥትን" በመመሥረት ላይ ያተኮረ ሲሆን፥ የአንጃዎች ዋነኛ ትግል ደግሞ ከላይ ለተጠቀሰው "የተራዘመ ጦርነት" ብሎም ለመጨረሺያው "ሕዝባዊ መንግሥት" ነበር።

ከወቅታዊ ችግሮች ባሻገር፥ ዋናው ፓርቲ እና አንጃዎች ወደፊት ለመራመድ ቀናውን መንገድ ሲሹ፥ በእስትራተጂና ታክቲክ ትንተና ተለያዩ እንጂ፥ መሠረታዊ ርዕዮተ አለማቸው አንድ አይነት ነበር። በሁለቱ መካከል ሲካሄድ በቆየ ንትርክ ምክንያት፥ የፓርቲው (የአንጃ ተከታዮችንም ጨምሮ) መሠረት የሆነው የአባላት መንፈስ ተበረዘ። ከሁለቱም አቅጣጫ በሚሰነዘሩ ሠፊና ጥልቅ በሆነው የፖለቲካ ትንተናቸው ምክንያት፥ የፓርቲው አባላት ሁሉ የፓርቲውን አቋም አጠያያቂ አደረጉት (ጥርጣሬ ውስጥ ከተተን)። ታላቅ የፖለቲካ ቀውስ ተከሰተ።

ፓርቲው በመጣላት ፋንታ መስማማትን የሚፈልግ ቢሆን ኖሮ፥ እንደምንም ብሎ አንጃዎችንና ተከታዮቻቸውን ከጉያው ባያስወጣ ኖሮ፥ ያ ኢሕአፓ የተባለ ታላቅ ኃይል እስከ ዛሬ ባልጠፋ ነበር። ግን ማን የሁለቱን እውነት ያስታርቅ?

"በደብተራው" የሚመራው ዋናው ኢሕአፓ፥ "ትግል ካልመረረ፥ ካልከረረ፥ ምኑን ትግል ሆነ?" በሚል መርሆ መሠረት፥ ከቀድሞው አቋሙ ትንሽም ፈቀቅ (ፍንክች) የማይል ሆነና፥ በአንጃዎች ላይ ተቃውሞውን በማስተጋባት፥ የራሱን የማያወላዳ አመለካከቱን አጠናከረ። በፓርቲውና በአንጃዎች መካከል የተፈጠረው ጭቅጭቅ በጣም ተካረረ።

ፓርቲው ተገንጣዮችን በማቀፍ አብሮ መሥራት ስላልቻለ፥ ሀ እና ለን በአንጃ ፈጣሪነት ከፓርቲው አስወገዳቸው። ሀ እና ለ ግን በውስጣዊ ትግል የፓርቲውን አመለካከት ለውጠው፥ አብሮ መዝለቅ (አብሮ መታገል) የሚቻላቸው መስሏቸው እንደነበር ካቀረቡት ዘገባ መረዳት ይቻል ነበር፤ ግን ይህ አልሆነም። አለመሆኑ ሲገባቸው ይሆናል፤ አንጃዎችም አመረሩ። ከዋናው አብዮታዊ ትግል ይልቅ የእርስ በርስ ትግሉ ላይ አተኮሩ።

እንዲህ ከሁለት በተከፈለው የውስጥ ፓርቲ ጭቅጭቅ የተነሳ፥ ሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚጎዳ ባለማሰብ፥ አንዱ ሌላውን በጠላትነት መውጋትን መረጠ። "አብዮታችንም ከገጠር ወደ ከተማ እንጂ፥ ከከተማ ወደ ገጠር መሄድ የለበትም" በማለት አንጃዎች ለተራዘመ ጦርነት በበኩላቸው ሲዘጋጁ፥ የፓርቲውን የጦር ክፍል መደበኛ ሥራውን እንዳይሠራ ያሰናከሉት ጀመር[11]።

ይህ በዚህ እንዳለ፥ የሱማሌ ጦርነት ተጀመረ። ፓርቲው በሱማሌ ጦርነት ጉዳይ ላይ፥ "ሁለቱም ፋሺስቶች ስለሆኑ፥ ሁለቱንም እንዋጋለን" የሚል፥ ለአባላቱ ግልጽ ያልሆነ መመሪያ አወጣ። አሁንም ፓርቲው በመሠረታዊ አቋሙ ላይ የጸና በመሆኑ፥ ሁለቱም ፋሺስቶች ናቸው አለ እንጂ፥ የሱማሌን ጦር የመደገፍ ዝንባሌ

[11] የዛን ጊዜ "ሀ" ተብሎ የሚጠራው የአንጃ መሪ ነበር የጦር ክፍሉ ኃላፊ።

አልነበረውም። ሁለቱም ፋሺስቶች ናቸው ሲል ደግሞ፥ ሁለቱም የሕዝቦች ጠላቶች መሆናቸውንና፥ ገና ለገና የውጪ ጠላት መጣብን በማለት ስንደናገጥ፥ የቆምንለትን ትግል እንዳንረሳ በማሰብ ነበር እንጂ፥ ሀገር ሊወር ከመጣ ጠላት ጋር እናብር ማለቱ አልነበረም።

የዚህ የቆምንለት ትግል አላማ፥ በሕዝቦች የተቀነባበረ ሕዝባዊ አመጽ (በገጠር እንዲሁም በከተማ) ይህንን ፋሺስታዊ መንግሥት ገርስሶ፥ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት መመሥረት ስለሆነ፥ ጓዶች በግርግር የቆሙለትን አላማ ስተው እንዳይወናበዱ፥ የኢሕአፓ የበላይ አካላት መልእክታቸውን ለበታች አካላት አስተላልፈዋል።

ነገር ግን ከፉ ወሬን ለሚበትን እርኩስ መንፈስ ትንሿ ቀዳዳ ትበቃለችና፤ ሀ እና ለ "የውጪ ጠላት ሀገርን ሲወር እንዴት ዝም ይባላል?" በማለትና ነገር በማጋነን ኢሕአፓን ማስጠላት ጀመሩ። "ይልቅስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት እንዲህ በተደፈረበት በአሁኑ ወቅት ከማንም ጋር ያለንን ልዩነት ትተን ሀገራችንን ከወራሪ ጠላት መከላከል ይገባናል እንጂ፥ ገለልተኛ አቋም መውሰድ ተገቢ ነውን?" በማለት ኢሕአፓን የኢትዮጵያ ጠላት አስመስለው፥ እነርሱ በሱማሌ ጦርነት ላይ የያዙትን ጥርት ያለ አቋም አስተጋቡ።

መቼም አንጃዎች ነገሮችን ሲያብራሩ የጊዜውን ሁኔታ እያስታከኩ ስለሆነ፥ የኢሕአፓን ደካማ ጎኖች ተጠቀሙበት። ነገር በማጋነን፥ የራሳቸውንም አቋም ግልጥልጥ አድርገው ስለነበር፥ እነርሱን የሚሰሙ በረከቱ። አንጃዎች በጎን ፓርቲውን የኢትዮጵያ ጠላት የማስመሰል ፕሮፓጋንዳቸውን ቀጠሉ፤ በመጠኑም ቢሆን ተሳክቶላቸዋል።

የኢሕአፓን ጥልቅ ፍልስፍና መረዳት ቀላል አልነበረም። እስከዛሬ ድረስ በፓርቲው ላይ ትችት የበረከተው፤ ጥልቅ ፍልስፍናውን ባለመረዳት ነበር። ይልቁንም በፓርቲው ውስጥ ምንም ተሳትፎ ያልነበራቸውና በውስጥ ትግል የነበረውን ልዩነት ያልደረሱበት (ያላወቁ) ጥራዝ ነጠቆች፥ ከልብ የደከሙላትን - የደሙላትን - የሞቱላትን ጀግኖች እያጥላሉ፥ ሕአፓዎችን ልክ እንደ ሀገር ጠላት - አናርኪስት መቁጠራቸው እጅጉን የሚያስተዛዝብ፥ የሚያሳዝን ሆኗል።

"ሁሉም በበኩሉ"፥ ለሥልጣን ሲሽቀዳደም (???)፥ "ሁሉም" የኢትዮጵያን አብዮት መልክ አሳጥተውታል። *[ምናልባት ባልተገነጠለው በኢሕአፓ አመራር ላይ ያሉቱ፥ የመንግሥት ኃይል ከሱማሌ ጋር በሚደረግ ጦርነት ሲዳከም፥ ኢሕአሠ የበላይነት ያገኛል ብለው አስበውም ይሆናል።]* ያም ቢሆን፥ ሀገር ሲወረር፥ የሀገር

ፍቅር እና አብዮት የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ግልጽ አለማድረጉና ጥርት ያለ አቋም አለመውሰዱ፥ በብዙዎቻችን ፖለቲካዊ ምልከታ ላይ ብዥታን ፈጥሯል።

በተፈጠረው የውስጥ ትግል ምክንያት፥ በፓርቲው ውስጥ የተከሰተ የአመለካከት ልዩነት የአባላቱን የትግል መንፈስ አዳከመው፤ የትኩስ አብዮታዊ አባላትን ተስፋ አጣመመው፤ ቀና አስተሳሰባቸውን መረዘው፤ ርዕዮተ አለማቸውን አጨለመው፤ ስሜታቸውን ሁሉ በጠበጠው፤ ሃሞታቸውንም አፈሰሰው። በዚሁ ልዩነት ምክንያት ብቻ የፓርቲውን ሥራ በትክክል መሥራት፤ ከበላይ አካል የሚመጣውንም ወደታች ማስተላለፍ አስቸገረ።

ኢሕአፓ የራሱን እውነት ሲያስተጋባ ከሌላውም እውነት ጋር በማዋሃድ መሆን ነበረበት። እኛ ኢትዮጵያኖች ለኢትዮጵያችን ስንታገል፥ ጠላት ከውጪ መጥቶ ሀገራችንን ሲወር ቅድሚያ መስጠት ያለብን ጠላትን መዋጋት ነበር። ኢሕአፓ ግን ሁለቱም ኢምፔሪያሊስቶች ስለሆኑ ሁለቱንም መዋጋት አለብን አለ።

ከሱማሌ ጦርነት በኋላ አንጃዎች (ከመኢሶኖች እና ከሌሎችም የኢሕአፓ ጠላቶች ጋር) የፓርቲ አባላትን ለመንግሥት እያጋለጡ ማስጨረስ ጀመሩ። አንጃዎች በመንግሥት ከፍተኛ ሥፍራ እየተሰጣቸው ከደርግ ጋር እጅና ጓንት ሆኑ። የፓርቲውን የአሰራር መዋቅር (እስትረክቸር)፥ በውስጡ የተካተቱትንም አባላት የስም ዝርዝር አሳልፈው ሰጡ። በየከፍተኛውና በየቀበሌው በመሠማራት አባላትን በየስማቸው እየጠሩ አሳሰሩ፤ አስገደሉ። አዬ! ተቻችሎ፥ አብሮ መዝለቅ ሲቻል!

## <u>የኢሕአፓ መዳከም እና የአባላቱ መሳደድ</u>

አንጃዎች በተፈጠሩ በጥቂት ወራት ውስጥ፥ በዋነኛነት ሲታገል የነበረው የኢሕአፓ ኃይል እጅጉን ተዳከመ፤ የመንግሥት ኃይልም ከአባሪ ኃይላት ጋር እጅጉን ተጠናከረ። በመንግሥት ካድሬዎችና በአንጃዎች እገዛ፥ በየቀበሌው የኢሕአፓ ተከታዮች የሆኑትን ሁሉ ማሰር ተጀመረ።

የፓርቲው መሠረታዊ ተቋም ባልተነካበት ወቅት፥ እኔ ከዴሞክራሲያዊ ግንባር አባላት ጋር እንድሠራ ታዝዤ ነበር። የዴሞክራሲያዊ ግንባር ዋና አላማ፥ ዴሞክራሲያዊ ዝንባሌ ያለው ሠፊው ሕዝብ ለሕዝባዊ አመጽ በሚነሳበት ወቅት (መብትና ፍትህ ማጣት፥ መታሰርና መገደል ሲበዛበት፥ ሲመረውና ሲቸግረው መነሳቱ ስለማይቀር)፥ የትግሉ አቅጣጫ አንድ ወጥ እንዲሆን፥ ያንን በቋፍ ላይ ያለውን ፋሺስታዊውን የደርግ መንግሥት ለመጣል በሚያስችል መንገድ ትግሉን ማቀነባበርና መምራት ነበር። ይህንን የፓርቲውን አላማ ወደ ሠፊው ሕዝብ ሰርጎ እንዲገባ

ለማድረግ ነበር፥ አንዳንድ የፓርቲው አባላት በየዴሞክራሲያዊ ግንባሮች እንድንገባ የተደረገው።

በአንጃዎች እርዳታ የፓርቲው መዋቅር በመንግሥት እጅ ገባ። የወጣቶች ክንፍና የዴሞክራሲያዊ ግንባር በቅድሚያ ተመታ። እኔም በዛን ወቅት በዴሞክራሲያዊ ግንባር ተሳትፎ ስለነበር፥ ቀበሌዎች ከቤቴ መጥተው እንደሚወስዱኝ እርግጠኛ ነበርኩና፥ ሌላ ክፉ ነገር ሳይመጣ ተዘጋጅቼ ጠበቁኋቸው።

ከቀበሌአችን ሊቀመንበር ጋር አልፎ አልፎ ከአንድ ቢራና አረቄ መቃመሺያ ቤት ስለምንገናኝ በተለይ የኔ "ጸረ አብዮተኛ" ሆኖ መገኘት እጅጉን አስገርሞት፥ አስቆጥቶትም ስለነበረ፥ ከአጃቢ የቀበሌ ዘበኞች ጋር ሆኖ ወደ ቤቴ እየገሰገሰ መጣ። እኔም ከቤቴ የተደበቀ ሌላ የፓርቲ አባል ስለነበረ፥ ትኩረታቸው በእኔ ላይ እንዲሆን እንጂ፥ ወደ ጓዳ እንዳይገቡ ስለነበር፥ በሩን ሲያንኳኩ ቶሎ ብዬ ከፈትኩላቸው።

ልክ በሩ ሲከፈትና ከቀበሌው ሊቀ መንበር ፊት ድቅን ስል፥ በዛ ደንዳና መዳፉ አንዴ ፊቴን ሲመርግብኝ ከአንድ የአብዮት ጠባቂ ላይ ወደቅሁ። "በሉ ውሰዱት!" ብሎ አዘዘ። እያዳፉ ወስደው ከቀበሌው እስር ቤት፥ ከኔ በእድሜ ከሚያናንሱ ወጣቶች ጋር ደባለቁኝና ከዚያ ሰነበትኩ።

## <u>የመሥሪያ ቤታችን ካድሬዎች የፈጸሙት የቂም በቀል እርምጃ</u>

ከእለታት በአንድ ቀን፥ የታሰርኩበት የቀበሌው ዋነኛ ካድሬ፥ ከእስረኞቹ መካከል እኔን ብቻ ነጥሎ አወጣኝ። "ና! ለከባድ ጉዳይ ትፈለጋለህ" ብሎ፥ ከቢሮው አስገባኝ። እኔም "የፓርቲ አባል መሆኔ ስለተነቃብኝ ሊገለኝ መሆን አለበት" በማለት፥ እራሴን ለሞት ማዘጋጀት ጀመርኩ። ወዲያውም ለካድሬዎች ብቻ የተዘጋጀ ጃኬት አምጥቶ "በል ይሄንን ልበስ" አለኝ። እኔም ለተጠየቅሁት ሁሉ ተባባሪ በመምሰል "እሺ" አልኩና ጃኬቱን ለብሼ እሱኑ መሰልኩለት።

በዛን ወቅት፥ "ጭቁን የመንግሥት ሠራተኞች" የተሰኙ፥ በየመሥሪያ ቤቱ በዝቅተኛ ደምወዝ የተቀጠሩ (ተላላኪዎችና ዝቅተኛ የቢሮ ሠራተኞች)፥ ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን ካላቸውም ጋር ሆነው የሶሻሊስት የፖለቲካ ትምህርት እንዲሰጣቸው ተደርጎ ነበር። ከእነኚህም መካከል፥ በአብዮታዊ ካድሬነት ለተመረቁት "ለአብዮት መከላከያ - መጠበቂያ" እየተባለ፥ ሽጉጥ ይሰጣቸው ነበር። እነርሱም ከተቀጠሩበት ከየመሥሪያ ቤታቸው ሲመለሱ፥ ሽጉጥ ታጥቀው "እኛስ ለአብዮታችን ምን እናድርግ? እንዴትስ በመንግሥታችንና በሀገራችን የተነሳውን ጠላት እንከላከል?.." በማለት ለመንግሥት ተቆርቋሪነታቸውን ለመግለጽ የሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ነበር። እኔ ከምሠራበት መሥሪያ ቤትም እንዲሁ ሲደነፉ፥ በሠራተኛው ላይ

አላስፈላጊ ሁከት እና ሽብር ሲፈጥሩ ነበር። ከነኚህ መካከል፥ የፖለቲካ ትምህርት ከመሄዳቸው በፊት፥ የጥቂቶቹ ትኩረት በሀገሪቷ ፖለቲካ ሳይሆን፥ በተጣሏቸው፥ ወይንም በማይወዷቸው ላይ ስለነበር፡- "ቆይ ካድሬ ሆኜ ስመለስ፥ የማደርገውን ታያለህ/ታያለሽ" በማለት፥ በቂም በቀል ሊያሳስሯቸው ተዘጋጅተዋል።

የቀበሌው ካድሬ "በል ተዘጋጅ፤ ዛሬ አንተ ወደምትሠራበት ወደ መሥሪያ ቤትህ ሄደን ጸረ አብዮተኞችን ሁሉ እንለቅማቸዋለን፤ እየፈነቃቀልን እናወጣቸዋለን" አለኝ። ምን ማለቱ እንደሆነ አልገባኝም። ከውጪ ወደተዘጋጀልን መኪና ገባንና ወደ መሥሪያ ቤቴ አመራን። ልክ እንደ ደረስን የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ሁሉ በግዳጅ ከውጪ ከባንዲራ መስቀያው ሥፍራ - ከሜዳው ላይ ቆመው እኛን ይጠባበቃሉ።

እኛ ከመምጣታችን በፊት ግን፥ እነኛ "ጭቁን የመንግሥት ሠራተኞች" የጊዜው ካድሬዎች፥ "ጸረ አብዮተኞች" ያሏቸውን ሁሉ ለብቻ ለይተው ወደ እስር እንዲጓዙ ወስነውባቸዋል። እንግዲህ የኔ ከዚያ ሥፍራ መገኘት፡- አንድም "ጭቁን የመንግሥት ሠራተኞች" ለይተው ያወጧቸውን "ጸረ አብዮተኞች" የተባሉትን በኢሕአፓ በኩል ያላቸውን ተሳትፎ እንዳረጋግጥላቸው ሲሆን፥ በተለይ ያልተጠቆመባቸው የኢሕአፓ አባላት ካሉ ደግሞ፥ ወዲያውኑ እየጠቆምኩ እንዳወጣ ነበር። ይህንን ጉዳይ ለማጠናከር ሲል የቀበሌው ሊቀመንበር በጣም ይገፋፋኝ ጀመር። "ሲጋራ ልስጥህ? ሽጉጥ መታጠቅ ፈለግህ? በል ቀኑ ሳይመሽ በቶሎ አውጣ" ይለኛል።

በኔ መሥሪያ ቤት ውስጥ በወጣት ክንፍ እንዲሁም በፓርቲው የታቀፉ ብዙዎች ነበሩ። ግን በዚያን ወቅት የታሰርኩት እኔ ብቻ ነበርኩ። በፓርቲ ሕዋስ በመታቀፍ ላይ ያሉትን እና በሌሎችም መዋቅሮች ውስጥ ከፓርቲው ጋር ንክኪ የነበራቸውን ከሞላ ጎደል ሁሉንም አውቃቸዋለሁ። ከሩቅ ቆሜ ሳያቸው "ካሁን ካሁን ያጋልጠናል" እያሉ የፈሩም ይኖራሉ። እንዳው መተያየት ብቻ ሆነ። የፓርቲያችን አሠራር የረቀቀ ስለነበር፥ በፖለቲካ ካድሬነት የተመረቁ ጭቁን የመንግሥት ሠራተኞች ኢሕአፓዎችን ጠቁመው ለማውጣት የሚያስችል ብቃት ስላልነበራቸው፥ እነርሱ ከፓርቲው ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው የሚችሉትን ግለሰቦች አጋልጠው ለማውጣት አይችሉም። ካድሬ በመባላቸውም ብቻ በሠራተኛው ላይ ያላቸውን ሥልጣን በማሳየትና በማስፈራራት፥ ተጣልተዋቸው የነበሩትን ሁሉ "ጸረ አብዮተኞች" እያሉ፥ በቂም በቀል ያንገላቷቸዋል።

የቀበሌው ካድሬ "በል እንጂ፥ መሸብን እኮ! አታወጣም እንዴ?" አለኝ በቁጣ፥ እንደማስፈራራትም ብሎ። እኔም "ምንድነው የማወጣው?" አልኩት። "አሁን ከዚህ ሁሉ ሕዝብ መካከል የኢሕአፓ አባል ይጠፋል? በል ጠቁም፤ አለዚያ

ትቀምሳታለህ..” ብሎ በድጋሜ አስፈራራኝ፡፡ እኔም ፍርጥም ብዬ “ከዚህ ሁሉ ሕዝብ መካከል የኢሕአፓ አባል ይጠፋል ማለት እንዴት ይቻለኛል? ነገር ግን አንተም እንደምታውቀው፥ በቀበሌ ተጠቁሞብኝ ነው የታሰርኩት፡፡ በዴሞክራሲያዊ ግንባር ተሳታፊነቴ ተይዤ ታሰርኩ፡፡ የማውቀውን ሁሉ በዚያ ተናግሬአለሁ፡፡ ከመሥሪያ ቤቴ ሠራተኞች ጋር ንኪኪ ቢኖረኝ ኖሮ እጠቁምልህ ነበር፡፡ እኔ ከዚህ በላይ ምንም የማውቀው ነገር የለኝም” በማለት ስናገር የአመነኝ ይመስለኛል፡፡

እነኛም ከጭቁን የመንግሥት ሠራተኛነት ወደ ካድሬነት የተሸጋገሩ አዳዲስ ፖለቲከኞች ከኛ ለመስማት እየተጣደፉ ቀረቡን፡፡ የቀበሌአችንም ካድሬ ቆጣ ብሎ “በሉ የተጠቆሙትን አምጧቸው!..” አለ፡፡ እነርሱኑ አምጥተው ሦስቱን እኔ ካለሁበት መኪና ከኋላ አስገቧቸው፡፡ ሌሎቹ ሁለቱ በሌላ መኪና ገቡ፡፡ ሁሉንም በደንብ ስለማውቃቸው፥ አንዳቸውም በኢሕአፓ ውስጥ እንዳልሠሩ እርግጠኛ ነበርኩ፡፡

እኔ ካለሁበት የገቡት ሦስት ሴቶች ልክ እንደገቡ፥ ሁሉም፥ ልክ ዘመድ እንደሞተባቸው ማልቀስ ጀመሩ፡፡ ሁለቱ ይንሰቀሰቃሉ፥ አንደኛዋ “አሁን ምን ባጠፋሁ፥ ምንስ ስሠራ ተገኘቼ! እያለች” በፍርኃት ትንቦቀቦቃለች፡፡ ካድሬውም ቆጣ ብሎ “ዝም በሉ፤ የሠራችሁትን መቼ አጣችሁት?” ይላል፡፡

ካድሬው ወደኔ ፊቱን ዞር አደረገ፤ እኔና እርሱን እንደ አንድ የፖለቲካ መሥመር ተከታዮች በማስመሰል፡፡ ቀስ ብሎም “እንግዲህ እነኚህ ናቸው በኢሕአፓ ተሳትፈዋል የተባሉት፡፡ ስለነኚህስ ምን የምታውቀው አለህ?” አለኝ፡፡ እኔም “በእውነት ስለእውነት እኔ እነኚህን የማውቀው በመሥሪያ ቤት በሥራ ጉዳይ ብቻ ነው እንጂ፥ ከዛ ውጪ የሚሠሩትን አላውቅም” አልኩት፡፡ “እሺ አንተ አታውቅም፡፡ ግን የሚያዋጣቸው በቶሎ ቢያጋልጡ መሆኑን፥ አለዚያ የሚያስከተለውን ፍዳ አብራርተህ ንገራቸው” አለኝ፡፡ እኔም “እሺ” አልኩና፥ ወደ ኋላ ዞር ብዬ፥ ማባበል ጀመርኩ፡፡

“እንግዲህ የሚያዋጣችሁን ስነግራችሁ በደንብ ስሙኝ፡- እኔ በቀበሌ ተጠቁሞብኝ በተሳታፊነቴ በሠራሁት ታሠርኩ፡፡ የሠራሁትንም ሁሉ ተናገርኩ፡፡ እኔ ከእናንት ጋር ከመሥሪያ ቤት ሥራ ውጪ ምንም ግንኙነት ስለሌለኝ፥ እናንተ በኢሕአፓ የሠራችሁትን ያልሰራችሁትን ላውቅ አልችልም፡፡ እስቲ እናንተስ ብትሆኑ፥ ከእኔ ጋር ምን የሠራችሁት ነገር አለ? እናንተ የሠራችሁትን ሁሉ ተናገሩ፡፡ ከማን ጋር ምን እንደሠራችሁ እውነቱን ብቻ ተናገሩ፡፡ የሠራችሁትን ሁሉ እንደ እኔ ምንም ሳትደብቁ ብትናገሩ፤ ምንም አትሆኑም፡፡ ምንም ካልሠራችሁ “ምንም አልሠራንም” በሉ፤ ነገር ግን፥ ዋ! ገና ለገና እንለቀቃለን ብላችሁ የማታውቁትን ሁሉ ብትቀባጥሩ ወዮላችሁ፤ መገረፍ ብቻ አይደለም፤ ከዛው ከስር ቤት ትማቅቃላችሁ፤ ዋ! ሞትም

ሊከተል ይችላል" በማለት ፍርጥም ብዬ መከርኳቸው። እነርሱም በጥሞና ሰሙኝና ትንሽ ተረጋጉ።

ከቀበሌው እስር ቤት ደረስን፤ ካድሬው ሁሉንም ወዲያው ወደቢሮው እየወሰደ አነጋገራቸው። በኢሕአፓ ምንም ተሳትፎ ስላልተገኘባቸው ከጥቂት ቀናት በኋላ ተለቀቁ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ የዋናው ፓርቲ መዋቅር አልተመታም ነበር።

## *የፓርቲያችን መዋቅር መመታት*

የመንግሥት ኃይል እጅጉን አይሎ፥ ጭካኔዎችም በዛው ልክ ስለነበርና፥ በከተማው ውስጥ እንደልብ መንቀሳቀስ ስላስቸገረ፥ ሁሉም ራሱን ለማዳን ነበር የሚሯሯጠው። የፓርቲ አባላት ከተያዙ ወዲያው ይገደላሉ።

በየከተማው የነበሩ የኢሕአፓ የጦር ክፍል አባሎች በክላሺን ጠብ መንጃያ እየተጠቀጠቁ ረገፉ (እነርሱም አርግፈዋል)። ሌሎችም ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርጉ በመትረየስ ተረፈረፉ። ይህ በጠቅላላ ኢትዮጵያ የተፈጸመ ግፍ ሲሆን፥ በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ በአንድ ሳምንት ውስጥ፥ ከሁለት ሺህ የሚበልጡ ወጣቶች የተገደሉበት ጊዜም ነበር።[12]

በዚሁ የቀበሌ እስር ቤት ሁለት ወር ሊሞላኝ ሲል፥ እንደኔ የተጋለጡበትን ብቻ ተናግረው፥ ያላጋለጡትን ደብቀው የተደበቁ፥ በከፍተኛ ደረጃ የተሳተፉ የኢሕአፓ አባላት መኖራቸውን ተጠራጠርኩ። ቀስ ቀስ እያልኩ፥ ፊታቸው ላይ ጭንቀት የሚታይባቸውን እየለየሁ ወሬ መልቀም ጀመርኩ። ከነኚህ ተጨናቂዎች መካከል አንዱ ቀስ ብሎ ሹክ አለልኝ። እዛው እስር ቤት እንዳለሁና ለመፈታት ጥቂት ቀን ሲቀረኝ፥ ሌሎች ከኔ ጋር ይሠሩ የነበሩ የዋናው ፓርቲ አባላት ሌላ ቀበሌ መታሠራቸውን በድብቅ ነገረኝ።

ከእስር ቤት ሳልወጣ ይህ በከፍተኛ ደረጃ የተሳተፍኩበትን አለማጋለጤ ቢታወቅ የሚገድሉኝ ስለሆነ፥ ባጋልጥም መገደሌ ስለማይቀር፥ በውስጣዊ ፍርኃትና ጭንቀት ተጠመድኩ።

ተመስገን። ምንም ሳልጠረጠርና እንዳጋልጥም ሳልጠየቅ በሁለት ወር እስር ብቻ ተገላገልኩ። በዚያን ወራት ውስጥ የመታሰር ጽዋ ያልደረሳቸው የዋናው ፓርቲ አባላት በከተማም ሆነ በገጠር ድምጻቸውን በማጥፋት፥ ፓርቲውን እንደገና ለማደራጀት ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉበት ወቅት ነበር።

---

[12] ይህ ቁጥር የዚህ መጽሐፍ ደራሲ በግሉ አስልቶ ያገኘው ነው።

ከእስር ቤት ከተፈታሁ በኋላ መሄጃ አጣሁ። ተመልሼ ቀበሌ ብቀመጥ ይይዙኛል፤ ይዘውም ይገድሉኛል ብዬ መደበቅ ጀመርኩ። ተደብቄም ሁለት ሃሳቦች በጭንቅላቴ ይመላለሱ ጀመር። የኸውም፡- አብረውኝ ይሠሩ ከነበሩትና ከታሰሩት ጋር ሌላ እስር ቤት መቀላቀልና እንደነርሱው ኃጢአቴን ተናዝዤ መቆየት፤ የሚከተለኝንም የመዳን ወይም የሞት ጽዋ መጠባበቅ። ሌላውም አማራጭ፡- የጀመርኩትን አብዮት ዳር ማድረስ ስለሆነ፥ እንደገና ለመደራጀት ከፍተኛ ጥረት ከሚያደርጉ ጓዶች ጋር በመሆን፥ ለአዲስ ትግል መዘጋጀት።

ከእስር ቤት ወጥቼ ትንሽ ቀናት እንደቆየሁ፥ የፓርቲ ኮሚቴአችን አገናኝ (የበላይ አካል) ስለእኔ በሌላ የፓርቲው መዋቅር (የስነ ጽሑፍ ኮሚቴ) ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ስለመሳተፌ እንደተናገረ በድብቅ ሰማሁ። ደግነቱ ይህ ግለሰብ የፓርቲ መጠሪያ ስሜን እንጂ፥ እውነተኛ ስሜን አያውቅም ነበር። ግለሰቡ አቅመ ደካማ ስለነበር በቅጥቀጣ ብዛት ሞተ (አዝናለሁ)።

ከኔ ጋር ለጥቂት ቀናት በስነ ጽሑፍ ኮሚቴ ውስጥ የሠራች፥ ከዚሁ ግለሰብ በላይ የRC (Regional Comitee) አባል የነበረችዋን፥ ሊይዟት ሲሉ የራሷን ሕይወት በገዛ ራሷ አጠፋች። ይህቺ ሴት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ጥሩ ሥራ የነበራት፥ ከቁንጅናዋ ጋር ፈገግታ የማይለያት፤ በህቡዕ በመታገል ብዙ ያገለገለች ምሁር ነበረች። ገና ከአፈጣጠሯ፥ ለአብዮት የተሰጠች ይመስል፥ ልክ እንደ ደናግል (መነኩሴ) ሕይወቷን በአንድ አቅጣጫ ብቻ መርታዋለች።

እኔስ ለጠላት እጄን አልሰጥም በማለት፥ ለጓዶቿ ያላትን ፍቅር ለየት ባለ መንገድ አሳየችን። አንዳንዶች ግን፥ “አይ ይህች ሴት! ከኢሕአፓ ውጪ ሌላ ሕይወት መኖሩን አላውቀች!” ይሉ ይሆናል። ለእርሷ ግን፥ ከሕይወቷ በላይ ለሚበልጠው የሠፊው ሕዝብ ደህንነት ስለሆነ፥ በርሷ ሥር የነበርነውን አንዳችንን ሳታጋልጥ አረፈች።

አዬ! አንቺ ቆንጆ፥
የተከበረ ሥራሽን በፈቃድሽ ለቀሽ፥
ነጠላሽን ተከናንበሽ፥
የቤት ሠራተኛም መስለሽ፥
መልካምነትን ከልቡናሽ
ጽሑፎችን ከጉያሽ፥
ጥዑም ልሳን ከአንደበትሽ፥
ስትመሪ፥ ስታስተምሪ ቆይተሽ፥

ደከምሽ - ደከመሽ ለሀገርሽ - ለአብዮትሽ፤

ሕይወትሽን አሳለፈሽ ሰጠሽ - ለሀገርሽ፤

ከራስሽ ተለየሽ - በፈቃድሽ።

በሥራ ብዛት ብርር ያሉ - ፍዝዝ ያሉ አይኖችሽ፥

ድከም ያለው ሰውነትሽ፥

ለደርጎች በድን ሆኖ ወደቀልሽ - ገላገለሽ፤

ግን እንደ ጎበዛዝት የኢሕአፓ ጓዶችሽ፥

ምንጊዜም አትረሽም፤

ህያው ነሽ - በመንፈስሽ።

በደርጎች የተገደሉ የኢትዮጵያኖች መንፈስ በሥፍራዎች ሁሉ ይመላለሳል፤ ቁልጭ ያለ እውነት በኢትዮጵያ እስኪመጣ ድረስ ይጮሃል፤ ይዘምራል። ኢሕአፓዎችና ሌሎችም የራሳቸው እየመሰላቸው የዘመሩት መዝሙር በራዲዎ ሲዘመር በየመንገዱ ይሰማል። “ታጋይ” የተባለው ቃል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲታገሉ ሕይወታቸውን ያጡትን ሁሉ የሚያጠቃልል ከሆነ፥ ይህ አብዮታዊ መዝሙር ለማንኛውም ታጋይ የሚገባ ነው።

“እንዲህ አለች ሙታን ተራማጅ፥

እንዲህ አለች እርሱም እንዲህ አለ፤

መች ሞቱና ሞቱ ተባለ።

የታጋይ ድምጽ ይጮሃል፥

ይጮሃል ከመቃብር፥

ተከቶን ታጋይ ያልፋል፥

ትግላችን ይቀጥላል።”

ሌሎች በጎን (በስነጽሑፍ ኮሚቴ) አብረውኝ ይሠሩ የነበሩት ግን እንዳልታሰሩ ሰማሁ፤ ይኑሩ ይሙቱ እስካሁን አላወቅሁም። እኔም የማደርገው ጠፍቶኝ ብቻዬን መንከራተት ሆነ ሥራዬ። የጀመርኩትን ትግል በፈቃዴ መግታት ኃጢአት መስሎ ታየኝ። ፓርቲው እንደገና ለመደራጀት በሚያደርገው ከፍተኛ ጥረት መሳተፍ አማራጭ የሌለው መፍትሄ መስሎ ታየኝ።

ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ በኋላ፥ የከተማው ትግል ከጥቅሙ ጉዳቱ ስላመዘነ፥ ፓርቲው ልብ ገዝቶ፥ የተቀሩትን አባላት የገጠሩ ትግል ወዳለበት ሥፍራ ይሰበስብ

ይሆናል የሚል ተስፋ አደረብኝ። አንጃ ፈጣሪዎቹ (ሀ እና ለ) የሚሉትን አይነት የተራዘመ ትግል ባይሆንም፥ የፓርቲውን መመሪያ በመከተል፥ የማያቋርጥ ትግል ለመጀመር ምኞታዋ ተስፋ አደረብኝ። ውስጣዊ የፓርቲ ትግል ማካሄድ ካስፈለገም፥ ለዚህም ቢሆን ዝግጁ ሆኜ የመገኘት ኃላፊነት እንዳለብኝ ሆኖ ተሰማኝ። ምንም እንኳን የፓርቲውና የእኔ አመለካከት ሙሉ በሙሉ የማይጣጣም ቢሆንም፥ ምናልባት ይህ ጊዜያዊ እንጂ ዘለቄታዊ ስላልሆነ፥ የጀመርኩትን ትግል ለዚህ ጊዜአዊ ችግር ብዬ ማቋረጥ የለብኝም በማለት ቆራጥ ውሳኔ አሳለፍኩ። ምንም እንኳን በወቅቱ ፓርቲው የሚወስዳቸው እርምጃዎች ስህተቶች እንዳሉበት ቢገባኝም፥ እነኚህ መለስተኛ (የታክቲክ) እንጂ፥ መሠረታዊ ስህተቶች ስላልሆኑ፥ አስፈላጊ እርማቶችን ማድረግ ይቻላል በማለት፥ ቃል ኪዳን የገባሁለትን ፓርቲ እንደገና በትኩስ ኃይል ለማገልገል ቆርጬ ተነሳሁ።

## ትችቶች በኢሕአፓዎች ላይ

የዘመኑ ተቺዎች፥ የሀገር ተቆርቋሪዎች፥ እውነተኛ ታጋዮች በመምሰል፥ በተለያዩ መድረኮች ላይ በመውጣት፥ "ከጥንቱም ኢሕአፓ የሻዕቢያ ቅጥረኛ እንጂ፥ ለሰፊው ሕዝብ የቆመ፥ የእውነተኛ ታጋይ ድርጅት አልነበረም....." እያሉ ይተቻሉ።

አንዳንድ ጊዜ ትችቶች መረን የለቀቁ (አጉል አሉባልታዎች) ይሆኑና ያናድዳሉ። አልፎ አልፎ የኢሕአፓ ፓርቲ አባል ካልነበሩ ግለሰቦች የምንሰማቸው ትችቶች፥ ከመሠረቱ ከኢሕአፓ ጠላቶች፥ ወይንም ተቀናቃኝ ኃይላት የመነጩ መሆናቸውን ሳይገነዘቡ፥ በተደጋጋሚ የሚሰሟቸውን፥ "ኢሕአፓዎች የሀገር ጠላቶች፥ አናርኪስቶች፥ ቅጥረኞች ናቸው (ነበሩ)" እያሉ የሚያናፍሱት የሃሰት ፕሮፓጋንዳዎች መሆናቸውን አንባቢ ያስተውል። ዋናው ፓርቲም ቢሆን፥ አንጃዎችም ቢሆኑ፥ በእውነት ከልባቸው ታገሉ እንጂ፥ ቅጥረኞች፥ የሕዝብ ጠላቶች፥ አናርኪስቶችም አልነበሩም። ይህንን ጉዳይ አብራርቶ ለማቅረብ የዚህ መጽሐፍ አላማ አይደለም። ሆኖም፥ የኢሕአፓ ተከታዮች የነበርን፥ ሀገርን ለመምራት ኢሕአፓ ያስቀመጠውን የፖለቲካ ፍልስፍናውን እና የመጨረሻ ግቡን በመመልከት፥ ሕዝባዊ መንግሥትን ተስፋ አደረግን እንጂ፥ ኢሕአፓ መቶ በመቶ (100%) ፍጹም አለመሆኑን እናውቃለን። የጊዜውም ሁኔታ፥ ባንድ ትግል ከፋሺስታዊ መንግሥት ጋር ትግል፥ በሌላ በኩል በዙሪያችን ከነበረ የፖለቲካ ቅራኔዎች ጋር፥ ጥምር ትግል ሆነና - በምድራዊ የሰው እውቀት ብቻ የማይፈታ ታላቅ እንቆቅልሽ ሆኖብን ነው ከዚህ ያደረሰን።

ነገሮችን ሳያውቁና ሳያገናዝቡ፥ ከውጪ ሆኖ በማስተዋል ብቻ፥ ለትችት መሽቀዳደም ፋይዳ የለውም። ይልቅስ ተቺዎች ከትችቶቻቸው በማስቀደም የኢሕአፓን ርዕዮት ይመርምሩ፤ ቀጥሎም እነርሱን ራሳቸውን የኢሕአፓ አባል ከነበሩት ጋር (ተሳትፎአቸውንም) አወዳድረው ይመልከቱት። በእርግጥ ከውጪ ሆኖና ከውስጥ ሆኖ መመልከት አንድ አይሆንም። መሠረተ ቢስ ከሆኑ ትችቶች ይልቅ፥ ትክክለኛ መረጃዎችን የተከተሉ - በእውነቶችና በእውቀቶች ላይ የቆሙ ትችቶች ናቸው ወደፊት የሚያራምዱት።

ሰዎች ሁሉ ከግላዊ ስሜቶቻቸው ሁሉ ባሻገር (ፖለቲከኞችም ከፖለቲካ ግቦቻቸው ባሻገር) እውነቱን እውነት፥ ውሸቱን ውሸት ማለትን ቢደፍሩ፥ ብዙ ችግሮች በተቃለሉ። በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወቶቻችን መካከል እውነት የሚመስሉ ውሸቶች፥ እንዲሁም ቅልጥጥ ያሉ ውሸቶች እየተሰገሰጉ ነው ሰላም ያጣነው።

ውሸትም እውነትም አንዱ አንዱን ሳያውቀው፥

ጊዜ ነው መስተዋት ገላልጦ 'ሚያሳየው፤

ውሸት ሲሽማቀቅ ጊዜ ሲያሳፍረው፥

እውነት ግን ቦግ ይላል፥ ጊዜ ሲያሞግሰው።

እውነት ሁል ጊዜ ከእውቀት ብዛት አትገኝም። እንዳውም እውቀት በበዛበት ነው ውሸት የሚበራከተው። ሰዎች ብዙውን ጊዜ ግራ የሚጋቡት፥ ብዙ እውቀት ያላቸው ሰዎች ብዙ ስለሰበኳቸው፥ እውነትን ከእነርሱ የሚያገኙ እየመሰላቸው ይሆናል። "ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል" እንደሚባለው ሁሉ፥ የቅን አሳቢ ኢትዮጵያውያን አስተሳሰብ ለተንኮል ሠሪዎችና መሠሪዎች እየተጋለጠ፥ ጥርት ያለውን እውነት ማየት አስቸግሯል። አንድ ሰው ትምህርት ቤት ስለሄደ ብቻ አይደለም አዋቂ የሚሆነው፤ ማንም ሳያስተምረው፥ በራሱም ሊያውቅ ይችላል። እውነትን መጠቀም ለሚያውቅበት፥ ብዙ እውቀት አያስፈልግም፤ ከብዙ እውቀት ትንሽ እውነት ይበልጣልና።

እንደ ሀገራችን ሥፋት እና የህዝብ ብዛት፥ ሰዎች በቡድን ሲኖሩ፥ ጠባዮቻቸውም እንደየአካባቢያቸው፥ የአንዱ ከሌላው መጠነኛ ልዩነት ቢኖረው አያስገርምም። ሆኖም፥ አንዳንድ ግለሰቦች፥ ከአብሮ አደጋቸው፥ ወይንም በቋንቋ፥ በባህል፥ በአኑኗር ይመስለናል ከሚሉት ውጪ፥ ሰውን የማመን ችግር አለባቸው። እነርሱ አለምን በጠባቧ ስለሚመለከቷት፥ ለትንሺቱ አለማቸው ሲሉ እንጂ፥ ለትልቁ አለማችን የሚተርፍ ሥራን ሲሠሩ አይታዩም።

አንዳንድ ሰዎች፥ ከእውቀቶች መካከል እውነተኛውን (ለሕዝቦች ፍቅርን እና አንድነትን የሚያመጣውን) ለይተው ባለማወቃቸው፥ ዝም ማለትን ይመርጣሉ። አዎ! ሕዝቦችን ከሚለያይና ከሚከፋፍል እውቀት ድንቁርና ይሻላል። መማርና ማወቅ ጥሩ ሆኖ ሳለ፥ ከሁሉም የተሻለው ግን ጥበብ ነው። ጥበብ በመማርና በማወቅ ሊገኝ ቢችልም፥ መማርና ማወቅ ግን ብቻውን ጥበብን አያስገኝም። እኛ ኢሕአፓዎች የደማነው - የሞትነው ለነጻነት እና ለእኩልነት፥ ብሎም ለሀገር አንድነት፥ ለዴሞክራሲ እና ለእድገት እንጂ፥ በገዛ ሀገራችን ላይ ጠላት ለመሆን አይደለም። ሠፊውን ሕዝብ በእኩልነት እና በነጻነት ለማስተዳደር ተነሳን እንጂ፥ ስርዓት አልባዎች - አናርኪስቶች ለመሆን አልተነሳንም።

አንዳንድ ሰዎች አይቶ ማለፍ የማያስችል አዛኝነትና የርህራሄ መንፈስ ተፈጥሮአቸው (ጠባያቸው) ስለሆነ፥ ክፉውን አይተው አያልፉም፤ እስከ ሞት የሚያደርሳቸው ጦርነትም ቢሆንም ይገቡበታል እንጂ፥ ተረጋግተው አይቀመጡም። የእነኚህ ሰዎች መኖር የአለምን ገጽታ ይቀይራል። እነርሱ አለምን ይቀይራሉ እንጂ፥ አለም እነርሱን አትቀይርም።

ከእውቀቶችም መካከል ጥላቻና መከፋፈልን በሚያመጡት ላይ ማተኮር ወደኋላ ያስቀረናል። ለሕዝቦች ፍቅር እና አንድነት የሚጠቅሙትን እውቀቶች ማዳበር ነው ወደፊት የሚያራምደን።

ከአጉል (በታኝ) ትችት መቆጠብ ነው የሚሻለው፤ አብሮም መዝለቅ የሚቻለው። አለዚያ፥ ኢትዮጵያችን - ለእርሷ የሚጠቅማትን ጥሩውን ከማን ዘንድ እንደምታገኝ ሳታውቅ ትቀራለች።

# ምዕራፍ አራት

## ዘመቻ ወደ መርካቶ

በአእምሮዬ ለብዙ ቀናትና ሰዓታት አውጠንጥኜ፥ በቁርጠኛነት ከዋናው ፓርቲ ጋር ለመገናኘትና ለመሥራት ስለቆረጥሁ፥ ከፓርቲው ጋር የሚያገናኝ (ኮንታክት) ፍለጋ ከተማውን ማሰስ ጀመርኩ። ካዛንቺስ አካባቢ በማንዣበብ የማውቀው ኢሕአፓ መሳይ ሰው ስፈልግ እውላለሁ፤ ምንም የፓርቲው የሚመስል ሰው አጣለሁ፤ ወደ ፒያሳ እወጣለሁ፤ ከዚያም ሰው አጣለሁ፤ እንዳው በከተማው ሰው ሲጠፋ፥ “ሰው ሁሉ ከእስር ቤት ታጎረ? ወይንስ ሜካ ገባ?” እላለሁ።

ከብዙ የፓርቲ አባል ፍለጋ በኋላ፥ ከእለታት አንድ ቀን (እሮብ ለት)፥ ልክ የቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት፥ ወደ መርካቶ በሚያወጣው መንገድ ላይ፥ አንድ ጓደኛዬ - ጓድ መድህን - ወደ ታች - ወደ ሜክሲኮ አደባባይ ሲኳትን አገኘሁት።

አንድ ጓደኛ  ጓድ ሊሆን የሚችል መሠረታዊ አስተሳሰቡና የፖለቲካ ተቋሙ ሲታወቅ ነው። ከመድህን ጋር  በጓደኘነት ስለምንተዋወቅና አስተሳሰቡንም ስለምረዳ ነው በጓድነት የቀረብሁት።

ከጓዱ ጋር ሰላምታ ተለዋወጥንና ከአንድ ቡና ቤት ገባን። ቡና አዘዝንና እየተጎነጨን ለጥቂት ጊዜ ያህል ዝም - ዝም ተባባልን። ትንሽ ቆይቶ መንፈሶቻችን እርስ በርስ የተነጋገሩ ይመስል፥ በገጽታዎቻችን ከሚታየው ጭንቀት ሁሉ ባሻገር፥ አንዱ የሌላውን ጭንቅላት ያነብ ጀመር።

ካለ ምንም ንግግር፥ እንዲያው በመተያየት ብቻ፥ መድህን የኔን አንጃ አለመሆን እንደተረዳ ገመትሁ። እኔም መድህን የፓርቲው እንጂ የአንጃ ደጋፊ አለመሆኑ ቶሎ ገባኝ።

ወዲያው “አይዞህ! አለን እኮ! ሞተን አላለቅንም እኮ!” አለኝ። ቀጥሎም “ሀ እና ለ አሁንም በደብረ ብርሃን አካባቢ እያሰቸገሩ ናቸው። ፓርቲአችን በአዲስ አበባ አካባቢ የተጎዳ ቢሆንም፥ አሁንም በገጠሩ እንደተጠናከረ ነው ያለው። እዚህ

መንቀሳቀስ ቢያቅተንም ጫካ ገብተን ከሠፊው ባላገር ጋር እንቀላቀላለን፤ አይዞህ! አይዞን!" አለ፤ በግድ ፈገግ ለማለትም እየታገለ።

መድህን ይህን ሲናገር፥ በአእምሮዬ የነበረው ጭንቀት እልም ብሎ ጠፋ። የኔ ፊት ፈገግ ሲልና እርሱም ሳቅ ሲል፥ ለሁለታችንም ለሰው የማይታይ ጸጋ ከሰማይ የወረደ ይመስል ነበር። ፊቴን ወደ ግራ ዞር ሳደርግ በመስተዋቱ ውስጥ፥ ከመንገዱ ባሻገር፥ ከአጥሩ ዙሪያ ድሆች የተኮለኮሉበት፥ ያው የቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን[13] ነው ጎላ ብሎ የሚታየኝ የነበረ፤ ግን ይህንን የምጽፍ እኔ - የዛን ጊዜ በእውነት ስለራሴው ችግር እንጂ "ስለ ሌላ ነገር" አላሰብኩም።

*መቼም የሰው ልጅ በሁለትነቱ ሁለት የተለያዩ ነገሮችን ማሰብን ሳያስበውም መፈጸሙ አይቀርምና፤ በጭንቀቴ ውስጥ የተቀረጹ "ነገሮች" ቢኖሩም - "አይ! አይደለም! መድህን ነው መድህኔ፤" አልኩ (ጠባቂ መላእክትስ ለቅዱሳኑ ነው እንጂ፥ እንደኔ ላለው ኃጢአተኛ አይሆንምና)።*

እኔም እንዲህ አልኩ "ከእንግዲህ አጥብቄ የምይዘው ጓደኛም ጓድም የሆንከውን አንተን ካገኘሁ ነፍስ እንደዘራሁ ነው የምቆጥረው።"

አንዳንድ መረጃዎች ከተለዋወጥን በኋላ፥ በሌላ ቀን (ቅዳሜ) መሃል መርካቶ ለመገናኘት ተስማምተን ተለያየን። በዘመድና በጓደኛ ቤት እያፈራረቅሁ ስደበቅ ቆይቼ ሳለሁ፥ የቀጠሮው ቀን እስኪደርስ ድረስ አንዱ ቀን እንደ አንድ ወር ሆነብኝ። ወቅቱ ሳያጋልጡ፥ በየቤቱ የተደበቁ "ጸረ አብዮተኞች የተባልን እኛ" የምንታደንበት ወቅት ነበር።

የወደፊቱ ታውቆት እንደፈራ ሰው ሃሳብ የገባኝ መሆኑ ከፊቴ ላይ ቢነበብም፥ በደርግ ጥይት ከመገደል የሚያድነኝን የማውቅ እኔው ነኝ እንጂ፥ ሌላ ማንም ሰው እንዳልሆነ አውቄአለሁ፤ መስሎኛል። ለኔ የሚመክረኝ እኔ ሳለልኝ፥ ለኔ እኔው ከጎኔ የሚነገረኝን ብቻ የምሰማ ሆኛለሁና፤ ከማንም ሰው ምክርና ሃሳብ መውሰድን የምፈልግ አይደለሁም።

የቀጠሮው ቀን ሲደርስ፥ ለመጥፋት መነሳቴን ማንም ሳያውቅ፥ የሀገር ድንበር ለማስከበር ወደ ግዳጅ እንደሚሄድ እንደ አንድ ቆራጥ ወታደር ሆኜ፥ ለማያቋርጥ ትግል ወደ መርካቶ አመራሁ። ለመልመድ አስቸጋሪ የሆነውን የመርካቶ መንገድ ሀ ብዬ ለማጥናት ተዘጋጀሁ። የመድህን ቤት መርካቶ መሃሉ ላይ ስለነበር፥ መንገዱንና

---

[13] ያ ቤተ ክርስቲያን ይታደሳል፤ ከውስጡ ገብተውበት የማያውቁትም በዙሪያው።

የቤቱን አካባቢ አጠናሁ። ከጫካ ወጥታ ከተማ እንደገባች ዝንጀሮ ሆንኩና መርካቶ ውስጥ ስምጥ አልኩ።

በአራቱ ቀናት (ከእሮብ እስከ ቅዳሜ) ሃሳቦቼ እኔን እንደምንም አሻገሩኝ። በቀጠሮውም ሰዓት ከተቃጠርንበት ሥፍራ ተገናኘን። መድህን ሕጋዊ ስለነበር፥ በፓርቲው ውስጥ ጓዶችን ወደ ባላገር ለማሸጋገር ይጥር ነበር። እኔን በየቀኑ በማግኘት፥ ባላገር የምገባበትን ቀን በተስፋ እንድጠባበቅ ይመከረኝ ጀመር። የእኔም ሃሳቦቼ ከመርካቶ አውጥተው የሚወስዱኝ ሥፍራ ከከተማ ውጪ ሆነ።

መድህን ከሥራ እስኪመጣ ድረስ ቀኑ እየረዘመብኝ፥ በየቀኑ በተስፋ ብቻ መኖር ጀመርኩ። የዛሬው ተስፋ ወደ ነገ፥ የነገው ደግሞ ወደሚቀጥለው ቀን እየተላለፈ፥ ነገዎች እየበዙ ሲመጡ ጊዜ፥ ሌሎች አላስፈላጊ ሃሳቦች በጭንቅላቴ ይንገዋለሉ ጀመር።

የፓርቲው ከፍተኛ አካላት እኔን "ይህ ሰው የንኡስ ከበርቴነት ጠባይ ስለሚኖረው ለአብዮታዊ ትግል ብቁ አይሆንም...." የሚሉኝ እየመሰለኝ፥ ያሰብኩት ረጅም የትግል ጉዞና መስዋእትነት እንዳይከሽፍብኝ የምፈራ ሆንኩና፥ ይህንኑ ፍርኃቴን ለመድህን ገለጽኩለት። እርሱም እንዲህ አይነቱን አስተሳሰብ ከጭንቅላቴ እንዳወጣ መከረኝ።

በዛን ወቅት አባላቱን የመንከባከብ ኃላፊነት ጉዳይ ፓርቲው በከፍተኛ ደረጃ የሚመለከተው መሆኑን በመግለጽ አጽናናኝ። እንዲሁም፥ "ካንተ ጋር የሚሄድ ሌላ ካንተ የበለጠ የተጋለጠ (የተበላ) ጓድ አለ። ከርሱ ጋር ስለማስተዋውቅህ ነገ በዚህ ቡና ቤት እንገናኝ" ብሎኝ ተለያየን።

**<u>ከአሻግሬ ጋር በመርካቶ</u>**

በነጋታው መድህን ከጓድ አሻግሬ ጋር አስተዋወቀኝ። አሻግሬን ቀደም ብዬ አላውቀውም ነበር። ግን ብዙም ጊዜ ሳይፈጅ ጥሩ ጓደኛ ሆነኝና በየቀኑ ከመሃል መርካቶ ሻይ ቤቶች መገናኘት ጀመርን። ካነጋገሩና ከሁኔታው ቆራጥ ጀግና ይመስላል። እንደማንኛችንም ካለ ጠብ መንጃ (ወይም ካለ ሽጉጥ) በጦርነት ውስጥ ያለን የኢሕአፓ የሃሳብ ወታደሮች ሁሉ፥ አሻግሬም በፍርኃትና በጀግንነት መካከል የተጠመደ ነበር። ከኔ የበለጠ አካባቢውን በቁጥጥሩ ያደረገ ይመስላል። ቀልድና ጨዋታ ያውቅበታል፤ አጠር አጠር ያሉ ጨዋታዎችን እየለዋወጠ ሲያመጣ፥ እራሱን በቀላሉ ከድብርት ማውጣት የሚችል መሆኑ ያስታውቃል። እኔ ግን ኑሮን የጀመርኩት አብዮት ከፈነዳ በኋላ ይመስል፥ ከጊዜው ሁኔታ የሚዛመድ ወሬ ካልሆነ በስተቀር፥ ወደ ኋላ መለስ ብዬ ስላለፈው ጥሩም ሆነ መጥፎ ጊዜ ማውራት፥ ጊዜ ማጥፋት እየመሰለኝ እንደሆንም እንጃ እንጂ፥ እንዳው አያሰኘኝም። አንዳንድ ጊዜ የኔ ዝምታ እንደሰለቸው ከፊቱ ሳነብ፥ እጅግ አስደናቂ የሆኑ ህልሞቼን አወራለታለሁ። እርሱም በተመስጦ ከሰማ በኋላ፥ ልክ ሲኒማ ቤት ገብቶ እንደ ወጣ ሰው ይሆንና በመገረም፥ ምን ይሆን ፍቺው? ብሎ ዝም ይላል። እኔም "በል ለፍቺው ሌላ ቀን" እለዋለሁ።

አሻግሬ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚፈለግና እኔም በተቻለ መጠን ይህን ግለሰብ እንዳይጋለጥ ለመሸፋፈን መጣር እንዳለብኝ በመድህን በኩል ስለተነገረኝ፥ ጉዳዩ ባይገባኝም፥ ለዚህ ግለሰብ አስብለት ነበር።

ከአሻግሬ ጋር ዘወትር ጧት ጧት ብቻ ነበር የምንገናኘው። የምሳ ሰዓት ሲደርስ ጥፍት ይላል። እኔም ከምሳ ሰዓት ጀምሮ እስኪመሽና መድህንን እስካገኘው ድረስ፥ መርካቶን ማሰስ መደበኛ ሥራዬ ሆነ።

በደርግ "አብዮት" ካለ ሥራ መንገላወድ ወይንም ባንድ ሥፍራ መቆም ስለማይቻል፥ አውቆ አበድ መስሎ ሮጥ - ሮጥ እያሉ መራመድ፥ አለዚያም፥ የቀን ተቀን ኑሮውን ለሚሟላት እንደሚሯሯጥ ነጋዴ ጣደፍ - ጣደፍ ማለትና መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። ማንም ሰው በመንገድ ላይ ሲሄድ አብዮታዊ ካድሬ በመምሰል፥ ግንባርን ኮስተር አድርጎ፥ ደረትን ነፍቶ፥ ትምክህት በተሞላበት መንፈስ፥ ገልመጥ - ገልመጥ እያለ መራመድ ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ፥ ከቡና ቤት ወደ ቡና ቤት፥ ከጠላ ቤት ወደ ጠላ ቤት እየዞሩ መጎለትና፥ ከዚያ ጊዜ ማጥፋት ነበር የተቀረው አማራጭ።

ከመድህን ጋር ስንገናኝ የምንጨዋወተው የጊዜውን ሁኔታ የሚመለከት ጉዳይ ብቻ ስለነበር፥ እርሱን በየቀኑ ሳገኘው ከመጠን በላይ ደስ ይለኛል። መድህንና

አሻግሬ በማይኖሩበት ወቅት፥ በየቀኑ ሻይ ቤትና ጠላ ቤት እየተመላለሱ ጊዜን መፍጀት እየሰለቸኝ መጣ። ይህም ምናልባት የንኡስ ከበርቴነት ጠባዬ እያቅበጠበጠኝ ይሆናል በማለት፥ ያለኝን ትእግስት ላለመጨረስ ስል እራሴን አጽናናለሁ።

ከዛች ከአንድ ቀን (መድህን ለኔ አሻግሬን ያስተዋወቀኝ ቀን) በስተቀር፥ አሻግሬ መድህንን ሊያገኘው ስለማይችል (ስለማይፈቀድለት)፥ የአሻግሬ ተስፋ (ኮንታክት - አገናኝ) እኔው ብቻ ነበርኩ። እኔን ካላገኘ ከፓርቲው ጋር ያለውን ግንኙነት ለመቀጠል ቀላል ስለማይሆንለት፥ በመድህን በኩል የቀረበ ተስፋ መኖሩን በየቀኑ ስንገናኝ ይጠይቀኛል።

ከእለታት አንድ ቀን፥ መድህን ከበላይ አካል ጋር በመነጋገር ስለገጠሩ ጉዞአችን አንዳንድ ዝግጅቶች እያደረገ መሆኑን በመግለጽ እንዲህ አለ፡- “እንግዲህ ለሁለታችሁም የቀበሌ የፈቃድ ወረቀት ለማውጣት መሯሯጥ ይኖርብኛል። ይህ የፈቃድ ወረቀት ከተገኘ በኋላ ነው ኮዱ (የምሥጢር ቃል) የሚዘጋጅ። ሁሉም በቶሎ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ ባሁኑ ጊዜ ቀላል እንደማይሆን ሊገባህ ይችላል። የተቻለኝን አደርጋለሁ፤ አይዞህ በርታ።” መድህን ይህንን ብቻ ተናግሮ ቶሎ ተለየኝ።

በነጋታው ጧት ይህንን የምስራች ለአሻግሬ ነገርኩትና በጣም ደስ ተሰኘ። ከአንድ ሳምንት በኋላ መድህን ሌላ የምሥራች ይዞልኝ መጣ። “መልካም ዜና ይዤልህ መጥቻለሁ” ሲለኝ፥ የደስታ ኮረንቲ ሰውነቴን ወረረው። ከዛም ገልመጥ - ገልመጥ እያለ በሹክሹክታ እንዲህ አለ፡- “ከእንግዲህ አንተና ጓዱ የኮረም ሰዎች ናችሁ። ከዚህ የምትቆርጡት የአውቶቡስ ቲኬት እስከ ኮረም ድረስ ሲሆን፥ እናንተ ግን እዛ ሳትደርሱ፤ ቆቦ የሚባል ሥፍራ ትወርዳላችሁ። አውቶቡሱ ከአዲስ አበባ ተነስቶ፥ ከምቦልቻን፥ ደሴን እና ኮረብታማውን የወልድያን ከተማና አካባቢ አልፎ፥ ገላጣ እና ሜዳማ የሆነው ራያ አካባቢ ትገባላችሁ። ከዚያም አውቶቡሱ ቆቦ የሚባል ትንሽ ከተማ ሲደርስ ከዚያ ይቆማል። እናንተም ከዛ ወርዳችሁ ከሆቴሉ አጠገብ ትቆማላችሁ (በዛን ጊዜ ቆቦ ያለው ሆቴል አንድ ብቻ ነበር)። ከመንገዱ ዳር አንድ ባላገር እግሩን አጣምሮ፥ ነጠላ በራሱ ላይ ጣል አድርጎ፥ በትር ተመርኩዞ፥ ቆሞ ታገኛላችሁ። ከሁለት አንዳችሁ፥ እንበል አንተ፥ “ጤና ይስጥልኝ” ስትለው፥ “ሰላምና ጤንነት ይስጥዎት” ይልሃል። ከዛም፥ “ይህ መንገድ የት ያደርሳል?” ስትለው፥ “ቀይ መስቀል” ይልሃል። በዚህን ጊዜ “እኛው ነን” ትሉትና ባላገሩ እየመራ ያደርሳችኋል” አለ ጓድ መድህን፤ ፍቅርና እንክብካቤ በተሞላ አንደበቱ።

እንዲሁም በድጋሜ "ከእንግዲህ ይህን ያልኩህን እንዳትረሳ፤ እስቲ ያልኩህን መልሰህ ንገረኝ" አለ። እኔም በትክክል ከነገርኩት በኋላ፥ "ከእንግዲህ ይህ በአእምሮ የሚያዝ፥ በልብ የሚጻፍ እንጂ፥ በወረቀት የሚጻፍ አይደለም። ስለዚህ አደራህን እንዳትረሳ" አለኝ። እኔም ብዙ - ብዙ ኮዶችን በመቀበልና በማስተላለፍ የሠለጠንኩበት ጉዳይ እንዳልሆነ ሁሉ፥ በሙሉ ልቤ "እሺ" አልኩትና ተለያየን።

በማግስቱ ይህንን ታላቅ ዜና ለማብሰር ወደ ተለመደው ሻይ ቤት አመራሁ። የምስራቹን ለአሻግሬ በሹክሹክታ ስነግረው፥ ልክ በገንዘቤ ነፍስ ገዝቼ የሰጠሁት ይመስል እጅግ ደስ አለው። እኔም፥ ጣደፍ ጣደፍ እያልኩ፡- "ከነገ ወዲያ ወደ ኮረም ለመሄድ የአውቶቡሱን ቲኬት ነገ መቁረጥ አለብኝ፤ በል እንግዲህ ቲኬቱን ቆርጬ ስለምመጣ፥ ነገ በአምስት ሰዓት እዚሁ ሥፍራ እንገናኝ" አልኩትና ተለያየን።

የኮረም አውቶቡስ የሚነሳው ከጧቱ ሦስት ሰዓት ነው። ቲኬቱን ቶሎ መቁረጥ ይሻላል ብዬ፥ በማግስቱ፥ ገና ሳይነጋ በመነሳት፥ ከሥፍራው ስደርስ ከምሽቱ 12 ሰዓት (ወይንም ከጧቱ 6:00 A.M.) እንኳን አልደረሰም። ከኔ በፊት አንድም ሰው ይገኛል ብዬ አካሰብኩም ነበር። ዳሩ ግን ከኔ በኋላ መጥቶ የሚሰለፍ ሰው ጠፋ።

ከኔ ፊት የተሰለፈውን ሰው ስለ ሰልፉ መርዘም እያጋነንኩ ላናግረው ስሞክር፥ "እባክህ ቀልዱን ተወው፤ እኔ ካንተ አንድ ሰዓት በፊት መጥቼ፥ ካላንተ የቀደምኩት ሰው የለኝም" አለ። በዚህን ጊዜ ፍርኃትና ድንጋጤ አደረብኝ። እንደ ምንም ሦስት ሰዓት ደረሰና ቲኬት መቁረጥ ተጀመረ። ልክ የሰልፉ አጋማሽ ላይ እንደተደረሰ፥ "ቲኬቱ ስላለቀ ነገ ተመለሱ" ተባለ።

ይህንን አሳዛኝ ሁኔታ ለሁለቱ ጓዶች እንዴት አድርጌ እንደምነግራቸው ነው ግራ የገባኝ። አውቄ ያደረግሁት ወይም ንዝህላልነት ያስመስልብኛል በማለት እጅግ ተጨነቅሁ። መድህን እኔን በአንጃነት ይጠራጠረኝ ይሆናል በማለትም የሃሳብ ጭንቀት ያዘኝ።

አምስት ሰዓት ላይ ከአሻግሬ ጋር ሻይ ቤት ተገናኘን። ሁኔታውን ሳስረዳው ለጊዜው ክው ብሎ ደነገጠ። ግን ደግነቱ፥ ለሚቀጥለው የተቻለኝን እንዳደርግ አደፋፈረኝ እንጂ፥ እኔን እንደ ጥፋተኛ አልተመለከተኝም። እንደወትሮው የመሄጃው ሰዓት ሲደርስ በቅሬታና በሃዘን ተለየኝ።

ማታ ሲሆን መድህንን አገኘሁትና ለርሱም እንዲሁ ስለ ሁኔታው አለመሳካት አስረዳሁት። ጓዱም "የሚያሳስበው የኮዱ ጉዳይ ነው እንጂ፥ የቀበሌውን ወረቀት

እንኳን ለሌላ ጊዜም መጠቀም ይቻላል" አለና፥ ለሚቀጥለው እንድጠነቀቅ መከሮኝ፥ እርሱም በሃዘን ተለየኝ።

ሳምንታት አለፉ፤ ኮዱን በድጋሜ ሠርቶ ማስተላለፍ እጅግ ከባድ ነው የሚሆን። መድህን ካለ ወትሮው ተስፋ የመቁረጥ ምልክት ይታይበት ጀመር። እርሱም "አንጃዎች ጓዶቻችንን ከየመንገድ እየጠለፉ ለደርግ ማስረከብ ጀምረዋል፤ እኔም ራሴ በመሥሪያ ቤት አካባቢ ጥቆማ ሳይደርስብኝ አይቀርም" ብሎ ሲነግረኝ፥ የእርሱ ተስፋ መቁረጥ ወደኔም ይዛመት ዘንድ ግዴታ ሆነና፥ አእምሮዬን በጠበጠው።

ብዙ ቀናት አለፉ፤ መድህን በየቀኑ አልገኝ አለ፤ በእጄ የነበረ ገንዘብ መነመነ። በየቀኑ ለጠላና ለሻይ የማወጣውን ገንዘብ በቁጠባ መያዝ ጀመርኩ። ከጊዜ በኋላ ለአልቤርጎ የሚሆን ገንዘብ አጣሁና በድንገት የማላውቀውና ያልተለማመድኩት ችግር ውስጥ ገባሁ። ጨለማን ተገን አድርጎ፥ ግርግዳን ተደግፎ መተኛት ሊመጣ ሆነ። "እንግዲህ ያለው አማራጭ ይኸው ከሆነ፥ ማን ይፈራዋል። ለኔም ጥሩ ነው፤ የጫካውን ኑሮዬን እለማመድበታለሁ..." አልኩ በለሆሳስ።

ለማደሪያ ጸጥ ያለ ሥፍራ ስፈልግ አምሽቼ፥ ጨለምለም ያለና ገላጣ ሥፍራ አገኘሁ። ስዞር ውዬ፥ ሰውነቴ ዝሎ፥ እንቅልፍም አስቸግሮኝ ነበረና፥ ቶሎ ብዬ ጨለምለም ካለው ስፍራ ሰውነቴን ጣልኩትና ኩርምት ብዬ ተኛሁ።

ትንሽ እንቅልፍ ሸለብ እንዳደረገኝ ውሾች መጥተው ከበቡኝ። አሁን ብድግ ብዬ ተነስቼ ብሄድ ግማሽ ጎኔን ቦጭቀው፥ የተቀረውን ግማሽ ጎኔን ለቀበሌ ዘበኞች ይሰጡታል በማለት፥ ቀረብ ሲሉኝና ሲያሸቱኝ ትንፋሼን ያዝ በማድረግ ልክ እንደ ሞተ ሰው ሆንኩባቸው። በቁጥር ሰባት የሚሆኑ ውሾች እያንዳንዳቸው በየተራ እየዞሩ አሸተቱኝ። ነፍስ እንዳለኝ የገባቸው አልመሰለኝም፤ ሞቷል ብለውም ሳያዝኑልኝ አልቀረም። ተጠራጣሪ የሆኑ ሁለት ውሾች ብቻ በመደጋገም እየመጡ ይመረምሩኝ ጀመር፤ የሚያውቁኝ መሆኑን ለማጣራት ይመስላል። በመጨረሻም "ይህን ሰው አናውቀውም፤ ግን ሞቷል፥ ወይንም ማደሪያ ያጣ ድሃ ይሆናል" ብለው በማዘን ሁሉም ጥለውኝ ሄዱ። አልፎ አልፎ እንዳይመጡብኝ በአይኔ እየቃኘሁ፥ ከእንቅልፍ ጋር ትግል ጀመርኩ። ከምሽቱ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ሲሆን እነሱም እንቅልፋቸው መጣና፥ ሁሉም በየተራ ተኙ።

ውሾች ምስኪኖች ናቸው። እነርሱስ ከጊዜያዊ አለመስማማት የተነሳ እርስ በርሳቸው ትንሽ - ትንሽ ይጣላሉ። ግን ወዲያው ይታረቁና አብረው ይተኛሉ፤ የእኛ የሰው ልጆች ጠብ ግን ንዝንዝ ያለ፤ መጨረሺያ የሌለው...።

እንደ ምንም ትንሽ እንቅልፍ ሸለብ አደረገኝ፤ ግን ወዲያው ብንን አልኩ። በዚህን ጊዜ ቀና ብዬ ወደ ሰማይ በግማሽ በማንጋጠጥ ተመለከትሁ። እግዚአብሔር ኮሙኒስቶችን ባያይም፥ ከዋክብት አፈጠጡብኝ።

ከዋክብት እንዲህ ድምቅ ብለው ሳያቸው የመጀመሪያዬ ሳይሆን አይቀርም። ቦግ ቦግ ብለው ወደ መሬት ለመውረድ የተዘጋጁ ይመስላል። ባንድ በኩል “እኛም አለንልህ እኮ! አይዞህ አትፍራ...” ሲሉ፥ በሌላ በኩል ደግሞ “መጣን አንጠልጥለን ልንወስድህ..” የሚሉኝ ይመስለኛል። “ሁለቱም ለኔ ቆንጆ ነው፤ ያሻችሁን አድርጉኝ እባካችሁ!” እያልኩ ቁንጅናቸውንም በልቤ ሳደንቅላቸው፥ እነርሱም እየሰደቁ (በደስታ እየፈነደቁ) እኔንም ከእነርሱው ደስታ ያካፈሉኝ መስሎኛል።

የማላየው የሰማይ ክፍል በዙሪያዬ በከበቡኝ የቤቶች ጣሪያዎች ስለተሸፈነና የማየው የሰማይ ክፍል የተወሰነ ሆኖ፥ እነኛ የማያቸው ከዋክብት ከላይ ሆነው ይህ ነው የማይባል ደስታ፥ የናፍቆት ሰቀቀን እና ተስፋ የተቀላቀለበት ስሜት (የገጠር ትግል፥ ደርግን አሽቀንጥሮ መጣል፥ ሥልጣን ለሕዝብ መስጠት፥ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ስርዓትን መመሥረት...) አፈሰሱብኝ።

ከሚታሰበኝ ስሜት ጋር የተቀላቀለው ወቅታዊ ችግር ቀሰቀሰኝና “እናንተም'ኮ ስላላወቅናችሁ ይሆናል እንጂ፥ ደጎች ናችሁ። በሉ እንግዲህ! ላርቤርጎ የሚሆን ገንዘብ ወርውሩልኝ” አልኳቸው። እነርሱም “ከሰማይ ቤት ገንዘብ አለ ብሎ የነገረህ ማነው? አንተ ባለጌ! በል ተነስ! አይዲያሊስትነት ያልተላቀቀህ ግማሽ ኮሙኒስት! ተነስ! ይልቅስ ሳይነጋና፥ ውሾቹ ከእንቅልፋቸው ሳይቀሰቀሱ ሹልክ ብለህ ከዚህ ጥፋ!...” የሚል መልዕክት ከአንዷ ኮከብ የደረሰኝ ይመስል፥ ድምጼን በማጠፋት፥ እኔም በአራት እግሬ፥ ውሻ መስዬ፥ ሹልክ ብዬ ጠፋሁባቸው።

የዛሬውስ በዚህ አለፈ፤ የነገውስ? እንደተለመደው አሻግሬን ወደማገኝበት ሻይ ቤት ሄድኩ። ምናልባት አሻግሬ ገንዘብ ይኖረው እንደሆን በማለት፥ ሻይ ቤት ስንገናኝ፥ ከውሻ ጋር ማደሬን ሳይሆን የገንዘብ እጥረት እያሳሰበኝ መምጣቱን ነገርኩት። እርሱም “ስለ ገንዘብ አታስብ፤ አንዳንድ እቃዎች (እንደ ሙዚቃ ማጫወቻ የመሳሰሉ) አሉኝ፤ እነርሱን በርካሽ እሸጥና እንካፈላለን። አንተ ብቻ በርታልኝ፤ እንደምታውቀው ብዙ መጋለጥ የለብኝም። ካንተ በስተቀር ሌላ ማንንም የበላይ አካል ማግኘት አልችልም...” ብሎ፥ የአንድ ቀን አልቤርጎ ማደርያ ሰጥቶኝ ተለየኝ።

በማግሥቱ አሻግሬ መልኩ ሁሉ ተለዋውጦ፥ ሌላ ሰው መስሎ መጣ። እርሱ መሆኑን ያወቅሁት ሲጨብጠኝና ሲያነጋግረኝ ብቻ ነበር። ትላንት በሰጠኝ ተስፋ

መሠረት ገንዘቡን በጄ አስጨበጠኝ። "ይህን ሁሉ ገንዘብ ከየት አመጣኸው?" ስለው ደንገጥ ብሎ ዝም አለ። እኔም ከዋክብቶቹን "በሉ ላርቤርን የሚሆን ገንዘብ ወርውሩልኝ" ያልኳቸው ትዝ አለኝና፥ ለጊዜው ማንን ማመስገን እንደሚገባኝም አላወቅሁ፤ ድንግርግር አለኝ፤ ቶሎ ማመስገን ሲገባኝ፥ ለደቂቃዎች ጭጭ አልኩ። ትንሽ ቆይቼ፥ እንዳላመሰገንኩት ትዝ አለኝና፥ "አሻግሬ በጣም ነው የማመሰግንህ፤ በነፍሴ ደረስክልኝ እኮ!" አልኩት።

አሻግሬም "ይኸውልህ ጓድ፥ ስሜና ፎቶግራፌ በጋዜጣ ወጥቷል፤ በጥብቅ እፈለጋለሁ" አለ። ጋዜጣውንም ከኪሱ አወጣና አሳየኝ። ከአይኖቹ በስተቀር፥ አሁን የማየው አሻግሬ ጋዜጣው ላይ ካለው ይለያል።

"እንዴት ነው ሌላ ሰው አልመስልም?" አለ፤ የኔን መልስ በጉጉት የሚጠባበቅ በመምሰል። እኔም በደንብ አስተዋልኩትና፤ "አዎን! ጭራሽ ሌላ ሰው ነው የምትመስለው" አልኩት። እርሱም፡- "ይኸውልህ! ጸጉር በመላጨት ብቻ ሌላ ሰው መምሰል ይቻላል። ካወቅህበት፥ አለባበስ፥ መነጽር፥ ኮፍያ፥ አካሄድ፥ ወ.ዘ.ተ. አንተነትህን ይደብቁልሃል" አለኝና፥ ቀጠል በማድረግ፡-

"ቅድም ወደዚህ ስመጣ፥ አንድ የሚያውቀኝ ሰውዬ ከፊት ለፊቴ ድቅን አለብኝ። እኔም አይኖቼን በማንሸዋረር ስገላምጠው ጊዜ፥ እንደማፈር ብሎ ሄደ" አለኝ። እኔም በአድናቆት "ይገርማል!" አልኩ። እርሱም ቀጠል አድርጎ፡-"ከእንግዲህ እኔና አንተን አንዳንድ ያልታሰበ አደጋ ሊያጋጥመን ይችላል፤ ሆኖም ከአደጋ ለመዳን ጭንቅላታችንን በፍጥነት ማሠራት ይኖርብናል። ተስፋ መቁረጥ እራስን እንደ መግደል፤ ቃል የገባንለትን ሠፊውን ሕዝብም እንደ መካድ ይቆጠራል..." አለኝ።

እኔም "ከምግብ የበለጠ የሚርበኝ፥ ከመጠጥ የበለጠ የሚጠማኝ፥ ከጓዶች ጋር በአንድነት እየታገሉ ሠፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ ጨቋኝ መንግሥት ነፃ ማውጣት ስለሆነ፥ ይህን አላማዬን ከግብ ለማድረስ በምታገልበት ወቅት ሕይወቴ ብታልፍ፥ አብዮታዊ ግዴታዬን እንደተወጣሁ ነው የምቆጥረው። ስለዚህ ተስፋ መቁረጥ ከኔ ዘንድ ሥፍራ የለውም፤ ሞትም ቢመጣ አልፈራውም" አልኩት።

የዛን ለት ብቻ ከአሻግሬ ጋር ቀኑን ሙሉ አብረን ዋልን። ለመሸሸጊያ ያመቻል ብዬ የማስበውን፥ መታወቂያ የማይጠየቅበትን አልቤርን ጠየቀኝና፥ መሸትሸት ሲል ወደማውቀው አልቤርን አመራን፤ ባለ ሁለት አልጋ ክፍል ተከራየንና ገባን። የዛን እለት ብዙ አወራን፤ በመካከላችን ያለውን አንዳንድ የስሜታዊ አመለካከት፥ ልዩነቶቻችንንም ሳንደብቅ ተነጋገርን።

ስለ አንዳንድ የፓርቲያችን ታክቲክና እስትራተጂ (የወደፊት አላማዎችና እቅዶች) በሰፊው ስንነጋገር፥ "እኔ እንደ አንጃዎች አላስብም፤ ሆኖም በወጣቶች እልቂት ትይዩ የኛን ትግል ስመለከት፥ ታክቲክና እስትራተጂአችንን (የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅዳችንን) ለማጣጣም አንዳንድ ለውጦች ማድረግ የሚኖርብን ይመስለኛል" አልኩት። እርሱም በመሠረተ ሃሳቡ ተስማማ፤ ግን በንግግሬ ውስጥ አንዳንድ "ተመጻዳቂ ርህራሄ" የሚከሰት መሆኑን እና ይህም ለወቅታዊ ችግሮቻችን የበለጠ ችግር የሚጋብዝ መሆኑን አስረዳኝ።

"እርግጥ እኛ ኮሙኒስቶች ርህሩሆች ነን፤ በተፈጥሮ ለሰው የመራራት ዝንባሌአችንም ነው ኮሙኒስቶች እንድንሆን የገፋፋን። ዳሩ ግን የአብዮቱ ሂደት ያስከተለውን አስከፊ ሁኔታ እየተመለከቱ፥ በግብታዊነት ርህራሄ መጠመድ፥ ለትግላችን እንቅፋትን ሊፈጥር ይችላል። ሰው ሲገደል፥ ሰው ሲበደል አንወድም። የትግላችን መነሻ ምክንያት ይኸው ሲሆን፥ መጨረሻውም የሰዎችን በደል ማቆም ነው። ስለዚህ፥ ባንተ በግልህ ለትግላችን ማድረግ የምትችለውን ብቻ አስብ እንጂ፥ በዚህ ባለንበት ሁኔታ፥ በቁንጽል ለዚህም ለዛም አስበንና ተጨንቀን አንችለውም፤ ከግባችንም እንዳንደርስ እንቅፋት ይሆንብናል" በማለት መከረኝ።

እኔም እጆቼን ጭብጥ በማድረግ "የወጣቶች መስዋእትነት፥ በየመንገዱ ኮለል ብሎ መሬት የሰረገው ደም፥...እህ! የሁላችንም ትግል ካለ ውጤት አይቀርም! ካለ ውጤት አይቀርም!" ብዬ ጭጭ አልኩ።

ስለ ውስጣዊ ችግሮቻችን ብዙ በመወያየት እራሳችንን ድክም ካደረግን በኋላ፥ "የአንጃዎችና የፓርቲያችን የተራራቁ አመለካከቶች በአንድ አቅጣጫ ቢነፅሩ ኖሮ፥ እኛም ከዚህ ባልደረስን ነበር...." እያልን በማላዘን ወደ እንቅልፋችን ተሸጋገርን።

በማግስቱ ጧት ተነስተን፥ ቁርስም ሳናደርግ፥ በቀጠሮ ተለያየን። እኔ ግን ብዙ - ብዙ ሃሳቦችን በጭንቅላቴ ማጉላላትና ማብላላት ጀመርኩ። በውስጤ የጋየውን ስሜት መቆጣጠር አላስችል አለኝና አንድ ባለ ብዙ ወረቀት ደብተር ከነ መጻፍያው (እስክሪፕቶ) ገዛሁና፥ በኢሕአፓነት ተሰጥቶኝ የነበረ የመጻፍ ሥራዬን በልዩ መልኩ ተያያዝኩት።

"ታማኝ ሰው ታማኝነቱንም ራሱ ካልገለጸ፥ ማን ይረዳዋል?" በማለት የሃሳቦቼ ግፊት "ቶሎ ቶሎ በል" የሚለኝ እየመሰለኝ ስጽፍ፥ ጽሑፉ የማያቋርጥ ሆነ። በገባሁበት ጠላ ቤትና ሻይ ቤት መጻፍ ብቻ ሆነ ሥራዬ። ግን፥ "በኢሕአፓነት የተሰጠኝ የጽሑፍ ሥራ አላማው የመንደር ሰዎችን ወደ ኢሕአፓ ለመቀስቀስ ነበር፤

የዚህኛው አላማ ደግሞ፥ ኢሕአፓን ወደኔ ለመሳብ ነው እንዴ?…ባይሆንም፥ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ኃጢአትን ተናዞ፥ ንስሐ ገብቶ እንደመሆኑ መጠን፥ ወደ ትጥቅ ትግል የሚገባውም በሆድ ውስጥ ያለውን ተናዞ መሆን አለበት" በሚል ስሜት፥ ስለራሴ አቋምና ስለ ኢሕአፓ የሚሰማኝን ሁሉ ፍርጥርጥ አድርጌ ጻፍኩ። በጽሑፌ ውስጥ በተደጋጋሚ ለኢሕአፓ ያለኝን ታላቅ እምነትና ለገጠሩ ትግል ያለኝን ከፍተኛ የሞራል ዝግጅት ገለጽኩ። በስነ ስርዓቶች (ዲሲፕሊን) በኩልም፥ ከሥጋዊ ፍትወት ሁሉ የተቆጠብኩ እንጂ፥ ያካባቢዬ ሁኔታ አዘናግቶኝ አላማዬን የምስት አለመሆኔን አረጋገጥኩ። በርዕዮተ አለም የበሰልኩ፥ በሞራል የጠነከርኩ መሆኔን ዘረዘርኩ። በመጨረሺያም፥ በደርግ የተቀናጀውን የሰዎች እልቂት ዘመቻ እንደ እኔ ያለ ቆራጥ ወደ ባላገር ሄዶ በትጥቅ ትግል ካልተጋተረው በስተቀር፥ እስካሁን ያደረግነው ትግል ውጤት አልባ እንደሚሆን አሳሰብኩ። ባጠቃላይ፥ የጽሑፉ ስሜት "እባካችሁ ወደ ገጠሩ ውሰዱኝና ካናንተው ጋር ልቀላቀል" የሚል የልመና ጥሪም ይመስላል።

በሌላ ቀን መድህን ከተቃጠርንበት ቡና ቤት አገኘሁት። ወዲያውም "ይህንን ጽሑፍ እቤትህ ውሰድና አንብበው፤ ካነበብህ በኋላ ለበላይ አካል አስተላልፈው ወይንም አቃጥለው" አልኩት።

በሁለተኛው ቀን እንዲሁ ከመድህን ጋር ሌላ ቡና ቤት ተገናኘን። "ጽሑፉን አነበብከው ወይ? ስለ ጽሑፉ ምን ተረዳህ?" ብዬ ብጠይቀው፥ ካለ መልስ ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም አለ። እንደገና ጠየቅሁት፤ እርሱም፡- ሁላችንም የገባንበትን ግራ የተጋባ ሁኔታ በተለያየ መንገድ መግለጼን እና የራሴኑም ጭንቀት የሚያንጸባርቅ ጽሑፍ መሆኑን፤ ይህም ባሁኑ ጊዜ ለማንም የማይጠቅም መሆኑን በማስረዳት፥ ጽሑፉን አንብቦ ከጨረሰ በኋላ፥ ቀዳዶ እንደጣለው ነገረኝ።

መድህን ሃሳቤን ሁሉ የተረዳልኝ መሆኑን እና ኮዱ በሁለት ቀን ውስጥ ተዘጋጅቶ እንደሚደርሰን በማብሰር፥ "አይዞህ - አይዞህ" እያለ አደፋፈረኝ። በዚህን ጊዜ ቀለል አለኝና ተዝናናሁ፤ ኃጢአትን ከተናዘዙ በኋላ የሚገኝ፥ የምህረት ምልክት ይመስላል።

በነጋታው አዲሱን ዜና ለአሻግሬ ነገርኩት። እርሱም በጣም ደስ ብሎት አቀፈኝ። እኔም "ቆይ እስቲ፤ ሁሉ ነገር ሲሳካልን እዛው ጫካ እንተቃቀፋለን" አልኩት። እርሱም "ጓዴ እንደምታውቀው አውቶቡስ ጣቢያ ሄጄ ቲኬት መቁረጥ አልቻልም፤ አሁንም ተስፋዬ ባንተ ላይ ስለሆነ በርታልኝ" በማለት፥ የመጠራጠር ምልክት አሳይቶ ተሰናበተኝ።

ከመድህን ጋር በቀጠሮው ሰዓት ተገናኘን፤ ኮዱን ይዞልኝ መጥቷል። ይህ ኮድ ከበፊቱ የሚለየው ቀይ መስቀል በጥቁር መስቀል መተካቱ ነው። በልቤ “ይህስ ቀላል ነው” አልኩና መድህን ጣደፍ - ጣደፍ ብሎ ስለነበር፥ ብዙ ሳናወራ ካለወትሮው ቶሎ ተለያየን።

እኔም ወዲያው እዛው ከአውቶቡስ ጣቢያ ለማደር እየተጣደፍኩ ሄድኩ። ከቲኬት መቁረጫው ሁለት ሜትር ያህል ራቅ ብዬ ቁጭ አልኩ። ወዲያው አንድ ድሃ መሳይ ወደ ቲኬት መቁረጫው ሲጠጋ አየሁት። አካሄዱ ስላላማረኝ፥ ቶሎ ብዬ ቀደምኩትና ከቲኬቱ መቁረጫ መስኮት ሥር፥ ከግርግዳው በስተቀር ማንም እንዳይቀድመኝ አድርጌ ቁጭ አልኩ። እርሱም በንዴት “ሁለተኛነቴን ማን ይነፍገኛል!” በማለት፥ ከጎኔ ተጠግቶ ተቀመጠ። ትንሽ ቆይቶ ሌላ ሰው መጣ፤ አንድ አንድ እያለ ከምሽቱ ስድስት ሰዓት ላይ የቲኬት ገዢዎች (ብዙዎቹ ተከፍሏቸው ቲኬቱን እንዲገዙ የተላኩ የኔ ብጤዎች ናቸው) ሰልፍ ተገባደደ። ቆም ብሎ ቁጭ፥ ቁጭ ብሎ ጋደም፤ እንቅልፍ አልባ የሆነው የመኝታ ሰልፉ ተገባደደ።

ከምሽቱ 11 ሰዓት (5:00 AM) ላይ፥ ልክ እንደ ቤተ ክርስቲያን ጸሎት ብድግ - ብድግ ማለት ተጀመረ። እስከ ጧቱ ሦስት ሰዓት ድረስ ቆምን፤ አንድም ሰው በሰልፉ አንደኝነቴን የተዳፈረ ሳይኖር። ሦስት ሰዓት ተሩብ ሲሆን የቲኬት መቁረጫው መስኮት ተከፈተ። ከውስጥ ቲኬት ቆራጩ ጎረምሳ እጁን አሾልኮ የያዝኩትን ገንዘብ ተቀበለኝ። ለኔና ለአሻግሬ ሁለት ቲኬቶች በመግዛት ቲኬቶቹን በእጄ እንደጨበጥኩ፥ የአወቶቡስ ጣቢያው ድንገት በወታደሮች ተከበበ።

በአንጃዎች ጠቋሚነት፥ ከዛ ሁሉ ሕዝብ እኔን ብቻ መንጥቀው ለመውሰድ የመጡ መሰለኝና በቆምኩበት ደርቄ ቀረሁ። እግሮቼ ቀጥቀጥ - ቀጥቀጥ ማለት ጀመሩ። ሮጬ የማመልጥበት ስለሌለ፥ “አልሳሳም ለነፍሴ፤ የትግሉ ነው ሕይወቴ” የሚለውን የኢሕአፓ መዝሙር በልቤ መዘመር ጀመርኩ።

“ለዘመናት በጭቆና ማጥ፥

በግፍ ሰንሰለት ታስሬ፥

መብቴን ላስከብር፥

ጨቋኙን ልሽር፥

ተነስቻለሁ ዛሬ።

ይኸው ታጥቄአለሁ ዛሬ፤

ባንድ እንደሚነሳ፥

ጭቁን ሕዝብ ሁሉ፥

ለማያጠራጥር ድሉ፥

ፍጹም ነው እምነቴ፥

የትግሉ ነው ሕይወቴ፥

ልጓዝ በድል ጎዳና፥

በተሰዉት ጓዶች ፋና፥........”

አልጨረስኩትም። በልቤ ስዘምር ካለሁበት ቆሜ ቀረሁ። ወዲያው አንድ የሚሊታሪ ካድሬ የሚከተለውን መግለጫ ሰጠ።

“ከዛሬ ጀምሮ፥ ላልተወሰነ ቀን፥ የማመላለሺያ አውቶብሶች በጠቅላላ፥ ለአብዮታዊ ግዳጅ - ለአብዮታዊ ወታደሮች ወደ ሰሜኑ ጦር ማጓጓዣ ስለሚውሉ፥ አብዮታዊ ይቅርታን እየጠየቅን እናሰናብታችኋለን።”

ወታደሮቹ እኔን ለመያዝ አለመምጣታቸው ደስ ሲለኝ፥ በሌላ በኩል ደግሞ የአዲስ ሕይወት ጎዳና የሚከፍትልኝን አውቶቡስ በማጣቴ ጥልቅ ሃዘን ተሰማኝ። ይህ በሁለት ተቃራኒ ስሜቶች ውስጥ መዋጥ እኔነቴን ያሳጣኛል፤ ፈሪም ያስመስለኛል በማለት፥ ቶሎ ብዬ ወደ ጊዜያዊው እውነታ ውስጥ ገባሁና፥ የዛሬውን አሳዛኝ ዜና ለማርዳት ወደ ተለመደው ሻይ ቤት ገሰገስኩ። እንደ ደረስኩም አሻግሬ “ቲኬቱስ” አለኝ፤ አሳየሁት። ፈገግ ብሎ ሊስመኝ ሲል፥ አውቶቡሳቻንን በወታደራዊ ግዳጅ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀማን መሆኑን ነገርኩት።

ጓድ አሻግሬ ሰውነቱ ጭምድድ ሲልና ሲያዝን ሳየው፥ ምንው ባልተፈጠርኩ አሰኘኝ። እኛ ኮሙኒስቶች፡- ይህስ ከላይ (ከእግዚአብሔር) የመጣ ማለትን አንወድምና፤ መጥፎ አጋጣሚ እያልን ብቻ ተራገምን። ትንሽ ቆይቶ፥ ቀልጣፋው አሻግሬ ስለ ወደፊቱ ማሰብ ጀመረ። እኔ ደግሞ ስለ መጀመሪያው አውቶቡስ አለመሳካት እራሴን እየወቀስኩ አላዘንኩ።

“ከእንግዲህ ምንድነው ያለን አማራጭ?” አለ አሻግሬ። እኔም “በእግር መሄድ ወይም ሌላ ኮድ መጠበቅ ነዋ!” አልኩት። ሁለቱም እንደ ሰማይ ሩቅ መስሎ ታየን። የተዘጋጀልን የቀበሌ ወረቀትም አገልግሎቱን የሚጨርስበት ቀን ቀርቧል። ለማንኛውም የበላይ አካል የሚለውን እንስማ በሚል ሃሳብ ተስማምተን ተለያየን።

መሸት ሲል፥ መድህንን አገኘሁት። በዛሬው እለት የተፈጠረውን ስነግረው በጣም አዘነ። “ያጋጣሚዎች መደራረብ እኛን ችግር ላይ ሲጥለን፥ አንጃዎች ደግሞ ከደርግ ጋር በመሆን ፓርቲአችንን ለማዳከም ሲታገሉ፥ ሌላ ኮድ ለማዘጋጀት ምን ያህል እንደሚያስቸግር በቀላሉ ሊገባህ ይችላል! አይደለም?” አለ በቅሬታ እና በፍርኃት። ቀጥሎም፡-

“ካሁን በፊት እንደነገርኩህ፥ በመሥሪያ ቤት ጥቆማ ተካሂዶ፥ አንዳንድ ግለሰቦች ተይዘዋል። ይህንኑ ጉዳይ ለበላይ አካል አሳውቄ፥ ለኔ ደግሞ አማራጭ እስኪገኝልኝ ድረስ፥ እኔም እንዳንተ አንደር ግራውንድ (ራስን ከሕጋዊ ሰዎች በመሰወር መደበቅ) መግባት ይኖርብኛል፤ እስከዛውም ካልተበላሁ (ካልያዙኝ) ነዋ!” አለኝ መድህን።

እኔም በልቤ “ወይ ጉድ! በችግር ላይ ችግር ሲደራረብ፥ መጨረሻው ምን ይሆን?” አልኩ።

መድህን “ከእንግዲህ እኔ ኮንታክት (አገናኝ) ልሆንህ የምችል አይመስለኝም። ነገ ማታ ከዚህ ሥፍራ መጥተህ ባታገኘኝ፥ ችግር ውስጥ መግባቴን ትረዳዋለህ። ይህንን ስልህ፥ ሁኔታው ወደዛ እየገፋፋኝ መሆኑን ስለተረዳሁት ነው። በተቻለኝ መጠን ላለመያዝ እጥራለሁ። የበላይ አካል ይህንን የእኔን እና የእናንተንም ጉዳይ ያውቃል። እኔ ብያዝ ወይንም ብሰወር እንኳን፥ የኔ ኮንታክት (አገናኝ) በእኔ ፋንታ ያገኛችኋል። ስለዚሁ ጉዳይ ቀደም ብዬ ከበላይ አካል ጋር ተነጋግሬ ስለነበረ፥ ከእኔ አገናኝ ጋር የምትለዋወጡበት ኮድ (የምስጢር ቃል) ተሰርቶላችኋል። ስለዚህ ወደዚሁ ሥፍራ እንዲመጣ እነግረዋለሁ። ምልክቱም እንደሚከተለው ነው፡-

ልክ ከቀኑ 12 ሰዓት (6፡00 PM) ሲሆን፥ ከዚሁ ቡና ቤት ፊት ለፊት፥ ከመንገዱ በስተ ሰሜን በኩል፥ ጓዱ በቀኝ እጁ የጋዜጣ ጥቅል ይዞ፥ በጋዜጣው ግራ እጁን እየመታ ይቆማል። አንተም “ሰዎቹ አለፉ ወይ?” ስትለው፥ እርሱ ደግሞ “በባቡር ተሳፍረው ሄደዋል” ይልሃል። ይህ አንድም የምትለዋወጡበት ኮድ (የምስጢር ቃል) ነው፤ አንድም የኔን መያዝ የሚያነግርህ ነው” አለ መድህን።

መድህን ይህንን ሲናገር ድንግጥ አልኩ። “እንዴ!...” አልኩ በልቤ፤ “መድህን እጁን ሊሰጥ ነው እንዴ? እርሱም እንደ አንጃዎች?” በማለት፥ በፊቴ ላይ ጥቁር ጉም ሽው ሲል ተመለከተ መድህን።

እንኳን የፊቴን የጭንቅላቴንም የሚያነበው መድህን ነገሩ ገብቶት “አይዞህ፥ እንዴ አይዞህ! ካልተያዝኩ እኔኑ ነው እኮ ከዚሁ ሥፍራ የምታገኘኝ። ስታውቀኝ? እኔ

እጄን የምሰጥ እመስልሃለሁ? ተለውጬ አንጃ የሆንኩ መሰለህ? ኮዱን የሰጡሁህ ድንገት ከተያዝኩ ለእናንተ ለራሳችሁ፥ ለፓርቲውና ለቆምንለት ሕዝብም ሁለት ነፍስ ላትርፍ ብዬ፤ የሁኔታውንም አዝማሚያ ስመለከት፥ ምናልባት ያለኝ ቀን ዛሬ ብቻ ሊሆን ስለሚችል ነው። ምን ላድርግ? ተታኩሼ እንዳልሞት እንኳን ጠብ መንጃ የለኝ፤ ሽጉጥ እንኳን የለኝም..” አለ በቅሬታ።

እኔም “አይ አይደለም፤ እንዳው የወደፊቱን እያሰላሰልኩ ነው ሃዘን የገባኝ። አይዞህ፥ የሆነው ይሆናል” አልኩ በትካዜ።

መድህን “በል እንግዲህ ብዙ ማውራት አልችልም። እስከዚህ የደከምኩላችሁ በትግላችን አንፃር፥ የኔም የናንተም ነፍስ አንድ ናት ብዬ ነው። እና ያልኩህን ካለመጠራጠር አድርግ። በነገርኩህ መሠረት - ከቡና ቤት ፊት ለፊት፥ ከመንገዱ በስተ ሰሜን በኩል፥ ጓዱ በቀኝ እጁ የጋዜጣ ጥቅል ይዞ ስታይና ኮዱን ከተለዋወጣችሁ በኋላ፥ ምን ማድረግ እንደሚቻል ከጓዱ ጋር ትወያያላችሁ” በማለት፥ ጥልቅ በሆነ ቅሬታና ሃዘን በተቀላቀለበት ስሜት የመጨረሻ መልእክቱን አስተላልፎ ተለየኝ።

መድህን ጥሩ ጓደኛዬ ነበር። እግዚአብሔር ካንተ ጋር ይሁን እንዳልለው ኮሙኒስት ነኝ። “አጋጣሚዎች ተስተካክለው፥ ከአቸናፊው ሠፊ ሕዝብ ጋር በሰላም ይግጠመን” አልኩ፤ በመረረና በተዳከመ ድምጽ። ከዛም ተሳሳምንና ተለያየን።

በማግስቱ፥ ልክ 12 ሰዓት (6:00 PM) ሲሆን፥ የተባለው ጓድ ኮዱን እየሠራ ቆሞ አገኘሁትና፥ ኮዱን ከተለዋወጥን በኋላ ንግግር ጀመርን።

ይህ ጓድ (ጸጋዬ) በተክለ ሰውነቱ፥ በአለባበሱና በሁኔታው ሁሉ እንደጠበቅሁት ሆኖ አላገኘሁትም። እኔ የማውቃቸው የበላይ አካላት በብዛት በትምህርት የመጠቁ ናቸው። ይኸኛው ግን እንደነሱ አይመስልም። ጸጋዬ በሰውነቱ ኮሳሳ፥ የአለባበሱም ሁኔታ እንደ መለሰተኛ ድሆች አይነት ሆኖ፥ ሲያዩት የቀን ሠራተኛም ይመስላል። ይህ ጓድ ቀልጠፍ - ቀልጠፍ የሚል፥ ባላገርና ከተማ የሚመላለስ የመርካቶ ሰው ሳይሆን አይቀርም። አካባቢውን ሁሉ በቁጥጥሩ ያደረገ መሆኑ ከሁኔታው ያስታውቃል።

ኮዱን ከተለዋወጥን በኋላ፥ ጓድ ጸጋዬ እንዲህ አለ፤ “ከእንግዲህ ባጭር ጊዜ ውስጥ ይሳካል ብዬ ተስፋ አልሰጥህም፤ ያለህ እድል በትእግስት መጠበቅ ብቻ ነው፤ እኔን እንደ ጓዱ በየቀኑ ልታገኘኝ አትችልም። ቀጠሮም ልሰጥህ ያስቸግረኛል፤ ስለዚህ

ዘወትር በዚህ ሰዓት አካባቢ፥ እዚሁ ሥፍራ ፈልገኝ። ካለሁ አለሁ፤ ከሌለሁም የለሁም ማለት ነውና ብዙ አታንዣብብ" አለኝ።

እኔም "እሺ" አልኩና ስለ መድህን ሁኔታ የሚያውቀው ካለ ብዬ እንዲነግረኝ ጠየቅሁት። እርሱም "እንጃ! አላወቅሁም፤ ምናልባት ሳያመልጥ አልቀረም፤ ግን እኔ ይህንን በዚህ ሰዓት ማወቅ አልችልም። ወደናንተው ጉዳይ ብናተኩር ይሻላል" አለ ኮስተር ብሎ። ጸጋዬ ይህን ብቻ ተናግሮ፥ ካጠገቤ ጠፋ።

እኔም "ወይ ጉድ!" አልኩና፥ ወደመሬት አይኖቼን ተክዬ፥ የፍርኃት ሃዘን ተሰማኝና፥ እንደገናም ወደ ሰማይ አንጋጠጥጬ በተስፋ ተዋጥኩና፥ አምላክና አጋጣሚን አንድ ላይ አዋህጄ፥ "ሦስታችንንም (እኔን አሻግሬን እና መድህንን) ሜዳ ቢያገጣጥመን እንዴት ደስ ባለኝ!" አልኩ በለሆሳስ።

ከቀን ወደ ቀን አሻግሬን ለጥቂት ደቂቃዎች ከማግኘት በስተቀር ብቸኝነት እያጠቃኝ መጣ። በቀበሌ ውስጥ ካለ ሥራ መቆምና ማንዣበብ መታሰርን የሚያስከትል በመሆኑ፥ ያለው አማራጭ ቀኑን ሙሉ ሲዞሩ መዋል ነው። ይህ ደግሞ ያልተመጣጠነ ምግብ እየተመገበ ለሚኖር ሰው ያደክማል፤ አይቻልም። ጠላ ቤት በመግባትና ከዛ ቁጭ በማለት ነው ጊዜው የሚገፋው።

እንደ ጸጋዬ ቀልጠፍጠፍ የምል፥ የመርካቶ አራዳ ብሆን ኖሮ፥ እስከዛሬ ራሴን ከችግር ማውጣት ይቻለኝ ነበር እያልኩ አስባለሁ። ሰው የራሱን ጠባይ (ተፈጥሮ) በራሱ ይለውጠው ዘንድ እንዴት ይቻለዋል? እንዲህም ሆነ እንዲያ፥ በሕዝቦች መካከል ነው ያለሁት፤ ስለዚህ ራሴን ከራሴ ጋር ሙጭጭ አድርጌ በውስጣዊ ንግግር ብቻ አልወሰን፤ ከሕዝቦችም ጋር ላውራ አልኩ።

ሻይ ቤትና ጠላ ቤት እየገባሁ ከሕዝቦች ጋር አንድ ሁለት ቃል መናገሬ አልቀረም። ነገር ግን፥ እኔ በተፈጥሮዬ ብልጣ ብልጥ ስላልሆንኩ፥ ሦስትና አራት ቃል ከጨመርኩበት፥ የኢሕአፓ ወገን መሆኔን ለመረዳት አያስቸግርም በማለት፥ እራሴን እየደበቅሁ ከራሴ ጋር ብቻ ሳወራ ቀኑ ያልፋል።

አንዳንድ ጊዜ ለምታገልለት ሠፊ ሕዝብ የሚረዳ ሃሳብ አገኝ እንደሆን እያልኩ፥ ወሬ በጥሞና ለማዳመጥ ስሞክር፥ ፖለቲካ መሰል ካልሆነ በስተቀር፥ ወሬ ቶሎ አልገባህ ይለኛል። ሰው ቀልጠፍ - ቀልጠፍ ብሎ ሃሳብ ለሃሳብ ሲለዋወጥ፥ አንዱ ሌላውን ቶሎ - ቶሎ ይረዳዋል። አንዱ ተናግሮ ሳይጨርስ ሌላው ይቀጥላል።

የመርካቶ ሰዎች የእርስ በርስ የመግባባት ችሎታቸው እጅግ ከፍተኛ ነው። በወቅታዊ ኑሮአቸው ውስጥ ያለውን ጥቃቅን ሃሳቦችን መተረክ ያደጉበት ስለሆነ፥

ሲያወሩ የአማርኛን ቋንቋ ተራቀውበታል። መራቀቅ ብቻ አይደለም፤ ይህ ቋንቋ የተሰጠው ለእነርሱ ብቻ ይመስላል። ባይሆንማ ኖሮ ከሚያወሩት ውስጥ ለምን በብዛት አይገባኝም?

ከአንዳንዶቹ የሚሰነዘረውን ጥልቅና የሰላ አስተሳሰብ እኔ በድጋሜ ቀስ እያልኩ ሳመነዥገውና ብዙ ከቆየ በኋላ የወሬው ለዛ ሲገባኝ፥ “እነኚህስ እድል ቢያጋጥማቸው በአለም ከሚታወቁ ሳይንቲስቶችና ፈላስፎች እኩል የሚሆኑ ወይንም የበለጡ ናቸው በእውነት..” እላለሁ።

አንዳንድ ጊዜ ያነበብኳቸው የኢሕአፓና የአንጃዎች የልዩነት ዘገባዎች በአእምሮዬ ይመላለሳሉ። በተጨባጩ ሁኔታ አንጃዎች ያቀረቡት ዘገባ ብዙ ጠቃሚ ሃሳቦችን ያዘለ ስለመሆኑ ልክድ አልቻልኩም። ነገር ማክረር ባይኖር ኖሮ፥ በእነኚህ ጠቃሚ ሃሳቦች መጠቀም ይቻል ነበር።

እውነትም ኢሕአፓ ባለ ሁለት እውነት!! እውነትም ኢሕአፓ ባለ ሁለት እውነት!! ሰው እንዴት ለሁለት እውነት ይከፈላል። አባት በአስቸጋሪ ልጁ እንደሚናደድ፥ ፓርቲውም እንዲሁ በአንጃዎች ላይ አመረረ። ትንሽ እንኳ በጎ መንፈስ ቢኖር ኖሮ፥ የአባትና ልጅ መታረቅ ይህን ያህል አስቸጋሪ አይሆንም ነበር። ፓርቲው ሀ እና ለን በማግለል ፋንታ ለምን መታገስ አቃተው? በግለሰብ ደረጃ የሚወቀስ ማን ይሆን?

ኢሕአፓ የወቅቱንም ተጨባጭ ሁኔታዎች በማስመልከት፥ ሌላ ለየት ያለ ሃሳብ ከገዛ አብራኩ ሲመነጭ፥ በርዕዮተ አለም የከረረ አስተሳሰቡን ገታ ቢያደርግ፤ አንገቱን ዘንበል - ቀለስ አድርጎ፤ በጥሞና የሚያዳምጥ ቢሆን ኖሮ፥ ይህ ሁሉ ችግር አይደርስም ነበረ።

እውነት እና ትህትናን አብሮ ጨብጦ መያዝ የኢሕአፓ መሪ የነበረውን (ደብተራውን) ከመጣበት ከቤተ ክርስቲያን የሚመልሰው መስሎት ይሆን እንዲህ ያመረረው? አዎ! ትህትና በሃይማኖተኛነት እንጂ በኮሙኒስትነት አይገኝም (ይሆን?)። ፖለቲካ ማለትም የሰዎችን ከፋት በቃላት ሸንገላ ጥሩ የሚያስመስል እንጂ፥ ፍጹም እውነት ሊሆን አይችልም (ይሆን?)። እንጃ! አስቤ፥ አስቤ ለጥያቄዎቼ ሁሉ የማገኘው መልስ “እንጃ!” ብቻ ሆኖ ቀረ።

የሁለትነት ቀውስ የማይገባበት ሥፍራ የለም፤ ምንም እንኳን ፓርቲው የተሳሳተ መስመር ቢይዝም፥ እስከ መጨረሺያው በውስጥ መታገል ነው እንጂ፥ እርስ

በርስ መጣላትና መዋጋት፥ መፈረካከስን፥ መዳከምን፥ ብሎም እራስን ማጥፋትን እንደሚያስከትል እንዴት ፓርቲው (አንጃዎችም) ሊገነዘቡት አልቻሉም? አልገባኝም።

አንጃዎችስ ሠፊውን ሕዝብ በማስቀደም ፋንታ፥ አብረን ስንታገል የቆየናቸውን ጓዶች መግቢያ መውጫ ማሳጣት፥ እንኳን ከሰው ከእንስሳስ የሚጠበቅ ነው ወይ? አልገባኝም።

አንድ ትልቅ መጽሐፍ ከሚወጣው፥ በወረቀት ጽፈው ለአባላት ካስተላለፉት የፖለቲካ ምጥቀትና ፍልስፍና በግልጽ ከሚያንጸባርቅ ከሁለቱ (ከኢሕአፓና ከአንጃ) ዘገባዎች የሰው ልጅ የማሰብና የእውቀት ማማ ምን ያህል የመጠቀ መሆኑን ያሳያል።

ከዚህ ሁሉ የተራቀቀ እውቀት ባሻገር፥ የሰው ልጅ የእንስሳነት ጠባይ ተደብቆ ይሆን? የየትኛው እንስሳ ጠባይ ከየትኛው እንስሳ ጠባይ ይሻላል?

አዎ! እስከዛሬ ድረስ በአለም ዙሪያ እንዳየነው ከሆነ፥ አከራካሪውስ በእውቀት መበላለጥ የተነሳ አይደለም። አዎ! እስከዛሬ ድረስ በአለም ዙሪያ እንዳየነው ከሆነ፥ አከራካሪውስ በእውነቶችና በውሸቶች መካከል ባለው ልዩነት የተነሳ አይደለም። አዎ! እስከዛሬ ድረስ በአለም ዙሪያ እንዳየነው ከሆነ፥ አከራካሪውስ በሰዎች በውስጣቸው ያለ ተፈጥሮ (ልዩ ያልታወቀ ጠባይ) ነው። ምናልባት ይህም ከሰዎች ብቻ ሳይሆን፥ ከውጪ ከመናፍስት አለም የሚመጣ ሊሆን ይችላል። እንጃ! አስቤ፥ አስቤ ለጥያቄዎቼ ሁሉ የማገኘው መልስ "እንጃ!" ብቻ ሆኖ ቀረ።

የአስተሳሰብ ዝንባሌዬ በመሀል ተንጠለጠለ። ከግራ ወደ ቀኝ፥ ከቀኝ ወደግራ የሚያናፍሱ ሃሳቦቼ እኔን አንገላቱኝ። ግን ከአንጃዎች የወረስኳቸው አስተሳሰቦች ቢኖሩኝም፥ እስከሞት ድረስ በውስጥ ትግል እታገላለሁ እንጂ፥ ወይንም ትግሉን ትቼ ለጊዜውም ቢሆን ዞር እላለሁ እንጂ፥ እኔም ነፍሴን ለማዳን ብዬ፥ አንጃ በመሆን ተጠግቼ፥ የገዛ ጓዶቼን መልሼ አላጠቃም።

አንጃዎች ደርግ የሰጣቸውን ሥራ እርሱ እንደሚፈልገው ከሠሩለት በኋላ፥ ሌላ ሥራ ሊሰጣቸው አልፈለገም። እነርሱ በሥራቸው ሁሉ ደርግን አስደሰቱት፤ እርሱ ግን በሥራቸው አልሸለማቸውም።

አንጃዎች (ምናልባትም የአንድ ግለ ሰብ ድርጊት ይሆናል) ነፍሳችንን ይምራታል ብለው (ይሆናል?) በአንድ ጊዜ እስከ አምስት መቶ ሺህ ብር ከአባላት የተዋጣ የኢሕአፓ ገንዘብ ለደርግ አስረክበዋል (?)። ደርግ ግን ከእኔና ከጓዶቼ የተጠረቃቀመውን ገንዘብ ከኪሱ አስገብቶ፥ አንጃዎችን አላመሰገናቸውም፤

ነፍሳቸውንም አልማረላቸውም፤ እነርሱኑ አንድ ባንድ መልቀምና መግደል ጀመረ እንጂ።

የደርግ ፋሺስትነት (ወይም ፋሺስታዊነት) የእንስሳነት ጠባዩን በቀላሉ እንዲታይበት አደረገው። ሌሎችም አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ድርጅቶች አባሎች ለራሳቸው ሕሊና እንኳን የሚቆጫቸውን ሁሉ አደረጉ እንጂ፥ ደርግን ፋሺስት እንበለው ወይንም ፋሺስታዊ መንግሥት፥ ያው እርሱው ነው - ሰው የሚመስል አውሬ፤ ወይንም ሰው የሚመስል "እርኩስ መንፈስ"።

ሁኔታዎችን ለተከታተለ ከሚከተለው ጋር ተመሳሳይነት አለው:-ከእለታት አንድ ቀን፥ አንድ የተራብ አንበሳ አንድ ምስኪን አውሬ ይዞ እየበላ ሳለ፥ በጉሮሮው አጥንት ተቀረቀረበትና ተሰቃየ።

"እባካችሁ ከጉሮሮዬ የተቀረቀረውን አጥንት አውጡልኝ.." ብሎ እያሳዘነ ቢለምን፥ ደፍሮ አንበሳውን ለመርዳት የሚጠጋ ጠፋ። አንበሳው መላ ሲያጣ፥ እንዲህ አለ፡- "በጉሮሮዬ የተቀረቀረ አጥንት አለና፥ ይህን አጥንት ላወጣልኝ ሽልማት እሰጠዋለሁ።"

አሁንም እንስሳት ሁሉ ፈሩ። ግን አንድ የደፈረ ጀሬ አሞራ፥ ሽልማት አገኛለሁ ብሎ፥ ከአንበሳው ተጠጋና "እኔ አወጣልሃለሁ፤ በል አፍህን ክፈት" አለው። አንበሳውም "እሺ" ብሎ አፉን ከፈተለት። አሞራውም ከአንበሳው ጉሮሮ ውስጥ ገባና አጥንቱን አወጣለት።

አሞራውም "አጥንቱን አውጥቼልሃለሁና፤ ሽልማቴን ስጠኝ" ብሎ አንበሳውን ጠየቀው። አንበሳውም "ከአንበሳ ጉሮሮ አጥንት አወጣሁ ብለህ ማውራቱ፤ ይህ ላንተ ትልቅ ሽልማት ስለሆነ፥ ይህንኑ እያወራህ ኑር። ይህ ነው ሽልማትህ፤ በል ሂድ ካጠገቤ ጥፋ ሳልቦጭቅህ!" ብሎ አባረረው ይባላል።

እንዲያ ነው እንግዲህ፤ የማንም ሰው ጠባይ ከመንፈሳዊነቱ ይልቅ ምድራዊነቱ ካመዘነ፥ እንደ እንስሳ ሆኗል ማለት ነው። ሰው እርስ በርሱ ሲባላ፥ የማይጠግበውን የሥጋ ከርሱን ሲሞላ፥ ሞራላዊነቱን ረስቶ፥ እንስሳዊነቱን ሲያጎላ፥ ምን ይባላል? ያው ከመ እንስሳ። አዎ! ክፉ ቀን ሲመጣ፥ የረከሰው የሰው ልጅ ጠባይ በገሃድ ይታያል፤ ውሸታምና ከዳተኛም ይበዛል።

በፖለቲካ የተሰማራ ሁሉ፥ አንድ ባንድ፥ በሚከተለው የእንስሳዊነት ጠባዮ ረከሰ፡- ውሸታምነት (እንደ ፖለቲካ ታክቲክ እየተቆጠረ)፥ ራስን ወዳድነት፥ የሥልጣን ጥም፥ ክፋት፥ ውዳሴ ከንቱ፥ ስግብግብነት፥ ትምክህተኛነት፥ እብሪተኛነት፥

ጀብደኝነት..። የሰው ልጅ ይህን ሁሉ አስከፊ ጠባያት ተሸክሞ ሠፊውን ሕዝብ ሊያገለግል እንዴት ይቻለዋል? እንዴት ይቻለዋል? እንዴት ይቻለዋል።

ከላይ የተጠቀሱት እንደ ስድብ እና እንደ እርግማን ያሉ ክፉ ነገሮች ለክፉ ሰዎች ነው እንጂ፥ በውስጣቸው ጥሩዎች ሆነው በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ፥ ካላሰቡት ጎዳና ገብተው ከማይፈልጉት ሥፍራ እራሳቸውን አግኝተው፥ በገዛ ሥራቸው የሚጸጸቱና የሚያዝኑ ብዙዎችን አይመለከትም። ለነገሩ ከሃይማኖት መጻሕፍት ያላነሰ ሞራል የሚያስተምር፥ የፓርቲ ዲሲፕሊን በሚል በእንግሊዝኛ የተጻፈ፥ እንዲሁም በአማርኛ የተተረጎመ ጽሑፍ ለብዙዎቻችን ተዳርሶ አንብበነዋል። ለነገሩ ይህንን የፓርቲ ዲሲፕሊን የሚከተሉ የኢሕአፓ አባላት በንግግራቸው፥ በጠባያቸውና በተግባራቸው ሁሉ፥ ከአንድ ቄስ ያላነሰ ትህትና ነበር የሚያሳዩት። እነ ዴሞክራሲያ ሲያስተላልፉ የነበረው መልዕክት ከሐዋርያቶች መልዕክት በምን ያንስ ነበር? ምን አይነት እርኩስ መንፈስ መጥቶ ነው የበጠበጠን? መሪዎቻችን እንዴት ከዱን? እንዴት ከዱን።

ሃይማኖተኞች እጹብ ድንቅ ለሆነ፥ ፍጹም እውነት ለነገሠበት ሀገረ ሕይወት ይታገላሉ። አዎ! አዎን! እኔም ደፋር ነኝና፤ ወደ ባላገር ገብቼ የምታገለው:- ይህ ትውልድ እውነትን ባያገኝ፥ የኢሕአፓዎች እውነት ለሚቀጥሉት ትውልዶች ተላልፎ፥ በኢትዮጵያ ምድር የኮሙኒስት ስርዓትን (ምድራዊ ሀገረ ሕይወትን) እንዲያገኝ ለማድረግ፤ የሰውን ልጅንም መጥፎ ጠባያት ለማጥፋት (ለመቀየር) ነበር። አለዚያማ እንዴት ይሆናል? ጥንትስ የፊውዳሎችና የአሪስቶክራቶች ጠባይ አይደለም እንዴ ሠፊውን ሕዝብ መቀመቅ የከተተው? የእነርሱ ሆዳምነትና አልጠግብ ባይነት አይደለም እንዴ ሕዝቡን ያደኸየው? የእነርሱ ማናለብኝነት አይደለም እንዴ ሰብአዊ ሙብትን የጣሰው? የእነርሱ አምባገነናዊ ጠባይ አይደለም እንዴ ሕዝቦችን ረግጦ መግዛት፥ ጭቆናና ምድራዊ ስቃይን ሁሉ ያስከተለው? ነው እንጂ።

ይገርማል፤ አንዳንድ ሰዎች ኢትዮጵያን በሙሉ፥ ሁለመናዋን ማየት ያቅታቸዋል። አብዛኛውን ሠፊ ሕዝብ ወደ ጎን ያደርጉና፥ ጥቂት የበለጸጉና የደረጁ ሃብታሞችን ብቻ መላ ኢትዮጵያን እንደሚወክሉ አድርገው ይቆጥራሉ። የደላቸው፥ የተመቻቸው ቱጃሮችን መቼ አጥታ ታውቃለች ኢትዮጵያችን? የኢትዮጵያ ቱጃሮች በቁጥር ጥቂቶች ናቸው። ኢትዮጵያችንን የሚወክሉ፥ ብዙኃኑን የሚወክሉ ድሆቹ ናቸው እንጂ፥ ጥቂቶቹ ቱጃሮች ብቻ አይደሉም። አዩ! የትግላችንን ይዘት የተረዱልን ጥቂቶች መሆናቸው ያሳዝናል።

በአንድ ሀገር ውስጥ አንድ ዜግነት ያለው ሕዝብ ለሁለት ተከፍሎ፥ አንዱ በዪ ሌላውም የበዪ ተመልካች ሲሆን፤ አንዱ የተንደላቀቀ ኑሮን ሲኖር፥ ሌላው በድህነት ሲማቅቅ። እንዲህ ያለውን አስከፊ ስርዓት በመለወጥ፥ አብዛኛው ሕዝብ በልቶ የሚያድርበትን፤ በሕብረተሰቡ መካከል እጅግ የተራራቀ የኢኮኖሚ መበላለጥ የማይታይበትን ስርዓት ለመመስረት ነው ኮሙኒስትነት ያስፈለገው። ይህ በሌላ መንገድ ከመጣም መልካም ነው። ለጊዜው ግን፥ እኛ ያጋጠመን፥ ከደጋግ ፈላስፎች የወጣ ጽንሰ ሃሳብ፥ ለተሻለ የሀገር አስተዳደርም ይሆናል ብለን ያሰብነው ርዕዮት ይህንን ነው።

አንዳንድ ሰዎች ኮሙኒስትነትን ሲያጥላሉ፥ የኮሙኒስት ስርዓት አያበለጽግም፤ አያሳድግም ይላሉ። እውነት ነው፤ የኮሙኒስት ስርዓት ድሆችን ከወደቁበት ሲያነሳ፥ አህጉራዊ ሃብትን ሲያደላድል፥ ለሁሉም እንደ ሥራውና እንደ ችሎታው ሲያከፋፍል፥ ብልጽግና እና የእድገት እመርታ ጎልቶ በአጭር ጊዜ ውስጥ ላይታይበት ይችላል።

ታግሎ ታግሎ፥ ከትግሉም በኋላ በአሸናፊነት ብቅ ሲልና ሀገር መገንባት ሲጀመር፥ በኮሙኒስት ስርዓት የተዋቀረ ኢኮኖሚ እንደ ካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ ቶሎ አያድግም ይሆናል። ሆኖም፥ ጊዜ ይፍጅበት እንጂ፥ የኋላ ኋላ፥ በከፍተኛ ደረጃ ማደጉ፥ መደርጀቱ አይቀርም። እድገቱም፥ ብልጽግናውም የጋራ (የሕዝብ) ይሆናል እንጂ፥ የጥቂት ግለሰቦች ብቻ አይሆንም።

አንዳንድ ሰዎች ኮሙኒስትነትን በእግዚአብሔር ካለማመን ጋር ያገናኙታል። የእግዚአብሔር መቀመጫው አንድም በሁሉም ሥፍራ ነው፤ አንድም እኛ በማናውቀው በመንግሥቱ ነው፤ አንድም በአንጎላችን (በልባችን) ውስጥ ነው። ከእነዚህ ውስጥ አንዱንም የማያምን ሰው ሊኖር አይችልም።

የግለሰብ ሃይማኖት ሰብአዊ ዴሞክራሲያዊ መብት ስለሆነ፥ ይህንን መብት የሚያሳጣ የኮሙኒስት ስርዓት ቢኖር፥ እድሜው አይረዝምም፤ ቢኖርም፥ እንዳውም ገና ከጅምሩ ቅጭጭ ብሎ የሚጠፋ ነው የሚሆነው።

ዝብርቅርቁ የሰው ልጅ ጠባይ ወደ ጥሩነት ሲለወጥ፥ የዛን ጊዜ በእግዚአብሔር የማያምን እንደ መጥፎ ሰው ይቆጠራል። ኮሙኒስትነት እና ጥሩ ሰው መሆን አይለያዩም። ስለዚህ፥ የኮሙኒስት ሕብረተሰብ በምድራዊነቱ ከፍተኛ ደረጃ የሚደርሰው፥ በመንፈሳዊነቱ ከፍተኛ ደረጃ ሲደርስ - ራስ ወዳድነትን አስቀርቶ፥ በእኩልነት እና በጋራ ብልጽግና አብሮ መኖር ሲጀምር ነው።

የኮሙኒስትነትን ጽንሰ ሃሳቡን እንደ መጥፎ የሚቆጥሩት ሰዎች፥ አንድም ባለማወቅ ነው፤ ወይንም፥ ጽንሰ ሃሳቡ ጥሩ መሆኑን ቢቀበሉትም፥ "የሰው ልጅ በተፈጥሮው የማይደርስበት፤ በተግባርም ሊተረጎም የማይችል፤ እንደማይጨበጥ ደመና ነው" ይላሉ። አዎ! እውነት ነው። ሕብረተሰባዊነትን (ሶሻሊዝምን) መንገዱን[14] ይዘን እስከምንደርስበት ድረስ እንጓዝ አልን እንጂ፤ ፍጹም የሆነውን ኮሙኒዝምን የሰው ልጅ ይደርስበታል ብለን አላሰብንም። አዬ! ብዙ ባናውቅም፥ ካስተዋልነው ብዙ፥ የታዘብነውን ጥቂቱን በሚከተለው ሃሳብ ላይ መቋጨት ይሻላል፦

ብቃት በሌለው አእምሮ ፍጹም እውነት ሰርጎ አይገባም፤ ወይንም ብቃት ያለው አእምሮ ፍጹም ያልሆነውን እውነት አይቀበለውም። የሁለቱም ውጤት ያው ነው - እንዲሁ እየተናቆሩ እድሜ መፍጀት። ገና ከጥንቱም፥ የምድራዊነት መንፈስ አእምሮአችንን አበላሽቶት ሳለ፥ የሰውን ልጅ ወደ ጥሩው መምራት ቀላል አይሆንም። ማን የማንን የተበላሸ አእምሮ ያክማል (ያስተካክላል)? የሃይማኖት መሪዎችም ቢሆኑ፥ እንዳው መስበክ፥ መስበክ፥ መስበክ ብቻ ነው እንጂ፥ እነርሱው የሚሰብኩትን በሥራ ተርጉመው ሕብረተሰቡን ሲያክሙት አይታዩም።

አዎን! መጥፎውን ሁሉ የመቀበል ችሎታ ያለው አእምሮ፥ ከመጥፎው ጋር ደስ ብሎት መኖርን ያውቅበታል። ሌሎቻችንም "ከክፉ አሳቤዎች - ከማይጠቅሙ ሃሳቦች" ጋር እየተጣላን፥ የሕብረተሰቡንም ተቋም ወደ ጥሩው ለመለወጥ እየታገልን፥ ወይንም እንዲሁ እየቆዘምን እንኖራለን። ነገር ግን፥ ለሰው እድገቱ ገደብ የለሽ ስለሆነ፥ የወደፊቱ እንዳሁኑ እንደማይሆን እናውቃለን።

ብዙ የደረቁ እውነቶቼ እኔን የተለየ ሰው እንዳያስመስሉኝ፥ ምናልባትም ወደ "ሌላ አለም" ከመሸጋገር ተርፌ እዚችው ከቀረሁ ጉዳት ላይ እንዳልወድቅም እየፈራሁ፤ ይህንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች እንደ ልማዴ ጻፍኩ። እራሴኑ በገዛ እውነቶቼ ብጠምደው፥ ከእውነት አልርቅም (አላብድም) ስል ነበር የምጽፈው። አዎ! ሰው ሆኖ ለተፈጠረ፥ ማንኛውም ወሬ - ንግግር (ከሰው ጋርም ቢሆን፥ ከራስ ጋርም ቢሆን)፥ በጣም አስፈላጊ ነው። ሰው ከሰው ጋር ካልተነጋገረ፥ ከወረቀት እና ከመጻፊያ እስክሪፕቶ ጋር ቢነጋገርም አይከፋም፤ ይሻላል።

***<u>መጠነኛ ህመም</u>***

በየቀኑ 12 ሰዓት ሲሆን ጸጋዬን ከተባለው ሥፍራ እየሄድኩ መመልከቴን አላቋረጥኩም። ቀን ቀን በሃሳብ እወጠራለሁ፤ ማታ ማታ ደግሞ በሕልም እና በቅዠት

[14] ሶሻሊዝም ወደ ኮሙኒዝም በሚወስደው መንገድ ላይ አንዱ ምዕራፍ ነው።

ሌላ አለም ውስጥ እገባለሁ። በህልሜ የማየውንና በእውን የማየውን ለማስታረቅ አልቻልኩም፤ ጤንነቴም እየታወከ መጣ (ኤጭ)።

አሻግሬም ለጥቂት ቀናት ጠፍቶብኝ ነበር። ከእለታት አንድ ቀን፥ ሻይ ቤት ተገናኘንና ጨዋታ ጀመርን። ይኸኛው ሻይ ቤት በጣም ትልቅ እና ተወዳጅ ስለሆነ፥ ብዙዎች ይገቡበታል። ከወትሮው የተለየሁ ሆንኩበት። አትኩሮ እያየኝ፥ አንዳንዴም ጎንተል እያደረገኝ ተጨዋወትን። "ደህና ነህ ወይ?" ይለኛል፤ እኔም "ደህና ነኝ" እለዋለሁ።

እኔ ግን ድምጽ የተባለ ሁሉ አንድ አይነት ሆኖብኛል። የሰዎቹ ጩኸት ከማንኪያዎች፥ ከብርጭቆዎች፥ ከወንበሮችና ሌሎችም የሻይ ቤት ኳኳታዎች ጋር ተደበላልቆ፥ የትኛው የየትኛው ድምጽ መሆኑን መለየት አቅቶኛል። እንደ ወንዝ ጎርፍ ኹው ኹው ይልብኛል። ድምጽ የተባለ ሁሉ እንደ አንድ ከፍተኛ ሞገድ ከፍና ዝቅ ሲል፥ በጠፈር መንኮራኩር የዘለአለማዊ ጉዞ እንደሚጓዝ ሰው የሆንኩ ይመስለኛል።

አሻግሬ ሲያወራ፥ አዎ! አዎ! ማለቱ ሰለቸኝና "ከዚህ እንውጣ! ከዚህ እንውጣ!" አልኩት (አሁንም በልቤ ኤጭ እያልኩ)። እንደወጣንም "ጺጋዬን ካገኘሁት ሰንበት ብሏል፤ ምናልባት ዛሬ ማታ ሳላገኘው አልቀርም" አልኩት። እርሱም፤ "እንዴት እርግጠኛ ልትሆን ቻልክ? በሕልምህ አይተህ ነው?" ብሎ ቀለደና፥ ልንለያይ ስንል፥ "ለመሆኑ ደህና ነህ? እባክህ ንገረኝ?" በማለት አጥብቆ ጠየቀኝ። እኔም "አይዞህ ደህና ነኝ፤ ምን እሆናለሁ ብለህ ነው? ትላንትና በደንብ ስላልተኛሁ ደክሞኝ ነው" አልኩት።

አሁንም በጥርጣሬ መልክ ሲመለከተኝ ጊዜ፥ ፊቴን ኮስተር አድርጌ፥ ክርር ባለ ንግግር "ስማኝ ልንገርህ ወዳጄ ጓዴ" አልኩት።

"እኔኮ ሀገር ለቆ እንደሚወጣ ስደተኛ፥ መሃል አዲስ አበባን ተሰናብቼ መርካቶ ስገባ፥ ጓዶቼ በቆራጥነት የታገሉበት ክልል ውስጥ መሆኔን አልረሳም። መርካቶን ነጻ ባናወጣትም፥ በደርግ ቅኝ ግዛት ውስጥ ገና አልገባችም። ይህንን አውቃለሁ፤ በተጨማሪም ተዋድቀው የወደቁት ጓዶቻችን መንፈስ አብሮኝ አለ። በከንቱ የፈሰሰው ደም ይታየኛል፤ የሠፊው ሕዝብ ጩኸት ከሻይ ቤቱ ጩኸት በልጦ ይሰማኛል። የሁላችንም የትግል መንፈስ ወደፊት እንጂ፥ ወደኋላ አያስመለከተኝም። መርካቶም ቀረሁ ወይም ጫካ ገባሁ፤ ይህ መንግሥት ከመለወጡ በፊት የማልመለስ መሆኔን ለራሴ ቃል ኪዳን ገብቼአለሁ። ይህን ቃል ኪዳን እንዳጥፍ የሚያደርገኝ ምንም ምድራዊ ኃይል አይኖርም..." አልኩት።

እርሱም ቀበል አደረገና፥ ሳቅ ሳቅ እያለ፥ "እኔኮ ቆራጥ ታጋይ መሆንክን በመጠራጠር አልነበረም የጠየቅሁህ፤ ሁኔታህን ስመለከተው የታመምክ መስሎኝ፥ ስለጤንነትህ ጠየቅሁህ እንጂ!" አለ።

"ደህና ነኝ" አልኩት። እርሱም "በል በርታ፥ በጸጋዬ በኩል ተስፋ ከመጣ እንድትነግረኝ፥ ነገ ከዚሁ ሻይ ቤት ተመልሼ እመጣለሁ" ብሎኝ ተለያየን።

**ሦስተኛው ሙከራ**

በነጋታው መሸት ሲል (12 ሰዓት) ጸጋዬን ከዚያው ሥፍራ አገኘሁት። የሥራ ጉዳይ ስለሆነ፥ በሰላምታ ልውውጥ ጊዜ ማጥፋት የለም። ወዲያውኑ የቀበሌ ወረቀቱን ለእኔና ለአሻግሬ ያዘጋጀ መሆኑን ነገረኝ። አስቀድሞ የገዛሁትን የአውቶብስ ቲኬት ይገፔዋለሁ። "አዎ! ይገፔዋለሁ፤ ስለዚህ፥...አዎ! ሁለተኛ እዛ (አውቶቡስ ጣቢያ) ሄዶ ማደር አይጠበቅብኝም..." በማለት፥ ይህንን ለጸጋዬ አረጋገጥኩለት።

ጸጋዬ ካለወትሮው እጅግ ጣደፍ ጣደፍ ብሎ "ኮዱ የተዘጋጀ ስለሆነ፥ ከነገ ወዲያ ሁለታችሁም አውቶቡስ ጣቢያ በመምጣት እዛው እንገናኝ" አለ።

በማግስቱ ይህን የምስራች ለአሻግሬ ነገርኩትና ታላቅ ደስታ ሆነ። በተባለው ቀን ሁለታችንም አውቶብስ ጣቢያ ሄድንና፥ ጸጋዬን ከዚያ ቆሞ እኛን ሲጠብቅ አገኘነው።

ጸጋዬ ሹፌሩንና ረዳት ሹፌሩን (አውቲስታውን) ያውቃቸዋል። በዚያ አካባቢ ጸጋዬን የማያውቅ ሰው የለም፤ ከሁሉም ጋር ያወራል፥ ይቃለዳል (ይጫወታል) ይስቃል፥ ያስቃልም።

ጸጋዬ አውቶብሱ ውስጥ እንድንገባ ነገረን። "መቼ ኮዱን ነገረንና?" እያልኩ ብዙ ሃሳቦችን ማብከንከን ጀምሬአለሁ። "ምናልባት ብንቀርና ኮዱን ለደርግ አሳልፈን ብንሰጥ፥ የሚከተለውን ችግር በመመልከት ይሆናል አውቶቡሱ ውስጥ እስክንገባ የጠበቀው" ብዬ አሰብኩ።

"ግን እንዴት ይህን ያህል ሊጠራጠረን ቻለ?" በማለት የማይታሰበውን ሁሉ እንዳስብ የሚያደርገኝ አንድም ሁኔታው ሲሆን፥ ሌላም እኔና አሻግሬን በደንብ ስለማያውቀንና ስለማይተማመንብንም ሊሆን ይችላል ብዬ አሰብኩ።

ጸጋዬ አውቶብሱ ውስጥ ከገባን በኋላ፥ ያንን በጉጉት ስንጠብቀው የነበረውን ኮድ ነገረን። ጸጋዬ የተጠራጠረው ነገረ ያ<u>ለ</u> መኖሩ ከሁኔታው ያስታውቃል። "አይዟችሁ! ዛሬ ባይሳካ ነገና ከነገ ወዲያ ሊሳካ ይችላል፤ ከሦስት ቀን በላይ ከሆነ ግን፥ ኮዱ መለወጥ ይኖርበታል" ሲለን፤ እኔና አሻግሬ በስርቆሽ አይን ለአይን እየተያየን ድንጋጤአችንን እየተጋገዝን ለመሸፈን ሞከረናል።

ሹፌሩ እንደልማዱ የአውቶብሱን ሞተር ለማሞቅ አስነስቶ፥ እርሱ ከውጪ ወጥቶ ቆሟል። ከመኪናው ሞተር ጩኸት በስተቀር፥ ትንፍሽ የሚል የለም። ብዙ ጊዜ ጠፍቶ የተገኘን አውቶብስ በናፍቆት ሲጠባበቅ የነበረ ተሳፋሪ፥ ሁሉም በሃሳብ ጭልጥ ብሎ ሄዷል።

ጺጋዬም ካጠገባችን አልራቀም፤ ከዚህ በኋላ እርሱን ማግኘት እንደማይቻል፥ ከአውቶብሱ ሳይወጣ ጠቆም ለማድረግ ፈልጎ፡- "እንግዲህ ይህም ካልተሳካ፥ እ፥ እ፥ ..." ሲል፥ ምን ማለቱ እንደሆነ ገባኝና፤ "ከዛው ሥፍራ?" አልኩት። እርሱም "ሞከር" ብሎኝ ተለየን።

እኔና አሻግሬ ጎን ለጎን ተቀምጠን፥ የአውቶብሱ ጎማዎች በቶሎ ሥራቸውን እንዲጀምሩ በጉጉት በመጠባበቅ፥ ካሁን አሁን ተነሳ ስንል ጊዜው እጅግ ረዘመብን። የሁለታችንም የማውራት ችሎታ ወደ ሃሳባችን ተቀይሮ፥ ስለ ወደፊት ትግላችን በድምጽ አልባ ንግግር የምንለፈልፍ ይመስላል።

ሹፌሩ አውቶብሱ ውስጥ ገብቶ ራሱን መቀመጫው ላይ በማስተካከል ላይ እንዳለ፥ አንድ ሰው እየሮጠ መጣ። ሹፌሩን ለሁለት ደቂቃዎች ካነጋገረው በኋላ ሄደ። ሹፌሩም ወደ ተሳፋሪዎቹ ዞር በማለትና ሃዘን በተሞላበት አነጋገር እንዲህ አለ፡-

*"አውቶቡሱ ለአብዮታዊ ግዳጅ የሚፈለግ ሰለሆነ፥ በተቻለ ፍጥነት እንድትወጡ ትለመናላችሁ።"*

ወዲያውኑ ሁሉም ጭጭ ብሎ፥ ውልቅ ውልቅ እያለ ወጣ። አንድ ያጉረመረመ ወይንም የብስጭት መልክ ያሳየ አልነበረም። እንዲህ አይነት ታዛዥነት (ፍጹም መገዛት) ከየት መጣ? እውነትም የሰውን ልጅ ተፈጥሮ የጠብ መንጃ ኃይል ይለውጠዋል! አልኩ በልቤ።

እኛም ከአውቶቡሱ ወጥተን፥ አይዞህ! አይዞን! ተባባልን። እኔም አሻግሬን ሳጽናና፥ "እንግዲህ አይዞን። ጺጋዬም አይዟችሁ፤ ዛሬ ባይሳካ ነገና ከነገወዲያ ሊሳካ ይችላል" ብሎናል አልኩ። አሻግሬም "ያ የፈረደበት የባላገሩ ጓዳችን እስኪያገኘን ድረስ በተባለው ሰዓት በየቀኑ ኮዱን ይሠራል ማለት ነው። እንዲሁ ኮዱን እየሠራ ለስንት ቀናት ይጠብቀናል ማለት ነው? ግፋ ቢል ለሦስት ቀናት እንጂ እኮ ነው!..."።

እኔም "ትግላችን ረዥም፤ መንገዱም ጠመዝማዛ፤ ተስፋ መቁረጥ የሰው ልጅ ካሰበበት እንዳይደርስ እንቅፋት ነው። አዪ!.......ቢሆንም እንበርታ። እንግዲህ ከዛው ሻይ ቤት በየቀኑ እንገናኝ፤ አንድ ሁለት ቀን ብንቆይም ምንም አይደል፤.." አልኩ።

በሃሳብ መዋጥና መቆዘምም የሚመቸው ለየብቻ ሲሆኑ ነውና፤ "በቃ እንግዲህ እንደወትሮአችን እንገናኝ"ተባብለን ተለያየን። ከዛም በኋላ እየተገናኘን፥ በየቀኑ የአውቶብሱን ሁኔታ መከታተል ቀጠልን። አንድ ሳምንት አለፈ፤ ግን ሁኔታው አልተቀየረም። የኤርትራ ጦርነት ከምን ጊዜውም የበለጠ እየተፋፋመ በመሄዱ፥ አውቶብስ ማግኘት አልተቻለም።

## ሚሊሺያ

በየቀኑ ከየባላገሩ እየታፈሱ የሚመጡት ወጣቶች “ታጠቅ” የተባለው ጦር ሰፈር ይገቡና ጥቂት ሰልጥነው፥ “ሚሊሺያ” የሚል ስም እየተሰጣቸው፥ ወደማያውቁት፥ የሽምቅ ውጊያ ወዳለበት ወደ ኤርትራ በረሃ ይወሰዳሉ።

ባላገሮች (በብዛት የኦሮሞ ተወላጆች) ከሚስቶቻቸው ተለይተው - ከዘመዶቻቸውም ተገንጥለው ከግብርና ሥራ ወደ ውትድርና (ሚሊሺያነት) ሥራ ሲሸጋገሩ፥ “ሀገራችንን ከውጪ ጠላት እንከላከላለን” በሚል መፈክር ነበር።

ወጣት ገበሬዎች፥ ከቤተሰቦቻቸው ተነጥለው ከግብርና ሥራቸውም ተፈናቅለው፥ በግዳጅ “ታጠቅ ሰፈር” ይገባሉ። በሞፈር እና ቀንበር ፋንታ ጠብመንጃ ይጨብጣሉ። በውትድርናም ሰልጥነው፥ ሚሊሺያ እየተባሉ ከሩቅ ሥፍራ (ኤርትራ እና ትግራይ) ይዘምታሉ፣ ከዚያም እነርሱ ቀባሪ አጥተው በየሜዳው ሲቀሩ፥ የመጡበት መሬት ጦሙን ያድርና ቤተሰቦቻቸው በረሃብ ይሰቃያሉ።

ኤርትራ እስክትገነጠል ድረስ ይህ የማያቋርጥ ክስተት ነበር። በየቀኑ አዳዲስ የሚሊሺያ ምሩቆች አውቶብሱ ውስጥ ሲገቡ፥ ሌሎችም ሲከታተሉ፥ የኤርትራ በረሃም ለነኛው ለባላገሮቹ - ለወጣት ገበሬዎች “የመጨረሺያ ማረፊያ ሥፍራ” ሲሆን፤ ብዙ ሰው ግራ በመጋባት ሲያዝን፥ የእናት፥ የእህት፥ የሚስት ሃዘን ምርር ሲል፥ ጠቅላላ ሕብረተሰቡ የኤርትራን መገንጠል እስከመደገፍ ደረሰ።

ፖለቲከኞችም ታሪካዊ ክስተቶችን ሲጠቅሱ፥ ስለ ሰው ዘር እና አመጣጡ ይረሱና፥ በጊዜአዊ ችግር ላይ ብቻ ያተኩራሉ። ኤርትራም እንደ ሕዝብ እራሴን በራሴ አስተዳድራለሁ በማለት ብትነሳ፥ ካለ በቂ ምክንያት አይደለም። ከኢትዮጵያ ማሕበረሰቦች ውስጥ፥ ኤርትራ ብቻ ናት ለመገንጠል የሚያበቃውን መሥፈርት ሙሉ በሙሉም ባይሆን፥ ከሞላ ጎደል የምታሟላ። ኢሕአፓም ይህንን ስለሚያውቅ፥ የኤርትራን ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት ያከብራል። የኤርትራን መገንጠልን ባይደግፍም፥ የሕዝቡን ፍላጎት አይቃረንም። የሕዝብን የመገንጠል ዴሞክራሲያዊ መብት ማን ደፍሮ ይነጥቃል? ማን በጉልበቱ የበላይነቱን ማሳየት ይችላል? የደርግ መንግሥት ግን፥ በሰላም ከመደራደር ይልቅ ጦርነትን መረጠ።

**<u>የሚሊሺያ ሚስቶች እና የእናቶች ፍቅር ሲገለጥ</u>**

የእኛ ሴቶች፥ ሚስቶች፥ እናቶች፥ የዘወትር ወሬዎቻችን በቤተሰብ ዙሪያ የሚያጠነጥን የሚሆንበት ምክንያት፥ የህብረተሰብ ሥር መሠረት በመሆናችን መሆኑን ብዙዎች ይዘነጋሉ። የኛ ፍቅር እስከ ራስን መሰዋት እንደሚደርስ ያወቀልን የለም።

የኢትዮጵያ ታሪክ የሁሉም ዜጎቿ ታሪክ ተደምሮ በጥቅሉ ሲነገር ነው እንጂ፥ የአንድ ንጉሥ ወይም የግለሰብ ታሪክ ብቻውን አይደለም። ሠፊው ሕዝብ እንዲሁ ሳይወራለት ይተዋል፤ አንዱ ብሄር ከሌላው እበልጣለሁ ይላል፤ የገዢውም መደብ የራሱን ብሄር ከሌላው ያስበልጣል።

ወጣት ፖለቲከኞችም ከኛ ጉያ ወጥተው ወደማይውቁት ሥፍራ ይሄዳሉ። ቀዝቃዛውና ፍቅር አልባው ምድራዊነት ይበርዳቸውና ይታመማሉ። የዛን ጊዜ የእነርሱ ፖለቲካ ብቻውን መድህን የሚሆናቸው ይመስላቸውና፥ ወደ ጦርነት ውስጥም ሲገቡ ምን እንደጎደላቸው አያስተውሉም። አንዳንድ ጊዜ፥ ስለ ሀገር ጉዳይ ሲነሳ፥ እሳት እንዳቃጠለው ሰው እየተንገበገቡ መለፍለፍ ያበዛሉ። ነጻነት በእኩልነት እንደሚከበር፥ የእርስ በርስ ፍቅር ሲቀንስም ሰላም እንደሚደፈርስ ቢያስቡበት፥ ጦርነትን ለችግሮች ሁሉ እንደ መፍትሄ ከማድረግ ይቆጠቡ ነበር።

አዬ! ባሎች፥ አዬ! ባላገሮች፥ አዬ! ወጣት ምልምሎች...በሉ ሂዱ እንሸኛችሁ፤ እግዚአብሔር ይጠብቃችሁ (ቶሌ፤ ዴሚ፤ ዋቃ ሲሃኤጉ)።

ከቡሬ - ከቡሬ

የኢትዮጵያ ባላገር፥

የታጨህበት ሚሊሺያ፥

የመቃብር ስምህ ወታደር፤

በል ደህና ሁን፥

ካውቶብሱ ተሳፈር።

ልትዘምት ነውና፥

ወደ ኤርትራ - ወደ ዘመዶቼ ሀገር፤

ልትዘልቅ ነውና፥

ወደ ትግራይ - ከወገኖቼ መንደር፤

በል ሂድ! እኔ ችዬ አንተን አላስቀር።

የእኔስ ነገር ቢቀር ይሻላል ባላስበው፥
የውስጤን ጦርነት ማንም የለ የሚረዳው፤
ሰላሙን እንዲያውርድልን ጸሎቴ ነው።
በል ሂዳ! በጠብ መንጃያህ ፍቅርን ዝራ፥
አንዲቷ ሀገራችን በሕዝቦቿ እንድትኮራ።
ታዲያ፥ ወደ ሰሜን - ሜዳ ሜዳውን፥
እስከ በጎው ምድር (ቤገምድር)፥
ሊማሊሞን ስትሻገር፥
አውቶብሱ ሲነቀንቅህ፥
ፈሱን ሲፈሳብህ እንዳትቸገር፥
እንካ ወንድሜ - ይህችን ፎጣ፥
ሸንጥ አድርጋት ከአስቤዛው ሥር።
ወይ ጉድ! ግራ የገባ ነገር፤
ምንም ሳይከብድ አብሮ መኖር፥
ጠብና ጭቅጭቅ እንዳይፈጠር፥
ከደቡብ፥ ከምሥራቅ ከመሃል ሀገር፥
ምሩጥ አንተ ገበሬ - ምሩጥ አንተ ባላገር፥
ሰው ጠፋ! ከአንተ በቀር?
አንተው የሀገር ሰላም ልታስከብር?
በል ሂድና አንተው ዝራ ልዩ ፍቅር።
ይሁና! ምን ይደረግ፥
ውይይት የለ በደርግ፤
ወንድሜ በል ሂድና ለሀገርህ ሙት፥
ይሻል ይሆናል ከመቸገር - አፈር ከመግፋት።
በኛ ልፋትና ጥረት በልጆቿም ብርታት፤
የዴሞክራሲ በር ሲከፈት፥

ኤርትራም ቁንጅናዋ እንዲታይላት፤
ባንዲራ መትከያ “ትልቅ እንጨት”፥
በኢትዮጵያ እንዲጸናላት፤
የነፃነቷ ምልክት እንዲውለበለብላት፥
ሰላሟ በሁላችንም ደም እንዲጠበቅላት፤
በል ሂድና ዝመት።
ግን አትዘንጋ፤
በሁለቱም ሥፍራ የቃል ኪዳን ልጆች ያሉባት፥
ኤርትራ ምንጊዜም ኢትዮጵያ ናት፤
ኢትዮጵያም ምንጊዜም ኤርትራ ናት፤
ውዴ፥ ፍቅሬ በል ሂድ፥ ውዴ ደህና ሁን፤
*መቼም በእግዚአብሔር እንጂ በሰው አይሆን፤*
*ሁሉም በእግዚአብሔር ነው የሚሆን፤*
*ካለ እግዚአብሔር ምንም አይሆን።*

# ምዕራፍ አምስት

## የብቸኛ ትግል

በዚህ አለም የሚከናወነው ሁሉ (ወይንም እኔ የምወስደው እርምጃ) እኔን ከተሳታፊነት አግልሎ፥ የተለየሁ አድርጎ አስቀመጠኝ፤ ከማውቃቸው ሁሉ ለየኝ። ወይ ከኢሕአፓ፥ ወይ ከተቀረው ሰው ሳልሆን በመሃል የቁም እስረኛ ሆንኩ።

የብቸኛ ትግል ማለት ምንድነው? ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ከአእምሮ ውስጥ እያሰላሰሉ በብቸኝነት ማሰብና በመጨነቅ ውስጣዊ (ምስጢራዊ) ትግል ማድረግ ማለት ነው?

ዙሪያዬ ጨለማ እየሆነ ቢያስቸግረኝም፥ በፖለቲካና በፍልስፍና መካከል ጣልቃ የሚገባ ሃይማኖታዊ መሰል ቀና አስተሳሰብ በውስጤ እንዳለ አውቃለሁ። እንዳውም ሰውን ሙሉ ሰው የሚያሰኘው ይኸው ይመስለኛል። ግን ትንሽ ዞር ብሎብኛል፤ በዛ የመርካቶ ግርግር መካከል፥ የሰውና የሌላውን ጩኸት መለየት አቅቶኛል።

በአንድ በኩል "የመርካቶ ሕዝብ ምን አይነት ጆሮ ቢኖረው ነው በዚህ ሁሉ ጩኸት መካከል የሰው የሆነውን ጩኸት አጣርቶ የሚሰማ?" እላለሁ። በሌላ በኩል ደግሞ፥ የኔ ጥንካሬ ማጣት፥ ባካባቢዬ ከማየው ሰው ሁሉ ያሳነሰኝ እየመሰለኝ፥ በራሴ አዝናለሁ።

ጆሮዬስ ከዳኝ፤ ግን የጆሮዬ መክዳት ለሃሳቦቼ ጥንካሬ የሰጠው እየመሰለኝ፥ ጽሑፎቼን ቀጠልኩ፤ ጠላ ቤት እየገባሁ መጻፍ ሆነ ሥራዬ። ሃሳብ ሲበራከትና ሲጽፉት ቀለል - ደስ ይላል። ግን ይህ ጽሑፍ የት ይደርስ ይሆን?

የሰውነቴ አካል የሆነው ልብሴ፡- አንድ ሰማያዊ ሸሚዝ፥ ጠቆር ያለ ሱፍ ኮት፥ ቡናማ ሱሪ እና ጥቁር የቆዳ ጫማ፤ የጠቅላላ ኪሶቼ ቁጥር አስር፤ ሻይ ቤት ገብቼ ገንዘብ ለመክፈል አስሩን ኪሶቼን ደጋግሜ መዳበስ ለምዶብኝ፥ ከውጪ ለሚያየኝ ትኩረት እስባለሁ።

ኪሶቼን በየጊዜው ስደባብስ የተገዙትን የአውቶቡስ ቲኬቶች አውጥቼ ጥያቸዋለሁ ማለት ነው። ችግር ይጠነሰሳል፤ ይወለዳል፤ ሰውን ያስቸግራል፤ ችግር

ሲመጣ ይደራረባል። አይ! ቲኬቶቹ ጠፍተዋል። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ማለት ይህ ነው'ኮ።

በኪሴ የቀሩኝን ብሮች ደጋግሜ ከቆጠርኩ በኋላ፥ ለሁለት ቲኬት መግዢያ የሚሆን ገንዘብ (23 ብር) በአንዱ ኪሴ አስቀምጫለሁ። መቸገሬን አይቶ ሥጋ የተባለ ከሰውነቴ ጠፍቶ አጥንቴን ስለቀረሁ፤ ተወዛዋዥ አጽም መሰልኩ። ጉልበት ሊከዳኝ ነው፤ ትንሽ ስሄድ ይደክመኝ ጀመር። ከጆሮዬ ቀጥሎ እግሮቼም ሊክዱኝ ነው መሰለኝ። አቅጣጫን የሚያሳውቅ የአእምሮዬ ክፍል ድንገት ሳይዘጋ አልቀረም፤ መንገድ ይጠፉኝ ጀመር። ቡና ቤቶቹ ሁሉ አንድ አይነት ሆነውብኛል።

ቀደም ብሎ ድምጽ ሁሉ አንድ አይነት ሆነብኝ፤ አሁን ደግሞ በአይን የሚታይ ሁሉ አንድ አይነት እየሆንብኝ ነው። ሌላ ሀገር ውስጥ ያለሁ መሰለኝ። ብሄድ ብሄድ አንድ የምለየው መንገድ፥ አንድ የማስታውሰው ቡና ቤት አጣሁ። ከእንግዲህ ማንንም ላላገኝ ነው ብዬ ተበሳጨሁ። ለመሆኑ የመርካቶ መንገዶች እንዲጠፉብኝ ያደረገ የአእምሮዬ መድከም ይሆን? ወይንስ የሞራሌ መላሸቅ።

አሻግሬ ካጠገቤ ጠፋ፤ ወይ ፈልጌ አላገኘሁት፤ ወይ ፈልጎ አላገኘኝ። ጸጋዬንም ለማግኘት ሞከርኩ፤ እርሱ ባገር የለም። መድህን ጠፍቷል። ሁለቱን (እሻግሬን እና ጸጋዬን) ለማግኘት ካልቻልኩ፥ አውቄ የጠፋሁባቸው ይመስላቸው ይሆን? ጸጋዬን ለማግኘት ካልቻልኩ ለአሻግሬ አልጠቅመውም። ግን ጸጋዬን እንኳን ባጣ አሻግሬን ባገኘውና ሃሳብ ለሃሳብ ብንለዋወጥ ጥሩ ነበር።

በሄድኩበት የቀበሌ ዘበኞች ይከታተሉኝ፥ ሁኔታዎችም ተስፋ እንድቆርጥ ያስገድዱኝ ጀመር። ሌላ መንደር ውስጥ ገባሁ። ቀስ በቀስ ከዚህ መንደር ያሉትን የሻይ ቤቶችና አካባቢያቸውን አጠናሁ። በዚህ መንደር ውስጥ ብዙ ሴትኛ አዳሪዎች አሉ። ለመሆኑ ሴትኛ አዳሪ ማለት ምን ማለት ነው?

እህ! የኢትዮጵያችን ታሪክ የሁሉም ሕብረተሰብ (የድሃውም የባለጸጋውም) የአኗኗሩ ታሪክ ተደምሮ በጥቅሉ ሲነገር ነው እንጂ፥ የነዛ የተለዩ የሕብረተሰብ አካሎች (ጥቂት ሃብታሞች እና የደላቸው ግለሰቦች) አኗኗር ብቻውን አይደለም። ታዲያ፥ ሁሉም ፖለቲከኛ በሆነበት ምድር፥ ማን ያውራ ስለነርሱ - ስለ ሴትኛ አዳሪዎቹ።

ሴትኛ አዳሪ ማለት ሴቶች በምድር ላይ ራሳቸውን ችለው መኖር ሲያቅታቸው፥ በኑሮ የሚያግዛቸው ባል ሲያጡ፥ በምድር ለመቆየት ሲሉ ወንዶችን የሚለምኑበት ዘዴ ነው። ወንዶችም የሚሠሩትን ሥርተው፥ በድጋሜ እንዲያገኟቸው በሚያስችላቸው የደግነታቸው መጠን፥ ገንዘብ ጣል አድርገው ይሄዳሉ።

በዛ በረሃቡ ዘመን - ድርቅ በሆነበት ሥፍራ (በሰሜን እና በሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ) ባሎች ሚስቶቻቸውን ማስተዳደር አቃታቸው። ሚስቶችም የሚያበስሉት

ምግብ አጡ። በትዳር ውስጥ የረሃብ ሞት ገባ። ከዚህ ለማምለጥ ብለው፥ ባልና ሚስት በሕግ ሳይፋቱ፥ የተለያየ ሥራ ጀመሩ። ባል ባቅራቢያው ከሚገኘው የባላገር ከተማ በቀን ሥራ ሲሸቅል፥ ሚስት ደግሞ፥ ሸቃዮች ከሚያስገኙት ገንዘብ ለመካፈል ስትል፥ ጠላ ሻጭ ሆነች። ይህችና ሌሎችም ሴትኛ አዳሪዎች ዘመዶቻቸው በምግብ እጦት ሥጋና ነፍሳቸው ሲለያይ የተመለከቱ ናቸው። የባላገር ኑሮ ሲያል እየሆነ መኖር ሲያቅታቸውና ከሞት በስተቀር ሌላ አማራጭ ሲጠፋባቸው፥ በሥጋቸው ተደስተው ለመኖር ሳይሆን፥ ለዛ ነፍስን ለተሸከመ ሥጋ እንዳያንቀላፋ መደለያ ይሆናል ብለው ነው ሴትኛ አዳሪ የሆኑት። በነርሱ ምርጫ ሳይሆን ተገደው ነው። ታዲያ ገጠር በነበሩ ጊዜ ከተፈጥሮ ጋር ታግለው የሰውን ልጅ ከሞት ለማዳን ይጣደፉ ነበር። አልሆን ሲላቸው የራሳቸውን ነፍስ ለማዳን ብለው፥ ሰው በበዛበት ገቡ፤ እና ከዚያ ሌላ ለየት ያለ ሥራን መሥራት ጀመሩ።

በሰው ሰራሽ ችግር የሰው ምርጫው ሲሆን ኃጢአት፥

ጾታ በጾታ ላይ እንዲነግሥበት፥

ሥጋ በሥጋ ላይ በገንዘቡ እንዲያዝበት።

ሴቶች ነፍስ ዘሪዎች፥ ጡት አጥቢዎች፥

ነፍስ ዘርታችሁ ዝም የማትሉ፥ አሳዳጊዎች፥

በሕይወታችሁ ሁሉ፥ ለሰው ልጅ ተቆርቋሪዎች፥

በእውን የናንተ የቢሮ ሥራ ይህ ይሁን? ይህ ይሁን?

የደላውማ ተዝናንቶ ሲወንጅል ሌላውን፥

በሴቶቹ ላይ ያላከካል፥ ጥፋቱን፥

የገዛ ኃጢአቱን።

እነኚሁ "ሴትኛ አዳሪ" የተባሉ ሴቶች፥ በልተውና ጠግበው የሚኖሩ ወጣቶች በጥይት እየተገደሉ ከደጃፋቸው ሲጣሉም ተመለከቱ። ተመልክተው ግን ዝም ማለት አልተቻላቸውም። ከሴትኛ አዳሪነት ጋር ሌላ ተጨማሪ ሥራ ወሰዱ። በምርጫቸው በወሰዱት ሥራ መሠረት፥ የሰብአዊነት ተቆርቋሪዎች ሆኑና፥ ከኢሕአፓ ታጋዮች ጋር ተቆራኙ።

ይህም ትንሽ ልጅ ገና ከልጅነቱ ከአባቱ ተለይቶ፥ ከሞት እንዲተርፍና እንዲያድግ እናቱ የምታደርገውን ትግል ሁሉ ለማስተዋል ይበቃና "...ይህች እናቴ ሴትኛ አዳሪ ሁና ያሳደገችኝ፤ ፍቅርን ስለመገበችኝ፥ ውለታ አለብኝ፤ ተምሬ፥ ሥራ ይዤ፥ እናቴን ነጻ አወጣታለሁኝ ይላል።" አዎ! ይህንን ይላል፥ ያ ገና ነፍስ ያላወቀ የሴትኛ አዳሪዋ ልጅ። ግን በጉርምስና እና በእውቀት፥ እርሱም የሚወድቅበት ጎዳና

ከእናቱ የከፋ ይሆናል። አዎ! ይህንን ይመስላል፤ አንድ ትውልድ ሙትትትት... ሲል፤ ትውልድ ሙትትትት... ሲል።

ቀደም ሲል፥ በኢሕአፓ በኩል የተደረገው ቅስቀሳ የመርካቶ ሴትኛ አዳሪዎችን የዴሞክራሲያዊ ግንባር ውስጥ እንዲሳተፉ አድርጓቸው ነበርና፤ ብዙ ሴቶች በዚሁ መዋቅር አመራር መሠረት በኡኡታ ኮሚቴዎች በመሳተፍ "ኡ!ኡ!ኡ!ኡ!ኡ!ኡ!ኡ!ኡ!ኡ!........." እያሉ በመጮህ፥ የደርግ ወታደር መርካቶ እንዳይገባ ባቅማቸው ተከላክለዋል። እኔም "በሴትኛ አዳሪ ወታደሮች ከሚጠበቅ መንደር - ከመርካቶ መግባቴ ድንገት ከመገደል ያድነኛል፤ ወይንም የመሞቻዬን ጊዜ ያራዝመዋል" እያልኩ አስብ ስለነበር፥ ከዚሁ ሥፍራ ጥገኛ ሆኛለሁ። በገዛ ሀገሬ ተሰድጄ የገባሁበት መንደር ሆነ የኔ ሰላማዊ ሀገሬ።

በዛ በቀውጢ ቀን፥ መጠጊያና መሄጃ አጥተው ባለቤት እንደሌለው ውሻ ከርታታ በመሆን፥ ለማኝ በሽተኛ መስለው የሚታዩትን የኢሕአፓ ታጋዮች፥ የመርካቶ ሴትኛ አዳሪዎች በማስጠጋት ረድተዋል። ከደጋግ ሰዎች ዘንድ ያ<u>ለ</u> (የተፈጠረ) ርህራሄ በሴትኛ አዳሪዎችም አለ። ስለሆነም፥ ከሰዓት እላፊ በኋላም ቢሆን፥ ለአልቤርጎ የሚከፈለውን ያህል ብቻ እያስከፈሉ፥ ወይንም በነፃ በማሳደር፥ የብዙዎችን ነፍስ አድነዋል።

በተቃራኒ ደግሞ፥ አንዳንድ ሴትኛ አዳሪዎች፥ ሰዓት እላፊ ሲቃረብ፥ እንደ እኔ አይነቱን ጠውላጋ፥ ከርታታ ገና ከሩቅ ሲያዩ፥ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው "እኛ አልቤርጎ አይደለንም፤ እንዴ! አሁንስ በዛ፤ እንዴ!.........." ይላሉ። ታዲያ፥ በዚህን ጊዜ ነው መፈጠር የሚያስጠላው። ግን ጥቂቶች ናቸው እንዲህ የሚሉ። እንደነዚህ ያሉቱ፥ ከኢሕአፓ ወገን ለመሆን የፈሩ፥ ሥጋዊ እውነት ያላቸው፥ መንፈሳዊነት የራቃቸው፥ የተለዩ፥ የተለዩ፥ የተለዩ፥ የተለዩ፥.......ናቸው።

## <u>የአንድ ቄስ ምክር</u>

ከዕለታት በአንድ ቀን፥ ጠላ ቤት ገብቼ ለመጎለት ወደ በሩ ጠጋ ስል፥ አንድ ቀዥቃዣ ሰው ከቄስ ጋር ሲጣላ ደረስኩ። ይህም ሰው እንዴት አንድ ቄስ ከሴትኛ አዳሪ ሴት ቤት ይገባል ብሎ የራሱን የከፋት አስተሳሰብ አንጸባረቀ፤ ሊጣላ፥ ሊማታም ከጀለ። ሴቲቱም ቄሱ እንዳይመታባት በመፍራት ከሁለቱ መሃል ቆመችና እንባዋን ኮለል ኮለል በማድረግ ሰውዬውን እንዲህ አለችው፡-

"ሰማህ የኔ ወንድም! ለመሆኑ ምንም እንኳ እድሌ ሆኖ በዚህ ሥራ ብሰማራ፥ እኔስ እንዳንተው ከሰው አይደለም እንዴ የተፈጠርኩት? ሥጋዬ ቢበድልና እግዚአብሔርን ባስቀይመው፥ ነፍሴን እንዲያድንልኝ ብለምነው፥ ማነው

የሚከለክለኝ? እርሳቸውስ አባቴ ከቤቴ ገብተው ቢጸልዩልኝና ቢያማልዱኝ አንተ ምን ገደደህ? ኸረ ተው! ወንድሜ ተው። ከቤቴ እርኩስ መንፈስ እንዳይመጣብኝ፥ ከመጥፎ ሰዎች እንዲያርቀኝ፥ ደጋጎቹን እንዲያቀርብልኝ፥ ወይንም ከዚህ አሁን ካለሁበት የከፋ ኑሮ ውስጥ እንዳልገባ፥ ወይንም ሻል ያለ ኑሮ እንዳገኝ አባቴ እግዚአብሔርን ቢለምኑልኝ፥ ከቤቴስ ጸበል ቢረጩልኝ ያስነውራል? ወይንስ ተከልክሏል? አዪ! ተው! ተው የኔ ወንድም! ፍርድ የእግዚአብሔር ስለሆነ ሰውን ለመኮነን አትቻኮል" በማለት፥ የሰውዬውን ቁጣ ለማብረድ ሞከረች።

ቄሱም ቀስ ብለው በትእግስት እንዲህ አሉ፦ "ሰማህ የኔ ወንድም! አሁን እርሷ ያለችህን ሰማህ። ቄስ የሴትኛ አዳሪ ዘመድ ሊኖረው አይችልም? ሴትኛ አዳሪዎችስ የቄስ ዘመድ እንዳይኖራቸው ምን ይከለክላቸዋል? ይህች ሴት ዘመዴ ስለሆነችና ስለምወዳት፥ በሥጋዋ ረክሳለች ብዬ፥ ተጠይፌ አልራቅኋትም፤ ልጸልይላት አስቤ ከቤቷ መጣሁ እንጂ። ይህን ማድረጌን እንደ ኃጢአት ቆጠርከው? የኔ ወንድም።

አውቃለሁ፤ ከዚህ ስለገባሁ በሌላ ነገር ጠርጥረኸኝ እንደሆነ። የሁላችንንም ሥራ የሚያውቅ እግዚአብሔር ነው። ለመሆኑ፥ ከኔ፥ ካንተና ከሷ የሚጸድቀውን የሚያውቅ ማነው? እኔ ቄስ ስለሆንኩ ብቻ የምጸድቅ፥ እርሷ በዚህ ሥራ ስለተሰማራች ብቻ የምትኮነን ለመሆኑ ማን አወቀ? እኔ ግን በዚህ ሥራ ተሰማርታለች ብዬ ዝምድናዋን አልፍቀውም። ማንም ሰው የፈለገውን ይበለኝ እንጂ፥ እኔስ ድሮ እንደምጠይቃት አሁንም እጠይቃታለሁ።

ይህች አለም አታላይ ናት። "ለኑሮአቸሁ የሚሆን ከዚህ ሥፍራ ተዘጋጅቶላችኋልና፤ ኑ እዚህ!" ብላ ሰውን ካልሆነ ሥፍራ የምትጥል አሳሳች ናት ይህች አለም።

ሴቶች ልጆቻችን እና እህቶቻችን አይናቸው እያየ ምድራዊ ሲዖል ውስጥ እየዘለሉ የገቡት በምርጫቸው ሳይሆን ተገደው ነው። ይህችም ሴት ሳትወድ የገባችበት ሥራ ሁል ጊዜ እየጸጸታት ነው፤ እድሉ ሲያጋጥማት ከዚህ ሥራ ትወጣለች። እኔም የመጣሁት አንዱም ሌላ አማራጭ እንድትፈልግ ልመክራት ብዬ ነው። እስከዛው ግን በሥጋዋ ብትረክስ ነፍሷ እንዳይረክስ በምታደርገው ጸሎት ልራዳት ብዬ ነውና፤ ወንድሜ እ.ባ.ክ.ህ! አትቆጣ። ይህ ጥለን የምንሄደው አለም ሁላችንንም የተለያየ ችግር ውስጥ ይከተናል፤ ማነው ወዶ የሚፈልገውን ብቻ እያደረገ የሚኖር? ማንስ ነው ከማይፈልገው ርቆ መኖር የሚችል?" አሉ በትካዜ።

በዛን ወቅትና በዛ ሥፍራ ብዙ ጭቅጭቅና ብዙ ወሬ ነበር። ሴቶቻችን መሄጃ አጥተው ሲንከራተቱ፥ መንግሥትም እያየ ዝም ሲል፥ እኔ በሰማሁት ብቻ ሳይሆን፥ በሃሳብ በተወጠረው አንጎሌ፥ ይህን እና የመሳሰለውን ሳይሆን አይቀርም ሴቲቷ እና

ቁሱ የተናገሩት በማለት አስቤአለሁ። አሁንም የሰው ልጅ በዕድሜው ውስጥ የሚደርስበትን ፍዳ ከሁኔታው ጋር በማገናዘብ ለመግለጽ ስል ነው ከራሴው ሃሳብ ጨማምሬ የተናገርኩ። “ይህ ጥለን የምንሄደው አለም ሁላችንንም የተለያየ ችግር ውስጥ ይከተናል፤ ማነው ወዶ የሚፈልገውን ብቻ እያደረገ የሚኖር?” የተሰኘው አባባል ግን፥ እኔንም ስለሚመለከት፥ ከነከነኝ። አዎ! ጊዜ ያልፋል፥ እስኪያልፍ ያለፋል። የሰው ልጅ ሕይወቱ አካል ሰውነቱ፥ ቢረክስ ቢዋረድ፥ ክብር አልባ ከንቱ፥ ሌላም ሕይወት አለው፥ የመንፈስ ሰውነት፥ ከጥፋት አውጥቶ ጨዋ ሥፍራ ‘ሚከት። አለም ሁለት ናት፥ በሁለት ዓይን ስናያት፥ መጥፎውን በጥሩ ይቻላል መተካት።

ክፉውን ብቻ እያየን፥ ተስፋ ከመቁረጥ ያድነን። ባቅማቸው የተራበን ያበሉ፥ የተጠማን ያጠጡ፥ የታረዘን ያለበሱ ሴትኛ አዳሪዎች በሰማይ የሚያገኙትን ሥፍራ፥ ከአልጋቸው ሳይነሱ፥ የቤት ሠራተኞቻቸውን “ውሃ ቀጠነ” ብለው የሚጨቃጨቁ፥ የሚያመናጨቁና የሚቆጡ የቤት እመቤቶች አያገኙትም (ይሆናል)።

ረዓብ የምትባል ጋለሞታ ሁለት የእስራኤል ሰላዮችን ከቤቷ ደብቃ የኢያሪኮ ንጉሥ እንዳይገድላቸው ስላደረገች፥ ስሟ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎላት እስካሁን ትታወሳለች፤ ምሕረት የሚገባት (ሩሐማ) እየተባለች (ኢያሱ 2፡1- መጨረሻ)።

ለኢትዮጵያም ሴትኛ አዳሪዎች ምሕረት ይመጣል። ደጋግ የኢትዮጵያ ሴቶች የድህነትና የረሃብ ጦር ከባላገር አባሮ አዲስ አበባ አመጣቸው፤ ከዚያም የሚወዱትን ሳይሆን፥ የሚጠሉትን ሥራ እየሠሩ ይኖራሉ። እነርሱ ጋለሞታዎች አይደሉም። ቸሩ እግዚአብሔር ሁኔታቸውን ተመልክቶ ከጥሩ ሥፍራ ያስቀምጣቸዋል።

# ምዕራፍ ስድስት

## ሃሳቦች እና ጭንቀቶች

ከእለታት በአንድ ቀን፥ ከጧቱ ሁለት ሰዓት ላይ፥ አንድ የንኡስ ከበርቴ ቡና ቤት ገባሁና፥ ቡና አዝዤ፥ ከአንድ የግርግዳ ማዕዘን ተጠግቶ የተቀመጠ ወንበር ላይ ቁጭ አልኩ። ከኔ በስተቀር ሌላ ሰው አልነበረም። የቡና ቤቱ ሠራተኛ (ቦይ) ሲጠራርግና ሲወለውል አየዋለሁ። እርሱ ጭቁን ነውና፤ ገቢውም ሴቶቹ ከሚያገኙት ያንሳል። እርሱ የእነርሱን ፍላጎትና ስሜት በተቻለው መጠን ይጠብቃል፤ ስለዚህም ይመስለኛል፥ ለሴቶቹ ሁሉ እርሱ ታዛዥ የሆነው።

እንደገባሁ፥ ያዘዝኩትን ቡና ግማሹን ጠጥቼ፥ ልክ እንዳስቀመጡት እቃ ሳልንቀሳቀስ ብዙ ቆየሁ። መቼስ የት እሄዳለሁና፤ እስከ ቀኑ አምስት ሰዓት ድረስ ቁጭ አልኩ። ለተመለከተኝ፥ በሃሳብ ሰጥሜ ያለሁበትን የማውቅ አልመስልም። ቦዩም ሥራውን ጨርሶ ሥፍራውን ለተረኞች ሴቶች ለማስተላለፍ ሲሰናዳ፥ የኔ ከቡና ቤት አለመውጣት አሳሰበው። ሳልንቀሳቀስ - ከወንበሩ ተጣብቄ ብዙ ስለቆየሁ ቦዩ ተጨነቀ፤ ተቅበጠበጠ፤ ሴቶቹ ሊመጡ ሆነ።

ሴቶቹ ከእንቅልፋቸው ተነስተው፥ ተፅዳድተው፥ ቁርሳቸውን በልተው፥ ተኳኩለውና አበባ መስለው ብቅ፥ ብቅ ሊሉ ሆነ። ሂሳቡን ከፍሎ እንዳይሄድ፥ የማይፈለግ ሰው ከዛ ወንበር ተጣብቋል። ከዛ ሰዓት በኋላ፥ ከዚያ ሥፍራ መቆየት እንኳን ለኔ ለርሱም አልተፈቀደ።

ቦዩ ልክ እንደሌለሁ ቆጥሮ፥ የዝንብ መግደያ (ፍሊት) ሲነፋ ለኔም ጭምር መሆኑ በደንብ ገባኝ። እኔም ልክ ከእንቅልፉ እንደተቀሰቀሰ ሰው ብንን አልኩ። ቦዩን ምንም ሳልቀየመው አይኔን እያሻሸሁ ቶሎ ብዬ የቡናውን ሂሳብ ከፈልኩና ወጣሁ።

አዎ! ወንዶች ደጎች ናቸው፤ ግን ደግነታቸው እንደ ሴቶች ደግነት አይለሰልስም። ይህስ ቁንጽል፥ ኢሳይንሳዊ አባባል ላይሆን ይችላል፤ ምክንያቱም፥ ደግነትን ከርህራሄ ጋር ለማዋሃድስ እንደ ሴቶች ለወንዶች ቀላል አይመስለኝም።

ወይ ጉድ! በኦሮምኛ እንዲህ የሚል አባባል አለ፤ “ኢዬይሳ በካ ቡሉ ወጋ ጀቤ፥ ድፉ ኢቲ ባይሳ” ይህም ማለት፡- ደሃ ሰው ማደሪያ ሲያጣ ፈሱን ያበዛበታል

ማለት ነው። ከዛን ጊዜ በኋላ፥ "ጥንትም የንኡስ ከበርቴ ቡና ቤት ለኔ አይሆነኝም" አልኩና፥ ቡና ቤት መግባት አቆምኩ።

በጠላ ቤት አካባቢ ያለውን ሕይወት ሲመለከቱት እንጂ ሲኖሩበት ከባድ ስለሆነ፥ ጠላውን ትቼ ሻይ ብቻ በመጠጣት ጤንነቴን ለመቆጣጠር ከጀልኩ። ይህን የቀድሞውን አይነት የኳኳታ ጩኸት የሚያባብስ፥ ሽብርና ትርምስን የሚፈጥር፥ አእምሮን የሚያውክ እንደገና ደፍሬ ገባሁበት። ግን የሻይ ቤቱን ጩኸት ችዬ ልቆይ የምችልበትን ጊዜ ስቆጥረው፥ አንዷ ደቂቃ እንደ አንድ ሰዓት ሆነችብኝ። ይህንስ አልችለውም አልኩና ወጣሁ።

ከጠላው ቤት ደግሞ ምንጊዜም እኔ በገባሁበት የሚከታተለኝ አንድ ሰው አለ። ይህ ሰው ምድቡ ከደጋግ ሰዎች ይመስላል፤ ገር ከሚመስለው ፊቱ የሚፈነጠቅ የብርሃን ኃይል ከደግነት በስተቀር ክፋት እንደሌለበት ይመሰክርበታል። እኔን አናግሮኝ አያውቅም፤ ግን ሁል ጊዜ ለኔ የሚያዝንልኝ ይመስለኛል። እኔን በጠላትነት ክፋት የሚከታተል ቢሆን ኖሮ፥ እንዴት ሁልጊዜ ከኔ አስቀድሞ ከምገባበት ጠላ ቤት ይገባል? የዚህ ሰውዬ ነገር አሁንም ቢሆን ይገርመኛል። መርካቶ ደጋግ ሰዎች የሚበዙበት አካባቢ ከመሆኑም በላይ፥ አላፊ አግዳሚው ሁሉ ኢሕአፓን በተለያየ መንገድ ይደግፋል። የነኚሁ የደጋግ ሰዎች መንፈስ ነው የደርግን ታንክና መትረየስ በመመከት መርካቶ እንዳትቃጠል የተከላከለ። የዛ የደግ ሰውዬንም ክትትል፥ ምንም እንኳን ከእኔ እንቅስቃሴ ጋር ባገናኘውም፥ አካባቢው የተረጋጋ መሆኑን ነው የሚያረጋግጥልኝ።

ከእለታት በአንድ ቀን፥ ያን አሻግሬ የሚገኝበትን ሻይ ቤት ስፈልግ ውዬና አምሽቼ፥ ድክም ብሎኝ ማደሪያ ስፈልግ፥ ሰዓት እላፊ ደረሰብኝና እራሴን ከቀበሌ ዘበኞች ለማስመለጥ ስደናበር፥ አንድ ግቢ ውስጥ ገባሁ። እንዳጋጣሚ ሆኖ በዝቅተኛ ዋጋ የሚከራይ ትርፍ አልጋ ነበር። ወዲያው ገንዘብ ከፍዬ አልጋውን ተከራየሁ። ልክ ርቦት ምግብ ሲያገኝ ለመብላት እንደሚጣደፍ፥ እኔም ወዲያው ከአልጋው ላይ እንዘፍ ብዬ ተኛሁና፥ ወዲያው ልዩ የሕልም አለም ውስጥ ገባሁ። ጧት ብንን ስል ከጧቱ ሁለት ሰዓት ሆኖ ነበር። እንደ ዛሬም ታላቅ እረፍት ተሰምቶኝ አያውቅም አልኩና፥ በልቤ ተመስገን፥ ተመስገን፥ ተመስገን እያልኩ ወጣሁ።

አሁንም ያ ከአሻግሬ ጋር የምንገናኝበትን ሻይ ቤት ላገኘው አልቻልኩም። ምን እንደሰወረብኝ ሊገባኝ አልቻለም። ያ ከሩቅ ይታየኝ የነበረ ገላጣ ሜዳ፥ ከመሃሉ አንድ ባለ ግርማ ቤተ ክርስቲያን፤ እርሱም ከዋናው ከአዲስ አበባ ልለቅ ስል ያየሁት የቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ነው። ይህንን ቤተ ክርስቲያን ብዙ ጊዜ ከሩቅ አየው ነበር። ያ የኔ ሀገር - የመጨረሻው መጠጊያዬ - ሰላሜን የማገኝበት -

እርሱም በሁለት ሀገር መካከል ወሰን ድንበር ሆኖ እንደተተከለ፥ ጥሩ ምልክት ሆኖልኝ - ናፍቆቴ...ሰላሜን ሳገኝ ለወደፊት የምደርስበት፤ ዛሬን ግን፥ "ቁም፤ ካገር ድንበር ደርሰሃልና ወደዛ አትሂድ..." እያለ የሚከለክለኝ መካሪዬ!... አዬ! ወዲያ ብሄድ ወዲህ ብመጣ፥ ይህ ቤተ ክርስቲያን አልታይ አለኝ ("ተሰወረብኝ")፤ ምልክት የሚሆነኝንም አጣሁ።

አሻግሬን አግኝቼው፥ የተቋረጠውን የኢሕአፓ ግንኙነት መሥርቼ፥ ከታጋይ ጓዶቼ ጋር የምገናኝበትን መንገድ ሁሉ በተስፋ እያሰላሰልኩ ብዙ ቀናት አለፉ። ይህ የማይጨበጥ ተስፋ ከቀን ወደ ቀን አስጨናቂ እየሆነ መጣ።

በችግር ጊዜ ስለ እግዚአብሔር መኖር ወይም አለመኖር ማሰብ አይቀርም። አንዳንዴ ይህንንም አስባለሁ፤ ግን፥ በጭንቅላቴ ከማይጠፋው የአንጃዎች ርዕዮት፥ የኢሕአፓ ግትረኛነት፥ እና ሌሎችም የሚታሰቡ ሃሳቦች ሁሉ ጋር ተደባልቆ፥ ከቀበሌ ዘበኞች ማሳደድ ጋር፥ ከመርካቶ ትርምስና የድብብቆሽ ኑሮ ጋር፥ ከእውነታና ከቅዠት ጋር፥ ጤንነትን ማጣት ተጨምሮ፥  አጠቃላይ ሁኔታውና ትርምሱ ጭንቅላቴን አደነዘዘው።

መሄጃ አጥቼ ተደነባበርኩ፤ ያለሁበትንም አላወቅሁት። በጭንቀት ተወጥሬ ሳለሁ፥ ተስፋ የተሞላበትና ደስ የሚል ስሜት በሰውነቴ ይሰራጫል፤ ምክንያቱ ምን እንደሆን ሊገባኝ አይችልም። የሰው ልጅ ሰውነቱ ሲጎዳ ደስ ይለዋል እንዴ? እኔ ሁለት ነኝ። አንደኛው እኔ ሲከፋኝ፥ ሌላኛው የእኔነቴ "ተቀናቃኝ" ደስ ይለዋል።

ወይ ጉድ! ጀግንነትና ፍርኃት በውስጤ ይደበላለቁብኛል፤ ከፋትና ደግነትም በአንድነት ይወሩኛል። በፍልስፍና ውስጥ ስምጥ ያልኩ እንደሆነ፥ ቶሎ ብዬ ሌላ አለም ውስጥ እገባለሁ። ያለሁበትንም ነገረኛና ነትራካ አለም በውስጣዊ የአዎንታዊነት ተስፋ እለውጠዋለሁ።

ይህ ሥፍራ (መርካቶ) የድሃ ልብስ (ራካ) የለበሱ ሰዎች ብዙ ብሮች ከኪሶቻቸው እየመዘዙ ለሚጠቀሙባቸው ሰዎች ሲያከፋፍሉ የሚታይበት ሥፍራ ነው። ሃብታሞቹ እንደ ተንቀሳቃሽ ባንክ ቤት ሆነዋል። ባለ ገንዘብ ሳይሆን፥ ሥራ የሚከበርበት፤ ገንዘብ መነገጃ፥ መጠቃቀሚያ፥ ኑሮን በጋራ ማሻሻያ እንጂ፥ በሰዎች መካከል ከፍና ዝቅን ፈጥሮ፥ የሌለው ላለው የሚሰግድበት ሥፍራ አይመስልም።

ግን በሌላ በኩል ደግሞ፥ ፍቅር ከድሃው እስከ ሃብታሙ ድረስ ካለ ምንም ይሉኝታና እፍረት፥ በነፃነት ሲንሸራሸር አላይም። ታዲያ ይህ ተለዋዋጭ ሁለት መልክ ከየት መጣ?

አብዮታዊው ትግላችን ጠቅላላ ኢትዮጵያን ነጻ ለማውጣት መሆኑን እየዘነጋሁ፥ ባካባቢዬ ላይ ብቻ በማተኮሬ፥ የሃሳብ ውዥንብር ውስጥ ገብቼ በሆዴ ብዙ - ብዙ የምለፈልፍ ወሬኛ ሆኛለሁ።

ምንም ይሁን ምን፥ በውስጤ ያለውን እውነት የሚያንጸባርቅ ኃይል፥ እኔንም ጥሎ እንደማይጥለኝ አውቀዋለሁና፤ በአእምሮዬ ብቻ ስኖር የሥጋዬንም መጎዳት እንድረሳው ያደርገኛል። በልቤ የቀረጽኳቸውን ጥሩ ጥሩ መጽናኛ ሃሳቦችን እደጋግማለሁ። ብዙውን ጊዜ በሰዎች የማይታሰቡ ስለሆነ፥ የተለዩ "ሰማያዊ" ሃሳቦች ናቸው ልበል? "ባካባቢዬ ሰው ባይኖር ኖሮ፥ የኔው አለም ለራሴ እንዴት ባማረልኝ ነበር!" እያልኩ፥ እራሴን በራሴ የማታልልበት ሃሳብ እየፈጠርኩና እያባዛሁ ብዙ መቆየት ቻልኩ።

ከፊት ለፊቴ የተደቀኑትን የሕይወት አማራጭ መንገዶች ሚዛን ውስጥ በማስገባት፥ እኔ በኩሌ ለራሴ ሕይወት ብቻ የሚጠቅመኝን ቁርጥ ያለ ውሳኔ ማድረግ የሚያቅተኝ ሰው አልነበርኩም። ወንዝ ሲያቁርጥ ድንገተኛ ጎርፍ ከበላዩ መጥቶ እንደተገፋ ሰው ሆኛለሁ። ግን ምንም አይደል፤ ነፍሱን ከጎርፍ ለማትረፍ እንደሚታገል ሰው፥ በሕይወት ስለእውነት መቆየት የምችለውን ያህል እቆያለሁ እንጂ፥ ለሀገሬ ሕዝብ የገባሁትን ቃል ኪዳን ለሥጋዬ ብዬ በውሸት አልለውጠውም።

አስተሳሰቤ ከራስ ወዳድነት ጋራ የሚጣላ ነውና፤ ሞት ጠሪ መሆኔንም እያወቅሁት፥ ወደ ጤነኛ ሰው ተጠግቼ ሞት አልጋብዝም። ካለ አጃቢ ብቻዬን እሞታለሁ እንጂ፥ ሌሎችን አላስቸግርም። እንደገና ወደ ቀበሌዬ ተመልሼ ነፍሴን የአብዮት ጠባቂ መጫወቻ አላደርጋትም። እነርሱም "እኛ አጋልጧል ብለን ስንፈታው፥ ለካስ ቀንደኛ የኢሕአፓ አባል ሆኖ ተገኘ! ወይ ጉድ! "በሬ ካራጁ ይውላል፤" የሚባለው ተረት በኛ ላይ ደረሰ እኮ!" ብለው፥ ቀጥቅጠው ይገድሉኛል። ስለዚህ፥ ቢከፋም ቢለማም ከመርካቶ የተሻለ ሥፍራ ስለሌለ፥ ከዚሁ ከርሜና ሰንብቼ እድሌን መሞከር ነው ያለኝ ምርጫ።

## <u>የብቸኛ ወሬ</u>

አእምሮዬ ባንድ በኩል የራሱን ጤንነት ለመጠበቅ ሲል ይታገላል፤ ግን ለሰውነቴ የሚጠቅመውን መምከር አቅቶታል። "አንተ እንቅልፍ የማይወስድህ አእምሮዬ፥ በጭንቅላት ሕዋሳት ስትንቀሳቀስ እንዳሻህ ስሜቶችን የምትሰርጽ፥ አንተ በጉልበትህ አብራኮችን የምትገዛ፥ እስቲ ምን አለህ ለእኔስ የምትነግረኝ? ምን አለህ የምትመከረኝ?" በማለት፥ እራሴን የራሴ ጓደኛ በማድረግ፥ ጥያቄ አበዛሁ።

የሰው ህመሙ ምንድነው? የገዛ ፍጥረቱ አተኩሶ በሽታ ሲሆነው፤ ተስፋ የቆረጠውም መኖሩን ሲያስጠላው። አይ! ሰው መሆን!.... ተሸካሚ ሥጋን ማሰማመር፥ ካለ ምንም ፍርኃት ወደ ጎዳና ወጥቶ፥ ደረትን ሰፋ አድርጎ፥ ከአፍ የሚወጣውንም ወደ ጆሮ ከሚገባው ጋር አስተካክሎ......፤ አይ! ሰው መሆን!.... መናገር፤ መጫወት፤ ምንጊዜም እያስመሰሉ መኖር...፤ ፊትን ኮስተር፥ ፈገግ፥ ሳቅ፥ ቆጣ ማድረግ፤ አይ! ሰው መሆን!.... ሰለማያውቁት ነገር ጸንቶ መጠበቅና መሰልቸት፤ አይ! ሰው መሆን!.... ቁጭ በማለት ሰውነትን ማቁሰል፤ በመተኛትም በሌላኛው አለም (ቅዠቶች) ከተንኮለኞች ለማምለጥ መሮጥ። ይህን ሁሉ ሰው የመሆን ዕዳ የተሸከመ ችሎ የሚኖር ሰው "አሁንስ የመኖር ዕዳዬን ተወጥቼአለሁና፤ ተፈጥሮ ከመጣሁበት ትመልሰኝ" ብሎ አይጸልይም ሰው። እኔ ልኑር እንጂ፥ እኔ ልሙት አይልም ሰው። ሰው ተንቀሳቅሶ ወደሞት የሚያደርስ ጉስቁልና ውስጥ ቢገባ፥ ቢቆስል፥ ቢታመም፥ ፍርደ ውሳኔ የሚመጣው ከሌላ ሥፍራ ነው። ምድራችን እርሷ ታውቃለች፤ የምትታቀፈውን ሰው እርሷ ራሷ እያንገዋለለች ርጋፊውን ትጥላለች።

አልሞትኩም እንጂ፥ ምድር እኔን አንገዋላ ጥላኛለች። ዘመዶች፥ ጓደኞችና የሚያውቁኝ ሁሉ ይህ ጨካኝ፥ እራሱን ደበቀብን እያሉ ይንጫጫሉ። እኔም፡-

"ሰው በምክንያት ይለወጣልና፤ ከእንግዲህ ምድቤ ያልታወቀ፤ እኔ ዛሬና ነገ፥ ምንጊዜም የምደበቅ ሰው ነኝ። የምደበቀውም በአእምሮዬ ውስጥ ካሉ ደጋግ ሰዎች መካከል ነው። ደግነታችሁ ለሰማይ ቤት ይቆየኛል እያልኩ፥ ከቀን ወደ ቀን ሞቴን የምጠባበቅ ሆኛለሁ። ከእንግዲህ እኔ ልክ እናንተ እንደምታውቁኝ እሆንላችሁ ዘንድ የማይቻለኝ ሆኛለሁ፤ እባካችሁ ይቅርታ አድርጉልኝ....." በማለት በሃሳቤ ተማጸንኩ።

ሰው ሲጨነቅ ሃሳብ ያበዛል፤ አንጎልም ሊሸከም የሚችለው የሃሳብ መጠን የተወሰነ ነው። አንጎልም ሰው የጉልበት ሥራ ሲሠራ እንደሚደክመው ድክም ይለውና፤ የመሰልቸት ሥራን ሲሠራ የማይታሰበውን ሁሉ ያስባልና፤ ሙታን የሚባሉ ሰማያዊ ሕያዋን ካጠገብህ አሉልህ የሚል "ድብቅ እውነታ" ውስጥ ገባሁ።

ርህሩህ የሴት አያቴ ሥጋቸው ቢሞት፥ መንፈሳቸው አልሞተም አልኩና፤ ባንድ በኩል፥ ወደርሳቸው መጠጋትና ከርሳቸው ጋር መሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ፥

እስከዛው ጊዜ ድረስም ቢሆን፥ እርዳታ እንዳገኝና ከዚህ ማጥ ውስጥ እንዲያወጡኝ ፈለግሁና ተጣራሁ። የልቤ መጣራት በአፌም ጩኸትን ቢያወጣ፥ በመርካቶ ካለ ጩኸት ሁሉ፥ የእኔ ጩኸት ከመሬት አልፎ ሰማይ ላይ ይወጣ ነበር ብዬ እገምታለሁ።

ባንድ በኩል "ሕይወት ያለው ከዚህ ነው፤ ያ ያለህበት የውሸት አለም ስለሆነ፥ ተወውና ና! እዚህ አብረን እንኖራለን...፤" በሌላ በኩል ደግሞ፥ "አይዞህ ካጠገብህ ሆኜ እረዳሃለሁ" የሚል፤ የስውር አለም የተለየ ድምጽ የምሰማ ይመስለኛል። በምድር ላይ ተንከባክበው እንዳሳደጉኝ አሁንም በጭንቀቴ እንዲደርሱልኝ አጥብቄ ለመንኳቸው። ለጩኸቴ ምንም መልስ ባለማግኘቴ፥ ጩኸቴን አቁሜ ራሴን ማዳመጡ ነው የሚሻለው በማለት እራሴን አጽናናሁ። አእምሮዬ የራሱን ጤንነት ለመጠበቅ ሲል ከስሜታዊነቴ ጋር ይታገላል።

ከባድ የትዝታ አለም ውስጥም ገብቻለሁ። አይኖቼን በአንድ ሥፍራ ላይ አነጣጥሬ ተከልኳቸው። ከዚያ ሥፍራ ተነቅለው ወደሌላ እንዳያዩ ሳደርጋቸው፥ ምድራዊ እኔን እና ምድራዊ ዙሪያዬን ረሳኋቸው። ከዚያም፥ በጊዜ ውስጥ በደኋላ ተመልሼ፥ ከሕጻንነቴ ጀምሮ ያሳለፍኩትን ሁሉ በተመስጦ አነበብኳቸው። አንኳር አንኳር ከሆኑ ኩነቶች መካከል፥ በፍቅር ካሳደጉኝ፥ እናዬ ከምላቸው የሴት አያቴ (የእናቴ እናት) ጋር ያሳለፍኳቸው ጊዜያት ናቸው ሃሳቦቼን ሙልት ያደረጉት።

እናዬ አሁንም በውስጤ ስላሉ፥ እሳቸውን ማስታወስ ይጠቅመኛል፤ ያጽናናኛል ብዬ እንዳሰብኩት፤ እውነትም፥ የትዝታ እና የናፍቆት ደስታ ውርር አደረገኝ። ከምወደው ሕዝብ መፈጠሬ የፍቅር ዕዳ ተሸካሚ ቢያደርገኝ፥ ይኸው ለዚህ እንግልት በቃሁ። ነገር ግን፥ በኢትዮጵያችን ውስጥ እንዴት እንዴት አይነት ሰው እንደሚበቅል ሳስበው፥ "ለካስ እኛ ኢትዮጵያኖች ተፈጥሮአችን እንደዚህ አይነት ነው" እያልኩ፤ ከእርሳቸው መፈጠሬን ወደድኩት፤ በራሴም ተጽናናሁ።

እናዬ በጣም ደግ፥ ርህሩህና ሃይማኖተኛ፤ ከበስመ አብ እስከ ጸሎተ ሃይማኖት ድረስ ያለውን ጸሎት ሳይደግሙ፥ መቁጠሪያቸውንም ሳይቆጥሩ የማይተኙ፤ ከእንቅልፋቸውም እንደነቁ፥ ያንኑ ጸሎታቸውን የሚደግሙ፤ ቤተ ክርስቲያን መሄድን የሚያዘወትሩ፤ ከመሞታቸው በፊት የቀረቡ፤ እማሆይም የተባሉ ናቸው።

እናዬ እኔን እንዴት አድርገው እንዳሳደጉኝ በዝርዝር መናገር አስፈላጊ አይሆንም፤ የርሳቸውን ከሌሎች ደጋግ ቤተሰቦች የተለየ አያደርገውምና። እርሳቸው ሲሞቱ ጸጉሬን ተላጭቼ፥ ጥቁር ቆብ ደፍቼ ለአንድ አመት ያህል ባስታወስኳቸው ቁጥር አልቅሻለሁ። ከሞቱ ብዙ ቆይተዋል፤ የማይሞተው ፍቅራቸው ግን አሁንም አለ። እናዬን እንዳልረሳ የሚያደርገኝ አንድ ነገር ስላለ፥ እርሱን ብቻ ልናገር።

ብዙ ጊዜ ታማሚ ስለነበርኩ፥ ሲያስታምሙኝ ጭንቀታቸው አይረሳኝም። ከሕጻንነት ጀምሮ ከእኔው ጋር ያደገ የትክ ትክ በሽታ ነበረብኝ፤ እርሱም በዘጠኝ ዓመቴ እጅግ አይሎ ስለነበር፥ አስበተፈሪ (ጭሮ) ሆስፒታል ይዘውኝ ሄዱ። ዶክተሩ አይቶኝ፡- "ይህንን አይነት በሽታ እዚህ ማከም አይቻልም። የሳንባ ነቀርሳ ሆስፒታል የሚገኘው ከሐረር ከተማ ስለሆነ፥ ፈጥነው ከዚያ ወስደው ካላሳከሙት ቶሎ ሟች ነው" አላቸው።

እርሳቸውም በሃዘን፥ በፍርሃትና በድንጋጤ እያለቀሱ፥ አባቴ እኔን ልጁን ማሳከሚያ በርከት ያለ ገንዘብ ይዞ፥ ከሚኖርበት ከበደኖ ከተማ በቶሎ ወደ ሐረር እንዲመጣ አሳሰቡት። እርሱም እንደታዘዘው ገንዘቡን ይዞ መጣ።

በሽታው አድክሞኝ ስለነበር የምሞትባቸው እየመሰላቸው፥ እናዬ በደከመ ጉልበታቸው እኔን አዝለው ብዙ መንገድ በመጓዝ፥ እንደምንም ሳንባ ነቀርሳ ሆስፒታል ደረሱ፤ ከአባቴም ጋር ከዛው ተገናኘን።

ምርመራውን ጨርሼ ሆስፒታል አልጋ እንዲሰጠኝ ሲደረግ፥ አያቴ "ለኔስ?" አሉ። የሳንባ በሽታ በቶሎ የሚተላለፍ ስለሆነ፥ ከታማሚው በስተቀር፥ ከሆስፒታል ብዙ መቆየት አይፈቀድም።

ዶክተሩም በቁጣ መልክ "እንዴ እርስዎማ ቶሎ ከዚህ መውጣት አለብዎት፤ እርስዎ ደግሞ ተጨማሪ በሽተኛ እንዳይሆኑብን" በማለት አስጠነቀቀ። አባቴም ስለ መልካም ሥራቸው አመስግኖ "የፈጠረን አምላክ ካለ ምክንያት አልፈጠረንም፥ ልጄ እስካሁንም በሕይወት የቆየው በምክንያት ከእርስዎ ጋር ስለቆየ ይሆናል። አሁንም እርስዎ ከዚህ ካደረሱት የሚቀጥለውን ለእግዚአብሔር እና ለሆስፒታሉ ብንተወው ይሻላል። ፈጣሪ ዝም አይልም፤ እኔም ካለማቋረጥ እጸልይለታለሁ። አይዞዎት፤ ይድናል፤ ሐኪሞቹም እንደመከሩት የእርስዎ ከዚህ መቆየት ለሁላችንም ድርብ ችግር ይሆንብናልና፤ እርስዎ ከውጪ ሆነው በቅርብ እየተመላለሱ እንዲያስታምሙት ሁኔታዎችን እንዳዘጋጅ እባክዎትን ይፍቀዱልኝ" በማለት ተማጸናቸው።

እርሳቸው ግን ይህ ከቶ ሊሆን እንደማይችል ሲያስረዱት እንዲህ አሉ፡- "ሰው ምግብ ካልበላ፥ ወይም የሚበላው ምግብ ሆዱ ገብቶ ካልረጋለት ሊሞት እንደሚችል ታውቃለህ። እንዲህ ከስቶ ምንምን ብሎ የምታየው ልጅህ ከበሽታው ጋር በበላ ቁጥር እያስታወከው ነው። ሲበላ ይስላል፤ ከበላም በኋላም ሲስል፥ የበላው ሁሉ እንዳይወጣ፥ ትንሽ እንኳን ከሆዱ እንድትቆይለት፥ ደረቱን ደገፍ እያደርኩ ነው እስካሁንም ልጅህ በሕይወት የቆየው። አሁንም የሚበላው ምግብ ካጠገቡ እስኪረጋለት ድረስ እንኳን አብሬው ካልቆየሁ ልጅህ ሟች እንደሆነ እስቲ አስበው..." አሉት።

ቀጥለውም፥ "መቼም አንተ ካህን ስለሆንክ፥ ዘወትር ቤተ ክርስቲያን እየሄድክ የምትቀድሰውና የምትጸልየው ጸሎት፥ እንኳን ለልጅህ ለኔም ለደካማ እናትህ እንደሚረዳ፤ እግዚአብሔር ጸሎትህን እንደሚሰማ አውቃለሁ። በቃ፤ አንተ ሂድ፤ ተመለስ እና ልጄን እና የተቀሩትን ልጆችህን ጠብቅ። ይህም ልጅህ ድኖ ከተቀሩት ልጆችህ ጋር እስኪቀላቀል ድረስ ፈጣሪ አምላክህን ከመለመን አታቋርጥ።

መቼም ሰው እንቅልፍ ካልወሰደው፥ እንዲሁ በማሳል ቀንም ሌትም የማይተኛ ከሆነ፥ ከበሽታ ጋር እንቅልፍ እጦት ተደርቦበት፥ ቶሎ የመዳን እድሉ ይጨልማል። ሲስል ደረቱን ደገፍ ሳደርግለት ሲሻለው እንቅልፍ ይወስደዋል። ይህንን ሳላደርግ፥ ከዚህ አንድ ክፍል ብቻውን ትቼው ብሄድ፥ እኔንም እንቅልፍ አይወስደኝ፤ ልጅህም አይተርፍም፤ እኔም በሃሳብ ደቅቄ መሞቴ ነውና፤ ይህንን እወቅ።

ልጄ! እኔም እናትህ ነኝ፤ እኔም ከልጅህ በለይ በሃሳብና በጭንቀት እንደምሞት አስበው። ሁላችንንም በምክንያት የፈጠረ እግዚአብሔር አምላካችን እኔንም ከልጅህ ጋር ያቆራኘኝ በምክንያት ስለሆነ፥ እባክህ አሁንም ስማኝ፤ ይህ ልጅ ከኔ ከተለየ ይሞታል። ስለዚህ፥ በመኝታ ክፍሉ ለእኔም አንድ አልጋ እንዲገባና እኔም ከጎኑ ሆኜ እንዳስታምመው አድርግ፤ እባክህ!" በማለት፥ አባቴን በእንባ ተማጸኑ።

አባቴም ይህንን የእናዬን ልመና ተቋቁሞ እምቢ ማለት ስላልቻለ "እሺ እንዳሉት አደርጋለሁ" በማለት፥ ለእኔም ለእናዬም ሁለት አልጋ እንዲዘጋጅ በማድረግ፥ በቂውን ገንዘብ ከፍሎ ተመለሰ።

ሰው ስንት ቀን ነው እንቅልፍ እያንገላታው ሳይተኛ የሚቆየው? ምናልባት ትንሽ፥ ትንሽ ሸለብ እያደረገን ይሆናል እንጂ፥ እናዬም እኔም ለአስራ አምስት ቀናት በቂ እንቅልፍ አላገኘንም። ከሳል ብዛት ከማስታወክ ጋር እንቅልፍ መተኛት አልተቻለም። እውነታቸውን ነበር፤ ከምበላው ምግብ ትንሿ እንኳን ከሆዴ እንድትቆይልኝ ደረቴን ደገፍ ያደርጉልኛል። ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ማስታወክ ቀረ፤ የምበላውም ምግብ ይረጋልኝ ጀመር። ከዚያ በኋላ ሁለታችንም በቂ እንቅልፍ ማግኘት ጀመርን።

ሁለታችንም ለሁለት ወራት ያህል ከዚያው ሆስፒታል ቆየን። ከዚያም በሕዝቡ የተወደደና የተከበረው ዶክተር "በቃ ካሁን በኋላ መውጣት ትችላላችሁ፤ ለእርሱ በየቀኑ የሚወጋውን ፔኒሲሊን አዝለታለሁ። ይህ ልጅ በቶሎ የዳነው እርስዎ ይህንን በቶሎ የሚተላለፍ በሽታ ትንሽም ሳይፈሩ፥ ከልጄ አልለይም ብለው በድፍረት በመቆየትዎም እንደሆነ ገብቶኛል፤" አለ። የእርሳቸውንም ጤንነት መርምሮ በዚህ ተላላፊ በሽታ አለመያዛቸውን ካረጋገጠ በኋላ፥ "ጤነኛ ነዎት፤ ከዚሁ ክፍል ሳይወጡ

ለሁለት ወራት ቆይተው በዚህ ክፉ በሽታ አለመያዝዎ የሚገርም ነው" በማለት አሰናበተን።

በጸሎት እና በሕክምና ብዛት ድኜ ከዚህ ደረስኩ። ከዚህ ያደረሰኝ አንድም የመልካም ሰው ፍቅር ነው። እንዲህ አይነት የፍቅር ዕዳ በተግባር እንጂ በመጻፍና በመናገር ብቻ እንደማይቃለል አውቄአለሁ። መከፈል ያለበትን ዕዳ ሳልከፍል የማልሞት ሆኛለሁ። ምናልባት ይህ ይሆናል የኔ ያለመሞቴ ምሥጢር። ታዲያ፥ እንዲህ ያለውን የፍቅር ዕዳ እንዴት፥ የትስ ተሄዶ ነው የሚከፈለው? ኢሕአፓ የለም፤ አሲምባም ሰማይ ላይ ወጥቷል፤ አያቴም የመንግሥተ ሰማያት አገልጋይ ሆነዋል።

ወይ ጉድ! ጉድ'ኮ ነው። አሁን ደግሞ ሌላ ነገር ላስብ ነው። ለምን? እንጨት ቢነድ ምግብ ያበስላል። የዱር እሳት ነፍሳትን ይገድላል። የሰው የሃሳቡ እሳት ጥቅም ላይ እንዲውል ካልተደረገ ጉዳትም ሊያስከትል ስለሚችል፥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

ወደዚች አለም ስመጣ፤ ትንሽ ልጅ ሆኜ፥ እንደ ማንኛቸውም ትናንሽ ልጆች ሆኜ ስኖር፥ ፍቅር እና ጥላቻ፥ ክፋት እና ደግነት በውስጤ አደጉብኝ። ይህ የእኔነት የተፈጥሮ ጠባይ ሆኖ አናገረኝ። ወደኋላ እና ወደፊት ለመንሸራሸር የሚያስችል ሃሳባዊ ልቦና እንዲኖር የሚያደርግ ይኸው ዝብርቅርቆሽ አለም ነውና፤ "የሰውን ልጅ የሚገዛው (የሚያስተዳድረው) የገዛ አስተሳሰቡ ነው? ወይንስ እርስ በርስ የሚቃረኑ መንፈሶች (ቅዱስ እና እርኩስ)" ብዬ እራሴን ጠየቅሁ። አሁንም፥ አንድ ነገር ትዝ ብሎኝ፥ "ሰው ኃጢአተኛ መሆን የሚጀምረው ስንት ዓመት ሲሞላው ነው?" ብዬ እራሴን ጠየቅሁ። ለሁሉም ያገኘሁት መልስ "እንጃ" ነው። በኢትዮጵያችን ውስጥ ደጋጎች እንዳሉ ጨካኞችም እንዳሉ፤ ገና ስድስት ዓመት ሳይሞላኝ፥ በልጅነቴ ያየሁት አንድ ዘግናኝ ትእይንት ትዝ አለኝ።

ከእለታት በአንድ ቀን፥ ሁለት ሴቶች ተጣልተው ሲሰዳደቡ ቆሜ እመለከት ነበር። መሰዳደቡ እየተባባሰ ሲሄድ፥ የሁለቱ መጯጯህ እኔን በድንጋጤ ተገትሬ እንድቆም አደረገኝ። በድንጋጤ ላይ እንዳለሁ፥ አንደኛዋ ሌላዋን አይኗ ላይ ቢላዋ ስትተክልባት፤ የተጠቂዋም ደም ከአይኗ ጀምሮ ወደ ሰውነቷ ሲወርድ ተመለከትሁ። እንዲህ አይነት ጭካኔ በልጅነቴ አይቻለሁ። ከዚያን ቀን ጀምሮ የሰው ልጅ በውስጡ የአውሬነትም ጠባይ እንዳለው ተገንዝቤአለሁ።

በዚህ አለም ላይ መኖሬ፥ ይህን በልጅነት አእምሮ የተቀረጸ አሳዛኝ ትእይንት አብራራልኝ፤ በጉልህ በተደጋጋሚ እንድመለከተውም አደረገኝ። ይህንኑ አይነት ትርእይት ሳይ ነው የኖርኩት። አዎ! ዘመን አለፈና፥ አእምሮዬ ጎለመሰና፥ ሰውነቴ አደገና፥ አይኖቼም ክፍትፍት አሉና ይህቺን ጉራማይሌ አለም "በደንብ" ለማየት

በቃሁ። “በደንብ” ለማየት በቃሁ ስል የምሬን ነው። “እውነትም” አይኖቼ ቦግ ቦግ አሉና፤ በወጣትነቴ የሚከተለውን ለማየት በቃሁ።

ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሴት ወንድሞቿ ሁሉ በደርግ ተገድለው አንዱ ሲቀር፥ የዚህን የመጨረሺያውን ታናሽ ወንድሟን ከመንገድ አስፋልቱ ላይ ተጥሎ ተመለከተች። ወዲያውም ሮጣ ከሬሳው ዘንድ ስትደርስ፥ የወንደሟ ደም ኮለል ብሎ ባስፋልቱ ላይ ሲፈስ ተመለከተች፤ ውሾችም ወደ ደሙ ተጠጉ። የወንድሜን ደም ውሻ ከሚልሰው ብላ ነው መሰለኝ፥ ከደሙ ላይ እንዘፍ ብላ ወደቀች። ሁለት እጆቿን ዘርግታ ከዚያው በደረቷ ተኛች።

ቆይቶ የቀበሌ ዘበኞች መጡና፥ “ቀንደኛ ጸረ አብዮተኛ” እያሉ፥ እያዳፉ ከነ ደሟ ከእስር ቤት አስገቧት። ይህቺም ሴት ልጅ አልፎ አልፎ ጭንቅላቷን ወዘወዝ፥ ወዘወዝ ያደርጋታል። ድንጋጤ ለዚህ አበቃት። አንዳንድ ሰዎች “የወንድሟን ደም ውሻ ከሚልሰው ብላ፥ እሷው ራሷ ልሳው ነው እንዲህ የሆነችው” ይላሉ። ታዲያ፥ እህ!......

በጥይት ከተመታ ወጣት፥ ደም ኮለል ብሎ ሲፈስ፥
የብዙሃን አይን አላይም ብሎ ሲሸፍት፥
የፈሪዎችም አይን ሲያፍር - ትእይንቱን ላለማየት፥
ውሾች ሬሳውን ሲቀርቡት - ወንድሟ ከተኛበት፥
ያቺ ጉብል ሮጠች፤
ውሾች የወንድሟን ደም የሚጠጡ መስሏት።
　　ከውሾች ስትከላከል - እንዘፍ ብላ ወድቃ ከመሬት፥
　　ወንድሟን ታቅፋ - “አልለቀውም” ብላ - ሬሳውን ከተኛበት፥
　　የቀበሌ ዘበኞች ከሩቅ አይተው በግድ አላቀቋት።
ከራስ ጸጉሯ እስከ እግሯ - ደም በተነከረ ቀሚሷ፥
ከእስር ቤት ወስደው ወረወሯት።
እርሷም፡- “ትንፋሹ ቢቋረጥ - ቢለየኝም በሞት፥
ከአንድ ሕይወት ወደ ሌላ ሕይወት፥
እኔስ ወንድሜን መች አጣሁት!”
　　እንዲህም ስትለፈልፍ - ከዛው ከእስር ቤት፤
　　ታዲያ - አንዳንድ ጊዜ - አንገቷን ወዝወዝ ሲያደርጋት፥

“አይ ልክፍት - በወንድም ደም ሁለትነት”
እያልን ለርሷ ስናዝንላት፤
እንዲህማ ነው እስር ቤት፤
ሃዘንም የጋራ ብልጽግና የሆነበት።

የቀበሌው ያየሁት ድብደባ በአእምሮዬ ውስጥ ተቀርጾ፥ እየቆጠቆጠኝ ለዘለአለም እንዳይቀመጥ፥ በውስጤ የሚገፋፋኝ መንፈስ “ያቺ ሴት ያቺ ብቻ አይደለችም'ኮ!” ይለኛል። “ያቺስ? ያቺኛዋ፥ እንዲሁም ሌላዋ፥ እህት፥ እናት። በኢትዮጵያችን ውስጥ፥ ወንድም፥ አባት፥ በጉልበተኛው ሲረገጥ፥ ማነው ባለ ታሪክ፥ ስሙ የገነነ፥ ከሞት ያመለጠ ከእብደትም የዳነ?” ይለኛል።

ይህንን ሁሉ ብጽፍ፥ ቀን አልፎ ቀን ሲተካ፥ የኢትዮጵያ ታሪካችን የኛ፤ ደስ የሚለው ብቻ አለመሆኑ፥ አንድ አሌ የማይባል ሃቅ ስለጻፍኩ እራሴን አልወቅስም። በሁላችን ላይ የመጣ መዓት ከጠባዮቻችን ጋር ተደምሮ እኛን ጎዳን።

በመንፈሱ ዘለአለማዊ ሕያው የሆነውን ሰው ማሰቃየት፥ በተፈጥሮ ላይ ጥላቻን እንደ መግለጽ፥ የእግዚአብሔርንም ድንቅ ሥራ እንደ መንቀፍ ይቆጠራል። ሰውን ሰው ሲመታው እግዚአብሔርንም አብሮ እንደመታው ይቆጠራልና።

ሰው በሥጋው ሲያዩት ሁሉም ተመጣጣኝ ሰውነት ነው ያለው። የሁለት ግለሰቦች ነፍስ ሚዛኑ ሲታይ፥ ያንዱ እንደ አንበሳ ነፍስ አይነት ይሆንና፥ የሌላው ደግሞ የዶሮ ነፍስ አይነት ይመስላል። አንዱን ሰው እንደ አለት ከባድ፥ ሌላውን ደግሞ እንደ ዶሮ ላባ ቀላል የሚያደርግ፤ በአይን የማይታይ የነፍስ ክብደት፤ ከሰው ሚዛናዊ አስተሳሰብ ጋር የተዛመደ፥ የሰውን ጠባይ የሚወስን ነገር ምንድነው?

ሰው ለራሱ እውነት የሚለውን ሁሉ (ጠቅላላ ህልውናውን) ይህች ቀውስ ምድር ሳያስበው ግልብጥ ልታደርግበት ትችላለች። የራሱን እውነት በዚች የእውነትና ውሸት ዲቃላ በሆነች ምድር የፈተነ ሰው እራሱን ለአደጋ ያጋልጣል።

እውነት እውነት ስለሆነ ዘለአለማዊ ነው፤ ውሸትም ውሸት ስለሆነ ጊዜያዊ ነው። ታዲያ፥ ሰው ለዘለአለም የማይኖረው በተፈጥሮው ውሸት ስላለበት አይደለም እንዴ? አዎ! ልክ ነው። ለዚህ ማስረጃው፥ የሰው ልጅ ከተፈጠረ (ከተወለደ) ጀምሮ ትንሽ ትንሽ እየሞተ፥ ትንሽ ትንሽ ይኖራል። ነገር ግን ከእውነትና ውሸት አንዱ ማሸነፍ ስላለበት ከብዙ ትንንቅ በኋላ፥ በሥጋ ሞት ዘለአለማዊ ሕይወት ያቸንፋል፤ ሥፍራውን ለፍጹማዊና ዘለአለማዊ እውነት ለቀቀ ማለት ነው። ስለዚህ በምድር መኖር ማለት፥ በጊዜያዊ ውሸት እየተወጠሩ፥ በዘለአለማዊ እውነት መሰንበት ነው። አይደለም እንዴ?

ሰው ሲሞት፥ እውነት ከሙታን ተለይቶ ሲወጣ፥ ሥጋና ውሸት አብረው ሲቀበሩ፥ የሚያዝኑና የሚያለቅሱ ሰዎች በሞተው ውስጥ የነበረ እውነት እየታያቸው “የታለ እውነት? የታለ እውነት? ወዴት ሄደ?” እያሉ ያለቅሳሉ።

በጣም የሚያዝኑትን ሰዎች “እገሌ አልቃሻ ነው” ማለት ትክክል አይሆንም። ምክንያቱም ያ አልቃሻ የተባለው ሰው የቅርብ ወዳጁ ሲለየው፥ ለርሱ የሚታየው የሟቹ እውነት (ሟች የሠራቸው ጥሩ ሥራዎች ሁሉ) ለሌላው ላይታይ ይችላል። ከሥጋ ቁስል በስተጀርባ፥ የሰው ሃዘኑ “መንፈሳዊ መልክ” ሲያወጣ፥ ከሰው እድሜ በላይ ለሚኖረው መንፈሳዊ ሰብአዊነትም (ነፍስ) መልክ መስጠቱ ይቀራል?

ጥንትም ሆነ አሁን፥ በአለም ዙሪያ ከሚኖሩ ሰዎች መካከል፥ እንዲህ አድርጌ ገደልኩት እያሉ የሚያወጉ “ጀግኖች” ብዙዎች ናቸው። እንደዚህ አድርጎ ገደለኝ ብሎ የሚያወራ ግን አንድ አይገኝም። እንዴ! ለምን? - ሞቷላ! - ሞቷል እንዴ!

እነ እገሌ እና እነ እገሌን ስናስታውሳቸው
አንዳንዶቹ ጥይት የበላቸው፥
አንዳንዶቹ ግርፋት የገደላቸው፥
አንዳንዶቹ መሬት ወድቆ የተገኘ፥
በከፊል የተገኘ አካላቸው።
የእነ እገሌስ ይገርማል፥ ከሞት መትረፋቸው።
ከሞት ቢተርፉም፥ በአለንጋ ተሰንጥቆ
ተተፍትፎ ቆዳቸው፥
እንደ ታረሰ መሬት - መስመር አበጅቶ፥
መልክ (ከታራ) አውጥቶ ጀርባቸው፤
ካድሬዎችም ከአድር ባዮች ጋር ተወዳጅተው፥
ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቷቸው፥
ደም ከጠማው ንጉሣቸው፥
የሰው ደም አርከፍክፈው በየቀዬው፥
ሲፈነጥዙ በከተማው፤
አባት ከሞት የተረፉትን ሲቆጥር፥
እናት ከቤቷ ደጃፍ ተገድሎ የተጣለ ልጇን ታቅፋው ስትዞር፥
በድን ሲሆንባት የማይናገር፥

እርሷም በድን ሆና ስትቀር..።

ይህን እና የመሳሰለውን ሁሉ፥

ታሪክ ባይዘግበው፥

የምድሪቱ መንፈስ ይጮሃል፤

የሰው ገላው ሰንበር - ጠባሳው - ምልክቱ ይናገራል።

ኢትዮጵያችን ይሄን ሁሉ ታቅፋ ቆይታለች፤

አሁንም ጨካኞችን ታስተናግዳለች፤

የማትታዘብ፥ የማታስብ ትመስላለች።

አዬዬዬ... አዬ..ዬ...ዬ ..ሆይ! ..

አለ ወይ! አለ ወይ፥ አለ ወይ!

ተመልካች ከላይ! ...ተመልካች ከሰማይ!

በምድር የሚሠራውን ግፍ ሁሉ የሚያይ።

አለ ወይ! ተመልካች ከላይ! ተ..መልካች ከ..ላ.....ይ!

ተ..መልካች ከ..ሰ..ማይ።

አሁንም ከትርምስምስ ትዝታዎች መላቀቅ አልቻልኩም። እራሴን በራሴ ሳከም፥ ደግ ደጉን አስባለሁ፤ ወዲያው፥ ወደ ጊዜያዊ እውነታ መለስ ስል ደግሞ፥ የወገኖቼ ስቃይ ይሰማኛል። አንዳንዱን በመንደር መጽሔት (የድል ኮከብ) አስፍሬዋለሁ። ይኸኛው ግን ከቶ ከአንጎሌ አልጣፋ ብሏል። ይኸውም ትንሿ ልጅ ስትገደል፥ ቀሪዋ ስትጽፍ በዛው በኖርኩበት በመንደሬ የተፈጸመ ነው። ልክ መኪና በሰው እንደሚነዳ፥ የሰውም ልጅ በእርኩስ መንፈስ ሲነዳ በነበረበት ዘመን፥ እኔ ይኸንን የሚከተለውን በማየቴ፥ "በእውነት ይህቺ አለም ውስጥ ያለነው እኛ ሰው ብለን እራሳችንን የምንጠራው ፍጥረት ብቻ አይደለም፤ እርኩሳን መናፍስትም (ሰይጣናት፥ ጂኒዎች፥ አጋንንት..።) ከኛ ጋር ይኖራሉ - አሉ" እንድል አድርጎኛል።

ከታሪክም በላይ ታሪክ፥ ከትዝታም በላይ ትዝታ፥

እስቲ ስለ አንዲት ወጣት ልጃገረድ ጥቂት እናውራ ላንድ አፍታ።

ቀይ ቀለም ከብሩሽ ጋር በጉያዋ ሸጉጣ፥

ነጠላ ተከናንባ ከቤቷ ስትወጣ፥

የቀበሌው ዘበኛ ጠብ መንጃውን አንግቶ፥

የአውሬ አደን እንዳይመስልበትም ሰግቶ፥

ቀስ እያለ፥ ተከትሎ፥ መሄጃዋን አጣርቶ፥
ጓደኛዋም ብቅ ስትል አይቶ፥
ሥራ እንዳይበዛበትም ፈርቶ፥
ሁለት ሆነው ተገናኝተው ሲቀርቡ ከግርግዳው፥
ቀለሞቻቸውን ከጉያቸው አውጥተው፥
የኢሕአፓን መፈክሮች ሲጽፉ ባንድነት ተባብረው፥

ክንዱን አነሳ፥ አስተካከለ አፈሙዙን፥
ቃታውን ሊስብ አሾልኮ ጣቱን፤

በል፥ በል ሲለው እርኩስ መንፈስ በፍጥነት፥
ሳያስበው ሹልክ አለ ጥይት፤
አንዷን ከሩቁ አደባያት - ገደላት - አሳ..ረ..ፋት።
ሌላኛዋንም - ያው ገዳይ - የአባቷ ወንድም - አጎቷ ቀረባት - ሊገድላት።

ያቺ ትንሽ ወጣት ወዲያው ስትል ድፍት፥
ሰውዬውም ከሁለት ተከፍሎ በድንጋጤ ጭንቀት፥
ሲታየው የወደፊቱ ጸጸት፥
የገዛ መንፈሱ ሲነግረው፥ በማያውቀው ገብቶ የሠራውን ስህተት፥
ቶሎ፥ ቶሎ አሰበ፥ አሁንም ለርሱ ሥራ እንዳይበዛበት።

በሩጫ ወደ ጓደኛዋ - ወደ ወንድሙ ልጅ ተጠግቶ፥
እንዲህ ሲል መከረ፥ በድንጋጤ ተርበትብቶ፥
“ጓደኛሽ ስትገደል፥
አንቺ ሸሽተሽ አታመልጪም?
ደግሞስ ይህን የምትጽፊውን አታቆሚም?
አቁሚ ብዬሻለሁ፥ አንቺንም ሳላቃጥልሽ!
ተነስተሽ ሂጂ ሳልገድልሽ።”

ምንም ቢላት፥ በቁጣም መልክ ቢመክራት፥
በፍርኃት ተንቀጥቅጣ መሮጥ አቅቷት፥
ከዛው ቁጭ ብላ መጻፏን ቀጠለች፥
“ኢ.አ.አ.ጎ.ቴ!.....ጽ.ሑ.ፌ.ን ስ.ጨ.ር.ስ ት.ገ.ድ.ለ.ኛ.ለ.ህ!” እያለች።

**ተከፍተው እንዘጋም ያሉ አይኖች**

አይኖቹ የተመለከቱልኝ ከፉ ከፉውን ብቻ ከሆነ፥ እዚህ ላይ ልግታው በማለት፥ ጭንቅላቴን ወደተለየ አቅጣጫ አዘነበልኩትና የብቸኛ ወሬዬን ትንሽ ቀጠልኩ፤ እንዲህም አልኩ። ከልጅነቴ ጀምሮ ያየሁት የሰውን ልጅ ክፋት ብቻ ነው ብዬ አልዋሽም።

ከእለታት አንድ ቀን በልጅነቴ፥ እጅግ ርቦኝ ሳለ፥ በጎርጓዳ ሳህን ብዙ የስኳር ድንች (ሚጣጢስ) ቀረበልኝ። እኔም ሆዴ ጥግብ እስኪል ድረስ በላሁና የሚቀጥለውን አሰብኩ፡- “ወይ ጉድ! እንዲህ የሚጣፍጥ ነገር እስከዛሬም በልቼ አላውቅ፤ ከመጣፈጡም በላይ ሆድን ጥግብ ማድረጉ። ለመሆኑ ከዚህ የተሻለ ምግብ በአለም ላይ ይገኛል? ለንጉሡ በየቀኑ የሚያቀርቡላቸው ምግብ ይህን ሳይሆን አይቀርም” አልኩ።

ይህ በልጅነቴ ያሰብኩት ነው። ይህን በማሰብ፥ በዚች ትንሽ ነገር ሕይወቴን ያስደሰትኩበት ጊዜ ነበር ለማለት ስል ተናገርኩ። አዎ! በዚህ አለም ላይ መኖሬ ይህን በልጅነት አእምሮ የተቀረጸ ደስ የሚል ትእይንት አብራራልኝ፤ በጉልህ በተደጋጋሚ እንድመለከትም አደረገኝ፤ ሰዎችም በምግብ ሲደሰቱ አየሁ። አዎ! ዘመን አለፈና፥ አእምሮዬ ጎለመሰና፥ ሰውነቴ አደገና፥ አይኖቼም ቦግ - ቦግ አሉና፤ በወጣትነቴ የሚከተለውን ለማየት በቃሁ።

የዚህ አለም ሕዝቦች መደሰቻ ብዙ ብዙ ነገር እያለ፥ የኢትዮጵያ ሠፊው ሕዝብ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ ለስኳር ድንች (ለሆድ) ብቻ ሆኗል። ከፈላስፋው ከኤንጀልስ ዳስ ካፒታል ከተባለው የኢኮኖሚ መጽሐፉ፥ የሚከተለውን የኤንጀልስ ሕግ አስታውሳለሁ። “ድሃ ሰው በደኸየ ቁጥር፥ አብዛኛውን ገንዘቡን (ጊዜውንም) የሚያጠፋው ለሆዱ ብቻ ይሆናል” ይላል። ይህንን አባባል በማንኛውም መንገድ ብንመዝነው እውነት መሆኑ አይካድም። የእኛም ሀገር ሰዎች፥ ሠርቶ የማያልፍለትን፥ ከድህነት መላቀቅ ያቃተውን አሳዛኝና ምስኪኑን ሰው፥ እሱን ልክ እንደ አህያ “ተጭኖ ለሆዱ” ይሉታል።

ኑሮአችን ለሆዳችን ብቻ ከሆነ (ሥጋን ለማደለብ) ምንድነው የመኖር ትርጉሙ? መኖር ላለመሞት የሚደረግ ትግል ብቻ ሆኖ ከቀረ፥ ምንድነው የምድራዊ ሕይወት ትርፉ? እንስሳት ለምግብ ፍለጋ ይሮጣሉ፤ ሰውም እንዲሁ። ምንድነው ልዩነቱ? እህ! ሥጋን ለማደለብ ሳይሆን፥ ነፍስና ሥጋ እንዳይላቀቁ የደከሙት (የታገሉት) ወገኖቼ ትዝ አሉኝ። በደረቅ አይኔ የተመለከትኳቸውና ፎተግራፍ ያነሳኋቸው፥ በአፋር በረሃዎችና በወሎ ሸለቆዎች የሞቱትንና ለሞት የተዘጋጁትን ሁሉ አሰብኳቸው። ግን ይህንን ሳስብ፥ አእምሮዬ የትላንትናውን ከዛሬው፥ የዛሬውንም

ከወደፊቱ ጋር እያመሳጠረ ጭራሹኑ ሊያሳብደኝ ይችላል። እኔ ልከላከለው አልችልም። ስለዚህ፥ በጊዜ ውስጥ እንደ ጥላ የሚያልፍ ትእይንት ሁሉ በውስጡ ተስፋ እንደሌለው፥ እንደ ጨለማ ብቻ እንዳይሆን ይህንን ከዚህ ልግታው።

አዎ! ሲነገር በጥቅሉ፥ እንዲህ ይመስላል - ነበረ ማለታችን፥ ያለፈው እንዲሁም የወደፊቱን ሲያሳስበን፥ በየቀኑ በረሃብ ፍንግል፥ ፍንግል እያሉ ሲሞቱ የሚታዩንን፥ ስናስተውል - አሮጊት፥ ሽማግሌ፥ ሕጻናት ማለቃቸውን፤ አዎ! ሁሉ ነገር እንደ ጨለማ ብቻ እንዳይሆን በዚሁ እንግታው። በሀገራችን እልፍ አእላፍ ረገፉባት፤ አዛኝ ልብ ጠፋ፤ ጨካኝ ነገሡባት።

አእምሮም የራሱ አለም አለው። በውስጡ የሚከፈትና የሚዘጋ በር የለም፤ መጥፎ ለሚያስብ የአእምሮው ክፍል ክዳን አልተበጀለትም። ግን ሰው በተፈጥሮው ጭንቅ ሲለው፥ ይህ ጭንቀት ምክንያታዊ መሆኑን ለመግለጽ ሲል፥ አእምሮ በሃሳብ ይቀሰቀስና፥ ክፉ ክፉውን ከተደበቀበት ጓዳ እያወጣ፥ ፊት ለፊት ይደረድረዋል።

"እንግዲህስ ይኸውልህ፤ ከጭንቀት ለመግባትህ በቂ ምክንያት አለህ...." ሲል አእምሮ ለራሱ (የቀኙ ክፍል ወይንም የግራው፥ አንዱ ለሌላው) ያስረዳዋል። ነገር ግን፥ ተስፋ የማይቆርጥ ሰው መጥፎ መጥፎውን ያሳየኝ አእምሮዬ ጥሩ ጥሩውን ያሳየኛል በማለት በተስፋ ይጠባበቃል።

እድለኛ የሆነ ሰው፥ "ጥሩ አእምሮ" ያለው፥ በተስፋ ሲኖር፥ አዎንታዊ ይሆንና፥ ጥሩ ጥሩውን ብቻ እያየ ይኖራል። እድለ ቢሱ "መጥፎ አእምሮ" ያለው (መጥፎ አልኩ እንዴ?)፥ በተስፋ መቁረጥ ሲኖር፥ አሉታዊ ይሆንና፥ መጥፎ መጥፎውን ብቻ እያየ ይኖራል (እብደት የሚሉት አይነት??)። ደስተኛው ጥሩ አእምሮ አለው ይባላል፤ እርሱም ጥሩ አእምሮ አለኝ ይላል። የተከፋውም፥ መጥፎ አእምሮ አለው ይባላል፤ እርሱም መጥፎ አእምሮ አለኝ ይላል። አዬ! ጤነኛውን በሽተኛ የሚያደርግ፥ በሽተኛውንም ጤነኛ የሚያደርግ ጊዜ። "ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሠብራል፤" ይባል የለም?

የሃይማኖት መሪዎችም እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ እያሉ ይሰብካሉ። በገንዘብ በኩል የሚመጣ መበላለጥ ሳይቀር፥ የሆዳምነት ፍልስፍና ሳይጠፋ፤ የግለኝነት አስተሳሰብ ሳይደመሰስ፥ እውነተኛ ፍቅር ከየት ይመጣል?

በመጀመሪያ የሆዳምነትን ፍልስፍና ማጥፋት ሞራላዊ ግዴታ እንደሆነ፥ እንዴት ይህንን የሃይማኖት ሰባኪዎች አይረዱትም? (እነርሱም ሆዳሞች ሆነው ነው?) ገንዘብ የሚፈጥረውን መበላለጥ ተፈጥሮአዊ የሚያስመስሉትም አሉ'ኮ። ሰው ሁሉ መቶ በመቶ እኩል አለመሆኑን የማይገነዘብ የለም። እርግጥ ለመጠነኛ መበላለጥ ቅናት የሚያድርበት ሰው አይኖርም፤ ግን ፍቅርም የሚያካትተው መበላለጥ አለ፤ ፍቅርም

የማያካትተው መበላለጥ ይኖራል። ታዲያ፥ ከልዩነቶቻችን ሁሉ ባሻገር፥ አንዱ በገንዘቡ እንደ መልአክ ሲከበር፥ ሌላውም በእጦቱ እንደ ውዳቂ ዕቃ ሲጣል፥ እንዴት በሰዎች መካከል ፍቅር ሊመሠረት ይችላል? ይህስ መበላለጥ በሕብረተሰብና በሀገር አቀፍ ደረጃ ተባብሶ ስለቆየ አይደለም እንዴ ጦርነትን ያስከተለው?

ከመጠን በላይ የሆነ መበላለጥን ለማጥፋትና በሰዎች መካከል ጤነኛ ሰብአዊ ግንኙነቶች ተመሥርቶ፥ ሰዎች እርስ በርስ እንዲፈቃቀሩና በሰላም እንዲኖሩ ለማድረግ ሲሉ ሕይወታቸውን ያጡ የኢሕአፓ ሰማዕታት፥ ከምድር ምንም ክብር አልጠበቁም፤ ከሰማይም የድካም ዋጋ ይከፈለናል ብለው አልተመኙም (ይህንንስ ጭራሽ አላሰቡትም)፤ በሙታን ትንሳኤ፥ በመንግሥተ ሰማያትም መኖር የማያምኑ ናቸውና። ነገር ግን፥ በመልካም መንፈሳቸው (በቀና አስተሳሰባቸው) ሰማያዊው እድል ፈንታቸው ከጻድቃኖቹ ጋር ይደምራቸዋል፤ ምንም እምነት ሳይኖረው ጥሩ የሠራ በሥራው (ጽድቅ) ሰማያዊ ዋጋውን አያጣምና።

ሰውም በፍጥረቱ፥ አንዲት ለልጆቿ ሁሉ የምታስብ ደግ ምድር እናቱ፤ በዙሪያዋ የሚነፍስ ነፋስ አፍ አውጥቶ ቢያወራ፥ "ከጸብ ፍቅር ይበልጣል፤ ከስግብግብነት እርስ በርስ መተሳሰብ ይሻላል፤ ሰው እርስ በርሱ እንዳይተላለቅ፥ እናት ምድርም እንዳትጠፋ፥ ሰብአዊነት አእምሮ ገዝቶ፥ ምድራዊ አስተሳሰቡንም ግትቶ፥ የሰዎችን ሁሉ ሰብአዊ መብት የሚያስከብርና የማያዳላ ስርዓትን በሕብረት ቢገነባ፥ ለሁላችንም ጥሩ ይሆናል" ትል ይሆናል።

በየመንገዱ የተረፈረፈው የሰው ሥጋ በመኪና እንደተጨፈለቀ ቲማቲም ሲቆጠር በማየቴ፥ የሞቱ ሰዎች መንፈሶቻቸው ከመጮህ የማያርፍ በመሆኑም ነው እኔም የምለፈልፈው (ይመስለኛል)። እስትንፋሴ የእነርሱን ጩኸት ያስተጋባል (ይመስለኛል)።

አ! የኢትዮጵያ ተራሮች! ምን ነካቸው? ይህን የሰው ጩኸት አያስተጋቡም። ጋዜጠኞች ባገር የሉም፤ በኢትዮጵያ ዙሪያ ምድር ሰው እንደሌለባት ባድማ ሆናለች። ሌላው አለም ስለ ኢትዮጵያ ወሬ አይደርሰውም።

ቋሚዎች እውነቶቻቸውን በሚያንቀላፉ አእምሮአቸው ዘግተው ዝም ብለዋል (ረቂቅ የመኖር ፍልስፍና)። እያዩ የማይሰማቸው ሆነው ነው? ጥሩ (ምርጥ) አእምሮ ስላላቸው፥ አዎንታውያን (ደስተኞች) ሆነው ነው በተፈጥሯቸው? አዎ! ሁለት ተቃራኒ የሆነ አስተሳሰብ ያላቸው "ኃያላን" ሰዎች አስተሳሰባቸውን ለሕብረተሰቡ ያስተጋቡ እንደሆነ፥ የአስተሳሰብ ወገናዊነትን ይመሠርታሉ። ከሁለቱ አስተሳሰብ ውጪ በገለልተኛነት የተቀመጡ፥ አእምሮአቸውን ከጭንቀት በማውጣት፥ ከዚች

አለም ጋር "ካለ ቅራኔ" ለመኖር ሲሉ፥ ተፈጥሮን እየደለሉና እየተለማመጡ እድሜአቸውን ያራዝማሉ።

አንድ እውነተኛ ሰው ከምርምር እና ከሃሳብ ብዛት፥ ከሚያስበው እውነት እና ከራሱ እውነት በስተቀር የተቀረው አለም ትርጉም አልባ ይሆንበታል። እውነትን ፍለጋ ሰውነቱ (ሥጋው) የደከመ ግለሰብ፥ ወቀሳና ችግር ይደርስበታል፤ ደካሞች ሲዘባበቱበትና ሲያላግጡበት አካባቢውን መምሰል ያቅተዋል።

የሰው ልጅ ሕሊና አርፎ የማይተኛ በመሆኑ፥ እውነት እየተዛባ ፍርድና ፍትህ ተጓድሎ ሰዎች ሲቸገሩ እየተመለከተ፥ በገለልተኛነት መኖር የሚያቅተው ሰው ለማንኛውም አደጋ እየተጋለጠ የእሳት እራት ይሆናል።

አዎ! እውነት ያስፈራል፤ ህልውናም ያሳጣል። ገለልተኛ የሆኑ ሰዎች፥ በማንኛውም የአስተሳሰብ አውታሮች (በፖለቲካ፥ በሃይማኖት፥ ወ.ዘ.ተ...) በሰዎች መካከል የተካረረ አስተሳሰብ እየተከሰተ፥ ሰዎችን እርስ በርስ ሲያጣላ እና ሲያጋድል፥ "ይህ የሕብረተሰብ በሽታ ነው፤ እኛ ከደሙ ንጹህ ነን፤.." ይላሉ። ለእነርሱ ደስ የሚሰኛቸውን አዱኛ (ምድራዊ ሃብት) ሁሉ እየሰበሰቡ፥ በደስተኛነት ይኖራሉ፤ አለም የነርሱ ናትና።

የሰው ልጅ ተፈጥሮው የእውነትና የውሸት ዲቃላ፥
ሥራው ብዙ፥ የማይወደድ፥ የማይጠላ።
ባለ ምድራዊ ሥልጡን ሃቅ፥
እውነትን ከውሸት ደብለቅ፥
ትንሽ ትንሽ ማታለል፥ ትንሽ ትንሽ መስረቅ።
ከፊት ለፊት እውነት፥ ሃሰትም ከጉያ፥
ይህ ነዋ! እውቀትና ፍልስፍና፥
ኑሮና ብልሃቱን ማስማሚያ፤
ሁሉን እንደያመጣጡ መቀበያ፥
የውሸት ሳቅ መደለያ።

ይህች ምድር የተጣመመ እውነት፥
የተቃና ውሸት የበዛባት፥
ያልጠራ ሕይወት፥
ግማሽ ጤንነት፥ ግማሽ እብደት።

## የአለመሞት ምሥጢር

ከእለታት አንድ ቀን፥ በመሄድና በመንከራተት መካከል እንዳለሁ ቀኑ ጨለመና፤ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሆነ። ከአንድ የግንብ አጥር አጠገብ ስደርስ፥ በመጥፎ ሽታ አካባቢን መበከላቸውን ከምንም እንደማይቆጥሩ ሰዎች ለመሆን ወሰንኩ። ግን በቅድሚያ ይህ የኔ ውሳኔ ትክክል መሆኑን እና አለመሆኑን ሳሰላስል ብዙ ቆየሁ። ጨለምለም ካለ ሥፍራ ቆሜአለሁ፤ ሰውም ባጠገቤ አያልፍ። ሽንቴን ላለመሽናት ምን እንደሚከለክለኝ አላወቅሁትም። አንድ ግለሰብ በሁለት ሃሳብ ሲወጠርና መወሰን ሲያቅተው፥ መረጃዎችን ወደአእምሮ የሚያስተላልፉ ነርቮች መረጃዎቹን በቶሎ እንዳያደርሱ በየመንገዱ እክል ሲያጋጥማቸው፥ አንጎል አስቦ ወቅታዊ ውሳኔ መስጠት ሲያቅተው፥ ይህ ሁኔታ የግለሰቡን ታማሚነት እንጂ፥ ጠባዩን ወይንም ማንነቱን አይደለም የሚያንጸባርቀው።

የቀበሌ ዘበኞች ከሩቅ አይተው ወደኔ ሲጠጉ ሃሳቤን ለውጬ ሳልሸና ሄድኩ። ቶሎ ብዬ በአንድ ታጣፊ መንገድ ዞር ብዬ ካቅራቢያዬ ከሚገኝ ሻይ ቤት ገባሁ። ከሰዎች መካከል ለብቻዬ ጨለም - ደበቅ ያለ ሥፍራ፥ ጠረቤዛ ይዤ ቁጭ አልኩ። ዘበኞቹም በር ላይ ቆመው፥ በአይኖቻቸው ቃኘት ቃኘት እያደረጉ ሲፈልጉኝ፥ እኔም በሃሳቤ "የእናንተ የሦስታችሁም ደምወዝ ተደምሮ በአምስት ሲባዛ የሚከፈለኝ የመንግሥት ሠራተኛ ነበርኩኝ፤ ሥራዬን ጥዬ ለእናንተ በመታገሌ አታሳዱኝ፤ ሂዱ! ሂዱ!..." ብዬ በሃሳቤ አባረርኳቸው፤ እነርሱም ሄዱ።

በቆራጥ ውሳኔ ይህንን ጥብቅ ትእዛዝ ለማስተላለፍ የቻለው አንጎሌ ደስ አሰኘኝ፤ ግን ወዲያው ሊያስከፋኝ ነው መሰለኝ። ዘበኞችን በሃሳብ የሚያባርር አእምሮዬ የፊኛዬን ንጭንጭ ሊቋቋመው አልቻለም። አእምሮዬም "ቆይ ትንሽ ረጋ በል፤ ቆይ ትንሽ ረጋ በል..." እያለ፥ የተለመደውን ትእዛዝ ከማስተላለፍ አላቋረጠም። ለይስሙላ አንድ ሻይ አዘዝኩ። ሻዩን ሲያይ በላዬ ላይ ሊጨምርብኝ ነው ብሎ ነው መሰለኝ፥ ፊኛዬ ተነፋ፤ ተወጥሮ ከፋኛ አሳመመኝ። ወዲያው በጭኖቼ መሃል ሙቀት ተሰማኝ።

ከሻዩ የተለየ እንፋሎት ከወደ ታች ወደ ላይ እየተነነ ወደ አፍንጫዬ ሲገባ፥ ምን መሆኑ ገባኝ። ተነፈስኩ፤ ግን ሌሎችን እንዳይሸታቸው፤ እንዲህ ያለውም ነውር ይፈጸማል ብለውም እንዳይጠራጠሩ፥ ሻዩን በጠረቤዛው ላይ አፈሰስኩት፤ ወደ ሱሪዬም እንዲዳረስ አድርጌ። ይህ ሁሉ ሲሆን፥ ለካስ የሻይ ቤቱ ሠራተኛ ይመለከተኝ ነበር። ቀስ ብሎ ወደኔ መጣ፤ ጠረቤዛውን ጠራረገልኝና እንደ እናት በመንከባከብ፥ "አይዞህ! አይዞህ.." እያለ አበረታታኝ። ሌላ ሻይ ሊያመጣልኝ ሲል "አይ በቃኝ" አልኩት።

መታመም አለመታመሙን ለይቶ የማያውቅ አእምሮዬ መረታቱን አውቋልና፤ እስካሁን የተፈጸመው ሳይሆን የወደፊቱ ምን ይሆናል ብሎ ማሰላሰል ጀመረ። በማሰብ ብዛት ከባድ ድካም ላይ ስለሆነ፥ ዝም እንደማለት ብሎ፥ በቀሰስተኛ ድምጽ “መንገዱ ሁሉ ታጥሯልና፤ ያለው አማራጭ እራስን እንደማይፈለግ፥ እንደ አሮጌ እቃ ቆጥሮ መንገድ ላይ መጣል ነው” ይለኝ ጀመር።

የእውን እንቅልፍ፥ የሕልም ንቃት፥ ሰውን ለሞት አጋልጦ መስጠት፤ የሰው ሥጋ፥ ከአንገል እስከ ፊኛ ከዳተኛ። ሥጋዊ አብራኬ አናደደኝ፤ ከፉኛ አበሳጨኝና እንዲህ እያልኩ አካል ሰውነቴን ተራገምኩ፡- “ፈራህ? ሸሸህ? ዛሬ ባንዳነትህ ታወቀብህ፤ ጥለኸው ልትሄድ ከጀልክ? ክብሩን ሰውነቱን አዋርደህ፤ እወቅ አይለቅህም፤ ይጥልሃል እንጂ አትጥለውም።”

ይህን እና የመሳሰለውን ስፎክር፥ ስዝት፥ ሳስብ፥ በውስጤም ስነጋገር፥ ከፍርኃትና ከድንጋጤ ጋር ላብ አጠመቀኝ፤ እራሴ ዞረብኝ (አዞረኝ)። የባሰ ሳይመጣ ከዚህ ልውጣ አልኩ።

የሻዩን ዋጋ ከፍዬ ልወጣ ስል፥ የሻይ ቤቱ ሠራተኛ “ለፈሰሰ ሻይማ አትከፍልም” አለኝ። የጥንካሬ ምልክት በማሳየት እጁን ጭብጥ አደረገና፥ “አይዞህ! በርታ!...” ብሎ፥ በድጋሜ በማበረታታት አሰናበተኝ።

ከሻይ ቤቱ በር ወጣ እንዳልኩ፥ ቆሞ መራመድ ተሳነኝ፣ እንደሰከረ ሰው መንገዳገድ ጀመርኩ። ራሴን እያመመ ያዞረኛል፤ አይኔም አላይ ብሎ እንደ እውር እደናበራለሁ። በዛ ላይ ጨልሟል። ያ “እራስን እንደማይፈለግ፥ እንደ አሮጌ ዕቃ ቆጥሮ መንገድ ላይ መጣል ነው” ያለኝ የገዛ አእምሮዬ ልክ ሳይሆን አይቀርም አልኩ በልቤ። ቢሆንም እንኳ፥ አካባቢው “በእኔ ብጤዎች” እጅግ የተጨናነቀ ስለሆነ፥ የሰው እንቅፋት ከመሆን በስተቀር፥ እራስን መጣያ ሥፍራ የለም። መራመድ ሲያቅት፥ መቀመጫ ያና ማረፊያም ሲጠፋ፥...ግርግዳ በመደገፍ እየቆምኩም፥ እያረፍኩም፥ እንደምንም ብዬ ብዙ ተጓዝኩና ከአንድ በር ደጃፍ እንዘፍ አልኩ።

አይኔ ባይለየውም፥ አእምሮዬም ባይገነዘበው፥ እድል ፈንታዬ ነው ከዛች ከደጓ ሴት በር ላይ የጣለኝ። ግባ ብላ አስገባችኝ። አመጣጤ በጤናዬ አለመሆኑን በመረዳት፥ በተለየ የሃዘኔታ አቀባበል ተቀበለችኝ። ሁኔታዬ ሁሉ ቶሎ ስለገባት፥ “ሱሪህን አውልቅና ስጠኝ ልጠብልህ” ብላ አጠበችልኝና እንዲደርቅ ከወንበር ላይ ሰተረችው (አሰጣችው)፤ እጣቢውንም እንዳይሸት ከውጪ ራቅ አድርጋ ደፋች።

አዎ! በዚህ ምድር ላይም እንዲህ አይነት ደግነት ይሠራል። በሁለት ቦታ የተጠቀለሉ ብሮች ነበሩኝ። አንደኛው ነገ ጧት አውቶቡስ ጣቢያ ሄጄ ለኔና ለአሻግሬ የአውቶቡስ ቲኬት እንድገዛበት የታሰበ ይመስለኛል። ያለኝን ገንዘብ (23 ብር)

በጠቅላላ ባንድ ላይ አድርጌ፥ ሰዓቴንም ጭምር በካልሲ ውስጥ አስገብቼ፥ ካልሲውን ቋጠርኩና ከትራሱ ሥር አስቀመጥኩት (እኔ በደመ ነፍስ)፤ ጊዜው ሲመጣ ትወስደዋለች ብዬ።

የሰሞኑ እንቅልፍ እጦት አይኔ እንዳይከደን ማድረጉ ብቻ ሳይሆን፥ ሰውነቴንም አደንዝዞ ለመግደል የከጀለ ይመስላል። አእምሮዬ ግን "አንተ ከዳተኛ፥ አሻግሬ ቲኬቱን ለነገ ጧት እንድታደርስለት እየተጠባበቀህ አይደለም ያለው?" ይለኛል። በሌላ በኩል ደግሞ የቲኬቱ መገዛት ለምን እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም። የአውቶብስ ጣቢያ መንገዴን ለማስታወስ ብሞክር፥ ምንም ምንም ትዝ ሊለኝ አልቻለም። ታዲያ አሁን ትንሽ እንቅልፍ ቢወስደኝ ይሻላል እላለሁ። በሌላ በኩል ደግሞ፥ እዛው አውቶብስ ጣቢያ ካላደሩ ቲኬቱን መቁረጥ እንደማይቻል ይገባኛል። አውቶብስ ጣቢያው የት ነው? ኩዱ መቼ ተሠራና???? ጸጋዬ ስለዚህ ጉዳይ ምን የነገረኝ አለ? ለመሆኑ እስከዛሬ የት ነበርኩ? ለምን ቀደም ብዬ ቲኬቱን አልቆረጥኩም? ለማንኛውም ትንሽ ጋደም ብዬ ስነቃ፥ ሴቲቱን አቅጣጫ እጠይቃትና እሄዳለሁ" እያልኩ በሃሳብ ስንገላታ፥ መግለጽ በሚያስቸግር ስሜት ውስጥ ገባሁ።

የጭንቅላቴ መደንዘዝ ሁሉን ሃሳብ ሲዘጋብኝ፥ ቲኬት፥ ቲኬት፥ ቲኬት የምትለዋን ቃል ብቻ እንድትቆረቁረኝ ትቶልኛል። ይህን ብቻ ሳሰላስል እንቅልፍ ሊወስደኝ አልቻለም። ሰውነቴ የመደንዘዝ በሽታ ይዞታል፤ ተኝቼ ሳለ፥ እግሮቼና እጆቼ ለብቻቸው ነፍስ ያወጡ ይመስል ብርግግ ብርግግ ይላሉ። አዛጋለሁ፤ አይኖቼም ክፍት ዝግት ይላሉ (ይመሰለኛል)። ከእንግዲህ ምንም ተስፋ እንደሌለኝ የተገነዘበው ልቦናዬ ሰውነቴን በቁጥጥሩ ለማዋል ባለመቻሉ፥ ለአንድ ላልታወቀ ኃይል አሳልፎ ሳይሰጠኝ አልቀረም። ራሴን ሳትኩ። ባጠቃላይ የነበረኝ የበሽተኛ ምልክት ሴትዬዋን ሊያስተኛት አልቻለም፤ ፍርኃት ውስጥ ከተታት። ሰዓት እላፊ ደርሶ፥ ሰው ሁሉ በሩን ዘግቷል። ሴቲቱ "ምን ሆንክ? ምን ሆንክ?" እያለች ትወተውተኛለች (ይመስለኛል)። ከእኔ ምንም መልስ በማጣቷና ስለተጨነቀች፥ ጎረቤቶቿን ልትጠራ በሩን ከፍታ ወጣች።

ወዲያው ሴቶች ተሰባስበው እንደ ጉድ ይመለከቱኝ ጀመር። በዚህን ጊዜ አንዷ ሴት "ይህ ሰውዬ በእጃችን ላይ ቢሞት፥ ተጠያቂ የምንሆነው እኛ ሁላችንም ነን። ይልቅስ የቀበሌ ዘበኞች ጠርተን ቢወስዱልን ይሻላል፤..." ስትል ሰማኋት። እኔም ወዲያው ብድግ አልኩና፤ እርጥቡን ሱሪዬን ለበስኩና፤ ኮቴንና በካልሲ የተጠቀለሉ ብሮቼን ትቼ፥ ጫማዬን በደረቁ አጠለቅሁና፥ ከፊቴ የተደረደሩትን ሴቶች በመጣስ ገፈታተርኳቸውና ሩጫ ጀመርኩ።

እንደ ፈራሁት የቀበሌ ዘበኞች ተከተሉኝ። ያቺ ደግ ሴትዮም ከሩቅ ሆና "በእንቅልፍ ልቡ ሊሆን ስለሚችል አታስደንግጡት" የምትል ይመስለኛል። የእኔም

ፍላጎት በአንድ በኩል ለማምለጥ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ተኩሰው እንዲገድሉኝ እንጂ፥ ይዘው እንዳያንገላቱኝ ስለሆነ፥ ጠጋ ሲሉ ስሮጥ፥ ራቅ ሲሉ ስቆም፥ በመርካቶ ጠባብ መንገዶች ስሽሎኮለክ፥ ባንድ በኩል እንደ ሌሊት ጅብ፥ በሌላ በኩል ደግሞ እውነተኛ ሰው የሆንኩትን እኔን ሳልሆን፥ ሌሊቱን በሙሉ ሳልቆም፥ ሳልቀመጥ፥ እንዲሁ በእንቅልፍ ትእይንት ስንቀሳቀስ ሌሊቱ ተገባደደ።

ሊነጋጋ ሲል፥ እንደመንቃትም ያልኩ ይመስለኛል፤ አንድ ሰው ግቢ ውስጥ ገባሁ። ለመደበቅ የምሞክር ይመስለኛል። የመርካቶ ድሆች መኖሪያ አካባቢ በመሆኑ፥ ለመጸዳጃ በእጅ የተቆፈረ ሰገራ ውስጥ አንድ እግሬ ድንገት ጥልቅ አለ። ሁለት እግሮቼን የሚከት ቢሆን ኖሮ፥ እዛው ጥልቅ ብዬ በቀረሁ ነበር። እግሬን ከሰገራው አወጣሁና ከጨለማው ሥፍራ ተደብቄ ቆየሁ።

የጸሐይ ጮራ ሲፈነጥቅና በግቢ ውስጥ ያለውን ቁሳቁስ ሁሉ ሲያሳይ፥ አንዲት ሴት ብቅ አለች። እስካሁን ድረስ ሴቶች አዳኞቼ ናቸው፤ ከሞትና አደጋ ይጠብቁኛል። ይህች ሴት እኔ ሳላያት፥ እርሷ አስቀድማ ሳታየኝ አልቀረችም። ስለ ሁኔታዬ እንድትረዳና እንድታዝንልኝ፥ ከአፌ የወጣ ምንም እስትንፋስ፤ ወይንም የገጽ ምልክት አልነበረም። ነፍስ እንደሌለው የወደቀ እቃ ነበር ግርግዳ ተደግፌ የተቀመጥኩት። እርሷ ግን ስለ ሁኔታዬ ለመረዳት ደቂቃም አልፈጀባት። ወዲያው በባልዲ ውሃ አምጥታ በእግሬ ላይ አፈሰሰችልኝ፤ ማድረቂያ ጨርቅም አምጥታ ሰጠችኝ። ምናልባት ታወራኝም እንደሆነ ትዝ አይለኝም። “በል እንዳይመጡብህ ከዚህ ተደበቅ....” የምትለኝ ይመስለኛል።

ይህች ሴት ደግነትን እንደምታሳየኝ ገብቶኛል። በጣቶቿ አፍንጫዋን ይዛ አልሸሸችኝም፤ ለኔ ውሃ ለማምጣት ስትል ተጣደፈች እንጂ። አፏን በጇ ይዛ አልታዘበችኝም፤ ለእኔ ምክር ለመስጠት ስትል ለፈለፈች እንጂ።

የሴቶችን ደግነት ከልቤ እረዳዋለሁ፤ ሆኖም የሞተ ሰው ለማዳን በምታደርገው ጥረት አልተባበርኳትም። ፍርኃት ተደምሮ፥ ተደማምሮ ድፍረትን እንደሚያመጣ ሁሉ “ግድ የለም! ግድ የለም! እንደ ሌሎቹ ጓዶቼ ቀጥቅጠው ይግደሉኝ” ብዬ ቆረጥኩ።

እስኪገድሉኝ ድረስ ልታገል፤ ለአብዮታዊው ድርጅቴ፥ ለኢሕአፓ ያለኝን ታማኝነት ዛሬ ላስመስክር። በዚች በቀረችኝ ሕይወቴ “ኢሕአፓ ያቸንፋል” እያልኩ ልጨኽ። ይህ የመጨረሺያ ትግሌ ይሆናል። ይህም አብዮታዊ ቅስቀሳ ሰሚ ጆሮ ውስጥ ቢገባ፥ የሚያስብ የሕዝቦችንም የአእምሮ ህዋሳት ቢቀሰቀስና በኔ ምትክ አንድ ሰው እንኳን ለኢሕአፓ ቢገባለት፥ ይህ ብቻ ከእኔ የሚተርፍ እውነት መኖሩን ያረጋግጣል። ቼ ጉቬራም ይህንኑ ነበር ያለው፡-

“Where ever death might surprise us, it shall be welcomed, provided that this new battle crisis reach some receptive ears, and that those other men come forward to intone our funeral dirge with staccato of machine gunes.”

አዎ! “ሌሎችም በሙታን መቃብር ላይ የመትረየስ እሩምታ ያሰማሉ” ሲል፥ እኛ ብንሞት ምንም አይደል፤ ለእውነት ያደረግነው የኛ ትግል ይቀጥላል ለማለት ነው፤ ለእውነት ሲታገሉ የሞቱ እውነት የማይሞት መሆኑን ለሌሎች ያበስራሉና።

እኔም “ቅስቀሳዬን በዚሁ ልቀጥልና ዘበኞች ተኩሰው ይግድሉኝ፤ አሁን እኔ ብሞት፥ በውስጤ ያለ እውነት አይሞትም፤ ስለዚህ፥ ዛሬም ቢሆን ነገ የእኔን እውነት ሰምተው የሚቀሰቀሱ እንደሚኖሩ አምናለሁ” በማለት፥ በራሴው ቆራጥ ውሳኔ፥ ራሴን ለውጬ፥ ሌላ ሰው ሆንኩ፤ በሽታዬ ሁሉ ከእኔ ጠፋ፤ የእኔ ፍርኃት ከዚህ ላይ አከተመ። በዚህ አለም ላይ የመኖርና የመታገል ተስፋዬንም ባጭሩና በጉልህ ለአለም ሕዝብ ለማሳየት ቆራጥ ውሳኔ አሳለፍኩ።

በየመንገዱ የሚያጋጥመኝን ሰው ሁሉ “ኢሕአፓ ያቸንፋል” በሉ እያልኩ መጮህ ጀመርኩ። ትናንሽ ልጆችን እያስፈራራሁ በግድ ኢሕአፓ ያቸንፋል ማስባል ጀመርኩ። ይህ የመጨረሺያ የጣረ ሞት ትግል አስደሰተኝ። ብዙዎችን ኢሕአፓ ያቸንፋል አሰኘሁ።

የቀበሌ ዘበኞች ሲከተሉኝ እንዲገድሉኝ ብዬ ሮጥ ሮጥ እልባቸዋልሁ። ግን ተኩሰው አይገድሉኝም፤ ወይም አይይዙኝም። ከሩቅ ሆኜ ሳያቸው ከትናንሾቹ ልጆች ጋር ያወራሉ። “ያ ሰውዬ ምን አላችሁ?” ብለው ነው የሚጠይቋቸው። ልጆቹም፥ ዘበኞቹ ተኩሰው እንዳይገድሉኝ በማሰብ፥ “አብዮታችን ግቡን ይመታል ነው የሚለው” እያሉ የሚነግሯቸው ይመስለኛል።

ሮጬ፥ ሮጬ ሲደክመኝ ከአንድ ሥፍራ ተገትሬ ቆምኩ፤ የቀበሌ ዘበኞቹ ባጠገቤ ሲያልፉ አየኋቸው፤ በዚህን ጊዜ የራሴ መኖርና አለመኖር አጠራጠረኝ። አንገቷን እንደተቀነጠሰች ዶሮ፥ መንፈሱ ከውስጡ አፈትልኮ እንደሄደበት፥ እንደ “አንድ ሰው ብቻ” ሆኜ በሥጋዬ ብቻ ቆምኩ፤ ማንም አላየኝ። ግራ ገባኝና እንዲህ አልኩ “እኔ ማነኝ? እኔ ማነኝ? በእግዚአብሔር ለማላምን አንድ አቴይስት፥ ከየት መጡ ልሙት ስል እንዳልሞት የሚከላከሉ መላእክት?” የቀበሌ ዘበኞች ለይተው አውቀውኛል፤ ግን የቀይ ሽብሩ በረድ ያለበት ጊዜ ስለነበር፥ እንደበፊቱ ሥራ አልበዛባቸውም። “የት ይሄዳል፥ የትስ ያመልጠናል” ብለው ይሆናል የተውኝ።

በዚያው እለት ከረፋዱ (ይመስለኛል፥ ክፉኛ ተከታተሉኝ፤ አሁንስ የሚለቁኝም አልመሰለኝም። በተለያዩ እቅጣጫዎች ሲያጠምዱብኝ፥ መሄጃ አጥቼ፥

ከአንድ የቤት ጣሪያ ላይ ወጣሁ፤ እንዴትም ጣሪያ ላይ እንደወጣሁ አላስታውስም። የመርካቶ ቤቶች ትፍግፍግ ያሉ፥ ካንዱ ጣሪያ ወደ ሌላው በቀላሉ የሚዘለልበት ስልሆነ፥ ካንዱ ቤት ጣሪያ ወደሌላው ተሽጋግሬ መንገድ ዳር ካለው ጣሪያ ስደርስ ቆምኩ። አንድ ትንሽ ልጅ ከታች ቆሞ ቀለደብኝ። "በላ ዝለል! ዝለላ! አንተ የዘለልከውን እኔ የሚያቅተኝ ይመስልሃል? ዝለል እስቲ ጉብዝናህን እንይልህ!" አለ። ከጣሪያው ብዘል የማልሞት መሆኑ ገባኝ፤ እዛው ቁጭ ከማለት የተሻለ አማራጭ አልነበረኝም። ወዲያው የቀበሌ ዘበኞች ከጣሪያው ላይ ወጥተው ዙሪያዬን ከበቡኝ። ከየት እንደመጣ አላውቅም፤ ከዛው ከጣራው ላይ የምጽፍበትን ደብተርና እስክሪፕቶ አገኘሁ።[15] ይገርመኛል፤ ይህ ቀድሞኝ የመጣ ነገር - "የተገለበጠ አጋጣሚ...።"

ዘበኞቹን ችላ ብዬ መጻፍ ጀመርኩ። ልክ በየቀበሌው እንደሚደረገው፥ እራሴን የማጋለጫ ጽሑፍ የምጽፍ መስሏቸው ነው መሰለኝ፥ ቆመው ይጠበቁኛል። እኔ ግን ምን ነበር የምጽፈው? የጻፍኩትን የማላውቅ ነኝ እንጂ፥ ይህን ነበር የጻፍኩት ብዬ አልዋሽም፤ ይህንንስ ማስታወስ አልችልምና። ግን በዚህ አጋጣሚ የነበርኩበትን ሁኔታ ሳስበው ምናልባት የጽሑፌ ስሜቱ ይህንን ይመስል ይሆናል፡-

"ይድረስ ለጓዴ ለአሻግሬ፤ እንደምን ከርመሃል? እኔስ እንዲሁ በመንከራተት ላይ ነኝ። ግን እስካሁን አለሁ፤ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የማልኖር ስለሆንኩ ይህንኑ ልነግርህ ብዬ ነው የምጽፈው። ሳላገኝህ በመቅረቴ በጣም አዝናለሁ። ከቁጥጥሬ ውጪ ስለሆነብኝ ነውና አትፍረድብኝ። ሞተህም ከሆነ ከሰማይ ቤት፥ በሕይወት ካለህም በምድር፤ በእውነት እኔ ከልቤ ያላጠፋሁህ መሆኑ በደንብ ይገባህ ዘንድ በዚህ አጋጣሚ ይህንን ጻፍኩ።

ውድ አሻግሬ! ደህና ሰንብት ብዬ ስሰናበትህ፥ ሁላችንንም የሚያገናኝ የታጋዮች መንፈስ እንደማይሞት፤ ያሰብነውም ሁሉ በተለያዩ መንገዶች እንደሚስተካከል ተስፋ በማድረግ ነው። ካንተ ጋራ ሳወራ በነበረበት ወቅት ስሜቶቼን ሁሉ በዝርዝር ታውቃለህ።

የወደፊቱ ትውልድ፥ በእኔ በኩል ያለውን የትግል መንፈስ፥ የከሸፈ መንፈስ ቢመስልም፥ ከዚህ ደብዳቤ አውጥተው ይወስዳሉ። እነርሱም፥ "የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መብት በእውነተኛ ታጋይ ሕዝቦቿ መስዋእትነት ይመሠረታል። ሀገራችን ኢትዮጵያም ነፃነት እና እኩልነት፥ ሰላም እና አንድነት የሰፈነባት ሀገር ትሆናለች!" እያሉ ሲጮሁ ይሰማኛል። ላንተም ሕይወትህ ከወገኖችህ ጋር ሆኖ

[15] መቼም አንባቢያን "ይህ ሰው ይዋሻል" እንደማይሉ እተማመናለሁ።

እንደምትፈልገውና እንደምታስበው እንዲሆን የሚያደርግ ታላቁ አብዮታዊ ተስፋህ ምን ጊዜም ከልብህ እንደማይጠፋብህ አምናለሁ።

ከጓዶቻችን ኢሕአፓዎች ጋር ትደባለቅ ዘንድ ልባዊ ምኞቴን አስተላልፋለሁ። በሄድክበት የሕዝቦች ፍቅር ይጠብቅህ። ግን፥… አሻግሬ፤ አንተ ከኔ ስለምትሻል፥ ምናልባት በቀይ ሽብር ተገድለህ በመንገድ ላይ ተጥለህ ይሆናል። ብትሞትም፥ ከእንግዲህ በእኔ በኩል ጨርሻለሁና፤ ትግሌና ሕይወቴ በዚህ ላይ አከትሟል በማለት፥ ለማይበገረው አብዮታዊ መንፈስህ ነው የማወራው። እኔስ ትግል ከብዶኝ ሳይሆን፥ ለትግል የከበድኩ በመሆኔ ምክንያት ከምድር ገጽ መጥፋቴ ነው።

ምናልባት፥ እንዳጋጣሚ ሳልሞት ብቀር ግን፥ ለወሬ ነጋሪነት እንደሚተርፉ ሰዎች መሆኔ ነውና፤ ምንም አይደል! በአብዮታዊ ትግል ተሳታፊ ለመሆንና ታሪክ ለመሥራት ሳይበቁ ያበዱትም ቢሆኑ፥ መንፈሳቸው ለኢትዮጵያችን የሚሠራ እንጂ፥ የማያንቀላፋ መሆኑን በእርግጠኛነት እናገራለሁ።

ውድ አሻግሬ! አንተ ካልሞትክና እንዳጋጣሚ መድህን እና ጸጋዬን ካገኘሃቸው፥ አብዮታዊ ሰላምታዬን አስተላልፍልኝ። ምንም ባይሳካም፥ ስለደህንነቴ ስላሰባችሁልኝ አመሰግናለሁ በልልኝ። በል ደህና ሰንብት!..”

ካጠገቤ የቀበሌ ዘበኞች ጠብመንጃቸውን እንዳነገቱ ቆመው አይቻቸው አልነበረም? ወዴት ሄዱ? ከጣሪያ ላይ ቁጭ ብዬ የምጽፈውን እጽፍ ነበር። ስጽፍ ቆይቼ፥ “ከብዙ ሰዓታት፥ ወይንም ከጥቂት ደቂቃዎች?” በኋላ፥ በድንገትም ዞር ስል ዘበኞቹ የሉም። ይህም ሕልም እንጂ እውነት ባይሆን ይሻል ነበር። ግን ዘበኞቹ ጽሑፉ የማያቋርጥ ሲሆንባቸው ጊዜ፥ እንተወው፥ ጽሑፉን ከጨረሰ በኋላ እንይዘዋለን ብለው ይሆናል ጥለውኝ የወረዱት። እንጃ! ይህ ደግሞ ምን አይነት አጋጣሚ እንደሆነ ሊገባኝ አይችልም። ዞሮ ዞሮ ሁኔታዎች ሁሉ የሚስተካከሉት እኔን ለማሳበድ እንጂ እኔን ለመግደል አልሆነም። ግን በእውነት አእምሮዬን ሳልስት (ሳላብድ) የአንዳንድ ሁኔታዎች ክስተት (ያጋጣሚዎቹ ትርምስ) እስካሁን ይገርመኛል። እስካሁን በእኔ ላይ የደረሰ ሁሉ ማንንም ጤነኛ ሰው ያሳብደዋል ብዬ እገምታለሁ።

ከበላዩ ሆኖ፥ መውጪያ መግቢያዬን ሁሉ እየተቆጣጠረ የሚመራኝ አንድ ኃይል ሳይኖር አይቀርም። ይሁን፤ ምንም ይሁን ምን፥ እኔን፥ ሃሳቤን እና ኢትዮጵያን የሚገነጣጥል ኃይል አይኖርም። ደብዳቤውም ከማስታውሰው እያልኩ፥ አሁን ተጻፈ እንጂ፥ በዛን ጊዜ በዚህ ስሜት የተጻፈው ከዚህ የበለጠ የተብራራም ሊሆን ይችላል፤ አላውቅም።

ከጣሪያው ላይ በወጣሁበት አቅጣጫ ወረድኩ። ለጥቂት ደቂቃዎች እንደጤነኛ ሰው በሰዎች መካከል ተመላለስኩ። ማበድስ የተስፋ መቁረጥ የመጨረሻ

ደረጃው ይሆናል እንጂ፥ ባለ ርዕዮት ለሆንኩት ለእኔስ እብደት ማለት፥ ኢትዮጵያችንን ረስቶ፥ ከራስ ወዳድነት የተነሳ ለብቻ መኖርን መለማመድ ነው። ስለዚህ፥ እንደ እኔ አይነት ሰው ልበድ ቢልም አይችልም።

በዚች አለም ካለ ጭንቀት ለመኖርም ተስፋ መቁረጥና መሰናበት ለችግሮች ሁሉ አንዱ "መፍትሔ" መሆኑን አእምሮዬ በደንብ ስላስረዳኝ፡- "የመርካቶ እብድ ተብዬ ብቀር፥ ሌላውን እያስቸገርኩ በመኖር፥ በሕብረተሰቡ ላይ ሸክም ከመሆን በስተቀር፥ ሥጋዬ እየተወዛወዘ ለማንም ጥቅም አይሰጥም። ስለዚህ፥ ተፈጥሮ ቸርነቷን በኔ ላይ ለመግለጽ ከፈለገች፥ ይህን በእውር አይኔ ያየሁትን፥ በደንቆሮ ጆሮዬ የሰማሁትን፥ ባልበሰለ አእምሮ ያሰብኩትን ሁሉ ጥፍት አድርጋ፥ ሌላ አለም ውስጥ ትክተተኝ (በራሷ ትውሰደኝ)። አለበለዚያ ይህን እንስሳ የሆነ ሥጋ እኔው ራሴ ገድዬ ባሳርፈው ነው የሚሻለው" በማለት ቁርጥ ውሳኔ ሳደርግ ቆይቻለሁ።

በሌላም በኩል፥ "ግን ቆይ፤ በቅዱሳን ሬሳዎች ላይ የእውነት አበባ አለምልማ፥ የሌሎችን አስተሳሰብ በጥሩ ሽታ ታውዳለች፤ በኔ በኃጢአተኛው ሬሳ ላይ የምታድግ አበባ የምትገማ ከሆነስ፥ ሞቴም ለጥሩ ሳይሆን ለመጥፎ ሆነ ማለት ነው። አደለም እንዴ?" የሚል ሃሳብ አንገዳገደኝ።

ስለ ሞት ሳስብ፥ ከመጠን በላይ መንፈሴን ደስ ይላትና፥ ወዲያው ደግሞ ክፍት ይላታል። በሰውነቴ ላይ የሚደርስ ጉዳት፡- ረሃቡም ህመሙም፥ ሁሉም ወደ ሞት የሚያመራኝ እየመሰለኝ፥ የተደበቀ ደስታ ይሰጠኝና እንደገና ልውጥ ይላል። ግን ባጠቃላይ፥ የሥጋዬ መጎዳት አስቤው ከነበረው ጋር በመስማማት ወደ ሞት ከሚያመራው ጎዳና የሚከተኝ እየመሰለኝ፥ ከምን ጊዜውም የበለጠ ውስጣዊ ደስታ ይሰማኛል።

ምን ማለት ነው? መሞት ሌላ አዲስ ሕይወት መዝራት ይሆን? ያ አዲስ ሕይወት ያስደስታል ማለት ነው? ኮሙኒስት ስለሆንኩ፥ በሙታን ትንሳኤ አላምንም። ነገር ግን፥ አንድ የማላውቀው ነገር እንዳለ ገብቶኛል።

የመኪና መንገድ የማቋርጥ እየመሰልኩ መሃል መንገድ ላይ መቆም ጀመርኩ፤ ሹፌሮችን ከማናደድ በስተቀር የጠቀመኝ ነገር አልተገኘም። አስተሳሰቤ ሁሉ ሞት ላይ ቢያተኩርም፥ በተጻራሪ ሃሳቦቼ ምክንያት፥ ሞት በረከሰበት አለም ለሞት እንኳን የማልበቃ ሆኛለሁ።

ይህን የመሳሰሉ ድርጊቶች በላዩ ላይ የተፈጸመበት ሰው፥ እሱ ራሱ ደራሲ ከሆነ፥ እንደ ልብ ወለድ አድርጎ ውሸትን እየደባለቀ ካልጻፈ በስተቀር፥ በእውነት የተፈጸሙ ድርጊቶችን ሁሉ አስታውሶ መጻፍ ያስቸግረዋል። ደግሞም፥ ለቀጣይ ሕይወቱ በመሳሳት፥ አንዳንድ ለማመን የሚከብዱ ነገሮችን፥ ማስታወስ፥ መጻፍ፥

መናገርም አይፈልግም። ስለዚህ፥ የሚጻፈው ሁሉ፥ ከብዙው በጥቂቱ መሆኑን አንባቢ ያስተውላል።

የረሳሁት ባይኖር ወሬ በጣፈጠልኝ። ስለረሳሁት አሁን ዝም ልበል። የማስታውሰው ቢኖር፡- በንዑስ ከበርቴነት ሁለት አይነት ኑሮ - ደስ የሚል የቢሮ ሥራ እና ድብቅ አብዮታዊ ትግል። አሁን ሁለቱንም አጣሁ። አሲምባም ገብቼ ልታገል ብዬ የተማጸንኩት፥ አንድም የራሴን ሕይወት ለማትረፍ ይሆናል። የትም ሆነ የት፥ በምድር ለመኖር የሚያበቃ አእምሮ የለኝም።

ተስፋ መቁረጥ፥ ክህደት፥ ሃሳብ ማብዛት እና እልኸኛነት እኔን ወደ አንድ ሥፍራ ዳርጎኛል። አዎ! የማልዋሸበት፡- ሄድ ብያለሁ፤ እንደ ስካር ወይም እንደ እብደት አይነት አይደለም፥ በእውነት። ዝም ብሎ መሄድ - አይርብም፤ አይጠማም፤ አያምም (ሰው አያይህም፤ ሰውም አታይም)።

እና፥ በዚህ አይነት ብዙ ሰዓቶች አለፉና፥ ቀኑ ወደ መገባደዱ ተቃረበ። መቼም ሥጋ ለባሽ፥ ሥጋ ነኝና፥ ሥጋዊ ስሜቶቼ ቀሰቀሱኝ። እኔው ከእኔ ተገንጥዬ፥ ከሄድኩበት ተመልሼ መጥቻለሁ። የቀን ጸሐይ ሙቀት ከጧቱ ብርድ አላቆ ተሲአት (እኩለ ቀን) ላይ ሲያቃጥለኝ እንደነበረ ትዝ ይለኛል።

ልክ እንዳሁኑ አይነት፥ ደስ የሚል የጸሐይ ሙቀት ትዝታ አለኝ። ይኸውም፥ በልጅነቴ (እድሜዬ አስራ አንድ ዓመት ብቻ ነበር)፥ በሳር ልምላሜ የተሸለመ ኮረብታ ላይ ከብቶች ስጠብቅ፥ ድክም ብሎኝ፥ ከአንድ ገላጣ መሬት ላይ ጋደም እንዳልኩ ድብን ያለ እንቅልፍ ወሰዶኛል። በእንቅልፍ ልቤም ቢሆን፥ የጸሐይ ሙቀት በሰውነቴ ሰርጎ ስለገባ፥ ሰውነቴን ደስ አሰኝቶታል። በሥጋዬ የተደሰትኩት ከጸሐይ ሙቀት የመጣ ደስታ ምን ያህል እንደሆነ ለመግለጽ ቃላት ያጥሩኛል። ነገር ግን፥ የዛን ጊዜ ይህንን ደስታ የማጣጥመው በሕልም አለም ሳለሁ ነበር እንጂ፥ በእውን አለም አልነበረም።

ከእንቅልፌ ድንገት ብንን ስል፥ ያ የሕልም ደስታ ወዲያው አልለቀቀኝም ነበር። ያንን ከእንቅልፍ አለም ተከትሎኝ መጥቶ ደስ ያሰኘኝን ደስታ ለመግለጽ ያዳግታል። ለተወሰኑ ደቂቃዎች፥ የከብቶቼን መሰወር እስከረሳ ድረስ ደስ ብሎኛል በእውነት። "በጸሐይ ጮራ ብቻ ይህን ያህል ደስ ካለኝ፥ እዛው እሷጋ የሚሄደው በእሳት የማይቃጠለው ነፍሴ ከዚያ ሥፍራ ቢሄድማ እንዴት ደስ ባሰኘኝ!.." እያልኩ እንዳስብ የሚያደርግ የተለየ፥ ግን ተመሳሳይ ነገር ካጠገቤ መጣ።

እንደ ቀድሞው አይነት፥ ከጸሐይ ጮራ በሚመጣ ሙቀት ሰውነቴ ግሎ ደስ እያሰኘኝ ነው። ግን፥ በዚያ በተገኘሁበት ሥፍራ - በአካባቢዬ ቁሻሻ እንጂ፥ የለመለመ

ሳር የለም። ትርኪ ምርኪ እንጂ ሜዳ የለም። ከብቶችም የሉም፤ ሰዎች ግን፥ ከሩቅ ይታያሉ።

የሰው ልጅ ራሱን ነፃ ለማውጣት ሲል ተክለ ሰውነቱን ከራሱ ላይ አያራግፍም፤ ግን ሁኔታዎች ከሁለት አለም እየመሩት፥ *ሥጋዊ* ማንነቱን እስኪስት ድረስ ያንገላቱታል፤ ወደ አልታሰበ *ሥፍራም* ይከቱታል። "እውነተኛ" *መንነቱን* የማይስት ሰው በውስጠ መንፈሱ ይኖራል እንጂ፥ አይሞትም።

ንኡስ ከበርቴዎች ከማይደርሱበት "*ሥፍራ*" *መቆሜ*፥ *መቀመጤም* ትዝ ይለኛል። *ጋደም* ማለቴን አላስታውስም፤ እንደ እንቅልፍ አይነት ሰመመን ውስጥ ገብቼ ያለሁበትን እስክረሳ ድረስ ለተወሰኑ ሰዓታት (ወይንም ደቂቃዎች) ያህል እራሴን ከራሴ ሰውሬአለሁ፤ እጅግ ደስ የሚያሰኘው የጸሐይ ጮራ ሞቅታ፥ የቀኑም መርዘም ትዝ ይለኛል። በቃ ይኸው ነው።

እውነተኛ ኮሙኒስቶችም፥ በምድራዊ ኑሮአቸው ውስጥ ስለ ሰዎች እኩልነት ብዙ በማሰብ ምክንያት፥ ጭንቀት በማብዛታቸው፥ ምድራዊውን ከሰማያዊው መለየት አቅቶአቸው ነው እንጂ፥ በውሱን አእምሮአቸው፥ ለእውቀታቸውም ገደብ እንዳለባቸው ያውቃሉ።

አካላዊ *ሥጋ* ሞቶ (አፈር ቢሆንም)፥ ጥፍት ብሎ ወደ አካላዊ "ምንምነት" ቢለወጥም፥ ያ "ምንምነት" ለእኛ በእግዚአብሔር ለምናምን ኮሙኒስቶች ሕያው ነፍስነት ነው። ሰው ሆኖ የተፈጠረ በውስጡ መንፈስ የሌለው የለም። ስንሞት ጭራሹኑ እንጠፋለን የሚሉ በእግዚአብሔር የማያምኑ (አቴይስቶች) ናቸው። እኛ ግን፥ ኮሙኒስት ብንሆንም፥ እግዚአብሔርን አንክድም። እኛ *ሥጋ* ብንሆንም፥ መንፈስ (ሕያው ነፍስ) አለን - ወደ ፍጹማዊ ምንምነት አንለወጥም።

እኛ ሕያዋን ነን፤ እንደ ከዋክብት የታመቀ *ኃ*ይል ያለን። ጥፍት ብንልም፥ ጥፍት ብለን ብቅ የምንል ነን እንጂ፥ ጠፍተን የምንጠፋ - ወደ ዘለአለማዊ ምንምነት የምንለወጥ አይደለንም።

# ምዕራፍ ሰባት

## ቀጣይ ሕይወት በከፍተኛ አምስት

ከሰዓት በኋላ ይመስለኛል። መንገዴን ወደ ሰሜን አመራሁ። ከሩቅ ለሩቅ አንድ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ታይቶኛል። ይህም አውቶብስ ወደ ደብረ ሊባኖስ የሚወስድ ነበር። ለኔ ግን፥ አውቶብስ ሁሉ ወደ ኮረም የሚወስድ መስሎኛል። አሁን የጠፋብኝ ሁሉ ተገኘልኝ አልኩ። ታጋይ ጓዶቼ ከሚገኙበት የሚያደርሰኝ መስሎኝ፥ እንዳያመልጠኝ ብዬ ወደ አውቶብሱ ሮጥኩ። አውቶብሱ ዘንድ እንደ ደረስኩ ተሳፋሪዎቹ ሁሉ ቦታ ቦታቸውን ይዘው ቁጭ ቁጭ ብለዋል። ሹፌሩም ሞተር አስነስቶ ከውጪ ቆሞ ከሰዎች ጋር ያወራል።

ከአይኔ ተሠውሮ የቆየውን አውቶቡስ ዛሬ አየሁት። የአውቶቡስ ቲኬት የለኝም፤ መግዢያ የሚሆን ምንም የለኝ። ምን ማድረግ እችላለሁ። አንዱ አልሆን ሲለው ሌላ ከመሞከር የማይሰለች አእምሮ አሁንም "ሊመክረኝ ወይንም ሊያታልለኝ" ነው። ጭንቅላቴ መሥራት አለመሥራቱን በጥቂት ሴኮንዶች ውስጥ ፈተንኩት።

ሰዎች አውሮፕላን እንደሚጠልፉት አይነት አሳሰበኝ። ተንደርድሬ ካውቶብሱ ገባሁና የሹፌሩ መቀመጫ ላይ ቁጭ ብዬ ለመንዳት ተዘጋጀሁ። ወዲያው ማርሹን ወደ አንደኛ ማርሽ ለማድረግ ስታገልና ቤንዚን መርገጫውን በእግሬ ስፈልግ፥ ሹፌሩ ዘሎ ገባና እጄን ያዘኝ። ከዛም ከሹፌሩ ጋር ትንንቅ ሆነ።

የቀበሌ ዘበኞች ከአውቶብሱ ገቡ፤ ሁኔታውንም አይተው ትንንቁ ወደ መጥፎ እንዳያመራ ቶሎ ብለው እጆቼን ከሹፌሩ እጅ አላቀቁ። ወዲያውም ተሳፋሪዎች "ይህ እብድ ገደል ሊከተን ነበር እኮ! ወይ ጉድ! ሊጨርሰን?.." እያሉ ተንጫጩ። የቀበሌ ዘበኞች በጠመንጃ እየጎሻሸሙ ከፊትለፊታቸው እንድሄድ አስገደዱኝ፤ እያዳፉ ከቀበሌ እስር ቤት ከተቱኝ። ከዛ እንደደረስኩ፥ መሬት ላይ አጋድመው ረጋገጡኝና በጠብመንጃው መዳፍ ደበደቡኝ። ሰውነቴ ደንዝዞ ነበር መሰለኝ ብዙም ህመም አልተሰማኝም።

መሬት በደረቴ ተኝቻለሁ። አንዱ የቀበሌ ዘበኛ በጆሮዬ የጠመንጃውን አፈሙዝ ከተተና ማንነቴን ለማወቅ ይጠይቀኝ ጀመር። ሁሉም ተራ በተራ በጥያቄ አጣደፉኝ። እኔም ቶሎ ቶሎ መለስኩላቸው፤ ግን አፌ ከመሬቱ ጋር ስለተጣበቀ፥

ድምጼ በደንብ አይወጣም ነበር። *"ሥራህ ምንድነው?"* ሲሉኝና ስመልስላቸው፥ የንግድ ሚኒስቴር፤ ወታደር ነኝ..." ያልኩ፤ ቢመስላቸው፥ "ዘበኛ ነኝ፤ ነጋዴ ነኝ፤ ሥራ ፈት ነኝ...." ብላቸውም፥ ቀብጠርጠር በማድረግ፥ ከነርሱ ጥያቄ የኔው መልስ እንዲበረከት።

ከመካከላቸው አንዱ "መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ታውቀዋለህ?" ብሎ ጠየቀኝ፥ "አዎን አውቀዋለሁ፤ እርሱ ወታደር ነው፤" አልኩ፤ ቀስ ብዬም እገድለዋለሁ ያልኩ ይመስለኛል (እኔው ራሴ በውስጤ ሁለት ሰው እንደሚያወራ ሆኛለሁ)። ቀስ በሚል ድምጽ ብዙ አወራሁ። "ምንድነው የሚቀባጥረው ይህ ሰው? ኮሎኔል መንግሥቱን ታውቀዋለህ ወይ?" ነው የምንልህ" ሲሉኝ፥ እኔም ቀስ ብዬ "አዎ አውቀዋለሁ" ስል፥ ጓደኛዬ ነው ያልኳቸውም ይመስላቸዋል።

በጆሮው ላይ የጠመንጃ አፈሙዝ የተተከለበት ሰው ጮክ ብሎ ካወራ፥ ከጠመንጃው ቃታ ውስጥ ያሉ ጥይቶች በድንጋጤ ተፈትልከው ይወጡና ሰው ይገድላሉ (ይህን ሊያውቅ የሚችል የደረሰበት ብቻ ነው፥ ሌላ ሰው ይህንን አያውቅም)። የጠብመንጃውን አፈሙዝ በጆሮዬ ቀዳዳ ከትተው ሲገፉት፥ ልክ ሃኪሞች ቀዶ ጥገና ሲያደርጉ ለማደንዘዢያ መርፌ እንደሚወጉ አይነት ሆነልኝ። የሚያም ደስታ ሲሰጠኝ፥ "ከእንግዲህ ቢተኩሱም አይሰማኝ.." እያልኩ እንዳስብ ያደርገኛል። ግን ደግሞ፥ እራሴንም ከመሬቱ ፍትግ ሲያደርጉት ህመሙ ያነቃኛል። ታዲያ፥ የዛን ጊዜ፥ በጠመንጃቸው አፈሙዝ ጆሬዬን ሲኮረኩሩትና ሲጎሻሽሙት ይገድሉኝና ያሳርፉኛል የሚል እምነት ቢያድርብኝም፥ ለመትረፍም እየጓጓሁ፤ ቀብጠርጠር እያደረግሁ እብድ መስዬ ስለፈልፍ፥ በቋንቋም ግራ አጋባኋቸው።

ይህን ከመሬት የተደፋ ሰው መግደል ለምን እንዳስፈለገ የባለጠብመንጃው ሕሊና እየተመራመረ እንዲቆይ እንጂ፥ ቶሎ ብሎ ቃታውን ስቦ እንዳይገድለው ለማድረግ፥ እንደ ህጻን መንተባተብ እና እንደፈላስፋም አጣርቶ መናገር አስፈለገ።

የመርማሪው ሰውዬ አእምሮ ከጥሩው መንፈሱ ጋር ተወያይቶ እንዲምረኝ ጊዜ ለመስጠትም ነው - ይህ 'ማይደል በሕይወት ለመቆየት የሚያስችል ተፈጥሮአዊ ብልሃት? (ምንኛ ብልጥ ነኝ!)።

ሰው እንዳይሞት እንዲሞትም የሚያደርጉትን ምሥጢሮች፥ አውቀንም፥ ሳናውቅም እንጠቀምባቸዋለን። የሰው ልጅ ሁሉ የሁለትነት ጠባይ በከባድ ሁኔታዎች ሲፈተን፥ አንዱ ሰው ከውስጡ ራሱን ለመግደል ሲታገል፥ ሌላው ሰው ደግሞ ከውስጡ ራሱን ለማዳን ሲታገል፤ ከሁለት የአንዱ የመሰናበቻያ፤ የሌላውም የመቆያ ምሥጢር።

የጠመንጃውን አፈሙዝ ከጆሮዬ ዞር አድርገው በእርጋታ፥ "ሊቀ መንበሩን (ጓድ መንግሥቱን) የት ነው የምታውቀው? አጋዴን ነው ሐረር?" ብለው ሲጠይቁኝ፤ እኔም ሊቀ መንበር የተባለው ቃል ግራ እንዳጋባኝ ሆኜ፥ ቶሎ ቶሎ እየደጋገምኩ፥ "የት ነው ያለሁት? የት ነው ያለሁት? የት ነው ያለሁት?" ማለቴ በጣም ትዝ ይለኛል። በዚህን ጊዜ አንዱ ዘበኛ "ይገርማል! ከህመሙ ይልቅ፥ የት እንዳለ ማወቁ ባሰበት፤ ምን ፍጥረት ነው ይሄ?" በማለት፥ በአጋዴን ያለሁ መስሎኝ የምለፈልፍ መስሎት እንደሆን እንጃ፥ "ይህ ሰው በአጋዴን በረሃ ችግር ደርሶበት ያበደ ወታደር ነው" ብሎ ደመደመና ሌሎቹንም አሳመናቸው።

ሌላው ዘበኛ "እባክህ ይህንንስ እብድ እዛ ወስዶ መጣል ነው" ይልና፥ ከአንድ የእቃ ማስቀመጫ ክፍል ውስጥ ዘግተው ይተውኛል። ረስተውም ሆነ አውቀውም እንደሆነ አላወቅሁም፤ ለሦስት ቀናት በሩን ከፍቶ የተመለከተኝ አልነበረም። እኔም ሌትና ቀን ጨለማ በሆነበት ሥፍራ ሰነበትኩ። ደግነቱ በጭላንጭል አንድ ትንሽ ከረጢት አይቼ ነበርና፥ ከፈት ሳደርገው በውስጡ ስኳር አገኘሁ። ቀስ ቀስ እያልኩ ሁሉንም ስኳር ቅሜ ጨረስኩ፤ ይህም ለሦስት ቀን ምግብ ሆነኝ።

በዚህ እስር ቤት ውስጥ ሆኜ፥ ብዙ ብዙ ለሰው መግለጽ የሚያዳግት አስገራሚ ትእይንቶች ታዩኝ። ግን ይህ ነው ብሎ መናገር የማይቻል በመሆኑ፥ እስከ ዛሬ ድረስ ምን ነበር ያየሁት የሚለውን ለእኔም ለራሴ ማወቅና መረዳት ያቅተኛል። ግን ከሁሉም በላይ ብዙ ወጣቶች (ወንዶችም ሴቶችም) ይታዩኛል፤ የማድናቸውም ይመስለኛል።

የመርካቶ ቀበሌ ሠራተኞች፥ እንደ ስምጥ ሸለቆ ከብት አርቢዎች ወሬ ቶሎ ቶሎ ይለዋወጣሉ መሰለኝ፤ በሦስተኛው ቀን ከየት ተነስቼ እዚህ እንደደረስኩ ተመርምሮ ስለተደረሰበት፥ ወደ ሌላ ቀበሌ እንድሄድ ተደረገ።

ለመሸጥ ወደ ገበያ እንደሚነዳ በግ፥ በከተማ መሃል፥ ጠብመንጃ ባነገቱ ሰዎች እየተነዳሁ፤ ሁለተኛውን ቀበሌ አልፌ ሦስተኛው ቀበሌ ደረስኩ። ይህ ቀበሌ ያች እናት የሆነች ደግ ሴት ያለችበት ቀበሌ ነው። ከቀበሌው እንደደረስኩ፥ ያቺን ደግ ሴት ከቀበሌው ጽሕፈት ቤት ቆማ አየኋት። "ይህ ነው ወይ?" ብለው ሲጠይቋት ሰማሁ። እርሷም እኔን ስታየኝ እንባዋ ቅርር አለና፥ በቀጭን ድምጽ "አዎን" አለች። ከዛም በጇ የያዘችውን ኮቴን እንድትሰጠኝ አደረጉ።

"ሌላስ ከርሷ የቀረህ እቃ አለህ?" ብለው ጠየቁኝ። በዚህን ጊዜ ትኩር ብላ አየችኝ። "አንተ ተናዘህልኝ የሄድከውን ገንዘቡንና ሰዓቱን፥ አሁን አልሞትኩምና መልሺልኝ.." የምላት መስሏት ይሆን? አልኩ በልቤ። አይ፥ ይህ የኔ እስተሳሰብ ነው። እርሷ ግን በድምጽ አልባ ንግግር፥ በሕይወት በመትረፌ ፈጣሪዋን ማመስገኗ መሆኑ

ገባኝ። ወዲያው ብንን እንደማለት ብዬ፥ “የለም፤ የለም፤ የለም፤ ምንም የቀረ የለም” አልኳቸው። እንደገናም ጠየቁኝ፤ እኔም ምንም የቀረኝ አለመኖሩን በማረጋገጥ መለስኩላቸው።

እርሷንም “በይ ሂጂ!” ተብላ ልትሄድ ስትል፥ ፊቷን በትንሹ ወደ እኔ ዞር አድርጋ፥ ለእኔ ብቻ እንዲገባኝ፥ ሌሎች እንዳይገባቸው አድርጋ፤ ምስጋናዋን ከምርቃት ጋር በፍቅር የሞቅታ ሞገድ ላከችብኝ። የርህራሄ ስሜቷን እና ፍቅሯን፥ በገጽታ ንግግሯ ለኔ ብቻ ለመግለጽ በቅታለች (የሴቶች ችሎታ)። ምስኪን ሴት፥ በቀስታ “እግዚአብሔር ይጠብቅህ!!!” ብላኝ ነው የሄደችው።

እኔም፥ “አንቺ ሴት ገብቶኛል ደግነትሽ፥ በሄድኩበት ደግፎኛል መንፈስሽ፤ አዙሮ፥ አዙሮ አቁሞኛል ከፊትሽ። በይ ሂጂ ግቢ ከቤትሽ.....” ብዬ አንገቴን ወደ መሬት ደፋሁ። ሴቲቱም ካጠገቤ ርቃ ሄደች፤ ሄደች የደግነቷን መንፈስ ከበስተኋላዋ ትታ።

“በል ልበስ!” ተባልኩ፤ በቁጣ። ኮቴንም ለበስኩና እጆቼን ቶሎ ቶሎ ወደ ኪሶቼ መክተትና መፈታተሽ ጀመርኩ፤ እቃ ጠፍቶት እንደሚፈልግ ሰው ሆንኩና። የጻፍኩበት ደብተሬ የለም። “ጽሑፌን ከዚች ደግ ሴት መላእክት (ወይም ኢሕአፓዎች) ወስደው ያነቡታል፤ ሁሉም ደግ ነው...፤” አልኩ በልቤ።

ከኮቴ የጉያ ኪሴ እጄን ሳስገባ የሆነ ወረቀት አገኘሁ። ስመለከተው የቀበሌ የፈቃድ ወረቀት መሆኑ ትዝ አለኝና ቶሎ ከአፌ አስገባሁና ማኘክ ጀመርኩ (ይህ ነው የሰው ልጅ የአርባ ቀን እድሉ፥ ሴኮንድ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ የሚወሰን)።

ዘበኞች አንዴ ዘለው አፈኑኝ። አፌን ጥርቅም አድርገው ይዘው ወረቀቱን ከአፌ አወጡት። የቀበሌ የፈቃድ ወረቀት መሆኑን ሲረዱ፥ እውነትም እንደተጠራጠሩት ተራ እብድ ሳልሆን፥ እውነተኛ የኢሕአፓ አባል መሆኔ ገባቸው።

ሁሉም እንደ የማርያም ጠላት በየተራ ደበደቡኝ፤ ቀጠቀጡኝ፤ ወገሩኝ። እውነተኛ ዱላ የቀመስኩት የዛን ጊዜ ነው። ሁለት እጆቼን የኋሊት በገመድ ጥፍር አድርገው አስረው፥ እያዳፉ ወደ ከፍተኛው ጽሕፈት ቤት (እስር ቤት/ከፍተኛ አምስት) ወሰዱኝ።

የመርካቶ ከፍተኛ አምስት እስር ቤት እንደደረስኩ፥ የታሰሩ ወጣቶች ውጪ ተፈቅዶላቸው፥ ተደርድረው አየኋቸው። በዚህን ጊዜ ሦስት ቀን በቀበሌ ታስሬ ሳድር ካየሁት ትእይንት ጥቂቱ ግልጥልጥ ብሎ ታየኝ። በእውነትም የራሴን ሕይወት አሳልፌ በመስጠት እነኚህን ወጣቶች ለማዳን የምችል መሰለኝና የሚከተለውን አሰብኩ፡-

“ከጥቂት ወራት በፊት፥ ቀበሌዎች ድንገት ቤቴ ቢመጡብኝስ እያልኩ የኢሕአፓ ጽሑፎችን እደብቅ ነበር። ትዝ የሚለኝ፥ እኔን በዚህ ምክንያት

እንዳይገድሉኝ ብዬ ከኢሕአፓና ከአንጃዎች የሚደርሱኝን ጽሑፎች  ከቤቴ ውስጥ ሊገኝ ከሚችል የመደበቂያ ሥፍራ ሁሉ ደበቅሁ፤ በመጨረሺያም በጓሮ በኩል መሬት ቆፍሬ ቀበርኩ።  የእነኚህ ወጣቶች እናቶች ደግሞ፥ ልጆቻቸውን ለመደበቅ ወደ ማህጸናቸው መልሰው መከተት ብቻ ሲቀራቸው ሁሉን አደረጉ። እነኚህ ከፊት ለፊቴ የሚታዩት ወጣቶች ከዛ ሁሉ ድብቃ በኋላ፥ ከተገደሉት የተረፉት ናቸው እኮ! ዛሬ ለእነኚህ ወጣቶች ስል እሞታለሁ፤ ዛሬ ለእነኚህ ወጣቶች ስል እሞታለሁ፤ ለመሞቻዬ የሚሆነኝ በቂ ምክንያት አሁን ገና አገኘሁ!" አልኩና ከሥጋ ቁጥጥር ውጪ የሆነ ጩኸት ጮህኩ፡-

"ወጣቶችን በማሰር ምን ትጠቀማላችሁ? ያው ግደሉኝ፤ እኔ አለሁላችሁ! ወጣቶች ምን ባጠፉ ይቀጣሉ። ያው አለሁላችሁ ግደ..ሉኝ! ግደ.....ሉኝ" አልኩ።

የከፍተኛው ሊቀመንበር ወጣቶቹን በቁጣ ቃል "በሉ ቶሎ ግቡ! ግቡ! ግቡ!.." ብሎ እየጮኸ ቶሎ ወደየክፍላቸው እንዲገቡ አደረገ። ወደ እኔም ዞር በማለት ከተመለከተኝ በኋላ፥ በዙሪያዬ የከበቡኝን የቀበሌ ዘበኞች፥ "ይህ አናርኪስት ባይናችን ላይ ቅስቀሳ ሲያካሄድ ዝም ብላችሁ ታያላችሁ?" ብሎ በመጮህ፥ አንድ ጡጫ በፊቴ ላይ አሳረፈብኝ። እኔም እጆቼን የኋሊት ታስሬ፥ ሰውነቴም በጾም ብዛት የደከመ ስለነበረ፥ ወዲያው መሬት ላይ ባፌ ተተከልኩ። እዛው እንዳለሁ እያንዳንዱ የአብዮት ጠባቂ (ዘበኛ) አብዮታዊ ግዴታውን እኔን በመደብደብ አስመሰከረ።

ከዛም ሊቀመንበሩ "በቃችሁ! በቃችሁ!" አለ፤ የኔ ነፍስ ያደረችበትን ሥጋ በቀላሉ ለቃ የማትወጣ መሆኑን ባለማወቁና የምሞት ስለመሰለው፥ ከእኔም መረጃ ስለሚፈልግ፥ ሳልሞት በፊት ሊመረምረኝ፥ ኑዛዜዬንም ለመስማት አሰቦ።

ወዲያው ከቢሮው እንዲወስዱኝ ትእዛዝ አስተላለፈ። ከቢሮው እንደገባሁ፥ "ሃሸሽ ትወስዳለህ እንዴ?"  ብሎ ጠየቀኝ ሊቀመንበሩ።  እኔም "አይ አልወስድም" አልኩት። "ጭራሽ ወስደህ አታውቅም?" ብሎ በመደጋገም ጠየቀኝ። እኔም እንደማልወስድ አረጋገጥኩለት። "በትምህርትህ ስንተኛ ክፍል ደርሰሃል?" አለኝ። እኔም አስራ ስድስተኛ ክፍል መጨረሴን ነገርኩት።

የሊቀመንበሩ ፊት በድንገት ትንሽ ደንገጥ ያለ ይመስላል፤ ወዲያው ፈገግ አለ፤ ያዘነልኝም በመምሰል "ኮድ ተቀብለህ አሲምባ ከጓዶችህ ጋር ለመቀላቀል ስትዘጋጅ እንደተያዝክ ተነግሮኛል። ይህ እውነት ነው ወይ?" አለ። እኔም "አዎን እውነት ነው" አልኩት።

አሁንም የበለጠ ፈገግ አለ፤ ከወንበሩ ላይ በመደላል ዘና ብሎ፥ ወረቀትና እስክሪፕቶ ያዘና፥  "ታዲያ ኮዱን ለኔ ልትነግረኝ ፈቃደኛ ነህ?" አለ ለስለስ ብሎ።

እኔም በማረጋገጥ "አዎን ፈቃደኛ ነኝ" አልኩት። በዚህን ጊዜ እጅግ ደስ አለው። ረጋ ብሎ ኮዱን ለመጻፍ ይችል ዘንድ፥ እራሱን በወንበሩ ላይ አስተካከለ።

"ለአብዮታዊ ትብብርህ ሳናመሰግንህ አናልፍም" በማለት ሳቅ አለና፥ "ጓድ በል ኮዱን ንገረኝ" አለ፤ ከፊትለፊቱ ያለውን ወረቀት በእስክሪፕቶው እየወጋ። እኔም በልቤ "ያንጎድጉድህ" አልኩና፥ "ኮዱ'ኮ ከልቤ ውስጥ ነው ያለው፤ ስትፈልግ ደረቴን ሰንጥቀህ ከልቤ ውስጥ አውጥተህ መውሰድ ትችላለህ" አልኩት።

"ኮዱን አውጣ ነው የምልህ! ቀጥቅጬ ሳልገድልህ!..." እያለ፥ በመደጋገም ሲጠይቀኝ፤ እኔም "እንዴ! ኮድ የለም አልኩህ እኮ! ቢኖርም በልቤ ውስጥ ነው የሚኖረው፤ ከቻልክ ከዚያ ፈልቅቀህ አውጣው..." እለዋለሁ። ሊያምን አልቻለም፤ እንደገና ድምጹን ከፍ በማድረግና በመጮህ በታላቅ ቁጣ "ኮዱን አውጣ!" ሲል ሰማሁት። ከዚያ በኋላ፥ እኔም በልቤ ከርሱ ጩኸት አስራ ሁለት ጊዜ አስበልጬ የጮኽኩ ይመስለኛል፤ ካፌ ሲወጣ ግን ስልል ያለ ድምጽ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። "ኮዱ ልቤ ውስጥ ነው ያለው፤ ከቻልክ ልቤን ቀደህ አውጥተህ መውሰድ ትችላለህ ብዬሃለሁ!.." አልኩት። እንዳልሰማ ሆኖ፥ "ምን? ምን?" አለ። እኔም ያልኩትን ደግሜዋለሁ፤ መልሶም ቢጠይቀኝ ይህንኑ ነው ደጋግሜ የነገርኩት።

ከዚህ ቀጥሎ የሚከተለውን፥ ዝርዝር ሁኔታውን አውቄ፥ በደንብ አብራርቼ ብናገረው ጥሩ ነበር። ግን፥ መገመት አያቅትም፤ ያው የተለመደው ድብደባ ነው፤ ምን አዲስ ነገር አለ? አንድ የተለየ ነገር ቢኖር፥ በጥይት የለመዱትን መግደል፥ ከእኔ ዘንድ ሲሆን፥ በድብደባ መግደል ያልተቻላቸው መሆኑ ነው።

**<u>ተረካቢ ያጣች ነፍስ</u>**

ይህን መከራ ላይ የጣለኝን ሥጋዬን ለመጨረሺያ ጊዜ የሚያሳርፍልኝን ነገር አሁን ገና አገኘሁት ብዬ ነበር መሰለኝ። በአማርኛ እንኳን ተቀራራቢ ፍቺ የማይገኝለት "ቶርች" የተባለውን፥ የሚገድል ወይንም ከሞት አፋፍ የሚያደርስ ድብደባ ሰጥተውኝ ይሆናል፤ ግን፥ እኔኮ ደንዝዣለሁ፤ ምንም ምንም አይሰማኝም፤ ደግሞም የማይሰማኝ በሥጋ ስለማልገኝ፤ እያለሁ እንደሌለሁ በመሆን ሊሆንም ይችላል። እኔ በተደጋጋሚ እንዳውቅ (በደንብ እንዲገባኝ) የሆንኩበት ጉዳይ (ምሥጢር) አለ። ድብደባ ልክ እንደ ጠጅ እየጣፈጠ ገብቶ ያሰከረኛል፤ ሰመመን ውስጥ አስገብቶ ራሴን ያሳጣኛል፤ ማንነቴን ሁሉ ያስረሳኛል። በዛን ጊዜ የነበረውን ሁኔታ በሌላ መንገድ መግለጽ አልችልም።

ከሊቀ መንበሩ ጩኸት ቀጥሎ የኔ ጩኸት ሊቀ መንበሩን በሰውነት ኩምሽሽ አድርጎ ያሳነሰው፤ በዙሪያዬ የነበሩ ሌሎቹም በኔ ጩኸት ተደናግጠው ሮጠው ያመለጡ፤ እኔም ለብቻዬ የቀረሁ እንዲመስለኝ ያደረገ ኃይል እኔን ሰውሮኛል (እኔ ሄጃለሁ ወይንም እነርሱ ሄደዋል)።

አእምሮዬ ከሥጋዬ በመገንጠል ለብቻው ማሰብ ጀምሯል፥ ወይም ሄዷል (ሞቻለሁ)። ከእንግዲህ ለኃጢአቴ ሁሉ የቶርችን ፍሬ ከበላሁ፤ አዳምና ሔዋን ከነበሩበት ከገነት እገባለሁ፥ የሚል ተአምራታዊ ሃሳብ ቅሬት በጭንቅላቴ የተቀረጸ ይመስል፥ የሚፈልገኝና የሚያሳድደኝ አለመኖሩን በማስታወስም ይሆናል...፤ ይህ ነው የማይባል እረፍት ተሰምቶኛል።

እንጃ! እንጃ! ስለማላውቀውና ስለማይገባኝ ነገር ብዙ ማውራት አልፈልግም። ግን፥ ከአእምሮ በስተጀርባ የተቀበረ፥ ይህ የማ<u>ይረ</u>ሳ ትዝታ፥ ዝም ቢሉ የማያስችል፥ ቢናገሩት ለማሳመን የሚያስቸግር.....።

ከተጣልኩበት የዋናው ቢሮ የፊት ለፊት ደጃፍ፥ በአንድ እንጨት ላይ የተንጠለጠለ የኢሌክትሪክ አምፖል አለ። ልክ እንደ ጥጥ ብናኝ (ወይንም እንደሌላ) በቀስታ ወደ ላይ ተንሳፈፍፌ (??) ወደ አምፖሉ እንደተጠጋሁ በጣም ትዝ ይለኛል። አምፖሉ ዘንድ እንደረስኩ ብቻ ይህንን በጣም እርግጠኛ ሆኜ እናገራለሁ። እኔም ለራሴም ቢሆን፥ ይህንን ሳልናገር ብደብቅ፥ ግልጽነት የሌለኝ፥ ውሸታም ነኝ።

ከዛ በኋላ (አምፖሉ ጋ ከደረስኩ በኋላ) አላውቅም፤ ግን፥ እንዳው ጥፍት ብያለሁ - ቅጽበታዊ መጥፋት። አምፖሉን አልፌ፥ ምድሪቱን በቅጽበት ለቅቄ ሄጃለሁ፤ አዎን ሄጃለሁ። እራሴን ስጓዝ አላየሁትም፤ ግን ከአንድ ሥፍራ ደርሻለሁ።

በደረስኩበት ሥፍራ ውስጥ ያለውን እጅግ በጣም የሚያስደስት፥ በምድራዊ ቋንቋ የማይገለጽ፥ ፍጹም የሆነ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘለአለማዊ ሥፍራ አይቻለሁ፤ ከዚያም ገብቻለሁ (እውነቴን ነው)።

እኔ የደረስኩበት ሥፍራ፥ ኢትዮጵያ ሕዝቦቿን አቅፋ በሰላም የምትኖርበት፥ ለጠላት የማይታይ እውነተኛ ሥፍራ ይመስላል። ግን፥ ቤት ይሁን ሀገር ይሁን አልለየሁትም። ያ ሥፍራ ብርሃን የሚያገኘው ከጸሐይ አይመስልም፤ ግን ልዩ አይነት፤ በምድር ላይ ሊነጋጋ ሲል ያለውን የሚመስል፤ እንደሚተነፈስ አየር የሆነ፥ ልዩ የብርሃን አየር (ወይንም የአየር ብርሃን)። ራቅ ብዬ ብሄድ፥ የሰው ዘር ሁሉ የሚኖርበት ሥፍራም ከዚሁ መሆኑን ሳልገነዘብ አልቀርም። እኔ ግን፥ በአንድ ብዙ ብርሃን ከማይደርስበት፥ ሌላው ሰው ከማያየኝ ሥፍራ ጥጉን ይዤ፥ ተመልካች ብቻ ነበርኩ እንጂ፥ ለመሳተፍ ገና አልተፈቀደልኝም።

እጅግ የሚያማምሩ፥ አዳዲስ "ልብስ" የለበሱ፥ ቆንጆ ቆንጆ ወንዶችና ሴቶች ደስ ብሏቸው፥ አምረውና አጊጠው፥ አሸብርቀው፥ በመዝናናት ሽር ጉድ ሲሉ ከሩቅ ይታዩኛል። ከዚህ ሥፍራ፥ በእድሜ ሕጻን ሽማግሌ፥ በአካል ቀጭን ወፍራም፥ በመልክ ቆንጆ አስቀያሚ፥ በጠባይ ጥሩ መልካም ሳይባል፤ ሁሉም አንድ አይነት ናቸው፤ የሁሉም ተሳትፎ ገደብ የለሽ ነው። ከዚህ ሥፍራ ምድራዊ ስበት ያለ አይመስልም፤ እንደ ልባቸው፥ ሲፈልጉ ወደ ላይ፥ ሲፈልጉ ወደታች፤ እንዳሻቸው አቅጣጫ በመቀያየር፥ ከመሬት የተለየ አይነት እንቅስቃሴ ያሳያሉ። "በአንድ ቦታ ተቀምጠው - ተንሳፈው?" የሚያወሩም አሉ።

የአድማሱ ክልል አይታይም፤ መጨረሻም የሌለው ይሆናል (እንጃ)። ሥፍራውም አካላዊ ይመስላል፤ ግን ከዚህ ሥፍራ አፈር፥ ድንጋይና ውሃ አይታይም (እንጃ)። ሁሉም ነገር ከእሳትና ከአየር የተገነባ ይመስላል። በመሬት ካሉት ነገሮች መካከል እንደ ትምህርት ቤት (ዩኒቨርሲቲ) የበዛበት ይመስላል። የሚማሩትም ትምህርት በአጠቃላይ ጊዜን እየደመሰሰ፥ ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየሄደ፥ እንደ ታሪክ፥ እንደ ሃይማኖት አይነት ሰማያዊ ፍልስፍና (ስለ ሰው ልጅ፥ ስለ ተፈጥሮ፥ ስለ እግዚአብሔርም) ይመስላል።

ምናልባት "ያ ትምህርት" ለመላእክት ሲሰጥ፥ ወደ መሬት ወርደው የሰውን ልጅ በሚያገለግሉበት ጊዜ እንዲረዳቸው ይሆናል። ወይንም፥ ከምድር ተሰናብተው ሰማይ ለሚገቡ ሰዎች ስለ መላእክት እና ስለአኗኗራቸው የሚሰጥ ትምህርት፤ ይሆናል።

የእኛ የምድር ሰዎች ምድራዊ ክንውኖቻችን (ታሪካችን ሁሉ) ለሰማይ ቤት መማሪያ ይሆን? መላእክት (ወይንም የሰማይ ሰዎች) በሰማይ ቤት የሚማሩትን ትምህርት የሚያገኙ ከምድራችን መሆን አለበት። አለዚያማ ከሰማይ ቤት ምን ትምህርት ያስፈልጋቸዋል? የት ሊደርሱ? ምንስ ሊጠቅማቸው። እኛ እድሜ ልክ ተምረን፥ ግፋ ቢል በእግራችን ጨረቃን እንረግጥ ይሆናል፤ እነርሱ ምንም ሳይማሩ በጠፈር ሁሉ ይንሸራሸራሉ።

በሰማይ ቤት ስለ ምድራችን ቢማሩ፥ ምድራችን ሃሪፍ ናት፤ በውስጧ ኃጢአት ስላላት። ምድራችን ምንም ኃጢአት ባይኖርባት፥ ምን ልታስተምር ትችላለች? መላእክት (ወይንም የሰማይ ሰዎች) መማር ካለባቸው ስለኛው ስለኃጢአተኞቹና ስለ ምድራችን ይማራሉ ማለት ነው (ይሆን?)።

እኛ የሃይማኖት ትምህርት የምንማረው በተፈጥሯችን ክፉ መሥራት ስለተዋሃደን እና ጥሩ መሆን ስላለብን ነው። እነርሱ ጥሩዎች ስለሆኑ ምንም አይነት የሃይማኖት ትምህርት አያስፈልጋቸውም። ነገር ግን፥ በዚህች ሃሪፍ የሆነች ምድራችን ውስጥ የተለያዩ ሃይማኖቶች ስላሉ፥ እነርሱን ይማሩባቸው ዘንድ ካስፈለገ፥ እነርሱ ወደ መሬት ተሰደው፥ ከሰዎች ጋር ተደባልቀው እኛን ለማስተማርም ቢሆን እነርሱ እኛን ይማሩናል ማለት ነው። እኛ ሰዎች ግን፥ የኛ ታሪክ ሁሉም (ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ) ኃጢአትን ከመሥራት ጋር የተያያዘ ነውና፤ ስለራሳችን ታሪክ መማር ይኖርብናል። መላእክት ግን፥ እነርሱ ኃጢአት ስለማይሠሩ፥ ከዚህች ሃሪፍ የሆነች ምድራችን ውስጥ የተለያዩ ታሪኮች ስላሉ፥ እነርሱን ይማሩባቸውና፥ እኛኑ መልሰው ያስተምሩበታል።

ፍልስፍናስ ቢሆን፥ ለአንድ ሰማያዊ ሰው ወይንስ መላእክት ምን ያደርግለታል? ሰዎች ፍልስፍና የሚያስፈልጋቸው፥ የወጣትነት ዘመናቸውን ካለአንዳች መመሪያ ቢያሳልፉት፥ ምድራዊ ሕይወታቸውን ወደማገባደዱ ሲጠጉ፥ “ለምን ጊዜዬን በዚህ መልክ አሳለፍኩት?” በማለት በራሳቸው እንዳይቆጩ ነው። የሰማይ ሰዎች (ወይንም መላእክት) ፍልስፍናን ቢማሩት ምን ይጠቅማቸዋል?

እስቲ ወደ ቀድሞ ነገራችን እንመለስ። የሰማዩን አለም በጨረፍታ ስመለከተው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ሆኖብኛል። ታዲያ፥ በምድር ላይ መኖርና መሞትም የመጨረሻ አላማው በዚሁ አዲስ ሰማያዊ አለም ውስጥ ፍጹማዊ ሆኖ ለዘለአለም መኖር ከሆነ፥ በምድር ላይ እንኳን ሰይጣን ኖረ፤ እርኩሳን መናፍስትም እንኳን ሰውን አስቀያሚ አስመሰሉት ያሰኛል። ይህም፥ ሴት ልጅ አርግዛ በስቃይ አምጣ የምትወልደውን ህጻን እቅፍ አድርጋ ስትስመው ከምታገኘው ደስታ ጋር ይመሳሰላል።

(እርግዝና - አምጦ ልጅ መውለድ ጥሩ ከሆነ፥ በምድር መኖርም ጥሩ ነው እንደማለት ይቆጠራል)።

ሰማዩን ደፍሬ ቀና ብዬ አልተመለከትኩትም። አንድ ነገር ብቻ እንደ ፈራ ሰው ቀና ማለት አቅቶኛል። እግዚአብሔር የሚያየኝ መስሎኝ ይሆን የፈራሁት? ተደብቄ ከገባሁበት ሥፍራ “ውጣ!” እንዳልባል ፈርቻለሁ። በዚህ ቆንጆ ሥፍራ ማንም ሳያየኝ ብዙ ብዙ ቆየሁ። ለደስታዬም ወሰን አልነበረውም። በተመልካችነት ሳስተውል፥ የዛ ሀገር ሰዎች ሁሉ፥ በሰማያዊ አካላቸው ረዘም- ረዘም፥ ጎላ ጎላ ያሉ፥ በሁኔታቸውና በጠባያቸው፥ ለመግለጽ በማይቻል አይነት፥ ፍጹም ጥሩዎች በመሆን፥ በፍጹም ደስታ ውስጥ የሚኖሩ ናቸው።

ይህ በጣም ግልጽ ሆኖ ታይቶኛል፤ ግልጥ ከመሆኑ የተነሳ እስካሁንም አልፎ አልፎ በሃሳቤ ይመጣብኛል። ይህ ነገር እውነት ስለመሆኑ እንዳልጠራጠር፥ በደንብ የማውቃቸውን ሁለት ሰዎች (ወንድና ሴት) ከዚያ ሥፍራ በግልጽ አይቻቸዋለሁ።

በዚያን ጊዜ፥ በዚያን ሥፍራ፥ እነዚህ ሁለት ሰዎች ሲያወሩ ይሰማኛል፤ ድምጻቸውም እጅግ ጥርት ያለ ሆኖ የሙዚቃ ቃና ያለው ይመስላል። የወንዱ ድምጽ ወፈር ያለ ሆኖ፥ የድምጹ ጥራትና የሚናገረውም የፍልስፍና ንግግር፥ ለመግለጽ የማይቻል እውነተኛነትና ፍጹምነት ያለው ነው። የሴቲቱም ድምጽ ቅጥን ብሎ፥ የሙዚቃ ቃና ያለው ነው። ስትነጋገር ሴትነቷንና ደግነቷን በተለየ መልክ ግልጽ ያደርገዋል። በአሮጌው አለም ከሌላው ሰው ተለይቶ የማይታየው የእነኚህ ግለሰቦች ጠባይ፥ በአዲሱ አለም ውስጥ እጅግ ጥሩ ሆኖ አገኘሁት። እነኚህ በሁለንተናቸው ፍጹምነት ደረጃ የደረሱ ሰዎች፥ እኔን ሊያዩኝ የሚችሉ አይመስሉም። ቢያዩኝማ ኖሮ በእንዴት አይነት ደስታ ተቀብለው ባስተናገዱኝ ነበር።

***<u>ወቅታዊው እውነታ</u>***

*አዬ! እስቲ ወደማላውቀውና "እኔ" ወደምለው ወደራሴው ልመለስ። እኔ በዛን ወቅት፥ ከሞተው እኔ የተረፈው እኔ "ለካስ አልሞትኩም" ነው። አለመሞቴ (በአዲስ አለም ውስጥ አለመወለዴ) በደንብ እንዲገባኝ ሆነና፥ የሥጋ ህመም ቀሰቀሰኝ፤ ድንግጥ አልኩና፥ ያ ሁሉ ከምኞት ጋር የተቀላቀለ አስተሳሰብ ወይም ምናባዊ ፍልስፍና ተረስቶ፥ ወደ ምድራዊ እኔነት ተለውጦ፥ በሥጋዊ ህመም፥ በሃዘን ስሜት እና በአሉታዊ አስተሳሰብ ተተካ።*

*"ውሸት! ሁሉም ውሸት! ውሸት! መሬት ውሸት! እኔም ውሸት! ሁሉም ውሸት...." እጆቼ የኋሊት እንደታሰሩ ከቢሮው ደጃፍ እውጪ ተጥዬ በጣረ ሞት ላይ የምገኝ ሥጋ ነኝ። ሁሉ ነገር ውሸት መሆኑ በጣም ገባኝ፤ ውሸት በጣም አሳመመኝ።*

*አዬ ጉዴ! ከዚያ ከሄድኩበት ሥፍራ ከአንድ ጥግ ተቀምጬ፥ ከተመልካችነት አልፌ ተሳታፊ ሳልሆን መቅረቴ - ነፍሴ ከሸረሪት ድር በቀጠነች ሐረግ ላይ ተንጠልጥላ፥ እዚህና እዛ ስትወዛወዝ ነበር አዲሱን አለም ያየችው። አንድ ወጥ የሆነውን ንጹህ አለም በቀጭን ሐረግ ላይ ተንጠልጥዬ ነበር ያየሁት። ያ ቀጭን ሐረግ አጉል ሥፍራ ስደርስ ተበጠሰ። አይ ጉድ! ምነው አዲስ አለም ስገባ - ከዚያ በተበጠሰ ኖሮ። እየጎመጀሁና እየጓጓሁለት፥ ያ ደስ የሚል አለም በመጋረጃ ተዘጋ። እድሌ ሆነና፥ ከዚሁ ከምድር ላይ ተመልሼ ወደቅሁ። ተረካቢ ያጣች ነፍስ ተመልሳ መጣች ወደ ሥጋው እኔ። እኔና ነፍሴ፥ ቤታችን ካፈር ላይ ነው - ከመሬት።*

*አዬ! ምነው ቀና ብዬ ወደ ሰማይ አንጋጥጬ በተመለከትኩ ኖሮ? ኮሙኒስትነቴ ቀርቶብኝ፤ "አምላኬ ላንተ እሰግዳለሁና፤ እባክህ አትጨክንብኝ" ባልኩት ኖሮ። ለሚጠይቀኝ ጥያቄ ሁሉ፥ "ታዲያ ምን ላድርግ፤ ታዲያ ምን ላድርግ?" እለው ነበር። እርሱም የልቤን ቅንነት አይቶ ስለማይጨክንብኝ፥ "በል ለጊዜው እዚህ አረፍ በል" ብሎ፥ ለየት ያለ ሥፍራ ይሰጠኝ ነበር እንጂ፥ መልሶ ወደ ጠላሁት መሬት አይጥለኝም ነበር።*

*እራሴን ባላገኝ፥ በማላውቀው እኔ፥ ሥጋዊ ሞትን እንዳልፈራ የሚያደርግ፥ እውነት አለኝ እኮ በውስጤ። የእኔ በሰማይ መኖር ለምን ተፈራ? አዲስ ኃጢአት እንዳልዘራ? ከሰማይም ከእግዚአብሔርም ሳልሆን ቀርቻለሁ ለመከራ። በቃ! አለቀ፤ የኔ ነገር በዚህ ላይ አበቃ።*

*አይ! ሃሳብ ማብዛት በከንቱ! እንዳው በከንቱ...። በጊዜው የነበረው ወቅታዊ እውነታው ግን፥ እኔ በዛን ወቅት አልሞትኩም፤ የትም አልሄድኩም፤ ሰማይ ቤትም አልወጣሁም ነው።*

ቀኑ መሽቶ፥ ሌሊቱም ወደ መገባደድ ተዳርሷልና፤ ሰው ሁሉ ተኝቷል። እዛው እንደተደፋሁ ሰውነቴ በውሃ ጥም አረረ። እውነተኛውን ሞት አሁን ገና ላገኘት ነው ብዬ አሰብኩ፤ “ውይ! ምናለ በሞትኩና፥ ማየት መስማቴም ቀርቶ እንዳው ዝም ባልኩ...” አሰኘኝ።

የጠጣሁት ቶርች በብርሌ የተቀዳ አሬት እንጂ፥ የሚያሰክር ጠጅ አልነበረም። አሬቱን ብዙ ባጠጡኝና በሞትኩ ምናለበት ነበረ? አፌ ደርቆ ምላሴም ከላንቃዬ ተጣብቋል።

“ወይ ሞት! ለካስ የሰው ልጅ የሞትን ጥሩነት ባለማወቅ ክፉኛ ተጎድቷል” አልኩ። ቀጥዬም፥ “የፈጠርከኝ አምላኬ ሆይ! እኔ ዛሬ ባንተ አምኛለሁና፤ እባክህ! እባክህ ውሰደኝ። ጨርሰህ ያልወሰድከኝ ስላላመንኩብህ አይደለም? በል አሁን አምኜብሃለሁና ውሰደኝ፤ እባክህ ውሰደኝ፤ እባክህ ውሰደኝ። ከዛሬ ጀምሮ ፈጣሪ አምካኬ አንተ መሆንከን ተቀብያለሁና እባክህ ውሰደኝ” እያልኩ ተማጸንኩ።

በዚህ የሞት ሽረት ሲቃ ውስጥ ሳለሁ፥ ወደ መንጋቱ ተቃረበ። አንዲት ትንሽ ሴት ልጅ በሳህን እንጀራ፥ በኩባያ ውሃ በነጠላዋ ሸፍና አመጣችና፥ ማንም ሳያያት ተደበቃ ውሃውን አጠጣችኝ። ትንሽ ደቂቃዎች ብቆይ ይለይልኝ ነበር (የመጨረሻውንና እርግጠኛውን ሞት አገኝ ነበር)። እኔም ለመሞት የከጀልኩት ሰውዬ፥ ውሃ ባፌ ሲንቆረቆር ጊዜ ሞትን ረሳሁት። ያቺ ሴት ልጅ ምግብ ልታጎርሰኝ ሞከረች፤ አልሆነላትምና ፈጥና ተመለሰች (እስከዛሬ ያቺ ሴት ልጅ ማን እንደሆነች አላወቅሁም)።

የጠጣሁት ውሃ ነፍስ ዘራልኝ። ቀስ በቀስ ያለሁበትንም ቦታ በደንብ መረዳት ጀመርኩ። ታዲያ ይህ ነወይ የጸሎቴ መልስ?..ታዲያ የትኛው ነው ውሸት? የትኛው ነው እውነት?..ብኖርም - የመኖሬ ህልውና ቢረጋገጥም፥ ውሸት! ሁሉም ውሸት!.. መሬት ውሸት! እኔም ውሸት! ሁሉም ውሸት።.

አዎ! በመንፈስ ሄጄ ነበር፤ ነገር ግን፥ ስላልሞትኩ፥ እውነተኛውን መንግሥተ ሰማይን አላገኘሁትም። ከሥጋዊነቴ ሳልላቀቅ በመቅረቴ፥ በዛው ሥጋዊ አለም ተወስኜ ቀረሁ። “እዚህ ቦታ ደረስኩ፤ ይህንን አየሁ፤...” እያልኩ የተንተባተኩትንም፥ ሰዎች ከቁም ነገር ባይቆጥሩት ይሻላል።

ከአንድ ትንሽ ኮሙኒስት ሰው የሚተረክ እውነት እውነትነቱ ለእርሱ ብቻ ሆኖ ቢቀር እንኳን፥ ከእርሱ አንድ ትንሽ የእውነት ጠባሳ ቢታይ እንኳን፥ ለወደፊቱ ትውልድ መማሪያ፤ ማስታወሻ እና ማስተዋያ ይሆን?

የሥጋ መዘዙ ብዙ ነው፤ ለድጋሜ ፈተና (re-exam) ተመለስኩ። በእርግጥ ሥጋዬ ደክሞ ነበር፤ ነገር ግን፥ የሥጋዬ መድከም፥ የነፍሴን ሰማያዊ ሕያዊነት ከሥጋዬ ምድራዊ ሕያዊነት መለየት አልቻለም። ስለዚህ፥ ተመልሼ መጥቻለሁ - ታጥቦ ጭቃ።

ከዛን ጊዜ ጀምሮ ሴቶች ተራ በተራ እየመጡ በድብቅ ውሃ ያጠጡኝ፥ ይመግቡኝም ጀመር። በዚህ አይነት አንድ ሳምንት አለፈ። አሁንም ከቢሮ ደጃፍ (እጆቼ የኋሊት እንደታሰሩ) እንደተጣልኩ ነው። ካድሬው ቢሮ በገባና በወጣ ቁጥር፥ “ይህ አመጸኛ አሁንም አልሞተም?” እያለ፥ ልክ እንደ ተከላላይ የግር ኳስ ተጫዋች (ተርሲኒ) ሆኖ ይጠልዘኛል። የዛን ቀን ሊቀ መንበሩ ባሰቃቂ ሁኔታ ሲመረምረኝ፥ ካድሬው ቢኖር ኖሮ፥ እርሱ ብዙ የገደለ ስለሆነ፥ እኔንም ቶሎ ይገላግለኝ ነበር።

ሌሎቹ የአብዮት ጠባቂዎች እየዘለሉኝ ያልፋሉ እንጂ አይረግጡኝም። ሁሉም እየረገጡኝ ማለፍ ሲችሉ፥ አይነኩኝም። አንዳንዴ የማሰናክላቸው የአብዮት ጠባቂዎች፥ ብቻቸውን ሲሆኑ፥ “አይ!..” በማለት በስጨትጨት ይሉና፥ ሳያስቡት ሰብአዊ ርህራሄን የሚያንጸባርቅ የሃዘኔታ ቃል ካፋቸው ይወጣል። ሌላ ጊዜ ደግሞ፥ ያው ያዘነልኝ ሰው፥ ካጠገቡ ሌላ ሰው ያየ እንደሆነ፥ “ምን ይህ! ደንቃራ!” ብሎ፥ መሬቱንና እኔን አንድ ላይ አድርጎ፥ ክፉኛ የጎዳኝ በማስመሰል ይረግጠኛና ያልፋል። ይህ በተደጋጋሚ የተገነዘብኩት ሁለት አይነት የሰው ጠባይ ይገርመኛል።

ከሞት በስተጀርባ ያለውን ሕያውነት ስለቀመስኩ፥ ለሞት የሚያበቃ “ጥፋት ሳላጠፋ”፥ ለራሴ ሞትን ተመኘሁ። እጅግ “በረቀቀው” በኮሙኒስታዊ አስተሳሰቤ የምመኘው፥ ከሞቱት ጋር ለመሞት እንጂ ለመኖር ስላልሆነ፥ “ምንድነው ኃጢአቴ? ሰዎች እባካችሁ ድረሱልኝ፤...” ማለትን አልሻትኩም። ወይንም መላእክትን “ከዚህ ጭንቅ አውጡኝ፤..”እያልኩ አልተማጸንኩም፤ ምንም ስሜት እንደሌለው እንደ እንጨት ድርቅ ብዬ እራሴን ገታሁ እንጂ።

እንግዲህ ያ ሁሉ ትእይንት የገዛ አእምሮዬ እኔን ለማታለል የሚጫወተው ትያትር - በአንጎል ውስጥ በሚከናወን በነርቮች ንዝረት ብቻ የተደረሰ ድርሰት ነው?

ይህንን ሁሉ ሳይረሳ የተቀመጠ አንጎልስ ይህንን ውሸት ያልሆነ ታሪክ ቢያወራ፥ ለስነ አእምሮ ተመራማሪዎች ይጠቅማል? “ሰዎች እኛ ያልገባን አንድ ነገር አለ። ሥጋዊ ሕመምን ለማስረሳት አንጎል ብቻውን እንዲህ አይነት ሥራ (ትያትር) የመሥራት አቅም እንዳለው ተመልከቱ” በማለት፥ ይህንን እንደ አዲስ ግኝት መቁጠር ይቻላል? ወይንስ፥ ከዚህም የተለየ ነገር ቢኖርና ያንኑ “መንፈስ” የሚሉትን ነገር፥ ወደድንም/ጠላንም፥ መልሶ ወደእኛው እሳቤ ውስጥ ይከትብን ይሆን?

እንግዲህ ያ ሁሉ ትእይንት የገዛ አእምሮዬ እኔን ለማታለል የሚጫወተው ትያትር - በአንጎል ውስጥ በሚከናወን በነርቮች ንዝረት ብቻ የተከወነ እንቅስቃሴ መሆን/አለመሆኑን አንባቢ ያስተውልበት።

እንዲህ ያለ ትይንት በሌሎች ምድራዊ ስቃይ በሚበዛባቸው ሥፍራዎችም ይከናወናል። በኢትዮጵያችንም፥ ሰላም እና ሕብረተሰብአዊ መረጋጋት እስከሌለ ድረስ፥ በብዙ ሰዎች ዘንድ፥ በተለያዩ ጊዜአት ተደጋግሞ እንደተፈጸመ፥ ለወደፊትም ይፈጸማል።

አንጎል የእራሱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲል ይረሳል። ይህ ጽሑፍ ግን፡- “አንጎል ሆይ! እባክህ አትርሳ፤ ያንተ ታሪክ ምናልባት፥ ቢያንስ ሌሎች አንጎሎችን ያስተምር ይሆናል” በማለት ይማጸናል።

ቀጥሎም፥ “ሰዎች ያልገባን ነገር ይኖራልና፤ ሥጋዊ ሕመምን ለማስረሳት አንጎል ብቻውን እንዲህ አይነት ሥራ የመሥራት አቅም እንዳለው/እንደሌለው፥ ወይንም ብቻውን ባይሆንም፥ የውጭ ኃይል እንዳለበት/እንደሌለበት፥ እናንተም ይህንን እና የመሳሰሉትን ተመራመሩበት እንጂ፥ እባካችሁ ችላ ብላችሁ አትተዉት” በማለት ያሳስባል።

ከነገሮች ሁሉ በስተጀርባ፥ ይህንን የመሳሰሉ ትእይንቶች ለሚያጋጥማቸው፥ እነርሱ ለሚያስቡትና ለሚሰማቸው ማጠናከሪያ፥ እንደ ማንቂያ ደወል፥ እንደ ትምህርትም እንደሚሆናቸው አምናለሁ።

እኔም የዚያን ጊዜ፥ እንደ ተወርዋሪ ኮከብ ስበር፥
ከዚያ ሥፍራ ደረስኩ፤ አስቀድሜ አለምን ሳልዞር፤
ከምድር የቀረኝ ሳይኖር፥
ተመልሼ መጣሁ ከምድር፤
አዬ! ለካስ አልሞትኩም ነበር።
ለምን አየኋቸው እነሱንስ ከዚያ?
ይህቺን አለም ትቼ - ርቄ ከሄድኩበት፤
ከብርሃን ፍጥነት በላይ ፈጥኜ ከደረስኩበት፤
ሰማይ አለም ፍጹም ደስታ ከሆነበት።

ወጣቶች በአካል ፍጥን ፍጥን ይላሉ፤
አለማቸው መሬት መሆኑን ያረጋግጣሉ።
ሽማግሌዎችም በአካል ቀርፈፈፍ ይላሉ፤

ጊዜአቸው ደርሷልና፥ በሃሳብ ብቻ አለምን ይዞራሉ።
ባህታውያን፥ መነኮሳትም ይህቺን አለም ይሸሻሉ፤
በሥጋቸው መሬት፥ በነፍሳቸውም ከሰማዩ ላይ ይኖራሉ።
የሰው መንፈሱ በጠፈር፥
በጊዜና በቦታ የማይታጠር፤
ለጊዜው በሥጋው አለምን ቢዞር፥
ለነፍሱ ተዘጋጅቷል አዲስ ሀገር።
“ከኢትዮጵያችን ምን አለኝ?” የማይል፥
እርሷን የሚወዳት አይሄድም ርቋት፤
እርሷም ከሞት በላይ መንፈስ አላት፤
ምድራዊም ብትሆንም ሰማያዊ ናት።
እኔስ ምን ልበል አሁን?
“እኔነቴን ጣልኩት?
ማንነቴን ረሳሁት?
ምድራዊነቴን ካድኩት?
ሥጋዬንም ተውኩት?”
አዬ!..ግና
አሁንም ተስፈኛው ነኝና
እኔ፥ የብዙሃን ድምጽ በውስጤ፥
እውነት ካላቸው ጋር ልኑር፥
በሰማይም ሆነ በምድር፤
እነርሱ በኖሩበት ልኑር፤
ሞተውም በሚቀበሩበት ሥፍራ ልቀበር።

**<u>ኮሙኒስት/አይዲያሊስት</u>**

የሰው አይነቱ ብዙ ስለሆነ "ሰው ማለት እንዲህ ነው" አይባልም። ሆኖም፥ ከብዙ ሰዎች ውስጣዊ ጠባይ በመነሳት፡- "ሰዎች በተፈጥሮ ደጎች ነን፤ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ሰው መጥፎ ሊሆን አይችልምና" ማለት ይቻል ይሆናል። ሆኖም፥ ይህ የተጣልንበት አለም ክፉ ስለሆነ፥ እኛንም ክፉዎች እንድንሆን አደረገን። አዎ! የሰዎችን ውስጣዊ ደግነት የሚሸፍን አለም ውስጥ ነው ያለነው። ታዲያ፥ ጥፋተኛው ማነው? በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ሰው ወይንስ የሥጋውያን መኖሪያ ምድራችን[16]?

ይህች ምድር (አለም) የሰይጣኑም የክፋቱ ኃይል ውስጣዊ ደግነታችንን እስከ መበረዝ፥ ወይንም እስከ ማጥፋት የደረሰበት አለም መሆኗን ከሃይማኖት መሪዎች በደንብ መረዳት ለሁላችንም ሳይጠቅም አይቀርም፤ በምድር ስንኖር እውነተኛው ጠላታችን ሰይጣን (ዲያቢሎስ) ነውና።[17]

"መጥፎውን ያላየ ጥሩውን አያመሰግንም" እንዲሉ፥ የሰው ልጅ የነገሮችን መልካም ጎን በደንብ ያይ ዘንድ መጥፎውን አስቀድሞ ማየቱ የሚረዳው ይመስለኛል፤ ለዚህም ይሆናል ፈላስፋውም ማርክስ "በካፒታሊስት ስርዓት ውስጥ ብዙሃኑ ለፍቶ አዳሪዎች በጥቂቶች ብልጣብልጥ አታላዮች፥ ራስን ወዳዶችና አልጠግብ ባዮች እየተመዘበሩ ለዘለአለም አይኖሩም፤ አንድ ቀን ይነሳሉ፤ የብዙሃን መንግሥት (የኮሙኒስት ሥርአት) ይመሠርታሉ" ያለው። ታዲያ፥ ካፒታሊስቶቹስ ምናቸው ሞኝ ነው፤ ላብ አደሮች ሆድ እንዳይብሳቸው፥ እንዳያምጹባቸውም፥ አልፎ አልፎ ድጎማ ማባበያ ያደርጉላቸዋል። ግንኮ! ይህ ማባበል ለዘለአለም አይቀጥልም። ለፍቶ አዳሪዎችም "እስቲ እኛም እንደነርሱ እንሁን" የሚሉበት ጊዜ ይመጣል።

የኮሙኒስት ስርዓት ሰውን ከሰው የማያበላልጥ፥ በሰዎች እኩልነት - በአብሮነትና በአንድነት የሚያምን፥ ተፈጥሮአዊ ሃብትን በጋርዮሽ የሚያከፋፍል ሕብረተሰብአዊ ስርዓት ነው። አንድ በሰዎች እኩልነት የሚያምን ኮሙኒስት በእግዚአብሔር ካመነ፥ ያ እምነቱ ከእግዚአብሔር ጋር የበለጠ ያቀራርበዋል እንጂ አያርቀውም።

---

16 ይህንን አስመልክቶ - "የእንፋረዳለን ቅዠት" በሚል ርዕስ አንድ ግጥም ከሁለተኛው መጽሐፍ ይገኛል።

17 *"ይህን አለም አትምሰሉ፤ ልባችሁንም አድሱ፤ እግዚአብሔር የሚወደውን መልካሙንና እውነቱን፥ ፍጹሙንም መርምሩ።" ሮሜ፡ 12፥ 2*

አንድ እውነተኛ በእግዚአብሔር የሚያምን ኮሙኒስት “አባታችን ሆይ! በሰማይ የምትኖር፥ *መንግሥትህ ትምጣ...*” እያለ ሲጸልይ፥ የሰማይ *መንግሥት* ከምድር በወረደ ጊዜ፥ ያንኑ እጅግ የተጠላ የካፒታሊስት (የግለኝነት) ስርዓት መልሶ እንዲያመጣበት አይደለም፤ ፍጹም ፍቅር የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ ሰዎችን ሁሉ በእኩልነት፥ በሕብረት እና በአንድነት አስተሳስሮ፥ ደስ የሚል ኑሮ እንድንኖር ነው እንጂ።

ራሱን ከሚወድ፥ ከሌባው አስቆሮቱ ይሁዳ በስተቀር፥ ሌሎቹ የክርስቶስ ተከታዮች ከጌታቸው ጋር ሲኖሩ፥ አንዱን ከሌላው ሳያበላልጡ በኮሙኒስትነት አልነበረም?

በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ ሀገር በገዳም የሚኖሩ መናንያን ኑሮአቸው ግለሰባዊ ሳይሆን፥ ኮሙኒስታዊ (የጋርዮሽ አኗኗር) መሆኑ ታዋቂ ነው። በየከተማው የምናየው ግን እንደዚያ አይደለም። የሰይጣን ዋነኛ አላማውና ቀዳሚ ሥራው በምድራችን ላይ የራሱን መንግሥት ማስፋፋት ስለሆነ፥ በገጠር ያሉትን ገዳማት መቆጣጠር ቢያቅተውም፥ በየከተማው የሚገኙ መንፈሳዊ ሥፍራዎችን አላማ እያሳተ፥ የንጹሃን አማኞችን ልብ ወደ ምድራዊነት (ስግብግብነት፥ ራስን ወዳድነት፥ ምቀኝነት፥ ወ.ዘ.ተ.) በመቀየር፥ እጅግ ርቅቅ ያሉ የማታለል እና የሥርቆት ዘዴዎችን የሚጠቀሙ ግብረአበሮችን መልምሎ፥ የእርሱ ደቀ መዝሙር ያደርጋቸዋል።

በአሁኑ ጊዜ፥ በአለም ዙሪያ አያሌ ታላላቅ ምድራዊ እና መንፈሳዊ ተቋሞች እንደ አስቆሮቱ ይሁዳ በመሳሰሉ ሌቦች ተይዛለች። አዎ! ኮሙኒስትነት ለሌብነት አይመችም። እና! የትኛው ነው ለሰማይ የቀረበ? የካፒታሊስት ስርዓት ወይንስ የኮሙኒስት ስርዓት?

በአጠቃላይ ሲታይ፥ በአሁኑ ወቅት የሰው ልጅ ለእውነተኛ የኮሙኒስት ስርዓት ብቁ አይደለም። ስለዚህ፥ ሰይጣን ሰውን ሁሉ የራሱን ጠባይ በማውረስ፥ የራሱን መንግሥት በምድራችን ላይ እንዳያጸናብንና እንዳንቸገር፡- “አባታችን ሆይ! በሰማይ የምትኖር፥ *መንግሥትህ ትምጣ...*” እያልን በየጊዜው የምንጸልየውን ጸሎት፥ ያንን የሰማይ መንግሥት እስክናገኝ ድረስ አናቋርጥም።

ሞቼ በነበረ ጊዜና፥ ከሰማዩ ጥግ ሆኜ፥ እኔም ከዚያ ማዶ እንደሚንሸራሸሩት ሰማያዊ ሰዎች፥ ለእኔም ከዚያ መኖር መልካም እንደሆነ ተመኘኋ (እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ምኞት ማለት ነው)።

*“ጴጥሮስም መልሶ ጌታችን ኢየሱስን “አቤቱ በዚህ መኖር ለእኛ መልካም ነው፤ ብትወድስ ሦስት ቤቶችን በዚህ እንስራ፤ አንዱን ለአንተ፥ አንዱንም ለሙሴ፥ አንዱን ለኤልያስ አለው።” ማቴ. 17፡4*

አዎ! ኮሙኒስትነትም፥ ሞትም ብቃትን ይጠይቃል። እኔም “ሞቼ” በነበረ ጊዜ፥ ለእውነተኛው ሞት “ለእውነተኛው ሰማያዊ ስርዓት” ብቃት አልነበረኝም። ለጊዜው “ከዚያ መኖር ለኔ መልካም እንደሆነ” ያሰብኩት፥ ጥጉን ይዤ፥ ኩርምት ብዬ፥ ካለሁበት ሆኜ፥ ጥሩ ጥሩውን እየሰማሁና እያስተዋልኩ እንድኖር ነበር እንጂ፥ እኔ ከእነኛ ካየኋቸው ከደጋግ ሰዎች ጋር ተደምሬ እንደነርሱ እንድኖር በመመኘት አልነበረም (የደረስኩበት ሥፍራ ያልጠበቅሁት ሥፍራ ስለሆነ፥ እኔ ለዚህ ቆንጆ ሥፍራ ገና ነኝና - ልቦናዬ በሚያውቀው ገና ነኝና.....)።

የሰው ልጅ በዚች ምድር ላይ ሲኖር፥ ያ “መኖር” የምንለው ቃል የመኖርና የመሞት ክስተቶችን በአንድነት አጣምሮ በመያዝ ነው፤ ሰው በየሰከንዱ ሲኖር በየሰከንዱም እየሞተ ነውና። ከምድር የመሰናበቺያ (ሞት) እስኪመጣ ድረስ ሁለቱም አብረው መጓዝ ስላለባቸው፥ በምድር ላይ ሁለቱም (መኖርና መሞት) የማይነጣጠሉ ክስተቶች ይሆናሉ። ለዚህም ነበር፥ የአይሲሲው ቅዱስ ፍራንቼስኮ (Saint Francis of Assisi) ሞትን “እህቴ” እያለ የሚጠራት።[18]

የሰው ልጅ፥ ካልገደሉ መኖር ከማይችሉ ሥጋ በሊታዎች (carnivors) ከነ ጅቦች፥ ነብሮች፥ አዞዎች፥...የሚለየው፥ ሳይገድልም መኖር ይችል ዘንድ፥ ሥጋም ቅጠላ ቅጠልም እየበላ መኖር እንዲችል (omnivor) ሆኖ ስለተፈጠረ ይሆናል። ምድሪቱን ይገዛ ዘንድ ሥልጣን ቢሰጠውም፥ በምድራዊነቱ ተመችቶት እንዲኖር ያህል ነው እንጂ፥ ልክ እንደ ሥጋ በሊታዎች እየገደለ ብቻ እንዲኖር አይደለም።

ምድሪቱም ለሰው ልጅ ምግብ ሆነችለት እንጂ፥ ያን ያህል ጨካኝ ይሆን ዘንድ አልገፋፋችውም። ይልቁንስ ከጥንቱም የገዛ ሕሊናውን በአግባቡ ቢጠቀምበት ኖሮ፥ ገና ከአፈጣጠሩ እንደ ሰማይ መላእክትም በምድሪቱ ለመኖር የሚያስችል ውስጣዊ መንፈሳዊ ጠባይ ተሰጥቶታል።

ይህንን ውስጣዊ ጠባይ በአግባቡ ቢጠቀምበት ኖሮ፥ የሰው ልጅ፥ ከላይ ከሰማይ (ከእግዚአብሔር) የተሰጠውን አስርቱ ትእዛዛትን መጠበቅ ያን ያህል አስቸጋሪ አይሆንበትም ነበር (ላይችል አይሰጥምና)። ስለዚህ የሰው ልጅ ምድራዊ ኑሮው ሳይጓደልበትም፥ ሰማያዊ ማንነቱንም ለማስጠበቅ የሚተጋ ቢሆን፥ ሲሞት የሚያገኘው ጠፈራዊ ንኪኪ ለዘለአለም ያኖረዋል እንጂ፥ ከዚችው ጉራማይሌ ምድር ላይ አያስቀረውም።

---

[18] “Praised be my Lord, through our sister Bodily Death, from whom no living person can escape.” እንደሚል፥ ስለ ቅዱስ ፍራንቼስኮ የተጻፉ ድረ ገጾችንም ይመልከቱ። ይህም አራተኛው መጽሐፍ (ከምድራዊነታችን ባሻገር) ላይ ተብራርቷል።

ሰው ሲሞት (ምድራዊነቱ ሲለቀው)፥ በቀጥታ ወደ ሰማይ ቤት ይገባና ያ የመኖር ክስተት (ሰማያዊ ሕልውና) በዘለአለማዊነት (መንፈስ በሕያው ነፍስነት) ይቀጥላል። ሆኖም፥ መጥፎ ሰው ሲሞት፥ ያቺ የማትሞት ነፍሱ ከክፉ ሥራው ጋር አብራው የምትጓዝ ከሆነ፥ ሰማያዊ ፍርድ እና ቅጣትም የማይቀር ዕዳ ይሆናል።

ሰማያዊ ፍርድም የማያዳላ፥ እውነተኛና ቀጥተኛ ስለሚሆን፥ ምንም እንኳን፥ አስር፥ መቶ እና ከዛም በላይ የገደሉቱ በውስጣቸው ጥሩነት ቢኖርባቸውም፥ ያንን ሁሉ ግፍ ፈጽመው በጥሩነታቸው ብቻ ከጻድቃን ተደምረው እንዳይኖሩ ሰማያዊ ሕግጋት ያግዳቸዋል፤ ወይንም የተገዳዮቹ መንፈስ አይለቃቸውም።

ብርሃን ከጨለማ ጋር ዝምድና የለውም። ስለዚህ፥ አንዱ በተገኘበት ሌላው አይገኝም። የአለሙ መጨረሻ እስኪሆን ድረስ፥ በብርሃን እና በጨለማ (በመልካም እና በክፉ መካከል) ጦርነት ይኖራል። ጨለማ ብርሃንን ለመሸፈን ይሮጣል፤ ነገር ግን፥ ከአጠገቡ እንኳን ሳይደርስ ይዋጣል። የሰው ልጅ ግን፥ ሁለቱንም ማስተናገድ በሚያስችል ልዩ ጠባዩ ምክንያት፥ ጨለማ (የጨለማው መንፈስ) ከውስጡ ይገባል፤ እንዲሁም በውስጡ ብርሃን (የብርሃን መንፈስ) በውስጡ ይገባል። ለዚህም ይሆናል ሰው (ሥጋ ብቻ ስላልሆነ) እርስበርሱ የሚጋጨው።

የሀገር መሪዎችም በአለም ዙሪያ፥ ሁሉም በበኩላቸው የተሻለውን የሚፈጽሙ እየመሰላቸው ግዴታቸውን ያከናውናሉ። ሕዝባዊ ኃይላን (ወታደሮች)፥ ከታላላቅ የጦር መሳሪያዎቻቸውና፥ መረጃዎችን ከሚያጠናቅሩ የሰው እና ሰው አልባ ሰላዮቻቸው ጋር ጦርነት ውስጥ ይገባሉ።

ምድራዊ ክስተቶች ጭራሹኑ ምድራዊ አለመሆናቸውን የገባኝ መስሎኛል። ሳይንቲስት ብባልም ኮሙኒስት፥ በመካከላችን ጥልቅ ብሎ እየገባ እርስ በርስ የሚያጋድለን የሚያጨራርሰን ውጫዊ ኃይል ያለ ይመስለኛል።

## <u>**የምሽት ትርኢቶች**</u>

ሁለት እጆቼ የኋሊት እንደታሰሩ፤ ከከፍተኛው ጽሕፈት ቤት ደጃፍ፥ ከውጪ እንደተጣልኩ፥ በዛው ቅጥር ግቢ ውስጥ ስለተፈጸሙ አንዳንድ የማይረሱ ወቅታዊው ሁኔታዎች ሳስታውስ፥ "በእውነትም ሰው ብቻውን አስቦ ያን ያህል በሰው ላይ ይጨክናል? የውጪ ኃይላት (እርኩሳን መናፍስት) ጣልቃ ገብነት እና ግፊት ተጨምሮበት ነው እንጂ" እላለሁ።

መሸትሸት ማለት ሲጀምር፥ በምድር ላይ የነገሡ የቀበሌ ባለ ሥልጣኖች የከፍተኛ አምስት ጽሕፈት ቤት ክልል ውስጥ የሚገቡትን ግለሰቦች እንዴት እንደሚያሰቃዩአቸው ከዛ ከተጣልኩበት ሥፍራ ሆኜ፥ በፍርሃት፥ አይኔን ገለጥ እያደረግሁ እመለከት ነበር። ማታ ማታ ሲሆን፥ አልፎ አልፎ የማየው ምድራዊ ትእይንት፥ ይህች ምድር በእውነት፥ በእውነት "ገሃነመ እሳት"[19] መሆኗን አረጋገጠልኝ።

ከከፍተኛ አምስት ጽሕፈት ቤት አጥር ግቢ ውስጥ አንድ ትንሽ የጨለማ ቤት አለች። በዚች ቤት ውስጥ መስኮት የለም፤ መብራት የለም (ምንጊዜም ጨለማ ነው)። በውስጡ ጸሐይን (ወይንም ሌላ ብርሃን) ለማየት ያልተፈቀደላቸው፤ አስራ አምስት የሚሆኑ ግለሰቦች ይኖራሉ። እነኚህ የቀይ ሽብር ሲፋፋም በነበረ ጊዜ፥ አብረዋቸው በዛችው ክፍል ውስጥ ታጭቀው ከነበሩት፥ ከእኩለ ሌሊት (ከምሽቱ ከስድስት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ)፥ ወጣ አድርገው "ጸረ አብዮተኞች" ለሚሏቸው ማስፈራሪያ እንዲሆኑ ተገድለው በየመንገዱ ከተጣሉት የተረፉት ናቸው። ቁጥራቸው ሁል ጊዜ አስራ አምስት ነው። አይጨምርም፤ አንዳንዴ ይቀንሳል፤ የሚቀንሰውም የመሞት እድል ፈንታው የሆነ ተገድሎ በእኩለ ሌሊት ወደ አውራ ጎዳና ሲጣል ነው። ከውጪ አንድ የዲፌንስ አባል ሲያዝ የጨለማው ቤት እስረኞች ቁጥር ቶሎ ይተካል።

ተገድሎ የተጣለ በጨለማ ቤት ውስጥ ከሚኖር የተሻለ እድል ያጋጠመው ነው። የኢሕአፓ ዲፌንሶች (የጦር ክንፍ አባላት) ቤት እንጂ፥ የእንደኔ አይነቱ ለፈስፋሳ የማይገባበት በመሆኑ ነው ወደዛ ያልተጣልኩት።

ካድሬው "ለአብዮተኞች" ብቻ ከተመደቡ መጠጥ ቤቶች ቆይቶ ሲመጣ፥ ትንሽ ሞቅ ብሎትም ከሆነ፥ ከፍተኛ የመሬት መናወጥ ይከተላል። ደስ ሲለው የሚገድል ስለሆነ ነው የ<u>ሚፈ</u>ራው (የርሱ ምድብ መቶና ከዛ በላይ ከገደሉት መካከል ነው)። "የከፍተኛው ገድል በዘመነ ቀይ ሽብር" በሚል አርእስት ቢጻፍ አንድ ትልቅ

---

[19] በዚህች ምድር ከምናየው ገሃነም እሳት" የተለየ "ዘለአለማዊ እሳት" የሚሉት ከየት ሥፍራ ሊኖር ይችላል? ይህም ጉዳይ አራተኛው መጽሐፍ (ከምድራዊነታችን ባሻገር) ላይ ተብራርቷል።

ጥራዝ ይወጣዋል። ካድሬዎች ከሊቀመንበሮች ጋር የአሜሪካን ሀገር ቴክሳሶች የሆኑበት፤ ወይም ሰዎቹ ወደ ሰይጣኖች የተቀየሩበት ወቅት ነበር ብሎ ማለፍ ይሻላል።

ይገርማል! ሌላ ለየት ያለ ትእይንት አየሁ፤ ከከፍተኛው እስር ቤት ተይዘው ከሚመጡት መካከል፥ አንዳንዶቹ አውቀው ለመገደል ሲሉ የሰከሩ በመምሰል ሲለፋደዱና ሲሳደቡ ቶሎ በጥይት ይቀለባሉ። እነኚህም እንደ እኔ ተንከራተው ተንከራተው፥ አለም ጭልምልም ሲልባቸው፥ ሆነ ብለው ሞትን በመፈለግ የመጡ የኢሕአፓ አባላት ሳይሆኑ አይቀርም ብዬ እገምታለሁ። እነርሱ ቶሎ የመገደልን ምስጢር በማወቃቸው እና እድላቸው ሲስተካከል (ሲሰምር) ቶሎ ሞትን ያገኟታል።

በግቢው ውስጥ በውድቅት ሌሊት የሚፈጸመውን ሰይጣናዊ ትእይንቶች የምመለከት እኔ፥ ከዛው ከተደፋሁበት ሰው በጥይት ሲገደል ስላየሁ፥ በካድሬው ወይም በሊቀመንበሩ እጅ የምወድቅበትን ወቅት ብቻ በጉጉት እየተጠባበቅሁ የምኖር ሆንኩ። ግን፥ ከዚህ በጣም ዝነኛ - ገዳይ - እስር ቤት የገባሁበት ጊዜ፥ ነገር ከበረደ በኋላ ሆኖ ነው መሰለኝ፥ የመሞቻዬ ቀን ተራዘመብኝ።

ሰው ሁሉ በሃሳቡ ይኖራል፤ ያ ሃሳቡ የተለየ አለም ውስጥ ይከተዋል። ሰው ሁሉ ለራሱ ጥሩ ነገር ስለሚያስብ፥ በዚህ አለም የማይገኘውን እጅግ ጥሩውን ነገር ያስመለከተዋል። ያ ጥሩ ነገር ጥሩ ከመሆኑ የተነሳ ከምድር ላይ አይገኝም በማለት፥ ሃሳብ ወደ ላይ - ወደ ሰማይ (መንግሥተ ሰማይ) - ወደ መንፈስ ይመጥቃል። ታዲያ ሰው ይህን በማሰቡ ምን አጠፋ? በእውነት ያለ ነገር በመኖሩ ምክንያት አይደለም ወይ ምድራዊ ክንውኖች በሰው ሃሳብ ውስጥ የሚቀረጹት?

በህልሜም ሆነ በቅዡቴ፥ ያየሁትን፥ ለኔ መንግሥተ ሰማይ የመሰለኝን አስበዋለሁ። አእምሮም እኮ የራሱን ህልውና ማስጠበቁን ያውቅበታል። መጥፎ ነገር ውስጥ ሲገባ ጥሩ ጥሩውን ያስባል። እኔም እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ፥ ለእኔም ከዚያ መኖር መልካም እንደሆነ የተመኘኋትን - ያቺን ሥፍራ፥ በአእምሮዬ ውስጥ ከአንድ ቦታ "ቁጭ ያደረኳትን"፥ እርሷን እያሰብኩ እኖራለሁ። እርሷ ብቻዋን በዚች ምድር ልታቆየኝ ትችላለች።

ህልሜና ቅዠቴ መዳኛ መድኃኒት ሆነልኝ። ካለፍርኃት፥ ማንም ሰው በማያውቀው፥ ለኔ የኔ የሆነውን ውስጣዊ ደስታዬን እየተመገብኩ፥ ኑሮ ያልኩትን ኑሮዬን ኖርኩበት።

**<u>የጓዶች ፍቅር</u>**

በሁለት ሳምንታት ውስጥ ማንነቴ ተጣርቶ ተደረሰበት። ታስሬ የተፈታሁ መሆኔና ከኔ ጋር በፓርቲ ውስጥ ይሠሩ የነበሩ አሁንም በሌላ ከፍተኛ እስር ቤት እንደታሰሩ መሆናቸው ታወቀ። ኮድ የተባለውም፥ ለኔ ለጊዜው መስሎኝ ነው እንጂ፥ በየቀኑ ለኔ ሲል ኮድ እየሠራ የሚጠብቀኝ እንደማይኖር እነሱም ስለገባቸው፥ በእልህ ብቻ ቀጥቅጠው ሊገድሉኝ አልፈለጉም።

ስለኔ ጉዳይ የከፍተኛው ሊቀ መንበርና ካድሬው ይጨቃጨቁ ጀመር። ሊቀመንበሩ "ይህ ግለሰብ ከፍተኛ ተሳትፎ ኖሮት ሊሆን ይችላል፤ ግን እንደነጋበት ጅብ መሄጃ አጥቶ ሲንከራተት ነው የተያዘው። ባሁኑ ወቅት ኢሕአፓ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራችን ውስጥ ነው ያለው። ስለዚህ ካሁን በኋላ ያንድ ግለሰብ መገደል ለአብዮታችን ምንም የሚያመጣው ለውጥ ስለሌለ፥ እጆቹን ፈትተን ከሌሎቹ እስረኞች ጋር ቢደባለቅ ይሻላል" የሚል ሃሳብ አቀረበ።

ካድሬው ደግሞ፥ "ቆይ! ትንሽ ይቀጥቀጥ! ያንድ ግለሰብ መገደል ለአብዮታችን ምንም የሚያመጣው ለውጥ ባይኖርም፥ የአንድ ኢሕአፓ አባል እንቅስቃሴ ለአብዮታችን ጠንቅ መሆኑን አለመገንዘብህ ከአንድ የከፍተኛ ሊቀመንበር የሚጠበቅ አልነበረም!" ብሎ ተቆጣ። ሊቀመንበሩም ዝም አለና እንደተስማማ ሆነ።

አሁንም ሁለት እጆቼ የኋሊት በገመድ እንደታሰሩ ናቸው።[20] ለአንድ በግ የሚታዘነውን ያህል ሃዘኔታ ከሰዎቹ አላገኘሁም። ምን ይደረግ! በግን ቢያስሩት አርደው ሊበሉት፤ እኔን ምን ያድርጉኝ። የካድሬው እርግጫ አጥንቶቼን አድቆታል። ደግነቱ እንዳልሞት ሕይወቴን የሚጠግኑልኝ ሴቶች የድብቅ እንክብካቤአቸውን አላቋረጡም።

ይህ በዚህ እንዳለ፥ ካድሬው ለከፍተኛ አብዮታዊ ግዳጅ ተፈልጎ ወደ ሌላ ሥፍራ ተቀየረ። ከዛ በኋላ የከፍተኛው ሁኔታ ተሻሻለ። ካድሬው በሄደ ማግስት ሊቀመንበሩ እጆቼን ፈትቶ ከሌሎች የኢሕአፓ እስረኞች (ጓዶች) ጋር ቀላቀለኝ። በዚህ እኔን ባስገቡኝ ክፍል ውስጥ፥ ከኔ ጭምር፥ ሃያ ስንሆን፥ በኢሕአፓ መዋቅር ውስጥ የነበረን ተሳትፎ የተለያየ ነበር።

በዛች ጠባብ ክፍል አእምሮን ለማዝናናትና ለመርሳት የማይወራ ወሬ የለም። የተረት፥ የታሪክ፥ የግጥም፥ የዘፈን፥ የመዝሙር፥ የኩምክና ችሎታ ያላቸው ሁሉ እራሳቸውንና ሌላውን ለማስደሰት በሞቃት ስሜትና በፍቅር ይሳተፋሉ።

[20] የገመዱ ምልክት እስከ ሃያ አምስት ዓመታት ድረስ እንዳለ ቆይቷል።

በመጀመሪያው አንድ ወር ያህል እንደ ታማሚ ሰው ሆኜ ብዙ አላወራም ነበር። ከእስር ቤት ውስጥ ሁሉም ስለራሱ ሲያወራ በያንዳንዱ አእምሮ ውስጥ የሚያስጨንቅ ሃሳብ ፈታ ይላል። እኔም እንደነሱ ስለራሴ እያወራሁ ከጭንቀቴ እንድላቀቅ ጓዶች ይሻሉ። ግን አልሆነላቸውም። እኔ ብዙ ዝም ስል ስለራሴ ማውራት የማልፈልግ በመሆኔ ብቻ ሳይሆን፥ ብዙ ነገር ስለምረሳ፥ ባስታውስም የማይገቡኝ ነገሮች ስለሚበዙ እንደሆነ ጓዶቼ አልተረዱልኝም። ግን አልፎ አልፎ የምናገረው ሁሉ ያስገርማቸዋል፤ አንዳንዴም ያስቃቸዋል።

ብዙዎች ሲዝናኑ ደስ ይለኛል፤ ግን አንዳንዶቹ (በኢሕአፓ ተሳትፏቸው ከፍተኛነት ጭራሽ የማይፈቱ የሚመስላቸው) መሬት እየቆረቆሩ ሲያንጎራጉሩ፡-

አልነገርኩሽም ወይ ባጥር ተንጠልጥዬ፥

ከእስር ቤት ከገቡ መውጣት የለም ብዬ፤

ለምን የኔ ሕይወት ካንቺ ተጣመረ፥

እንደማጣሽ ሳውቀው ልቤ ተሸበረ።

ጉድ እኮ አረገችኝ፤ ጉድ እኮ ሠራችኝ፤

ለፋኖነት ሳስብ ከእስር ቤት ጣለችኝ።

እውነት አሳውሮኝ፥ ቀኑም ጨለሙብኝ፥

ስላንቺ ማሰቡ ጭንቀት ሆነብኝ።

ጉድ እኮ ዘየቴ፤ ጉድ እኮ ቀናቴ ይሏታል ይህችን ልጃገረድ አብዮትና በውስጧ የነበሩ እክሎችን ሁሉ በማጠቃለል። ከቀልዶችና ከቁምነገሮች ብዙ ትምህርት ይገኛል፤ እንደምንም ይመሻል፤ እንደምንም ይነጋል።

በአንድ የተወሰነ ወቅት የከፍተኛው እስረኞች ሁሉ (በተለያዩ ክፍሎች የነበርነው ሁሉ) በአንድ አዳራሽ ውስጥ እንድንዛወር ተደረገ። ለምን ይህ እንደሆነ ሁኔታው ተረስቶኛል። ሁላችንም ብርድ ልብሶቻችንን እየያዝን ወደ አዳራሹ ገባን። ከዚያም ሁላችንም እንደ ቀድሞው በየከፍላችን እንደ ነበርነው ተፈላልገን ተቀመጥን። ትንሽ ቆይቶም፥ መኝታ ሥፍራዎቻችንን አስተካከልን።

በአዳራሹ ውስጥ ለመጀምሪያው ቀን ብቻ ደህና ተኛን። ግን ከቀን ወደቀን ቁንጫዎች እየበረቱ እንቅልፍ ያሳጡን ጀመር። አንዱ ሲገላበጥ፥ ሌላውም ሲቀሰቀስ፥ እንዲሁ ከዳር እስከዳር መተረማመስ ሆነና፤ ለጤንነታችን በቂ የሆነውን እንቅልፍ ማግኘት አቃተን።

አንድ ቀን፥ ከጎኔ ለሚተኛ፥ በእድሜም ጠና ላለ ሰው፥ ቀስ ብዬ፥ “እያንዳንዳችን የየራሳችንን ቁንጫዎች ከለበስነው እንዳይወጡ ጥርቅም አድርገን ይዘን፥ ዝም ብለን ብናጠግባቸው፥ እነርሱም ሲጠግቡ እንቅልፍ ወስዷቸው ይተኛሉ እኮ! እኛም እናርፋለን። አለዚያ፥ ሆዳቸውን ለመሙላት ሲሉ ቁንጮቹ ሲራወጡ፥ እኛም ስንገላበጥ፥ እንቅልፍ ላናገኝ ነው። እስቲ ይህን ዘዴ እንሞክረው” አልኩት።

እርሱም ይህንን የነገርኩትን በማጣፈጥ፥ ድምጹን ጎላ አድርጎ እንቅልፍ ለወሰደውም ላልወሰደውም እንዲሰማ አድርጎ ተናገረ። ረጋ ያለ መካሪ፥ በእስረኞችም መካከል የተከበረ ስለነበረ እርሱን ሰሙትና ሁሉም በዚህ ሃሳብ በመተባበር፥ ቁንጮቻቸውን ማጥገብ ጀመሩ። በማግስቱና ከዛ በኋላ የተሻለ እንቅልፍ ተኛን።

በአዳራሹ የቆየነው ለሁለት ሳምንታት ብቻ ነበር። ከዛ በኋላ ቁንጫ ወደሌለባቸው ክፍሎቻችን ተመለስን። ከዛም የተለመደውን ወሬ ቀልድና ጨዋታ ቀጠልን። ብዙዎቹን ትንሽ ነገር ያስቃቸዋል። ያም በእድሜው ጠና ያለ ሰው ቁንጮቹን ስለማጥገብ ሃሳብ የፈለቀው ከኔ መሆኑን ስለተናገረም እንደሆን እንጃ፥ እንዳው የኔ ነገር ያስገርማቸውና ያስቃቸው ጀመር፤ የነርሱም ሳቅ ለኔ መድኃኒት ሆነኝ።

ሁሉም ለኔ ሲያስቡልኝ፥ ዝም ብዬ የነበርኩትን ቀስ በቀስ እንደምንም ሲያናግሩኝ፥ ሲንከባከቡኝና ሲያጽናኑኝ፥ ሰው ከሰው ጋር ከሆነ ምንም ቢደርስበት ሁሉን ችግር ሊወጣው እንደሚችል ሲያስተምሩኝ፥ እኔም ከእንቅልፉ ብንን ብሎ እንደተነሳ ሰው ጤናማ ሆንኩ። ያለሁበት የደጋግ ሰዎች እስር ቤት መሆኑ በደንብ ገባኝና ተዝናናሁ።

እኔን እንዲህ ውድድ የሚያደረጉኝ ለምን እንደሆነ እየገረመኝ፥ በሚያስተሳስር ጓዳዊ ጓደኝነት ጣፋጭ ኑሬዬን ቀጠልኩ፤ በእውነት የነርሱን ውለታ በሰማይ እንጂ በምድር መክፈል ይከብዳል።

**ከእስር ስለ መፈታት ወሬ**

እስረኞች ሁሉ እንደየጥፋታቸው እየተመዘነ፥ የሚፈቱትን ለመፍታት፥ የማይፈቱትን ደግሞ ወደ ከርቸሌ እስር ቤት በመላክ፥ የከፍተኛውን ጽሕፈት ቤት የቀን ተቀን ጉዳዮች ሥራ ማስኬጃ ብቻ ለማድረግ እቅድ ከወጣ ሰንብቷል። ስለ መፈታት ወሬም ብዙ ይወራል።

የከርቸሌው ሃሳብ ከመጣ በኋላ መዝናናት ጀመርኩ። ሁላችንም የእስር ቤት ኑሮን የተለማመድን ስለሆንን፥ አንዳንዶቻችን፥ በተለይ ዘመዶቻችን የሚኖሩበት አካባቢ ለከርቸሌ የሚቀርብ ከሆነ፥ ከዛው ከርቸሌ ለመሸጋገር እና እዛ ለመኖር እንመኛለን። እኔም ያቺን ቀን ስጠባበቅ ቆየሁ። ሆኖም እፈታለሁ/አልፈታም እያልን ሁለቱንም በልባችን ማሰብ አይቀርምና፤ ወሬ የተባለ ሁሉ መደምደሚያው ስለመፈታት - የስነ አእምሮአዊ ተስፋ የሚሰጥ አይነት መሆን አለበት።

በዚህ በጭንቅ ሰዓት “አንቱ! አንቱ! አይፈቱኝም?” ያለችዋም የዋህ ይቀለድባታል። “አይ አንቺ! መፈታት እንዲህ በቀላሉ..” እያሉ።

እንደ አጋጣሚ ሆኖ፥ ወይንም አሁንም አንጎሌ ለብቻው ወይንም ከሌሎች ኃይላት ጋር በመጣመር፥ “አንድ ሰው ሰይጣናዊ ቢሆንም መልአካዊ ጠባይም በውስጡ ይኖረዋል” እያልኩ እንዳስብ፤ ከዚሁም ጋር፥ “ያ ሁለት እጆቼን አጣምረው በገመድ እንድታሰር ትእዛዝ የሰጠ ሰውዬ፥ በኋላም የእጆቼን እስር ፈትተው ከሌሎች ጓዶቼ ጋር እንድቀላቀል ያደረገኝ ሰውዬ፥ ምንም ቢሆን እኔን ከእስር ቤት መፍታት አያቅተውም...” እያልኩ እንዳስብ ያደርገኛል።

ያ ሲጠበቅ የነበረ ቀን ደረሰ። ወደ ከርቸሌ የሚሄዱት እስረኞች ስም ተጠራ። በፓርቲው ከፍተኛ ተሳትፎ የነበራቸውም ያልነበራቸውም ወጣቶች ስም ሲጠራ ሁላችንም ተደናገጥን። እርስ በርሳችን አይዞህ፥ አይዞን መባባል ሆነ። እኔም “አይዟችሁ፥ ከእንግዲህ ወደ ከርቸሌ ብንሄድም ምንም አይደል፤ ከዛ ደግሞ ሌላ ኑሮ እንመሠርታለን....” እያልኩ ማደፋፈር ጀመርኩ።

አንዱ ስለሌላው መፈታት ያስባል። እኔ እንድፈታ የሚያስቡልኝ ብዙዎች ነበሩ። በደጋግ ሰዎች መካከል የሚኖር መልካም ምኞት በምግባር ተለውጦ አየሁት። እጅግ ይገርማል፤ እራሴን ወደ ከርቸሌ ለመሄድ ሳዘጋጅ ጭራሹኑ “ተፈተሃል” ተባልኩ። እኔስ ተፈታሁ ከማለት ይልቅ፥ አመለጥሁ ማለት ነው የሚቀለኝ። ተ...ተፈታሁና፥ መፈታቴን ከሚያስረዳ የመታወቂያ ምስክር ወረቀት ጋር ወደ ጠላሁት አለም ተተፋሁ - ተለቀቅሁ።

እስካሁን ያወራሁት ሁሉ በእውነት፥ እውነት ስለሆነና በመርካቶ አብረን የታሰርን ጓዶቼ ስለሚያውቁት፤ እኔ ይህን ሁሉ ስጽፍ በስሜት እያለቀስኩ እንደሆነ ይገባቸዋል፤ እነርሱም ሲያነቡት በትዝታ እንባቸው ይፈሳል።

እስከ ዛሬ ድረስ፥ ችዬ ባፌ ሳልናገረው የቀረሁትን (ያቃተኝን) ከዝምታ የማይሻል ወሬ የጻፍኩት፥ በዚህና በሚከተሉት መጻሕፍት የተካተቱ ፍሬ ሃሳቦች አመጣጥ ከየት እንደሆነ፥ መድረሻቸውም እስከየት ድረስ እንደሆነ ግልጽ ማድረግም ስላስፈለገ ነው።

ከገዛ ሀገሬ ያተረፍኩት የስነ አእምሮ ጠባሳ ሲያስለፈልፈኝ፥ ከመጥፎው ጎን ጥሩውን ለማየትም እየታገልኩ ሆነና፤ ሰው በሥጋውና ለሥጋው ብቻ እንደማይኖር፤ በመንፈሱ እና ለመንፈሱም እንደሚኖር የተማርኩትን ማካፈሌ መስሎኝ፥ ደብቄ ማቆየት ያቃተኝን (ጊዜ ከዝምታ ፈልቅቆ ያወጣውን ወሬ) ተናገርኩ። እኔም "በምክንያት" ሸክሜን አራገፍኩ።

*"ይህ ችግረኛ ጮኸ፤ እግዚአብሔርም ሰማው፥*

*ከመከራውም ሁሉ አዳነው።" መዝ. 34፡6*

ሲያወሩት ደስ የሚል፥ ምድራዊ ክብር የሚሰጥ የጀግኖች ታሪክ ሲወራ ደስ ይላል፤ በአንጻሩ፥ እንዲህ ከመደበኛ ወሬዎች ሁሉ "ለየት ያለ ወሬ" ቢወራም፥ አንዳንድ ግለሰቦች ጀግንነት ሳይጎድላቸው፥ ግን "ሁኔታዎች" በበላይነት ሲቆጣጠሯቸው ማየቱ አይከፋም፤ ይህም ትምህርት - ታሪክም ሊሆን ይችላልና።

መቼም ታሪክን በግለሰብም ሆነ በሀገር ደረጃ በመገምገም፥ ወደ ኋላ መለስ እያሉ ያለፈውን ሕይወት መመርመር የተለመደ ነው። እስቲ ከተለያዩ የሕብረተሰብ አካል ከእያንዳንዳቸው (ከሁሉም) የነበረውን ተሳትፎ እናስበው። በአንድ ሀገር ውስጥ ሥር ነቀል ለውጥ ቢመጣ፥ ያ ለውጥ በቀላሉ አልመጣም፤ ለዛ ለውጥ ተሳታፊ የሆኑት፥ ከሴትኛ አዳሪዎችና ጠላ ሻጮች ጀምሮ፥ እኛም ሁላችንንም ጨምሮ ነው። ወታደሩ ሚስቱን ልጆቹን ትቶ ወደ ጦር ግንባር ሲዘምት፥ ዘማቾችም የሞቀ ቤታቸውን ትተው ወደ በረሃ ሲዘልቁ፥ ሁሉም ነባራዊ ሁኔታዎችን ቀይረው ለኢትዮጵያችን የተሻለውን ለማምጣት ብለው ነው።

የአንድን ሀገር ታሪክ የሚወስነው የጠቅላላ ሕዝቦቿ ሥጋዊና መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በመሆኑ፥ እንዲህና የመሳሰለው የግለሰብ ወሬ፥ የግለሰቦችን ተሳትፎ፥ መጠንና ይዘቱንም ያሳያል። በዚህ ጽሑፍ የቀረበውን የመሳሰለ በአፍ መናገር የሚያቅት ብዙ የተደበቀ ታሪክ እንደሚኖር አያጠራጥርም። ሁሉም በየቤቱ ከብጤው ጋር ያወጋዋል።

አንዱ ሲያለቅስ አይቶ ሌላውም እንደሚያለቅስ ሁሉ፥ ለመኖር ፈቃድ ተሰጥቶት የሚኖር ሰው ሁሉ የሌሎችንም መንፈሶች ተሸከሞ የሚኖር መስሎኝ፤ በግርፋት ብዛት ደምተው የሞቱ የምወዳቸው ጓደኞቼ ወገኖቼ ሁኔታ ሁሉ ትዝ ትዝ እያሉኝ ጻፍኩት።

አንዳንድ ሰዎች ማየት የሚፈልጉትን ብቻ ያያሉ፤ መስማት የሚፈልጉትን ብቻ ይሰማሉ፤ ስለዚህም በዚህ ዝብርቅርቅ አለም ውስጥ የራሳቸውን አለም መሥርተው ይኖራሉ (እራሳቸውን እየደለሉ፥ እያሞካሹ)።

መናገር ሲያቅተኝ የነበረውን ታሪኬን (ታሪካችንን)፥ ዛሬ ለናንተና ለሌሎችም ከዚህ ምድር ለተለዩኝ ጓደኞቼ (ጓዶቼ) ስል አወራሁ። በቃ! የውሃ ነፋስ ተነፈስኩ፤ የዝምታ ዕዳዬንም ከፈልኩ።

ታግሎ መታሰር፥ ታስሮ መፈታት፥ ተፈቶም በቀጣዩ ሕይወት ከቤት መቀመጥ ኢትዮጵያችንን አያድናትም። ትግሉ ገና አልተቋጨምና፤ እነሆ! ከትግል ትግል ተሻግራችሁ፥ ከዚህ የደረሳችሁ በውጪም በሀገር ቤትም ያላችሁ ወገኖቼ ሆይ! የእናንተን የትግል መንፈስ እንደቀላል ነገር አትዩት። በረቀቀ መንፈስ (እናንተ በሚመስላችሁ መንገድ) ትግላችሁን ቀጥሉ፤ ኢትዮጵያ የሁላችንንም ሞቃት ተሳትፎ ትፈልጋለች።

የታሪካችን ምድራዊ ጎኑ ቢረሳ፥ ሰማያዊ (መንፈሳዊ) ጎኑ እንዳይረሳ "ያንን" ብዙ ሰው ሊመለከተው ያልቻለውን የእውነተኛ  የኢሕአፓዎች በጎ አሳቢነትና መልካም መንፈስ - ስሜት (ወኔ) በየቦታውና በያቅጣጫው "ልዩ በሆነ መንገድ" እንቀስቅሰው።

ኢትዮጵያችን የእውነተኞች መንደር ተብላ እንድትጠራ፥ ከተለያየ አቅጣጫ የእውነት ብርሃን የምትፈነጥቁ ሰዎች ሁሉ፥ በዚህች ምድር ላይ ስትኖሩ፥ ለጠቅላላ ሰብአዊነት እንጂ ለራሳችሁ (ለግላዊ ክብራችሁ እና ጥቅማችሁ) ብቻ ሳታስቡ ከሆነ፥ **እናንት** ለዘለአለም ኑሩ።

አንቺም "የድል ኮከብ"፥ ከመንደር ያለሽው፥

ወጣ በይ ከጓዳ፥ ወገንሽን እዩው፤

ብርሃን ሰጪ አካል፥ መሆንሺን አትርሺው፤

ተደብቆ ኑሮ፥ መሸነፍን ፍሪው፥

ድሉ የሕዝብ እስኪሆን፥ ተስፋሺን አታጥፊው።

በቆራጥነት ታግለው ካለፉት ጎን - በአሲምባ፥ በበጌምድር ገጠር የነበራችሁ፥ ይህ የኛ የኢሕአፓዎች ታሪካችን ባለ ብዙ ዘርፍ መሆኑን ተመልከቱት። ከዚያን ጊዜ

ጀምሮ እስካሁን ድረስ በትግል ላይ ያላችሁ፥ የአሁኑም ትውልድ የእናንተን ፈለግ እንዲከተል፤ የእናንተም መንፈሳዊ ጥንካሬ እና ብርታት ለወደፊቱ ትውልድ እንዲተላለፍ ብታደርጉ መልካም ነው።

ያኔ፥ እ.ኢ.አ. ከ1966 ዓ.ም. በፊት፥ "መሬት ላራሹ" በሚል መርሆ ተነሳስተው ሲታገሉ የነበሩ ወጣት ኢትዮጵያውያን፥ እንሸለማለን፥ ምድራዊ ክብርን እናገኛለን ብለው አልነበረም፤ የድሆች እና የጭቁን ገበሬዎች ሕይወት እንዲሻሻልላቸው ሲሉ ነበር እንጂ።

ባዶ እጃቸውን ሰላማዊ ሰልፍ እያደረጉ ሲጮሁ የነበረው፥ ሰሚ ያጣውን የድሃውን ብሶት እና እሮሮ ለማስተጋባት ነበር እንጂ፥ ፖለቲካዊ ዝናን ለማትረፍ አልነበረም። የዛን ጊዜ በትግል አለም ውስጥ ሲታገሉ የነበሩ፥ እነኛ ወጣቶች ያለፉቱ፥ አሁንም ከሞቀ ቤታቸው ወጥተው በትግል ላይ ያሉቱ፥ በማንኛውም ደቂቃ ሕይወታቸው እንደምታልፍ ያወቃሉ። የገቡበት ትግል፥ በገንዘብ ምድራዊ ደስታን ለመሸመት አልነበረም፤ የውስጣዊ ማንነታቸው ጥሩነት መክሯቸው፤ በጎ መንፈሳቸውም መርቷቸው ነው እንጂ። የእነርሱን (የታጋዮቹን) ግላዊ ሕሊና ከሁለንተናዊ ሕሊና ጋር በማቆራኘት፥ እነርሱ በሕይወታቸው የከፈሉበትን ምድራዊ ደስታ የወደፊቱ ትውልድ እንዲረከበው አስበው፥ ምድራዊ መከራን በጫንቃቸው ላይ አሳረፉት። ጥሩ ለሚሠራ ጥሩ ሰው ሽልማት ቢኖረውም፥ ያ ሽልማት ምንጊዜም ከምድራዊ አለም እንደማይጠበቅ ውስጠ መንፈሳቸው ነግሯቸዋል። ነገር ግን፥ እነርሱ ለምድራዊም ሆነ ለሰማያዊ ሽልማት አልሮጡም።

እጅግ ብዙ መከራ የደረሰባቸው የብዙ ታጋዮች ወንድሞችና እህቶች፥ አባቶችና እናቶች ታሪክ (ያለፈው፥ የዛሬው እና የወደፊቱም) ቢወራም ባይወራም፥ ቢጻፍም ባይጻፍም፤ የሁሉም ታሪካዊ አቅጣጫው አንድ ነው። የሚያመራውም ከግለሰብ ወደ ሕብረተሰብ፥ ከሥጋዊነት ወደ መንፈሳዊነት ነው። ይህም ሂደት የኋላ ኋላ በመንፈሳዊ ግንኙነት ተዋሕዶ፥ እንደ አንድ አቢይ ክስተት (የአንድነት መንፈስ) በጉልህ የሚታይበት ወቅት ያስገኝ ይሆናል።

ይህም በመልካም መንፈስ ግፊት የተጻፈ ጽሑፍ (መልዕክት) ልብ ወለድ ካለመሆኑም በላይ፥ በውስጠ ታዋቂነት የሚታወቀን የመንፈሳዊነታችን ነገር፥ ፈጽሞ ችላ የማይባል መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

# ምዕራፍ ስምንት

## ቅሪተ ሃሳብ

የኢትዮጵያችን ነገር እሳት ላይ ተጥዶ አልበስል ብሎ እንደቆየ ጎመን ሆኖ ቆይቷልና፤ “በጊዜ ውስጥ ምን ተፈጸመ ባገራችን?” ብለን ስንጠይቅ፥ ብዙው የሚያሳዝን፥ የሚያስለቅስም ቢሆንም፥ እኛ የኢትዮጵያችንን ሂደቷን - ከዚህ ቀጥሎስ እያልን በማስታወሺያችን ዘግበናል።

ከእስር የተፈታሁበትን ወረቀት (የነፃነት ፓስፖርት) በኪሴ ይዤ፥ እንደገና በአዲስ አበባ መንገዶች ውስጥ መዘዋወር ጀመርኩ። ከከፍተኛ ወደ ከርቸሌ ተሸጋግረው ከዚያ ብዙ የቆዩትን ለተወሰኑ ጊዜያት ብቻ ጠየቅኋቸው። ምድራዊ ሁናቴዎች፥ የኔም አሻግሮ አለማየትና ራስን ወዳድነት ጠባይ ተጨምሮ፥ እስኪፈቱ ድረስ በየሳምንቱ እየሄድኩ ባለመጠየቄ ይቆጨኛል።

ያልታሰሩት ጓደኞቼ ምንጊዜም ጓደኞቼ ናቸውና፤ “ወይ ጉድ! ለካስ አንተም እንዲህ ያለህ ነበርክ!...” ብሎ የራቀኝ ማንም ሰው አልነበረም። ታዲያ፥ አንዳንዶቹ አስተሳሰቤን ሲመለከቱት፥ ማንም ሰው እራሱን የሚያመሳስልበት ሲያጣ፥ የገዛ ሕይወቱ ከሁለቱ አለም ለአንዱም የማይጠቅም እንደሚሆንበት ይሰማቸውና፥ “እህ!..” ብለው ዝም ይላሉ።

እኔ ግን እራሴን ለቀቅ እያደረግሁ፥ አካባቢዬንም እየመሰልኩ እንድኖር የሚያስችል ጠባይ የለኝም። ስለዚህ፥ በዚሁ ልለውጠው ከታገልኩለትና ተሸንፌ ከተውኩት አለም ውስጥ ብቻዬን ያለሁ መስሎኝ ተከፍቻለሁ። ለዚህ አለም ሕይወት ትርጉም ስላጣሁበት ለቀሪ ጓደኞቼም ግራ የማጋባ ሆንኩባቸው፤ ጥንትም በደንብ አያውቁኝ ነበር፤ አሁን ደግሞ የባሰ እንግዳ ሆንኩባቸው።

የኮሙኒስት ስርዓት መሠረታዊና የምኞታዊ - መንፈሳዊ መሰል አስተሳሰብ ይማርከኛል። በሰዎች ልጆች ፍቅር፥ በማንኛውም ረገድ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ኑሮን እመኛለሁ።  ለኔ ኮሙኒስት መሆን ማለት የራስን ድሎትና ደስታ ሁሉ ለጋራ ድሎትና ደስታ አሳልፎ በመስጠት ውስጥ፥ የራስን ደስታ ማግኘት ማለት ነው። የክርስቲያናዊነትም አላማ ይህንኑ የሚመስል ስለሆነ ይመስለኛል፥ ከኮሙኒስትነት

ሲወጡ ወደ ክርስቲያናዊነት (ሃይማኖተኛነት - መንፈሳዊነት) ዘንበል ማለትን በገሃድ የተመለከትነው።

በኮሙኒስት ዶክትሪን፥ በሳይንስ እውቀት፥ በግትረኛነትና አመጻኛ ጠባይ፥ እኔ ከእኔነቴ በስተቀር ሌላ ምን አለብኝ ብዬ፥ የራሴን ሕይወት በራሴ ለመምራት ስሞክር፤ "ተው አንተ!..." ብሎ የሚገታኝ ኃይል ተቋቋመኝ።

ሰዎች ማንኛውንም አይነት ምድራዊ ሰማያዊ ምልከታ ቢኖራቸው፥ ምንጊዜም የደግነታቸው ውስጣዊ ጠባይ አይለቃቸውም። ግን በሰዎች መካከል እየገባ የሚያበጣብጥ አለ። ከሀገሬ ከኢትዮጵያ ጋር እራሴን ማጣጣም አቃተኝ። ኢትዮጵያ የማላውቃት (ባይተዋር) ሆነችብኝ - በባእድ ሀገር የምኖር መሰለኝ።

***<u>መንግሥታዊ አስተዳደርና ስርዓቶች</u>***

ሰውን ሁሉ በእኩልነት የሚመራ መንግሥታዊ መተዳደሪያ ደንቦች - ሕግጋትም ይረቃሉ፤ ፖለቲከኞች ይሯሯጣሉ፤ ቅን አሳቢዎችም በየአቅጣጫው ይደከማሉ። ግን ማነው ለጋራ ብልጽግና የቆመ? ማን? ምንድነው የሰብአዊነትን ሁለንተናዊ ህልውናን የሚያስጠብቅ ስርዓት የሚያስገኝ?

በኮሙኒስት አገሮች የተገኘ የሰዎች የሕሊና እድገት ሥጋዊ ስነ አእምሮን አጎለመሰ እንጂ፥ መንፈሳዊነቱን አቀጭጮታል። ከዚያ የኮሙኒስቶች አገሮች ነዋሪ የሆኑ፥ የሚፈልጉትን ለማድረግ እንዳይችሉ ይገታሉ። በኑሮአቸው ውስጥም፥ የጋራ ካልሆነ በስተቀር፥ ግላዊ መንፈሳዊ ደስታቸው በብዛት (በየጊዜው) እየተነፈጋቸው እንደሆኑ ይነገራል።

ኮሙኒስት መሆን እግዚአብሔርን ከማመን ጋር ቢሆን ኖሮ፥ ከየትም ይምጣ ከየት፥ የደጋግ መንፈሶች ጣምራነት አቻናፊ ይሆን ነበር። ኮሙኒስቶች ምድር (ተፈጥሮ) ወጣ ገብ እንደመሆኗ፥ በዛውም ልክ (ወይንም ከዚያ በባሰ መንገድ፥ የሰው ልጅ በፍጥረቱ ወጣ ገብ (የተለያየ) መሆኑን ባለመገንዘብ፥ ሰውን ሁሉ በጋርዮሽ አስተዳደር ማካተትና እንቅስቃሴውንም መቆጣጠር (መምራት፥ መወሰን፥ መግታት...) ለእነርሱ ትክክል መስሎ ይታያቸዋል። ነገር ግን፥ ይህ ከሰብአዊ አመለካከት አንጻር፥ ለትክክለኛነቱ ማረጋገጪያ አያገኙም። የሰው ፍጥረቱ ሁለት አይነት (ሥጋ እና መንፈስ) መሆኑ አልገባቸውም።

በፈጣሪ የማያምኑት ከሰው በላይ ሁሉን ሊያስተካክል የሚችል እግዚአብሔር መኖሩን አላወቁም። የምድርን ወጣ ገብነት (ለሰው ሁሉ እኩል አለመሆን) በደንብ አልተረዱትም፤ ቢረዱትም በሶሻሊስት ርዕዮት ማስተካከል

የሚችሉ መስሏቸዋል። የሰው ልጅ በተፈጥሮው ሁሉም እኩል ሆኖ የተፈጠረ ቢሆንም እንኳን፥ ይህን እኩልነት የምድር አድሎአዊነት ሊለያየው እንደሚችል ቢገባቸውም፥ በእነርሱ ጥርት ሁሉን ማስተካከል የሚቻል መሰላቸው።

የኢኮኖሚ እድገትን በሶሻሊስት ርዕዮተ አለም ሲቀይሱ፥ የሰዎችን አልጠግብ ባይነትና ስግብግብነት በቀላሉ ተመልክተውታል። ይህ የሰው ሁሉ ምድራዊ ጠባይ በኢኮኖሚ ላይ የሚኖረውን ወሳኝነት ወደጎን አደረጉት። በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ስርዓት ብቻ ቶሎ ቶሎ ወደፊት መራመድ የሚያዳግት መሆኑን በወቅቱ አላወቁትም ነበረ።

ቀደም ሲል ሌኒኒስቶች ይህን ችግር ከሞላ ጎደል ተረድተውት ልዩ (መለስተኛ) የኢኮኖሚ ፕላን (New Economic Policy) ዘርግተው ነበር። በኋላም ትሮትስካይቶች የሰዎችን ጠባይ፥ ድክመቶች እና ችግሮች በመረዳት የጊዜያዊ ካፒታሊዝምን አስፈላጊነት ሲሰብኩ ነበር።[21]

እስታንሊኒስቶች ግን፥ የሰውን ውስጣዊ ጠባይ አልተረዱትም፤ ክፉውን ሰው ከደጉ ሰው በጉልበት ለይተው ለማላቀቅ የሚችሉ፤ ወይንም ክፉውን ሰው ገድለው ቢጨርሱት የሚቀረው ሁሉ ደግ ብቻ የሚሆን መሰላቸው(?)።

የኮሙኒስት ጽንሰ ሃሳብ ከሰው ተፈጥሮ ውስጥ መጥፎውን ማጥፋት የሚችል፤ ኮሙኒስትነትም የምድርን ወጣ ገብነት የሚያስተካከል - የሰውን ጠባይ የሚያርቅ (የሚያሻሽል) መሰላቸው(?)። በአንድ ኃይለኛ ስርዓት ድንጋጌ ብቻ የሰው ሁሉ ተፈጥሮአዊ ጠባይ በጉልበት ወይንም በስብከት አንድ ወጥ ሊሆን እንደሚችል አድርገው ወሰዱት(?)።

ኮሚኒስቶች በአንድ ካፒታሊስት ልቦና ውስጥ ቅንነትና ክፋት ባንድነት እንደሚኖሩ ሁሉ፥ በአንድ ኮሙኒስት ሰው ልቦና ውስጥም ቅንነትና ክፋት ባንድነት እንደሚኖሩ አልገባቸውም? ታዲያ፥ ያ የሰው (ሰብአዊ) ልቡና ክፋቱን በቅንነት እስኪለውጠው ድረስ፥ ያ የምናስበው መልካም ስርዓት (መንፈሳዊ ኮሙኒዝም) በቶሎ አይመጣም ማለት ነው?

ሰው በሚሠራውና በሚያደርገው ሥራ ሁሉ ዘለአለማዊ አስተሳሰቡ (ጥሩው)፥ እሩቅ ወደ ሆነውና ወደማይጨበጠው አለም ያስመለክተዋል። በዚህ አንጻር፥ የአንዳንድ ዘመን አመጣሽ ሃይማኖቶችን (cults) መሠረታዊ አላማ ብንመረምረው፥ ባሁኑ ጊዜ የማይቻለውን ምድራዊ ሕብረተሰብአዊ አንድነት

21 እነኚህን መጻሕፍት ያንብቡ፡- The Prophet Armed/The Prophet unarmed/The Prophet Outcast

ለመፍጠር እንደሆነ እንገነዘባለን። በቶሎ ከመፍረድና ስህተተኞች ናቸው ከማለት ይልቅ፥ አሁን ላለንበት ዘመን የማይሆን ነው ብሎ ማለፍ ይሻላል።

በተመሳሳይ፥ ማርክስና ኤንጀልስ እራሳቸውን ከፍ፥ ሌላውን ዝቅ አድርጎ የሚያሳይ የፊውዳላዊ እና ካፒታሊስት ርዕዮት (አስተሳሰብ - አመለካከት)፥ ብዙሓኑን ሲጎዳ ተመለከቱና፤ “ይህን በሰብአዊነት ውስጥ ተረጋግቶ የተቀመጠ በሽታ ለማጥፋት እንነሳ፤ የሰውም ልጅ እስከዘለአለሙ ጤነኛ ሆኖ ይኑር” ብለው አሰቡ።

የማርክስ እና ኤንጀልስን መሠረታዊ ፍልስፍና ብንመረምረው፥ እነርሱም ቢሆኑ መሠረታዊ ፍልስፍናቸው የተጠነሰሰው፥ ለሰው ልጅ እኩልነት በማሰብ፥ ምድራዊ ሕብረተሰብአዊ አንድነት ለመፍጠር ነበር። በቶሎ ከመፍረድና ስህተተኞች ናቸው ከማለት ይልቅ፥ አሁን ላለንበት ዘመን የማይሆን ነው ብሎ ማለፍ ይሻላል።

ያም ሆነ ይህ፥ መልካም አስተሳሰቦች ከክፉው ጋር ሳይጋጩ ለዘለአለም ረግተው አይቀመጡም፤ መላው ጠፈር በቅራኔውች ትግል ውስጥ ያለ ነውና። ሆኖም፥ ጊዜው ይርዘም እንጂ፥ አንድ ቀን የጠፈር ኃይላት ቀና አስተሳሰቦች ሁሉ በረድፍ በረድፍ ይስተካከሉና፥ በዚች በምድራችንም ላይ ቀናውን መንፈሳዊ ተጽእኖ ያሳድሩብን ይሆናል። ጊዜው ይርዘም እንጂ፥ አንድ ቀን አለም አቀፋዊ ወንድማማችነት (መንፈሳዊ - ኮሙኒስታዊ አመለካከት) መምጣቱ አይቀርም (መንግሥትህ ትምጻ)።

የወደፊቱን ለሕዝቦች የሚጠቅም መንግሥት መመሥረት የሚቻለው፥ በከፍተኛ የመንፈሳዊነት እድገት መሆኑን በሃይማኖታዊ ስነስርዓታዊ አስተዳደር የሚ<u>መ</u>ሩ አገሮችም (ለምሳሌ፥ አንዳንድ የእስላም አገሮች) የሚገነዘቡት ይመስላል። በእነኚህ አገሮች ውስጥ ሃይማኖት የበላይነት ስላለው፥ የሰዎችን ሞራላዊነት (መንፈሳዊ ጨዋነት) በአንድ በኩል ከፍ አድርጎታል፤ በሌላም በኩል ጎድቶታል። ለምሳሌ፡- የእስላም ወንዶች ብዙ ሴቶች ያገባሉ፤ ሚስቶቻቸውን ከራስ ጸጉር እስከ እግር ጥፍር ሸፋፍነው ይደብቋቸዋል። ማታ ማታ ለእነርሱ አይን ብቻ እንዲታዩ አድርገው ይገልጧቸዋል። ሴቶቹም ወንዶቻቸው ባወጡት ሕግጋት እየተመሩ በሴትነታቸው ዝቅተኛነታቸውን (ከወንድ እኩል መብት መነፈጋቸውን) ባያምኑበትም በግድና በፍርኃት ተቀብለውት ይኖራሉ።

ሴቶች ከወንድ እኩል ወይንም ከወንድ በላይ መብት የነበራቸው ዘመን ነበር ይባላል። የሴቶች መብት ከጠፋ ቆይቷል። ባሁኑ ጊዜ በአለም ዙሪያ ወንዶች ለሴቶች

በቂ ክብር አይሰጡም። ሴቶችም በወንዶች ስላልተከበሩ፥ ራሳቸውን ዝቅ አደረጉት፤ ከዝቅተኛነታቸውም የተነሳ አንዳንድ የሚሠሩት ሥራ የማያምር ሆነ።[22]

ብዙውን ጊዜ በዚህ አለም ላይ ለጥሩ ነገር (ለሰላም፥ ለፍቅርና ለደስታ) ምክንያት የሚሆኑ ሴቶች ሆነው ሳለ፥ ወንዶች ሴቶችን ስለማያዳምጧቸው፥ አንድም ይህ ነው (ይሆናል) በምድር ላይ ጭካኔ የመብዛቱ ምክንያት። ወንዶች ሴቶችን ባለማክበራቸው የሰብእነት ማንነት (ሰው መሆን ምን ማለት መሆኑ) ቁልጭ ብሎ አልታየም - መንፈሳዊ ጎኑ አልተገለጠም።

በበለጸጉት የካፒታሊስት አገሮች የግለሰቦች ሠርቶ የማደር ችሎታ ፊውዳላዊ መበላለጦችን የደመሰሰበት ሥፍራ ስለሆነ፥ ማንም ለማንም አያጎበድድም፤ በመጠኑም ቢሆን፥ የሰው ልጅ በተፈጥሮአዊ እኩልነቱ ይከበራል። በጦርነት ሳይሆን በድምጻቸው ብቻ የመንግሥት አስተዳደርን የመለወጥ ችሎታ አላቸው። ሰብአዊ መብት ስለሚከበር ሰው በሥጋውም በመንፈሱም "ደመቅ" ያለ ኑሮ ይኖራል።

ሆኖም፥ ግለሰብ ምድራዊ ፍላጎቶቹን ብቻ እየተከተለ ሲጓዝ፥ ተቆጣጣሪ ስለሌለው፥ ከመጠን በላይ ስግብግብ፥ ከመጠን በላይም እራስን ወዳድ እየሆነ መጥቷል። ይህም ወደተለያዩ ጥፋቶች እያመራ፥ አጠቃላይ ሰብአዊነትን አራክሶታል - የሰዎች ሞራላዊነት (መንፈሳዊ ጨዋነት) ዝቅ ብሏል። ስግብግብነትና ግለኛነት እጅግ ከፍተኛ በመሆኑም፥ የሰዎች ማሕበራዊ ኑሮ ተበላሽቷል - ጠፍቷል ማለትም ይቻላል።

እጅግ የሚገርመው፥ ሕብረተሰቡ በማይገታ (በማይታረም) ግለኛነት ወደ ሰይጣናዊነት ሲያመራ፥ ይህንን እንደ ሰብአዊ መብት የሚቆጥሩ ይኖራሉ። በካፒታሊስት ስርዓት ውስጥ የግለሰቦችን ስንኩል ሥራ የሚገታ መንግሥታዊ ተቋም የማይኖረውም ለዚህ ይሆናል።

ጥንት ሰዎች በጋርዮሽ ሲኖሩ በነበሩበት ጊዜ የነበረው ሕብረተሰብ፥ ምንም እንኳን በኋላ ቀር ስርዓትነት ቢታይም፥ በጋርዮሽ አስተሳሰብ ላይ በተመሠረተው የሰው ጠባይ፥ ቀለል ያለ፥ ምናልባትም፥ ቢያንስ ማሕበራዊ ደስታን የተላበሰ ነበር ማለት ይቻል ይሆናል። እንዲህ ያለው አኗኗር፥ ህብረተሰቦች በሺህ ዓመታት ውስጥ ባሳዩት እድገቶች ጥፍት ብሎ ተሰናብቷል። የባርያ ስርዓት የሚሉትም አሁን የለም።

ሦስተኛው አለም ተብለው በሚጠሩ እንደ ኢትዮጵያችን ባሉ በድሆች አገሮች ያሉ ሕዝቦች "ይህችን ምድር በስነስርዓት የሚያስተዳድር መንግሥት ከወዴት

---

[22] *"መበለቲቱንና ደሀ አደጉን፥ መጻተኛውንና ችግረኛውን አትበድሉ፤ ከእናንተ ማንም በወንድሙ ላይ በልቡ ክፉ አያስብ።" ዘካ. 7፡10*

ይገኛል?” እያሉ ይጮሃሉ። ፖለቲካዊ ፍልስፍናን እንደ እነርሱ ያወቀበት የለም። አለም አቀፋዊ ርዕዮት በድሆች አገሮች እንደሚገኝ፥ ሌላ “ሰለጠነ” ተብሎ ከሚጠራው አለም አይገኝም። ግን በዚህ ድሆች የበዙባት የአለማችን ክፍል ውስጥ፥ የፖለቲካ ችግርም የመላበት፥ መፍትሔውም እንቆቅልሽ የሆነበት ሥፍራ ነው።

ሃብት በጥቂቶች እጅ ስለሆነ፥ ኃይለኞች የሆኑት በገንዘባቸው እንዳሻቸው ሲኖሩ፥ የተቀረው ሕዝብ በድህነት ይኖራል። ሰው በሰው ላይ ግፍ ሲሠራ በግላጭ ይታያል። በአንጻሩም፥ ለተጨቆኑ እና ለተበደሉ የሚያዝኑ፥ አምላካቸውን በጸሎት የሚማጸኑ ትጉሃን ሃይማኖተኞች የሚበዙት፤ ሕዝቦች ከችግሮቻቸው በራሳቸው ይወጡ ዘንድ፥ መንፈሳዊ ብርታትን የሚሰጣቸውን ትክክለኛውን ምርጫቸውን (መንፈሳዊነታቸውን) ሲያጠናክሩ በጉልህ የሚታየውም ከዚያ ነው።

*“ለምስኪኑ ተስፋ አለውና፤ የዐመጻኛም አፍ ይዘጋልና።” ኢዮ. 5፡17*

የሰው ልጅ በአካላዊ (ሥጋዊ) አለም ውስጥ እየኖረ ከመጥፎ ነገሮች (እራስን ወዳድነት፥ ስግብግብነት፥ ክፋት፥ ወ.ዘ.ተ.) ሊላቀቅ ስለማይችል፥ ያ ፍጹም አስተዳደር ከመሬት ሊገኝ የሚችል አይመስልም። ምናልባት መንፈሳዊነትን ያላጣመረ ሶሻሊዝም እንደማያዋጣ የተገነዘቡ፥ እንዲሁም ለወደፊት ካፒታሊዝም ሲወድቅ ተመልክተው የሚማሩ ቢኖሩ፥ ምናልባት የዛን ጊዜ በመንፈሳዊነት የታነጸ ሁለንተናዊ የሶሻል፥ የፖለቲካና የኢኮኖሚ መፍትሔ ይፈጥር ይሆናል።

የአንድ ሀገር ሕዝብ፥ በቅድሚያ መንፈሳዊ የበላይነቱን የሚያስከብር ቢሆን፥ የዛን ጊዜ ዋናውና ወሳኙ የአጠቃላይ የሕዝቦች መንፈሳዊ ንቃት ይረጋገጣል። የዛን ጊዜ፥ የማንኛውንም አይነት የመንግሥት ሥርዓት (ዴሞክራሲ፥ ሞናርክ፥ ወ.ዘ.ተ...) በንድፈ ሃሳብ (በቲዎሪ) በተግባርም ቢከተል ለክፉ አይሰጠውም፤ የዛን ጊዜ በ“ኢዝሞች” ፋንታ “አብሮነት” ይተካል።

**<u>የለውጡ ትሩፋቶች</u>**

ዴሞክራሲ በሌለበት ሀገር፥ መንግሥታዊ ስርዓት ቢለወጥ፥ የርዕዮተ አለም አይነቶችም ቢቀያየሩ፥ አንዱ ካንዱ የማይሻል ይሆናል። ባጠቃላይ ሲታይ፥ አንድ መንግሥታዊ አስተዳደር ከሌላው የማይሻል ከሆነ፥ ገዳም ገብተው የራሳቸውን አስተዳደር ከመሠረቱት በስተቀር፥ ለሰው ልጅ ምንም አይነት ሥጋዊ (ምድራዊ) አስተዳደር የሚበጀው አይመስልም።

የዛን ጊዜ (በአብዮቱ)፥ ከፍ ሲል እንደ "ዴሞክራሲያ" ያለ ሀገር አቀፍ መጽሔት፥ ዝቅ ሲልም እንደ "የድል ኮኮብ" የመሳሰሉ የመንደር መጽሔቶች በውስጣቸው ሲያስተጋቡ የነበሩት ጽንሰ ሃሳቦች ቢመረመሩ፥ የድሃውን እና የተጨቆነውን የሠፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሶት እና ጩኸት ፖለቲካዊ ቅርስ በመስጠት፥ ያንን አስከፊውን በባላባት እና የጭሰኛ ስርዓት ላይ የተመሠረተ ኋላቀር የኢኮኖሚና የሶሻል ስርዓት በተሻለ የኢኮኖሚ እና የሶሻል ስርዓት ለመቀየር እና ለመገንባት ነበር እንጂ፥ አሁን አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት፥ የውጭ አገሩን - የባዕዳኑን ፍልስፍና በመከተል፥ ኢትዮጵያችንን በውጪ አእምሮ ለማስገዛት አልነበረም።

በሀገራችን ያልነበረውን፥ ስለ እኩልነት የሚሰብከውን የሶሻሊስት ፍልስፍና ከውጪው የምሁራን አለም መበደር ግዴታ የሆነበትም ምክንያት፥ የሀገራችንን ታሪካዊ፥ ባህላዊ እና መንፈሳዊ ቅርጾች በውጪው አለም ለመተካት አልነበረም፤ የዛን ጊዜ የነበረውን ጭቁን ሕዝብ ነጻ ለማውጣት፤ በቅድሚያ ንቃተ ሕሊናውን ከፍ የሚያደርግለት የሰብአዊነት እና የእኩልነትን መንፈስ በጥልቀቱ የሚያሳየው፥ በጊዜው የተገኘው የሶሻሊስት ፍልስፍና ስለነበረ ነው እንጂ።

አንዳንድ ሰዎች፥ በኢሕአፓም ሆነ በሚኤሶን ሲታገሉ የነበሩትን ሲተቹ፥ "አያሌ ወጣቶች ያለቁት በእነርሱ የተሳሳተ የፖለቲካ አመለካከት ነው" ይላሉ። ታዲያ የዛን ጊዜ፥ በዚያን ጊዜ ለነበረች ኢትዮጵያችን የተሻለው እና ያልተሳሳተው የፖለቲካ አመለካከት የትኛው ነበረ? የንጉሡ ወይንስ የደርጉ። በወቅቱ ከነበሩትስ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የትኛው ነበር ያልተሳሳተው? የተሳሳተውን የሚጠቁም ያልተሳሳተውንም ማሳወቅ ይኖርበታል።

በእርግጥ እጅግ ታላቅ ስህተት መሠራቱ አይካድም። ስህተቱ ግን በጊዜው በነበረው አጠቃላይ የፖለቲካ ርዕዮት (አመለካከት) ሳይሆን፥ በተሳሳተው የትግል መንገድ ነበር፤ ማለትም የታክቲክ እና እስትራተጂ ስህተቶች ነበር ማለት ይቀላል።

ብዙውን ጊዜ ኢሕአፓ የሚተቸው፥ የኢትዮጵያን ምድራዊና መንፈሳዊ ታሪኳን ያላወቁ ወጣቶች፥ ከውጪ ቀድተው ባመጡት ርዕዮት (ideology) ብቻ

ተመርተው፥ ኢትዮጵያን በማይመጥናትና ከርሷ ማንነት (ከመንፈሳዊነቷ) ጋር አብሮ በማይሄድ መንገድ ሊመሯት ስለፈለጉ፥ አላስፈላጊ እልቂትን አመጡብን ይላሉ።

መቼም "በወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል" እንደሚባለው ሆነና ነው እንጂ፥ በደርግ ፋንታ ከሁለት አንዱ (ኢሕአፓ ወይንም መኢሶን) ሥልጣን ቢይዝ ኖሮ፥ ባሁን ሰዓት ኢትዮጵያችን፥ በአንድነቷ፥ በሶሻል እና ኢኮኖሚ ይዘቷም ከፍተኛ ደረጃ ልትደርስ ትችል ነበር ብሎ ማሰብ ይቻላል።

የዛን ጊዜ፥ "እኛ ምድራዊ ምኞት ካገኘን ስለኢትዮጵያ መንፈሳዊነቷ ምን ጨነቀን" የሚሉ፥ ዛሬ እነርሱ መንፈሳውያን መስለው፥ ትችት በተለይ በእነርሱ ባሰና፥ "ኢሕአፓዎች አናርኪስቶች ባይሆኑም'ኮ! እነርሱ ኢአማንያን/እግዚአብሔርን የካዱ ኮሙኒስቶች ስለሆኑ፥ በምንም መልኩ ለኢትዮጵያ አይመቹም" ይላሉ።

ኢሕአፓ የግለሰቦችን ግላዊ እምነት የሚዳፈር አልነበረም። ኢትዮጵያ ውስጣዊ መንፋሳዊ ባሕሬዋን ረስታ፥ ፈጣሪ አምላኳን ክዳ፥ በምድራዊ ከፍታ ብቻ እንድትተማመን የሚያደርግ ሶሻሊዝም/ኮሙኒስም የተሰበከባት በደርግ ዘመን በነበረ አቅጣጫ ቢስ ስርዓት መሆኑ ይታወቃል። ይልቁንስ፥ በዚያ በደርግ ዘመን ባጠቃላይ "ተፈጥሮን በቁጥጥር እናደርጋለን" በሚል መርሆ፥ ሰው ከፈጣሪው በላይ በራሱ እንዲመካ እና እግዚአብሔርንም እንዲክድ ሲያደፋፍር የነበረው የደርግ መንግሥት እንጂ፥ ኢሕአፓ አልነበረም።

ከተጠቀሱት ትችቶች ሁሉ ባሻገር፥ "ከምድራዊና ሰማያዊ ኩነቶች ተነስተን፥ ሀገራችን የገባችበትን ቀውስ ስናስበው፥ ምናልባት ከሰዎች ቁጥጥር የሆነ "የመንፈስ ኃይል" ሀገራችንን ተጠናውቷት ይሆናል" ብሎ ማሰቡ ሳይቀል አይቀርም።

እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር፥ መስከረም 3 ቀን 1967 ዓ.ም. ደርጎች ጃንሆይን (ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን) ከሥልጣን አወረዷቸው፤ በኋላም ገደሏቸው። ወታደራዊው መንግሥት ሥልጣኑን ከጨበጠ በኋላ፥ ሰማንያ ሦስት (83) ዓመት የሞላቸውን አዛውንት በቁጥጥሩ ሲያውላቸው፥ የዛን ጊዜ ንጉሣዊ አገዛዝ እንዳከተመ፥ የወደፊቷ ኢትዮጵያችንም አቅጣጫዋ ወደፊት እንጂ፥ ወደኋላ እንደማይሆን ያስታውቃል። ታዲያ፥ ጃንሆይን ከአንድ ገለልተኛ ሥፍራ ተቀምጠው በቀሪ ዘመናቸው ፈጣሪያቸው በፈቀደ እንዲኖሩ ማድረግ ሲቻል፥ እርሳቸውን በዛን ወቅት መግደል፥ ምን ትርጉም ይኖረዋል? የተፈለገውን "ሰይጣናዊ አስተሳሰብና ጭካኔ" ለመለማመድ፥ ለቀጣዩም ደም የማፍሰስ ሥራዎች ጥርጊያ መንገድ ለማስተካከል ይሆናል እንጂ።

የጃንሆይንም ስልሳ (60) ባለስልጣናት በቁጥጥር ካዋሏቸው በኋላ፥ አቅመ ቢስ ሆነው፥ ምንም ማድረግ እንደማይቻላቸው እያወቁ ገደሏቸው። እነኚህም ባለ

ሥልጣናት አብዛኛዎቹ እድሜ የጠገቡ አዛውንት ነበሩ። አብዛኛዎቹም በሃብትና በንብረት የደረጁ ከመሆናቸው ጋር፥ በዘመኑ ትምህርት ጥልቅ እውቀት ያላቸው ምሁራን እና ጠበብት ነበሩ። ከእነኝህም መካከል ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር አክሊሉ ሃብተወልድ "እኛን መግደል ኢትዮጵያን ከድህነቷ የምታወጧት ከሆነ፤ ድርጊታችሁን እንደ ታላቅ በረከት በፀጋ እንቀበላለን" ያሉ አስተዋይ መሪ ነበሩ።

ታዲያ፥ እነኚህን ሊቃውንቶች አስሮ ማቆየት እና፥ ከዛው ሥፍራ መጠነኛ ምቾት ሰጥቶ፥ ከእነርሱ ለሀገር ጠቃሚ እውቀቶቻቸውን እንዲለግሱ፤ ጥፋተኞችም ቢሆኑ፥ ጥፋታቸው በፍርድ እንዲታይ ማድረግ ሲቻል፥ ስልሳውንም በአንድ ወቅት መረሸን ምን ትርጉም ይኖረዋል? የተፈለገውን “ሰይጣናዊ አስተሳሰብና ጭካኔ” ለመለማመድ፥ ለቀጣዩም ደም የማፍሰስ ሥራዎች ጥርጊያ መንገድ ለማስተካከል ይሆናል እንጂ።

በደርግ ዘመን፥ ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ለ144 ቀናት ያህል የኢትዮጵያ ጠላይ ሚኒስቴር ሆነው ሳለ፥ “ለኢትዮጵያችን የሚያስፈልጋትን የለውጥ አይነት ተረጋግተን እንመልከት፤ ፋታ ስጡን፤...” እያሉ ሲወተውቱ እንደነበር አይረሳም።

እስቲ ከተባለው ሁሉ ያቺን ኢትዮጵያችንን እናውጣትና ወደ ኋላ እንመልከት ላንዳፍታ። ለአለማዊ ኑሮ ተስገብግበን፥ የአንድነታችን ማጠናከሪያ፥ የጥቁር ሕዝቦች መመኪያ የሆኑት ንጉሣችንን እና በዙሪያቸው የነበሩ ደጋፊዎቻቸውን ሁሉ እንዲወገዱ ምክንያት ሆንን። በምትካቸውም የተገነባው የደርጉ ጊዜ “ሶሻሊስታዊ” የስርዓት መጥፎ ጎን ቢኖረውም ጥሩ ጎን ነበረው። ጥሩ ጥሩ የሶሻል እና የፖለቲካ ለውጦችን (በፊውዶ ካፒታሊስት ስርዓት ፋንታ የሶሻሊስት ስርዓት) አሳይቶናል። በገንዘብ እና በንብረት የሚመጣ መበላለጥ በከፊልም ቢሆን ተገቷል። በዚሁም አንጻር፥ የህብረተሰቡ የእርስ በርስ ግንኙነት፥ ከበፊቱ ይልቅ የአሁኑ ሻል ያለ ይመስላል። ለምሳሌ፡- እንደ በፊቱ ለፊውዳሎች ማጎብደድ ቀርቶ፥ በእኩልነት መንፈስ እርስ በርስ መከባበርን ተመልክተናል። ግን አሁንም የፖለቲካ ሥልጣን ካላቸው ጋር ሲሆን የመፈራራት መከባበር መሆኑ ያስታውቃል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ፥ በፊውዳላዊ ስርዓት አስተሳሰብ የሚመሩ ገዢዎቹን ሲያስተዳድር (ሲያበላና ሲያጠጣ)፤ ኑሮውን ሁሉ ለነርሱ አድርጎ፥ የራሱን ኑሮ ትቶ፥ እነርሱን ብቻ ሲያስኖር ኖረ በፍርኃት። አሁንም (ያ የፊውዶ ካፒታሊስት ስርዓት ከተገረሰሰ በኋላ) የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍርኃት አልተላቀቀም። አሁንም ስነአእምሮው በነፃነት አያስብም፤ ውስጣዊ አስተሳሰቡን ካለፍርኃት መግለጽ አልቻለም። ጥንት የሚሽልሉትና የሚያቅራሩት ፊውዳሎች ነበሩ፤ አሁን በእነርሱ ፋንታ እግዚአብሔር የለም እያሉ፥ አ<u>ለ</u> የሚለውን የመናገር መብት የሚነፍጉት

ናቸው። መንግሥት ለብቻው ኃይለኛ ሆኖ ሕዝብን እንደ ራሱ ፍላጎት ያስተዳድረው ጀመር (ሰብአዊ መብትን እየረገጠ)።

ከጥንት ጀምሮ በታሪኳ፥ በሀገራችን ኢትዮጵያ ጥቂት ጀግናዎች ለራሳቸው ክብርና ለሆዳቸው ሲሉ፥ ጠብ መንጃ ይዘው ሕዝቦቿን እያስፈራሩ፥ ካለውዴታ በግዴታ እንዲገብሩላቸው አደረጓቸው። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ አየር በፍርኃት የተበከለ ሆኗል። ከነርሱ ከጀግኖቹ በስተቀር ሃሳቡን ካለፍርኃት ገልጦ የሚናገር ጠፍቷል። ጥንት በፊውዳሊዝም፥ ዛሬ ደግሞ በሶሻሊዝም፥ እንዲሁ እንዳቅራሩና እንደሸለሉ አሉ (ጥንት በአባቶቻቸው፥ አሁንም ደግሞ በልጆቻቸው)።

በኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ጭቅጭቅ የሚከረው ከጥንት ጀምሮ ሥር በሰደደው ፊውዳላዊ ጠባይ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም። የፊውዳሎች ጆሮአቸው የሚሰማው እነርሱ እራሳቸው የሚናገሩትን ብቻ ስለሆነ፥ ከግል ጥቅማቸው ውጪ ለሆነ ነገር ጆሮአቸው አይከፈትም። የሰፊውን ሕዝብ የልብ ትርታ ቀስ ብሎ የሚነግራቸውን ሰው አይሰሙትም - የድሃው ተሰሚነት የጠፋበት፤ ታዋቂ ፖለቲከኛ ብቻ የገነነባት ሀገር።

ይህች ምድር ከተፈጠረች ጀምሮ በሰዎች ላይ በደረሰ ፈተና የማይማር ሁሉ እየተቀጣ እዚህ ደረስን። ሰው እየተማረ ስህተቶችን ባይደጋግም - ጠባዩን ቢያሻሽል፥ በምድራዊነት ላይ ብቻ የሙጥኝ ከማለት ፋንታ እራሱን ትንሽ ረቀቅ ቢያደርግ፥ በሕይወቱም ውስጥ መንፈሳዊነቱን ቢያጎለምስ፥ ሰላሙን እና የጋራ ብልጽግናውን ማሻሻል እንዲህ ከባድ አይሆንም ነበር።

ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የጋራ ትግል ያስገኘው የአስተዳደር የስርዓት ለውጥ ትንሽ ወደፊት አራመደን፤ ግን ያልገባን ነገር አብሮን ስለቆየ፥ ከማጡ ውስጥ ጨርሶ መውጣት አቅቶናል። አሁንም ቢሆን፥ እግዚአብሔርን ክዶ፥ ሃይማኖትን አውግዞ፥ የሰብአዊነት ምድራዊነቱን ብቻ ይዞ የሚጓዝ መንግሥታዊ አስተዳደር ብዙ እንደማይዘልቅ ማስተዋል አቅቶናል።

ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን በመካድ ላይ በተመሠረተ ፍልስፍና ወደፊት መራመድ አልቻለችም (አትችልም)። በዚች ምድር ሰው ከሃይማኖቱ ተለይቶ መኖር አይሆንለትም። በተለይ ኢትዮጵያና ልጆቿ ከእግዚአብሔር ርቀው ብዙ መቆየት እንደማይችሉም ከትላንት፥ ከዛሬ እና ከነገም እያየን ያልገባን ጉዳይ መሆኑ ነው።

**በደርግ መንግሥት ውስጥ የታዩ አቅጣጫ ቀያሽ ወሳኝ ኩነቶች**

ከምድራዊነት ውጪ (ፖለቲካ የሌለበት) አለም ውስጥ ገብተን በመንፈሳዊነት ለኢትዮጵያ ጥሩ ጥሩውን እየተመኘንና እየጸለይን ብንኖርም፥ ከአእምሮአችን የማይጠፉ ቅሪተ ሃሳቦች ስለሚኖሩ፥ ተነግሮ በማያልቅ ብዙ ትአይንት ከተፈጸመባት ሀገራችን ውስጥ፥ ጎላ ጎላ ያለውን ትእይንት እንኳን ቢጽፉት የወደፊቱ ትውልድ ጠቃሚ ትምህርት ያገኙበት ይሆናልና፤ ጥቂቶቹን ብቻ እንመልከት።

ሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማሪያም የተባለው የሀገር መሪ ኢትዮጵያን ለ17 ዓመታት በሚያስተዳድርበት ወቅት (ከ1966 ዓ.ም. እስከ 1983 ዓ.ም.) ምን ምን እንደተሠራ መግለጽ የዚህም መጽሐፍ ዓላማ አይደለም። ነገር ግን ሰውዬው ሰይጣናዊ እንደሆነ፥ ወይንም "ከራሱ ቁጥጥር በሆነ ኃይል" እየተመራ ሀገራችንን ልክ እነኛ "የውጪ ኃይላት" ወደሚፈልጉት አቅጣጫ እንድትመራ ያደረጋት መሆኑን ለመጠቆም ያህል ጥቂቱን ብቻ እንጠቅሳለን።

ገና ሲጀመር፥ "በጎ ሃሳብ" ከአንድ አቅጣጫ ሲመነጭ፥ ያንን በጎ ሃሳብ የሚያመነጭ ሰው መግደል ሃሳቡን መግደል እየመሰለው ብዙ ደግ አሳቢዎችን የሚገድል ሰው ነው?

ትውልደ ኤርትራዊ የሆነ፥ ስለ ሀገር ጥበቃና ስለ አንድነት ከአባቱ ከጃንሆይ የተማረ ሚሊታሪ እስትራተጂስት፥ አንድ ጄነራል አማን ሚካኤል አምዶም የተባለ ኢትዮጵያዊ የኤርትራ ጥያቄ ሊመለስ የሚችልበትን መንገድ ለማስረዳት ሞክሮ ነበር።

ይህ ጄነራል ኤርትራን ከእናት አገራቸው ለመገንጠል ጫካ የገቡትን የሽምቅ ተዋጊዎች [23] (guerrilla fighters) በሰላም ድርድር ብናቀርባቸው ይሻላል በማለት፥ እንዲህ ሲል መከረ፡- "መደበኛው የኢትዮጵያ ወታደር ከሽምቅ ተዋጊዎች ጋር የሚያደረገው ጦርነት ማለቂያ አይኖረውም። ሕዝባችንን በከንቱ እናስጨርሳለን። ለሀገር እድገት የምናደርገው ጥረት ስኬት የሚኖረው ካለ ጦርነት በሰላም መኖር ስንጀምር ስለሆነ፥ ወደ ጦርነት ባንገባ ይመረጣል። ይልቁንም፥ ጦርነቱን በሰላም መቋጨት የሚቻልበትን መንገድ ብንቀይስ ነው የሚሻለው።"

ለዚህ ወታደራዊ ገለጻ ጄኔራል አማን አምዶም የተሰጠው ምላሽ በጥይት መገደል ሆነ። ወታደሮች ከቤቱ ሄደው እንዲገድሉት ተደረገ። ጄነራሉ እንደተነበየው በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራውና የትግራ ጦር (ወያኔ) እና የኤርትራ ሽምቅ ተዋጊ

---

[23] ከትልቅ የፖለቲካ-ወታደራዊ ስትራቴጂ ጋር በመተባበር ታጣቂዎች በፈጣን እርምጃዎች፥ ገባ ወጣ እያሉ፥ ከመደበኛ ወታደራዊና የፖሊስ ኃይሎች ጋር የሚዋጉበት የጦርነት ዓይነት።

ቡድኖች ከኢትዮጵያ መደበኛ ወታደሮች ጋር ባደረጉት ፍልሚያ አያሌ ሕዝቦች አልቀዋል።

የኤርትራ ኢትዮጵያ ጦርነት ከመጀመሩ በፊት አያሌ ኤርትራውያን በኢትዮጵያ ይኖሩ ነበር። ከእነርሱ መካከል፥ አብዛኛዎቹ ባይባልም፥ በኢትዮጵያዊነት መንፈስ በታነጸ አመለካከታቸው (ኢትዮጵያውያን ነን ብለው) አገራቸው ኢትዮጵያን ከልብ ሲያገለገሉ የነበሩ ኤርትራውያን በገፍ ተባረዋል።

ኤርትራዊ/ኢትዮጵያዊ ወጣቶችን ሁሉ "ሂዱ፤ ጫካ ግቡና ውጉኝ፤ ከተቻላችሁስ መንግሥታዊ ስልጣኔን ከኔ ፈልቅቃችሁ ትወስዳላችሁ፤ ከዛ በኋላ ነፃ ትወጣላችሁ....." በሚል የሰካራም ጉልበተኛ ድንፋታ ተመርታ ሀገራችን ተከፋፈለች። ኤርትራዊ በመሆናቸው ብቻ በተገደሉ ኤርትራውያን - ኢትዮጵያውያን ፋንታ፥ ያ የጥፋት መላእከተኛ ቢሞትልን ኖሮ፥ የኢትዮጵያ ሀገራችን መልኳ (የጂኦግራፊ ቅርጿ) እንደ ቀድሞው ይሆን ነበረ።

ሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማሪያም የኢሕአፓ ደጋፊዎች ናቸው ብሎ ካስገደላቸው ሌሎች ስድስቱ የደርግ አባላት መካከል፡- ለተወሰነ ጊዜ የደርግ ሊቀመንበር የነበሩ በ"ኢትዮጵያ ትቅደም" መርሆ የምናስታውሳቸው ብ/ጄነራል ተፈሪ በንቲ ይገኙበታል።

ታጋሽ እና አስተዋይ በመሆን የሚታወቅ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር ኮሎኔል አጥናፉ አባተ "እኛ የፈለግነውን ከማድረግ ይልቅ ሃይማኖተኛ ለሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሻለውን አይነት አስተዳደር ብንመክርበት ይሻላል፤ ግለሰቦችን በመግደል ለውጥ አናመጣም፤ ሥልጣን ለሕዝብ አስረክበን ወደ ካምፓችን እንመለስ፤..." ሲል እንደነበር ይታወሳል። እርሱም በጥሩ አሳቢነቱ ተገደለ።

በወቅቱ የነበሩትንም ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች (ኢጭአት፥ መኢሶን፥ ኢሕአፓ፥ ማሌሪድ፥ ኢኮፓ) አንድ ባንድ አጥፍቷቸዋል። እነርሱም የፖለቲካ ብርድልብስ ተከናንበው፥ እርስ በርሳቸውም በመጣላት ፈንታ ለኢትዮጵያችን የተሻለውን ለውጥ ለማምጣት አንድላይ ቢመክሩ ኖሮ፥ ምናልባት የኢትዮጵያችን መጻኢ እንዲህ ባልከፋ ነበር።

ይህ ገንዘብ ከባንክ እያወጣ፥ ጥይት እያመረተ ብዙ ሰዎችን ያጨራረሰ፥ ይህ አንድ ደመ መራራ ያገር መሪ (አጥፊ) ከአጠቃላይ የጥሩ አሳቢዎች ጀግኖች ወታደሮች (መኮንኖች፥ ሻለቃዎች፥ ኮለኔሎች፥ ጄኔራሎች) መካከል ለብቻው ተገንጥሎ፥ እነርሱን አስጨርሶ፥ አዛውንት፥ ምሁራን፥ ወጣቶችም ተገድለው፥ ሕዝቦች ደህይተው፥ ጦሩ ተቀንሶ፥ የሕዝቦች ቅስም ተሰብሮ፥ ሀገራችን እንድትዳከም ያደረገ፥ ይህ ወታደር ሀገራችንን ለብቻው ዲክቴተር ሆኖ ለ17 ዓመታት ገዛ። ለርሱም አልቀረለትም፤

በኤርትራ እና በትሕነግ (ወይንም ወያኔ) የሽምቅ ተዋጊዎች፥ በሲአይኤ ዲሪክተር ሃርማንኮህም እርዳታ በ1983 ዓ.ም ከስልጣን ተወገደ።

ከላይ የተጠቀሱትን እና ሌሎችም ተመሳሳይ ኩነቶች ደማምረን ስናያቸው፥ አንድ እኛ የማናውቀው “የውጭ ኃይል” ካዘጋጃቸው ሰዎች ጋር አብሮ በመሥራት፥ በጊዜው የሀገራችን መሪ መንግሥቱ ኃይለማርያምን እና ተከታዮቹን የተቆጣጠረ፤ ኢትዮጵያችንንም በተወሰነ አቅጣጫ ብቻ እንድትመራ ያደረገ ይመስላል።

## ልውጥ ሕብረተሰብ

አንድ መንግሥት ሲለቅ፥ ሌላውም በምትኩ በትረ መንግሥቱን ሲጨብጥ፥ ያንን መንግሥት ተከትሎ ሕብረተሰቡም ለወጥ እንደሚል አይተናል። የመንግሥት ስርዓት ሲለወጥ፥ የተለያዩ የሕብረተሰብ አካሎችም ልዩ ጠባዮች ማውጣታቸው የማይቀር ነውና፤ ሕብረተሰቡም እንዲሁ ልውጥውጥ ይላል። ስለ ሕብረተሰብ የሚያጠኑ ምሁራን ይህንን ጉዳይ በስፋት ይመለከቱታል።

እያንዳንዱን የሕብረተሰብ ክፍል እየለየን ስናስተውል፥ በወቅቱ የነበረው የመንግሥት ስርዓት የሀገራችንን አጠቃላይ ደህንነት ምን ያህል እንዳቃወሰው ያመላከታል። እኛም፥ ያለፈው እንዳይረሳ ብቻ ሳይሆን፥ “ለምን? ምንድነው እንዲህ የአንድ ሀገር ሕብረተሰብን የሚያገለባብጥ?” እያልን እንድናስብበት ለወደፊትም ቢሆን፥ የመንግሥት ስርዓት በተለወጠ ቁጥር ምን እንደሚያጋጥም ለማገናዘብ እንዲቀለን፥ በደርግ መንግሥት የነበረውን የሕዝቦች አኗኗርና ስሜት እንደሚከተለው ዘግበናል።

## ወታደሮች

ወታደሮች ትእዛዝ አክባሪዎች ናቸውና፤ ግደሉ ሲባሉ የሚገድሉት ከበላይ አካል የሚሰጣቸው መመሪያ ለሀገር - ለወገን የሚጠቅም መሆን አለበት በማለት ነው። የበላይ ትእዛዝ የማያከብር ወታደር፥ አለማክበሩ ሀገሩን የጎዳ ሊመስለው ይችላል። ስለዚህ፥ ያለው ምርጫ፥ ብዙ ሳያስብ እና ሳይመራመር፥ ትእዛዝ ማክበር ይሆናል።

መልካም ነው፤ በየአቅጣጫው ኢትዮጵያን የሚጠብቃት የእውነት አምላክ እንጂ ሰው አለመሆኑን የተረዱ ወታደሮች ፈጣሪያቸውን በጸሎት እየተማጸኑ ሥራቸውን በማክበር ይሠራሉ።

እንግዲህ፥ ገና ከጅምሩ፥ ጥሩ መንግሥት ስለ መምጣቱ ወታደሮችን እንደ አንድ ምልክት መቁጠር እንችላለን። ይኸውም:- ወታደሮች በሥራቸው

በሕሊናቸውና በልባቸውም ደስተኛ ሆነው ሲታዩ፥ ያ ጥሩ መንግሥት ስለ መምጣቱ ምልክት ሊሆን ይችላል።

በደርግ ዘመን የነበሩ ወታደሮችን ሁኔታ በኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ከነበሩት ወታደሮች ሁኔታ ጋር ስናወዳድር፥ በደርግ ዘመን የነበሩት እንደ ቀደሙት በሥራቸው ደስተኞች አይመስሉም። በሚሠሩት ሥራ ሁሉ፥ ትእዛዛትን እያከበሩ ወደተመደበላቸው ግዳጅ ከመሠማራታቸው በስተቀር፥ በሚሠሩት ሥራ ሁሉ፥ በሕሊናቸውና በልባቸውም ደስተኛ ሆነው አልታዩም።

በተለይም፥ የፖለቲካ ንቃት ያላቸው ወታደሮች፥ የሀገር ሰላም ጠባቂዎች እንዳልሆኑ ሁሉ፥ እንደ ሕዝብ ጠላት እየታዩ፥ ኑሮአቸው በሥጋዊም በመንፈሳዊም መንገድ የማያስደስታቸው ሆነ (የከፋውን ስርዓት አንጸባረቀ)።

## ድሆች እና ጭቁን ሠራተኞች

በሶሻሊዝም ችግረኞችና ድሆች አይኖሩም ቢባልም፤ በወታደራዊው መንግሥት በተያዘው ሶሻሊስት የአስተዳደር አይነት ግን፥ ድሆች ከድህነታቸው ሲላቀቁ አልታዩም።

የሚበሉት ያጡ ድሆች በምን አይነት መንገድ ምግብ አግኝቼ ሕይወቴ ቶሎ እንዳታልፍ ልከላከል እያሉ ይጨነቃሉ። የሚበላ ባገኙም ጊዜ ያ ጭንቀታቸው ይወገድላቸውና በሰላም መኖር ይጀምራሉ፤ በመኖራቸው ብቻ ይደሰታሉ።

ጭቁን ሠራተኞችም፥ መንገድ ላይ እየወጡ ባይለምኑም፥ እነርሱም ድሆች እና ችግረኞች ናቸው። ሆኖም በዚያ ሶሻሊስት ነኝ ባይ መንግሥት፥ ለይስሙላ በደሞዛቸው ላይ ጥቂት ብሮች ተጨምሮላቸው፥ ፖለቲካ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት እየሄዱ ርዕዮተ አለማቸውን ሶሻሊስት አድርገውታል (አስመስለውታል - መስሏቸው ነው)። ቋንቋቸውም የበሰሉ ፖለቲከኞችና ፈላስፎች እንደሚናገሩት አይነት ሆኗል።

የፖለቲካውን ትምህርት ለጨረሱትና ለከደሩት (የፖለቲካ ካድሬ ለሆኑት) “ከጸረ አብዮተኞች” እራሳቸውን የሚከላከሉበት አንዳንድ ሽጉጥ ተሰጥቷቸዋል። በሄዱበት ሁሉ ደረታቸውን ነፍተው፥ ጎርደድ - ጎርደድ እያሉ፥ እንደልባቸው “አብዮታዊ ስድብ” ይሳደባሉ። ከፈለጉም ያስራሉ፤ ያሳስራሉ።

ተንኮለኛ ሰው አውቆ ያጠፋል፤ የሥልጣን ጥም ያለበትም ለራሱ ክብርና ጥቅም ሲል የሀገሩንና የወገኑን ጥቅም ይለውጣል። ምንም ቢያደርጉ ምን፥ እነኛ ጭቁን ሠራተኞች የተባሉት በኑሮአቸው፥ እነርሱም ድሆች ከሚባሉት ጎን ሲያዝኑ እንጂ፥ አልፎላቸው ሲደሰቱ አይታዩም።

**ንኡስ ከበርቴዎች**

የንኡስ ከበርቴዎች አኗኗር መጠነኛ ስለሆነ፥ በዚህ አነስተኛ የሆነ የሕብረተሰብ ክፍል የተመደቡ ለኑሮ በቂ የሆነውን ያገኛሉ ማለት ይቻላል።

ቤት የማይሠራ፥ መኪና የማይገዛ ገንዘብ፥ በመጠጥ ቤት ሲበተን ነው ብዛቱ በይፋ የሚታወቅ። ንኡስ ከበርቴዎች በየቡና ቤቱ ይሰገሰጋሉ፤ ጣዕም ያለው ሙዚቃ ይሰማሉ። ሙዚቃውም ለትካዜ ያመቻል። ለአንድ ንኡስ ከበርቴ የሚታሰቡት ሁሉ በርከትከት ይላሉ። አንድ ንኡስ ከበርቴ ለብቻ ቁጭ ብሎ ሙዚቃ በማዳመጥ እና በሃሳብ በመመሰጥ፥ ሁሉንም (ከፉውንም ደጉንም) አንድ ላይ ሰብሰብ አድርጎ፥ የስሜቶችን ሁሉ ግለት ቀዘቅዝ ያደርግበታል።

አንዳንድ ጊዜ፥ አስደስቶ የሚያስፈነድቅ ዘፈን ተፈላጊነት ስለማይኖረው፥ ዝም ብለህ ሙዚቃውን አዳምጥ ተብሎ የተገደደ ይመስል፥ ንኡስ ከበርቴው የሞተ ዘመዶቹንና ጓዶቹን ሁሉ እያሰበ፥ ለሚያዳምጠው ሙዚቃ ከሚስማማ ሃሳባዊ ትእይንት ውስጥ ራሱ ትያትረኛ ሆኖ ይገባል። የኦሮምኛ ወይንም የምንጃር ዘፈን ሲሰማ፥ ድንገት ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ሰውነትን ማፍታታት የመሰለ ውስጣዊ ዳንኪራ ያከናውናል። ግን ወዲያው፥ ለዳንኪራና ለደስታ አለመፈጠሩን ሲያስታውስ፥ ቢራውን (ወይንም አረቄውን) ያጫልጣል፤ ከዚያም፥ ትዝታዎችን ሁሉ በመደምሰስ ታዋቂ ወደ ሆነው ስካር ውስጥ ይገባል፤ ገንዘቡን ከፍሎ ይወጣና፥ እየተወለጋገደ የሰአት እላፊ ከመድረሱ በፊት ወደ ቤቱ ይደርሳል፤ ልክ ከምሽቱ ስድስት ሰዓት ሲሆን የቤቱን በር በጁ ይነካል።

ዝም ያሉትን ምሁራን ሁሉ ከአጠቃላይ ንኡስ ከበርቴዎች ጋር ብንደምራቸውም፥ ከእነርሱ መሃል፥ ጥሩ ገቢ የሚኖራቸው የተማሩቱ (ባለዲግሪዎች) ናቸው። ከመካከላቸውም፥ ለመንግሥት ቀረብ ያሉቱና ተናጋሪዎቹ፥ በዛው መጠን ገቢያቸውም ከፍ ይላል።

ታዲያ፥ መስሎ ለማደር ካልሆነ በስተቀር፥ አምባ ገነን የሆነውን ወታደራዊ መንግሥት በመቃወም ለመናገር የፈለገ፥ ሃሳባዊ ሚዛናዊነቱን ለራሱ አድርጎ ዝም ማለት ነው ያለበት። ቢናገርም ተሰሚነት እንደማያገኝ ስለሚያውቅ፥ የልቡን ቅዋሜ ከማሰማት ይልቅ፥ ዝምተኛነቱን መርጧል። እንዳው ዝምታም የተቃዋሚ ምሁራን መገለጪያ የሆነበት ዘመን።

**<u>አጽናኞች/ሰባኪያን</u>**

*አጽናኝ ሰባኪያንም ለሃዘንተኞችና ጭንቀት ውስጥ ለገቡ ሁሉ መንፈሳዊ እድሳትን የሚያመጡ ሆነዋል። እንደ ንኡስ ከበርቴዎች ለመዝናኛ የሚሆን ገንዘብ የሌለው ተረፈ ኢሕአፓ (ወይንም ሌላው) በሳምንት አንድ ቀን ሰንበትን ጠብቆ ከቤተ ክርስቲያን ሲሄድ ብቻ ነው ደስታው።*

*ወቅቱ ብዙ ወጣቶች ከቤተ ክርስቲያን መሄድ የጀመሩበት ወቅት ነበረ። አንዳንድ የፕሮቴስታንት መሰባሰቢያ ቸርቾች (ቤተ ክርስቲያናት) የልቅሶ ቤት ይመስላሉ። ሰውም በርከት ብሎ የሚመጣው ከእንደዚህ ያለው መላቀሻ ሥፍራ ነው። ወቅቱ ከቤታቸው ለማዘን እና ለማልቀስ የተከለከሉ ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን እየመጡ የሚያለቅሱበት፤ ጴንጤቆስጤዎችም በመንፈሳዊ መዝሙር እና በስብከት የሰውን መንፈስ የማረኩበት ወቅት ነበር።*

*ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚሰሙት በልባቸው ያለውን ነው፤ እውነት ደግሞ ከወቅታዊ ኩነቶች ጋር ተደርቦ በስሜት ሲነገር፥ አድማጮቹም በስሜት ሲሰሙት ሊያስለቅስ ይችላል። ሰባኪያንም ደግመውና ደጋግመው፥ "በቃ! እስከመቼ?... ከሚከብደው ወደሚቀለው አለም እንሻገር፥ ወደ እግዚአብሔር እንሂድና በእግዚአብሔር መንፈስ እንጽናና...." እያሉ ይሰብካሉ (ያስተምራሉ)።*[24]

---

[24] *"እናንተ ደካሞች፥ ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደኔ ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤....." ማቴ. 11፡28፥ 29*

***ተማሪዎች***

*ተማሪዎችን እንደ ሀገር ገንቢዎች፥ የወደፊት ሥልጣኔ ምልክቶች እናያቸዋለን። ሆኖም፥ በወታደራዊው ስርዓት ውስጥ ተማሪዎች ብሩህ ተስፋ አይታያቸውም። ትምህርት ቤት በብዛት ተከፍቷል፤ ግን የተማሪዎቹ የወደፊት ተስፋ ተጭለምልሟል።*

*ከድሮ ከኃይለ ሥላሴ ዘመን ወዲህ፥ በኢትዮጵያ የተማሪዎች የወደፊት ተስፋ እየቀነሰ መጥቷል። ቤተሰብ ሂዱና ተማሩ ብሎ ትእዛዝ ከማስተላለፍ በስተቀር፥ የሚማሩትን ሁሉ ለመከታተል አይችልም፤ መንግሥትም የወደፊት ተስፋቸውን እያዩ እንዲማሩ የሚያበቃ የሥራ መስክ አይከፍትላቸውም።*

*ይህ ዘመናዊ ትምህርት ለጠቅላላ የሰው ልጅ የተሰጠ ስለሆነ፥ ሁሉም ይማረው ዘንድ ግዴታ ነው። የትምህርት አላማውና ተግባሩም፥ ሕብረተሰብን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ከማራመድ ጎን ለጎን፥ በጥሩ መንፈሳዊ ፍልስፍና ማጎልመስም መሆን አለበት።*

*ከመኖር ጋር አለመኖር እንዳለ ሁሉ፥ ከማወቅ ጋር አለማወቅም አብሮ ያድጋል። በዚህም ምክንያት፥ በሕብረተስብ ውስጥ ከፍተኛ አለመግባባት እየተፈጠረ አብሮ መሥራት ስለሚያስቸግር፥ አለማወቅን (በልማድ ያደጉ ኋላ ቀር አስተሳሰቦችና ድንቁርናዎች ሁሉ) ከቤተሰብ፥ ከሕብረተሰብና ከሀገር ውስጥ፥ እጅግ ጥንቃቄ በተሞላው መንገድ ማስወገድ ይገባል።*

*ምድራዊ ትምህርትን ብቻ ይዞ መጓዝ ምድራዊ - ሰማያዊ የሆነውን ሰው በግድ ምድራዊ ብቻ እንዲሆን መገፋፋት ይሆናል። የሰው ልጅ ሥጋዊ እና መንፈሳዊ ህልውናው ካልተጠበቀለት በኑሮው ሙሉ ደስተኛ ሊሆን አይችልም። እኛም ምድራዊ እና ሰማያዊ ሆነን በመፈጠራችን ምድራዊ ትምህርት ብቻ አያረካንም፤ አይበቃንም።*

*እንደ ቀድሞው ቢሆን ኖሮ፥ በሶሻሊስት ስርዓት ውስጥ የማይሰጠው፥ የተናቀው መንፈሳዊ የሃይማኖት ወይም የግብረገብነት ትምህርት ነበር የኢትዮጵያኖችን እድገት የተሟላ የሚያደርገው።*

*እንደ ጥንቱ ቢሆን ኖሮ፥ ተማሪ ሲባል በኑሮ ተቸግሮም ቢሆን፥ በትጋት አጥንቶ፥ ፈጣሪውን ዘወትር በጸሎት መማጸን እና፥ ሕዝብን ማገልገል ነበር የመልካም ዜጋ መገለጫ። እንዲህ አይነቱን የትምህርት ስርዓት የመከተል ባህል እየጠፋ ስለሄደ፥ ለወደፊት፥ የኢትዮጵያችን እድገት በምድራዊ ምልከታ ብቻ የሚወሰን እንዳይሆን ያሰጋል።*

*ጤናማ ሕብረተሰብ የሚገነባው፥ የዜጋዎችን ሞራል ከእውቀት እና ከእውነት ጋር በማያያዝ፥ የመንፈሳዊ እውቀትንም ከዘመናዊው ትምህርት ጋር አብሮ በማስኬድ*

ነው እንጂ፥ ምድራዊ ትምህርት ብቻውን እራስን ወዳድ ከማድረጉም በላይ፥ አሁን እኛ መጥፎ (ሰይጣናዊ) የምንለውን አኗኗር፥ የወደፊቱ ትውልድ እንደ ጥሩ አድርጎ እንዲቀበለው፥ ቅድመ ሁኔታዎችን እንደ ማስተካከል ሊቆጠር ይችላል።

በዚህ በአካላዊነት ከሚታየን የዘመኑ “ሥልጣኔ” ሌላ “መንፈሳዊ ሥልጣኔ” በግልጽ ከማይታይበት አለም ውስጥ ነው ያለነው። በመንፈሳዊነት ብናድግ ኖሮ፥ ይህ “ሥልጣኔ” የምንለው ቃል ምናልባት “ኋላ ቀርነት” ከሚል የተሻለ ስም ባላገኘ ነበር። ይህንን አባባል ትንሽ ዞር አድርገን ብንመለከተው፥ ሰው ከቁመናው ጋር ትልቅ ጭንቅላት ስላለው ለዚህ ለዘመኑ “ሥልጣኔ” በቃ። ግን ይህን “ሥልጣኔ” ያገኘው በእንስሳዊ ጠባዩ ነው፥ ወይንስ በመልአካዊ ጠባዩ?

ሰው እንደ እንስሳ ሆኖ በአካላዊነቱ ብቻ የኖረበት ዘመን አልነበረም። በሥጋዊ አካሉ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ ስለተጨመረበት ዘመናዊ ሰው አላደረገውም። ሥጋዊ የሆነው አካሉ ለምድራዊነቱ ይስማማው ዘንድ፥ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ችሎታው ሁሉን ሲሞካክር ነው ከዚህ ደረጃ የደረሰው።

የሰው ልጅ ለወደፊት ሊደርስ የሚችልበትን እጅግ ከፍተኛ የተባለ ምድራዊ ሥልጣኔ እና አኗኗር ከሂደቱ ማወቅ ይቻላል ካሰብንበት። ስለዚህ፥ የዘመኑ “ሥልጣኔ” ሰውን ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር አርቆት እንደሆነ በማገናዘብ፥ ኑሮአችንን ከአሁኑ በቀናው መንፈሳዊ መንገድ ካልመራን በስተቀር፥ መጪው ጊዜ መጥፎ ሊሆንብን ይችላል።

**<u>የገበሬዎችና የከብት አርቢዎች አኑኗር</u>**

ገበሬዎችና ከብት አርቢዎች የምግብ አቅርቦት መለኪያዎች ሆነው ሳለ፥ በለውጡ መደሰታቸውን/አለመደሰታቸውን ከአኗኗራቸው መመልከት ይቻላል። ድርቅ ሲሆን በቅድሚያ የሚጠቁ የምንመገበውን ሁሉ የሚያመረቱ ገበሬዎችና ከብት አርቢዎች (በተለይም የስምጥ ሸለቆ ከብት አርቢዎች) ናቸው። እነርሱ ከተፈጥሮ እንጂ ከሰው ብዙ የማይጠብቁ ስለሆኑ፥ ሰማይ ሰማዩን እያዩ፥ ከየትም ከየትም ነፋስ ነፍሶ፥ ውሃ አዘሉን ደመና እንዳያመጣላቸውና እንዲዘንብላቸው እግዚአብሔርን ይለምናሉ።

የአፋርና የኢሳ ብሔረሰቦች እርስ በርሳቸውና በአቅራቢያቸው ከሚገኙ ደገኞች ጋር በሳር ግጦሽ ምክንያት ዘወትር ይጣላሉ። ሰውም ሆነ እንስሳ ሆዱን ለመሙላት ሲል ማድረግ ያለበትን ሁሉ ያደርጋልና፤ በጋ ሲሆን የበረሃው ሳር ተቃጥሎ ሲያልቅ፥ ቆለኞች ወደ ደጋው ሲጠጉ፥ ክረምት ሲሆንና ቆላው ሳር ሲያበቅል፥ ደገኞችም ወደአቅራቢያቸው የስምጥ ሸለቆ ከብቶቻቸውን ሲያሰማሩ፥ ግጭት ይጀመራል።

ይህ ከተፈጥሮ ሁኔታ ጋር የተያያዘ የሚመስል ግጭት ከጥንት ጀምሮ የቀጠለ ነው። አንድ መንግሥት ቢሄድ፥ ሌላም ቢከተል፥ ለስምጥ ሸለቆ ከብት አርቢዎች ያሰበላቸው ያለ አይመስልም። ከደጋው የኢትዮጵያ ክፍል፥ እስከ ቆላው፥ ቁጥቋጦ እንኳን ከማያበቅል፥ በንዳድ ያለቀው ሕይወት እንዴት ይረሳል - እንዴት ይረሳል።

“ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ለሕዝብ ማሰብ ያለበት መንግሥት አይደለም እንዴ?” በማለት፥ ባላገሮች፥ ገበሬዎችና የስምጥ ሸለቆ ከብት አርቢዎች፥ በተደጋጋሚ ከሚያጋጥማቸው ድርቅ ለመላቀቅ፥ መንግሥት አንድ መላ እንዲፈጥርላቸው ይጠይቃሉ። ወደ ከተማ ገብተው፥ የቀን ሠራተኛም በመሆን እንዲሠማሩ፥ አማራጭ እንኳን ቢጠፋ፥ መንግሥት ጊዜአዊ ማስታገሺያ ምግብ እና መጠለያ እንዲሰጣቸው ይጠይቃሉ። ለሁሉም መልስ ይጠፋል።

ተፈጥሮአዊ ድርቅን የመከላከል ብቃት ማጣት - አርቆ የአለማሰብ - የኋላ ቀርነት - የደካማ መንግሥት ምልክት እንደሆነ አድርገን መውሰድ እንችላለን። ሆኖም፥ ትላንት፥ ዛሬ፥ እና ለወደፊትም የማይቀረውን ይህንን እና መሰል ተፈጥሮአዊ አደጋ ተከላክሎ፥ የሰውን እና የእንስሳቱን ነፍስ የማዳን ሥራ ከሁላችንም የሚጠበቅ ዕዳ መሆኑን መገንዘብ ግድ ይላል።

በአፋር ሸለቆ ውስጥ፥ ሃብት ንብረት የተባሉ ከብቶች፥ ፍየሎች፥ በጎችና ግመሎች፥ የቆላው ሀገር ዘመዶች፥ ሳር ቅጠል ሲፈልጉ የደከሙ መጋቢዎች፥ የት ገቡ የኛ ሰዎች?

ከአስር ከብት ጋር አንድ ሰው ተዳብሎ ሲሞት፥ ክንብል - ክንብል በያለበት፤ ነጫጩ ብቅ ብቅ ሲል፥ በዚህም በዚያም አጥንት፥ ገና የአለም መጨረሺያ ሳይሆን፥ የፍጥረታት እልቂት።

በሱማሌ፥ በኢሳና በአፋር በረሃ፥ በቆላማው ሥፍራ፥ ተፈጥሮአዊ አየር ሲቃወስ፥ ሰውና እንስሳ ሲረግፍ በየተራ፥ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ሲያስባት፥ ሲራራልን፣ ሁሉም በበጎ ይለወጣል፥ አንድነታችንን ካስመሰከርን።

ከመንግሥት መሪዎች የሚያገኙት ምላሽ ዝምታ ብቻ ሲሆን፤ ሀገራችንን በተደጋጋሚ ድርቅ ሲያጠቃት፥ በድርቁም ምክንያት የሚቾች ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ፥ ከአንድ ቤት ውስጥ እናት እና አባት ሞተው አንድ ታዳጊ ሕጻን ብቻ ሲተርፍ፥ የዚህን ለወሬ ነጋሪ የተረፈ ታዳጊ ሕጻን እሮሮ፥ በቴሌቪዥን አይተን የሰማነው ይህንን ይመስላል፡-

“አሁን ካለ አባትና እናት፥ ካለ ወንድምና እህት፥ ካለ አጎትና ካለ አክስት፥ ብቻዬን ቀርቼ የምታዩኝ፥ እኔም ባለ ብዙ ዘመድ ነበርኩኝ። እናትና አባቴ ከራሳቸው እየቀነሱ ሲመግቡኝ፥ እነርሱ በየቀኑ እየሞቱ፥ የእኔን ሕይወት አራዘሙልኝ።

መሬት ሲታረስ፥ ተቆጥቦ የተቀመጠ እህል፥ ጥራጥሬው ሁሉ፥ አንዱም ነፍስ ዘርቶ ላይበቅል፥ ሲበተን፥ ሲዘራ፥ በተስፋ ወደ መሬት ሲጣል፥ ድርቅ ሲሆን፥ ዝናብ ሲጠፋ - ክረምትና በጋ ሲመሳሰል፥ አምናና ካቻምና አንዱ ከሌላው የማይሻል።

አየሩ ሲደርቅ፥ የጸሐይ ሙቀት ሲያቃጥል፤ ምን ይደረግ? ምን ይደረግ፥ ምድሪቷ ምግብ አልሰጥ ስትል?

ሳሩ ጎመን ነው ተብሎ እንዳይበላ፥ እርሱም ጠፍቷል፥ ሁሉ ነገር አመድማ፥ ቡናማ መስሎ ይታያል፥ ምን ይደረግ? ምን ይደረግ፥ ምድሪቷ ምግብ አልሰጥ ስትል?”

ያለፈው አለፈ። መጪውም ሳይዘገይ ይመጣል። ለዚህ በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ በተደጋጋሚ ለሚከሰት ድርቅ ማቃለያ ዘዴዎች እንዴት ይጠፋል? የወደፊቷን ኢትዮጵያችንን ለመታደግ ሁሉን ነገር በፍቅርና በአንድነት አስበን፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክም ተምረን፥ ስለ ዘላቂ መፍትሄም ቢታሰብበት መልካም ነው።

*“ከአራት ሺህ ዓመታት በፊት ፈርኦን በጥሩ ቀን እህል እያጠራቀመ ቆይቶ፥ ድርቅ ሲሆን ሕዝቦቹን ከረሃብ አዳናቸው።” ዘፍ. 4፡ 28-36*

**<u>ስደት</u>**

እሾክና አሜከላ በበዛበት ምድራችን የምንመላለስ እኛ፥ ስለ ኢትዮጵያችን ማሰቡን አላቋረጥንም። ለምን ነበረ በገዛ ሀገራችን ተደላድለን መኖር ያቃተን? ለምንስ ተሰደን፥ ከባእድ ሀገር ለመኖር ተገደድን? ከሰው ለተፈጠረ የማይገባ፥ ብዙ ድርጊት የተፈጸመባት ሀገር ውስጥ ያደግን እኔና ወገኖቼ (ያሉትም የሄዱትም) ኢትዮጵያን (ኤርትራንም ጨምሮ) አላጠፋናትም፤ ኢትዮጵያ አሁን እንደሚያዩአት ሳይሆን፥ ከዘመን ዘመን ተሸጋግራ፥ ልዩ ሆና በክብር ተቀምጣለች ከአእምሮአችን።

የአንድ ሀገር ኗሪ፥ ተፈጥሮአዊ ባልሆነ ምክንያት ሀገሩን ለቆ ሲሰደድ፥ ብዙውን ጊዜ ፖለቲካዊ ነው ምክንያቱ። የሚሰደድ የከፋው፥ የማይሰደድም ያልከፋው ነው ማለት ግን ልክ አይደለም፤ እየከፋቸውም ሀገር የማይለቁ ብዙዎቹ ናቸውና። ሆኖም፥ በአንድ መንግሥታዊ አስተዳደር ውስጥ በየጊዜው የሚሰደደው የሕዝብ ቁጥር የሚያመለክተው በመንግሥት እና በሕዝብ መካከል ያለውን ቅራኔ ነው።

የደርግን አገዛዝ አጥብቀን የምንቃወም፥ የተገኙ አጋጣሚዎችን በመጠቀም፥ በተለያዩ ጊዜአት፥ ሀገር ለቀን ሄደናል (ተሰደናል)። ነፍሳችንን ለማትረፍ ስንል ተሰደድን እንጂ፥ በእኛና በሀገራችን በሕዝባችንም መካከል ያለውን መንፈሳዊ የፍቅር ሰንሰለት የሚበጥስ፥ ምንም አይነት ምድራዊ ኃይል አይኖርም።

እህ! ተመልሶ መግባቱንም እንዳናስበው ቢያደርጉንም፥ ኢትዮጵያ አሁን እንደሚያዩአት ሳይሆን፥ ከዘመን ዘመን ተሸጋግራ፥ ልዩ ሆና በክብር ተቀምጣለች ከአእምሮአችን። ጊዜና ዘመን እንደሚለዋወጡ ሁሉ፥ በኢትዮጵያችንም ጥሩው ዘመን ይመጣል፤ ትጉሃን ሰዎችንም የሚያስኖሩ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ።

*“ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፥ እንዲሁ እግዚአብሔር ምሕረቱን በሚፈሩት ላይ አጸና።” መዝ. 102፡11*

ስደትን ተሰደው፥

ስደትን ያስቀሩ፥

ተወዳጁ ንጉሥ፥

ሀገር ያስከበሩ፤

ተፈሪ መኮንን፥

እዛው ተቀበሩ።

ከርሳቸው በኋላ፥

አመል እንደ አወጡ፥

እንደ ታላላቅ ወንዞች፥
ሀገር መልኳን አጣች።
የሕዝብ ጎርፍ ሆነ፤
ከፍታውን አጥቶ፥
ወደ ታች ወረደ።

አገሩን ለቆ መሰደድን ማን መረጠው?
እጣ ክፍላችን ይኸው ሆኖ ነው እንጂ የተገኘው፤
በሄድንበት ሁሉ ሬፉጂ መባላችን - እንግዳ ሰው።

ያገራችንን - የመሬቱን - ያፈሩን፥ የድንጋዩን፥ የሳር የቅጠሉን፥
የሜካውን፥ የሸለቆውን፥ የሜዳውን የተራራውን፥
የእርሻውን፥ የበረሃውን፥ የዱሩን፥ የቀዬውን፥
የከተማውን፥ የመንደሩን፥ ከዳር እስከዳር ሁሉን፤
አንረሳም ሁሉን፥ ትዝታዋን የሀገራችንን።

እኛስ በኢትዮጵያችን ተስፋ አንቆርጥም፥
ለውጥ ቶሎ ቢመጣ፥ ባይመጣም፥
ጊዜው ቢያጥር፥ ቢረዝምም፥
ኢትዮጵያችንስ አትጠፋም ከአእምሮአችን፤
ሥጋችን ከባዕድ ሀገር፥ ህልማችን ከሕዝባችን።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## በደርግ ምትክ ኢሕአዴግ

የኢትዮጵያችን ነገር እሳት ላይ ተጥዶ አልበስል ብሎ እንደቆየ ጎመን ሆኖ ቆይቷልና፤ “በጊዜ ውስጥ ምን ተፈጸመ ባገራችን?” ብለን ስንጠይቅ፥ ብዙው የሚያሳዝን፥ የሚያስለቅስ ቢሆንም፥ እኛ የኢትዮጵያችንን ሂደቷን - “ከዚህ ቀጥሎስ ምን ተፈጠረ?” እያልን በመጠየቅ፥ አንዳንድ አንኳር አንኳር ጉዳዮችን በማስታወሻያችን ዘግበናል።

ከደርግ በፊት (በንጉሡ በኃይለ ሥላሴ ዘመን) የነበረውን የፊውዶ ካፒታሊስት ስርዓት እንደነገሩ “በሶሻሊስት ስርዓት” የለወጠ፥ ያ የወታደር አገዛዝ (ደርግ) በኢትዮጵያችን ትቶ የሄደውን ጠባሳ አይተነዋል። የደርግ አብዮት፥ በ17 ዓመታት የግዛት ዘመኑ አብቅቶለት፥ በሌላ ተተክቷል። ደርግን ከሥልጣኑ ፈንቅሎ የተካው ኢሕአዴግ (ኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር - የቀድሞው ትሕነግ - ሕወሃት፥ ወይንም ወያኔ እየተባለም ይጠራል - ከወደሰሜን የመጣ፥ በብዛት የትግራይ ተወላጆች ያሉበት) ነው። ከደርግ የተሻለ ሳይሆን አይቀርም በማለት ልናይለት ጓጉተናል።

ኢሕአዴግ የደርግን መንግሥት በመደምሰስ፥ ኢትዮጵያችንን በክልል በመከፋፈል፥ ልዩነቶችን እና ጥላቻን የሚቀሰቅስ ሕገ መንግሥትን በማጽደቅ፥ በዘር የተዋቀረ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ መንግሥትን የመሠረተ በመሆኑ ይታወቃል።

እነሆ! ከደርግ የሰባት ዓመታት የግዛት ዘመን በኋላ፥ ከወያኔ አስራ አንድ የግዛት ዘመን በኋላ (በድምሩ ከ18 ዓመታት በኋላ - በ1998 ዓ.ም. እንደ አውሮፓ አቆጣጠር)፥ ከቤተሰቤ ጋር ወደ ኢትዮጵያ፥ ከስደት አለም ተመልሼ መጣሁ፤ የሳቅና የጨዋታ፥ የሃዘንም ሆነ የደስታ፥ የተለያዩ ትዝታዎችን ከሚያስታውሰን ሥፍራ።

ከቦሌ አይሮፕላን ማረፊያ ጀምሮ መሃል ከተማ እስከንገባ ድረስ፥ ሳርና ቅጠሉ፥ አፈርና ድንጋዩ፥ ሁሉም ከፈረንጅ አገሩ ለየት ያሉ ሆኑብኝ። በደራረቁ ሳሮቹ መካከል ደረቅ አፈር፥ አልፎ አልፎም የለመለሙ ሳሮች፥ ልምላሜና ድርቀት እዛው በዛው፤ በልምላሜና በድርቀት መካከል ትላልቅና ትናንሽ ድንጋዮች፥ እንዲሁም ጠጠሮች እና አፈሮች።

አዎ! እኛም ለብዙ ዓመታት በውጪ ሀገር ቆይተን ወደ ኢትዮጵያችን ብንመለስ፥ አንድም ዘመዶቻችንን ለመጠየቅ፥ እትብታችን የተቀበረበትንም ሥፍራ ጎብኝተን፥ በልጅነታችን ስንጫወት፥ ስንቦርቅ ያደግንበትንም ሥፍራ በማስታወስ፥ በሃሳብ ትዝታ ውዝዋዜ ደስ እንዲለን ነበር። ግን በዛቺው በአዲስ አበባ ተወስነን ቀረን እንጂ፥ ከቦታ ቦታ መዘዋወር እና ሀገራችን ያለችበትን ሁኔታ ለመመልከት እንኳን እድል አላገኘንም።

ስደተኞች (ዲያስፖራ) በአለም ሥፍራዎች ሁሉ፥ በራሳቸው ላይ ሃሳብ አብዝተው፥ እንቅልፍ አጥተው፥ "ሀገሬ! ሀገሬ!" እያሉ፥ ከእናት አባቱ የተለየ ልጅ እንደሚናፍቅ፥ የትውልድ ሥፍራውን እንኳን እንዳይጎበኝ ሲታገድ፥ "ወገኖች ነጽሩ አሾልካችሁ - አሉታዊነትን ትታችሁ፤ ያህቻት፤ ይህቺውና፤ ያቺ ቆንጆ ሀገር - አገራችሁ፤ መደሰቺያ፥ መቦረቂያ ሥፍራችሁ፤ ስትኖሩበት ሞቅ ይላል ቤታችሁ፤ ስትመጡ ተመልሳችሁ..." እየተባልን ቆይተናል።

እንዳው ሁሉም - ሳሩም ቅጠሉም፥ አፈር ድንጋዩም አብረው ሆነው፥ "ከጥንት ጀምሮ ያንተነትህ መሠረቱ እኛ ነን እኮ! ከኛ በቅለህ ሌላውን መሆን ላትችል፥ ለምን ጥለኸን ሄድክ? ....በቃ ይቅር፤ ሁሉም ይቅር፤ ግን እናንተ ደህና ናችሁ?" እያሉ ሰውን በናፍቆት ሰቀቀን ውስጥ ይከታሉ፤ ብዙ ሺህ ዓመታት ወደ ኋላ እየጎተቱ።

እኛስ ወዳገራችን ተመልሰን የመጣነው፥ ከዘመዶቻችን ተቀላቅለን፥ ላጭር ጊዜም ቢሆን ኑሮን ከወገኖቻችን ተቃምሰን፥ ስለ ሀገራችንም ክፉውንም ደጉንም አይተን ለመመለስ ነበር። ገና ከአይሮፕላን ስንወርድና ያገራችንን አየር ስንተነፍስ፥ ሰው ከገዛ አገሩ ለቆ መውጣት እንደሌለበት፤ ስደት ማለት እራስን በትንሽ በትንሹ እየቆረሱ ለሌላው መስጠት እንደሆነ ነበር የተሰማን ስሜት።

መናኸሪያችን አዲስ አበባ የሁላችን መገናኚያ፥ የኋላ ዘመን መሰባሰቢያ፥ መረካከቢያም ስለሆነች፥ ይህ የዛሬው አመጣጣችን የመጨረሺያ አለመሆኑን እናውቃለን። አዲስ አበባ ስንገባ የተሰማን የደጋግ መንፈሶች ስሜት፥ ኢትዮጵያውያን (ያሉትም፥ የሞቱትም) ከሩቅ - ከዳር ሀገር ተጠራርተው አብረው የሚኖሩበት ዘመን መቃረቡን ያበስራል።

አዎ! ሰዎች ጮኸውባታልና፥ ደጋግ መንፈሶችም በዝተውላታልና፥ ዛሬም ቢሆን ነገ፥ እንደ ስሟ የምትሆንልን፤ መጨረሺያው ሲቃረብ፥ ኑ! ግቡልኝ! የምትል፥ መልካም አስተናጋጅ - ቆንጆ ሞቃት ቤት፥ እርሷ ናት አዲስ አበባ ብለን የምንጠራት።

አዲስ አበባችን ደስ ብሏት ስትዋብ፥ ከፍቷትም ስታዝን፥ ከኢትዮጵያ - ከመሃል ሀገር - ከአፍሪካ፥ ከአለም ዙሪያም - ሰውን በሰውነቱ አክብራ የምትቀበል፥ ለሰው ልጅ በእጬነት የተቀመጠች፥ ትላንት የምናውቃት፥ ዛሬን ያየናት፥ የወደፊቷን

ስንመለከታት፥ በህንጻዎቿና በመንገዶቿ ማማር ሳይሆን፥ በደጋግ ሕዝቦቿ፥ ሳይበላ የሚጠገብባት ሥፍራ የምትመስል የፍቅር ከተማ፥ እርሷው ናት አዲስ አበባችን።

ከከተማዪቱ ማማር በስተጀርባ፥ የድሆች መብዛት፥ የሥራ ፈቶችም መበራከት ያሳዝናል። ሆድ ዛሬ ጦሙን ቢያድር፥ ነገም ከነገወዲያም እንዳይደጋገምበት የቀን ተቀን ኑሮአቸውን ለሚሟላት የሚራራጡ ብዙዎች ናቸው።

እንዲሁም፥ ከጥቂት ጊዜ የወለዳቸው ቱጃሮች በስተቀር፥ ከፍና ዝቅ ያለ ኑሮን የቀመሱ፥ ቢሯሯጡም አልሆን ብሏቸው ተስፋ የቆረጡ አሉ፤ ብዙ ስለደከሙ - ከድህነት ጋር ብዙ ስለቆዩ - ምድራዊ ሕይወት ስልች...ት ብሏቸው ለተመለከታቸው በግድ ኑሩ የተባሉ ይመስላሉ።

የተቸገረውም ያልተቸገረውም፥ ከመላው ኢትዮጵያ ወደ አዲስ አበባ ገብቶ መኖርን ይፈልጋል። የአዲስ አበባ ኗሪዎችን አኑኗር ስናይ፥ ስለ መላው ኢትዮጵያም ያሳስበናል።

ከላይ በዛፎች ላይ ተንጠልጥለው ቅጠሎቹ ምንም አይሉም፤ እንዳው መታዘብ፥ ቅሬታና ሃዘን። ከነፍስ አልባ ግኡዛን እስከ ባለ ነፍስ እጽዋት እና እንስሶች፥ ሁሉም በበኩላቸው ስለ ኢትዮጵያችን ያልሰማነውን (በምድራችን ላይ ስለሚታየው ከፍና ዝቅ ሁሉ - ቅሬታቸውን፥ ብሶታቸውን....) ሁሉን የሚነግሩን ይመስለናል።

ኢትዮጵያ - ኢትዮጵያችን ብዬ ልጥራሽ፤
የተስፋ ምድር - የሁላችን ስለሆንሽ።
እኛስ ቢመረን ተለይተንሽ፥ ብትናፍቂን መጣንልሽ፤
አንቺም እንደ ወትሮው ሞቃት ነው መንፈስሽ፤
ግን ምነው የከፋሽ መሰልሽ? ምነው ጎስቆል አለ ሰውነትሽ?
ችላ ተባልሽን? ወይንስ ተጠላሽ?

አንቺ ከፍጥረትሽ በመንፈስ የተሞላሽ ሆነሽ፥
የገነት ውሃዎች ሲፈሱብሽ፥
የበኩር ልጅ አብቅለሽ፥
የዘር ግንድ ከጉያሽ፥
ልጆችሽንም በአለም ዙሪያ ዘርተሽ፥
ሁሉም በያሉበት ሲያፈቅሩሽ፥
ማነው የሰደበሽ? እንዳትኩራሪ በታሪክሽ፥

የበሽታ፥ የድህነት መናኸሪያ ብሎ የጠራሽ።

ኢትዮጵያችን፥ ዛሬ ምድራዊነት ቢያጣጥልሽ፥

ዕጹብ ድንቅ ነሽ ለሚያፈቅሩሽ፤

ሰማያዊነት ነውና፤

እውነተኛው መልክሽ።

ዛሬ ምድራዊ ሃብት ባይኖርሽ፥

ሃብታም ነሽ አብሮነትን በሚሹ ልጆችሽ፤

የሕዝቦች ደግነት ነውና ሃብትሽ፥

አምልኮተ እግዚአብሔር ነውና እምነትሽ።

ቀኑን ሙሉ በየመንገዱ የሚቀመጡ የዛፍ ጥላ እንኳን ቢያገኙ ጥሩ ነበረ። ዛፎች በየቤቶች መካከል እና በየመንገዶቹም ዳርቻ ቢተከሉ ኖሮ፥ ቅጠሎች የጸሐይን ብርሃን ወደ ኃይል ለውጠው፥ ሕይወት አግኝተው ሲበራከቱ የከተማውን የአየር ሙቀት (ቃጠሎ) ይቀንሱት ነበር። ዛፎቹ ሰውን በጥላ ሲያቀዘቅዙት፥ የመሬቱንም አቧራ ሲይዙለትና ንጹህ አየር ሲሰጡት፥ ለአይን ውበት ከመሆናቸውም በላይ ለጤንነትም ይጠቅማሉ። በሳር መራቆት የደረቀውንም መሬት በእጽዋት እንዲሸፍኑት መንግሥት "መመሪያ" ቢሰጥ ጥሩ ነበር።

አሁንም (የ1998 እይታ) ቢሆን፥ ከሰው የሚወጣ "ደረቅና ፈሳሽ በካይ" አፈሩንና ውሃውን እየበከለው ነው። ይህ ችግር በተለይ በአንዳንድ የሕዝብ ቁጥር በበዛበት አካባቢ (በከተማዎችና በመንደሮች) በገሃድ እየታየ ነው።

የሕዝቦች ጤንነት እና የአካባቢ ጤንነት የተያያዙ መሆናቸውን ሠፊው ሕዝብ የተረዳ አይመስልም። በመንግሥት ደረጃም አስፈላጊው የአካባቢ ንጽሕና ካልተደረገ በስተቀር፥ የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ በሄደ ቁጥር፥ የሕዝቡም ጤና ማጣት ይባባሳል።

ከሰው የሚወጣውን "በካይ" ለአይን እንዳይታይ ብቻ በቀዳዳ ቢደብቁት፥ በመሬት ላይ ከሚፈስ ውሃ ጋር መገናኘቱ ይቀራል እንጂ፥ ከከርሰ ምድር ውሃ ጋር መነካካቱ አይቀርም። ያለው አማራጭ ከሰው የሚወጡ "በካዮችን" መቅበር ሳይሆን፥ በተወሰኑ ሥፍራዎች እያጠራቀሙ መሄጃቸውንና መድረሻቸውን መወሰን (በቁጥጥር ውስጥ ማዋል) ነው።

ለአካባቢ ጤንነት የሚወጣው ገንዘብ ለሕዝቦች ጤንነት ከሚወጣው ገንዘብ ጋር የሚደጋገፍ መሆኑ እየታሰበ፥ አስፈላጊውን መንግሥታዊ እርምጃ ለመውሰድ

የሚያበቃ ገንዘብ መመደብ ይገባል። ኗሪውም የራሱ ጤንነት እና የምድሪቱ ጤንነት (ንጽሕና) የተያያዙ መሆናቸውን በደንብ መማር ይኖርበታል።

በየመንገዱ ሠራተኛውና ለማኙ አብሮ ይርመሰመሳል። አንዳንድ ፖለቲከኞች ለድሃ ገንዘብ መስጠት የሰውን የፖለቲካ ንቃት ያዳክመዋል፤ ለተሻለ የመንግሥት ስርዓትም እንዳይታገል ያደርገዋል፤ አለዚያም ሥራ መሥራትን ትቶ የሰው እጅ ብቻ እየተጠባበቀ እንዲኖር ያደርገዋል (ያሰንፈዋል) ይላሉ። ግን፥ ምንም ቢባል ምንም፥ በድሆች ወገኖቻቸው ላይ መጨከን የማይቻላቸው ደጋግ ሰዎች፥ ከቤት ወደ ሥራ፥ ከሥራም ወደ ቤት ሲሄዱ፥ በየመንገዱ ተኮልኩሎ ለሚለምን ሁሉ (እጁን ቢዘረጋም ባይዘረጋም) ሳንቲሞችን ጠብ ጠብ እያደረጉ ማለፍ የተለመደ ሆኗል። ለማኞች በአንድ ቀን የሚሰበስቡት ገንዘብ ቢቆጠር አንድ የቀን ሠራተኛ ከሚያገኘው ሳይበልጥ አይቀርም የሚሉም አሉ (ሊሆን/ላይሆንም ይችላል)።

ጤነኞቹና ኑሮ የተሳካላቸውን ኢትዮጵያውያኖች በያሉበት ያገራቸውን ድሃ እንዲያስታውሱና እንዲረዱ፥ መስጠት የሚችሉ የመስጠትን ዕድል እንዲያገኙ የሚቀሰቅሱ ስንኞች ከዚህም ከዚያም ይሰማሉ፡-

እባካችሁ የኔ ጌቶች፥ ተወዳጆች የእግዜር ሰዎች፥
ምኞቴ ነው ፍላጎቴ፥ እንድትሆኑ ጤነኞች፤
ጸሎቴ ነው፥ ልመናዬ፥ እንድትሆኑ ደስተኞች።

እኔስ ሆኜ ቀረሁ በሽተኛ፥ የማልችለው ሡፍሮብኝ፥
መግቢያ አጣሁኝ መሸሸጊያ፥ ካቅሜ በላይ ሆነብኝ፤
ወድቄአለሁ ተመልከቱኝ፥ የእሳት አጥር ታጥሮብኝ።

አትጨክኑብኝ እያያችሁ፤
እኔምኮ ነኝ ወገናችሁ።
ቸሩ እግዚአብሔር ይባርካችሁ፤
ሰላም ፍቅር ያብዛላችሁ፤
በረከቱን ያድላችሁ፤
ዜማ መላእክት ያሰማችሁ፤
የምድር ሰማይ ያርግላችሁ፤
ከጭንቀት አውጡኝ እባካችሁ፤
አትለፉኝ - እርዱኝ በአምላካችሁ።

ኢትዮጵያችን ድሆች ሃብታሞችን እየለመኑ የሚኖሩባት ሀገር ስትመስል፥ ለማኙም፥ ሰጪውም ከሥጋዊነቱ አብልጦ ለነፍሱ እንዲያስብ አድርጎታል ያሰኛል።

ጥንት ከማውቃት ኢትዮጵያ አንድ ለየት ያለ ነገር ይታይባታል። ሰዎች ከምን ጊዜውም የበለጠ ሃይማኖተኞች በመሆን፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ፤ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ፥ ሲጸልዩ፥ ሰማያዊ መዝሙር ሲዘምሩ ይሰማሉ። ይህ በጣም ደስ ይላል፤ ግን በአንጻሩ፥ በሃማኖት ልዩነቶች ምክንያት፥ እርስ በርስ የመናቆር አዝማሚያም ይታያል።

ከዛ የሃይማኖት አልባ ዘመን በኋላ፥ ሰዎች በኢትዮጵያ ምድር ልብ ገዝተው ወደ ሃይማኖት ተመለሱ። ግን ባሁኑ ጊዜ የሃይማኖቶች ግጭት በየቤተሰቡ እየገባ፥ ሰዎች በገዛ ከፋቶቻቸው ልዩነቶችን እያከረሩ፥ የማሕበራዊ ኑሮ መናወጥን ፈጥረዋል።

ጻድቃን የደከሙበትንና ያስፋፉትን የክርስትና ሃይማኖት ኦርቶዶክስም ፕሮቴስታንትም ይኮትኩታት (ያልማት)። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስለ ምድር ኃጢአት አለቀሰች እንጂ፥ ወገን አልለየችም። እመቤታችን ስሟ መጨቃጨቂያ ሲሆንባት፥ እርሷም ልጇም ደስ አይላቸውም።

ሰው ሁሉ የየራሱ ሃይማኖት ለራሱ ይሁነው፤ ሁሉንም ውደዱ እንጂ፥ በመካከላችሁ አለመግባባትና ጭቅጭቅ አይፈጠር፤ የክርስቶሳዊነት አላማው በሰዎች መካከል ልዩነቶችን በፍቅር አስተሳስሮ፥ ማንም ለሌላው ራሱን ዝቅ በማድረግ፥ ለእግዚአብሔር እየሰገዱ መኖር ነውና።

የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ልክ አይደለም፤ የኛ ብቻ ነው ልክ፤ የኛን የሚያጸድቀውን ተከተሉ በማለት፥ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ደጃፍ ድረስ እየሄዱ ወረቀት የሚበትኑ መኖራቸውን ሰምተን እጅጉን አዘን። እነኚህ ግለሰቦች ጥቂቶች ቢሆኑም፥ እንደነርሱ ለሚያስቡ ሁሉ ምክር እና ትምህርት ያስፈልጋቸዋል።

ሰዎች እርስ በርስ ሲጣሉ የሚጎዱት የገዛ መንፈሳቸውን (ውስጣዊ ማንነታቸውን) ነው። ኢትዮጵያ የተለያዩ ሃይማኖቶች ቢያብቡ እግዚአብሔር የፈቀደው ነውና፤ እንደ ጥሩ መታየት ይኖርበታል።

ተው! ተው! ተው! እምነታችሁን ለራሳችሁ አድርጉ እንጂ፥ ከእግዚአብሔር ቤት ደጃፍ ደርሳችሁ በመንፈስ ላይ ሁከት አትፍጠሩ። የምትሠሩት ሥራ ሁሉ በጎ የሚመስላችሁን እያሰባችሁ ቢሆንም፥ በውስጡ የበጎ መንፈስ እገዛ ከሌለበት ውጤቱ መጥፎ ይሆናል፤ እናንተንም ጥፋተኛ ያደርጋችኋል። የጥሩ ሥራ ጥሩነቱ የሚረጋገጠው እንዳጀማመሩ ውጤቱም ሲያምር ነውና፤ ወረቀት ስትበትኑ የሚያስከትለውንም ውጤት እያሰባችሁ ይሁን።

እናንት የወንጌሉን ቃል ተከትላችሁ እራሳችሁን ትመራላችሁ፤ ግን ቅዱሱ መጽሐፍ፡- *"ወደ አሕዛብ ሂዱና አስተምሩ.." (ማቴ. 28፡ 19-20)* አለ እንጂ፥ በአብ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቁ አማኞች ዘንድ፥ ከሚሰግዱበትም ቤተ ክርስቲያን ደጃፍ ድረስ ሄዳችሁ የእነርሱን ሃይማኖት አስተካክሉላቸው አላለም።

በአንድ ጻድቅ ስም ቤተ ክርስቲያን እያሠሩ ጻድቁን ለመምሰል የሚጥሩ ሕዝቦች ሃይማኖታቸው የቀና ነው እንጂ፥ የተወላገደ ሊሆን አይችልምና፤ በከንቱ አትቃወሙ።

እናንት ወንጌላውያን፥ የክርስቶስ ተከታዮች የሆናችሁ ደጋግ ሰዎች ሆይ! የደግነታችሁ መጨረሻ ክፋትን እንዳያመጣባችሁ ተጠንቀቁ። እናንተ ስለምታውቁት ሁሉ የገለጸ አምላክ ለሌሎችም እንደየአቅማቸው የሚያሳውቅ (ያሳወቀ) መሆኑን አስቡ።[25]

የዚህን ጥቅስ ትርጉም ሙሉ በሙሉ ሊያውቅ የሚችል ከሰው የተፈጠረ ሊኖር አይችልም፤ ከራሱ ከኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር። ሆኖም፥ እኛ ልዩነቶቻችንን ከተለያየ በረት እንደመግባት ብንቆጥረው፥ የራስ ያልሆነውን ሃይማኖት በማጥላላት፥ ራሱ ክርስቶስን መስሎ፥ "ኑ ከዚህ በረት ግቡ፥..." እያሉ ሰውን ከማስጨነቅ ይልቅ፥ ዞሮ ዞሮ ያ አንድ የሆነው እረኛ - ጌታችን ፈልጎ ያገኛቸዋል፤ ከተለያየ በረት ብንሆንም፥ በእረኛችን አንድ መንጋ ልንሆን እንችላለን ብሎ በአዎንታዊነት መመልከት ይቀላል (ይሻላል)።

ለመሆኑ ከዚህ ምድር ውጪ ሌሎች በረቶች ቢኖሩስ ማን ያውቃል? እኛ ሁላችንም በአንድ በረት ውስጥ ያለን ብንሆን እና፥ "እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል" ሲል ከዚች ምድር ሌላ - ሌሎች የጠፈር ምድሮች ያሉበት ሥፍራ እሄዳለሁ ማለቱ ቢሆንስ? ማን ያውቃል። በማያውቁት ነገር መጣላትና መጨቃጨው ከንቱ ነው፤ ይቅር አይበጀንም። በክርስቶስ መንፈሳዊ አንድነትና ፍቅር ተስማምተን እንኑር።

---

[25] ክርስቶስ እንዲህ አለ፡-*"የራሴን በጎች አውቃለሁ፤ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤ ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ። ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል፤ ድምጼንም ይሰማሉ፤ አንድም መንጋ ይሆናሉ፤ እረኛውም አንድ።" ዮሐ. 10፡16*

## ቋንቋዎች እና ፊደሎች

ባላገሮች ወደ ከተማ ገብተዋል። እነርሱ የዋህነታቸውን ይዘው ሲገቡ፥ ከተሜዎች አዘኑላቸውና አስተናገዷቸው - አበሏቸው፥ አጠጧቸው። እነርሱ ግን ለከተሜዎች ምንም አላደረጉላቸውም። ግን የተፈጥሮ ቻይነታቸውንና ትእግስተኛነታቸውን አስተማሯቸው፤ ደግነታቸውንና ፍቅራቸውንም ገለጹላቸው።

ከጊዜ ብዛት ከተሜው ከባላገሩ ብዙ ነገር ተማረ። የአነጋገሩ ስልት ተለወጠ። አማርኛችን በትግርኛና በኦሮምኛ ተከልሶ፥ በሌሎች ቋንቋዎችም ተነካክቶ፥ ለሁሉም የሚጣፍጥ ቋንቋ ሆነ (ቀለል እያለ መለሳለስን በማግኘቱ)። በመንፈሳዊ መዝሙርና በዘፈን፥ በትያትር፥ በሲኒማ እና በተለያዩ ኪነ ጥበባት ቅንብብር፥ የብዙዎችን ቀልብ እየሳበ፥ አማርኛ የፍቅር ቋንቋ ሆኗል፤ እንደሰው ቋንቋውም ልስልስ።

የወቅቱ የሀገራችን ሕብረተሰባዊ የኢኮኖሚ እርከኖች በአማርኛ ውስጥ የሚካተቱ “የአራዳ” ቃላትን ፈጥሯል። ለሚጠቀሙባቸው ውስጣዊ ስሜታቸውን (ሁኔታቸውን) በበለጠ የሚገልጡበት ነውና፤ ለእነርሱ ያ ጥርት ያለ ቋንቋቸው ነው።

ባጠቃላይ፥ በሰዎች ንግግር ውስጥ ትህትናን የሚገልጹ ቃላት (እንደ “እናትዬ”፥ “አባት” የመሳሰሉ) በብዛት ይሰማሉ፤ የሰዎችም የርስ በርስ ግንኙነት፥ ትእግስትና ፍቅር በግልጽ የሚታይበት ሆነ። ድሃና ሃብታም ተረዳድቶና ተቻችሎ የሚኖርበት ሀገር - በእውነት ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው።

ጥንት ከማውቃት ኢትዮጵያ ለየት ያለ ነገር ቢኖር፥ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በላቲኑ መጻፋቸው ነው። በጥንት ዘመን የሕዝቦች መገልገያ ፊደል ኢምፔሪያሊስት ሆኖ ሌላውን ፊደል ሲወር አላየንም፤ አሁን ግን ኢትዮጵያ በፈቃዷ የራሷን ፊደል በላቲን ፊደል አስወርራለች። እኛው ራሳችን ነን ራሳችን ያስወረርነው እንጂ፥ የላቲን ፊደል ራሱ ኢምፔሪያሊስት ሆኖ ፊደላችንን (ወይንም ቋንቋችንን) ለማጥፋት አልተነሳም።

ለእስዋሂሊ፥ ለሶማሊያና ለሌሎች ቋንቋዎች የኛ የግዕዝ ፊደል ከላቲን ፊደል የበለጠ የሚጠቅም ሆኖ ሳለ፤ በኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ብቻም ተወስኖ መቅረቱ በእውነት የሚያሳዝን ነው። በአሁኗ ኢትዮጵያችን የግዕዝ ፊደል ተጠቃሚውን ሕዝብ ወደተወሰኑ ሕብረተሰቦች ማሸጋሸጉ ለወደፊት የሚያስከትለውን የእርስ በርስ መገፋፋት፥ እስከ ጦርነትም ሊያደርስ የሚችል ቅድመ ሁኔታዎችን እያመቻቸን መሆኑን ያልተገነዘብን ይመስላል።

አንድ ቋንቋ በደንብ የሚታወቀው በንግግር ብቻ ሳይሆን በጽሑፍም ሲደገፍ ነው። የግዕዙን ፊደል ለአማርኛ ምንባብ የሚጠቀሙ የኦሮሚያ ሕብረተሰቦች፥

ቋንቋውን (አማርኛን) በደንብ ካላወቁት ለማንበብ ይከብዳቸዋል፤ ቋንቋውን በደንብ ሲያውቁት ማንበብና መረዳቱ ይቀላቸዋል። ይህንንም ችግር አብሮ መገንዘብ ይገባል።

የግዕዝ ቋንቋን ያልተማረ አማርኛ ተናጋሪ፥ በግዕዝ የተጻፉትን ሲያነብ እንደሚከብደው፥ አማርኛ ቋንቋን የማያውቅ የኦሮሞ ተናጋሪ በአማርኛ የተጻፈውን ማንበብ ሊያስቸግረው እንደሚችል፥ እንዲሁም የግዕዙን ፊደል የሚጠቀሙ ሌሎች ኦሮሞ ያልሆኑ ሕብረተሰቦች ኦሮሚኛን በደንብ ካላውቁት፥ በግዕዝ ወይንም በላቲን የተጻፈን የኦሮሚኛ ጽሑፍ ለማንበብ ይከብዳቸዋል፤ ቋንቋውን በደንብ ሲያውቁት፥ ማንበብና መረዳቱ ይቀላቸዋል።

አማርኛ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ ስለሆነ፥ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አማርኛ ቋንቋን መማር የውዴታ ግዴታው ነው። እንግዲህ፥ የግዕዝን ፊደል ሲያጠኑ አማርኛ ቋንቋንም ከማጥናት ጋር አብሮ ይሄዳል ማለት ነው። እንዲሁም ይህንን ፊደል፥ ከኢትዮጵያ ሕብረተሰቦች መካከል አድርጎ አብሮ መማማር ለአንድነታችን ማጠናከሪያ እንደሚሆን አይካድም። ይህም ካልሆነ፥ የሚቀጥለው ጥያቄ፥ አማርኛ ቋንቋን እንደ ባዕድ ቋንቋ ቆጥሮ፥ “ለኦሮሚኛ ቋንቋ የሚጠቅመው ፊደል የትኛው ነው?” ብሎ መጠየቅ ነው።

ካሁን በፊት ጥቂት የኦሮሞ ነጻነት ግንባር መሥራቾች፥ መሪዎች እና አባሎች ተሰባስበው፥ ለኛ ለቋንቋችን ይህ ነው የሚበጀን ብለው የላቲኑን ፊደል እንደ መገልገያ መረጡ። “የላቲኑ ፊደል ከግዕዙ ፊደል ምን የተለየ ነገር አግኝተውበት ይሆን?” ብሎ መጠየቅም ተገቢ ነው።

እነርሱ በብሄርተኛነት፥ አጉል ግንፍል ፖለቲካ ተነሳስተው፥ የግዕዝን ፊደል አጥላልተው የላቲኑን ሲሰብኩ፥ ለዘመኑ ሥልጣኔ አዲስ በር የከፈቱ መስሏቸው ይሆናል። በእርግጥ ከ195 የአለም አህጉራት መካከል 141 የሚሆኑት በላቲን ፊደል ይጠቀማሉ። እና፥ እኛም ሌሎቹን እንምሰል ቢባል፥ ጥቅምና ጉዳቱን እያሰቡ ከሆነ መልካም።

በአንዲት ኢትዮጵያ የኦሮሞ ሕብረተሰብ፥ ከሌላው ተለይቶ፥ ብቻዬን ልሠልጥን ብሎ ቢነሳ፥ ልገንጠል ማለቱ እንደሚሆን ያስታውቃል። የፖለቲከኞቹም አዝማሚያ ወደዚሁ ነው የሚያመራው። እነርሱ የኦሮሞን ሕዝብ ከተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ገንጥለው፥ በብቸኝነት ለማስተዳደር ፈልገዋል።

“ለብዙ ዘመናት በግዕዙ ፊደል ሲጠቀሙበት የቆዩ አማሮች እና ትግሬዎች ብቻ በመሆናቸው፥ እኛ በላቲኑ ፊደል ከተጠቀምን፥ የእነርሱን የበላይነት በማስቀረት፥ እኛ የበላይ ሆነን የምንታይበት አንዱ አማራጭ መንገድ ይሆንልናል” ብለው የሚያስቡም ይኖራሉ።

አዩ! የአለም ፊደሎች ሁሉ የየግላቸውን ፊደሎች ወደ ላቲኑ ቢያሸጋሽጉ፥ የራሳቸውን ማንነት ከማጣታቸው በስተቀር፥ ይህ ድርጊት ብቻውን፥ በሥልጣኔ አንድ እርምጃ እንኳን እንደማያራምዳቸው፥ ወዳሰቡትም ከፍታ እንደማያወጣቸው አልተገነዘቡም። እንደ እንግሊዝ እንደ ፈረንሳይ እንሁን ቢባል፥ የነርሱን ቋንቋ እና ባህል በደንብ በማወቅ እንጂ፥ ፊደላቸውን ብቻ በመውረስ አይሆንም።

በፊደል አመካኝተው ልዩነትን ቢፈጥሩ፥ ያ ልዩነት ተባብሶ፥ በሃይማኖቱም ሕዝቡ አንድ ከሚያደርገው ከሃይማኖቱ ለየት ያለውን እምነት እንዲፈልግ ነው የሚያደርገው።

በአጠቃላይ ሲታይ፥ አክራሪ የኦሮሞ ፖለቲከኞች የፈለጉት፥ አንድነትን የጠሉ ሆነው ነው እንጂ፥ ጠቃሚውን ፈልገው ነው? እንጃ፤ እስቲ በጥሞና እንመልከተው።

## <u>የግዕዝ ፊደል ለኦሮሚኛ እና የላቲን ፊደል ለኦሮሚኛ</u>

የላቲኑን ፊደል አንዴ መማሩ ቀላል ሲሆን፥ የግዕዙን ፊደል ግን አንዴ መማሩ ጊዜ ይፈጃል። ሆኖም፥ ፊደሉ ከተጠና በኋላ፥ ለእያንዳንዱ ቃል ትክክለኛውን ሆሄ (Spelling) እንዳለ በማስቀመጥ ምንም ስህተት አይፈጠርም። በግዕዙ ፊደል በአፍ የሚነገረውን ሁሉ እንዳለ መጻፍ ስለሚቻል፥ በቃላቶች ላይ የሆሄ ችግር አይኖርም ማለት ነው።

በዚህ አንጻር ስንመለከተው፥ ለእንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ ተናጋሪዎች፥ ለሌሎችም ቢሆን፥ ከላቲኑን ፊደል ይልቅ፥ ምናልባት የግዕዙ ፊደል ሳይሻላቸው አይቀርም ነበር ብለን እናስባለን። ሆኖም፥ ለእነርሱ የሚሻላቸውን እነርሱ አንዴ ስለመረጡ፥ ወደኋላ አይመለሱም። “ለእኛ” የሚሻለንን “እኛ” እንምረጥ ከተባለ፥ “የእኛ” የሆነውን ትተን ሌላ መፈለጉ ወደኋላ መመለስ ይሆናል። ግን ምንም አይደል፤ ወደኋላ መመለሱ ደስ የሚያሰኛቸው ካለ።

በግዕዝ ፊደላችን ላይ ሰረዝም ሆነ ቅጥል (ነጥብ) በማድረግ፥ ፊደሉን ለኦሮሚኛ ቋንቋ ተስማሚ ማድረግ ይቻላል። በአማርኛችንም ቢሆን ቀድሞ በግዕዝ ያልነበሩ ፊደላት፥ እነ “ተ፥ ደ፥ ሰ” ላይ ሰረዝ ተጨምሮባቸው ነው፥ እነ “ቸ፥ ጀ፥ ሸ” የተገኙት። በተመሳሳይ፥ ደ ላይ ሁለት ነጥብ ተጨምሮ ጀ̈ ቢደረግ፥ በኦሮሚኛ ተፈላጊ ከሆኑት መካከል አንዱ ተገኘ ማለት ነው። ይኸውም፡- በኦሮሚኛ “አይታጠብም” ለማለት የፈለገ፥ “ኢንጀ̈ቀኒ” ይላል ማለት ነው። ጀ̈ሎታ ጋሪ (መልካም ልደት) እየተባባልን የእርስ በርሳችንን ግንኙነት ብናጠናክር አይሻልም?

እንዲህ በአዎንታዊ አስተሳሰብ አብረን ብንዘልቅ፥ አንዳንድ በአማርኛ የማይገኙ አባባሎችን ከኦሮሚኛ እየተዋስን ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ለምሳሌ፡- በኦሮሚኛ "በዱን በዲ መሌ ሰሬ ኢጃ ኢንጂቀኒ" የሚለው አባባል፥ ወደ አማርኛ ሲተረጎም "የጠፋው ይጠፋል እንጂ የውሻ አይን አይታጠብም" እንደማለት ሲሆን፥ ይህም፥ ጭምልቅልቅ ያለውን የሰውን ጠባይ ለማረቅ መሞከር፥ የውሻን አይን እንደማጠብ ይቆጠራል እንደማለት ነው። ይህንን የመሳሰሉ፥ በአንድ ብሔር ቋንቋ ውስጥ የማይገኙ አባባሎችን፥ ከሌላ ቋንቋ ጋር እያዋሃዱ መጠቀም ምን ይጎዳል? ይጠቅማል እንጂ።

የእንግሊዝኛ አረፍተነገሮችን በግዕዝ ፊደል በማስቀመጥ በትክክል ማንበብ ይቻላል። ለምሳሌ፡- What do you want? በግዕዙ ሲጻፍ፡- "ኋት ዱ ዩ ዋንት?" ልክ በአፍ ሲነገር እንደሚባለው ይነበባል። የአማርኛን አረፍተነገሮች በላቲን ፊደል በማስቀመጥ በትክክል ማንበብ ያን ያህል ቀላል አይሆንም። ለምሳሌ፡- ምን ትፈልጋለህ? በላቲን ሲጻፍ፡- min tifeligaleh? ሲነበብ "ሚን ቲፈሊጋለህ?" ስለሚሆን፥ ልክ በአፍ ሲነገር እንደሚባለው አይነበብም። እንዲሁም፥ ለኦሮሚኛውም በትክክል የሚያስነብበው የግዕዙ ፊደል ነው። ለምሳሌ፡- "እንደ አንበሳ እንበላለን፤ ይሁን እንጂ፥ አንጠግብም" የሚለውን ወደ ኦሮሚኛ ተርጉመን በግዕዙ ስንጽፈው "አካ ሌንጫቲ ኛና፤ ሃታኡ መሌ፥ ኢንቁፍኑ" ይሆናል። በግዕዙ ሲጻፍ፥ ልክ በአፍ እንደሚነገረው ይነበባል፤ በላቲኑ (በቁቤ) ሲጻፍ ግን፥ ምንጊዜም ጽሑፉ እና ምንባቡ አንድ አይነት እንደማይሆን አይካድም።

የላቲንን ፊደል (አልፋቤት) ለኦሮሚኛ ሲጠቀሙበት፥ ከጥቂት ልምምዶች በኋላ ኦሮሚኛን በደንብ ማንበብ አይቻልም ማለት አይደለም፤ ይቻላል። ሆኖም፥ የትኛው ነው ለኦሮሞ ተወላጅ፥ ለኢትዮጵያችን፥ ለአፍሪካም የበለጠ የሚጠቅመው ብለን ብናስብበት መልካም ነው። ይህንን ጉዳይ፥ በተለይ የኦሮሚኛ ተናጋሪ የሆኑ የቋንቋ ተመራማሪ (ምሁራን) ቢመለከቱት ነው የሚሻለው።

"በእጅ የያዙት ወርቅ እንደ መዳብ ይቆጠራል" እንደሚባለው ሁሉ፥ የኛን የግዕዝ ፊደል ብቃትና ችሎታ እኛ እያቀለልን ስንሄድ፥ ሌሎች (ፈረንጆች) ከኛ ቀበል አድርገው፥ በየዩኒቨርሲቲዎቻቸው ያጠኑታል (ለምን ይሆን?)።

ፊደላችን ፋይዳ የሚሰጥበት መንገድ ከምናስበው የበለጠ ሰፊ ሊሆን ይችላል። በግዕዝ ፊደል እያንዳንዳቸው በጥንቃቄ ካልተጻፉ በስተቀር ያሳስታሉ። ለምሳሌ፡- ከ እና ክ፥ ፉ፥ እና ፋ፥ ም እና ሞ፥ ወ.ዘ. ተ. አንዱ ሌላውን ሊመስል ጥቂት ነው የሚቀረው። ምናልባት፥ ይህ ሲጽፉት ፈታኝ የሆነ ፊደል፥ የተጠቃሚውን የአይን

ትኩረት ችሎታን ለማዳበር (ጥንቁቅ እና አስተዋይ እንዲሆንም ለማድረግ) ይረዳ ይሆናል።[26]

ያም ሆነ ይህ፥ ሕዝቡ ለራሱ የሚቀለውን ብቻ ሳይሆን፥ የሚጠቅመውንና የሚሻለውን (በዘለቄታዊነት ለወደፊቱ ትውልድ የሚያዋጣውን) በራሱ ያውቃል።[27]

በዚሁ በአሁኑ ሁኔታ ከቀጠለ ግን፥ በላቲኑ እና በግዕዙ ፊደል የሚጻፉትን መጻሕፍት ሁሉ እያነበቡ የሚያድጉ ልጆች፥ በኋላ በላቲን ብቻ ከሚጠቀሙት ጋር መግባባት ያዳግታቸዋል። እስከ ዛሬ የነበረ የእርስ በርስ መግባባት ይጠፋል፤ የወደፊት አንድነታችን ይናጋል። ይህም እስከ እርስ በርስ መጋጨት እና ተለያይቶ እስከ መቅረትም ሊያደርስ ይችላል።

ሀገራችን ብዙ የቋንቋ ምሁራን አሏት፤ ምነው እነርሱ የሚሉትን እንኳን ብንሰማ? ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ የሆነውን ፊደል ከሀገር ለይተው ቢያወጡት፥ ሕዝቦች በአስተሳሰብ፥ በኑሮና በባሕል ይራራቃሉ። መጨረሻውም፥ እኛ ኢትዮጵያውያን ከኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ጋር ተግባብተን በሰላም እንዳንኖር፤ በመካከላችን የእድገትና የእውቀት መዛባት፥ አለመግባባትም እንዲፈጠር፤ በጋራም እንዳንበለጽግ  የሚያደርግ አደገኛ መሰናክል መሆኑንም መረዳት ያስፈልጋል።

እስራኤላውያን ከተለያየ ሀገር ዜግነታቸውን ፈልገው (መርጠው) ወደ እስራኤል ሲገቡ፥ በመጀመሪያ ቋንቋቸውንና ፊደላቸውን ከሚያጠኑበት ኡልፓን ከተባለ ሥፍራ ይሰነብታሉ። ከዚያም ተምረው ሲወጡ፥ በአንድ ብሔራዊ (እብራይጥ) ቋንቋ ይግባባሉ። የእብራይስጥን ቋንቋ ካለ ፊደሉ ማጥናት እንደሚከብድ፥ የኛንም (አማርኛ፥ ኦሮሚኛ፥ ትግርኛ...) ቋንቋዎች፥ ካለ ራሳችን ፊደል መማርና ማዳበር ቀላል አይሆንም።

ሕዝቦች በአስተሳሰብ፥ በኑሮና በባሕል ሲቀራረቡ (የሚያቀራርባቸው መንገድ ሲበዛ)፥ ከእኩልነታቸውና ነፃነታቸው ባሻገር አንድነታቸውም ይጠናከራል፤ በአንድነታቸውም አብሮ በመሥራት የጋራ ብልጽግናቸው ያብባል። "አይሆንም፤ አይቻልም.."  የሚለው ሰፊው የኦሮሞ ሕዝብ ሳይሆን፥ ጥቂት የጥላቻን መርዝ

---

[26] የዱር አራዊት አይኖች በጥቂት ጨረር ማየት የሚያስችል አይኖች አሏቸው። የኛ አይኖች ደግሞ ለጥቃቅን ዝርዝር የቀለም አይነቶች ትኩረት የሚሰቡ (cone cells) የተባሉ አሉን። የኮን ሴሎች በዓይን ሬቲና ውስጥ ለቀለም እና ለቀን ብርሃን እይታ የሚጠቅሙ ናቸው።

[27] ከድህረ ገጾችም፥ እንደ mereja.com/amharic፤ ethioreference እና የመሳሰሉት ጠቃሚ ሃሳቦችን ይመለከቷል።

የሚነሰንሱ ፖለቲከኞች መሆኑን እናውቃለን (መንግሥትም ይህንን ያውቃል)። የሀገር መሪዎችም የጥላቻን መርዝ ከሚነሰንሱ ፖለቲከኞች ጋር በማበራቸው ምክንያት፥ የኢትዮጵያ ሕዝቦች እድገት እየቀረቀዘ ሲሄድ አየን። አይቶ ዝም አለማለትን የመረጡ ጋዜጠኞች፥ ምሁራንም ይናገራሉ፤ ይጽፋሉ፤ ይመክራሉ፤ እነርሱን ሰምቶ እርምጃ የሚወስድ ጠፋ። የላቲኑ ፊደል የመጣብን፥ እኛ ቅን ኢትዮጵያውያን የምናስበውን “የሕዝቦች አንድነት” በተግባር እንዳይተረጎም “ታስቦም/ሳይታሰብም” ሊሆን ይችላል። ግን፥ ለሕዝቦች አንድነት የሚቆረቆር ሕዝባዊ አስተዳደር ቢኖር፥ ይህንን አቢይ ጉዳይ ለዘረኞችና ለአክራሪዎች ለቆ፥ ችላ በማለት ፋንታ፥ ለወደፊት የሚያስከትለውን ብሔራዊ እና አህጉራዊ ጉዳት ከወዲሁ በመመልከት፥ ፈጣን እርምጃ መውሰድ ተገቢ ነው።

አሁን ይኽ ሁሉ ሃተታ ያስፈለገው፥ ሠፊው የኦሮሞ ሕዝብ የሚሻለውን ራሱ አውቆ መምረጥ እንደማይችል በመቁጠር አይደለም። ነገር ግን፥ ኦሮሚኛ የኦሮሞዎች ብቻ አይደለም። ብዙ አማሮች አሉ ኦሮሚኛን አቀላጥፍው የሚናገሩ። ኦሮሚኛ የእኛ የአማሮች፥ እንዲሁም በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ የሚኖሩ የሌሎች የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎችም ስለሆነና፥ ሁላችንንም ስለሚመለከት፥ የሁላችንም ድምጽ መሰማት አለበት። በእማርኛችንም ውስጥ ጥቂት ሁለት ፍቺ ያላቸው ቃላት፥ እንዲሁም በመጥበቅና በመላላት የሚነገሩ አሻሚ ቃላት በመኖራቸው፥ አፍ መፍቺያው አማርኛ ላልሆነ ሁሉ በዚህ ግራ እንደሚጋባ ይታወቃል። ይህንን እና ሌሎችንም ጉዳዮች ታሳቢ በማድረግ፥ ብዙሓኑ የኦሮሚያ ሕብረተሰብ በዘላቂነት የሚጠቅመውን በሚመርጥበት ጊዜ፥ በጥሞና (በእርጋታ) ካለ ምንም የፖለቲካ ተጽንኦ እና ካለምንም ጥላቻ (ኢትዮጵያዊነቱንም እያሰበ) ቢሆን መልካም እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል።

የተቀረውም የኢትዮጵያ ሕዝብ አጠቃላይ ምርጫ አካሂዶ፥ ይህን ከብነት የበዛበት፥ ሲያዩት እንደ ማሽላ ቆሎ የፈካ፥ ጥንታዊነትን የሚያስታውስ ቆንጆ ፊደል እየተወ፥ ወደ ላቲኑ መሸጋገር ይሻለኛል ካለ፤ የዛን ጊዜ “ሁሉም ለበጎ ነው...” ብሎ መቀበል ይቻላል። እስከዛው ግን፥ አማርኛ የሀገራችን ብሄራዊ ቋንቋችን ነው ብለን እስተቀበልን ድረስ፥ ይህንን ቋንቋ ማክበር፥ መንከባከብ፥ ማሳደግ እና ማዳበር ይገባል እንጂ፤ ሲነገርበትም፥ ሲጻፍበትም ከማንም የባእድ ቋንቋ የማያንስ ብሄራዊ ቋንቋችን ሆኖ ሳለ፡- እናት በማለት ፋንታ mother፤ አባት በማለት ፋንታ father፤ ስለዚህ በማለት ፋንታ therefore፤ ምክንያቱም በማለት ፋንታ because፤ ወ.ዘ.ተ. እያሉ፥ በገላጭነት ከማንኛውም ቋንቋ የማያንሱ የአማርኛ ቃላትን በእንግሊዝኛ ቃላት መተካት፥ ቋንቋውን ማበላሸትና ማሳነስ፥ እንዳይስፋፋና እንዳያድግ ማድረግም ነው። እንዲህ ያለው ቋንቋን እየበረዙ የመናገር አባዜ፥ ከሌሎች የሀገራችን ቋንቋዎች ይልቅ፥ በአማርኛ ቋንቋችን ላይ እየበረታ የመጣው የኢሕአዴግ የአገዛዝ ዘመን ካበቃ በኋላ

ነው። እንግሊዝኛ ቋንቋ ማወቅን እንደ ብርቅ ነገር እየተቆጠረ፥ እጅጉን መስፋፋቱ፥ “ሌላ ድብቅ ፖለቲካዊ ተልእኮ ቢኖረው ነው” ያሰኛል።

ሀገር በመምራትና በማስተዳደር ላይ ያሉ፥ የገዛ ሀገርን ብሄራዊ ቋንቋ ልዩ ክብር በመስጠት፥ መከበሪያና ማስከበሪያ በማድረግና ለሌሎችም ምሳሌ በመሆን ፋንታ፥ እንዲህ ማሳነስ፥ ኋላቀርነት እንጂ ዘመናዊነት አይደለም። እንዲህ ያለው አጓጉል ልማድ ለጊዜው ቀላል ይመስላል፤ ቆይቶ ግን፥ ጉዳቱ ብዙ ነው። በስነ ልቦና የበታችነት ስሜት የሚያሳድር፤ ብሄራዊ ማንነትንም እስከማሳጣት የሚያደርስ፤ ከታላቅነት አዘቅት የሚያወርድ፤ ለሥልጣኔም እንቅፋት ነው።

## <u>አጠቃላይ የሕብረተሰብ ችግር</u>

አንዳንድ ሰዎች ምክር አነሳቸው፤ ኑሮና ብልሃቱ ጠፋባቸው። ሥራው በተለይ ምክር በመስጠት የሕብረተሰብን ችግር ማቃለል የሆነ የሬዲዎ ፕሮግራም ቢኖር ጥሩ ነበር። ትምህርት ቤቶች በምድር ስለመኖር ጉዳይ (ኑሮና ብልሃቱን) አያስተምሩም። እናትና አባቶችም የሚያውቁትን በግልጽ ለልጆቻቸው አይነግሩም። ኋላ ቀር (ጎጂ) ባህል ያደናቆራቸው እናትና አባት፥ እነርሱ ያለፉበትን ነው ለልጆቻቸው የሚያስተላልፉት። ለወደፊት ተወልደው የሚያድጉ ልጆች ከመጪው ዘመን ጋር እንዴት ስምም ሆነው እንደሚኖሩ ተለይቶ አልታወቀም።

ልጃገረዶች ገና ለአቅመ ሔዋን ሳይደርሱ (ማህጸናቸው ልጅ ለመታቀፍ ሳይደርስ) ገና በልጅነታቸው (አስራ አምስት ዓመት እንኳን ሳይሞላቸው) እያገቡ በእርግዝና ይታመማሉ፤ ከዚያም ሽንታቸውን እንኳን መቋጠር የማይችሉ ይሆኑና ይሰቃያሉ።

አለማወቅን (የሚጎዱ ልማዶችና ድንቁርናዎችን)፥ በተለይ በአለም የተወገዙና ጎጂ ልማዶችን ከቤተሰብ፥ ከሕብረተሰብና ከሀገር ውስጥ አለማጥፋት፥ ከኋላቀርነት ተገንጥሎ እንደማይታይ አልተገነዘብንም። የብዙሐኑ ኋላ ቀርነት ካልተወገደ በስተቀር፥ ሥልጣኔ ግንጥል ጌጥ ነው የሚሆነው።

ባጠቃላይ ሀገራችንን ከገጠማት ችግሮች መካከል፥ ለአያድርስ (AIDS) በሽታ የተጋለጡት እጅጉን ያሳዝናሉ። ይገርማል! ይደንቃል! ሰው ካልሞተ ብዙ ነገር ያያል። እነኛ መሄጃያ አጥተው በዚህ አስነዋሪ ተግባር ተዘፍቀው የቀሩት፥ ከሞቱት የተረፉት ሴትኛ አዳሪዎች - ከነርሱም መካከል በአያድርስ (AIDS) በሽታ የተሰቃዩ አሉ፤ በእሳት ውስጥ ሌላ እሳት እየተቃጠሉ ስለሆነ፥ ይታያሉ እንጂ ይኖራሉ አይባልም።

ሥጋዬ አፈር መሰለ፥ በስባሽነቱን በቁሜ መሰከረ፤
ያ ሁሉ ውበት፥ ያ ሁሉ ቁንጅና ሄደ በረረ።
ሰው ሆኜ እንደ ሰው ሳልቆጠር፥
ተምሬ፥ ተድሬ፥ ሥራ ይዤ፥
እህ! እራሴን እንዳላስተዳድር፥
በሞትና ሽረት መካከል ስወጠር፥
ምነው ምናለበት ነበር፥
ለበሽታ ምግብ ሆኜ ከምቀር፥
አዬ! ምናለበት ነበር፥
ጥንቱን ሰው ሆኜ ባልፈጠር።
እንዲህ ነዋ ዕድሜ ሲያጥር፥
በልጅነት ላይ እርጅና ሲጠነክር፥
መቃብርም በጎልማሶች እንዲከበር።
መጥኔ “ብዙ - ብዙ” ለመኖር ሲሉ የሚደከሙ፥
ሞት መሆኑን ያላወቁ፥ መድኃኒቱ የህመሙ።

ሰውነት ሲውረገረግ፥
በዝማሬ ስሜት ሲነቃነቅ፥
ይህ ደስ የሚያሰኝ
ውስጣዊ ስሜት፥
የመኖርን ጣዕም የሚያንጸባርቅ፥
በአንድ አያድርስ ሲጠናቀቅ፥
ይህ እንጂ እኮ ነው፥ ጣፋጭ ኑሮ ማለት፥
ትንሽ - ትንሽ ሰቅየት፥ አልፎ - አልፎም ማቃሰት።
ይህ እንጂ እኮ ነው፥ የመኖር ለዛ፥
ቀኑን ሲቆጥሩት እንዲበዛ።
እህህ!... እድሜ ሳይገፋ፥
በሽታ ሲገፋ፥
ኑሮ ሲከረፋ።

ሰው ሁሉ በአያድርስ ታማሚዎች ላይ ይፈርዳል። የአያድርስ በሽታ ከኢትዮጵያ የሚጠፋው የዛሬ ህጻናት (የነገ ጎልማሶች) ቤተሰብና ጠቅላላ ሕብረተሰቡ በፍቅር ተሳስሮ፥ የገዛ ሕይወቱን ማክበርና መንከባከብ እንዳለበት ሲማር ነው።

በአስተዳደግ ጉድለት ምክንያት አንዳንድ ልጆች ማድረግ የሚገባቸውን ለይተው ስለማያውቁ ነው ችግር ውስጥ የሚገቡት። ያለፈውስ አለፈ፤ ህጻናት እንዲያውቁና እንዲጠነቀቁ መነገር ያለበት ገና ከፍ ሳይሉ (ገና 13 ዓመት ሳይሞላቸው) ነው። አያድርስ በብልግና የሚመጣ በሽታ መሆኑን ልጆች ገብቷቸው፥ እራሳቸውን ከዚህ በሽታ ለማራቅ፥ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ መምከር ያስፈልጋል።

ከሚቀጥለው ትውልድ ቀጥሎ፥ የኢትዮጵያ ልጆች አያድርስ እንዳያገኛቸው ለማድረግ የሞራል (የግብረገብነት) እና የሃይማኖት ትምህርት በሠፊው ማስተማር ያስፈልጋል።

ይህ የሀገር (የሕብረተሰብ)፥ የመንግሥትም ችግር ነው እንጂ፥ በግለሰቦች ላይ ብቻ የሚላከክ ኃጢአት አይደለም። የሀገር አስተዳደር የሕብረተሰብን ሥጋዊ እና የስነ ልቡና ጤንነት የሚጠብቅና የሚንከባከብ መሆን አለበት።

መፍረድ ቢኖርብን በሁላችንም ላይ እንፍረድ፡- ለምን ሞራላዊነታችንን በጋራ አልጠበቅንም? ለምን ከሃይማኖታዊ ተቋሞች ራሳችንን አገለልን? ለምን የቤተሰብ ፍቅር አጣን? ለምን ከጨዋነት ብልግናን መረጥን? ለምን የቀድሞውን ጥሩውን ባህላችንን ትተን መጥፎውን ወረስን?

ሸርሙጥና በሀገራችን የገባው ከጣሊያን ጊዜ ጀምሮ ነው ይባላል። አሁንም፥ በየጊዜው፥ በተለያዩ መንገዶች ከውጪ የሚገቡ፥ እንደ ግብረ ሶዶም አይነት ሰይጣናዊ ስነ ምግባሮች እና ልምዶች በየሥፍራዎች ሁሉ እየተዛመቱ ስለሆነ፤ ይህ አካሄድ በዛሬውና በወደፊቱ ትውልድ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት እያየን ዝም አንበል፤ ክፉ ነውና መዘዙ፥ በሽታ ነውና ትርፉ፥ የእግዚአብሔርን ሕግጋት ሲረሱ፤ መንፈሳዊነትን ሲንቁ፤ በምድራዊነት ብቻ ሲገሰግሱ፤ የሥጋን ግልጋሎት ለእርኩስነት ሲያውሉ።

ስለ መንፈሳዊነትና ስለ መንፈሳዊ ኑሮ ካልተሰበከ፥ አለማዊ ኑሮ ሲከብድ በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጡ ግለሰቦች ለገዛ ሕይወታቸው የማይሳሱ፥ ለጤንነታቸውም የማይጠነቀቁ ይሆናሉ። ዘወትር እራሳቸውን ስለሚያሳንሱም፥ በምድር መኖርና መሞት ካለ ምክንያት ይመስላቸዋል። በግዴለሽነት ስለሚኖሩም፥ የዘለአለም ጸጸት የሚሆን ድርጊት ውስጥ ሲገቡ እንኳን አይታወቃቸውም (አይታያቸውም)።

በአያድርስ በሽታ የሚሰቃዩ ሁሉ ስለበሽታው ስለማያወሩ፥ የዝቅተኛነት መንፈስ እየተሰማቸው፥ “የሰው ልጅ ጠባዩ ይቃኛል በግድ፥ እኔስ የቀረልኝ ምድርን

ትቶ መሄድ...” በማለት፥ የተቀረውን እድሜአቸውን እንኳ በሚገባ ሳይጠቀሙበት ያልፋሉ። የሌሎችን ስሜት ለመጠበቅ ሲሉም ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ያፍራሉ። እነኚህን የሚወደዱ ሴቶችና ወንዶች ወጣቶች፡- “ኑ! ከውጪ ሆናችሁ አታልቅሱ፤ ከኛ ጋር አብረን እንሁን” እያለ የሚያደፋፍራቸው ጠፋ።

እራሱ የማያለቅስ፥ አይዟችሁ አታልቅሱ የሚል ጠፋ፤ ለቀስተኞችም የሚያለቅሱት ለሟች ሳይሆን በቁም ለሚሰቃዩት ሆነ። የሟች መለየት በቋሚዎቹ ላይ በአለማዊና በመንፈሳዊ መንገድ ጉዳት የሚያስከትል ሲሆን፥ በዚህች አስደንጋጭና አስፈሪ ምድር ላይ ብቻዬን ቀርቼ እንዴት ሆኜ እኖራለሁ የሚል ውስጣዊ ስሜት እየቀሰቀሳቸው ምርር ብለው ያለቅሳሉ።

አዎ! ልቅሶም ብዙ አይነት ነው። እንጀራ ከሌማቱ እንዳይጠፋ ሠርቶ የሚገባ የልጆች አባት፥ ከውጪ አያድርስን ሸምቶ ሲገባ፥ ባልና ሚስት ሲታመሙ፥ ምግብ ከቤት ሲጠፋ፥ ልጆቹም “ራበን....ራበን..” ብለው ሲያለቅሱ የሚለቀስ ልቅሶም አለ። አንዳንድ ጊዜም እንዲህ አይነቱ ልቅሶ ጅማትን ወጥሮ፥ ትኩሳትና የራስ ምታት በሽታን የሚያመጣ ይሆናል። ኑሮ ከአቅም በላይ ሲሆን፥ ሃዘን ሲበዛና ከድህነት ጋር በጤንነት መኖርም ሲያቅት፥ አእምሮ “ለኔስ የሚቀለኝ ይህ ነው” ይልና፤ መደበኛ ሥራውን ለራሱ እንዲቀለው አድርጎ ይወስናል፤ ሰውንም ያሳንፋል። በዚህን ጊዜ፥ ሰው መደበኛ ሥራውን እየረሳ፥ መቀባጠር ይጀምራል፥ እብደትም ይከተላል።

አንዳንድ እናቶች፥ አባቶች፥ ሽማግሌዎችና አሮጊቶች ስለ ልጆቻቸው በጠና መታመም እንጂ፥ በምን በሽታ እንደታመሙ ስለማይነገራቸው አያውቁትም፤ ግን ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄዱ ከልቅሶ ጋር የተደባለቀ ጸሎት ከማድረግ አያቋርጡም።

የቤተ ክርስቲያን ጸሎትና ስነ ስርዓት ሁሉ ሲገባደድ፥ ሰውም መስቀል ተሳልሞ ወደየቤቱ ሲሄድ፥ እናት ወደ ኋላ ጎተት ብላ ትቀራለች፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ያለበት ስዕል አጠገብ ትቆማለች። ፈራ ተባ እያለች፥ እንደምንም የተቸነከረውን የጌታችንን እና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን እግር ነካ ታደርግና አንገቷን ትደፋለች። እንዲህም ትላለች፡

“እነሆ! ሰማይ ዙፋንህ፥ ምድርም የእግርህ መርገጫ....፤ አንተም እንደ ሰው በጠባብ ደረት ተወስነህ፥ .....አንተም እንደ ሰው በምድር ላይ መከራን የተቀበልክ አምላክ ሆነህ፥...ችግሬንና መከራዬን እያየህ፥.... እያየህ፥...ጌታዬና መድኃኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ምነው ጨከንክብኝ፤ ምነው ጨከንክብኝ፤ ምነው ጨከንክብኝ....።”

አዎ! በኢትዮጵያ ጨለምለም ያለውን ሥፍራ ለተመለከተ፥ ከሰማይ ነጭ ደመና የራቀውን ያህል በረከቱም እንዲሁ ርቋል ያሰኛል። ሰውም ወደ ፈጣሪ አምላኩ ይጣራል። እርሱም ሁል ጊዜ ይሰማል፤ ግን ብዙውን ጊዜ መልስ ሳይሰጥ ዝም ይላል።

ሰው ለሰው ደጅ ሲጠና፥ ተለማኝ ሰው ለማኝ ሲሆን፥.... ይህን ሁሉ እያየ እግዚአብሔር ዝም ይላል?

ሕዝቦች አለቀሱ በልባቸው፤ ምነው እግዚአብሔር ጨከነ ብለው። ደጋግ ሰዎች ግን የማያቋርጥ እርዳታ ያደርጋሉ፤ እነርሱ ችግረኞችን ለመርዳት ሲሉ፥ እነርሱ ራሳቸው ለማኞች ሆነው (ልመናን ተለማምደው)። የእግዚአብሔር ደግነት ከነኚህ ደጋግ ሰዎች ያነሰ ነው እንዴ? ከሰው በላይ ሆኖ የሚያይ አምላክ የሰዎችን ደግነት እያየ የራሱን ደግነት ማሳየት አቃተው ወይ?

እግዚአብሔር ሲያስብ እሩቅ፥ ጊዜውም ረጅም...። አይ!! ..እራሴን አመመኝ፤ ዞረብኝ፤ ምነው ጥንቱን እንደወጣሁ በቀረሁና ባልተመለስኩ አሰኘኝ፤ ምላሴ ተኮላተፈ፤ ተንተባተብኩ፤ መናገርም አቃተኝ።

ከምድራዊነት ራቅ ብዬ ካላሰብኩ ይህን ስሜት ልቆጣጠረው አልቻልኩም፤ አንዳንድ ጊዜ ምድራዊ ስሜታዊ አስተሳሰብ መንፈሳዊነትን ያስረሳልና።

አልገባኝም (አይ! ገብቶኛል፤ የእምዬን ለአብዬ አድርጌው ነው)። አዎ! የእግዚአብሔር ደግነት ከሰዎች ደግነት አያንስም። ደግነቱን በአካላዊ መንገድ ብቻ ሳይሆን፥ በመንፈሳዊም መንገድም መመልከት ያቃተን እኛ ነን። ምንም እንኳን ሥጋ ሲጎዳ ሃዘን የማይቀር ቢሆንም፥ በመንፈሳዊነት ሰማያዊ ደስታ ሊሰማን ይገባል።

የሰው ልጅ መንፈሳዊነቱን ረስቶ ሥጋዊነቱን በማስደሰት ብቻ ከተወሰነ፥ ብዙ ችግር ሊደራረብበት ይችላል። በጨዋነት አድጎ በጨዋነቱ የዘለቀ ሰው የአያድርስ በሽታ አይነካውም። እግዚአብሔር ሰው ጨዋ ሆኖ በኑሮው ተደስቶ ይኖር ዘንድ ይፈልጋል። ጨዋነት ብቻ ነው የመጨረሻ መፍትሔ ሊሆን የሚችል።

*"አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ፥ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፥ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና፥ ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ፥ ርስት ትሆኑልኛላችሁ። እናንተም የካህናት መንግሥት፥ የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ።" ኦሪት ዘጸ.* 19፡1 – 6

**ደብረ ሊባኖስ**

ከደርግ በኋላ የመጣውን የኢሕአዴግ መንግሥት ክፉና ደግ ባሕሬ እያጠናን፥ አንዳንድ በሀገር ልማት የታዩትን እድገቶች እያደነቅን፥ የሕብረተሰቡም መከፋፈል እያስደነገጠን በአዲስ አበባ ጥቂት ቀናት ቆየን።

እኔም ባለቤቴን እንዲህ አልኳት፡- "ተወልደን ባደግንባት በዚህች በኢትዮጵያ ምድር፥ ድሮ በኃይለ ሥላሴ፥ ቀጥሎም በደርግ፥ አሁንም በኢሕአዴግ፥ ብዙ ብዙ አስደሳች እና አስጨናቂ፥ ተስፋ ሰጪ እና ተስፋ አስቆራጭ ትርእይቶችን እየተመለከተን አእምሮአችንን ሳናጨናንቅ አልቀረንም። ወደመጣንበት ከመመለሳችን በፊት አገሩንና ሰውን የት ሄደን በድጋሜ እንመልከት? ከውጪ የሚመጣ ሰውማ (በተለይ ሀገሩን በደንብ የማያውቅ ዳያስፖራ) የአዲስ አበባን ፎቆች፥ የከተማ ዘናጮችንም ያስትውልና፥ ወደ ትላልቅ ሬስቶራንቶችና ሆቴሎች ገብተው የሚዝናኑትን ያይና፥ የኢትዮጵያ ሕዝብም እንዲሁ ያማረበት - ያለፈለት ሊመስለው ይችላል። እስቲ ጊዜአችንን ለመጠቀም ያህል፥ ከአንድ ለየት ያለ ሥፍራ ብቻ እንሂድ" አልኩ።

እርሷም እንዲህ አለች፥ እንደተለመደው ረጋ ብላ፡- "ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ለመሄድ እቅድ አውጥተን የለም እንዴ? ወደዛው እንሂድ እንጂ" አለች።

ይህን ዝነኛ ገዳም ሳናይ አንመለስም ብለን ወስነን ስለነበር፥ ወደ ደብረ ሊባኖስ አመራን።[28]

ሜዳ ሜዳውን ጨርሰን ወደ አዘቅቱ ሥፍራ አቆለቆልን፤ ከዚያም ገዳሙ ካለበት ሥፍራ ደረስን። ምን አይነት ሥፍራ ነው ይሄ?

ከመሬት እስከ ሰማይ በቆመ የአለት ገደል የተገነባ አጥር - በዙሪያው ተፈጥሮአዊ ዝቅጠ አለቶች (ከአሸዋ ድንጋይ እስከ የኖራ ድንጋይ) ድርብርብ ብለው፥ ከበላያቸውም የእሳት ወለድ አለቶችን ተሸከመው፥ ሁሉም ተስማምተው እንደ ግርግዳ፥ በከብነቱ፥ በቁመናው እና በውበቱ ግርማ ሞገስ ያለው።

ምን አይነት ሥፍራ ነው ይሄ? ዝቅ ብሎ ከረባዳው ሥፍራ፥ ባለ ግርማ ሞገሱ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን - እንዲሁም ከዚሁ ሥፍራ የደብረ ሊባኖስ ገዳም።

በሃሳብ ብቻ ሳይሆን፥ ያንን በእንጨት ሳይሆን፥ በድንጋይ አጥር የከበበ ግንብ - ያንን የደብረ ሊባኖስ ገደል - ከታች ከአዘቅቱ ሆነው ወደ ላይ ሲመለከተት፥

---

[28] የማይረሳ ከስተት። በዚያ በውስጡ ገብቼ መሪውን ያነቃነቅሁት፥ ቤንዚን መርገጫውን በእግሬ ልዳስስ ስል የተያዝኩበት የደብረሊባኖሱ አውቶብስ...።

የገደሉ ጫፍ ሰማይን የሚነካ ይመስላል። የገደሉ ግርማ ሞገስ ሌላውን የመሬት ክልል "ሂድ ወደዛ..." ብሎ በማባረር፥ ለራሱ በራሱ የሆነ ሌላ መሬት በመከበብ አዲስ አለም የፈጠረ ነው የሚመስለው።

ገዳማትን ለመመሥረት ምቹ የሆኑ ሥፍራዎችን የሚመርጥ ማነው? ከዚህ ሥፍራስ ምድርና ሰማይን የሚያገናኝ፥ የማይታይ ጎዳና ያለ ነው የሚመስል። ሰላምና ተስፋ የሞላበት፥ ምድራዊነትን የሚከላከል የመንፈሳውያን ምሽግ፥ ይህ ገዳም በእውነት እጹብ ድንቅ ነው።

ከደብረ ሊባኖስ ገዳም በደረስን ጊዜ ይህ ነው የማይባል እረፍት ተሰማን። ገዳሙ የአለምን ችግሮች ሁሉ ሊጋፈጥልን የሚችል መሰለን። እውነት ነው፤ ለጊዜውም ቢሆን፥ የአለምን ችግሮች ሁሉ ተጋፍጦልናል ማለት እንችላለን፤ እዛ በቆየንበት ወቅት ሁሉ፥ ምድራዊ ችግሮቻችንን ሁሉ ረስተን በመንፈሳዊነታችን ብቻ ደስታን ሸምተናልና።

ከዚህ ገዳም ሳለን ሰውነታችንን ሁሉ አቅፎ፡- "አይዟችሁ፤ ከዚህ አለም ውጣ ውረድ እረፍት የምታገኙት በመንፈሳዊነታችሁ ስትንቀሳቀሱ ነው...." የሚል ስሜት ተሰማን (እንጃ፤ መሰለን፤ ብዙ ብዙ መንፈሳዊ ስሜት ታሰበን)። አዎ! የጻዲቁ አባታችን የቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን አጽማቸው የተቀመጠበትን በእጆቻችን ዳሰስ ስናደርግ፥ እኛ በውስጣችን የተሰማንን መንፈሳዊ ስሜት የምናውቅ እኛ ብቻ ነን፤ ሌላ ሰው ሊያውቅልን አይችልም።

ስለ ቅዱሱ አባታችን ልባዊ (መንፈሳዊ) ኩራት የሚሰማን እኛ የርሳቸውን ገድል እናነባለን። በጥልቀት ገብቶን በተረዳነው መጠን የሚሰማንን መንፈሳዊ ሃሴት ማንም አይነጥቀንም። ሌሎች ግን፥ እነርሱ ሳይገባቸው፥ ገብቶናል የሚሉትን ይተቻሉ።

የሰው ልጅ አንጎሉ እውቀቶችን ከውጪ ሸምቶ፥ በስነ አመክንዮ አስልቶ፥ በራሱ ሊገነዘብ የሚችለው እውነት ኢምንት መሆኑን የሚረዱ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን በእምነት ያነባሉ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የታጨቁ እውነቶች የሚገለጡት እውነቶችን በመንፈሳዊ መንገድ መቀበል ለሚቻላቸው ሰዎች ብቻ ይሆናል።[29]

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፥ ስለ ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፥ በኢትዮጵያ ታሪክ 2ኛ መጽሐፍ (1951) ውስጥ በጥቂቱ አስፍረዋል። እርሳቸው የታሪክ ጸሐፊ እንጂ፥ የቅዱሳትን ገድል የሚጽፉ ባለመሆናቸው፥ "የዘመኑ ሰው" ስለ አባታችን የተተረከውን

[29] ብዙውን ትረካ ከአራተኛው መጽሐፍ (ከምድራዊነታችን ባሻገር) ይመለከቷል።

"በቀላሉ የሚቀበለው የመሰላቸውን" ብቻ መዝግበው የተቀረውን ትተውታል። ነገር ግን፥ የአባታችን ታሪክ በደንብ ባለመታወቁ እየጸጸታቸው የሚከተለውን[30] ጽፈዋል፡-

"የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ታላቅነትና መንፈሳዊነት ከሚያስረዱት ከብዙዎቹ ነገሮች ውስጥ አንባቢ ሊረዳላቸው የሚገባው በጳጳስነት ሲገዙ ኖረው፥ በዚያው በዘመናቸው ጳጳስ እንዲመጣ መፍቀዳቸው፥ ከመጣ በኋላም፥ ለሥልጣኑ ሳይጓጉ፥ ሳይቀኑም፥ ጠብና ጦርነትም ሳያስነሱ፥ በሰላም አስረክበው፥ እርሳቸው ወደገዳማቸው መግባታቸውን ነው።"

ይህንኑ በማስመልከት፥ በገድላቸውም የሚከተለው ተዘግቧል፡-"... አባ ዮሐንስ ከግብጽ ከመጣ በኋላ፡- "ለኔ ለምጻተኛው ይህ ሥራ አይገባኝም፥ ይህንስ የምወደው ከሆነ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ቀድሞም ታዝዤ ነበር፤ በመልአኩም እጅ ክህነት የሚሰጥበትን መጽሐፍና ቅብን ሜሮኑን ልኮልኝ ነበር፤ እነሆ እኒህ ናቸው" ብሎ አሳየውና ለሱ ሰጠው።" ገድለ ተክለ ሃይማኖት (ታህሳስ 15 ቀን 1946 ዓ.ም. ገጽ 205 – 206)። እንዲህ አይነቱ ቅዱስ አባት የተወለደባትን ሀገራችንን "አንቺም እኮ ቅዱስ ነሽ!" ብንላት ምን ይከፋል?

በደብረ ሊባኖስ በቅዱሱ አባታችን ስም የታነጸው ቤተ ክርስቲያን እጅግ የተዋበ ነው። እኛም ከገዳሙ አድረን በማግስቱ በባለቤቴ እናት (እናቴ) እየተመራን፥ በጧት ሄደን ጠበል ተጠመቅን። ካስቀደስንም በኋላ፥ መንፈሳውያን ድሆች ወደሚገኙበት፥ ከቤተ ክርስቲያኑ በስተሰሜን ካለው ሥፍራ ሄድን። ከዚህም ሥፍራ በደረስን ጊዜ እጅግ በጣም ብዙ ድሆች በእንጨትና በአሮጌ ጨርቅ በተሠሩ ትናንሽ ቤት መሳይ ዳሶች ውስጥ ትፍግፍግ ብለው ተመለከትን። አንዳንዶቹ ቁጭ ብለው፥ አንዳንዶቹም ተኝተው ይታያሉ። የታመሙትን ካልታመሙት መለየት አይቻልም። ሁሉም በሥጋ ቀሰስተኞች ስለሆኑ፥ ወደ መንደር ሄደው የሚለምኑ አይደሉም።

በመካከላቸው ያልታመሙ (ጤነኞች) ቢኖርባቸውም፥ የሚበሉት ምግብ የልባቸው ትርታ እንዳያቋርጥ የሚረዳ እንጂ፥ የእግር ጉልበት ሰጥቶ ከቦታ ቦታ የሚያላውስ፥ እየጮሁም ለመለመን የሚያበቃ የእስትንፋስ ኃይል (አቅም) የሚሰጣቸው አይደለም። እራሳቸውን አሳንሰው፥ ካለ ምንም ምድራዊ ፍላጎት፥ ድህነትን ተቀብለው፥ በቤተ ክርስቲያን ዝማሬ ተማርከው፥ ከፈጣሪያቸው ጋር በጸሎት እየተገናኙ ይኖራሉ፤ በሥጋው የተጎዳ ሰው ከቀደሙ መንፈሳውያን ጋር የተያያዘ መንፈሱ ያጸናዋልና።

[30] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ 1951 (የኢትዮጵያ ታሪክ 2ኛ መጽሐፍ፥ ገጽ 19)።

ከደብረ ሊባኖስ ገዳም የሚመጡና ከዚሁ የሚቀሩ ወንዶችና ሴቶች፥ የተለያየ ምድራዊ ሕይወትን ያሳለፉ ናቸው። ምድራዊነት ሲገፋቸው፥ እነርሱም ከምድራዊነት ሲርቁ ሲርቁ ነው ከዚህ ከደብረ ሊባኖስ የደረሱትና የቀሩት።

ታዲያ፥ የእያንዳንዱ ታሪክ ቢመዘገብ፥ የጠፈር አካላት ተመሳጥረው፥ ልክ ወደዚህ ቦታ እንዲመጡ ያስገደዷቸው ይመስል፥ የትም ቢሄዱ የትም፥ ወደ እግዚአብሔር ካልተጠጉ በስተቀር እንደማይሆንላቸው እርግጠኞች ሆነው ስለቆዩ ነው ከዚህ ሥፍራ ይመጡ ዘንድ ግድ የሆነባቸው። በገዳሙ አባቶች መንፈሳዊ እይታ ከዚያ እንዲኖሩ ስለተፈቀደላቸው ነው፥ መጨረሻቸውን ከዚሁ ሥፍራ ያበጃጁት።

የደብረ ሊባኖስ መንፈሳውያን ከቤተ ክርስቲያን ተጠግተው፥ በገዳሙ የድሆችን መንደር መሥርተው፥ በአባታችን መንፈስ ክልል ተወስነው፥ ከውጪው አለም ተገልለው፥ በመጽዋቾች እርዳታ ተንጠልጥሎ ነፍሳቸው፥ በረሃብ በሕማም ሲጣደፍ ሞታቸው፥ ሰማይ ቤት ለመሄድ፥ ዛሬና ነገን ተጠባብቀው፥ ሌት ተቀን ጸልየው፥ ሌት ተቀን ጸልየው....፤ ይህን የሚመስል ነው ምድራዊ ሕይወታቸው፤ በምድራዊ አይኖቻችን ስናያቸው።

ወደ መንደር ስንሄድ፥ ብዙ ለማኞችን ተመለከትን። እነኚህ በምድራዊነታቸው ተስፋ ያልቆረጡ፥ ነገር ግን፥ በመንፋሳዊነታቸው ጥንካሬ የጎደላቸው፥ ስለዚህም፥ ምድራዊ ጉስቁልናን መቋቋም ያልቻሉ ነው የሚመስሉት። እነኚህስ፥ በሚለምኑበት ጊዜ፡- "እንደምንም ብዬ በምድር ልኑር እንጂ፥ ስለማላውቀውስ ሰማያዊ አለም ብዙ አልጨነቅም.." እያሉ የሚያስቡ ነው የሚመስሉት። ነገር ግን እነሱም በማይለምኑበት ጊዜ፥ ነፍስና ሥጋቸውን ከቤተ ክርስቲያን ጸሎት ማላቀቅ አይፈልጉም። ስለዚህ፥ ከዚያ የቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ርቆ መሄድ አይሆንላቸውም።

አዬ!! ለኛስ ከባድ ነው የሚሆን፥ እንዲህ አይነት ኑሮ፥ ካለ ፍርኃት ተረጋግቶ፥ ከምድራዊ ውጣ ውረድ ተለያይቶ፥ በልዝብ ቋንቋ ተግባብቶ፥ ምስጋናን አብዝቶ፥ የተገኘውን በልቶና ጠጥቶ፥ በማወቅና አለማወቅ ትንንቅ፥ ትእግስትን አብዝቶ፥ እጅግ ይከብዳል ከዚህ ብዙ መቆየት፥ ሕዝቦች ሁሉ እንዲህ በርቀት ከደቀቁበት፥ ግን ከፍታና ዝቅታ በጠፋበት።

ባለቤቴ በነኚህ ድሆች ልቧ ተነካ። ለድሆች የመደብነው ገንዘብ ወዲያውኑ አለቀ። "ከእንግዲህ ከዚህ ሥፍራ መቆየታችን ለምንድነው? በይ እንሂድ" አልኩ ኮከቤን። እርሷ ግን ልቧ ተንጠለጠለ። ኮከቤ ደግ ሴት ናትና፥ መንፈሷን ከዚህ ሥፍራ ልታላቅቀው አልቻለችም (አልፈለገችም)። በተለይ አንድ ሰው፡-

"ኑ እባካችሁ፥ ድሆችን ለመርዳት የማደርገውን ተመልከቱልኝ" እያለ ሲጋብዘን፥ ኮከቤ ሰውዬውን ተከትላ መሄድ ፈለገች። እኔን ደግሞ አንዱ ዲያቆን፡-

"እዚህ ደርሰህ አሰቦን (አባታችን ቆመው የጸለዩበትን ዋሻ) ሳታይ ትሄዳለህ?" ይለኛል። ገድላቸውን ሳነብ ያነባሁት እንባ ትዝ አለኝና፥ ተመልሶ እንደሚመጣ ሰው ሆኜ ችላ አልኩት።

ኮከቤም፡- "እነኚህን ድሆች በተደራጀ መንገድ መርዳት ይቻል ይሆናልና፥ ወደዚህ ሰውዬ እንሂድ" ብላ ጨቀጨቀችኝ። እኔም፡- "እባክሽ ጊዜም የለን፤ አውቶብሱም ያመልጠናልና እንሂድ" ብዬ አከላከልኳት። ቅር እያላት አውቶብሱ ውስጥ ገባን። መንገድ ስንጀምር፥ እህ! እያልን..... በሃሳብ ተዋጥን። የባለቤቴን መንፈሳዊ ቅንአት እንዳልነካም እየተጠነቀቅሁ ቀስ ብዬ ተናገርኩ፡-

"ኮከብዬ፤ እኔም እኮ ምኞቴ የሥጋ ያይደለ፥
ምነው መንፈሴ ከደሆቹ ወገኖቼ ጋር በተቀላቀለ።"

እርሷም እንዲህ አለች፡-

"እንዳየሽውና እንደተመለከትከው፥
በኢትዮጵያችን በዝቷል ድሃው።
የተማረውም ያልተማረውም፥ ድህነትና ልመናን ሰልጥኖበት፥
ሆድ ሲርበው፥ እንጀራ ልመና፥ ከቤት ወደ ቤት ጉትት...ጉትትትት።
በጎስቋላ ሥጋ - በተጨማደደ ፊት፥
ውስጣዊነት ሲተካ በውጫዊነት፥....
የኛስ ኑሮ ምንድን ነው ከዚያ ማዶ፤
ከሀገር ከወገን ርቆ፥ ከባዕድ ሀገር ተሰዶ፤
ምንድነው የኛ ሩጫ፥ ለሥጋ ብቻ ተስገብግቦ፥
ዘለአለማዊነትን አርቆ፥ ጊዜያዊነት አቅርቦ።
ገንዘብ ለመሥራት ተጣድፎ፥
ፍላጎትን አብዝቶ፥
በፍቅረ ነዋይ ተጠምዶ፥
መንፈሳዊነትን ረስቶ።
የፈረንጅ ሀገር ምግብ በልተን ጠገብን፤
ከሁሉም በላይ ተራብን።

እንዴት እናርካ ጥማችንን?

ምን እናድርግ በኑሮአችን፤

ተወስነን እንዳንቀር ለራሳችን።

ከእንግዲህስ አቅማችን በፈቀደ፥ እኔና አንተ እነኚህን የደብረ ሊባኖስ ድሆች እንርዳ፤ እስቲ አስብበት፤" አለችኝ በአንክሮ። እኔም "እሺ...." አልኩ፤ ከልቤ (አብረውኝ እሺ የሚሉ ሰዎች እንዲኖሩ እየተመኘሁ)።

የገዳሙን ሥፍራ ለቀን ወደአቀበቱ ከፍ ከፍ እያልን ስንወጣ፥ ከሩቅ የሚጣራ "ነገር" ያለ መሰለኝ።

የጻድቁ አባታችን ልጆች የሚኖሩበት የድሆች መንደር - በደብረ ሊባኖስ ያለ መንፈስ እኛን ከቶ ሊለየን የፈቀደ አልመሰለኝም።

አይረሳምና ሥራቸው፥ ድሆችን የሰበሰበው መንፈሳቸው፥

እሱው ሳይሆን አይቀርም ከሩቅ የሚጣራው፥

የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደግነታቸው።

ማንም ይሁን ማን የሰው ደግነቱ፥

የሩቁን የሚስብ፥ ፍቅር ኃያል ነው ስበቱ፤

ደግ ሰው እጁን ሲዘረጋ መታየቱ፥

መንፈሳዊ አብሮነት ነው ሕይወቱ፤

ፍቅር፥ ደስታ ነው ውጤቱ።

እህህ!..ወይ የጊዜ ርዝመት፥

ቅጽበት እንደ ሺህ ዓመት።

ሲያደናቅፍ ደግነት፥

አብሮ መኖር ሲያቅት፤

ስጦታን መቀበል፥ መስጠትም ሲያዳግት።

አይከለከልም ምኞቴ፥

የጻዲቁን አባት

መንፈሳዊ ሕይወት መመኘቴ፥

ለኔ ብቻ አይደለም፤

ለኢትዮጵያችን ሁሉ ቢዳረስ፥

በከተማም፥ በገጠርም
ያ የደበረ ሊባኖስ ደግ መንፈስ።

በቃ! በቃ! በቃ! ምድራዊት ኢትዮጵያ፥
በእውነት አንቺ ነሽ መስተዋት፥
የሰማዩን መመልከቿያ።
ኪሩቤል የሰይፍ ነበልባል የያዘብሽ፤
በምድርና በገነት መካከል፥
አንቺ ኬላ (ድንበር) ነሽ።
ለአዳም ልጅ ለሁሉ፥
የዘለአለም ምሕረቱ እንዲጸናልሽ፥
የማርያም ጸሎቷ አይለይሽ።

እምዬ ማርያም፥ ቤዛይት አለም፥
እግዚእትነ ማርያም፥ የምንል ልጆችሽ፥
እኛ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የምንወድሽ፥
ተማጽነንብሻል ዛሬ፥ ስለፍቅርሽ፥
ምልጃሽን አታቋርጪ፥ እንዳንጠፉ ከሃሳብሽ።

በመሬት የመኖር ግዴታችን እነኚህን ድሆች አብረናቸው እንድንቆይ አላደረገንምና፤ ቅር ቅር እያለን ተለየናቸው። በዛች አንድ ቀን ጧት፥ የብዙ ድሆች መንፈስ ሞቅታ ከዚህ ከምናየው አካላዊ አለም የተለየ ስሜት አሳድሮብን አዲስ አበባ ገባን፤ ከዚያም ጥቂት ቀናት አድረን በግድ ወደ ፈረንጅ ሀገር ተመለስን።

**ጸሎት**

ቸሩ እግዚአብሔር አምላካችን፥
በመንፈስ - በሥጋ ፈጣሪያችን፤
ስንጨነቅ አንተ ነህ መጽናኛኢአችን፤
ስንፈራም አንተ ነህ ብርታታችን፤
ስንጠቃ አንተ ነህ መከታችን፤
አለማወቅ ሲያሳውረን፥ አንተ ነህ ብርሃናችን፤
አንተው ነህ እውነት - መመሪያችን።

አቤቱ አምላካችን፥ ተስፋችን - መመኪያችን፥
ባንተ መንፈስ ክልል ምንጊዜም እንድንሆን፥
ጠብቅ ልጆችህን፤ ተመልከት ፍጥረትከን።
እምነት ከእውነት አልሰምር ቢለን፥
በአለማዊነታችንም እንቅፋት ቢበዛብን፥
ምድራዊ ችግሮች ተስፋ ቢያስቆርጡን፥
ቸሩ እግዚአብሔር አምላካችን፥
ባንተ ነው ትኩረታችን፤
ባንተ ነው ተስፋችን።

ከጨለማ/ከጉድጓድ አውጣን፥
ቀናውንም መንገድ አሳየን፤
ወደ አንተ ይሁን ሕይወት አቅጣጫችን።

## ታሪካዊ ክስተቶች

በሀገራችን የተፈጸሙ ፖለቲካዊ ክስተቶች(ኩነቶች) ሁሉ ምክንያት፥ መነሺያና መድረሻ እንዳላቸው ይታወቃል። ሁሉም በብዛት እና በዝርዝር ቢጠቀሱ፥ እንደ ሰዉ አመለካከት፥ አጨቃጫቂና አወዛጋቢ ነው የሚሆኑት። ሆኖም፥ ታላላቅ እና ወሳኝ ከሆኑ አያሌ ኩነቶች ውስጥ፥ ማንም በቀላሉ የሚያስተውላቸውን፥ አወዛጋቢ ያልሆኑትን፥ ጥቂቶቹን ብቻ እየመረጥን፥ በእነኛ ላይ በመመርኮዝ፥ ወደ እውቀት እና ወደ እውነት ለመጠጋት ፈልገናል። ይህንን ለማድረግ የፈለግንበት ዋናው ምክንያት፥ "ይህ ለምን ተፈጸመ? ይህስ ለምን ተደረበ? በኢትዮጵያችን ሕዝቦች ላይ በተከታታይ ለሚደርስባቸው ስቃይ እና መከራ ሰማያዊ ምክንያቶች ይኖር ይሆን?" በማለት እራሳችንን እንድንጠይቅ ነው።

ነገሮችን በጥልቀቱ ለመመርመር ስንነሳ፥ ምናልባት በግልጽ ከሚታየው እና በአካላዊው አለም በቀላሉ ከሚተረጎመው እየተሻገርን፥ ምድራዊ ትርጉም ወደማይሰጠው መንፈሳዊ አለም ውስጥ ጥልቅ ማለትን ያስመኘን ይሆናል። ይህስ ቢሆን፥ ማን ከልካይ አለብን? ወደ አንድ አቅጣጫ ምልከታዎች ስናመራ፤ አዎ! ነገሮች ከመጥፎ ወደመጥፎ እየተሸጋገሩ ሄደዋልና፤ ምንጊዜም ነጻ አስተሳሰብ ተፈጥሮአዊ መብታችን መሆኑን ሳንርሳ፥ አንዳንድ አንኳር አንኳር የሆኑ ፖለቲካዊ እና ታሪካዊ ክስተቶችን በአጭር በአጭሩ እንመልከት።

## የቀዳማይ ወያኔዎች ትግል

በንጉሣዊው የኃይለ ሥላሴ ዘመን የተካሄደውን የቀዳማዊ ወያኔዎችን ጦርነት ያስታውሷል። የጥንቶቹ ወያኔዎች ከምሥራቅና ከደቡብ ምሥራቅ ትግራይ የተውጣጡ ጦረኞች ነበሩ። እነርሱ፥ ምናልባት ቁልጭ ያለ የፖለቲካ መመሪያ ባይኖራቸውም፥ ሕዝቡ ከሚችለው በላይ ቀረጥ ስለተጨመረበት፥ በንጉሡ ከተጫነባቸው የኢኮኖሚ ውጥረት ለመላቀቅ ነበር ታጥቀው የተነሱት።

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር፥ የጣልያን መንግሥት በ1890 ዓ.ም. ኤርትራን፤ በ1936 ዓ.ም. ኢትዮጵያን፥ ሶማሊያንም ጨምሮ ሲቆጣጠር ነበር። በ1941 ዓ.ም. እንግሊዞች እና ኢትዮጵያኖች በመተባበር ጣሊያኖችን ከዛ አካባቢ አባረሯቸው።

ጣሊያን ከኢትዮጵያ ተባሮ ሲወጣ፥ ከኤርትራም ነቅሎ እንዲወጣ ስለተፈለገ፥ ከ1941 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1952 ዓ.ም. ድረስ፥ ኤርትራ ለአስር ዓመታት ያህል በእንግሊዝ ጠባቂነት (protectorate) ሥር ነበረች። በዚህን ጊዜ (በ1943 ዓ.ም.) ነበር የቀድሞው የወያኔ ጦርነት የተቀሰቀሰው። የትግራይ ተቃዋሚ ኃይላት (ቀዳማዊ ወያኔዎች) በንጉሡ በኩል የተሰለፈውን የኢትዮጵያ ጦር ክፉኛ

ስላጠቁ፥ የትግራይም መገንጠል የሚያሰጋ ስለነበረ፥ እንግሊዝም በዚህ ሳቢያ ትግራይንም ከኤርትራ ጋር በአንድነት በበላይ ጠባቂነት (protectorate) ሳቢያ አስተዳድራለሁ እንዳይል፥ በወቅቱ ፈጣን እርምጃ መውሰድ አስፈለገ።

ስለዚህ፥ በንጉሡ ትእዛዝ፥ ቀዳማይ ወያኔዎች በአየር ኃይል ተደበደቡ። የወያኔዎች አመጽ ከሸፈ፤ እራስን በራስ ለማስተዳደር የተነሳሱት፤ ለመገንጠል የፈለጉም አልተሳካላቸውም። የወያኔዎች ትግል ተዳፍኖ ቆይቷል።

ባላባቶች ከያለበት እንዳይነግሡ፥ እንዳትፈረካከስ ሀገራችን፥ እንዲጠናከር ማእከላዊው መንግሥታችን፥ በወያኔ አሳቦ እንግሊዝ እንዳይወስድብን ትግራይን፥ እንዳይጋራ ሥልጣን የንጉሡን፥ በቦንብ ተደበደቡ ወገኖቻችን።

በቀዳማይ ወያኔዎች ጦርነት ሳቢያ የትግራይ ሕዝቦች እንደ ጠላት በቦምብ መደብደባቸው እጅጉን ያሳዝናል፤ ይጸጽታልም። ሆኖም፥ "እሾክን በሾክ" እንዲሉ፥ ፈጣን እና የማያዳግም እርምጃ ስለተወሰደ፥ በንጉሡ ዘመን ኢትዮጵያችን ሳትከፋፈል፥ በአንድነቷ ጸንታ ቀረች።

ከዛ በኋላ (በኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት) ለአንድነት በታገሉ ኤርትራውያን አርበኞች የአንድነት ፓርቲ (Unionist Party) ብርታት እና በኢትዮጵያም ከፍተኛ የመዋሃድ ፍላጎት ምክንያት፥ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ተዋሃደች (አንድ ሆነች)።

ሆኖም፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አንድነትን ያልፈለጉ ኤርትራውያን፥ ለትጥቅ ትግል እራሳቸውን አዘጋጁ። ኤርትራን ነጻ ለማውጣት መጀመሪያ ጀብሃ በኋላም ሻዕቢያ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ጦርነት ጀምረዋል።

***<u>የዳግማዊ ወያኔዎች ትግል/የኤርትራ መገንጠል</u>***

የበኋላ ወያኔዎች (ዳግማዊ ወያኔዎች) መንፈስም ከቀዳማዊ ወያኔዎች መንፈስ የተወረሰ (የቀጠለ) ይመስላል። ዳግማዊ ወያኔዎችም እንደ ቀዳማይ ወያኔዎች ተበድለናል ባዮች ስለነበሩ ይሆናል በስማቸው የተነሱት።

እንደ ኢ.አ. ከ1966 ዓ.ም. በፊት ጀምሮ፥ የኢሕአፓ የጦር ግንባር የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ) በሰሜን ትግራይ ውስጥ፥ አሲምባ በመባል ከሚታወቅ ሥፍራ፥ ታላቅ ምሽግ መሥርቶ ነበር። የዛን ጊዜ፥ የትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር (ትሕነግ - ሕወሃት ወይንም ወያኔ) በኋላም የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግንባር (ኢሕአዴግ) በወቅቱ በከፍተኛ ደረጃ በጦር ተደራጅቶ ከነበረው የኤርትራ ነፃ አውጪ ጋር ግንባር ፈጥረው ነበር።

የኤርትራ ነፃ አውጪዎችም የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው በማለት ትሕነጎችን (ወያኔዎችን) ተጠቀሙባቸው። ወያኔዎች ከኤርትራ ነፃ አውጪዎች ጋር ሲወዳጁ፥ የኢሕአፓን የጦር ግንባር (ኢሕአሠን) "እናንተ ኤርትራ የኢትዮጵያ ኮሎኒ (ቅኝ ግዛት) መሆኗን ከዳችኋል፤ ስለዚህ ኤርትራ ነፃ እንድትወጣ ፍላጎት የላችሁም" በማለት፥ ትንኮሳ ጀመሩ። ቀጥሎም፥ "እናንተ የምትታገሉት ለኢትዮጵያ፥ እኛ የምንታገለው ለትግራይ ስለሆነ፥ ሂዱና እዛው አገራችሁ ሆናችሁ ታገሉ..." በማለት፥ እና በሌሎችም በጥቃቅን ቅራኔዎች ጠመዷቸው፤ ቅራኔውም እየተባባሰ መጣ።

ትሕነግ እንደ አንዱ የፖለቲካ መመሪያ አድርጎ የወሰደው የኤርትራ መገንጠል፥ ከኢሕአፓ መመሪያ ጋር ተጻራሪ በመሆኑ፥ ቅራኔው እየሰፋ ሄደ። ከእንደዚህ አይነቱ የፖለቲካ ድርጅት መወዳጀት ያቃተው የኢሕአፓ የጦር ግንባር (ኢሕአሠ) ከትግራይ ለቆ መውጣት ግድ ሆነበትና፥ ከትግራይ በስተቀር ወደ ሌሎች ሥፍራዎች ሁሉ፥ ኢሕአሠ ሄደ፥ ተሰማራ።[31]

ከትግራይ ተባሮ ጎንደር፥ ከጎንደርም ተባሮ ሱዳን የገባውም፥ በየጫካው የተጣለው፥ የኢሕአፓ ወታደር (ኢሕአሠ) ቀባሪ ያጣው፥ እንዲሁም ከመላው ኢትዮጵያ በየአገሩ የተሰደደው፥ የሞተውም፥ ያልሞተውም፥ አሁንም በመንፈሱ እውነትን እንደጨበጠ ነው ያለው። ብሩህ ተስፋ የሚታያቸው፥ ተነሱ - ተነሱ እያሉ የሚቀሰቅሱን፥ አሁንም የሚታገሉ ብዙሓን ናቸው። ወድቀን አልወደቅንም፤ ብዙ ጎበዛዝት አሉ ከጎናችን።

ከሰላሳ ዓመታት ጦርነት በኋላ፥ በወያኔዎች አጋዥነት፥ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ራሷን የቻለች ሀገር ሆነችና ነፃነቷን አወጀች።

---

[31] ይህንን ጉዳይ በአግባቡ የሚተርኩ በኢሕአሠ የተሳተፉ ናቸው።

የኢትዮጵያን ሕዝብ ቁልቁል ወደ ረመጥ የነዳ፥ ፋሺስታዊው ደርግን የጣለ ወያኔ፥ ገና ከጥንቱም ከኢሕአፓዎች ጋር ባይጣላ፥ እነርሱንም አቅፎ፥ አብሮ መሥራት ቢችል ኖሮ፥ ምናልባት ይህ የርህራሄ ጎኑ አንድ ሊያስወድደው የሚችል መልካም ምግባር ይሆንለት ነበር። ይህ ሳይሆን ቀረና፥ በጊዜው የነበሩ ሌሎችም የፖለቲካ ኃይላት ሙሉ በሙሉ ከሕዝቦች ጋር ሳይሆኑ ቀሩና፥ "ሌሎችም ኩነቶች" በሀገራችን ተፈጠሩና፥ ዳግማዊ ወያኔ ለብቻው አገሪቱን በሞላ ተቆጣጠረ። "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ባይሆንም፥ የጠላቴ (የደርግ) ጠላት ወዳጄ ሊሆን ይገባዋል፤" በማለት አብሮ ለመሥራት የተመኙ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶችም ከወያኔዎች ጋር ሆኖ ሀገር መምራት አልቻሉም።

ወያኔዎች ሙሉ ኢትዮጵያን ሲቆጣጠሩ፥ ትሕነግ የሚለው መጠሪያቸው ቀረና ኢሕአዴግ (ኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር) ሆነ።

ኢትዮጵያ ከደርግ አገዛዝ ስትላቀቅ፥ ኤርትራም ነፃነቷን ስታውጅ፥ በሁለቱም አገሮች ጦርነት አብቅቶ ሰላም የሰፈነ ይመስል ነበር። እየቆየ ሲሄድ፥ በተለይም ከባድማ ጦርነት በኋላ፥ የሚዋደዱ ሕዝቦችን የሚያጣሉ የሀገር መሪዎች፥ እነርሱ ከአገራቸው ፍቅር ይልቅ የገዛ ሥልጣናቸውን የሚያስቀድሙ በመሆናቸው፥ ሰላም ደፈረሰ።

ለአድዋ ሰዎች አስመራ ቅርባቸው፥ የኖሩበት ሥፍራ ራማን ተሻግረው፥ ባህላቸው አንድ ነው፥ መግባቢያ ቋንቋቸው። ለአክሱምም ሰዎች ጎንደር ቅርባቸው፥ የኖሩበት ሥፍራ ተከዜን ተሻግረው፥ ባህላቸው አንድ ነው፥ መግባቢያ ቋንቋቸው።

ኤርትራን ከትግራይ ማነው የገፋው? ጎንደርን ከትግራይ ማነው የገፋው? አብሮ እንዳይኖር ሕዝቡ፥ ማን ለማን ነው? ጠላት የሆነው።

ኤርትራ ነፃነቷን ስታገኝ በደስታ ብዛት ያለቀሱ እንደ ደስታቸው አልሆነላቸውም። መቼም ሰው ሆኖ ወገን ለወገኑ የማይቆረቆር የለምና፥ "ሠፊው የኤርትራ ሕዝብ በምን ሁኔታ ውስጥ ነው ያለው? ከፍቶታል ወይንስ ደልቶታል?" እያልን ስንጠይቅ ቆይተናል። ከግለሰቦች የምናገኘው መልስ ይለያያል።

አንዳንድ ሰዎች፥ "አብዛኛው ኤርትራዊ ለብዙ ዓመታት ሲያልመው የነበረውን ፈጣን እድገት ሳያገኝ መቅረቱ ቅሬታ ውስጥ ሳይከተው አልቀረም" ይላሉ። አንዳንዶች ደግሞ፥ "ሠፊው የኤርትራ ሕዝብ እንደተመኘነው በይደላውም፥ ሰላሙን አግኝቷል፤ አይራብም፤ አይጠማም። የመንግሥቱም ስርዓት በሕዝቦች መካከል ከፍና ዝቅ የሚፈጥር ስላልሆነበት፥ በእኩልነት ያገኘውን ነጻነቱን እያጣጣመ፥ በመጠኑ ይኖራል" ይላሉ።

አንዳንዶች፥ በተለይ በእድሜ ገፋ ያሉት ኤርትራውያን፥ አሁንም ስለ ኢትዮጵያ ይቆረቆራሉ፤ እንዲህም ይላሉ፡- "ሕዝቦች ታግለው የሚፈልጉትን ቢያገኙ የሚጠላ የለም። ግን ወንድም የገዛ ወንድሙን እንዲጠላ የሚያደርግ በውሸት ላይ የተመሠረተ ፖለቲካ በጣሙን ያሳዝነናል። ሰው ግን እውነትን በራሱ ፈልጎ በማግኘት ፋንታ፥ ሌሎች የፖለቲካ አቀንቃኞች የሚሉትን ብቻ እየሰማ በጥላቻ አለም ውስጥ ይዘፈቃል። ብዙ ሰው ከፍርኃት የተነሳ የልቡን ከመናገር ይቆጠባል። በአንድ ባህልና ልምድ፥ በአንድ ሃይማኖታዊና ስነ ልቦናዊ አመለካከት ያደጉ ወንድማማቾችን የሚያለያይ፥ በውሸት ላይ የተገነባ እኩይ የጥላቻ ፖለቲካ ነው ከሁሉም የሚያስከፋው። አሁንም፥ ደግ ጊዜ ቢመጣና ኤርትራ እንደገና ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ ጋር ብትዋሃድ ደስ ይለናል" ይላሉ።

አዎ! በኢሕአፓ ፓርቲ ውስጥ አብረውን ሲታገሉ የነበሩ ትውልደ ኤርትራ (ኢትዮጵያውያን)፥ የሁላችንንም ችግሮች የሚፈታ ርዕዮተ አለም አገኘን በማለት፥ ስለሁላችንም ብለው ታገሉ እንጂ፥ ኤርትራን ከኢትዮጵያ በመገንጠል እሳቤ እንዳልተነሱ "እኛ" እናውቃለን።

ኤርትራ ከእናት ኢትዮጵያ ተገንጥላ የብቸኝነት ነጻነቷን ብታውጅም፥ በታሪካዊ ጉዞዋ ሁሉ፥ የኤርትራ ሕዝብ መንፈስ ከኢትዮጵያውያን መንፈስ ተለይቶ እንደማይታወቅ ብዙዎቻችን ይገባናል።

ነፃነት ሲባል ስሙ አንድ፥ ግልጋሎቱም የጋራ የመሰላቸው፥ እጅግ አዝነዋል ከልባቸው፤ "ኢትዮጵያ ስትጠላ፥ የኤርትራም ነፃነት ትርጉም ያጣል" ብለው። ቅር ያላቸው፥ ሀገር ለቀው የወጡ፥ እንደገና ስደትን መርጠው፥ የሰላምና የፍቅር መርሆ ይዘው፥ "ካብ መንጎ ኤርትራ፥ ካብ መንጎ ትግራይ፥ ምዕብዳን ምዕብዳኑስ አውሮፓ ይሃሸይ" ብለው።

እንደወጡስ ከዛ አይቀሩም፤ ይመለሳሉ ካገራቸው፤ ለአንድነት ይቆማሉ፤ ጎሳና ሃይማኖት ሳይለያያቸው። አንድላይ እንቀድሳለን፥ ልጆቻችን ከልጆቻቸው፥ ይዋሃዳል እጣናችን ከእጣናቸው፥ አንድ ላይ እንሰግዳለን፥ በመስጊዳችን በመስጊዳቸው፤ ይህ ብቻ ነውና መፍትሔው፥ በሥጋውም በመንፈሱም ለሚኖር ሰው።

ምናልባት እስከዛሬ በተፈጠሩት አወዛጋቢ የፖለቲካ ኩነታዎች (ክስተቶች) ምክንያት፥ ለወደፊት የሚፈጠረው በግልጽ ተለይቶ ላይታወቅ ይችላል እንጂ፥ እኛስ በሚሰማን መንገድ ቢሆን፥ ለወደፊቱ፥ ካለ ኢትዮጵያ ኤርትራ ብቻዋን መሆን ይከብዳታል። ኢትዮጵያም ካለ ኤርትራ ብቸኝነት ይሰማታል።

መሰናክሎች ከታለፉ በኋላ፥ ለሁላችንም የዴሞክራሲ፥ የአንድነትና የሰላም ጊዜ በቅርብ መምጣቱ አይቀርም፤ እግዚአብሔር ለእርሱ የሆኑትን ሕዝቦች በምድር ላይ በሰላም ለመኖር እንዲችሉ ያደርጋቸዋልና።

ጠንቋይ ያሰማራቸውን እባቦች የዋጣቸው፤ የኤርትራንም ባሕር ለሁለት የከፈለ የሙሴ ብትር፥ አሁንም ሥራውን ይሠራል በስውር። ከእንግዲህ፥ ከኢትዮጵያ ብቻ አይደለም፥ ከኤርትራም ተነቅሎ ይወጣል እርኩስ መንፈስ፤ ወዶ ሳይሆን በግዱ።

በሕዝቦች መካከል የሚኖር የእግዚአብሔር ፍቅር የተጣሉትን ያስታርቃል፤ መልሶም አንድ ያደርጋቸዋል። የኤርትራም ሕዝብ የቅርብ ጊዜ ያይደለ፥ የሩቅ ጊዜ ታሪኩን ሲያስታውስ፥ በመንፈስ የሚቀርበውን ሕዝብ ከአካባቢው ይፈልጋል፤ የዛን ጊዜ፥ ኤርትራችንም፥ ኢትዮጵያችንም በነጻነትና በእኩልነት ላይ በታነጸ አንድነት፥ የሚጠብቃትን የአምላኳን ሰላምና ፍቅርን ይዛ እንደምትዘልቅ “ይህ መጽሐፍ” ያውቀዋል።

ያቺ የነፃነት፥ የፍቅር፥ የሰላም፥

የእኩልነትና የአንድነት ባንዲራ፥

የኢትዮጵያ ብትባል፥ ወይንም የኤርትራ፤

ለአንድ ሕዝብ ታጭታ የተቀመጠች ሙሽራ፥

አሁንም አለች ከኛ ጋራ - በአይምሯችን ተከብራ።

**የዳግማዊ ወያኔዎች ጦስ**

በ27 ዓመታት የኢሕአዴግ (ወያኔ) የአገዛዝ ዘመን ውስጥ መጠነኛ ለውጦችን ብናስተውልም፥ በሁሉም አቅጣጫ እንዳሰብነው አልሆነም። በታሕታይ መዋቅሮች (እንደ ቤቶች እና መንገዶች የመሳሰሉ ጥቃቅን ለውጦች) ላይ መጠነኛ መሻሻል ተደርጓል። ላዕላይ መዋቅሩን ጨፍድደው የያዙት አመራሮች ግን፥ እጅግ በሚያስገርም ጥበባቸው ሠፊውን ሕዝብ አሞኝተው ቆይተዋል።

የኢሕአፓና የሌሎችም የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች፥ በወያኔዎች ሲታሰሩ፥ ሲገደሉ፤.... ይህንን እና የመሳሰለውን የታሪክ መጥፎ ጎን የሚመዘግብ የሕዝቦች አእምሮ አልተኛም። ስለዚህ የኢትዮጵያችን ነገር፥ ከሽማግሌዎች አእምሮ የማይጠፋ፥ ወጣቶችን የሚቆጠቁጣቸው፥ ልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችንም የማይረሱት ጉዳይ ሆነ።

ኢትዮጵያ ሕዝቦቿን ሁሉ የምታቅፍ መሆኗ እንዳይታወቅ፥ ሕዝቡን በሃይማኖት እና በጎሳ እየከፋፈሉ ለማጣላት፤ በፖለቲካም ሕዝቦች የሚፈልጉትን እንዳያውቁ ለማድረግ፤ የኢትዮጵያ መሪዎችም የሥልጣን ዘመን በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች መከፋፈልና እርስ በርስ መጣላት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ተስተላክሎ ከተቀመጠ ቆይቷል።

የሀገር መሪዎችን የፖለቲካ አቅጣጫ በመገምገም፥ ይህ የወያኔ መንግሥት ለኢትዮጵያ ሕዝቦች የማያዛልቅ መሆኑን የተረዱ ጥቂቶች አልነበሩም። በእርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ “ሁሉም በስነ ስርዓት ይፈጸምልን” በማለት፥ ከቀን ወደቀን ሲፈጸም የተመለከተውን አድሎአዊነት ተቃወመ እንጂ፥ ከደርግ በኋላ ወያኔም ሆነ ማንም ሥልጣን ቢይዝ ግድ አልነበረውም።

አብዛኛው የትግራይ ሕዝብ መገንጠልን የማይሻ፥ ቂም በቀል የማያውቅ ስለሆነ፥ ከጥንትም በንጉሡ፥ በኋላም በደርጉ በደል ቢደርስበትም፥ የትግራይ ሕዝብ የኢትዮጵያን ሕዝብ አልጠላም (አይጠላም)።

ዳግማዊ ወያኔዎች የትግራይን ሕዝብ አይወክሉም። የትግራይን ሕዝብ ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ የሚገነጥለው ኃይል አይኖርም። አንዳንድ ፖለቲከኞች፥ “ትግራይ ከእናት አገሯ ተገንጥላ፥ ሕዝቦቿም ለብቻቸው ነፃነታቸውን ያውጃሉ፤ አሊያም ከኤርትራ ጋር ይቀላቀሉ” ብለው የሚያስቡ ነበሩ። ነገር ግን፥ ይህ ሊሆን እንደማይችል፥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተፈጠረው ታሪካዊ ክስተት መረዳት ይቻላል።

ሕዝቦችን በጎሳ በመከፋፈል ላይ የተመሠረተ የአስተዳደር ፍልስፍና፥ የተለያዩ ጎሳዎችን (የሕብረተሰብ ክፍሎችን) በግድ አንድ በማድረግ ላይ ከተመሠረተ የአስተዳደር ፍልስፍና አይሻልም። መፍትሔው፥ በቅድሚያ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ነፃነት ነው፤ ቀጥሎም አንድነት ነው።

እኩልነት ሲባል፥ በሃብት አለመበላለጥን ብቻ አይደለም የሚያመለክተው። አንዱ የሕብረተሰብ ክፍል በሌላው ላይ የበላይነት ሳያሳይ፥ በሃብት መበላለጥ ኖረም አልኖረም ሕዝቦች ሁሉ በሰብእናቸው ተከብረው፥ የሁሉም ኢትዮጵያዊነት በእኩልነት ሲታይ፤ ያ ነው እኩልነት። አንዱ የሕብረተሰብ ክፍል በሌላው ላይ የበላይነት እያሳየ፥ በሀገራችን አንድነት አለ ቢባል ግን፥ ያ አንድነት የይስሙላ አንድነት ነው የሚሆነው እንጂ፥ በውስጡ ፍቅር እና ሰላምን ያካተተ ፍጹማዊ አንድነት ሊሆን አይችልም።

ኢሕአፓ "ሕዝቦች በቅድሚያ ለእኩልነትና ለዴሞክራሲያዊ ነፃነት መታገል አለባቸው" ሲል የነበረው፥ በዚህ መሠረት የሚመጣ አንድነት ፍጹማዊ መሆኑን ስለሚገነዘብ ነው። ኢሕአፓ የሰው ልጆችን ዴሞክራሲያዊ መብት ከግለሰብ እስከ ብሔረሰብ ለማረጋገጥ የሚሞክሩ ቲዎሪዎችን አስቦታል። "የማንኛውም ብሔር የራስን እድል በራስ የመወሰን ዴሞክራሲያዊ መብት እስከ መገንጠል (መገንጠልንም ጨምሮ) የተጠበቀ ነው" የሚለውን በቲዎሪ (ጽንሰ ሃሳብ) ይደግፋል (በተግባር ሳይሆን)። ይህ ከውጪ የተቀዳ ጽንሰ ሃሳብ በኢትዮጵያም መሥራት አለመሥራቱን የሚያሳይበት አንድም ሁናቴ አልታየም።

በተጠቀሰው ከውጪ የተቀዳ ጽንሰ ሃሳብ መሠረት፡- የመገንጠልን መስፈርት የሚያሟላ ዛሬም ሆነ ለወደፊት በኢትዮጵያችን ሊኖር አይችልም። ስለዚህ፥ ዴሞክራሲን ከሚያቀነቅኑ አሕጉራትና የፖለቲካ ድርጅቶች በቁንጽሉ የተወሰደ፥ ዛሬ በኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት ጸድቆ የተቀመጠ አንቀጽ 39 ለኢትዮጵያችን እንደማይሠራ ግልጽ ነው።

"አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይነሳም፤" እንደሚባል ሁሉ፥ በጥፋት ጎዳና እየተሰነካከለች ያለችውን ኢትዮጵያችንን "እባካችሁ ቀናውን መንገድ እናስይዛት..." ቢባልም፥ አውቆ የተኛ ሁሉ እንቅልፉን እየለጠጠ፥ ቢነቃም፥ ጆሮ ዳባ ብሏል፤ ብንናገር፥ ብንጽፍ፥  ብንለፈልፍ፥ ብንጮህ፥ ብናለቅስም ሰሚ አላገኘንም።

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ብዙ ቆይተው፥ በመጎዳታቸውና እየተጎዱም ሳሉ፥ የጎሳ ፖለቲካ የማያዋጣቸው መሆኑን፤ ኢትዮጵያችንን እንደሚከፋፍላት፥ ጉዳት ላይም እንደሚጥላቸው ተገነዘቡ። ተቃዋሚ (ተቀናቃኝ) የፖለቲካ ድርጅቶች፥ ከሕዝቦች ሁሉ ጋር ተባብረው፥ በዴሞክራሲ ተወያይተው፥ አገራቸውን አስቀድመው፥ ለእርቅ፥ ለሰላም፥ ለሕብረትና ለአንድነት መነሳት ስላቃታቸው፥ የዳግማዊ ወያኔዎች አገዛዝ ተጠናከረ።

"የማንኛውም ብሔር የራስን እድል በራስ የመወሰን ዴሞክራሲያዊ መብት እስከመገንጠል (መገንጠልንም ጨምሮ) የተጠበቀ ነው" ሲባል፤ በቅድሚያ መሟላት

ያለባቸው መስፈርቶች ይኖራሉ። እነኚህም መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው:- በሃማኖትና በተለያዩ ስነ ልቦና የሚገናኙ፤ አንድ ቋንቋ የሚናገሩ፤ አንድ ባሕል እና የኑሮ ዘይቤ (ልምድ) ያላቸው፤ ከሌሎች ተለይተው በአንድ የጂኦግራፊ ክልል ተወስነው፥ እራሳቸውን ችለው የኖሩ፤ የራሳቸው የሆነ የጦር ኃይልም ያላቸው/የነበራቸው፤ ከሌሎች ተለይተው የራሳቸው የሆነ ታሪክ ያላቸው።

የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ እነማን ናቸው? የኤርትራም ሕዝብ ከትግራይ ሕዝብ ጋር በቋንቋ፥ በሃይማኖት እና በባህል እንደሚዛመድ አይካድም። በተመሳሳይ፥ የኢትዮጵያ ብሔሮች ሁሉ እርስ በርስ ይዛመዳሉ። ታዲያ፥ በኢትዮጵያችን ማን ነበር፥ ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ የሚያሟላ። ምናልባት ኤርትራ ታሟላለች ቢባል እንኳን፥ በከፊል እንጂ ሙሉ በሙሉ አለመሆኑ ይታወቃል።

ከኤርትራ ሠራዊት ሌላ፥ ኤርትራን ከኢትዮጵያ መገንጥል እንደ ዋነኛ ፖሊሲው አድርጎ የወሰደ ሕወሓት (ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ) ብቻ ነበር። ኢሕአፓ ኤርትራ እንድትገነጠል ምንም ያደረገው ድጋፍ የለም። ሕወሓቶች ግን ኤርትራ እንድትገነጠልላቸው ይፈልጉ ነበር። ምክንያቱም ትግራይ ብትገነጠል፥ የኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር መሆን አይመቻቸውምና ነው።

ጸረ ዴሞክራሲ የሆኑት እውነተኛ ሀገር ገንጣዮች (ወያኔዎች)፥ ከተጠቀሱት መስፈርት መካከል አንዱን (ቋንቋን) ብቻ ይዘው፥ የኢትዮጵያን ሕዝቦች በዘር መከፋፈል ጀመሩ። ለከፋፈሏቸውም ሕዝቦች መገንጠል እንዲያመቻቸው፥ ተገንጥለውም እራሳቸውን እንዲችሉ፥ ሰፋፊ የጂኦግራፊ ክልል አበጁላቸው።

የመገንጠልን እሳቤ እንደ "ዴሞክራሲያዊ መብት" መቁጠር በራሱ አጠያያቂ ሆኖ ሳለ፥ ወያኔዎችም እንዲህ አይነቱ እሳቤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደማይሆን እራሳቸው እያወቁት፥ ይህንኑ የመገንጠል እሳቤ በሥራ ላይ በማዋል፥ አብሮ የኖረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እርስ በርሱ እንዲናቆር፥ ሰይጣናዊ የቅስቀሳ መረቦቻቸውን በኢትዮጵያ ዳርቻዎች ሁሉ ዘረጉ።

በቅድሚያ ኤርትራን አስወገዱ፤ በመቀጠልም ሌሎቹም እንዲገነጠሉ የሚያስችሉ፥ የተጠቀሱን መስፈርቶች እንዲያሟሉ ሁኔታዎችን ማስተካከል መደበኛ ሥራቸው ሆነ። ክልል ማበጀት፤ የራሱ ጦር ያለው፥ የራሱ የፖለቲካ ፓርቲ ያለው፥ እራሱን በራሱ የሚያስተዳድር የክልል መንግሥት ማቋቋም፥ ወ.ዘ.ተ.።

አንድ መንግሥት በራሱ አነሳሺነት ክልል አበጅቶ፥ "ከዛሬ ጀምሮ በዚህ ክልል ውስጥ የምትኖሩ እራሳችሁን በራሳችሁ የማስተዳደር መብታችሁ የተጠበቀ ነው" ሲል፥ የሕዝቡን ዴሞክራሲያዊ መብት ነጥቆ ለራሱ አድርጓል ማለት ነው።

ወያኔዎች በቅድሚያ የትግራይን ክፍለ ሀገር ወደ ክልል ሲለውጡት፥ ሰፋፊ እና ለም የሆኑትን ሥፍራዎች (ራያን አላማጣን፤ ወልቃይት ጠገዴን) የትግራይ ክልል አደረጉ። አማራ እና ኦሮሞ አብሮ የሚኖርበትን አካባቢ የኦሮሞ ሕዝብ ብቻ እንዲኖርበት ሠፊ ክልል አበጅተው፥ ይህ የኦሮሞ ክልል ነው አሉ። በእነርሱ እሳቤ፥ አማራ፥ ኦሮሞ እና ትግሬ ለየብቻ ነው መኖር ያለበት።

ክርስቲያኑ የሱዳን ሕዝብ ሳይሰልም በፊት፥ ከጥንት ኢትዮጵያ የሚለው ስም በምሥራቅ አፍሪካ የሚኖሩትን ሁሉ የሚያጠቃልል ነበር። አንድ የነበረው ታላቅ ሕዝብ ተከፋፈለና፥ ታላቋ ኢትዮጵያ ትንሽ ሀገር ሆነች። ምናልባት አሁንም ይህቿን ትንሽ ሀገር እንደገና ትንሽ ለማድረግ፥ ከተቻለም ለማጥፋት የሚፈልጉ ኃይላት ይኖሩ ይሆናል። ግን፥ ጥሩ መንግሥት እንዳይመጣ የታገሉ የእርኩስ መንፈሶች ሴራ በዚህ እንደማይቀጥል፥ አንዳንዶቻችን "እኛስ ይህንን ይህንን እናውቃለን!" ብንል፥ ይህ ቅዠት እንዳይደለ ጊዜ ያሳየናል (ለሁላችንም)።

በአራቱም ማዕዘን አለምን ዞሯታል፤<br>
እየደጋገመ ሕዝቦችን ቀጥቅጧል፤<br>
ኢትዮጵያን ለመምታት እቅድ ተዘርግቷል፤<br>
የሰይጣን ክፉ አይን አክሱምን አይቷታል፤<br>
ረዳት እንዲሆኑት ብዙ ሰው መልምሏል፤<br>
ግን የእሳት ግርግዳ አቃጥሎ ገርፎታል።<br>
ደጉ ብሔረሰብ አስተውሏል ገብቶታል፤<br>
አምሃራይ ከትግራይ የማይለይ ሆኗል፤<br>
የኦሮማይ ፍቅር ኢትዮጵያን አዳርሷል።

# ምዕራፍ አስር

## በኢሕአዴግ ምትክ ልዩ መንግሥት

የሕዝብ ድጋፍ በማጣት ሥልጣኑን በፈቃዱ የለቀቀው ኢሕአዴግ፥ ውስጠ ጠባዩ ከቀድሞዎቹ በጠባዩም በምግባሩም እጅጉን የተለየ፥ ተወዶ የተጠላ፥ ልዩ መንግሥት ተረከበው። ወያኔዎች በሕዝብ ግፊት ሥልጣናቸውን ሲለቁ፥ በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር የነበረው መለሰ ዜናዊን የተካው ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ነበር። የእርሱ የሥራ ዘመን ሳያልቅ፥ "እኔ አልቻልኩም፤ ሌላ ሰው ቢተካኝ ይሻላል" በማለት፥ ሥልጣኑን በፈቃዱ ለዶክተር ዐቢይ አህመድ አሊ አስረከበ።

በኤርትራ እና በኢትዮጵያ መካከል የነበረውን አለመረጋጋት ለማስፈን፥ ዶክተር ዐቢይ አህመድ (ጠቅላይ ሚኒስቴር) የወሰደው ሰላምን የማስፈን እርምጃ፥ የአለም ኖቤል ሽልማትን (Nobel Prize) አስገኝቶለታል። ዐቢይ አህመድ በ1912 ዓ.ም. (እንደ ኢ.ኢ.አ.) ሥልጣኑን እንደ ተረከበ፥ የብዙዎችን ቀልብ የሳቡ ንግግሮች አድርጓል። "ጥሩ" የተሰኙ ሥራዎችን ሠርቶም ከሆነ፥ ይህንን ወዳጆቹ (እርሱም ራሱ) አግንነው እና አስፍተው ተናግረውታል፤ ጽፈውታል።

አንድ ሰው እጅግ ጥሩ ሲሆን "እገሌ መልአክ ነው" ይባላል። እንዲሁም አንድ ሰው እጅግ መጥፎ ሲሆን "እገሌ ሰይጣን ነው" ይባላል። ስለ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ሲነሳ፥ "ዐቢይ አሕመድ መልአክ ነው" ሲሉ የነበሩ፥ "ዐቢይ አሕመድ ሰይጣን ነው" ማለት ከጀመሩ ቆይተዋል።

ጥሩ የሚሠሩ ሰዎች ሁሉ ምንጊዜም ጥሩዎች እንደማይሆኑ፥ በተለይም አንዳንድ ተንኮለኞች፥ መጥፎ ለመሥራት ሲያቅዱ፥ ለመጥፎ ሥራቸው መሸፈኚያ ጥሩውን ስለሚያስቀድሙ፥ በመጥፎ ሥራቸው ወቀሳ ቢበዛባቸው፥ የሠሩትን ጥሩ ሥራ በማጋነን እያወሩ፥ የየዋሃን ሰዎችን ድጋፍ ያገኙበታል።

ብዙዎችን በማሳሳት ወደ ከፋት የመራውን የዚህን "ተወዶ የተጠላ" መንግሥት ጉዳይ በዚህ መጽሐፍ መጥቀስ አስፈላጊ የሆነበት ዋነኛው ምክንያትም፥ ታሪክ ጸሐፊዎች ከደረቅ እውነታዎች ተነስተው ሲተርኩ፥ የሕዝቡንም የችግሮቹን መንስኤ በትትክል በመረዳት፥ መከራውን፥ ጉዳቱን፥ እንግልቱን፥ ስቃዩን፥ ብሶቱን፥ ሰቆቃውን፥ ሃዘኑን እና ልቅሶውን ሊያይዘው እንዳይረሱት ነው፤ የማይረሳ ነውና።

ከኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ በአለፉት አራት መንግሥታት ውስጥ፥ አንዳንድ ሰዎች አጓጉል አመል አውጥተው ከመንግሥት ጋር ሲወግኑ፥ ምክንያቱ ምን እንደሆነ፤ "በእውነት ለዚህች ጊዜአዊ ምድራዊ ኑሮአቸው በመስገብገብ ነው የሕዝቡን እንግልት የረሱት? ወይንስ እነርሱ ሳያስቡት፥ መጥፎውን በጥሩ በሚተኩ፥ አሳሳች እሳቤዎችና ምልከታዎች (ሰይጣናዊ ርዕዮት) ተጽእኖ አንገላቸውን ስለተቆጣጠሩት ነው?" ብለውም እራሳቸውን እንዲጠይቁ ነው።

በአንድ በተወሰነ ወቅት፥ ጠቅላላ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ንቅት ብለው፥ እጆቻቸውን አጣምረውና ወደ ሰማይ ሰቅለው፤ "ዘረኛነት ይብቃ፤ እኛ ሁላችንም አንድ ነን፤ አትለያዩን" እያሉ የጮሁት ጩኸት ትንሽ ከምድር ከፍ በማለቱ ትንሽ ለውጥ አመጣ። ለውጡ ሲመጣ፥ ከቤተ መንግሥት "እኛኮ! ስንኖር ኢትዮያውያን ስንሞት ኢትዮጵያ ነን.." የሚል፥ እጅግ የሚማርክ ልዩ ድምጽ ተሰማ። የዛን ጊዜ፥ እጆቻቸውን አጣምረውና ወደ ሰማይ ሰቅለው የነበሩት ሁሉ ተረጋግተው "አሜን፥ አሜን፥ አሜን.." በማለት ደስታቸውን ገለጡ። እነርሱ ግን፥ የዛን ጊዜ፥ ለማን አሜን እንደሚሉ አላወቁትም ነበር።

የወያኔ መንግሥት በሕዝቦች ጩኸት ሲወርድ፥ ተተኪው መንግሥት የተሻለ መሆን አለበት በማለት በእምነት የተቀበልነው፥ መንግሥታዊ ስርዓቱም እንዲሁ ዘር ተኮር በመሆን ፋንታ፥ ሁሉን የሚያቅፍ ይሆንልናል ብለን በማሰብ ነበር። ለብዙ ጊዜ ያልሰማናቸውን፥ አዳዲስ የእርቅ፥ የሰላም፥ የይቅርታ፥ የፍቅር እና የአንድነት ንግግሮችን ከቤተ መንግሥት አካባቢ በየቀኑ ስንሰማ፥ ሁሉም እንደሰማነው ይፈጸማሉ በሚል ተስፋ እና እምነት ነበር።

ከአሮጌው ኢሕአዴግ ተነስቶ እራሱን በአዲሱ የተካው መንግሥታዊ መስተዳደር "እርሱስ ጥሩም ባይሆን ሻል ያለ መንግሥት ሳይሆን አይቀርም፤ አንዳንድ መሠረታዊ ለውጦችም ያደርግ ይሆናል" በማለት፥ በተስፋ ሲጠባበቁ የቆዩ ሁሉ "ከድጡ ወደ ማጡ" እንደሚባለው ሲሆንባቸው ደነገጡ። "ምንጊዜም፥ የመጥፎ ነገር ተቃራኒው ጥሩ ነው መሆን ያለበት፤ ስለዚህ፥ ሕዝብ የጠላውን ኢሕአዴግን አዲሱም መንግሥት የሚጠላው ከሆነ፥ እርሱ ጥሩ መሆን አለበት" ብለው ያሰቡ ሁሉ፥ መሳሳታቸው ሲገባቸው ተበሳጩ፤ በሰንካላ እድላቸውም እጅጉን አዘኑ።

ከረጅም አስከፊ ጊዜያቶች (ከወያኔ የ27 ዓመታት አገዛዝ) በኋላ፥ የጠቅላላ ሕዝቦች ፍላጎት እና ምኞት "ለውጥ! ለውጥ! ለውጥ!" ስለነበረ፥ በሕዝቦች ጩኸት እና ሰላማዊ ሰልፎች ብዛት "ለውጥ" ቢመጣም፥ ለውጥ ፈላጊው ሕዝብ ለጊዜው ያተኮረው "ለውጥ" መምጣቱን ብቻ እንጂ፥ "መቼም ከዚህ የባሰ አይመጣም" በሚል ምኞታዊ ተስፋ ተጠምዶ፥ ከፊቱ የተደቀነውን የመጥፎ ለውጥ ውጤት በግል ሕይወቱ

እስኪመጣበት ድረስ አላስተዋለውም ነበር። ብዙዎቻችንም፥ መቼም አንድ መንግሥት ሌላውን ሲተካ፥ መንግሥታዊ ስርዓቱን እንዳለ ካልተረከበ በስተቀር፥ ጭራሹኑ ለመለወጥ፥ ለማስተካከል ወይንም ለመጠገን፥ ምክር መጠየቁ አይቀርም በማለት አስበን ነበር።

ወታደራዊው የደርግ መንግሥት እንኳን፥ ሕዝቡን ለማረጋጋትም ቢሆን፥ አዲሱን ሶሻሊስታዊ ርዕዮቱን ከመጀመሩ በፊት በጊዜያዊነት ነበር ሥልጣን የያዘው። እኛም፥ ከአርባ አምስት ዓመታት በኋላ፥ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት የመጣ መስሎን፥ ለወደፊቱ ቀና አስተዳደር የተሻለውን አማራጭ ከሕዝቦች ጋር ለመገምገም፥ ለመመካከርና ለመወያየት የሽግግር መንግሥትን ጠብቀን ነበር።

አዲስ መንግሥት አሮጌውን ሲተካ፥ በመሃል የሽግግር መንግሥት ያስፈልገናል የሚባለው፥ አንድም ሕዝቡ የራሱን መንግሥት በራሱ ይመሠርት ዘንድ ዕድል ለመስጠት፥ እንዲሁም ሕዝቡ የሚጠቅመውን የመንግሥት ስርዓት በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተወያይቶ እና መክሮ፥ የሚፈልገውን ስርዓት ሕዝቡ በራሱ (በወከላቸው አማካኝነት) እንዲወስን፤ በዚያውም መንግሥት እና ሕዝብ ተቀራርቦ አብሮ መሥራትን እንዲያውቅበት ነበር። እኛ ግን "ለዘመናት የቆየውን ዘረኛ እና ከፋፋይ ስርዓት ከሥሩ ደምስሶ እስካጠፋልን፤ በምትኩም በዘር የተከፋፈለውን ሕብረተሰብ ወደ አንድነት የሚያመጣ ፍትሃዊ መንግሥት እስካስገኘልን ድረስ፥ ጊዜያዊ እያሉ ነገር ማራዘም አስፈላጊ ላይሆን ይችላል..." በማለት፥ በትእግስት በመጠበቃችን ተሳስተን እንደነበር የገባን ብዙ ቆይቶ ነበር። "እኔ ጊዜአዊ መንግሥት እሆንላችኋለሁ.." እያለ፥ ሲያባብለን፥ እውነት መስሎን ጭጭ አልን እንጂ፤ "ከመልካም" ንግግሮቹ ባሻገር፥ በሥራ የተተረጎመ፥ ለሠፊው ሕዝብ የሚጠቅም ጥሩ ነገር ስናጣ፥ ጥርጣሬው ውስጥ ገባን እንጂ፤ ስናልመው የነበረውን ጊዜያዊ መንግሥት ያላገኘነው በምን አይነት የፖለቲካ ውስብስብ ውስጥ በመግባታችን ምክንያት እንደሆነ በደንብ አልገባንም ነበር።

ዐቢይ አህመድ ከኢሕአዴግ (የቀድሞው ሕወሓት) ከውስጣቸው የበቀለ በመሆኑ፥ የእነርሱን አሠራር እና ተንኮላቸውን ያውቃል። ሕወሓቶች (ወያኔዎች) መላው ኢትዮጵያን መቆጣጠር እና መግዛት እንደጀመሩ ትግራይ እንድትገነጠል የነበራቸውን ምኞት ትተውት ወይንም ችላ ብለውት ነበር። ነገር ግን፥ ዐቢይ አህመድ ሥልጣን ከያዘ በኋላ፥ ያንን ምኞታቸውን እንደገና በጠባብ ብሄርተኝነት ቀሰቀሱትና ወደ ትጥቅ ትግል አመሩ።[32]

[32] በዚህ ውስጥ የሚካተቱ አያሌ ፖለቲካዊ ውስብስብ ጉዳዮች ይኖራሉ።

ዐቢይ አህመድ ሥልጣኑን ሲረከብ፥ ሕወሓት ኢትዮጵያ እንድትፈርስ የሚያደርገውን የዘረኛነት እና የተንኮል ጥንስስ በመቃወም፥ የሕዝቡን ስሜት እና ምሬት አንግቦ የተነሳ፤ እንዲሁም፥ እርሱ የእስላም እና የክርስቲያን ሃይማኖቶችን ከሚከተሉ፥ ከአማራ እና ከኦሮሞ ሕብረተሰብ የተገኘ፥ ትግርኛም የሚናገር ምሁር በመሆኑ፥ ጠቅላላ ኢትዮጵያን እስከ አንድነቷ በዚህ በአንድ ሰው ውስጥ የአገኘን መስሎን "ኢትዮጵያ እስከ ዛሬ ያጣቻውን መሪ አገኘች!" በማለት ደስ ብሎን ነበር።

በተከታታይ ከእርሱ የምንሰማው ንግግሮችም በብዛት የሚያንጸባርቁት፥ ከቅን እና ከመልካም አሳቢዎች የሚፈልቁ በመሆናቸው፥ እርሱንም እንደ ጥሩ ሰው እና እንደ ጥሩ የሀገር መሪ ገምተነው ነበር። እንደታሰበው ሆኖ ባለመገኘቱ፥ ይህ ሰው ለኢትዮጵያ የሠራላት ሳይሆን፥ የሠራባት የእርሱ የከፉ ሥራዎቹ ውጤት ምንኛ አሳዛኝ እንደሆነ፥ ለወደፊት ታሪክ በሰፊው የሚያወሳው ሆነ - "ተወዶ የተጠላ" መንግሥት።

ገና ከጅምሩ፥ ዐቢይ አህመድ እውነተኛ ሰው ቢሆን ኖሮ፥ የአኖሌ ሃውልት መሠረተ እሳቤው የውሸት ትርክት እንደሆነ በመገንዘብ፥ ይህንን አንድ ኮናኝ፥ ታሪክ አጉዳፊ እና አሳፋሪ ሃውልት ቢያፈርሰው (ቢያስፈርሰው) እና በምትኩ፥ የኦሮሞን ሕዝብ ደግነት እና በጎ ባህል እና ታሪካቸውን የሚያንጸባርቅ ሃውልት (ቤተ መጻሕፍት ወይንም ሌላ) ቢያቆይ ኖሮ፥ ይህንን ማድረጉ ብቻ፥ ይህ ሰው በውስጠ ጠባዩ ጥሩ መሆኑን ያሳውቀን ነበር።

ልዩ ልዩ ሃሳቦችን በየጊዜው እየጠነሰሱ፥ የሃሰት ትርክቶችንም እየሰበኩ፥ ከታዳጊ ሕጻናት አንጎል ውስጥ እንኳን ሳይቀር ቀና አመለካከት እንዲጠፋ፥ የእርስ በርስ ቅራኔዎች እንዲፋፋሙ፥ አያሌ ሰይጣናዊ እቅዶች ተዘርግተው በሥራ ላይ ከዋሉ ቆየት ብሏል። ኢሕአዴግ ያቆመውን ሰይጣናዊ የአኖሌ ሃውልት እያዩ ያደጉ የኦሮሞ ታዳጊ ሕጻናትም፥ በስነልቦናቸው የሚቀረጸው መንፈስ አማራን ከመጥላታቸው ጋር እራሳቸውንም እንዲጠሉ አደረጋቸው።

መንግሥትም ይህንን በውሸት ትርክት የተገነባ ሃውልት አይኑ እያየ ዝም ማለቱ፥ የኢትዮጵያን እና የሕዝቦቿን ታሪክ አለማወቁን ነው የሚያሳየው። ካወቀም፥ አውቆ ዝም ማለቱ፥ በሚያስከትለው ጥፋት ሁሉ ተባባሪ መሆኑን ግልጽ ያደርገዋል። ኦሮሞዎችም ብዙ ብዙ አኩሪ ታሪክ እያላቸው፥ የኦሮሞ ልሂቃን ዝም ማለታቸው፥ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ግራ የሚያጋባ ሆነብን።

በኢትዮጵያ ወሰን ክልል ውስጥ ያሉ ዜጎች ሁሉ፥ በኢትዮጵያ ምድር በተመላለሱበት ሥፍራ ሁሉ ታሪክ ሠርተዋል። ይህንን አኩሪ የጋራ ታሪክ፥ የሁላችንም የጋራ መገለጫ በማድረግ ፋንታ፥ በማስረጃ የተረጋገጠውን እውነተኛ ታሪክ በውሸት ትርክት በመቀየር "ይህ ነው የእናንተ ታሪካችሁ" እየተባለ የተነገረውን ሁሉ

እንደ እውነት የተቀበሉ፥ በውስጣቸው የክፋት መንፈስ በየጊዜው እና በየሰዓቱ እያደገ መጥቶ፥ ጥሩ አሳቢው ሰው መጥፎ አሳቢ ሆነ።

የኦሮሞ አማኞችን ከሌሎች አማኞች እየለዩ፤ አጠቃላይ የኦሮሞን ሕዝብ የፖለቲካ መናገጃ ማድረግ፤ የኦሮሞ ተቆርቋሪ መስሎ ለመከፋፈል መሞከር ግን፥ ይህ ሰይጣናዊ ባህሪ ነው እንጂ፥ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?

የአካባቢውን ሕዝብ ስሜት ጠብቆ አይደለም መንግሥት የአኖሌን ሃውልት ያቆመለት። ለኦሮሞ ሕዝብ "ይህ ነው ያንተ ታሪክ" ተብሎ ሲነገረውና በውስጡ ጥላቻ ሲጠነሰስ፥ ግቡ እና መጨረሻው ምን እንደሚሆን፥ ይህንን አያውቅም ነበር መንግሥት? ባያውቅ ይሻላል (በሞኝነቱ)፤ ዝም ያለው አውቆ ከሆነ ግን (በብልጠቱ)፥ ተከትሎ ለመጣው ጥፋት ሁሉ ተጠያቂ ከመሆን አያመልጥም።

ሕዝቡ እራሱን በራሱ አልከፋፈለም። በሕዝቡ ፍላጎት አይደለም አገሪቷ ክልል የተበጀላት፤ በሕዝቡ ፍላጎት አይደለም የዘር ፖለቲካ በሕገ መንግሥት የጸደቀለት። ከወያኔ የአገዛዝ ዘመን ጀምሮ፥ መንግሥታዊ መዋቅራዊ ተንኮል እንደነበር አይካድም። እጠግናለሁ ብሎ የመጣ መንግሥት ሰባበረን።

ከብዙ ጥፋቶች በኋላ፥ "እንዴ! ይህ ሰው እኛ ስናውቀው ጥሩ ሰው አልነበረም እንዴ? አሁን ምን ነካውና ነው በቅጽበት ቅይር ብሎ እንዲህ የረከሰው?.." የሚሉ ሰዎች፥ እነርሱ ከጥንቱም፥ ያ "ጥሩ" የተባለ ሰው ውሎው ከማን ጋር እንደሆነ አላወቁም ነበር።

"ሞት የሌለበት ሀገር የለም፤ ሰው እየሞተ ችግኝ አይተከልም የሚል ጠላት ነው፤ እንዳትሰሙ። ሰው እየሞተ በሞተበት ቦታ ችግኝ እንተክላለን፤ ቢያንስ አስከሬኑ ጥላ እንዲኖረው....[33]" እያለ የሚናገር የሀገር መሪ መጣብን። እኛም "ሰው ብቻውን (ካለ ምንም እርኩስ መንፈስ አጋርነት) እንዴት እንዲህ ሊያስብ እና ሊናገር ይችላል?" ብለን እራሳችንን አልጠየቅንም።

እርሱ፥ "እኔ ያሠራሁትን እጹብ ድንቅ የሆነውን ቤተ መንግሥት ቱሪስቶች ሲጎበኙ፥ የኢትዮጵያን ታላቅነት፥ የእኔንም ታላቅ መሪነት ያደንቃሉ" ብሎ ያስባል። እነርሱ (ቱሪስቶቹ) ግን ዞር ብለው የአኖሌን ሃውልት ሲመለከቱ፥ እርሱ እንዳሰበው ሳይሆን፥ "አይ ኢትዮጵያ! ምነው እንዲህ እድለ ቢስ ሆነች!" ብለው ነው በሃዘን የሚመለሱት። እኛስ ኢትዮጵያኖች? በአዲስ አበባ ውስጥ እጅግ ለአይን ማራኪ የሆኑ የሃብታሞችን መኖሪያ፤ የሚያማምሩ መዝናኛ ሥፍራዎች እና ቤተ መንግሥቶችን

[33] ከጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አህመድ አሊ ንግግር በቀጥታ የተወሰደ።

ከሩቅ እየቆምን ስናይ፥ በሌላም በኩል፥ የሕዝቡን ድህነት እና ጉስቁልና ስናስተውል፥ ምን ይሰማናል?[34]

መንግሥት ከሕዝቡ ፍላጎት ይልቅ የሚገደው የራሱ ፍላጎት ብቻ ስለሆነ፥ ሕዝቡ የገዛ ፍላጎቱን እንኳን ለይቶ እንዳያውቅ ለማድረግ ብዙ ተሰብኳል። የኢትዮጵያ ታሪካዊ እና ስነ ልቦናዊ እሴቶችም ሲዳከሙ (ወይንም ሲጠፉ) የታሪክ ተመራማሪዎች እና ሌሎችም ምሁራን ዝም አሉ እንጂ፥ በመቆርቆር እምብዛም ጎልቶ የሚታይ ተቃውሞ ሲያሰሙ አለመታያቸው፤ ይህም በኢትዮጵያችን ላይ የተጋረጠው የክፉው መንፈስ ሴራ ምንኛ የረቀቀ ጥልቅ እንደሆነ ነው የሚያመላክተው።

እስካሁን (ባለፉት 50 ዓመታት ውስጥ) ኢትዮጵያ አልተለወጠችም፤ አላደገችም ማለት አይቻልም። ከሌሎች የአለም አህጉራት ትይዩ፥ የተጠበቀውን ያህል ባይሆንም፥ ተለውጣለች፤ አድጋለችም። ሆኖም፥ ባለፉት ስድስት ዓመታት ውስጥ፥ ትንሽ አድጋ ብዙ ቆርቁዛለች። የመቆርቆዟም ምክንያት፥ በብዙ ሺህ ዓመታት ውስጥ በተገነቡት ማንነቷ ላይ ጠላት በመዝመቱ ነው። በተለይም፥ መንፈሳዊ ማንነቷ እንዲጠላ በማድረግ፥ ሃይማኖታዊ፥ ባህላዊ እና ትውፊታዊ እሴቶቿን በማጥፋት፥ በማህበራዊ፥ በኢኮኖሚ እና በፖለቲካ ይዘቷ በከፍተኛ ፍጥነት ቁልቁል ወርዳለች።

በድብቅ የሚሠራውን ተንኮል በግላጭ የሚያሳይ መጥፋቱ ኢትዮጵያችንን ወዳልታሰበ ሥፍራ መራት። የሚሆነውን ሁሉ በአጽናኦት የተመለከቱ፥ አንዳንድ የሕብረተሰቡ አንቂ ክፍሎች፥ (ግለሰቦች፥ ጋዜጠኞች፥ ፖለቲከኞች፥ የታሪክ አዋቂዎች፥ ፈላስፎች እና ሌሎችም ምሁራን) በመሃል ጣልቃ እየገቡ፥ መንግሥት እየወሰዳቸው ያላቸው እርምጃዎች ሁሉ የማይደገፉ - ሀገር አውዳሚዎች መሆናቸውን አሳውቀዋል፤ ጠቃሚ (እውነተኛ) መረጃዎችንም አቀብለዋል። ሕዝቡም ቀስ በቀስ ይህንን ሲያውቅ፥ ተቃውሞ ማሰማት መብቱም ግዴታውም መሆኑን ተረድቷል።

በመሠረቱ፥ መንግሥት የሕብረተሰብ አንቂም ቢሆን ነበር ጥሩ። አዎ! እኛም "ጎሽ! ለውጥ መጣልን!" ብለን ከመንግሥት ጎን ቆመን፥ ደስ ብሎንም በቆየንበት ጊዜ ሁሉ፥ ሕብረተሰቡ ምን ያህል ወደ መርዛማው የጥላቻ አለም እንደገባና በክፉት እንደተመረዘ አላስተዋልንም ነበር።

ጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አህመድ፥ እርሱ እንደ ችሎታው እና እንደ ሥልጣኑ በውስጠ ጠባዩ ጥሩ ሰው ቢሆን ኖሮ፥ በንግግር ብቻ እንኳን ቢሆን፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዘር ፍጅት ይመልሰው፥ ያስተምረው እና ያነቃው፥ ከዘረኛነትም ያላቅቀው

---

[34] የአንዳንድ ሰዎችን አእምሮ ጥፍንግ አድርጎ የሚይዝ ሰይጣን፥ እርሱ ከሚያዘው ውጪ አንዳች ማድረግ እንዳይችሉ ያደርጋቸዋል። እኛም ሰይጣናዊ ግቦችን ለማሳካት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን በመንፈሳዊ አይኖቻችን ለይተን መመልከት እና መግታት ተሳነን።

ነበር ብለው ያሰቡ ብዙዎች ናቸው። ይህ ሳይሆን ሲቀር ያስተዋሉ "እርሱን ምን ነካው? ምን አይነቱ ጋኔን ነው ያደረበት?" በማለት ተገርመዋል።

ማንም ሰው (ለተማረም፥ ላልተማረም) ገሃድ የሆነውን ነገር ሁሉ እየደጋገሙ የማውራት እና ታላቅ ሥራን የተሠራ የማስመሰል ፖለቲካ፥ ብዙውን ሰው ቅዠት (illusion) ውስጥ ከተተው። በየቀኑ ስንሰማቸው የነበሩ ልስልስ ያሉ የንግግር ስልቶች እንኳን፥ ቁርፍድፍድ ያሉ፥ በግላጭ አምባገነናዊ (dictatorial) ባህሬ የሚታይባቸው እየሆኑ ሲመጡ፥ ዐቢይ አህመድም ያጠለቀው ጭንብል ወለቀበትና እውነተኛው ማንነቱ ታወቀበት።

ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ሥልጣኑን ተረክቦ ሥራውን ሲጀምር፥ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት፥ እሩቅ አሳቢ፥ አገሩን የሚወድ፥ ደግ እና ርህሩህ ይመስል ነበር። እርሱ ከጥሩነት (መምሰሉ) ወደ መጥፎነት (እሱነቱ) ቀስ በቀስ እየተለወጠ ሲመጣ፤ ውስጣዊ ማንነቱም ተገልጦ ሲታየን፤ "ለካስ እርሱ ከጥንቱም፥ ልክ እንደ ሥራው ብዙ - እንደ ሰይጣን አይነት ኖሯል" ማለት ጀመርን። አልተሳሳትንም።

ከአንድ ቤተሰብ ውስጥ አንድ ልጅ ሲጎድል ቤተሰብ እንደሚያዝን ሁሉ፥ የአንድ ሕብረተሰብ እልቂት የሚያስከፋው ሳይሆን የሚያስደስተው መንግሥት፥ በውስጠ ጠባዩ ከሰውእነት ውጪ "ሌላ" መሆን አለበት።

መጥፎውን ነገር አይቶ የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ እየተቻለው ምንም ሳያደርግ የሚቆይ ማንኛውም የሀገር መሪ፥ አንድም የመጥፎው ሃሳብ ጠንሳሽ (የከፋው መንፈስ ተባባሪ)፤ እንደ እንቁራሪት እዛም እዛም የሚረግጥ፥ ከወዲያ ወዲህ እያምታታ የሚኖር፥ ወይንም ፍርኃት በልቡ የነገሠ፥ በሃቀኛነት መኖር የማይችል፥ ልፍስፍስ እና አስመሳይ ፍጡር ነው።

ዐቢይ አህመድ በተግባር እንኳን ባይሆን በስሜት ከሕዝቡ ጋር አብሮነትን አለመግለጹ፥ በሕዝቦች ዘንድ የነበረውን አመኔታ አኮሰሰው። የሕዝቦችን ብሶት የመስማት ፍላጎት ቢኖረው ኖሮ፥ "ሁሉን አቀፍ ብሔራዊ ውይይት ይደረግ" የሚባለውም ባላስፈለገ፥ ወይንም ተፈላጊነቱ በቀነሰ ነበር፤ ምክንያቱም በዴሞክራሲ ምርጫ የተመረጠ መንግሥትም ቢሆን ራሱ ዴሞክራሲን የሚለማመደው የሕዝቦችን ጩኸት እየሰማ፥ "ምን ላድርግላችሁ? ምን እናድርግ? "ምንድነው ቅሬታችሁ? ምን ጎደለባችሁ?" እያለ ምክርን በየጊዜው ከሕዝቦች እየተቀበለ ሲሆን ነውና። ሕዝቡ የሚለውን መስማት የተሳነው የሀገር መሪ በራሱ አለም ውስጥ መኖርን ሲጀምር፥ ከሕዝቡ ተገንጥሎ ብቻውን ይቀራል። በኢትዮጵያችንም፥ በኢሕአዴግ ምትክ የተተካው መንግሥት እና ሕዝብ ተለያይቷል፣ በከፍተኛ ሥልጣን ሲያገለገሉ የነበሩትም፥ የከፋውን የመንግሥታዊ አስተዳደር ስልት እና ሂደቱን በመመልከትና

ከሕዝቡ ጎን በመቆም፥ "ጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አህመድ የኢትዮጵያን ለውጥ ያኮላሸ፥ በሰው ደም የሚጫወት፥ በሥልጣን ጥም ያበደ፥ ውሸታም እና አጭበርባሪ...." እያሉ፥ ጥለውት ሄደዋል። እርሱ ደግሞ፥ መንበሩን የሚቀማ ኃይል ይመጣብኛል ብሎ ስለሰጋ፥ የካቲት 12 ቀን 2016 ዓ.ም. የሚከተለውን የተለመደ ማታለያ ዲስኩር አሰምቷል፡-

"በምርጫ ነው የሰጣችሁን፥ በምርጫ ውሰዱት ስትፈልጉ፤ ከኛ የተሻለ ካገኛችሁ ምረጡ፤ ችግር የለም። ደሞ ታዩታላችሁ፤ በምርጫ ሕዝቡ ሲወስን፥ እንዴት እንደምናከብር፥ ጊዜው ሲደርስ ታዩታላችሁ። በአፈ ሙዝ ግን፥ በፍጹም። እኛ ወታደሮች ነን። የአድዋ አርበኞች ልጆች ነን።

ሰው በጉልበት ሊያሸማቅቀን አይችልም። ማንም ቢሆን፣ በሰላማዊ መንገድ እና በምርጫ ከሆነ ግን፥ ሕዝብ የወሰነበትን ነገር፥ ለሰከንድም አናቅማማም፤ እንቀበላለን።... ሥልጣን እኮ ሁለት ዓመት ነው የሚቀረው፤ እንታረቅ።"

ይህ ንግግር፥ የሕዝቡን ፍላጎት የተከተለ፥ ሕዝቡ የሚጠብቀውን ተስፋ ታሳቢ በማድረግ ነበር። ነገር ግን፥ እርሱ ይህንን ሲናገር፥ ውስጥ ውስጡን ሌላ የሚሠራው ተንኮል እንዳለ ሕዝቡ ያውቃል። ያቺን እርሱ የተመኛትን የሁለት ዓመት እድሜ ቢያገኝ፥ ከመቶ እጅ ዘጠና ስምንቱ (98%) እንኳን እርሱን ባይመርጠው፥ እርሱ ሥልጣኑን በጉልበቱ እንደሚወስድ አያጠራጥርም። ከዚያም በኋላ፥ ማንም ከእርሱ ሥልጣኑን ሊቀማ እንዳይችል አድርጎ ራሱን እንደሚያደራጅ፥ ማን ይህንን ይስታል? የተማመነበት ኃይል (ዲያቢሎስ ወይንም የውጭ አገር መንግሥት) ከረዳው፥ በልቡ ውስጥ የሚመኘውን ንግሥና ያገኛታል ማለት ነው?

በዐቢይ አህመድ ወይንም በሌላ የእርሱ ተቀጽላ የሚመራ፥ ምሥጢራዊ የገዳዮች እና የአፋኞች ቡድን (ኮሬ ነጌኛ) ተቋቁሞ፥ ሕዝቡን እያሰቃየ፤ በከተማም ሆነ በገጠር፥ እያገቱ በግድያ ማስፈራራት እና ገንዘብ መቀማት እንደ ሕጋዊና መንግሥታዊ ተግባር በተቆጠረበት በዚሁ የስድስት ዓመታት የስቃይ ዘመን ውስጥ፥ አለም ያየውን እና የሰማውን የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሰቆቃ፥ ስቃይና እንግልት፥ የቅዱሳን ሰዎችን ጾምና ጸሎት፥ ጩኸት እና ልቅሶ እግዚአብሔር አያይም፥ አይሰማም?

የገባንበት ጦርነት ሁሉ (በሰሜን፥ በምዕራብ...) የዚሁ ከኢሕአዴግ ቀጥሎ የመጣው ***የከፋው ስርዓት*** ጦስ መሆኑን ባለመገንዘባችን፤ እንዲሁም፥ በድብቅ የሚሠራውን ተንኮል - ሰይጣናዊ አሠራር በአለማወቃችን ምክንያት እጅጉን ተጎዳን።

እጅግ ሲበዛ የሥልጣን ጥም የሚያድርባቸው ሰዎች፥ ነገሮችን እነርሱ በሚፈልጉት መስመር ለማስያዝ ሲሉ፤ መሳሳታቸውን እያወቁ እንኳን ቢሆን፥ በ"ከአፈርኩ አይመልሰኝ" አይነት የግትረኛነት ጠባያቸው ይቀጥላሉ እንጂ፥

አይታረሙም። የሕዝቦች ጩኸት ለሥልጣናቸው አስጊ መስሎ ሲታያቸው ብቻ፥ ቀናውን መንገድ እንደያዙ በማስመሰል፥ አንዳንድ ማስታገሺያ እርምጃዎችን ይወስዳሉ። ከዚያም የሕዝቦችን ጩኸቶች እየቀሙ፥ ንግግሮችን በማብዛት ብዙዎችን እያደናገሩ፥ በአምባ ገነናዊነት (ዲክቴተርነት) ሥልጣናቸውን ያራዝማሉ።

የአንድ ሀገር መንግሥት ውሸትን፥ ከታክቲክ ደረጃ አልፎ፥ እንደ እስትራተጂ ሲጠቀምበት ከታየ፥ እውነትን ፈላጊው ሰፊ ሕዝብ በቶሎ ይከዳዋል። በእውነቶች ላይ በመጽናት ብቻ ኢትዮጵያችንን ከፍ ከፍ ማድረግ ሲቻል፤ እውነቶችን ከውሸቶች ጋር እያጋጩ ሀገር መምራት ብዙ እንደማያስኬድ፥ የመንግሥት ባለ ሥልጣናትም ይህንን የተረዱት አይመስልም። መንግሥት እና ሕዝብ ሆድና ጀርባ ሆነ። ነገሮችን በግልጽ እንዳናያቸው ደብዛዛነትን የሚፈጥረው የፖለቲከኞች ጉም የብዙዎችን አስተሳሰብ ይሸፍናል፤ ሆኖም፥ በአይነ ልቦና ለምናይ ለአንዳንዶቻችን እውነት እና ውሸት ግልጥልጥ ብለው ይታዩናል። በሀገራችን አያሌ እኩይ ድርጊቶች ሲፈጸሙ ምንም እርምጃ አለመወሰድ፥ በእርግጥ የኢትዮጵያን ህልውና (ታሪካዊ፥ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ እሴቶቿን) ለማጥፋት የታሰበ "የእርኩሳን መናፍስት" ተንኮል መኖር አለበት ይሰኛል። ከተለያዩ የሀገር ክፍሎች በሕዝቦች የተመረጡትም፥ "ሀገር እናቅና" ብለው ቆርጠው የተነሱ፥ ከዚያው የሕዝቦች ምክር ቤት አዳራሽ እስኪገቡ ድረስ ነበር እንጂ፤ ከዚያ ከገቡ በኋላማ፥ ጨለማ አይሉት ብርሃን፥ እንዳው ሁሉ ነገር ድንግዝግዝ ያለ ሆነባቸውና፤ "የሆነው ይሁን" የሚሉት ፍልስፍና መመሪያቸው ሆነ። እነርሱን ማን (ምን) አፈዘዛቸው?

ለቆሙለት አላማ ከታገሉት እና ወደ እስር ቤት ከተጣሉት በስተቀር፥ ሌሎች ሰነፎች ተመራጮችም ወደ ሥራቸው ሲገቡ፥ በተቃራኒ ሃሳቦች ብዛት፥ ልክ እንደሚፈራረቅ ሌሊት እና ቀን፥ እነርሱም ትኝት ንቅት እያሉ...፤ ካላጨበጨቡ ሥራቸውን ያልሠሩ የሚመስላቸውም ይኖራሉ። በአንጎላቸው አንደኛው ክፍል ውስጥ ጨለማ፥ በሌላውም ክፍል ደግሞ ብርሃን እያስተናገዱ፤ የሌሊቱ ቅዠት እና እንቅልፍ ማጣት ግን፥ ምክንያቱ ምን እንደሆነ አልገባቸውም። እነርሱ፥ ከፉና ደጉን እንደማይለይ ሕጻን ሆነዋል። በየጊዜው የሚሰበኩት "የሰው ልጅ መጥፎውን እንደሌለ በመቁጠርና ጥሩውን ብቻ በማየት ኑሮውን ማሻሻል ይችላል" የሚለው የጊዜው ፍልስፍና አስተሳሰባቸውን ተቆጣጥሮታል። በዚህ ፍልስፍና መሠረት፡-

*የሰው ልጅ ፈቃዳዊ ፍላጎቱ ተጠብቆለት፥ ያሻውን ሁሉ ያደርግ ዘንድ፥ በራሱ ሕሊና የመሰለውን (እንደመሰለው) እራሱ ሰይሞ፥ ሁሉን ነገር በገዛ አስተሳሰቡ ቁጥጥር ውስጥ ማስገባት ይችላል። ስለዚህ፥ አንድ ግለሰብ ኃጢአትና ጽድቅ፥ ክፋትና ደግነት፥ መጥፎነትና ጥሩነት ብለው ሰዎች በጋራ ሲኖሩ በሰየሟቸው ተጻራሪ*

*እሳቤዎች ውስጥ ግላዊ ኑሮውን ለማስማማት በመታገል እራሱን ማስቸገር የለበትም። የሰው ልጅ ነጻ በሆነ ግላዊ አስተሳሰቡ እና አንደበቱ ሁሉንም እንደፈለገው ሊቀያይረው እና ለራሱ (ለግሉ) ተስማሚ ሊያደርገው ይችላል - መጥፎ የተባለውን ሁሉ፥ እርሱ ጥሩ ነው ካለው ጥሩ ይሆናል ማለት ነው።*

ለጊዜው ቁልጭ ብለው ባይታዩም፥ ይህንን የመሳሰሉ ፍልስፍናዎች (ለምሳሌ የብልጽግና ወንጌል) በብዛት እየተስፋፉና በአለም ዳርቻ ሁሉ እየተሰበኩ ናቸው። ድብቅ አላማቸውም፥ የሰውን ልጅ ተፈጥሮአዊና መንፈሳዊ አስተሳሰብ ዘመናዊ ወደሚባለው ሰው ሰራሽና ቁሳዊ አስተሳሰብ በመቀየር የሰውን ልጅ ከእግዚአብሔር እያራቁ ወደ ዲያቢሎስ ለማቅረብ ነው።[35]

መንግሥት በአጥፊዎቹ ላይ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ቢወስድ፥ በሕዝቡ ዘንድ አመኔታ ይኖረው ነበር። ከአጥፊዎቹ ጋር ሲተባበር እንጂ፥ እነርሱን እየቀጣ፥ ለሕዝቦች ፍትህ ሲያመጣ አልታየም። መንግሥት እና ሕዝብ በአንድ አቅጣጫ የሚነጽሩ ቢሆን ኖሮ፥ በሁላችንም የተባበረ ኃይል የከፉት ኃይሎችን ቶሎ ቶሎ እየቀጨን፥ ሰላማዊ ኑሮ የሚያስኖረንን ሕብረተሰባዊ መዋቅር (ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት) ዘርግተን፥ ምድራዊ እና መንፈሳዊ ሕይወታችንን ወደማስተካከል እንገባ ነበር። ይህ ሳይሆን ቀረ፤ ብሔር ብሔረሰቦችም እርስ በርስ ተላለቁ። ይህንን እንደ መጥፎም እንደ ጥሩም መመልከት ያልቻለ መንግሥት፥ ጊዜውን የሚያጠፋው፥ ለሕዝቡ ሳይሆን ለግሉ ደስ የሚያሰኘውን ሁሉ በማድረግ ነው።

መንግሥት ወያኔያዊ አስተሳሰብን፥ ከመላው የትግራይ ሕዝብ አስተሳሰብ ሳይለይ፥ በጦርነቱም ወቅት ተጎጂዎቹ ኢትዮጵያኖች መሆናቸውን እስኪያጠራጥር ድረስ፥ ሲያጋድለን፥ ሲያጨራርሰን፤ "በዚህም ሆነ በዚያ፥ ክፉዎችን ከክፉ ሥራቸው ቶሎ ይቀጫቸዋል፤ መጥፎ ሥራቸውንም አውግዞ፥ በምትኩ ጥሩውን አስተዳደር በተግባር ያሳየናል" በማለት፥ ከሚገባው በላይ በትእግስት ስንጠብቅ ቆየን። ዳሩ ግን፥ ያቺ ትንሽ የተስፋ ዝናብን ያቀፈች ዳመና በየት በኩል ነፍሳ መቼ እንደምትዘንብልን ስንጠባበቅ፤ ለካስ እርሷም የከፉት እና የጭካኔ፥ የጦርነት እና የእልቂት ዳመና ነበረች፤ በኢትዮጵያ ሥፍራዎች ሁሉ እየተዘዋወረች ሕዝብን ከሕዝብ የምታጨራርስ።

በአንዳንድ ሥፍራዎች ዘር ተኮር ጭፍጨፋዎች ሲካሄዱ፥ መንግሥት ያንን ለማስቆም እየቻለ ምንም እርምጃ አይወስድም፣ ፖለቲከኞችም በፖለቲካ ሳይንስ የተማሩትን ሲያሰላስሉ፥ ኢኮኖሚስቶችም በኢኮኖሚ ስልት፥ የታሪክ ተመራማሪዎችና

---

[35] ከብልጽግና ወንጌል ስብከት ትይዩ፥ ሌሎችም በመተግበር ስላሉ ታላላቅ አለም አቀፍ ውሳኔዎችም በተከታታይ በአንክሮ የምንመለከተው ጉዳይ ይሆናል።

ሌሎችም ተፈላሳፊዎች በዘመናዊው እውቀት አወቅን ያሉትን ከተጨባጭ የሀገር ሁኔታ ጋር ሲያገናዝቡ፥ *የመንፈስን አሠራር ችላ በማለታቸው፥* (አዎ! ችላ በማለታቸው ወይንም ባለመረዳታቸው) ምክንያት፥ በየጊዜው እና በየሰዓቱ የሚያድግ ተንኮል ኢትዮጵያችንን *ታማሚ* - በሽተኛ አደረጋት።

*መንግሥት መጥፎውን እያየ እንዳላየ፤ እየሰማም "ጆሮ ዳባ ልበስ" እያለ፥ የራሱን የብቸኛ ሥራውን ቀጠለ፡- እየተመጻደቀ፥ እየዋሸ፥ እያታለለ፥ እያማለለ፥ እያስመሰለ...።* የአስተዳደሩም ስርዓት በዚያው መጠን፥ ቀስ በቀስ ከመጥፎ ወደ በጣም መጥፎ እየተቀየረ ሲመጣ፥ ኢትዮጵያችን የከፋውን *መንፈስን ዱላ ተሸካሚ ሆነችብን።*

*ዐቢይ አህመድም "የእኔ ትኩረት በልማት ሥራ ላይ ነው፤ ሕዝቡ እርስ በርሱ ይጋደላል፤ እኔ ምን ላድርግ?"* በማለት የችግር መንስኤ እርሱ ራሱ መሆኑን *ሊያዘናጋ* ይሞክራል። "ጨኸቴን ቀሙኝ" እንደሚባለው ሁሉ፥ ብሶትም በመንግሥት ብሶ፥ አግባብ ያለውን ጨኸት የሚያሰሙትን የሕዝቡን ጨኸት ለራሱ አደረገ። አጠቃላይ *የሥራዎቹ* ውጤት የሚያሳየው ግን፥ በኢትዮጵያ እና በሕዝቦቿ የተሠራባቸውን ጥሩ የመሰሉ ክፋቶችን እና ክፉ የሆኑ ክፋቶችን ነው።

ኢትዮጵያችንም የሰው *መገኛ* ምድር ስለሆነች፥ ሁሉን አይነት ሰው ማብቀል ነበረባትና፤ ይኸው! ጉራማይሌ ሰዎችን እና ጉራማይሌ *ሥራዎቻቸውን* ተመለከትን። የሰው የማንነቱ መገለጫ ተክለ ሰውነቱ፥ *ሥጋዊ ገጽታውና* መልኩ ብቻ እንዳልሆነ፤ ውስጣዊ ጠባዩም የማንነቱ መገለጫ እንደሆነ ይታወቃል። ሆኖም፥ ከውጪ የምናያቸው "ሰዎች ሁሉ በእርግጥ ሰዎች አለመሆናቸውን" ባለማወቃችን፤ ሰውም የሰውን ሰብነት (ሰብአዊነት) ማወቅ ተስኖት፥ ይኸው! እርስ በርሳችን ተላለቅን።

ሰው መስሎ በሰዎች መካከል የሚመላለስ ሁሉ ሰው አይደለም። አዎ! በውስጣዊ ተፈጥሮው የሰው ልጅ የሆነ ሁሉ ሰው ሲሞት እና ሲገደል ያዝናል። ሕዝብን ከሕዝብ በማጣላት ደስ የሚለው ቢኖር፥ የእርሱ ተፈጥሮአዊ ማንነት ከሰውእነት (ሰብአዊነት) ውጪ "ሌላ" መሆን አለበት። የሰው ሞት የማይገደውን ሁሉ ሰው መሳይ ሰይጣን ነው ብንል ማጋነን አይሆንም።[36]

---

[36] *"ይህም አያስደንቅም፤ ሰይጣን ራሱ ተለውጦ እንደ ብርሃን መልአክ ይመስላልና። መልክተኞቹም የጽድቅ መላእክትን ቢመስሉ፥ ይህ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜአቸው ግን እንደ ሥራቸው ነው።" 2ኛ ቆሮ. 11፡14፥15*

በሳይንስ፥ ወይንም በማንኛውም ሚዛናዊ ምልከታ፥ “የእያንዳንዱን ሰው እንቅስቃሴ የሚወሰነው፥ ከውጪ ሌላ ልዩ ኃይል ሳይገባበት፥ በግለሰቡ ውስጣዊ ባህሬ ብቻ ይወሰናል” ማለት ይቻላል። ነገር ግን፥ ያ አንድ ሰው - ያ አንድ የሀገር መሪ የአንድን ሕብረተሰብ ወይንም ሀገር አኗኗር እስከ መለወጥ የሚያደርስ ከፍታ ላይ ሲገኝ፤ “ያ ግለሰብ ያንን ሁሉ ኃይል ከየት አገኘው?” ብለን መጠራጠር ተገቢ ነው።

የአለም አህጉራትን ታሪክ ለየት ባለ መንገድ ብንመረምር፥ መንግሥታትም የቆሙለትን አገራቸውን፥ ሕዝባቸውንም ከደው፥ ዘግናኝ እና ኢሰብአዊ ድርጊቶችን እንደሚፈጽሙ ከታሪክ እናውቃለን። ታዲያ፥ በእያንዳንዱ አህጉራት ታሪክ ውስጥ “የእርኩሳን መናፍስት ተሳትፎ አይታጣበትም” ቢባል ስህተት ላይሆን ይችላል። እነኛ ዝነኛ ክፉዎች የሀገር መሪዎች፥ ሁሉም በራሳቸው ጭንቅላት (አስተሳሰብ) የሚመሩ እየመሰላቸው፤ ነገር ግን፥ በእርኩሳን መናፍስት (የውጪ ኃይላት) ፍላጎት እየተመሩ እንዳልሆነስ ማን አወቀ?

የገዛ ሀገሩን የጦርነት አውድማ ከማድረግ አልፎ፥ ሌሎች አገሮችንም ወደ ጦርነት እንዲገቡ ቅስቀሳ የሚያደርግ ኃይል፥ እንቅስቃሴው ሁሉ ከራሱ ብቻ በሚመነጭ ውስጣዊ ባህሬ ይወሰናል ማለት ያዳግታል። የኢትዮጵያችንንም ሁኔታ በዚህ አንጻር ስንመለከት፥ በሀገራችን ውስጥ የተፈጠረው ቀውስ አንሶ፥ ምሥራቅ አፍሪቃን የጦርነት ቀጠና ለማድረግ የሚነሳ መሪ (ቡድን) በዘመናችን ሲከሰት፥ እኛ ሰዎች በመሆናችን ብቻ፥ ከአንድ ግለሰብ (ወይም ቡድን) ውጪ “ሌላ” የማይታይ ቀስቃሽ ኃይል አይኖርብንም ማለት ይከብዳል።

በድብቅ የሚሠራውን ተንኮል - ሰይጣናዊ አሠራር በአለማወቃችን ምክንያት፥ ክፉና ደጉን መለየት እስኪያቅተን ድረስ ተታለልን። አንዳንድ ሰዎችም፥ “ይህ ሰው ክፉም ቢሠራ ደግም ስለሠራ ሊወቀስ አይገባም” በሚሉበት ጊዜ ሁሉ፥ ሰይጣናዊ አሠራሮቹን መሸፋፈናቸው መሆኑን አልተረዱም።

ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚደርሱን መረጃዎች የሚዘገንኑ ሲሆኑ፥ ፖለቲካዊ ትችቶችም እጅግ ከመብዛታቸው የተነሳ ፖለቲካዊ መላሸቅን ሲያስከትሉ፥ ሀገርን የማፍርስ ሴራ ከልዩ ምድራዊ ሃይማኖት ስብከት ጋር ተጣምሮ ሲሰበክ፥ ሀገር አቀፍ መንግሥታዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ፥ አህጉራዊ እና ሃይማኖታዊ ህልውናችንን የሚያሳጣ ሲሆን፤ የዛን ጊዜ፥ የሕዝቦች ማእበል እንደ እሳት ወላፈን ክፉውን እና

ከፋፋዩን መንግሥት ያቃጥለዋል። የዛን ጊዜ፥ የሚፈርሰው ከፋው መንግሥት እንጂ፤ ኢትዮጵያችን እንደማትፈርስ ይረጋገጣል።[37]

ከዚህ ከተጠቀሰው አላስፈላጊ (ግን ችለን የማናስወግደው) ተፈጥሮአዊ እና አካባቢያዊ እሳቤዎች ውጪ፥ ብዙ የሚያውቁ ሰላዮች (መንግሥታዊ ምሥጢር አዋቂዎች) ቢኖሩ፥ እነርሱ እኛ "የማይታይ ቀስቃሽ ኃይል" ያልነውን "በሚታዩ ኃያላን መንግሥታት" በመለወጥ፥ የኛን ምልከታ ከሚታየው ጋር ብቻ ሊያዛምዱት ይችላሉ።

በአንጎል ሰታቴ ወጥ እየተሠራ፥

ጨው እና በርበሬ ሁሉም በየተራ፥

ከሚያጣፍጥ ቅቤ ከቅመሞች ጋራ፥

ክለሳ በዝቶበት ሰታቴውም ሞልቶ፥

ተጎልቶ ሲቀር፥ መንተከትኩ ቀርቶ።

ምድራዊ እውቀቶቻችንም እሳት ሆነው ምግቦቻችንን የማያበስሉ ሲሆኑ፥ "ምንድነው ያልተረዳነው ነገር?" ብለን እራሳችንን እንጠይቅ።

ብዙውን ጊዜ፥ በአለም የታወቁ ፋሺስታዊ መሪዎችም ጥሩ ሰው ከመባል እየጀመሩ፥ ቀስ በቀስ ሲለወጡ፥ ለውጪ ሰዎች ግልጥ እንደሆነ፥ ለራሳቸው አይታወቃቸውም። ከጎናቸው ክፉ መንፈስ ስላለ፥ ሁሉንም በራሳቸው እና ለራሳቸው ማድረግ የሚችሉ ይመስላቸዋል። ሰዎች ሲከዷቸው እና ከማይወጡት አዘቅት ውስጥ ሲወድቁ እና ክፉኛ ሲጎዱ፥ ድንገት ንቅት ቢሉም እንኳን፥ በዛው ደንዝዘው ይቀራሉ እንጂ አይነቁም። የሚነቁም ይኖራሉ። *ነቅተው የሚጸጸቱ፥ እነርሱ ምድባቸው ከሰው ወገን ሲሆን፥ የማይነቁ እና የማይጸጸቱት ግን ምድባቸው ከሰይጣን ወገን ይሆናል* (ምንጊዜውም በኃጢአቱ የማይጸጸት ሰይጣን ነውና)።[38]

---

[37] *"ሰይጣንም ሰይጣንን የሚያወጣው ከሆነ፥ እርስ በርሱ ተለያየ፤ እንግዲህ መንግሥቱ እንዴት ትጸናለች?" ማቴ. 12፡26*

[38] በመንፈሳዊ ተጋድሎዋ ቅድስት የተባለች ኢትዮጵያዊት፥ ክርስቶስ ሰምራ ሰይጣንን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅ ቢቻል የሰው ልጅ ኃጢአት መሥራት ያቆም ነበር ብላ አሰበች። ሰይጣን ግን፥ በጥፋቱ ተጸጽቶ እግዚአብሔርን ይቅርታ የማይጠይቅ መሆኑን፥ እርሷ ባየችው ራዕይ ተገንዝባለች።

**<u>የማይጠገን ጥገና</u>**

ባጠቃላይ፥ ኢትዮጵያችን እየተጓዘችበት ያለችው መንገድ፥ የሕዝቦቿን የጋራ ማንነት (የጋራ ታሪክ፥ የጋራ ባህል፥ የጋራ ቋንቋ...)፥ የጋራ የሆነ ሁሉ እንዲጠፋ የሚያደርግ ስለሆነ፥ ይህንን በተንኮል ላይ የተመሠረተ ስርዓት ለመስበር ሪፎርም (ጥገና) የሚሉት ፈሊጥ በቂ አይደለም፤ ስር ነቀል መንግሥታዊ መዋቅራዊ ለውጥ ያስፈልጋል፤ የጋራ እድገት የሚታሰበው (ዘላቂነትም የሚኖረው) ከዚያ በኋላ ነውና።

ለውጥ ስንል በአብዮት (ሪቮሉሺን) የሚመጣ ለውጥ አለ፤ ጥቃቅን የጥገና እርምጃዎችን በመውሰድ (በሪፎርም) የሚመጣ ለውጥም አለ። አብዮት ተካሂዶም መሠረታዊ ለውጥ ላይመጣ ይችላል። በደንብ ከታሰበበት፥ አብዮት የማያስገኘውንም መሠረታዊ ለውጥ፥ በሪፎርም (በጥገና) ማግኘት ይቻላል። ለዚህ ነበር ሕዝቡ በሀገራችን የተጀመረው (ሊጀመር ያለው) ሪፎርም (ጥቃቅን ለውጥ) መሠረታዊ ለውጥን ያስገኝልናል እያለ በደስታ የሰከረው።

ጥገና ሲባል፥ ሕዝቡ የተረዳው፥ በቅድሚያ አንዳንድ ጥቃቅን፥ ግን የተስተካከሉ እርምጃዎችን በመውሰድ፥ የተበላሸውን ስርዓት ማስተካከል ነበር። ይህ ሳይሆን ቀርቶ፥ የሚወሰዱት እርምጃዎች ሁሉ አሮጌውን እና የተበላሸውን ስርዓት የሚያድሱ፥ ጸንተውም እንዲቀጥሉ የሚያደርጉ ሆኑ።

የቀድሞው በሕዝብ የተጠላው የወያኔ መንግሥት ሲወገድ፥ "ለውጡ ሥር ነቀል ይሆንልናል፤ መሠረታዊ ለውጥን ያመጣልናል.." እያለ፥ በጉጉት ሲጠባበቅ የነበረው ሕዝብ እንደጠበቀው ስላልሆነለት፥ ስሜቱ ከአዎንታዊ ደስታ ወደ አሉታዊ ቅሬታ ተለወጠ። ኢትዮጵያችን ከኢሕአዴግ ያተረፈችው ብዙ ነገር ቢኖር፤ የተበላሸባትም ጥቂት ብቻ ቢሆን ኖሮ፥ ያንን የተበላሸውን ጥቂቱን በመጠገን ኢትዮጵያችንን፥ ቀስ በቀስ ቢሆንም፥ ቀናውን መንገድ በማስያዝ ማሳደግ ይቻል ነበር። ግን፥ ምኑ ይጠገናል የተበላሸ ስርዓት?[39]

መሠረታዊ ለውጥ እናድርግ ሲባል፥ "ይሄኮ! እናንተ መሠረታዊ ለውጥ የምትሉት፥ ደም በማፋሰስ - በሪቮሉሺን የሚመጣ ነው እንጂ፥ እንዲሁ ካለ ውጊያ እና ካለ ጦርነት የሚመጣ አይደለም። እኛ የምንፈልገው ሰላማዊ ለውጥን ነው" በማለት ያወናብዳሉ። "ይጠና፥ ይጠና፥ ይጠና፥..." እያሉ ጊዜ የማይሰጡ አቢይ የሀገር ጉዳዮችን ወደ ጎን ዞር ማድረግ፥ የሕዝቡንም ትኩረት ወደ ሌሎች አናሳ ጉዳዮች ላይ እንዲሆን መገፋፋት ሆነ የነርሱ የፖለቲካ ዘይቤ።

---

39 *"በአሮጌ ልብስ ቀዳዳ ላይ የአዲስ ልብስ እራፊ የሚጥፍ የለም።" ሉቃ. 5፡39*

የጥገና ለውጥ (ሪፎርም) የተባለው ቃል የእውነተኛ ለውጥ ሽፋን እንዲሆን እንጂ፥ ኢሕአዴግ በዘር ላዋቀረው ፌዴራላዊ መንግሥት የተሻለ አማራጭ ለማምጣት የሀገራችን ምሁራን በዓመታት ሳይሆን በወራት የሚያጠናቅቁት የቤት ሥራ ይሆን ነበር። ይህንን ማከናወን ደግሞ መፈንቅለ መንግሥተኝነት ወይንም ሪቮሉሺን አይደለም።

የክፋት ድርጊቶችን ለመፈጸም በታቀደ ቁጥር፥ እጅግ የሚማርኩ ጥሩ ጥሩ ፖለቲካዊ ዲስኩሮችን ሰምተናል። የዛን ጊዜ የነገሮችን አካሄድ ባለመረዳታችን፥ እነኚያም ዲስኩሮች በእርግጥ የክፋት ድርጊቶች መሸፈኛ መሆናቸውን ባለማገናዘባችን፥ ብዙውን ጊዜ ተታለናል።

በሰሜንም ሆነ በምዕራብ ኢትዮጵያ የተቀሰቀሰውን ጦር ማባባስ እንጂ ማርገብ እንዳልተፈለገ በገባን ጊዜ፥ እንዲሁም፥ ጠቅላላ ምሥራቅ አፍሪቃን የሚያጠቃልል ጦርነት የሚቀሰቀስ የክፋት ጥንስሶች መኖራቸውን፥ በየጊዜው ከሚሰበኩ ሰይጣናዊ ስብከቶች እየሰማን ዝም ባልን ጊዜ፥ የእኛም የስሜቶቻችን ህዋሳት ድንዝዝ በማለታቸው ነው እንጂ፥ ገና ከጥንሡም ቢሆን፥ የዚህ መንግሥት ህልውና የተመሠረተው ሕዝቦችን እርስ በርሳቸው በማፋጀት መሆኑ ይገባን ነበር። እንዲህ ያለውን መንግሥት በጥገና ማስተካከል አይቻልም።

ቤተ ክርሲቲያናት ሲቃጠሉ፥ ክርስቲያኖችም ሲገደሉ በደረቅ አይኑ አይቶ እንዳው ዝም የሚል የሀገር መሪ፥ በድርጊቱ የረካ እንጂ፥ የተቆጨ አለመሆኑን እያየን (እያወቅን)፥ "እንዲህ አይነቱ የሀገር መሪ አመጣጡ ከወዴት ነው? የመጨረሻ ግቡስ ምንድነው?" ብለን አለመጠየቃችን፥ የእኛም የስሜቶቻችን ህዋሳት ድንዝዝ በማለታቸው ነው እንጂ፥ የዚህ መንግሥት አላማ ከመንፈሳዊነታቸውም ጋር የተቆራኘውን የኢትዮጵያውያንን ህልውና ማሳጣት መሆኑ ይገባን ነበር። እንዲህ አይነት ሰይጣናዊ አላማ ያለውን መንግሥት በጥገና ማስተካከል አይቻልም።

በምድራዊ ውስብስብ ኩነቶች ምክንያት ኢትዮጵያ አንድ እውነት አጥታለች። ሕዝቦቿም በጋራ የሚመለከቱትና "እውነት ነው" ብለው የሚከተሉት፥ ለመልካም መንግሥታዊ አስተዳደር የሚመች አንድ ወጥ የሆነ ርዕዮት (ርዕዮተ አለም) አላገኙም።

ሀገር ካለ አንዳች ውሱን ርዕዮተ አለም (ideology)፥ በአንድ ወይም ጥቂት ግለሰብ ፍላጎት እና ተለዋዋጭ አስተሳሰብ ብቻ የምትንቀሳቀስ ከሆነ፥ ሕዝቡ መጨረሻዋን መተንበይ ስለሚያቅተው፥ በመሪዎች እና በተመሪዎች መካከል ቅራኔዎች ይፈጠራሉ። በዚህን ጊዜ፥ ሕዝቡም መንግሥትም በሰላም መኖር አይችልም።

ከዚህ ቀደም፥ የአንድ ሀገር ሕዝብ እራሱን በራሱ ለማስተዳደር ይጠቅመኛል (ይሻለኛል) የሚለውን መንገድ የሚመርጠው አስተሳሰቡን ኮሙኒስት፥ ሶሻሊስት፥ ካፒታሊስት፥ ወ.ዘ.ተ. እየተባሉ በሚጠሩት የፍልስፍና ዘርፎች ውስጥ በማካተት ነበር። ለኢትዮጵያችን ፊውዳሊዝም እንዳልበጃት፤ ሶሻያሊዝም እንዳላዛለቃት፥ ካፒታሊዝምን ብትቀምሰውም እንዳልተስማማት፥ ለእርሷ ምድራዊ ፖለቲካ ብቻውን (ካለ መንፈሳዊነት) በቂ እንዳልሆነላት አይተነዋል (አውቀነዋል)።

ከእንግዲህስ፥ ይህቺ ሀገረ እግዚአብሔር የተባለች ኢትዮጵያ፥ የሁሉንም አይነት የምድራዊነት ድፍድፍ እንደቀማመሰች እና እንዳልተስማማት እያወቀች፤ የተሻለውን መርጣ ትጓዛለች እንጂ፥ በዚያው አትቀጥልም።

ርዕዮተ አለም በርዕዮተ ግለሰብ አይተካም። የጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አህመድ አሊ ርዕዮተ አለም ምን እንደሆነ ሳናውቅ እንዲሁ በደመ ነፍስ ተከተልነው። ወደ ጥፋት የሚያመራውን መንግሥታዊ ሂደቱንም እያየን፥ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ ባመነታን ጊዜ፥ የእኛም የስሜቶቻችን ህዋሳት ድንዝዝ ማለታቸውን ያረጋግጣል። ዘግይቶም ቢሆን፥ አሁን ይህንን መንግሥት በጥገና ማስተካከል፤ አብሮ መሥራትም የማይቻል መሆኑን ስለተረዳን፥ ያለን አማራጭ፥ የመንፈሳዊነታችንን ነገር ታሳቢ በማድረግ፥ የተበላሸውን በዘር የተዋቀረ ፌዴራላዊ አስተዳደር ከሥር ከመሠረቱ ገርስሶ፥ በምትኩ ሕዝባዊ መንግሥትን መመሥረት ነው።

**የማያበለጽግ ብልጽግና**

አይኖች ያያሉ፤ ልቦችም ይፈርዳሉ፤ ሕጻናት ጓደኞቻቸውን ይሻሉ፤ እውነት ወደ እውነት ይጠጋል፤ የሚያንጸባርቅ ሁሉ ወርቅ አይደለም። ሕዝብን አንዴ ያሞኙታል፤ ግን፥ ለምንጊዜም እያሞኙ መቀጠል አይቻልም።

አንድን ሀገር በትክክል ለማስተዳደር፥ ከውጪም ቢሆን፥ ከሀገር ውስጥም ቢሆን፥ ያለውን የጥሩ አስተዳደር እሳቤ በማሳደግ፥ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት የሚኖረውን እንድ ወጥ፥ ጥርት ያለ ፍልስፍና መከተል ያስፈልጋል።

በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችል የሀገር መመሪያ (ፍልስፍና) በሚታጣበት ጊዜ፥ ባህር ላይ የተጣለ ኩበት ነፋስ በነፈሰበት አቅጣጫ እንደሚወሰድ፥ ሀገርም በመሪዎቿ ሃሳብና ፍላጎት ብቻ የምትመራ፥ የጥቂቶች መደሰቺያ የብዙዎች መሰቃያ ሥፍራ ትሆናለች። ጥርት ያለ የሀገር መስተዳደሪያ ፍልስፍና በሚጠፋበት ጊዜ፥ እውነትም ውሸትም በአንድላይ እንንገሥ ይላሉ፤ የእውቀትም የድንቁርናም ትምህርቶች ይሰጣሉ። ጥርት ያለ ፍልስፍና በሚጠፋበት ጊዜ፥ እምነትም ክህደትም ባንድነት ቤተ እምነቶች ውስጥ ገብተው ይሰበካሉ። እነኚህ የተጠቀሱት ሁሉ፥ አሁን በኢትዮጵያ በጊዜአችን እየተገበሩ ነው።

የኢሕአዴግ መንግሥት ሕዝቡን አንገፍግፎት ሳለ፥ "አዲሱ" መንግሥት "ብልጽግና" የሚል መርሆ ይዞ ተነሳ። ይህም አንጸባራቂ መፈክር ነው እንጂ፥ ፍልስፍና አይደለም። ይሁን እንጂ፥ እንደ ሀገር መምሪያ፥ እንደ አንድ የፖለቲካ ፓርቲም ይሆን ዘንድ፥ ህዝቡን በማይጨበጥ ተስፋ (ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ) አጠናክሮ የሚይዝበት ሁነኛ ዘዴ፤ የምኞት እና የሃሳብ "እንቁልልጮ" ሆኖ ቆይቷል። እውነታው ግን፥ በኢትዮጵያችን የታወጀው "ብልጽግና" የሚያበለጽግ ሳይሆን፥ የሚያደኽይ ሆኖ ነው የተገኘው።

"ከሀገር ህልውና ይልቅ ብልጽግና ይቀድማል፤ ወይንም ሁለቱንም ጎን ለጎን ማስኬድ ይቻላል" በማለት፥ የብልጽግና ፓርቲ የወሰዳቸው መንገዶች፥ ብልጽግና ረጅም ጊዜ የሚፈጅ፥ የሀገር ህልውና ግን ጊዜ የማይሰጥ መሆኑን ካለመረዳት ይመስላል። መንግሥት ሁለቱንም ጎን ለጎን በማድረግ የሠራቸው አንዳንድ በጎ ሥራዎች ቢኖሩም፥ ቅድሚያውን ለሀገር ህልውና ባለመስጠቱ፥ የእርስ በርሱን እልቂት ማስታገስ አልተቻለም።

ካሁን በፊት ዐቢይ አህመድ "መንግሥታችን የብልጽግናን መንገድ ተከትሎ በትጋት ሲሠራ፥ ሕዝቦችም የብልጽግናን ትሩፋቶች ሲያዩ ወደ አንድነት ይጠጋሉ፤ በመበልጸጋችን ሳቢያ ይቀራረባሉ፣ አንድነትም ይፈጥሩና ሰላም ይወርዳል" በማለት ተናግሮ ነበር። በዚህ ንግግር ውስጥ ብልጽግናን ከአንድነት አስቀድሟል። የብልጽግና

ትሩፋቶች ብሎ በራሱ ምናባዊ አለም ያስቀመጣቸውን ሕዝቦች ተመልክተው ወደ አንድነት ሲያመሩ አልታዩም።

ቅድመ እይታው የተሰናከለ ከሆነ፥ መጨረሻውም እንደዚያው የተሰናከለ ነው የሚሆን። ሕዝቦች አስቀድመው ካልተባበሩ፥ ለጋራ ብልጽግናም አብረው ካልሠሩ፥ ሥጋዊ ተድላና ደስታን አያገኟትም። ከሁሉ አስቀድመን አንድ ላይ ብናስብ፥ ጥሩነታችን ይገለጻል፤ ጥሩነታችን ሲገለጽ ሕብረት ይኖረናል፤ በአብሮነታችን "ለጋራ ብልጽግና" ስንሠራ ነው የምናድገው፤ ከሥልጣኔ እና ከብልጽግና መቅደም ያለበት ሕብረት እና አንድነት ነውና። በከበደ ሚካኤል የተጻፈው "ጃፓን እንደምን ሠለጠነች?" የተሰኘውም መጽሐፍ የሚያመለክተው ይህንኑ ነው። ጃፓኖችም እንደ እኛ በውስጣቸው ባለ ብዙ ብሔሮች ነበሩ። ነገር ግን፥ አንድነታቸውን ከሁሉም ነገር በላይ በማስቀደም አንድ ስለሆኑ እና በሕብረት በርትተው ስለሠሩ በለጸጉ። አስቀድመን እንበልጽግ ቢሉ ኖሮ፥ አብሮ መሥራትን አያውቁበትም ነበር። አብረውም ባይሠሩ ኖሮ፥ እንዲህ ባልበለጸጉ ነበር።

ሰላም እና አንድነት ሳይኖረን፥ የተፈጥሮ ሃብቶቻችንን (ነዳጅ፥ ማእድናት፥ ወ.ዘ.ተ.) እያወጣን ለራሳችን መጠቀም እንደማንችል፥ በኦጋዴን አካባቢ የተደረጉ መለስተኛ ጦርነቶች አሳይተውናል። ከንጉሡ ከኃይለ ሥላሴ ጀምሮ፥ ያንን ተፈጥሮ ያከማቸውን ነዳጅ (ድፍድፍ) "እኛ እናወጣላችኋለን!" በማለት ሲያጠኑ የነበሩ ኩባንያዎች በተለያዩ ምክንያቶች ለቀው ቢወጡም፥ ዋነኛው ምክንያት ግን፥ የአካባቢው ሰላም እጦት ነው። የአካባቢው ሕዝብ ሳይረጋጋ፥ ሕብረት እና አንድነት ሳይኖረው፥ ነዳጁን ቆፍረን እናውጣ እየተባለ በተሞከረበት ወቅት ሁሉ፥ የውጭ ተቀናቃኝ ኃይላት ከውስጥ ተፎካካሪ ኃይላት ጋር ተባብረው ግጭቶችን እያስነሱ፥ በኦጋዴን ውስጥ ብዙሃን ነፍሳት (ኢትዮጵያኖች፥ ቻይናዎችም) ተገድለውብናል።

ቅኝ ገዢዎች በአፍሪካ አህጉራት የሚገኙትን ማዕድናት እየበዘበዙ ሲያወጡ፥ ወደ እኛ ሀገር ገብተው ያልበዘበዙት፥ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ የማዕድን ሃብት ባለመኖሩ አይደለም፤ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት መያዝና ማስተዳደር ስላልቻሉ ነው እንጂ።

ኢትዮጵያ ብዙ ያልተነኩ ማዕድናት አሏት። ያለንን ትንሿን ተካፍለን መብላት ብናውቅበት፥ በስምጥ ሸለቆ ከርሰ ምድር የታመቀ ኃይል (geothermal power) እና በኦጋዴን የተከማቸ ነዳጅ ብቻ፥ ሊያበለጽጉን ይችላሉ፤ ሌሎች እንደ ፖታሽ፥ ፕላቲነም፥ ወርቅ እና መዳብ የመሳሰሉትን ማእድናት ሳንነካ። ስለዚህ፥ ያ የምናስበው ድሎት - ብልጽግና (እድገት) በቅጽበት የማይመጣ፥ ጊዜ የሚወስድ የሶሻልና የኢኮኖሚ ክስተት ያለው ስለሆነ፥ እኛ ከዛ በፊት፥ በፍቅር ሰንሰለት ተሳስረን

ኢትዮጵያችንን በአንድነት ለማሳደግ ስንነሳ ነው የምንበለጽገው። ሀገራችን በአንድነቷ ጸንታ፥ በቅድሚያ አንዲት ኢትዮጵያ ሳትባል፥ አንዲት የበለጸገች ኢትዮጵያ አትባልም።

ከምድር የሚበቅለው የሚሆን በረከት፥
ሲኖሩባትም ደስ የሚላት መሬት፥
ሕዝቦች ሲስማሙ ነው፤ ሲቀድም አንድነት።
ዝናቡም ይዘንባል፤ የተዘራውም ይበቅላል።
የበቀለውም ይመረታል፤ ምርቱም ይዳረሳል።
ብሩም ይከመራል፤ የተከመረውም ይከፋፈላል።
መልካሙን የሚያስብ፥ ያጣውን ያገኛል፤
መጥፎውን የሚያስብ፥ ያገኘውን ያጣል።
ካለ አንድነት - ካለ ሕብረት - ማን ሠርቶ በለጸገ?
ወይንስ ማን ብልጽግናን አስቀድሞ፥ ሕብረትን አስከተለ?
ቃላትም ማባበያ - መለማመጫ፥
ካለ ሕብረትና አንድነት ብልጽግና
ሳይራመዱ ሩጫ።
ሕዝብ ሲያለቅስ - ሲነቀል ከእርስቱ፥
ምን ትርጉም አለው ብልጽግና?
ግንብ ቢገነባ፥ ወርቅ ቢነጠፍ ከመሬቱ፤
ለክብር፥ ለዝና ቢገተር ሃውልቱ፥
የጥቂቶች ደስታ አይሆን ለሞቱቱ።
ምንድነው የመበልጸግ ምሥጢሩ?
በናቡከደናጾር ጣኦት ዙሪያ ግርግሩ።
ከፉ ሰው ቢበለጽግም አይጸድቅም፤
ጻዲቅ ሰው ቢደኸይም አይከፋም፤
ብቻቸውን ያልተፈጠሩ ብቻቸውን አይሞቱም፤
ሃዘን እና ደስታ ነውና የሁሉም።

**<u>የብልጽግና ወንጌል ተልእኮ</u>**

በኢትዮጵያችን ውስጥ መፈጠራችን ለኛ ክብራችን መሆኑን ከታሪክ መጽሐፍት፥ ከመጽሐፍ ቅዱስም ተምረናል። በአንድነት እና በሕብረት፥ በሰላም እና በፍቅር ተሳስረን ለብዙ ዓመታት የኖርንበት ዘመን ሁሉ በሥጋችን ድሆች ቢያሰኘንም፥ በመንፈስ የበለጽግን መሆናችንን ነው የሚያመላክተው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፥ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ላይ አንድ ለየት ያለ ስብከት ተጀምሯል። የብልጽግና፤ ወይም የሃብት፥ የጤና እና የስኬት ወንጌል (Prosperity Gospel) ተብሎ  የሚጠራ መንፈሳዊ ወጥመድ ተጥሎብናል። ይህም በተለይ በክርስቲያን ተከታዮች እምነት ላይ ምድራዊ (ብልጽግናዊ) ምልከታዎችን የሚሰርጽ ስብከት ነው እንጂ፥ እራሱን የቻለ ሃይማኖት አይደለም። በይዘቱ መንግሥት ከሚገለገልበት የብልጽግና ፓርቲ ጋር ተመሳሳይ እሳቤዎች ይኖሩታል። ለደግ ይሁን ለክፉ ባይታወቅም፥ በተለይ በአሁኑ ጊዜ፥ የሁለቱ በጣምራነት መገለጥ ለምን አላማ እንደሆነ ማጤን ያስፈልጋል።

የብልጽግና ወንጌልን የሚሰብኩ፥ የገንዘብ በረከት እና አካላዊ ደህንነትን እንደ አንዱ የመለኮታዊ ሞገስ መገለጫያ አድርገው ይወስዱታል። ድህነትን ከእርግማን፥ ባለጸግነትንም ከመባረክ ጋር በማገናኘት፥ እንደ ምሳሌ የሚጠቅሱት አብርሃም (ዘፍ.12) የበለጸገው ስለተባረከ ነው ይላሉ። ይህ ከእውነት የራቀ ነው። ባለሃብቶች ስለተባረኩ አልበለጸጉም፤ ድሆችም ስለተረገሙ አልደኸዩም።

እጅግ ሃብታም መሆን የሚቻላቸው ሰዎች፥ ጥሩዎች በመሆናቸው እራሳቸውን ያደኸዩ እንዳሉ እናውቃለን። እነኚህም ሃብታሞች የደኸዩት እጅጉን ጥሩ በመሆናቸውና ሃብታቸውን ለድሆች በማከፋፈላቸው ነው እንጂ፥ ስለተረገሙ አይደለም። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ተወልዶ እስኪሞት ድረስ፥ በምድራዊ ሃብት ድሃ ነበር እንጂ፥ ባለጸጋ አልነበረም።

የብልጽግና ትምህርት መሪዎች ጠለቅ ያለ የክርስትና ትምህርት የሌላቸውን ድሆች ተከታዮቻቸውን "ስትባረኩ ትበለጽጋላችሁ" እያሉ በማታለል፥ ከድሆቹ ያላቸውን እየቀሙ፥ እነርሱ ባለጸጎች ሆነዋል።

*"አእምሮአቸው የጠፋባቸውና ከእውነት የራቁ፥ መልካም አምልኮን መናገኛ የሚያደረጉ አሉ፤ ከእነዚህ ራቅ።" 1ኛ ጢሞ. 6፡5*

መጽሐፍ ቅዱስ ሕይወታችን ሃብትን በማሳደድ ላይ እንዳያተኩር ያስጠነቅቃል እንጂ፥ አትበልጽጉ አይልም። ሆኖም፥ የሰው የእምነቱ አላማው ምድራዊ ብልጽግና ከሆነ፥ ይህ ከምናውቀው የክርስቲያን ሃይማኖት ጋር የሚጋጭ ከመሆኑም

በላይ፥ እንዲህ ያለው እምነት የአለምን ሕዝብ ወደ ምድራዊ ስግብግብነት በመለወጥ፥ መጨረሻው ለሰይጣን ተገዢነት ማመቻቸት እንደሚሆን ይገመታል።

*“...እንግዲህ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።” ማቴ. 6፡24*

ብዙውን ጊዜ፥ ሰዎች ጥሩዎች ሲሆኑ በንግድ ሥራም ሆነ በሌሎች ሥራዎች፥ ነገሮች ይስተካከልላቸዋል፤ ከዚያም ሃብት እና ንብረትን ለማከማቸት ይቀላቸዋል።

*“እናንተስ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት፥ ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።” ማቴ. 6፥33*

አዎ! ጥሩዎች ስንሆን፥ ለነፍሳችን ደስታ እንደሆነ፥ ለሥጋችንም እንዲሁ ሊሆን ይችላል። ሆኖም፥ የመንፈሳዊነት አላማው ጥሩ በመሆን ለመበልጽግ አይደለም። እኛ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም የምንፈልገው፥ በምድር ኑሮአችን ለመበልጸግ ብለን አይደለም፤ መንግሥተ ሰማይን ለመውረስ እና ከእግዚአብሔር ጋር ለዘለአለም ለመኖር ነው እንጂ።

*“...ሂድና ያለህን ሁሉ ሽጠህ ለነዳያን ስጥ፤ በሰማይም መዝገብ ታገኛለህ፤ መጥተህም ተከተለኝ።” ሉቃ. 18፡22*

በዚህች ምድር ላይ የሚበለጽጉ ግለሰቦች ጥሩዎች ብቻ አይደሉም፤ መጥፎዎቹም ይበለጽጋሉ። የብልጽግናው አይነት ግን ይለያያል። የመጥፎዎቹ ብልጽግና መጨረሻው አያምርም (በሃዘን እና በመከራ ሊገባደድ ይችላል)። የጥሩዎች ብልጽግና ግን፥ በግልጽ ላይታይ ይችላል እንጂ፥ መጨረሻው መጥፎ አይሆንም።

የብልጽግና ወንጌል ስብከት የጌታችንን እና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት መሸፈኛ፥ የኋላ ኋላ አለምን ለመግዛት ያመች ዘንድ፥ ተስተካክሎ የተቀመጠ ይመስላል።

*“ዕወቁ፤ ከቅሚያ ሁሉ ተጠበቁ፤ ሰው የሚድን ገንዘብ በማብዛት አይደለምና....።” ሉቃ. 12፡15*

በኋለኛው ዘመን ስለሚደርሰው ክፉ ነገር፥ ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ቀባጣሪዎች፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ወ.ዘ.ተ. እንደሚሆኑ በመዘርዘር፥ *“የአምልኮት መልክ ያላቸው፤ ኀይሉን ግን ይክዱታል፤ እንደ እነዚህ ያሉትን ራቃቸው።” 2ኛ ጢሞ. 3፡5* በማለት፥ ሐዋሪያው ጳውሎስ በውጪ ጥሩ መስለው በክፉ አላማ የተነሳሱትን እንድንርቃቸው ይመክረናል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፥ በአሜሪካ የተጀመረው “የብልጽግና ወንጌል” ስብከት ተሞክሮ፥ መጠነኛ ስኬትን በማስገኘቱ ምክንያት፥ ወደ ሌሎች አለማትም ተዛመተ

እንጂ፥ ይህ የማሳሳቺያ ዘዴ በክርስቲያኖች አለም (በካቶሊክ፥ በኦርቶዶክስ፥ በፕሮቴስታንትም ጭምር)፥ የተጠበቀውን ያህል ቅቡልነትን አላገኘም።

አሜሪካ አያሌ ሃብታሞች የበዙበት ሀገር እንደመሆኑ መጠን፥ የድሃውም ሕብረተሰብ ኑሮ በአንጻራዊነት ሲታይ እጅጉን ዝቅተኛ እንደነበር፥ አሁንም እምብዛም ተጨናቂ የበዛበት ሀገር ነው። በታሪክ እንደምናውቀው፥ የዚህን ዝቅተኛ የሕብረተሰብ ክፍል በመንፈስ አቅፎና ደግፎ፥ መንፈሳዊ ብርታትን ሰጥቶ የሚያጽናና ትምህርት ለብዙ ጊዜ አላገኘም ነበር አሜሪካ። ምንም እንኳን የካቶሊክ፥ የኦርቶዶክስ እና የአይሁድ ሃይማኖቶች ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ከቅኝ ገዢዎች ጋር አብሮ ቢገባም፥ ወደ ዝቅተኛው የሕብረተሰብ ክፍል ዘልቆ አልገባም ነበር።

በ19 እና 20ኛው ክፍለ ዘመን ነበር የፕሮቴስታንት ሃይማኖት በአሜሪካ የተስፋፋው። ሃይማኖቱ በሕብረተሰቡ ውስጥ ሥር ባይሰድም፥ ድሃው ሕዝብ በጥቂት የሃይማኖት መሪዎች (በተለይም በባፕቲስቶች) እየተሰበከ፥ ከምድራዊ ችግሮች ባሻገር፥ መጠነኛ መጽናናትን፥ ተስፋ እና መንፈሳዊ ንቃትን ሳያገኝ አልቀረም።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፥ ለዚህ በሥጋ ለተጎሳቆለ ሕዝብ እስከ ዛሬ በተሰበከበት በእምነቱ ላይ እንደ አንድ ማጣፈጪያ (ከምግብ በኋላ እንደሚቀርብ ኬክ አይነት) ስብከት ተጨምሮለታል። ይህም በአሜሪካ ታዋቂያን የብልጽግና ወንጌል ሰባኪዎች የሚባሉት (Osborn, Joel Osteen, Creflo Dollar, Kenneth Copeland, etc.)፥ በኢትዮጵያም ታዋቂያን የብልጽግና ወንጌል ሰባኪዎች የሚባሉት (ታምራት ታረቀኝ፥ ኢዩ ጩፋ፥ ዮናታን አክሊሉ፥ ወ.ዘ.ተ.) ሁሉም፥ የፕሮተስታንት ሃይማኖትን ተገን በማድረግ፥ በብዛት የሚሰብኩት የብልጽግና ወንጌልን ጽንሰ ሃሳብ በመከተል ነው። ከነኚህም አንዱ፥ “የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ለሁለት ትከፈላለች፤ ይህንን የማምንበት ኢየሱስ ክርስቶስ ነግሮኛል...” ብሎ በሃሰት ለማሳመን የሞከረ ነው።[40]

በአለም ዙሪያ ከሚሰበኩ ሃይማኖቶች መካከል የአብዛኛዎቹ አላማ የሰማይን መንግሥት ለመውረስ ስለሆነ፥ ይህንን አላማ በእጅ አዙር ጠምዝዞ፥ ወደራሱ አላማ (ወደ ምድራዊ መንግሥቱ) ለማስጠጋት ሰይጣን ተግቶ ይሠራል፡- “የእናንተ ሃይማኖት ለምድራዊ አለማ ማሳኪያ ቢሆንስ ምን አለበት?” በማለትም፥ እያደገ በመምጣት ላይ ባለው የክርስቲያኖች እምነት ላይ መንፈሳዊ እይታዎቻቸውን እያዛባ፥

---

[40] *“ወንድሞቻችን ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፤ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኛ ነቢያት ወደ ዓለም መጥተዋልና።” 1ኛ ዮሐ. 4፡ 1*

በምድራዊነት ይበርዘዋል። በተለይም፥ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ምድራዊ ፍላጎት እየጨመረ ሲሄድ፥ "የብልጽግና ወንጌል" ግልጋሎቱ እና የመጨረሻ ግቡ የሰይጣንን መንግሥት በምድር ለማመቻቸት መሆኑ አይቀርም።

በብልጽግና ወንጌል ሰባኪዎች የሚሰብኩ ሰዎችም፥ ምናልባት ለሰይጣን የመጨረሻ ግቡ መጠቀሚያ እየተደረጉ መሆናቸው አልገባቸውም። አንዳንድ ብርቱ እምነት ያላቸው ፕሮቴስታንቶች ግን፥ እንዲህ ያለው እምነት ኃላፊነት የጎደለው፣ ጣዖት (ገንዘብ) አምልኮን የሚያበረታታ እና ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር የሚቃረን መሆኑን፤ በብዙ ክርስቲያኖች ዘንድም ተቀባይነት እንደሌለው ያስረዳሉ፤ በብልጽግና ወንጌል ሰባኪያን እየተመሩ፥ አብረዋቸው የሚከንፉ የዋሃንም፥ ረጋ ብለው ቢያስተውሉ እንደሚሻል ያስገነዝባሉ።

የብልጽግና ወንጌል ስብከት ለሰው ልጅ ምድራዊ ድሎቱ የሚጠቅመው ቢሆን፥ ይህ ምንም ክፋት የለበትም። ሆኖም እንዲህ ያለው ስብከት ቋሚውን እና መደበኛውን ሃይማኖታዊ ስብከት ሊተካ (ሊሸፍን) ሲቃጣ፥ ተደጋግሞም ሲሰበክ፤ በሰዎች አእምሮ ምኞታዊ ድሎትን እየሰረጸ፥ ቀስ በቀስ የሰው ሃይማኖቱ በምድራዊነቱ ላይ ብቻ የሚያተኩር እንዲሆን የሚያደርግ፥ እግዚአብሔርም ባለጸጋዎችን እንጂ ድሆችን እንደማይወድ ሲያስመስል፤ እንዲህ ያለው ስብከት፥ ሰይጣን የሚነግሥበትን ምድራዊ መንግሥት ለማስተካከል ከሚዘጋጁ "ከሌሎች" ቅድመ ሁኔታዎች ጋር አብሮ እንዲደመር፥ በተለይ በዚህ ዘመን ተፈልጎ የመጣ እንዳይሆን ያሰጋል።[41]

እንዲህ ያለውን ምድራዊ ጉጉትን ፈጣሪ የብልጽግና ወንጌል ትምህርት የቀደሙ ፖለቲከኞች አልተጠቀሙበትም፤ የሃይማኖት አባቶችም የሚያውቁት ወይንም የሚያስቡት አይነት አይደለም። ሆኖም፥ በየሃይማኖት ተቋማት ውስጥ እንደሚሰበክ ሁሉ፥ ወደ ቤተ መንግሥትም እንደገባ፥ ፓርላማ ውስጥም ተንሰራፍቶ ፖለቲካዊ ይዘቱን የሚከውንበት መድረክ እንዳገኘ፤ ይህንን እናውቃለን።

በአለማችን ላይ ምሥጢራዊ ሂደቶች እንዳሉ ይገባናል። እኛም በግላጭ የሚታየውን እናያለን፤ ሥውር ሥራውን ግን በምድራዊ አይን ብቻ ማየት አይቻልም።

የብልጽግና ወንጌል (Prosperity Gospel) ከቤተ መንግሥት ገብቷል በማለት የጻፉ አሉ። ለምሳሌ፡- "It comes as no surprise, given the origins of Abiy Ahmed's rise to power, that the gospel of

---

[41] በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱትንም (አለም አቀፋዊ የሥርዓተ - ፆታ ትምህርት፤ የሰው ልጅ በራሱ ፈቃዳዊ ፍላጎት ጾታውን እንዲወስን፤ የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ፥ የሌዝቢያን እና ግብረ ሶዶማውያንም መንግሥታዊ እውቅና ማግኘት፥ ወ.ዘ.ተ.) ከዚሁ ጋር አብሮ ይመለከቷል።

prosperity is being used to mobilize Ethiopians to join his new political party."[42] ሲተረጎም፡-

*"የብልጽግና ወንጌል ለዐቢይ አህመድ ወደ ሥልጣን መምጣት እንደ መነሻ የሆነለት እንደመሆኑ፥ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር ወደ አዲሱ የፖለቲካ ፓርቲው እንዲቀላቀሉ ለማድረግ የተጠቀሙበት መሆኑ ምንም አያስደንቅም።"*

ይህ የብልጽግና ወንጌል፥ እስከዛሬ ያልነበረ፥ በዘመናችን በከፍተኛ ፍጥነት በአለም በመስፋፋት ላይ ያለ፥ ወደ ቤተ መንግሥትም እየገባ እንደ አንድ መንግሥታዊ መርሆ የመቆጠሩ ነገር አሳሳቢ ነው።

ቀደም ሲል፥ የሰው ልጅ ነጻ በሆነ ግላዊ አስተሳሰቡ እና አንደበቱ ሁሉንም እንደፈለገው ሊቀያይረው እና ለራሱ (ለግሉ) ተስማሚ ሊያደርገው ይችላል - መጥፎ የተባለውን ሁሉ፥ እርሱ ጥሩ ነው ካለው ጥሩ ይሆናል የሚል ዘመን አመጣሽ ፍልስፍና በአለም ዳርቻዎች ሁሉ እየተሰበከ መሆኑን ጠቅሰናል። እንዲህ ያለው ምልከታ፥ ከዚሁ የብልጽግና ወንጌል ስብከት ጋር የሚዛመድ፤ እውነታውን እየካዱ ደስታን በምናብ አለም ውስጥ እንደ መፈለግ የሚቆጠር መሆኑን አንባቢ ይገነዘባል።

ከትንሽ እስከ ትልቅ ሰይጣናዊ ተንኮል፥ አይነቱና ስልቱ ይቀያየራል እንጂ፥ የማያቋርጥ ክስተት ነው። ጥቂት ፈሪሳውያን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲገደል እንደ መከሩ[43]፣ ከጌታችን ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መሃል አንዱ ይሁዳ የተባለ ሌባ እና ሰላይ ስለሆነ፥ ጌታችንን እንዳስያዘው፤ በአለማችን ላይ (በኢትዮጵያችንም ላይ) ይህንን የመሳሰሉ የተንኮል ድርጊቶች ይደጋገማሉ። እኛ ግን፥ "ለእንዲህ አይነቱ ድርጊት ምን ምስክር ይገኛል?" እያልን ጥያቄ እናበዛለን።

ክርስቶስን ለመግደል የተጠመደ ሰይጣናዊ ተንኮል በዚያ ያበቃል ብሎ ማሰብ ከንቱ ነው። "ከእርኩሳን መናፍስት ጋር የተስማሙበት፥ እርስ በርስ የተማማሉበት ምን "ሰነድ" አለ? ብሎ መጠየቅም ሞኝነት ነው። ይልቅስ ተንኮል መኖሩን አውቆ መዘጋጀት ነው የሚሻለው፤ ወጥመድ ውስጥ ከመግባት።[44]

---

42 http://aigaforum.com/article2020/The-Prosperity-Gospel-Comes-to-Ethiopia.htm

43 *"ጌታችን ኢየሱስንም በተንኮል ይዘው ይገድሉት ዘንድ ተማከሩ።" ማቴ.* 26፡4

44 *"ከብዙ ቀንም በኋላ አይሁድ ሳውልን ይገድሉት ዘንድ ተማከሩ. ሳውል ግን፥ ሊያደርጉ የሚሹትን ዐወቀባቸው፤ ሊገድሉትም በቀንና በሌሊት የከተማውን በር ይጠብቁ ነበር። ደቀ መዛሙርቱም በሌሊት ወሰዱት፤ በቅርጫትም አድርገው በቅጽሩ ድምድማት ላይ አወረዱት።" ሐዋ. 9፡ 23 - 25*

አለምን ለመቆጣጠርና ለመግዛት የሚቻለው፥ በዚህም ሆነ በዚያ፥ የአለም ሕዝብ ወደ አንድ አይነት አመለካከት በማስጠጋት ስለሆነ፥ የብልጽግናን ንድፈ ሃሳብ ከመንግሥታዊ አመራር ጋር በማመሳጠር፥ አንዳንድ ቁልፍ የሆኑ አህጉራትን መቆጣጠር እንደተፈለገ ይገባናል። በተለይም፥ የሦስተኛ ሀገር መንግሥታት የሚመሩት ሕዝብ በአብዛኛው ድሃ ስለሆነ፥ ይህ የብልጽግና ወንጌል ስብከት፥ ለእነርሱ (ለሀገር መሪዎች) ሕዝቡ በኢኮኖሚ ተጽእኖ ሲጎዳም፥ ጥሩ ጥሩውን ብቻ እያሰበ፥ እንዳያምጽና ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛላቸው ይረዳቸዋል። በአለም አቀፍ ደረጃም ስናስተውል፥ ከላይ ከላዩ ለፖለቲካ ማሳመሪያ የሚታየው ለውጥ ብቻ አይደለም እጅጉን የሚያሳስበው። ይልቁንም፥ በብልጽግና ወንጌል ስብከት በኩል የሚመጣ የአሳሳቹ መንፈስ ሥራ በዚህ ከቀጠለ፥ ለወደፊት በቤተ ክርስቲያናችን ተከታዮች የእምነት መንገድ ላይ ሌላ የመንፈሳዊ እድገት እንቅፋት ሊሆን ይችላል። ፍቅረ ነዋይነት የብዙዎችን መንፈሳዊ ባህሪ የሚያሳጣ፥ ወደ ሥጋዊ ምድራዊነትም የሚመራ እንደሆነ ሁሉ፥ የብልጽግና ወንጌል ስብከትም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው።

የጥፋት መላእክት ከሰማይ ወደ ምድር በመውረድ የአጠቃላይ የሰዎችን ተፈጥሮአዊ እድገት በእነርሱው የጥፋት ጎዳና እንዲታጠፍና እንዲያድግ ቢያደርጉም፥ እንዲህ አይነቱን "ምድራዊ ሥልጣኔ" ሳትቀበል በራሷ ተፈጥሮአዊ እድገት ውስጥ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ስታድግ የነበረች ኢትዮጵያችን፥ አሁንም በመንፈሳዊነቷ አጥብቃ የያዘችውን የፍልስፍና፥ የእውቀት፥ የጥበብ፥ የእውነት እና የእምነት መንገድ ጨርሶ ለማጥፋት፥ በ"ብልጽግና" ስም በሀገራችን ሰርጎ የገባውን ታላቅ የጥፋት መላእክት (መናፍስት) ሴራ በቀላሉ ከተመለከትነው መዘዙ ብዙ ሊሆን ይችላል።

ሀገራችን የጦርነት አውድማ ሆና የሕዝቦች እልቂት ከቀን ወደቀን ሲጨምር፥ አምላካችን እንዲታረቀን፥ በተደጋጋሚ የምህላ ጸሎት የምታደርግ ቤተ ክርስቲያናችን፤ ለዘመናት የተጸለየላትም ሀገራችን ከብዙ የውጣ ውረድ መንፈሳዊ ጉዞና ተጋድሎ በኋላ፥ የአለም ሕዝብ የጎደለበትን መንፈሳዊነትን የምታጠናክር፥ ለሌሎች አገሮችም በምሌነት የምትቀጥል ትሆናለች እንጂ፥ እንዲህ ተዋርዳ አትቀጥልም። ለዘመናት ሲቀደስባቸው የቆዩ ቤተ ክርስቲያናትም፥ ከኢትዮጵያ ምድር እና ከሕዝቡ ተነጥለው ስለማይታዩ፥ ጠላት ሲያቃጥላቸው እነርሱ በዝተውና ደምቀው ይታያሉ። ቅዱስ ሀገር እና ቅዱስ ሕዝብ አይለያዩም።[45]

[45] *"እግዚአብሔር አምላኩ የሚሆንለት ሕዝብ ብጹእ ነው፤ እርሱ ለርስቱ የመረጠው ሕዝብ።" መዝ. 32፡12*

የኢሕአዴግ መንግሥት ሕዝቡን አንገፍግፎት ሳለ፥ "አዲስ" የተባለ፥ ግን በአሠራሩ ከቀድሞው ያልተለየ (እንዳውም የባሰ) መንግሥት መጣለት። የዚህ መንግሥት አሠራሩ አንዳንዴ መልካም ይመስላል፤ አንዳንዴም ሰይጣናዊ ይመስላል። መልካም ቢመስልም፥ ጥቂት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተከታዮችን ጠለላ በማድረግ፥ ጥቂት የሙስሊም ሃይማኖት ተከታዮችንም ድጋፍ በመሻት፥ የእውነተኛ ፕሮቴስታንቶች ተከታይም በመምሰል፥ የብዙሃኑን እምነት ሊያጠፋ፤ ሃቀኛ አማንያንን ከአላማቸው ለማሳት፥ የእምነታቸውንም አቅጣጫ ወደ ምድራዊ ብልጽግና ለመመለስ እንደተነሳ እናስተውል።

የሰው ልጅ በጊዜ ውስጥ፥ በሥጋዊ ዝግመተ ለውጥ እያደገ፤ በአስተሳሰቡም እንደሚረቅ፥ በዛውም ትይዩ በመንፈሱም ርቅቅ እያለ እንዳይሄድና፥ ምድራዊ ምልከታውን በመንፈሳዊነት እየቀየረ፥ ከቁጥጥሩ እንዳይወጣበት ሲል፥ ሰይጣን የማይጠቀመው ዘዴ የለም። ስለዚህ፥ የሰውን ልጅ በመንፈሱ ቅጭጭ እያለ፥ በሥጋዊ ትሩፋቶቹ ላይ እንዲያተኩር ለማድረግ ሲል፥ ይህንን መጥፎ የማይመስል፥ በውስጡ ግን መንፈሳዊ አቅጣጫን የሚያስት የብልጽግና ወንጌል ስብከት ማሰበክ ጀመረ።

ይህ የብልጽግና ወንጌል ስብከት አላማው ከምድራዊ አለም ማስወጪያ የሆኑ ቤተ እምነቶቻችንን መልሰው ወደ ምድራዊ አለም የሚከቱ ማድረግ፥ መንፈሳዊ አቅጣጫን ማሳት፤ መንፈሳዊ አንድነታችንን ማላላት፥ መንፈሳዊ ማንነታችንን መቀየር፥ መንፈሳዊ ህልውናችንንም ማሳጣት ስለሆነ፥ ሰዎች የዚህን ጣፋጭ መርዝ ውጤት ሳይቀምሱት ቢያውቁት ይሻላል።[46]

አሁን እና ለወደፊትም፥ ተመሳሳይ ጣፋጭ መርዞች በተለያዩ የማህበረሰብ አውታሮች ይሰራጫሉ፤ አላማቸውም አንድ ነው - የሰው ልጅ በኑሮው ግላዊ፥ በአስተሳሰቡም ምድራዊ ሆኖ እንዲቀር ማድረግ። በዚህ በተንኮለኛ አለም ውስጥ የኛ አዎንታዊ የዋህነት ከጊዜው ጋር አይሄድም (አያዋጣም)።[47]

በግልጽ ከሚታየው አሽብራቂ ኩነቶች ትይዩ፥ በሙታን ብዛት የበለጸገች ሀገራችን፥ ደስ ለምታሰኛቸው ደስ የምታሰኝ፥ ለምታስከፋቸውም እንድታስከፋ ሆና የተቀመጠች የእርኩሳን መናፍስት ላቦራቷር መስላለችና፤ ጊዜአችንን በጊዜአዊነት

---

[46] *"እነዚህን ከዚህ አስወጧቸው፤ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት!" አላቸው።" ዮሐ. 2፡16*

[47] *"እነሆ እኔ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ፤ እንግዲህ እንደ እባብ ብልሆች፥ እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ።" ማቴ. 10፡16*

ከምናጠፋ፥ የወደፊቱን አይተን፥ መጪው ትውልድ በከፋው እንዳይደናቀፍ ለማድረግ እንትጋ።

በጊዜ ውስጥ ሊሰበክ የመጣው እና ለወደፊትም የሚሰበከው በአለፉት ዓመታት ከተሰበኩት ጋር ሲወዳደር በእጅጉን የመጠቀ ሊመስል ይችላል። በጊዜ ውስጥ አለመራመድ ኋላ ቀርነት ወይንም ሞኝነት አይደለም። እግዚአብሔር ከእርሱ ሥር የሚሰግዱትን ለመበተን ቆርጠው የተነሱትን ዝም እንደማይላቸው ማወቅ ይገባናል። ስለዚህ፥ እኛም ንቅት ብለን፥ መጪውን ትውልድ እንዲታደግ እግዚአብሔርን በጸሎት መማጸን ይገባናል።

የሥጋ ፍላጎት መጨረሻም የሌለውና የማይገታ ነውና፤ የመበልጸጋችንን ጥግ ብናስበው የምናተርፈው ከንቱ ምኞትን እና በኑሮ አለመርካትና ብስጭትን ይሆናል። ስለ ነፍሳችን ስናስብ ደግሞ፥ የሥጋ ፍላጎት ይቀንሳል። የሥጋ ፍላጎት ሲቀንስም "ያለን ይበቃናል" በማለት በደስታ እና በምስጋና እንኖራለን። የቱ ይሻላል?

አንድ ሳይንሳዊ መላምት መሥራት አለመሥራቱ በላቦራቷር ይሞከራል፤ አልሠራ ሲል፥ ይተውና ሌላ መላምት ይጠነሰሳል፤ እሱም በላቦራቷር ይሞከራል። በተመሳሳይ፥ በኢትዮጵያ ሕዝቦች ላይ ያልተሞከረ የለም። እውነትን ጨብጣ የማትለቅ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ላይም፥ እርሷን ለማፍረስ (ብሎም ኢትዮጵያችንን ለማፍረስ) ብዙ ተሞክሯል፤ እንደታሰበው አልሆነም። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን ማንም ምድራዊ ኃይል አይነቀንቃትም፤ ማንም ሕግጋቷን እና ስርዓቷን ሊያናጋ አይችልም።

የኢትዮጵያን ሕዝቦች ሥጋዊ እና መንፈሳዊ አንድነት ለመከፋፈል የተጠነሰሰውን የከፋ መንፈስ ሴራ፥ አዝማሚያው እና ሂደቱንም ለመረዳት፥ እንደ ጊዮን ወንዝ ኢትዮጵያን የከበባትን ጦርነት፤ ያስከተለውንም እልቂት መመልከቱ ይበቃል። ከእርስ በርስ ግጭቶች እና ጦርነቶች የሚያተርፈው ማነው? ነጋዴ ለትርፍ እንደሚሠራ፥ ከሰዎች እልቂት የሚያተርፍ፥ ደም ቀለቡ የሆነ ሰይጣን ነው።

በጊዜው ማወቅ ያለብንን ብናውቅ ኖሮ፥ እራሳችንን ከእልቂቶች እና ጥቃቶች ለመከላከል እንትጋ ነበር። ከአሁን በኋላም ቢሆን፥ ከእውነተኞች የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች ጎን የብልጽግና ወንጌል ሲሰበክ፥ ከቤተ መንግሥትም ሰርጎ ሲገባ፥ ይህንን እንደ ባለ ሁለት ስለት ሰይፍ በመቁጠር፥ የሕዝቡን ምድራዊ እና ሰማያዊ ህልውና በማሳጣት የሚጠቀመውን ዲያቢሎስን በእግዚአብሔር ኃይል እንደምንረታው አንጠራጠር።

ለትግልም መድረኩን ሳያገኝ የቆየው፥

አይናከስ ነብሩ፥ አይባላ አንበሳው፥

እንዳው ጩኸት በዝቶ እንጂ'ኮ ነው፤
ትንሽ ለውጥ የመጣው፤
ማነው? "ይኼ ለውጥ የኔ ነው፤ ይኼ ለውጥ የኔ ነው"
እያለ የፎከረው - በሕዝቦች ቁስል ላይ እንጨት የሰደደው።
ይህንን ትውልድ ያመከነ የመሰለው፥
አልቻለም ሊያቸንፈው፤
ጧፉም እንደበራ ነው የሚቆየው፤
ማንም አይችልም ሊያጠፋው።
እርሻ ጦሙን ሲያድር፥ ምድሪቱም ሰው አልባ፥
ቄሱም ሼኩም ሲሄድ፥ ቀሪው ሰው አነባ።
አይዞሽ ኢትዮጵያዬ አትዘኚ በጣም፤
ክፉ ሰው ቢከዳሽ፥ ጥሩ ሰው አልጠፋም።
አልታረም ያለ ትልቅ ሰው በከንቱ፥
ጊዜ የከዳ ለት ይጨልማል ቤቱ።
*በኢትዮጵያችንም የፈሰሰው፥*
*የራሄል እንባ ምላሽ አለው።*
የሰይጣን በርጩማ አትሆንም ምድራችን፤
ሰላም፥ አንድነትን ያገኛል ሕዝባችን።
ጽኑ ነውና በእምነቱ፥ ፍጹም ነውና ሃይማኖቱ፤
መስቀሉ ነውና ኃይሉ፥ ጸሎት ነውና ብርታቱ።[48]

[48] አዎን! እግዚአብሔርን በማመን እቀጥላለሁ፤ እሱ ነው የሚቀረኝ፤ የሚሻለኝም እሱ ነው። Oui, je persiste à croir en Dieu. C`est tout ce qui me reste. Et c`est encore le meilleur. (Francine Dufresne)

# ምዕራፍ አስራ አንድ

## የሕብረተሰቡ ጭንቀት እና የብኸርታ ዘመን

የሕዝቦች የስሜቶቻቸው ግለት ከኢትዮጵያችን መጻኢ ጋር ስለተቆራኘ፥ በቀላሉ የማይበርድ ሆነና፤ ስለ መንግሥት ጉዳይ መጨነቅ፥ ማውራት፥ መከራከር እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ግዴታ ተቆጠረ። መንግሥት በተለወጠ ቁጥር፥ ሕዝቦችም በመኖር ወይም በአለመኖር አጣብቂኝ ውስጥ ሲገቡ፥ ስነ ልቦናዎቻቸው ይቀያየራሉ፤ ጠባዮቻቸውም በዛው መጠን።

እኛም ፖለቲካዊ ድንቁርና ሳይኖርብን፥ ገብቶን እንዳልገባው ስንሆን፥ የሚያሳዝን፥ የሚሰቀጥጥ ወሬ ሰምተንም ችላ ብለን ስናልፍ፥ የቀን ተቀን ኑሮአችንን ለሟሟላት ስንዋከብ፤ የመኖር መብታቸውን ተገፈው፥ ከሞት አፋፍ ላይ የደረሱትን ወገኖቻችንን ግን መርሳት አልቻልንም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአጥናፍ አጥናፍ ሃዘን ውስጥ ቢቀመጥ ደንታ የማይሰጠው መንግሥት እየመራን ሳለ፥ ሰው እና ሰው የማይተዋወቅበት ወቅት ላይ መድረሳችን  በውስጥ በመንፈሳችን እየጸጸተን፥ የእራስ ምታት ሆነብን እንጂ።

አንዳንድ ጊዜ፥ የአንድነትን መንገድ የሚያሳዩ የሚመስሉ፥ እጅግ  በሳል ንግግሮችን ስንሰማ፥ በሌላም ጊዜ፥ እጅግ የወረዱ፥ ከፋፋይ ንግግሮችን ስንሰማ፥ በዚችው በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ የሚተገበሩትን የክፉና የደግ ሥራዎች መገለጫ የሆኑትን ትእይንቶች - አንዱን ከሌላው (ክፉውን ከደጉ) ለያይቶ መመልከት እስኪያቅት ድረስ፥ "የከፋፍሎ አገዛዝ ምሥጢር" ሳይገባን፥ በዝብርቅርቆሽ አለም ውስጥ ቆየን። ዘመኑ የብኸርታ ዘመን ሆነብን።

የኢትዮጵያችን ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን እጅግ የሚያሳስብ እየሆነ ሲመጣ፥ ሕብረተሰቡ በሃሳቡ እረፍት ሲያጣ፤  በተለይም በትረ መንግሥቱን የያዘው ባለ ሥልጣን እጅጉን ግራ የሚያጋባ በመሆኑ፥ ስለ ሰውዬው ወሬ ከተነሳ፥ የእርሱ ጉዳይ ባልና ሚስት፥ አባትና ልጅ፥ ወንድምና እህት፥ ጓደኛ ለጓደኛ የሚያጨቃጭቅ ሆነ። በዚህም ምክንያት የአጠቃላይ ሕብረተሰቡ የእርስ በርስ ግንኙነቶች ከቀን ወደቀን እየሻከሩ ሲመጡ፤ ልክ እንደተፈራው የኮሮና በሽታ፥ አንዱ የሌላውን ሃሳብ እየፈራ፥

እንደ ወትሮው ለሳቅና ለጨዋታ ጊዜ መስጠት፥ መጠያየቅ እና መተሳሰብ እጅጉን እየቀነሰ መጣ።

ቅራኔዎችም እጅጉን ሰፍተው፥ ትዳር ያላቸው እስከመፋታት፥ ጓደኛማቾችም ተኮራርፈው እስከመጣላት ሲደርሱ፥ ሁለንተናዊ ሕብረተሰብአዊ ጭንቀት በያለበት ተከሰተ። ይህ የብኽታ ዘመን ሕብረተሰቡ ሳይወድ የገባበት ታሪካዊ ዘመን ስለሆነ፥ ከሌሎች ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚአዊ ክስተቶች ተለይቶ አይታይም። ስለዚህ፥ እንደዚህ አይነቱ አህጉራዊ ጭንቀት ከየት እንደመጣ፥ የችግሩ ምንጭ ምን እንደሆነ፥ በሕብረተሰብ ውስጥ ገብቶ የሚያበጣብጥ፥ የሰው የክፉው ሃሳቡ ምንጭ መነሻው ከየት እንደሆነ በጥልቀት መመልከቱ አይከፋም።

አልፎ አልፎ በምንሰማው የሕብረተሰብ ፖለቲካዊ ውይይቶች ውስጥ፥ በግላጭ “እኔ የመንግሥት ደጋፊ ነኝ” የሚሉትን እና “እኔ የመንግሥት ደጋፊ አይደለሁም” የሚሉትን ስንሰማቸው፥ በውስጣቸው የተካረረ ልዩነት ያለ ይመስለናል። ነገር ግን፥ ወደ ውስጣዊ ምልከታቸው ዘልቀን ስንገባ፥ ሁሉም ባይሆኑ አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያዊ መንፈስ ያልተለያቸው፥ ደጎች እና ለተጎዱ የሚያስቡ፥ አዛኞች እና አስተዋዮች መሆናቸውን እንረዳለን። ነገር ግን፥ በአንዳንድ አላስፈላጊ ከንቱ ወሬዎች ምክንያት፥ ሕብረተሰቡ በቆራጥነት እውነትን ጨብጦ እንዳይነሳ፥ ከፊት ለፊቱ የተጋረጠውንም የብርሃን እና የጨለማ ጦርነት መመልከት እስኪያቅተው ድረስ፥ ዘመኑ የብኽታ ዘመን ሆነበት።

በዚህ ግርግር እና ውካታ በበዛበት አለም ውስጥ፥ ገበሬዎች፥ አርብቶ አደሮች፥ ነጋዴዎች፥ አስተማሪዎች፥ ሽማግሌዎች፥ እናቶች፥ ወጣቶች፥ ወ.ዘ.ተ. መጥፎ መንግሥት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሕይወታቸውን ዘወትር ስለሚያውክ፥ ወደውም ሆነ ሳይወዱ ፖለቲከኞች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። የእነርሱ ፖለቲካ እውነት እውነቷን ብቻ ስለሆነ፥ እንዳው በደፈናው ስለ መንግሥት እንቅስቃሴ ያወራሉ (ይወያያሉ) ማለት ነው እንጂ፥ እንደ ታላላቅ የፖለቲካ ሳይንቲስቶች በጥቃቅን ትንታኔዎች ውስጥ ይገባሉ ማለት አይደለም። ነገር ግን፥ አገዛዙን “ይህስ የሰይጣን አገዛዝ ነው እንጂ፥ የሰው አገዛዝ አይደለም” በማለት፥ ከብዙዎቻችን ቀድመው እቅጩን የተናገሩ እነርሱ ናቸው። ቀስ ብሎ የገባቸው መንፈሳዊ ምሁራንም፥ ጥቂት የማይባሉ እርኩሳን መናፍስት በእኛ ላይ የዘመቱት፥ መንፈሳዊ ምልከታን ወዲያ ብለን፥ በምድራዊ ምልከታ ላይ ብቻ ብዙ ጊዜ ስላጠፋን እንደሆነ ነግረውናል።

የሰው ልጅ እውነቱን፥ እውቀቱን እና እምነቱን የሚሰርቅበት ክፉ መንፈስ በነገሠበት ሥፍራ፥ ውሸቶች ሁሉ እውነቶች ይመስላሉ። እና፥ በዚህ ሰባት ዓመታት ባልሞላው፥ በብልጽግና ፓርቲ በሚመራው የዐቢይ አህመድ የአገዛዝ ዘመን ውስጥ፥

የእውነት፥ የእውቀት እና የእምነት ምሶሶዎቻችንን ለማነቃነቅ ሲሞከር፥ የዋሃን ሰዎችም ቀናውን እያሰቡ መቆየት እስኪያቅታቸው ድረስ፥ እውቀቶች ሁሉ ወደ ድንቁርና፥ እምነቶችም ወደ ክህደት እንዲለወጡ የሚገፋፋ ኃይል እጅጉን አስጨናቂ ሆነ። እኛም፥ የክፉውን ስርዓት ክፋት ባለመገንዘብ፥ ወይንም ተገንዝበንም እርምጃ ሳንወስድ ብዙ ስለቆየን፥ በብዙዎቻችን ላይ የአእምሮ ጭንቀት በሽታ አምጥቶብናል።

ከቀድሞው ኢሕአዴግ እና ከአሁኑ "ተወዶ የተጠላ መንግሥት" ጋር ተያይዞ የመጣብንን ጠላት በአእምሮ ሃሳብ ከማስላትም አልፈን፥ መላ ስሜቶቻችን የሚነግሩንን ለማዳመጥ ስንሞክር፥ የክፉ እና የደግ፥ የመጥፎ እና የጥሩ መንፈሶች ትንንቅ ብዙዎቻችንን ጭንቀት ውስጥ ከተተን።

ሥጋችን ልቅሶውን አልቻለውም። በኢትዮጵያ ምድር በየቀኑ የሚከናወኑ ኩነቶች ቀኑን ሙሉ በሃሳባችን ሲንሸራሸሩ ውለው ያድራሉ። በህልም በቅዠትም እየመጡብን፥ ደግ ነገር ሳናይ ዓመታት አለፉ። ከማልቀስ በስተቀር ምንም ማድረግ የማይቻለው አልቅስ አልቅስ ሲለው፥ እንባዎቹ ካለማቋረጥ ይፈሳሉ። አላለቅስም ብሎ ሲነሳ፥ ውስጣዊ ስሜቱ "ለምን አታለቅስም? ማልቀስማ አለብህ፤ አንተ ማለት አልቃሻ ነህ፤ ያንተነትክን መለዮ ልትለውጠው አትሞክር፤ ስለዚህ አልቅስ" ይለዋል። እሱም "እሺ አለቅሳለሁ፤ ማልቀሱን አልጠላሁም፤ ግን ሥጋዬ ደካማ ስለሆነ፥ ማልቀስ ከሚችለው በላይ ይሆንብኛል" በማለት ተስፋ ይቆርጣል፤ ሞት ብቻ ይታየዋል፤ ስለ ሞቱ ያስባል (ይጓጓል፤ ይናፍቃል)።

በሥጋ ደከምከም ያለ ሽማግሌ አርበኛም ያሳለፋቸውን የቀድሞ የተጋድሎ ትዝታዎች እያስታወሰ፥ "አዎ! እኔም ሥጋ ከማይደክምበት ቦታ ሄጄ ባለቅስ ነው የሚሻለው፤ አዎ! ከዚያ ሥፍራ ያሉ አይኖች ምድራዊ ሥጋዊ ስላልሆኑ፥ ሃያ አራት ሰዓት ቢያለቅሱ አይደክማቸውም" በማለት፥ እርሱም ሞቱን ይናፍቃል። ግን፥ ጠመንጃ ይዞ፥ ከውዲያ ወዲህ እየተንጎራደደ መፎከር የማይችል ደካማ ሽማግሌ፥ አስተሳሰቡ ወደ ተስፋ መቁረጥ ይወስደውና፥ ልክ እንደ ነቢዩ ዳናኤል እያለቀሰ ሲጸለይ እንዲህ ይላል።

*"አቤቱ ስማ፤ አቤቱ ይቅር በል፤ አቤቱ አድምጥና አድርግ፤ አምላኬ ሆይ! ስምህ በከተማህ እና በሕዝብህ ላይ ተጠርቷልና፥ ስለራስህ አትዘግይ።" ዳን. 9፡19*

በውሸት ጎራ ያሉቱ፥ ከበላይ አካል የተሰጣቸውን ምድራዊ ድሎት ብቻ እየተመለከቱ፥ ሌሎችም ሲያዝኑ፥ ሲያለቅሱ፥ ሲገደሉ እና ሲፈናቀሉ፥ ሀገር ሲፈርስ፥ ሃይማኖት ሲደፈር፥ እየሰሙ አይሰማቸውም፤ እያዩ አያዩም። እነኚህ፥ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ፥ መንፈሶቻቸው በድን የሆኑባቸው ሥጋውያን ናቸው።

እነሆ! በኢትዮጵያችን ውስጥ ከሚታየው መደናቆር አንጻር - ከየአቅጣጫው ጎላ ብሎ ከሚሰማው ከንቱ ወሬ አንጻር፥ የኢትዮጵያችን ሂደትና መጻኢ ያሳስበናል። የብዙሓን ጩኸትና ልቅሶ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበዛና እየመረረ ሲሄድ፥ በእውነት በኢትዮጵያችን ከጀርባዋ ምቀኛ (የማይታይ ጠላት) እንዳለባት፥ ለብዙዎቻችን የሚያጠራጥር አልሆነም።

በዚህ ክፉ ጊዜ ውስጥ ሳለን፥ ለቅድስቲቷ ሀገራችን የማይመጥን ሰው መጣብን፤ ከእርሱም ከበስተኋላው እየተግተለተሉ የተሰለፉ - የሰውዬውን ማንነት ያልተረዱ - ከሚገባው በላይ አፈቀሩት። በአካላዊ አይኖቻችን ከምናየው ባሻገር፥ በልበ ሕሊናችን ማየት እንዳንችል፥ ድሃውን እና ሰፊውን ሕዝባችንን እየረሳን፥ ግለኞች እና ልበ ደንዳኖች እንድንሆን፥ የአብሮነት ባህሬአችንንም እንደ ኋላ ቀርነት እንድንቆጥረው፥ ልዩ ልዩ ብልጭልጭ ቁሳዊ ጣኦታትን በተለያዩ መንገዶች እየቀረጹ ያሳዩናል።

በዚሁ አዲስ አበባ ከተማ፥ በኮልፌ ቀራንዮ፥ ልዩ ስሙ ቆሼ የሚባል የቆሻሻ ማከማቺያ ትልቅ የቆሻሻ ተራራ አለ። በወርሃ መጋቢት 2011 ከዚሁ የቆሻሻ ማከማቺያ ሥፍራ ምግብ ሲፈልጉ፥ በመሬት መንሸራተት የቆሻሻው ክምር በላያቸው ላይ ተከልብሶ፥ መቶ አስራ ስድስት ሰዎች ሞተዋል። እነኚህን ቆሻሻ የበላቸውን ድሆች አናውቃቸውም ለማለት ይዳዳናል፤ ነገር ግን፥ "ታውቋቸዋላችሁ" ይለናል ሕሊናችን።

አሁንም ቢሆን፥ የቀን ተቀን ኑሮአቸውን ከዚሁ ሥፍራ ያደረጉ ብዙዎች ናቸው። ጥንብ አንሳ (ጆፌ አሞራ) ከላይ ያንዣብባል፤ እርሱ (ጆፌ አሞራ) ከላይ ምግብ አይቶ በቀላሉ ሲያነሳ፥ ከሥር የሚርመሰመሱ ውሾችን እና ሰዎች ግን፥ ቁሻሻውን ካልቧጠጡ አይሆንላቸውም። ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ የሚያገኙት ከቆሻሻ መሃል ፈልገው ስለሆነ፥ ለእነርሱ ከቆሼ ውጪ ሌላ ሕይወት የለም።

በዚህች ጉራማይሌ ሀገራችን፥ አሁንም በዚያው የግንጥል ጌጥ (የታይታ መንፈስ) ጥቂት ሥፍራዎችን በማሸብረቅ፥ የብዙዎችን ሰቆቃ ለመሸፈን ታስቦላታል። አንዳንድ ጠባቦችም "በሄድንበት ሁሉ ሲበላና ሲጠጣ፥ ሰው ሁሉ ሲጨፍር፥ ሲዝናና አይተናል..." ይላሉ። የእነርሱ "ሰው ሁሉ" የእነርሱ አይኖች የሚያዩላቸው እንደመሆኑ፥ በእነርሱ ልኬት የአዲስ አበባ የሕዝብ ቁጥር ምናልባት አምስት መቶ ሺህ ቢሆን ነው እንጂ፥ ስድስት ሚሊዎን አይደርስም ማለት ነው።

ከአዲስ አበባ ውጪም በየገጠሩ እጅግ የተባባሰ ድህነት መኖሩን ማየት የማይችሉ የአገሪቱ መሪዎች አይኖች፥ የድሃውን ገበሬ ሕይወት ከሚገነባ ሀገር አቀፍ ኢኮኖሚ ይልቅ፥ የውጪ ሀገር ቱሪስቶችን ይስባሉ በሚባሉ አሸብራቂ ግንባታዎች

(ቤተ መንግሥቶች፥ ፓርኮች እና መዝናኛ ሥፍራዎች...) ላይ ብቻ ማተኮር ይቀላቸዋል።

*ለወደፊት፥ ኢትዮጵያ ለአሸበረቁ ግንባታዎች በብድር ያገኘቺውን ወጪ እየከፈለች ስትኖር፤ ቆይታም ራሷን ስትችልና፥ እራሷን በራሷ ማሸብረቅ ስትጀምር፥ "የኋላው ወደፊት ባይመጣ ይሻል ነበር.." ማለቷ አይቀርም።*

አንዳንድ ሰዎች "እኛ በቤታችን ደስታን እንጂ፥ ሃዘንን አናስተናግድም" በማለት፥ ደስ ከማይል እውነታ ሲርቁ፥ ከኢትዮጵያም መራቃቸው አልታወቃቸውም። እነርሱ መስማት የሚፈልጉት ቆንጆ ቆንጆውን ነው። የዛሬውን እና የወደፊቷን ኢትዮጵያ እንዳያስተውሉ፥ በሚመኙት ብልጽግና እና የማይጨበጥ ደስታ ባለበት ምናባዊ አለም - በዩቶፒያ - ሻንግሪላ[49] (shangrila – utopia) ውስጥ ይኖራሉ።

አንዳንድ ሰዎች (እራስን ከመውደድ የተነሳ ቢሆንም ባይሆንም) መጥፎውን የአለማየት ስነ ልቦናዊ ችግር አለባቸው፤ ፍጹም አዎንታውያን ስለሆኑም፥ የማንኛውም ነገር አሉታዊ ጎኑ አይታያቸውም፤ እነርሱ መጥፎውን ለማየት ቢሞክሩ፥ የችግሩ ተካፋይ እንዲሆኑ የሚገደዱ ይመስላቸዋል። በተቃራኒውም፥ አንዳንድ ሰዎች፥ ፍጹም አሉታውያን ስለሆኑ፥ የማንኛውም ነገር አዎንታዊ ጎኑ አይታያቸውም። ከእነኚህ መካከል አንዳንዶቹ፥ ነገርን በክፉ ለመተርጎም የሚችላቸው የለም፤ ክፉውን ለይቶ ለማወቅ ግን ምንም ፍላጎት አይኖራቸውም።

ዜጎች ከሞቀ ቤታቸው ሲፈናቀሉ፥ በሽተኞች፥ ደካሞች፥ ሴቶች፥ አዛውንቶች እና ሕጻናት እንደ አሮጌ እቃ በየመንገዱ ሲጣሉ፥ እነርሱን አናይም ብለው አዳዲስ የተገነቡ ፎቅ ቤቶችን በማስተዋል ብቻ ይረካሉ (ይሆን?)። ሊሎች ግን፥ ኢትዮጵያ ዩቶፒያ - ሻንግሪላ እንደማትሆንላቸው የተገነዘቡ፡- "ወይኔ! ሀገሬ ኢትዮጵያዬ! አንቺ'ኮ! ወደ ዩቶፒያነት ባትለወጭም ታስኖሪናለሽ እንጂ አታጠፊንም..." ይላሉ።

እህ! የሀገራችንን አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ በማስታወስ፥ የሚሰማንን ርህራሄ የተመላበት ስሜቶቻችን እየገታን፥ እንዲሁ በደምሳሳው "ከዛሬ ነገ ይሻል ይሆናል፤ ከዛሬ ነገ ይሻል ይሆናል" እያልን፥ መልካም ቀን በጉጉት ስንጠባበቅ ዓመታትን አስቆጠርን።

ያሳለፍናቸው አቅጣጫ ቀያሽና ወሳኝ ኩነቶች ሁሉ የሚነጽሩት ወደ ሀገር አንድነት እና ልማት ሳይሆን፥ እራስን ወደማጥፋት፥ ወደ ሙስና እና መጨረሻው ወደማይታይ የጭለማ አለም ሆነ። በዚህም ምክንያት፥ "ከእነኛ ወደ ክፋት ከሚያመሩ

[49] a remote beautiful imaginary place where life approaches perfection**: UTOPIA**

ወሳኝ ኩነቶች ከበስተጀርባቸው ምን ቢኖር ነው፥ የኢትዮጵያችን ነገር ወደ ጥፋት የሚያመራው? ለምንድነው ነገር ሁሉ እንዲህ ምርር ክርር እያለ የተወሳሰበው? እውነቶች ከውሸቶች ጋር ተጋምደው፥ ውሉ የጠፋው፥ ጉራማይሌ የሆነው?" ብለን እንጠይቃለን።

በየጊዜው፥ የአለም ፍጻሜ የደረሰ እስኪመስል ድረስ፥ እርስ በርሳችን እየተጨራረስን ነው ከዚህ የደረስነው። ሕይወት በምድር ላይ መቀጠል እንዳለበት እና እንደሌለበት የመጨረሻው ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ፥ መማር ያለብንን ስንማር የሰብአዊነትን እድል ፈንታ እናሳምረዋለን፤ አለመማርን ስንመርጥ ደግሞ፥ እናበላሸዋለን።

በኢትዮጵያ ዙሪያ የምንሰማው ሕዝባዊ እሮሮ ውስጣዊ ማንነታችንን እየነካካ፥ ቆሽታችንን ድብን - እርር አደርገው። ሁኔታው "በእያንዳንዳችን ሃሳብ (ወይንም መንፈስ) ውስጥ እየገባ ጥቁሩን ነጭ ወይንም ደብዛዛ የሚያደርግብን ኃይል መኖር አለበት" እንድንል አደረገን። ቀደም ሲል የጠቀስነው ዘመን አመጣሽ ፍልስፍና የሰውን ልጅ በመንፈሳዊ ኃይሉና በአስተሳሰቡ ሲያዳክመው፥ ሁሉን ተቀባይ እንዲሆን፥ የክፉውንም ክፋት እንዳይለይ ያደርገዋል፤ በኢትዮጵያችንም ካልነገሥኩ ብሎ የሚታገለን ማን እንደሆነ (ሰው ወይንስ ሰይጣን) እስካሁን ድረስ ያልገባን ለዚህ ይሆናል።

መመሪያዎችም ከቤተ መንግሥት ሲወጡ፤ በአንድ በኩል ከጥንትም ከኢሕአዴግ ጋር በነበረ ትስስር፤ በሌላም በኩል፥ ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) አላማዎች ጋር የሚገናኙ እየመሰለን፥ እጅጉን ግራ በመጋባታችን አላስፈላጊ ጭንቀት ውስጥ ገባን።

ምንም እንኳን፥ ነገሮችን የምናይበት፥ የራሱ የተለየ መንገድ ቢኖረውም፥ "ግራ እጅ ግራ ስለሆነ፥ ተቆርጦ ይጣል" እንደማይባል፥ "ለኢትዮጵያችን ሁላችንም እናስፈልጋታለን፤ አንድነት ኃይል ነው" ስለምንል ብቻ፥ ከመጠን በላይ ታጋሾች ሆነን በመቆየታችን፥ በውስጣችን ክፋት ተወልዶ፥ አድጎና ጎልብቶ ክፉኛ አጠቃን።

ወያኔው "ትግራይ ትስእር" እያለ፥ ስለ ታላቋ ትግራይ ሲፋለም፤ ኦነጋውያኑም አዲሱን የኦሮሙማን ጽንሰ ሃሳብ በሥራ (በኃይል) በመተርጎም ከኢትዮጵያ ውስጥ "ኦሮሞ" የሚባል ሀገር ፈልቅቆ ለማውጣት ሲታገል፤ ቅድስቲቷን ኢትዮጵያችንን በምናብ ከፋፈሏት። ሌሎቻችንም የክፉውን መንፈስ ስሌት እና ውጤቱን አስቀድመን ባለመገንዘብ "ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ!" በማለታችን ብቻ የኢትዮጵያን አንድነት የጠበቅን መስሎናል።

በአጽንኦት ያላገናዘብነው ክስተት ኢትዮጵያችንን ወደ ከፋው መንገድ እየመራት፥ ታሪክ አዋቂዎች እውነቱን ቢናገሩ የሚታሠሩባት፥ ውሸት የነገሠባት፥ ሰላም የታጣባት፥ ችግር የበዛባት ሀገር ሆነች ሀገራችን።

መጥፎዎች (በሙስና የተጨማለቁ፥ ጉበኞች፥ ሌቦች እና ቀማኞች፥ ድሆችን የሚበድሉ፥ ነፍሰ ገዳዮች...) የመጥፎው ስርዓት ተጠቃሚዎች በመሆናቸው እና፤ መንግሥትም አስተማማኝ ድጋፍ የሚያገኘው ከእነርሱው ስለሆነ፥ እነርሱን መቅጣት የገዛ ስርዓቱን መገርሰስ ስለሆነበት፥ የብልጽግናው መንግሥት ከመጥፎዎቹ ጎን ቆመ እንጂ አልተቃረናቸውም - እራሱን ደፍቶ **ዝም** ያለ ቢመስልም፤ በውጪ እየሰደባቸው፤ በውስጥ ይተባበራቸዋል። እንዳው በአጠቃላይ፥ በውሸታምነት እና በሌብነት ኑሮን መምራትን ከመንግሥት እስከ ተራው ሰው የሚለማመዱባት ትምህርት ቤት መስላለች ሀገራችን።

አንድ መንግሥት ጦርነት አሸነፍኩ ብሎ ደስ ይለዋል፤ ይፎክራል፤ ይዘላል፤ ይጨፍራል፤ ከዚሁ አሸናፊ የተባለ መንግሥት ጋር ሌሎችም አጫፋሪዎች እንዲሁ ጩኸቶቻቸውን በሕብረት ያስተጋባሉ። ከበስተጀርባ ያሉ የማይታዩ ቀስቃሽ ኃይላትም "ሃይ! ሃይ!" እያሉ አብረው ያጫፍራሉ። ማነው ጨፋሪው? ማነው አጫፋሪው? በመካከላችን ያሉትን ሰው መሳይ "ጉዶች" አላወቅናቸውም።

የሰውን የውስጣዊ ክብሩ መገለጫ የሆኑትን ውስጠ ጠባዩን ሳያውቁ፥ ለአንድ የተቀደሰ አላማ አብሮ መሥራት ያስቸግራል። ለብዙ ሰዎች ሁሉ ነገር ወደ ነጭ እና ጥቁር እስኪቀየርና፥ በደንብ ተለይተው እስኪታዩአቸው ድረስ ብዙ ጊዜ ሊፈጅ ይችላል። ምክንያቱም፥ ብዙውን ጊዜ የዋሃን ነገሮችን በአዎንታዊነት ብቻ ይመለከቱና ከበስተጀርባ ያለውን ክፉውን፥ ቢያዩም እንዳላየ ይሆናሉ። ሌሎችም፥ በየጊዜው የሚፈጸሙ ኩነቶችን በተናጠል ብቻ ስለሚያዩና፥ ነገሮችን አያይዞ የመመልከት ኃላፊነት "አይመለከተንም" ስለሚሉ፥ ክፋቶችን በቶሎ ትውት ያደርጉታል። ስለዚህ፥ ልክ ነገሮችን እንደሚረሳ የአእምሮ ሕመምተኛ፥ ከጥቃቅን ጊዜአዊ የኩነቶች መለዋወጥ ጋር፥ በሃሳባቸው የሚይዙትን እና የሚጨብጡትን ያጣሉ፤ ስሜቶቻቸው ይለዋወጡባቸዋል፤ መጪውንም ጊዜ መመልከት ይሳናቸዋል።

አንዳንድ ሰዎች ውስጣዊ አይናቸው የታወረ ነው። ከቤት ውስጥ ቁጭ ብለው ወይንም በከተማ ሲዘዋወሩ ዝሆኖች ሲንቀሳቀሱ ካላዩ፥ በጫካ ውስጥ የሚኖሩ ዝሆኖች መኖራቸውን አያገናዝቡም። እንዲሁም በተመሳሳይ፥ በመንግሥት ትእዛዝ ሰላማዊ ሰዎች እየተገደሉ መሆኑን እነርሱ የሚገባቸው፥ ሰላማዊ በመሆኑ የሚተማመኑበት ሰው፥ ወይንም ወዳጅ ዘመዶቻቸው ሲገደሉባቸው ብቻ ነው። እጅግ የሚገርመው ደግሞ፥ በደረቅ (በውጫዊ) አይኖቻቸው እያዩም የማያዩ፥ በውጫዊ

ጆሮዎቻቸው እየሰሙም የማይሰሙ ሰዎች አሉ። እንደዚህ ያሉቱ ልበ ደንዳኖች፥ ሰብአዊ ርህራሄም የሌላቸው፥ ዓመጸኞች ናቸው።[50]

አንዳንድ ሰዎች ችኩሎች እና ቅብዝብዞች ናቸው፤ የሰው ልጅ ረጋ ብሎ፥ ክፉና ደጉን አመዛዝኖ ማስተዋል እንደሚገባው ይዘነጋሉ። እነርሱ ሲንቀሳቀሱ (ሲያወሩም፥ ሲጽፉም) ለጥሩም ሆነ ለመጥፎ፥ ሳይታወቃቸው ብዙ ርቀት ተጉዘው ከአንድ ያላሰቡት አደጋ ላይ ሲወድቁ ብቻ ነው ንቅት የሚሉት። እነርሱ በችኩልነት ሲሮጡ፥ በውስጣቸውም ክፉ መንፈስ እነርሱ ያልጠበቁትን ክፉ ሥራውን ይሠራባቸውና (ያሠራቸውና)፥ ከሰው ሁሉ ጋር በፍቅር እና በአንድነት መኖር ያቅታቸዋል።

አንዳንድ ምድራዊ ወይንም መንፈሳዊ ምሁራን እውቀት ተትረፍርፎ ቢሰጣቸውም፥ እውነት ስለሚጎድላቸው (ጥርት ያለው እውነት ስለሚሠወርባቸው) ትንሽ በማውራት በቀላሉ በሚገለጸው እውነት ዙሪያ ብዙ ያወራሉ (ይቀባጥራሉ)። ከእነርሱም መካከል ተንኮለኞች ከተገኙባቸው፥ እነኚያ ተንኮለኞች ውሸትን የመደበቅ ጥበብ ስለሚኖራቸው፥ ያቺን የደበቋትን ውሸት በብዙ ጥቃቅን እውነቶች ልባስ አሰማምረው እውነት እያስመሰሉ ሲናገሩ የሚሰሟቸውን ያሳስታሉ።[51]

በተፈጥሮአቸው፥ ነገሮችን ብጥብጥ የሚያደርጉ እና የሚዋሹ ሰዎችም፥ እነርሱ ብዙ ሲያወሩ፥ ብዙ በማውራታቸው ብቻ የየዋሃን አንጎል የእነርሱን ውሸት እስከመቀበል ይደርሳል። የዋሁ ሕዝባችንም የወላዋይና አታላይ ፖለቲከኞችን ሁለት መላስ እየተከተለ፥ ውሸት እና እውነቱንም መለየት ያቅተዋል።

አንዳንድ ሰዎች በሥጋም ሆነ በመንፈስ ከፍ ብሎ የሚታያቸውን ሁሉ ማንቆለጳጰስና ሙገሳ ማብዛት ይወዳሉ። የሀገር መሪም ሆነ የሃይማኖት ምሁር ሲሳሳት በመንቀፍና በመተቸት ፋንታ፥ ውዳሴ ከንቱን ያበዛሉ።

በአለማችን ላይ ብዙ ብልጣ ብልጥ ፖለቲከኞች አሉባት። እነርሱ ከሕዝቡ ጎን የቆሙ በመምሰል፥ ከመጥፎ መንግሥት ጋር እየተመሳጠሩና ሰፊውን ሕዝብ እየበደሉ፥ የራሳቸውን ሞቅ ያለ ኑሮ ይኖራሉ። እውነተኞቹ ደግሞ ወደ እስር ቤት

---

50 *“የሰው ልጅ ሆይ፥ በዓመጸኛ ቤት መካከል ተቀምጠሃል፤ ያዩ ዘንድ ዓይን አላቸው፥ እነርሱም አያዩም፤ ይሰሙም ዘንድ ጆሮ አላቸው፥ እነርሱም አይሰሙም፤ እነርሱ ዓመጸኛ ቤት ናቸውና። ” ሕዝ.12፡2*

51 “እነኚህ እንደ እነማን ያሉት ናቸው?” የሚለውን ጥያቄ ለአንባቢ እንተዋለን።

ይታጎራሉ።[52] የዚህ የአስከፊው ሥርዓት ተሳታፊ የሆኑ ባለሥልጣናትም፥ የሥልጣን ጊዜያቸውን ለማራዘም እና ጥቅማ ጥቅማቸውን ላለማጣት ሲሉ፥ ሕዝብ ከሕዝብ ጋር እየተጋጨ እርስ በርስ ሲጨራረስ ዝም ብለው ያያሉ።

አንዳንድ እውነት የጎደላቸው፥ እንዲሁ በበላይነት ስሜት የሚፎክሩ፥ የሚሸልሉ፥ የሚያቅራሩ እና የሚሳደቡ፥ ነገር በማጋነን የሚደሰኩሩ ምሁራን ነን ባዮች፥ የእነርሱ ልፈፋና ጩኸት በብዙሃኑ ላይ የሚያሳድረውን የስነ ልቡና ጫና፥ የሚያስከትለውንም እስከ እርስ በርስ መገዳደል የሚያደርስ መዘዝ፥ ከራሳቸው የግል ፍላጎት አንጻር፥ አይቆረቁራቸውም። በተለይ ሀገሪቷን የሚያጨናንቅና የሚፈትን ጊዜ ሲመጣ፥ የእነርሱ ዝም ማለት ነበር የሚሻለው፤ በዚህ ጭንቀት በበዛበት ወቅት፥ የአዋቂዎች እውቀት ብዛት ሳይሆን፥ እውነትን በትክክሉ የሚያንጸባርቁ የእውነተኞች እውነት ብዛት የሚፈለግበት ነውና።

አንዳንድ ብዙ እውቀት እና ብዙ እውነት ያላቸው ሰዎች (ምሁራን) በአንዳንድ አናሳ ጉዳዮች ላይ ለምድራዊ ስሜቶቻቸው ተገዢዎች በመሆን እውነትን ሙሉ በሙሉ መቀበል ያቅታቸዋል። ለምሳሌ፦

ስለ ኢትዮጵያ የመንግሥት ሥልጣን ሲወራ፥ “ቀዳሚውን ሥፍራ መያዝ ያለባቸው የዚህ ብሄር ሰዎች ብቻ መሆን አለባቸው” በማለት በድፍረት ይናገራሉ። እነርሱ ለኢትዮጵያችን የሚጠቅሙ እውነቶች በሌሎች (በሁሉም) ብሄር ሰዎች ውስጥም እንደሚኖሩ ይስታሉ። በአስተሳሰባቸውም የራሳቸው ስሜታዊ ብሔራዊ ስሜት ወደሚያጋድልበት ይሆንና ስለ እውነት እና ስለ ወደፊቷ ኢትዮጵያ ጠለቅ ብሎ ማሰብ ያቅታቸዋል። ብዙውን ጊዜ፥ እንዲህ ያለውን ጠባይ የሚጋሩትም፥ በበላይነት ስሜት የሚፎክሩ፥ የሚሸልሉ፥ የሚያቅራሩ እና የሚሳደቡ ሰዎች ናቸው።

ከሰው አንደበት ጥሩም መጥፎም ይፈልቃል፣ ወሳኙ ግን ንግግሩ ብቻ አይደለም፤ ድርጊቱም ጭምር ነው እንጂ። መጥፎ ሰው ጥሩ ጥሩ ነገሮችን እየተናገረ ጥሩ ሰው ቢመስልም፤ አንዳንድ ጊዜ፥ አስቦት ወይንም ሳያስበው መጥፎ ቃል ከአንደበቱ አፈትልኮ ይወጣል። አድማጮችም “እንዴ! ይህ ሰው ምን ነካው? ጥሩ ሰው አልነበርም እንዴ? አይ ሰው ማመን!” ሲሉ የሚሰሙት ለዚህ ነው።

አንዳንድ ሰዎች ቁምነገር የላቸውም፤ እምነታቸው የላላ፤ እውነቶቻቸውም የላሸቁ ስለሆኑ፥ በማንኛውም ጊዜ አንድ አላማ ይዘው የማይጓዙ በመሆናቸው፥ ሽንፈት እና ተስፋ መቁረጥ ጠባያቸው ይሆናል። በአመራር ላይ ያሉትም ይህንን

---

[52] “በእስር ቤት የተጣሉትን፥ እነ እገሌን፥ እነ እገሌን እናስባቸው” በማለት፥ በተመቸ ሰዓት ጥቂት የሕሊና ጸሎት ማድረግ ይገባል።

ድክመት በመጠቀም፥ በሠለጠኑበት ሰይጣናዊ አሠራር መሠረት፥ አንዴ አንዱን፥ ወዲያውም ሌላውን እየቀያየሩ ሲያሳዩን፥ በሃሳብ የምንደግፈውን እና የማንደግፈውን ለይተን እንዳናውቅ ያደርጉናል፤ በዝብርቅርቆሽ አለም ውስጥ ይከቱናል።

አንዳንድ ሰዎች (በተለይ ንኡስ ከበርቴ ምሁራን) ክፉና ደጉን በቶሎ ይለያሉ፤ ነገር ግን የቀን ተቀን ኑሮአቸው እንዳይናጋባቸው ስለሚፈሩ የወገንተኛነት አቋም ሲወስዱ አይታዩም። እነኚህ፥ "እናቴን ያገባ ሁሉ አባቴ ነው" እንደሚሉቱ፥ በጊዜው ሥልጣን ከያዘው መንግሥት ተባብሮ በመሥራት የሚገኘውን ጥቅማ ጥቅሞች ብቻ እያዩ የሚኖሩ፥ መስሎ አዳሪዎች (conformist) ናቸው። እንዲህ ያሉ ሰዎች መንግሥት በግልጽ የሚታዩ ችግሮችን ሲሸፋፍን፥ ወይንም አላይም ሲል፥ እነርሱም "አዎ! እኛም አናይም - ኸረ! አላየንም!" የሚሉ ስለሆኑ፤ ኑሮአቸውን ልክ አከርካሪ አጥንት እንደሌለው እንደ ጄሊ(ልፍስፍስ) ዓሳ የሚሽመደመድ ያደርጉታል።

አንዳንድ በራሳቸው የማይተማመኑ ሰዎች የአስተሳሰባቸውን ችሎታ በሌሎች ችሎታ ላይ ስለሚያስደግፉት፥ አንዳንድ ኢሰብአዊ ድርጊቶች ሲፈጸሙ "ለምን ይሆን?" በማለት ነገሮችን በጥልቀቱ አይመለከቱም። የሰብአዊነታቸውን እና የኢትዮጵያዊነታቸውን ባለአደራነት ይዘነጉታል።

የራሳቸውን ኑሮ ብቻ የሚኖሩ ራስ ወዳዶች፥ የሰው ሁሉ ኑሮ በአንድም ሆነ በሌላ የሚያያዝ መሆኑን አያወቁም፤ ቢያውቁም፥ የእነርሱ ሞቃት ኑሮ እስካልተነካባቸው ድረስ፥ ስለ ሌላው አይጨነቁም። በጊዜአዊ ጥቅማጥቅሞች የታወሩትም፥ በወቅታዊ ኩነቶች ላይ ብቻ እያተኮሩ ሀገራችን ያሳለፈቻቸውን ሕብረተሰብአዊ ቀውስ ይረሱታል።

አንዳንድ እጅግ የዋሃን የሆኑ ሰዎች፥ የኤደን ገነት መግባትን ያልፈራ ሰይጣን፥ ከቤተ መንግሥት መግባትን የሚፈራ (የማይችል) ስለሚመስላቸው፥ ምንጊዜም መንግሥት ሰይጣናዊ ሊሆን እንደማይችል እና፥ ቢሳሳትም እራሱን በራሱ ማረም እንደሚችል ይቆጥሩታል። ምንጊዜም መንግሥት ሲባል ችሎታ እና ብቃት ያለው፥ ለሕዝቡም የሚያስብ ስለሚመስላቸው፥ በመንግሥት እና በመንግሥት ደጋፊ ኃይላት የሚሰበኩ ፖለቲካዊ ስብከቶችን በማስተጋባት፥ በኢትዮጵያችን ስለተከሰተው ፖለቲካዊ ቀውስ እንደሚከተለው ያስባሉ፡-

*"ይህንን የተከፋፈለ ሕብረተሰብ ሰብስቦ አንድ ማድረግ ቀላል አይደለም። በመንግሥታዊ መስተዳደር ውስጥ ያለውን ፈተና በደንብ ሳንረዳ ነው ትችት የምናበዛው እንጂ፥ በኢኮኖሚ ግንባታ፥ በሚሊታሪ እና በመሳሰሉት መሠረታዊ ተቋሞች ላይ መደረግ ያለባቸውን ሁሉ መንግሥት በራሱ ያውቃል። ከያለበት የሚጎርፉትን ጥያቄዎች ብዛት እና አይነት፥ አብሮት የሚመጣውንም የውጪ ኃይላትን*

*ተጽእኖ በአግባቡ መመለስ የሚችሉ በመንግሥት ሥልጣን ላይ ያሉ ብቻ ናቸው እንጂ፥ ተራው ሰው አይደለም።"*

አዎ! መንግሥት እና በመንግሥት ሥልጣን ላይ ያሉ ሁሉን ያውቃሉ ቢባልም፤ በእውቀታቸው ልክ የእውነተኛነት፥ የደግነት እና ጥሩ አሳቢነት ባሕሬ ከሌለባቸው፥ ሰፊውን ሕዝብ መጠቀሚያ ከማድረግ ውጪ፥ አንድነቱ ተናግቶ፥ እርስ በርስ ቢጋደልም አይገዳቸውም።

አንዳንድ ሰዎች ከመጠን በላይ፥ በሥጋዊነታቸው ይሳባሉ፤ ሌሎችም ከመጠን በላይ በእውቀቶቻቸው ይሳባሉ። የሁለቱም ምንጭ ምድራዊነት ስለሆነ፥ ምድራዊ ከሆነው ውጪ ሰማያዊ የሆነ እውነትን ማየት ይሳናቸዋል፤ ልክ ዓይነ ጥላ እንዳለበት ሰው፥ ገሃድ የሆነ እውነት ሁሉ ይጋረድባቸዋል።

በአጠቃላይ ስንመለከት፥ ኢትዮጵያውያን ፖለቲከኞቻችንን (በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ) የሚፈልጉትን እንኳን እንዳያውቁ ያደረጋቸው፤ ወይንም የሚፈልጉትን ቢያውቁ እንኳን እንዳያገኙት የሚያደርጋቸው አንድ ኃይል አለ ያስብላል። አንዲያማ ባይሆን ኖሮ፥ በጥቃቅን ልዩነቶች የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ ወደ አንድ እውነት እና ወደ አንድነት ይሸጋሸጉ ነበር።

አንዳንድ ኃያላን ሰዎች የሀገር መሪዎች እንዲሆኑ "ሲመለመሉ"፥ እነርሱ ራሳቸው ባልተገነዘቡት፥ በራሳቸው ምንም ማድረግ እንደማይችሉ መሆናቸውን የሚያንጸባርቅ ጠባይ ይታይባቸዋል። ለዚህም ለዚያም ያነበድዳሉ፤ ይቅለሰለሳሉ። የእኛም ሀገር "መሪ" በክፉውና በደጉ ተወጥሮ፥ ግራና ቀኝ ሲረግጥ፥ አንዴ ሲያስከፋን፥ አንዴ ሲያስደስተን፥ ደግ ሲሉት ክፉ፥ ክፉ ሲሉት ደግ፥ ርህሩህ ሲሉት ጨካኝ፥ ጨካኝ ሲሉት ርህሩህ፥ ሰላማዊ ሲሉት ጦረኛ፥ ጦረኛም ሲሉት ሰላማዊ እየሆነ፥ ለራሱ ግራ ተጋብቶ እኛንም ግራ ሲያጋባን፥ "ይህ ሰው እውነትም በአጋንንት ተለክፏል" ብለን አሰብን። የእርሱ ተለዋዋጭ ባህሪው የብዙ ኢትዮጵያውያንን ምልከታ እና ስሜት በመቆጣጠር፥ በከፍና ዝቅ፥ በሙቀት እና በቅዝቃዜ እያፈራረቀ፥ እጅግ አስቸጋሪና አስጨናቂ ሆኖ ብዙ ስለቆየ፤ ሕብረተሰባችን ጭንቀት ውስጥ ገባ። እኛ ግን፥ በየዋህነት፥ ወይንም "በሌላ" ባልታወቀ ምክንያት፥ እውነታውን ከማወቅ ዘገየን።

ፖለቲከኞቻችንን ብዙ አይነት አዚም[53] የተጠናውታቸው ይመስላል፡- የግለኝነት አዚም፥ የመፍቅሬ ንዋይ አዚም፥ የሥልጣን ጥም አዚም፥ የትእቢተኛነት እና የጉረኛነት አዚም፥ የጅብደኝነት አዚም፥ የራስ ወዳድነት አዚም፥ የበላይነት ስሜት አዚም፥ የዝቅተኛነት ስሜት አዚም፥ የችኩልነት አዚም፥ የእኔ ሁሉን አውቃለሁ ባይነት

[53] በእንግሊዝኛ "who has bewitched you" እንደ ማለት ነው።

አዚም፥ ከታሪክ የአለመማር አዚም፥ ስህተቶችን የመደጋገም አዚም፥ የዘረኛነት አዚም፥ የስሜታዊነት አዚም፥ የጽንፈኛነት አዚም፥ አርቆ የአለማሰብ አዚም፥ በአንድ ሃሳብ ያለመጽናት አዚም፥ የምሁራዊ ወላዋይነት አዚም፥ ወ.ዘ.ተ.።

*"…ለእውነት እንዳትታዘዙ፥ አዚም ያደረገባችሁ ማነው?" ገላ. 3፡1*

ይገርማል! ከተጠቀሱት አዚሞች ውስጥ ብዙውን በአንድ ላይ የሚሸከሙ ሰዎች አሉ። እንደዚህ ያሉ ሰዎች መጥፎነትን ከዚህኛው ከዚያኛውም አዚም አቀነባብረው ስለያዙ፥ ውስጣዊ ማንነታቸው በግልጽ አይታይም። እንደነዚህ አይነቶቹን ነው ሰይጣን ለታላላቅ የኃላፊነት ሥራዎቹ የሚፈልጋቸው። ለዚህም፥ እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱ የሀገር መሪዎች፥ በተለያዩ ዘመናት እንደነበሩ፥ አሁንም እንዳሉ አንባቢ ያስተውል።

"ጠቅላላ ሕብረተሰቡን ያስጨነቀው፤ በሃሳብ የከፋፈለው ምንድነው?" ብለን እራሳችንን እንጠይቃለን። ቀጥሎም፥ ይህ እንዲህ ያለው መከፋፈል ምሁራን፥ አዋቂዎች የምንላቸውም ውስጥ ገብቶ ስናይ፥ ወደ ውስጥ ገብቶ ጉዳዮችን መመርመር ተስፋ አስቆራጭ ይሆንና እንተወዋለን። ነገር ግን፥ መቼም የሀገር ጉዳይ ነውና፥ ምናልባት የመናፍስት ጉዳይ ከሆነስ ብለን፥ በደንብ ወደማናውቀው ጉዳይ ውስጥ ለመግባት እንደፍራለን።

"ሰው በራሱ ላይ ምን ሥልጣን አለው? ክፉውን በደግ የሚለውጥ አምላክ አለን፤ ስለዚህ፥ በአንዳንድ አንኳር አንኳር በሆኑ ጉዳዮቻች ላይ ስንወያይ፥ የሚገለጥልን ነገር ይኖራል" በማለት፥ ከምድራዊ እይታዎቻችን ወጣ ብለን አንዳንድ ድብቅ ክስተቶችን በአይነ ልቡናችን ለማየት እንሞክራለን።

በእርግጥ፥ የተለያዩ ምድራዊ የሃሳብ እንቅፋቶችን ከመንገዳችን ላይ ቁጭ እያደረገ ስንደነቃቀፍ የሚሳለቅብን፥ የእርኩስ መንፈስ ኃይል አለ በመካከላችን። ይህንን ያልተረዱ አንዳንድ በፖለቲካ እውቀታቸው የምናደንቃቸውና የምናከብራቸው ምሁራን ግን፥ አቅጣጫው እንደጠፋበት መርከብ በሃሳብ ሲዋልሉ፥ ተራውን ሕዝብ ምን ያህል እንደሚያሳስቱት እና እንደሚያስጨንቁት አልገባቸውም።

ሌሎችም ጥራዝ ነጠቅ ፖለቲከኞች እና ሃይማኖተኞች ነን ባዮች "ኢትዮጵያ ይህንን ክፉ ዘመን በዚህ ዓመት ትሻገረዋለች፤ ከሚመጣው ዓመት ጀምሮ ወደ ብልጽግናው ማማ መውጣት እንጀምራለ" እያሉ፥ ሕዝቡን በማይጨበጥ ተስፋ ያታልሉታል።

ዓመት አልፎ ሌላ ዓመት ሲተካ፥ ኢትዮጵያችን ከመጥፎው ዓመት ወደ በጣም መጥፎው ስትሸጋገር፥ "ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?" ብለው የማይጠይቁ፥ የምድራዊ እና መንፈሳዊ ክስተቶችን ሂደቶች አቅጣጫ ማስተዋል እና በትክክሉ

መረዳት ያቃታቸው፥ ወደ መራራውም እውነት መጠጋትን የፈሩ፥ እነርሱ የገዛ ሕሊናቸውን እና ውስጣዊ መንፈሳቸውን በመመርመር፥ የምድራዊ ሂደቶችን አቅጣጫ በራሳቸው ሊያገናዝቡ እንደሚችሉ አላወቁም።

አንዳንድ ሰዎች ሳያስቡት በክፋት ሲጠመዱ እና መጥፎ ሥራ ሲሠሩ፤ ቆይቶም የሠሩትን መጥፎ ሥራ በማሰብ፥ በመጥፎ ሥራቸው ውጤት አለማማር ሲጸጸቱ፥ ይህ ለምን እንደሆነ ስለማያስቡበትና እራሳቸውን ማየት ስለሚያቅታቸው፤ በዛው በመጥፎ ሥራቸው ይቀጥላሉ። ከእነኚህ መካከል አንዳንዶቹ፥ ከማይወጡት አዘቅት ውስጥ ሲወድቁ እና በሥጋም በመንፈስም ክፉኛ ሲጎዱ ብቻ ነው ድንገት ንቅት የሚሉት።

አንዳንድ ሰዎች ከእውነተኛ ማንነታቸው ጋር ትንንቅ ውስጥ ይገቡና፥ በራሳቸው ለራሳቸው ምንም ማድረግ እንደማይቻላቸው ሲገባቸው፥ ወደ መንፋሳዊ አባቶች ጠጋ ይሉና ከእነርሱ ዘንድ ያስጨነቃቸውን ሥጋዊና መንፈሳዊ ፈውስን ለማግኘት ይማጸናሉ። በእርግጥ፥ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ጊዜያዊ ፈውስን በእነኚህ የመንፈስ አባቶች በኩል ያገኙ ብዙዎች መሆናቸውን እናውቃለን። እነርሱ ለጊዜውም ቢሆን ነገሮች ተስተካክለውላቸው ጥሩ ኑሮ ይጀምራሉ። ነገር ግን፥ ብዙዎች ያልተረዱት፥ ከመናፍስት ጋር ትንንቅ ሲገባና ፈውስ ሲገኝ፥ ያ ፈውስ፥ ልክ ለሥጋዊ በሽታ ኪኒን ተወስዶ በአንድ ጊዜ እንደሚዳን አይነት አለመሆኑን ነው። ከጊዜያዊ ፈውስ በኋላ ዳግመኛ ወደ ቀድሞው ጭንቀት እና መከራ እንዳይገባ፣ ጥብቅ መንፈሳዊ ክትትል (የማያቋርጥ ጸሎት) ያስፈልጋል።

እጅጉን ታጋሽ የሆነውም የሕብረተሰብ ክፍል፥ "የቁጣው ማእበል ረገብ ሲል፥ እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ መልካሙን ዘመን ያመጣልናል" በማለት በተስፋ ይኖራል። መታገስ ያቃተውም (በተለይ ፖለቲከኛ) የሚይዘውን የሚጨብጠውን ስለማያውቅ ይቅበጠበጣል።

ሕዝቡን ወደ አንድነት የሚያመጣውን የፍቅር እና የአንድነት ብቸኛ ጎዳና ማየት ያቃተን፥ በመምሰል እና በማስመሰል አለም ውስጥ ስላለን፥ ዋናውን (ክፉውን) እያየንም እንዳላየን መሆንን ስለመረጥን ይሆናል። ምንጊዜም የሰውን ልጅ ከመረበሽ የማያቋርጠውን፥ ጊዜ መርጦ ኢትዮጵያችንን ያናወጣትን፥ የዲያቢሎስን ማንነት እና ሥራውን ማወቅ ያልፈለጉ፥ እነርሱ በራሳቸው ምድራዊ እውቀት ብቻ አለምን የሚተረጉሙበት መንገድ በቂ አለመሆኑን አልተረዱም።

ዘመናዊ ሃኪሞች ሰዎችን በአካላዊ ደዌ የሚያሳምሟቸው ቫይረሶች እና ባክቴሪያዎች እንደሆኑ አስተማሩን፤ መድኃኒታቸውንም ቀምመው ሲሰጡን እንጠቀምባቸዋለን፤ ሥጋዊ ፈውስንም እናገኛለን።

የመንፈስ ጭንቀት የሚያመጡባቸውን ውስብስብ ማሕበራዊ ጉዳዮች ግን የዘመኑ ሃኪሞች ቢያውቋቸውም፥ እነኛን ማሕበራዊ ጉዳዮች በምድራዊ ሳይንቲስቶች በተቀመሙ መድኃኒቶች መዳን እንደማይቻል እነርሱም ያውቁታል።

በሰው አንጎል ውስጥ የነርቭ ሕዋሳት የሚንቀሳቀሱትና አለምን የሚተረጉሙት በሚያዩት አካላዊ ምድራዊ እይታዎቻቸው ብቻ ስለሆነ፥ ሰዎች በአንጎላቸው ብቻ እየተጠቀሙ፥ ዘለአለማዊ የሆነውን ሰማያዊ አለም መተርጎም አይችሉም - እውነትን በራሳቸው ጠባብ አንጎል ብቻ ፈልገው እና አግኝተው ሊያውቋት አይቻላቸውምና።

ሳይንስ ቅራኔዎች በጠፈር ሁሉ እንደሚኖሩ ያሳውቀናል። ቅራኔዎች (የእርኩስ እና የቅዱስ መንፈስ ግጭት) በሰዎች ውስጥ እንዳሉ፥ መንፈሳዊ ትምህርቶች ያሳውቁናል። የሰው ልጅ ከነኚህ ተቃራኒ ኃይላት ጋር ሲኖር፥ ፈቃዳዊ ነጻነቱን ተጠቅሞ ይማራል፤ ከሁለት አንዱን መርጦም ሕይወቱን ይመራል። በተቃራኒ የመንፈስ ግጭቶች ውስጥ እያለፍን (ተሳታፊዎችም እየሆን) ከዚህ ደርሰናል።

ሁለንተናዊ ሕብረተሰብአዊ ጭንቀት በያለበት የሚከሰተው፥ በተቃራኒ መንፈሶች መካከል የማያቋርጥ ቅራኔ ስላለ ነው። በየሰው ውስጣዊ ባሕሬ ውስጥ፥ በየፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥም ጣልቃ እየገባ የሚያበጣብጥ (የሚያተራምስ) ክፉ መንፈስ አለ። በዚህ ዘመን በኢትዮጵያችን ላይ የተከመረው የመከራ ፍዳ ከሙብዛቱ የተነሳ፥ እንዲህ ያለውን፥ ማሰብ የማንፈልገውንም ጉዳይ እንድናስበው ተገደድን።

ሁሉን እንደ ታሪክ ስንዘግብ እና ለወደፊቱ ትውልድ ስናቆይ፥ ከአንዳንድ ምድራዊ እና ፖለቲካዊ ትንተናዎች  ባሻገር፥ በግልጽ የማይታየውንም መመልከቱ፥ የምናውቀውን ሁሉ በደንብ እንድናውቅ፥ መርሳት የሌለብንን እንዳንረሳ፥ ትኩረት መስጠት ላለብን ሁሉ ትኩረት እንድንሰጥ፥ ለጋራ ችግሮቻችንም መፍትሄ እንድንፈልግ እና ስለ ሀገራችን ደህንነት ፈጣሪያችንን እንደ መለመኛ፥ መማጸኛም እንዲሆነን ነው።

በአለማችን ላይ ቅዱስ መንፈስ ባይኖር ኖሮ፥ እስከ ዛሬ ሰይጣን የፈለገውን ማሳካት አያቅተውም ነበር። ነገር ግን፥ እግዚአብሔር በሚወዳቸው ሕዝቦች መካከል የቅዱስ መንፈስ መገለጫ የሆነው "**ውስጣዊ ማንነታችን**" ስላለ፥ ሁሉን ማድረግ አልቻለም።

ሟች ሥጋ ቢሞት ቢበሰብስ፥ የቅዱስ መንፈስ መገለጫ የሆነው "**ውስጣዊ ማንነታችን**" አይሞትም አይበሰብስም። በምድር ሳሉ ጥሩ ሠርተው በሞቱ ሰዎች

መንፈስም እየተማርን - ምድራውያን ሥጋውያን ሊያውቁት የማይቻላቸውን እያሳወቁን ከዚህ ደርሰናል።[54]

እውነትን የሚከተል፥ እውነት ከሰው የማሰብ ችሎታ በላይ መሆኑን ስለሚያውቅ በገዛ አእምሮው አይመራም። ይህንን ባለማወቃችን እና ወደመንፈሳዊነታችን ባለማድላታችን - የሚጎድለንን በማያሳውቀን በምድራዊነታችን ላይ የሙጥኝ በማለታችንም ምክንያት፥ ከልጅነት እስከ እውቀት በኑሮአችን ደስታን አጣን፤ እራሳችንንም መልሰን ወደ መውቀስ ተጠጋን።

የረከሰው የሰው ልጅ ጠባይ በገሃድ እየታየ፥ ሞራላዊነቱን (መንፈሳዊነቱን) ረስቶ እንስሳዊነቱን ሲያጎላ፤ ውሸታምነት፥ ራስን ወዳድነት፥ የሥልጣን ጥም፥ ከፋት፥ ውዳሴ ከንቱ፥ ስግብግብነት፥ ትምክህተኛነት፥ እብሪተኛነት፥ አከራሪነትና ጀብደኛነት..፥ ይህ ሁሉ ሕዝቦችን ለመምራት የማይሆን አስከፊ ጠባያት ተሸክሞ፥ ሠፊውን ሕዝብ በቅንነት የሚያስተዳድር መንግሥት እንዴትና ከወዴት ይገኛል?

በምድር ላይ የመኖርን ለዛ በሚያሳጡ ሰይጣናት ስለተከበብን፥ የጥሩነታችን ዋጋ ጭንቀት ሆነ። አንዳንዶቻችን ጥሩ መንግሥት የመጣ መስሎን፥ ግድያ፥ ከእስር ቤት መታጎርም የቀረ እየመሰለን፥ ብዙ ጊዜ ተታለልን።

አምባገነኖች ለሚደግፏቸው ደጎች ናቸው፤ ለሚቃወሟቸው ተናዳፊዎች፤ የሕዝቦች እልቂት የማይሰማቸው ጨካኞች፥ ከፋፍለው 'ሚገዙ "ልዝብ ሰይጣኖች"፤ በችኮላ ሳይሆን በቀስታ፥ ፊት ለፊት ሳይሆን በእጅ አዙር፥ ተቃዊሚ - ተቀናቃኝ ሁሉ እንዲሰወር፤ ጥንትም እንዲሁ ነበር፥ የተለመደ ፈሊጥ - በሥልጣን የመቆያ ምሥጢር።

አንዳንድ ሰዎች "እገሌ ሰይጣን ነው፤ እገሌ ልዝብ ሰይጣን ነው፤ እያሉ በሰው ጠባይ ውስጥ ሌላ ተቀጽላ ስም ማውጣትና የሰውን ልጅ ያልሆነውን ሆነ ብሎ ማጥላላት አግባብ አይደለም" ይላሉ።

በእርግጥ፥ የሰዎችን ጠባይ ጠቅለል ጠቅለል በማድረግ፥ ከፉ ሰው፥ ደግ ሰው እያሉ እንደሚመደብ እና፥ በከፉ እና በደግ መካከልም ብዙ አይነት ሰዋዊ ጠባይ እንደሚኖር የታወቀ ነው። ሆኖም፥ ከዚሁ ጋር ተያይዞ፥ የሰው ልጅ ልዩ እና ፍጹም ምድራዊ መልኩን ከየት እንዳገኘው በጥልቀቱ ማጤን ያስፈልጋል።

---

[54] *"ነገር ግን በሟች ሰው ውስጥ መንፈስ አለ፤ ሁሉን የሚችል የእግዚአብሔር መንፈስም ያስተምራል።" ኢዮ. 32፥ 8*

ከጥንቱም መጥፎዎቹ መናፍስት በእኛ ኑሮ ውስጥ ጣልቃ ባይገቡ ኖሮ፥ ማለትም፥ እግዚአብሔር እኛን ሰዎችን ሲፈጥረን፥ ለራሳችን በተሰጠን የተፈጥሮ ባህሬአችን መሠረት ብቻ እንድናድግ ቢሆን ኖሮ፥ የእኛ የብቻችን እድገት ወደከፋት አይመራንም ነበር።

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሲፈጥረው፥ የራሱን ሕብረተሰብ መሥርቶ፥ ካለ እርኩስ መንፈስ ጣልቃ ገብነት ለብቻው እንዲኖር፤ ለራሱ በተሰጠው የተፈጥሮ ባህሬውም መሠረት እንዲያድግ፤ መላእክትንም ሲፈጥራቸው ለብቻቸው እንዲኖሩ፤ ለራሳቸው በተሰጣቸው ባህሬአቸውም መሠረት እንዲያድጉ ነበር።

ይህንን ስርዓት አስቀድሞ የጣሰ ሳጥናኤል ወደ መሬት ተጥሎ እኛን በጠበጠን፤ ከፋፈለን፤ ኃጢአትን እያሠራ አሳመመን። ከእኛ አስቀድሞ የተፈጠረው ሰይጣን የሰው ልጅ ለፈጣሪው እንዳይታዘዝ አሰናከለው፤ እኛም በሥልጣን ጥም ኃጢአቱ መሬት እንደተጣለ እያወቅን፥ ያንኑ ኃጢአት እንደጋግመዋለን። ሰላማዊውን ሰው በምድር ላይ አላስኖር ያሉ የክፉ መንግሥት ተባባሪዎች እና ክፉዎች፥ አንዳንዶቻችንን ልክ ድመት አይጥን እንደምታሳድድ ያሳድዱናል። እርስ በርስ እስከ መጠፋፋት የሚያደርሰን ምን እንደሆነ በቅጡ አልተረዳንም። የሰው ልጅ በውጫዊ መልኩ የሚታወቀውን ያህል በውስጣዊ መልኩ አይታወቅም። “ከእነኚያ” ሲያዩአቸው ቆንጆዎች፥ ደጋጎች ደስ የሚያሰኙ ሰዎች መካከል፥ በሰው አምሳል የሚመላለሱ ሰይጣኖች እንዳሉባቸው ማን አወቀ?

ምድራችን እጅግ ብዙ አይነት ሰዎችን ታስተናግዳለች። ማንነታቸው እና ምሥጢራዊ ሥራዎቻቸው እንዳይታወቅባቸው የሚጠነቀቁ፥ እጅግ ብልጦቹ “ልዝብ ሰይጣኖች” አሉ ከመሃላችን፤ ቅልስልስ እያሉ፥ እያሳሳቁ የሚገድሉ። እኛ ግን በሥጋ የተገደለውን ብቻ ነው ተገደለ የምንለው፤ ስንት አለ በቁሙ በመንፈሱ የተገደለ።

በላያችን በተፈጽሙ ድርጊቶች የምናዝን እኛ ቋሚዎች ብቻ አይደለንም። በከፍተኛ እምነት ውስጥ እያሉ የሞቱ፥ የሙታን ነፍሶች (መንፈሶች) እረፍት አጥተው ከቋሚዎች ጋር አብረው ያዝናሉ (በደረቅ አይናችን ባናያቸውም)። የሚጠጣ መርዝ ሰውን በሥጋ ይገድላል፤ ከሰይጣናዊ ሰዎች በየጊዜው የሚነገሩ ስብከቶችም የሰውን መንፈስ ይገድላሉ። ከአንዳንድ ሰዎች፥ ከሀገር መሪዎችም ቢሆን፥ ካለማቋረጥ እውነት በሚመስሉ መርዛማ ውሸቶቻቸው እርስ በርስ ያጨራርሱናል። እኛ ግን አልገባንም እንጂ፥ በመንፈስ የተገደልን፥ የቆሳሰልንም ብዙዎች ነን። የአንድነት እና የአብሮ መኖር ምድራዊ እና መንፈሳዊ ታሪካችን፥ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ እሴቶቻችንም እንዲጠፉ፥ ሕዝቡ እርስ በርሱ እንዲጠላላ እና እየተጋጨ ጠቅላላ ኢትዮጵያችን የጦርነት አውድማ ሆና እንድትቀር በሚያደርግ የክፉዎች ሴራ ውስጥ ቆይተናል። ክፉው

መንፈስ ሃይማኖት ጠል በመሆኑ፥ በእግዚአብሔር የሚያምኑትን የሁሉንም ቤተ እምነቶች አልተዋቸውም። በአንድ ወቅት ሁሉም ሆኖ (ተፈጽሞ)፥ በዚያ ላይ ቢያቆም መልካም ነበር። ነገር ግን፥ ይህ መልካም የሆነውን የሰዎች የመንፈሳዊነት ነገር በአውዳሚነት መቀጠል፥ መጨረሻው እንደማይታወቅ እጅግ ሰፊ የጨለማ ዋሻ ሆነ።

አይኖች ብዙ አይተው ፈዘዙ፤
ጆሮችም ብዙ ሰምተው ደነዘዙ፤
አብራኮቻችን አይተውና ሰምተው ቆሰሉ፤
ልብ እና አንጎል (መንፈስ እና ሥጋ) ለየብቻ ዋሉ፤
ኢትዮጵያና ኢትዮጵያ ፊት ለፊት ተያዩ።[55]
የሰው ልጅ እንደ ርካሽ እቃ - እንደማይጠቅም ነገር፥
ወይንም ለጥቂቶች አሽከር....፤
አዬ! የታየውም፥ የተሰማውም ሲተገበር፥
ከእንግዲህ ለምድሪቱ ማን ይቅር?
ከሰውም ሰው እየተመረጠ፥ እንደ ወሰራ ዶሮ፥
ጭዳ እየታረደ ሲጣል ከጓሮ፥
ምነው ብላ ስታለቅስ እናት፥
እርሷንም ከዚያው ሲደፏት፤
ኡ! ኡ! ቢባል - ቢጮህ የማይሰማባት፥
አ! ምድሪቱ ተጨናንቃለች፤
በእርኩሳኑ - በመናፍስት።
የሆዱን ጥላቻ፥ ሲጎረብጠው የቆየውን፥
እርሱ ለዓመታት ያሰናዳውን፥
ሰይጣን ከአፉ የተፋውን፥
መርዙን እንደ ጸበል ሲረጭብን፥
እንዴት ማየት ማስተዋል ተሳነን?
ያንን ከፉውን - ሰይጣኑን።
ቀን ቆጠርን፥ ወራት ዓመታትን፥

[55] ምድራዊት ኢትዮጵያ እና ሰማያዊት ኢትዮጵያ።

እስከመቼ? ምን እስክንሆን?
ምንም ተስፋ እንደሌለን፥
የምናምንበት ፈጣሪም እንደራቀን፤
ጠባቂ መላእክት እንደሌሉን፥
ጾምና ጸሎታችን፥
እርግማን በላያችን፥
ከፉውን እንደጠራብን፤
ያወቅነው አሳሳተን፥
የማናውቀው ነገሡብን።

በሞኝነታችን ተታለልን፤
በእብሪተኛነታችን ደነቆርን፤
በመታጀላችን እውነትን ተውን፤
በአልሰማ ባይነታችንም ወደቅን።
እራስ ወዳዶች በመሆናችን፥
ወገኖቻችንን ረሳን!

በአንዳንድ የኢትዮጵያ ሥፍራዎች ሕዝቡ ማንነቱን ተነጥቆ፥ ህልውናውን እስከሚያጣ፤ በጅቦች መካከል ብቻውን እንደቀረ ድኩላ እስኪሆን ድረስ፥ በወለጋ፥ በሸዋ፥ እንዲሁም በሌላ የተፈጸመው አረመኒያዊ ግፍ የማይረሳ ስለሆነ፥ በማስተዋሻችን ይዘነዋል። ለሰይጣን የሰው ሥጋ እና ደም እንደሚጣፍጥ የዶሮ ወጥ ስለሆነ፥ በኢትዮጵያ ምድርም ሰዎችን ጭዳ ሲያሳርድ፥ ለዚህ ዝግጅት ቅድሚያ ሰጥቶ አሰናድቶ ነው እንጂ፥ እንዲሁ ብድግ ብሎ አይደለም። ይህንን ጉዳይ ከሀገራችንም ሁኔታ ጋር ማገናዘብ እና ማስተዋል የአንባብያን ፋንታ ነው።

የከፋት ሁሉ ምንጭ የሆነውን አውቀን ምን ጊዜም እንዳንረሳው እንድንማርበትም ዘንድ ዘግበነዋል። ይህም፥ "ኡ!" የሚያሰኝ፥ በትግራይ ተወላጆች ላይ የደረሰ ሰቆቃ፥ በኦሮሞ ተወላጆች ላይ የደረሰ ሰቆቃ፥ በአማራ ተወላጆች ላይ የደረሰ ሰቆቃ፤ በአፋሮች እና በሌሎችም የደረሰ ሰቆቃ፥ በአጠቃላይ በኢትዮጵያችን ሁሉ፥ ከዳር እስከ ዳር የተዳረሰ ሰቆቃ ነው።[56]

---

56 "በእኛ ላይ የደረሰው ሰቆቃ በሌሎቹ ከደረሰው ሰቆቃ ይብሳል" እንዳንባባል እንጂ፥ በተለይ ከፍተኛ ሰቆቃ የደረሰበትን አካባቢ አንባቢ ያውቀዋል።

**<u>ሰቆቃ በምድረ ኢትዮጵያ</u>**

የወግኖቻችንን እሮሮ ሰምተን አለቀስን፤
እኛስ፥ ኦሮሞው እንደ ሕዝብ፥
ለአማራው ጠላት ሲሆን አላወቅን፥
እኛስ፥ ትግሬው እንደ ሕዝብ፥
ለአማራው ጠላት ሲሆን አላየን፥
በእርኩስ መንፈስ ሴራ የተቃኙ፥
ክፉዎች አፋጁን።

ከገደምንበት ከገዳሞቻችን፥
መነኮሳቱን ገደሉብን።
መጸለያ ሥፍራዎቻችንን የጦር ምሽግ፥
በእጣኑ ሽታ ምትክ የባሩድ ጭስ፥
በቅዱሳን ሥፍራዎች - ቅዱሳኑን ሲያተራምስ፥
ክፉ ሽታ - ሰማይ የወጣ ግፍ፥
የእርኩሳን መናፍስት - የዘር ፖለቲካ ጥንሥሥ፥
ከየአቅጣጫውም ጦርነት ሲቀሰቀስ፥
በውስጧ ተወልደው ባደጉባት፥
ኢትዮጵያችንን አስጨነቋት - አስለቀሷት፤
ስቃይ መከራ - ሰቆቃ በዛባት።

ሕጻናት፥ አቅመ ደካሞችን ሲገድሉብን፥
ቤታችን ሲዘረፍ፥ ሲቃጠል፥ ሲወድም ንብረታችን፥
እትብታችን ከተቀበረበት ቀዬ ስንባረር፥
“ሀገር ለቃችሁ ሂዱ! ውጡ!” ስንባል፥
ይህንን በትግራይ ተወላጆች ላይ
የደረሰውን ጉዳት የሚያይ፥
ይህንን በማራ ተወላጆች ላይ
የደረሰውን ጉዳት የሚያይ፥
ይህንን በኦሮሞ ተወላጆች ላይ

የደረሰውን ጉዳት የሚያይ፥
ይህንን በአፋር እና በሌሎችም ተወላጆች ላይ
የደረሰውን ጉዳት የሚያይ፥
ይህንን በአጠቃላይ በኢትዮጵያችን ላይ
የደረሰውን ጉዳት የሚያይ፥
አይቶ ዝም አይልም መንፈሳዊ አይን።
ስንቸገር መሄጃ መጠለያ ሥፍራ አጥተን፤
እራሳችንን የምንመክትበት መሳሪያ የለን፥
የሚሰማንም መንግሥት አላገኘን፤
ቢሰሙንም መልሰው እኛኑ የሚገድሉንን ላኩብን።
ኢትዮጵያችን በላያችን ቅይር ብላ የማናውቃት ስትሆንብን፥
እኛ ከሰው መሃል ተፈጥረን፥
ሰው ማጣታችን እጅጉን አሳዘነን፤
ሃዘኑና ልቅሶውም እጅግ ምርር - ክርር ያለ ሆነብን።
በደላችንንም የሚያወራ አፍ በአንድም በሌላ ሲዘጋ፥
"አቤት! አቤት! ኡ! ድረሱልን.." እያልን ብንጣራ፥
የሰውን ጭንቁን እና መከራውን የሚጋራ፥
አይደለም የሚራዳ፥
አይዟችሁ እንኳን የሚል - የሚያጽናና ጠፋ።

የ "እኛ ምን በደልን?" ጥያቄአችንን ማን ይመልስልን?
ይልቁንም ጭንቀታችንን የተረዳልን ማጣታችን፥
እጅጉን አሳዘነን።
"ከእንግዲህ ወዴት እንሂድ?" እስክንል ድረስ፥
እጅጉን ግራ ተጋባን፤
ሃዘኑና ልቅሶውም እጅግ ምርር - ክርር ያለ ሆነብን።

በገዛ ሀገራችን ሀገር አልባ ስንሆን፥
መጠለያ መጠጊያ ሥፍራ ስናጣ - ስንሰደድ፥ ስንደበቅ፥
ነፍስ ለማትረፍ ጫካ ገብተን፥

ከጥይት ያመለጠውን ሥጋችንን ለዱር አውሬዎች አጋለጥን።
ምነው እስከዚህ ምን በደልን?
ማነው የኃጢአታችንን ልክ የሚነግረን?
እኛ ዘር ሳንለይ ሀገር ሰላም ብለን፥
አብረን ተወልደን አብረን እንዳላደግን፥
በፍቅር አብረን እንዳልኖርን፥
ጥላቻን በቋጠረ መርዛማ የፖለቲካ ቋንቋቸው ለያዩን።
በዘር ማጥፋት ጭፈጨፋ በጅምላ ተገደልን፤
በጅምላ ተቀበርን።
እየመረጡ በጥይት እንዲለቅሙን፥
ጨፍጫፊውን ኃይል አዘው አሰማሩብን፤
አልቻለም፥ አብሮን ለረጅም ጊዜ የኖረው፥
የምንወደው የምናፈቅረው ጎረቤት ሊደብቀን።
በዘር ተለይተን የተፈጠርን እስኪመስለን፥
ከላይ እስከታች ደጋፊ በማጣታችን፥
እጅጉን ከፍት አለን፤
ሃዘን እና ልቅሶውም በረታብን።
ሳንሞት በሕይወት መገኘታችን፥
"እናንተስ እድለኞች ናችሁ" እንዳያስብለን፣
ይኸውና እዩት ገጻችንን - እንዲሁም ገላችንን፥
አፈር፥ አመድ የመሰለውን - የቀረፈደውን ቆዳችንን፥
በእንባ የበለዘውን - ደም ግባት አልባ ፊታችንን።
እዩት ተመልከቱት፤
በረሃብ የተጎዳ ሰውነታችንን።
የሚቆጠር አጥንት ተገጣጥሞ ቁመና ቢሰጠንም፥
የሞትነው የቆምነውም - በአንድ ላይ ሁላችንም፥
ሙታን ከመባል አልተረፍንም።
ኢትዮጵያን የጠላ ነው “እኛን” ለይቶ እጅግ የጠላን፥

በኢትዮጵያችን ከበላይዋ በተጫናት ልዩ ኃይል ነው፤
ከምድር ገጽ እንድንጠፋ የተፈረደብን።
ከንፏን እንደተመታች - መብረር እንደማትችል ወፍ፥
በመሬት ላይ ስትንቀሳቀስ ስትል ወልከፍ ወልከፍ፤
እኛም እንዲሁ በምድራችን፥
ባይተዋርነት ተሰማን።
መሸሸጊያ ምሽግ፥ መጠጊያ ጥግ፥ መጠለያም ሥፍራ አጣን፥
እንዳው ድንግርግር ስላለን፥ እጅጉን ከፍት አለን፤
ሃዘን እና ልቅሶውም በረታብን።
በተፈጥሮ እቅፍ ውስጥ አድገን፥
ስንመኝ፥ ስንጓጓ በዘመናችን፥
መጪው ከፍታችን ይሆናል ብለን፥
አስበን፥ ተመኝተን አልመን፥
ብዥታ ብቻ ሆነ ሕይወታችን፤
ጉራማይሌ ሆነ አለማችን።
በሃሳብ እና በስሜት
ከእራሳችን (ከማንነታችን) ርቀን፥
እንዳየን  አላገኘን፤
እንደሰማን አልሆነልን።
እንደ የጥጥ ፍሬ - ካልፈለቀቁት ‘ማይላቀቅ፥
ሰርክ አለም ትግል - የእውነት እና የውሸት ትንንቅ።
መንግሥት ሲቀያየር - በጦርነት በእልቂት፥
ድምቀት - ውድመት - የእድገት ሂደት - በደም ጅረት!
ግ’ንኮ! አንድ ኗሪ በምድር ስለደላው ሞትን ቢፈራው፥
ሌላው ኗሪ በምድር ካልደላው፥
ሞትን ምን አስፈራው?
ለነፍስም ጠባቂ - ኖላዊ  ቢኖረው፥
መሄጃውን አውቆ ከበረት ቢያስገባው፥

ቅልቅል ነው "ከዛፍ፥ ከቅጠሉ - "ከልምላሜው"፤
ጠፍተንም እንደማንጠፋ ተፈጥሮ ምስክር ነው።
ሲነድ ሲዳፈን በቆየ የጥላቻ ሰንሰለት፥
የሳለፍነውን መከራ ያያሉ መላእክት፥
ፈጣሪያችንም አይቶ ዝም አይልም የእኛን ጉዳት።
ኮለል ብሎ እንባችን - ቢያርስ ፊታችንን፥
ኮለል ብሎ ደማችን - ቢያጨቀይ መሬቱን፥
ጭቃው መድኃኒት ነው የሚያበራ አይኖችን፤
ይኸው ነው የቀረን ተስፋችን እምነታችን።
እጆች ሲዘረጉ ወደ ሰማይ፥
ወደ ታች ያይደለ፥ ወደ ላይ፥
አለ ሌላ ሕይወት ከምድር ሳሉ የማይታይ፤
በምድራዊነት ጥጋብ የለም፥
ምድራዊ ሰው በቃኝን አያውቅም፤
በመንፈሳዊነት አልጠግብ ባይነት የለም፥
መንፈሳዊ ሰው ረሃብን አያውቅም።
ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሊነግሥ አልመጣም፤
ኢትዮጵያም ምድራዊት ብቻ አይደለችም፤
ምድራዊነት አይጸዳም፤ አያምርም፤
ምድራዊነት ስለማይጸዳ፥ ስለማያምርም፥
ኢትዮጵያ ምድራዊነት ብቻውን አልተስማማትም።

ሰይጣን በሰዎች ላይ ሊፈጽም በሚችለው ላይ ገደብ አለበት። እርሱም የእግዚአብሔር አርጩሜ ከመሆን አልፎ ጅራፍ ልሁን ቢል አይችልም። የጥላቻ ቅስቀሳ ሲካሄድ ቆይቷል። የሕዝብ እልቂትማ ከታወጀ ቆይቷል። ነገር ግን፥ እንደተፈለገው ያላለቅንበት ምክንያቱ፥ በሁለት ተቃራኒ ኃይላት መካከል በመገኘታችን መሆን አለበት። መንግሥት ሊጨርሰን ክንዱን በኃይል ሲዘረጋ፤ ከቁጥጥሩ ውጪ በሆነም ኃይል ክንዱ

ሲታጠፍበትና ለማድረግ ያቀደውን ማድረግ ሳይችል ሲቀር[57]፥ አዎ! በእርግጥ እግዚአብሔር ለነፍሳችን ሲያስብልን፥ ለሥጋችንም እንደሚያስብልን ይገባናል።[58]

በክፉዎች አእምሮ ሲታሰብ፥ ከክፉ ስርዓት ጋር ተባብሮ ተስማምቶ መኖር ይቻላል። በደጋጎች አእምሮ ሲታሰብ ግን፥ ከክፉ ስርዓት ጋር ተባብሮ ተስማምቶ መኖር አይቻልም። ስለዚህ፥ በሀገራችን ሰላም እና መረጋጋት እስኪሰፍን ድረስ፥ በክፉዎች እና በደጎች መካከል ያለው ትግል አይቋረጥም። ፍጹም እርኩስ በሆኑ ሂደቶች በዘመናችን የገባው ክፉ መንፈስ በአባቶች ጸሎት እና ጦም ብቻ ሳይሆን፥ የሕዝቦች ሁሉ ጸሎት እና ጦም አስፈልጎታል። የመጣብንን ክፉውን ዘመን በጋራ ጸሎት እናሳልፈዋለን። ጥሩውን ጊዜ የምናመልከው እግዚአብሔር አምላካችን ያመጣልናል።[59]

---

57 በጣም ብዙ ከምድር (በታንኮች) ከሰማይም (በድሮን) የታሰቡ ጭፍጨፋዎች እንዳሰቡት አልተሳካላቸውም። ይህም፥ እግዚአብሔር ለነፍሳችን ሲያስብልን፥ ለሥጋችንም እንደሚያስብልን ያመላክታል።

58 *"ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፤ ቤዛነቱንም፥ እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት፥ ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰ።" ቆላ.1፡13*

59 *"...ከእግዚአብሔር ዘንድ መልካሙን ተቀበልን፥ ክፉውን ነገርስ አንታገስምን?" ኢዮ. 2፡10*

# ምዕራፍ አስራ ሁለት

## መልዕክት ከገደል አፋፉ ላይ

በኢሕአዴግ ምትክ ልዩ መንግሥት መጣባት ኢትዮጵያችን። ከዚህ ከተጻፈው፥ ዛሬና ለወደፊትም ከሚጻፈውና አንባቢ ከሚያነበው፥ በአፍም ሲነገር ከሚሰማው፥ በግልጽ ከሚታየውም በስተጀርባ ያለው እጅጉን የከፋ ሆኖ ሳለ፣ እኛ ግን፥ መንግሥት በሕዝብ ላይ፥ ሕዝብም በመንግሥት ላይ እንዲያምጹ የሚያደርጋቸው ሥር የሰደደ ቅራኔ ምክንያቱ ምን እንደሆነ የሚገባን በዛው በተለመደው የፖለቲካ፥ ሶሻል እና ኢኮኖሚ ትንታኔ ነው። በዚህም ረገድ ነገሮችን በጥልቀት መረዳት አላቃተንም። ሆኖም፥ በሀገራችን የደረሰው፥ ከማንኛውም ምድራዊ እውቀት በላይ ሆኖብናል። ስለዚህ፥ የኢትዮጵያችንን አካላዊ ገጽታዋን ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ገጽታዋንም መመልከት አስፈልጓል።

መጥፎ አስተዳደርን እና ክፉ መንግሥትን ስንቃወም በሃሳብ እስከ ጥግ ያደረሰን ከምድራዊ ፍልስፍና ያልተላቀቀ እሳቤ (በመንፈሳዊነት ያልተቃኘ ዘመናዊ ትምህርት) በመሆኑ፥ ገፍቶ ገፍቶ ከገደል አፋፍ አደረሰን። አሁን የቆምንበት ገደል አፋፍ መሆኑን እያወቅን፥ ወደፊት አንድ እርምጃ በመሄድ ገደል ውስጥ ገብተን ራሳችንን አናጠፋም፤ ከቆምንበት ሥፍራ ሳንንቀሳቀስ በትካዜ ተውጠን፥ ውስጣዊ ስሜቶቻችንን በእንጉርጉሮ እናሰማለን፤ የሚሰማ ይሰማናል።

በሚሊዎን ሰዎች ይሰቃያሉ፤ የብዙዎቻችን አእምሮ ታውኳል። ሰዎች በግላቸውም በህብረትም ኃጢአት ይሠራሉ። መንግሥትም ኃጢአት ይሠራል። እግዚአብሔር ሁሉንም ያያል፤ ሰውን በመፍጠሩ ቢያዝንም[60] እርሱ ጥሩ በሚለው ግለሰብ አማካኝነት ከፍጡራኑ ጋር እየተገናኘ ቀናውንም መንገድ እንድንከተል ይመከረናል። እኛ ግን፥ እራሳችንን በራሳችን ለማስተዳደር በቂዎች ሆነን አልተገኘንም።

---

[60] *"እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፤ በልቡም አዘነ።" ዘፍ. 6፡6*

ከሦስት ሺህ ዓመታት በፊት፥ በቁጥር ጥቂት የነበሩ እስራኤላውያን እንኳን በእግዚአብሔር እየተመሩ በሕብረት እንዳይኖሩ አስቸገሩ። ምክንያቱ ምን ይሆን? በሕዝብ እና በመንግሥት መካከል ጣልቃ የሚገባ ኃይል ይኖር ይሆን?

እስራኤላውያን ከግብጽ ምድር ወጥተው ሲንከራተቱ፥ አልፎ አልፎም ተረጋግተው ሲኖሩ፤ ከሙሴ ጀምሮ እስከ ሳሙኤል ድረስ ንጉሥ አልነበራቸውም። ሳሙኤል የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመከተል እስከ እርጅናው ድረስ መራቸው (አገለገላቸው)። ከጊዜ በኋላ፥ እርሱ ሲያረጅባቸው፥ የእርሱም ልጆች ጉበኞች በመሆን ፍርድ ሲያጣምሙ በማየት፥ ሽማግሌዎችን ወደ ሳሙኤል ላኩና፡- "አንተም በዙሪያችን እንዳሉ አሕዛብ ፈራጅ ንጉሥ አድርግልን" አሉት። እነርሱ በዙሪያቸው ያሉ አህጉራት በንጉሦች ሲስተዳደሩ እንዲሁ በቅናት ተመለከተው፥ "ለምን እኛስ እንደነሱ አንሆንም?" ብለው አሰቡ እንጂ፥ በንጉሥ እና በሕዝቡ መካከል ያለውን ግንኙነት - የንጉሥ ስርዓት በሕዝቡ ላይ የፈለገውን ማድረግ የሚያስችል - የገዢ እና የተገዢ አይነት ስርዓት መሆኑን አላወቁም ነበር። ይህ ጉዳይ ሳሙኤልን አስከፋው። ሳሙኤል እንደ አንድ ቅን የሕዝብ መሪ እና አገልጋይ፥ "እኔ ማድረግ ያለብኝ የሕዝቡን ፍላጎት መፈጸም ነው፤ ወይንስ ለእነርሱ የሚሻላቸውን ማድረግ" በሚል ሁለት ተቃራኒ ሃሳቦች ስለተወጠረ፤ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ።

*"እግዚአብሔርም ሳሙኤልን አለው፡- በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን እንጂ አንተን አልናቁምና በሚሉህ ነገር ሁሉ* ***የሕዝቡን ቃል ስማ****። ከግብጽ ካወጣኋቸው ቀን ጀምሮ፥ እስከ ዛሬ ድረስ፥ እኔን ትተው እንግዶች አማልክት በማምለካቸው ወደ ሠሩት ሥራ ሁሉ እንዲሁ ደግሞ ባንተ ያደርጉብሃል። አሁንም ቃላቸውን* ***ስማ****። ነገር ግን ጽኑ ምስክር መስክርባቸው። በእነርሱም ላይ የሚነግሠውን* ***የንጉሡን ወግ ንገራቸው።****" 1ኛ ሳሙ. 8፡7-9*

ሕዝቡ እግዚአብሔርን አስቆጥቶትም ቢሆን፥ "...*የሕዝቡን ቃል ስማ*" አለ እንጂ፥ ለእነርሱ የሚሻላቸውን አስተዳደር "እንዲህ ብለህ ንገራቸው!" አላለውም። ይህም፥ ከሕዝቡም መካከል ጥሩዎች እንዳሉበት እና የእነርሱም ቃል መደመጥ እንዳለበት ይጠቁማል - የሳሙኤል ማርጀት፥ የልጆቹም ጉበኞች መሆን እና ፍርድን ማጣመም፥ የከፊሉን ሕዝብ ጥያቄ ወቅታዊና ትክክል ያደርገዋል።

እግዚአብሔር ለሳሙኤል የነገረውን ካሳለፍናቸው ሦስት ሺህ ዘመናት ጋር እያሰላሰልን፥ ከሀገራችን የአሁኑ ሁኔታ ጋር በማነጻጸር፥ ስለወደፊቱም የሕዝብ እና የመሪዋ ግንኙነት መመራመር ይቻላል። ሰፊውን ትንታኔ ለአንባቢ እንተውና፤ ባጭሩ፥ ባለፉት ሦስት ሺህ ዘመናት ውስጥ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን እንደተመለከተ፤ ይህች ትንሽ ሀገር፥ እርሷም "በአሕዛብ" ዙሪያ ተከባ፥ ስትወድቅ ስትነሳ ከዚህ እንደደረሰች፤

አሁንም፥ ይህ "እኛ መንግሥት" ብለን የጠራነው፥ እርሱም "...የንጉሡን ወግ ንገራቸው" እንደ ተባለለት፥ እንደ ሳዖል አይነት፥ ወይንም የአለሙ ገዢ እንደሚባለው እንደ ሰይጣን ያለ ንጉሥ ሊሆን እንደሚችል፤ በሕዝቦች እና በመሪዎች መካከል ያለውን እና መኖር የሚገባውን ግንኙነት ሁሉ ማገናዘቢያ ይሆነናል።

በምድር ላይ ካለ ብዙ ችግሮች ብዙ ለመቆየት፥ ሰው የሆነውን ሁሉ በሰውነቱ ማወቅና ማክበር፥ ለሕብረተሰባዊ አንድነትም ቅድሚያ መስጠት ግዴታ እሙን ነው። መንግሥትም፥ እምነት የሚጣልበትና ሕዝቦችን መምራት የሚችል፥ ለራሱ ለሥልጣኑ ማቆያ ብቻ ሳይሆን፥ ለመላው ሰፊ ሕዝብም የሚያስብ መሆኑ በተግባር ሲረጋገጥ ነው። ሕዝቦችም መሪያቸውን ካልሰሙና ካልተከተሉ በስተቀር ሀገር ወደፊት ልትራመድ አትችልም። ሕዝቡ ሁልጊዜ ሰሚ፥ መሪዎቹም ሁልጊዜ ተሰሚ መሆናቸው ተገቢ እንዳልሆነ ነው እግዚአብሔር ለሳሙኤል ከነገረው የተማርነው።

ታዲያ፥ የሰው ልጅ በሕብረት ሲኖር፥ ሰላሙን የሚያገኘው በራሱ ጥሩ ሲሆን እና የሚያስተዳድረውም ምድራዊ መንግሥት ጥሩ ሲሆን ነው። ይህንን በሁለት ወገን ጥሩ መሆን ሳናገኝ እየቀረን ነው የተቸገርነው።

ኢትዮጵያም ለእስራኤል ንጉሥ ይሆን ዘንድ፥ ከንጉሥ ሳዖል ቀጥሎ የነገሠውን በእግዚአብሔር የተወደደውን ንጉሥ ዳዊት እንደ ምልክት ወስዳ፥ ከንግሥት ሳባ እና ከንጉሥ ሰሎሞን የተወለደውን ቀዳማዊ ምኒሊክን በሥርወ መንግሥትነት አጥብቃ ያዘች። አባታችን ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ተቋርጦ የነበረውን የሰሎሞን መንግሥት እንዲቀጥል የመከሩት፥ ሕዝቡ እግዚአብሔር በሚወደው (በሚፈቅደው) ንጉሥ በኩል እንዲገናኝ ነበር።[61]

እኛ ግን፥ ንጉሥም ሆነ ሌላ የሀገር መሪ፥ ከእግዚአብሔር የተሾመውን እና ከእግዚአብሔር ያልተሾመውን ለመለየት መንፈሳዊ ብቃት እያጣን፥ ወይንም በራሳችን ምድራዊ ፖለቲካ እየተማመንን ስህተቶችን እንደጋግማለን።

"ሕዝቦችም የሚገባቸውን መንግሥት ያገኛሉ" በማለት፥ መንግሥት ትክክለኛ ሆኖ፥ መንግሥት ሊሳሳት እንደማይችል አድርገው የሚያስቡ አሉ። ይህ ሁልጊዜም እውነት ላይሆን ይችላል። "እንዲህ አይነት ጨካኝ መንግሥት ለምን ወደ ሕዝብ መጣ?" በማለት መጠየቅ ያስፈልጋል፤ መንግሥታትም ጨካኞች እየሆኑ፥ ሕዝብን እንደሚበድሉ ከታሪክ ተምረናልና።

---

[61] በገድለ ተክለ ሃይማኖት እንደተገለጸው፥ በእርሳቸው እርዳታ ነው የሰለሞን ሥርወ መንግሥት የዛግዌ ሥርወ መንግሥትን የተካው።

የቀዳማዊ የኃይለ ሥላሴን ንጉሣዊ አገዛዝ በመቃወም ከተነሡት ተራማጅ ኢትዮጵያውያን መካከል፥ አንዳንዶቹ ከዚያ ጥሩ ከሚባለው ከዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመድረስ ነበር። ሳይሆን ቀረ። ይሆን ዘንድ በማይቀረው እና መሆን በሚገባው ጉዳይ መካከል፥ አንዳንድ ተፍጨርጫሪዎች በትግል ላይ ሳሉ እራሳቸውን ለሞት አሳልፈው የሰጡት (ሰማእታት የሆኑት) በውስጠ ባህሬአቸው ጥሩዎች ስለሆኑ ነው። በማሕበራዊ ኑሮአችን ውስጥም በባህሬአቸው መጥፎዎችም ስላሉብን ሰላማችንን አጣን። ይህ "እኛ መንግሥት" ብለን የጠራነውም፥ እራሱን ከሕዝብ ገንጥሎ፥ የራሱን ድብቅ መንግሥት መሥርቷል፤ እጅግ ከፉ ስለሆነብን፥ ማሕበራዊ ኑሮአችን ተናግቶብናል።

በዚችው በአለማችን እንደ ባይተዋር፥ እንደ እንግዳም ስለተቆጠርን፤ "አ! ፈጣሪያችን አምላካችን፥ ጌታችን፥ ተስፋች፥ መመኪያችን፥ አንተው እራስህ በመስቀል ላይ ተሰውተህ፤ አንተን መከተል የውስጣዊ ባህሬአችን ተፈጥሮ ሆኖ ሳለ፤ የበደላችንን ልኩን አላወቅነውም። ከእንግዲህ ይህችንም አለም ለቀን እስከንሄድ ድረስ፥ እንዴት እንኑር? ማንስ ይሁን ንጉሣችን?" በማለት፥ የእግዚአብሔርን ፍርዱን እየተጠባበቅን ነው። ምናልባት ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥትን ብንመሠርት እና ስለ መጪው ዘላቂ መንግሥት በአርምሞ እንድናስብ የሚያደርገን ትንሽ መንፈሳዊነት ቢኖረን፤ የእግዚአብሔር መሪነት ታክሎበት መጪው ጊዜ ይሰምርልን ይሆናል።

እስካሁን ድረስ፤ በአባቶቻችን ጸሎት እንደቆየን፥ ለወደፊትም በእግዚአብሔር ቸርነት ስንኖር፥ ዘወትር የምንጸልየው ጸሎታችን ያበረታናል፤ ከክፉው መንፈስ ያርቀናል፤ ወደ ቅዱስ መንፈስም ያስጠጋናል። *"እንግዲህ እግዚአብሔርን እሺ በሉት፤ ሰይጣንን ግን እንቢ በሉት፤ ከእናንተም ይሸሻል።" ያዕ. 4፡7*

ሰማይና ምድርን በቃሉ የፈጠረ አምላካችን፥ እኛን ሲፈጥረን፥ በጎ ፈቃድን ለእኛ ተወልን እንጂ፥ እኛንም በየጊዜው እያጠፋ መልሶ መላልሶ መፍጠር አላቃተውም። "እግዚአብሔር ለምን የክፋት ሁሉ ጠንሳሽ የሆነውን ሰይጣን አይገድለውም እና ሁላችንን አያሳርፈንም?" ብለን እንጠይቅ ይሆናል። ነገር ግን፥ ነገሮችን በሳይንሳዊ አረዳድም ብንመለከተው፥ አካላዊ ተፈጥሮ (እኛንም ጨምሮ) የምናድገው (የምንሻሻለው) በተቃርኖ ነው፤ ካለ ተቃርኖ እድገት (መሻሻል) የለም። ስለዚህ፥ የእውነት እውነትነት ግልጥ ብሎ ይታይ ዘንድ የግድ ውሸትም መኖር አለበት፤ ሰይጣንም መኖር አለበት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የኃጢአቱ እድገት - አድጎ አድጎ፥ ዘርን አጥፍቶ ዘር ወደማይለየው ጥሩ ሰውነት እና መጥፎ ሰውነት ተከፍሏል። አማራን አማራ

ከገደለው፥ ኦሮሞን ኦሮሞ ከገደለው፥ የእውነት እና የውሸት ትንንቅ ከዘር በላይ መሄዱን ያመላክታል (ከዘር በላይ ክፋት፥ ከዘር በላይም ደግነት)።

ምናልባት በፖለቲካ በመወናበድ ክፋና ደጉን መለየት ካቃታቸው በስተቀር፥ በአንድ ጎራ ያሉ፥ በብልጽግና መንግሥት የሚከናወኑትን ሁሉ ይደግፋሉ። በሌላ ጎራ ያሉትም፥ በዚህ በብልጽግና መንግሥት የሚከናወኑትን ሁሉ አይደግፉም። የተጠቀሱት ተቃራኒ የሕዝቡ አስተያየቶች የሚያመለክቱት፡- ሕዝቡ በሁለት ተቃራኒ የእድገት ጉዞ ውስጥ እየገሰገሰ መሆኑን ነው። የገጠመን ከምድራዊ እውቀቶች ሁሉ በላይ ሆኖብን።

በአንድ ጎራ ያሉ ሕዝብ (ዘረኛ ቢሆንም ባይሆንም)፥ ወደ ውሸታምና ክፉነት ተለውጧል (ወይንም በመለወጥ ላይ ይገኛል)። በሌላ ጎራ ያለ ሕዝብም (ዘረኛ ቢሆንም ባይሆንም)፥ ሰው ሲበደል እና ሲጎዳ ማየቱ የበለጠ እውነተኛና ደግ እንዲሆን አድርጎታል (ወይንም እየሆነ ይገኛል)።

ክፉ ሰዎች (እርኩሳን መናፍስትም ከሰዎች ጋር) በያሉበት የሚያደርጉት ምድራዊ ተሳትፎ ምንኛ የረቀቀ መሆኑን ማገናዘብ ቀላል ባይሆንም፥ ለወደፊት ሊመጣ ያለውን ክፉ ጊዜ ለመመከት፥ ፈጣን አቋምና እርምጃ ለመውሰድ እንገደዳለን።

የሰውን ክፋት እና የክፋቱን መጠን ከውስጣዊ ተፈጥሮው ብቻ መገመት ስለሚያስቸግር፥ ጥሩ ከሚመስለውና በግላጭ ከሚታየው ሁሉ በስተጀርባ ኢትዮጵያችንን ሀገረ ሰይጣን ለማድረግ የተንኮል ጉንጉን (የውጪ ኃይል - በአለሙ ሁሉ ያለ የክፉው መንፈስ ሴራ) መኖሩን በአእምሮ ሚዛን መመዘን፥ በስነ አመክንዮ መመርመር፥ በአይነ ሕሊና መመልከት፥ በሃሳባዊ ፍልስፍናም ማጤን ያስፈልጋል።

"ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስስ አይተውም" እንደሚባለው ሁሉ፥ ማንኛውም ሥራ ሲሠራ በውስጡ አንድ አይነት መንፈስ አቅፎ ነው። ካለ አላማ የሚተገበር አህጉራዊ ወይንም አለም አቀፋዊ ተግዳሮት አይኖርም።

ቢሳብም፥ ቢጠቀለልም፥ ቢዘረጋም፤ እባብ እባብነቱን አይተውም፤ አድብቶ መናከሱ አይቀርም። ስለዚህ፥ "የክፉ መንፈስ አሠራር ማንን እና ለምን ይጠቅማል? ለምንስ አስፈለገ?" ብለን ስንጠይቅ፥ በጥቃቅን ተግዳሮቶች ከሚገለጡ ተንኮሎች ባሻገር፥ ሰይጣን አንድ ከፍተኛ አላማ እንዳለው እንገነዘባለን። ይኸውም፡- የእግዚአብሔር መንግሥት ከሰማይ እንደሆነ በምድርም እንዳይሆን የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ ነው።

ስለ መጥፎው አለም መጥፎውን የሚያጋልጡትን ደፋሮች እና እውነተኞች፥ ቅዱሳን መላእክት ይወዷቸዋል፤ ከመጥፎው ጋር የሚወግኑትንም ሰነፎች እና ውሸተኞችን እርኩሳን መናፍስት ይወዷቸዋል።[62]

እንግዲህ፥ ተገፍተን ሄደን ከገደል አፋፉ ላይ ስንደርስ ቆም ማለት ግዴታ ሆኖብናልና፤ ለዚህ መፍትሄ ላጣ የእንቆቅልሽ ኑሯችን ያሉንን አማራጮች ለመገምገም፥ ቆም ብለን፥ በግልጽ ከሚታወቀውና ከምናየው ባሻገርም አርቀን እንድናስብ ተገደናል።

ይህ ጊዜ ወሳኝ ነው። ከእንግዲህ መጪው ጊዜ በጣም አስፈሪና አስከፊ ቢሆንም፥ በግራና በቀኝ ከሚታየው የሰዎች እልቂት በስተጀርባ ሰብአዊነት በማያቋርጥ ጉዞ ወደፊት ይገሰግሳል። ከእንግዲህ፥ በዚሁ በያዝነው ጎዳና የምንራመደው አንድ እርምጃ ወደ ገደል እንዳይከተን ቆም ብለን እናስተውል። ጠላት ከበስተኋላችን “ግፋ በለው! ሂድ ሂድ!” እያለ ይጮሃል። ከእንግዲህስ፥ በጉዞአችን ሁሉ፥ ከግራና ከቀኝ ብርሃን እያየን፥ ከፊት ለፊታችን ወዳለው ወደ ጨለማው አናመራም።

በጥቂት ክፉዎች ሰዎች እየተመራን ብዙ ተጓዝን። ብዙ ስንጠባበቅ ያገኘነው ትንሽ አላረካንም። በከንቱ ስንንከላወስ ያሳለፍነው ዘመን አብቅቷልና፤ አሁን ያለን ምርጫ፥ በእርግጠኝነት እና በቁርጠኝነት የሚታየንን የእውነት ጭላንጭል መከተል ነው።

አንድ ሰው አላዋቂ ስለሆነ በውስጡ እውነት የለውም አይባልም።  እውነት በስነ አመክንዮ መመራመርን ትጠይቃለች። በትንሽ እውቀትም ቢሆን፥ በብዙ ስነ አመክንዮ ምርምር እውነት ይገለጣል፤ ጥበብም ከዚያ ይፈልቃል፤ የመንፈስም ሥራ ከዚያ አልፎ ይሄዳል።

የሰው ቁመናው አካላዊ ሰውነቱ ብቻ አይደለም። አካላዊ ያልሆነውም እርሱ (ክፉው እንደ ክፋቱ፥ ደጉም እንደ ደግነቱ) ተሳትፎ ይኖረዋል፤ ሁሉም እንደ ጠባዩ። ዛሬ ዲያቢሎስን በሥጋ የሚያገለግሉ ክፉዎች፥ ሲሞቱም በነፍሳቸው እርሱን እንዲያገለግሉት ስለሚፈልግ፥ ነፍስና ሥጋቸውን ጭምድድ አድርጎ ይይዛል። ለዚህም ይሆናል አለም አቀፍ ጭካኔ እየተባባሰ የሄደው።

ስለ ጦርነት ሲነሳ፥ ታጣቂዎች፥ አማፂዎች፥ ሚሊሻዎች፥ ወይንም ወታደራዊ ቡድኖች፥ የአንድን አህጉራዊ ክልል ለማስከበር፥ ወይንም የአንድን ፖለቲካ አላማ

---

[62] *“የበግ ለምድ ለብሰው ወደ እናንተ ከሚመጡ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ።” ማቴ. 7፡15*

ለማሳካት፥ እርስ በርስ በመገዳደል (በመጋጨት) የሚፈጽሙት ሰዋዊ የትጥቅ ትግል ነው የሚታሰበን እንጂ፥ ሌሎችም ከእነርሱው ጋር የሚዋጉትን ስውር ኃይላት አናስባቸውም።

ኃያላን መንግሥታት ዶላር ያበድራሉ። ጥይቶች በገንዘብ ይገዛሉ፤ በጥይቶች ሰዎች ይገደላሉ፤ ቤቶች ይቃጠላሉ፤ ሰብል እንዳይሰበሰብ፥ የተሰበሰበውም ምርት በጥይት እንዲጋይ ሲደረግ፥ ከዚያ ቀጥሎ በረሃብ የሚያልቀውን የሰው ቁጥር ማን አሰበው?

ማንኛውም ጦርነት፥ በክፉ መንፈስ እና በደግ መንፈስ መካከል የሚደረግ፥ ለመጨረሻው ወሳኝ ጦርነት የሚያዘጋጅ መሆኑ ለሁሉም ሰው በግልጽ አይታወቅም። ሆኖም፥ አንድ ወሳኝ ጊዜ ላይ ሲደረስ፥ በሃሳብም ሆነ በተግባር ከሁለት አንዱ መርጦ መወገን ግዴታ ይሆናልና፤ ዛሬ ሁላችንም በያለንበት የጀመርነው ተሳትፎአችን ስለወደፊቱ የኢትዮጵያችን መጻኢ ወሳኝ እንደሚሆን አያጠራጥርም።

በጦርነት የሚሞቱት፥ ሥጋቸው ቢቀበርም፥ ባይቀበርም፥ ሬሳቸውን ጎርፍ ቢወስደው፥ ተቃጥሎ እሳት፥ ጢስ እና አመድ ቢሆንም፥ ሁሉም በሥጋዊነቱ ከመሬት እቅፍ አይወጣም። ታዲያ፥ ሰይጣን ዘለአለማዊ ነው ካልን፥ ሟች ከሆነ የሥጋ ሰው ጋር መቆራኘቱ ምን ይጠቅመዋል? እርሱ የሚፈልገው ወደ ገሃነም አብሮት የሚገባውን የሰውን ሕያው ነፍሱን ስለሆነ፥ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ያገኘውን ቅዱስ መንፈስ በእርሱ እርኩስ መንፈስ ለመተካት ሲል ይራወጣል፤ እኛም ክፉ ሥራን እንሠራለን። በዚህን ጊዜ፥ ባለ መጥፎ መንፈስ ወደ እርሱ ይሄድለታል፥ የተቀረውም ወደ ፈጣሪው ወደ እግዚአብሔር ይሄዳል።

***<u>የምድራዊነታችን ነገር በመንፈሳዊ እይታ</u>***

ቅዱሳን ኃይላት፥ ባናያቸውም ሰውን የሚወዱ ናቸው ብለን እናምናለን። ስለዚህ፥ በሕዝቦች መካከል ጦርነት ሲቀሰቀስ፥ ዝም ብለው እንደማያዩ፤ እነርሱም ከጦርነቱ እንደሚገቡበት እና ከእውነት ጎን ተሰልፈው እንደሚዋጉ፥ በአለም ላይ ከተቀሰቀሱ የሃይማኖት ጦርነቶች መገንዘብ ይቻላል። ለምሳሌ፡-

በ1096 እና 1291 መካከል የተቀደሱ ቦታዎችን ለመቆጣጠር ሲባል፥ “የመስቀል ጦርነት” የተባለው በክርስቲያኖች እና በሙስሊሞች መካከል ተካሂዷል።

ከዚያም በኋላ (1562-1598) በፈረንሳይ ፕሮቴስታንቶች (Huguenots) እና በሮማ ካቶሊኮች መካከል፥ ለ36 ዓመታት ያህል የሃይማኖት ጦርነቶች ተካሂደዋል።

በኢራቅ ሱኒዎች እና በኢራን ሺያቶች፤ በህንድ ሂንዱዎች እና በፓኪስታን ሙስሊሞችም፤ በፍልስጤም ሙስሊሞች እና በእስራኤል አይሁዶች፤ እንዲሁም በሌሎች የአረብ አገሮች መካከል ኢያሌ የሃይማኖት ጦርነቶች ተካሂደዋል።

በእነኚህ ጦርነቶች ውስጥ ቅዱሳን ኃይላት ከማን ጋር ወግነው እንደተዋጉ በግልጽ ላይታወቅ ይችላል። ሆኖም፥ *"ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም፤ ኃያልም በኃይሉ ብዛት አያመልጥም…መዝ. 32(33)፡17* እንዲል፥ በሥጋውያን መካከል ድል የሚገኘው እውነት በበዛበት እንጂ በሠራዊት ብዛት ወይንም በትጥቅ ብዛት አይደለም።

ለእውነት የቆሙ ጥቂት የእውነት ሰዎችን የእግዚአብሔር መንፈስ ይረዳቸዋል። ለምሳሌ፡- በአንድ ወቅት እስራኤላውያንን የአካባቢያቸው ሠራዊት በተደጋጋሚ ያጠቋቸው ስለነበር፥ ለህልውናቸው ሲሉ በቁርጠኝነት በመነሳት ከጠላቶቻቸው ጋር መጋጨት ግድ ሆኖባቸው ነበር። ጌዴዎን የተባለ የጀግኖች መሪ፥ ከብዙው ሠራዊቱ ጥቂቱን እና በውስጣቸው እውነት ያላቸውን፥ ሦስት መቶ ሠራዊት ብቻ ይዞ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ጠላቶቹን ለማቸነፍ በቅቷል።[63] እውነትን ይዞ የሚነሳ (በእግዚአብሔር የሚመካ) ድል እንጂ ሽንፈት አይገጥመውም።

አህመድ ግራኝ በ1528 ዓ.ም. የእስልምናን ሃይማኖት ለማስፋፋት፥ ከኢትዮጵያ ምሥራቅ ክፍል ተነስቶ፥ ሸዋን፥ ጎንደርን፥ ወሎን እና ከፊል ትግራይን በመያዝ ብዙ አብያተ ክርስትያናትን አውድሟል። በዚያን ጊዜ የነበረው ንጉሥ (ልብነ ድንግል) በጦርነቱ ሕይወታቸውን አጥተዋል።

በ1543 የአፄ ልብነ ድንግል ልጅ አጼ ገላውዴዎስ ዙፋኑን ከተረከቡ በኋላ፥ በጣና ሃይቅ አካባቢ ግራኝን ገደሉት፤ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጸንታ ቀረች፤ እንደገናም ማበብ ጀመረች።

በግልጽ ቢታዩም/ባይታዩም፥ አለም ከተፈጠረች ጀምሮ በሰዎች መካከል ሲደረጉ በነበሩ ጦርነቶች ውስጥ የክፉ መንፈስ እና የጥሩ መንፈስ ፍልሚያ እንደነበር ሁሉ፥ አሁንም በየአህጉራቱ መካከል እና በውስጣቸውም በሚካሄዱ ጦርነቶች ውስጥ ያለው ከዚህ የተለየ አይሆንም።

---

[63] *"በእጃቸውም ውኃ ወደ አፋቸው አድርገው የጠጡት ቁጥር ሦስት መቶ ሆነ፤ የቀሩት ሕዝብ ግን ውኃ ሲጠጡ በጉልበታቸው ተንበረከኩ። እግዚአብሔርም ጌዴዎንን "በእጃቸው ውኃ በጠጡት በሦስት መቶ ሰዎች አድናችኋለሁ…." አለው። መሳ.* 7፡6፥7

ያለፈውን ታሪካችንን ስናስበው፥ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፥ የኢትዮጵያ ነገሥታት በሃይማኖታቸው ያገኙትን መንፈሳዊ ህልውና ከሀገር ህልውና፥ የሀገርንም ህልውና ከመንፈሳዊ ህልውና ለያይተው አይመለከቱም ነበር።

የትግራዩ ንጉሥ አጼ ዮሐንስ አራተኛ ከሱዳን መሃዲዎች ጋር ጦርነት ገጥመው ሕይወታቸውን እስከመሰዋት የደረሱት፥ የሀገራቸውን ህልውና (ፍቅር) ከመንፈሳዊ ህልውናቸው (ህልውናችን) ለይተው ስላላዩት ነበር።

በአሁኑ ጊዜ ለሃይማኖቱ ብሎ ሕይወቱን የሚሰዋ የሀገር መሪ የማይታሰብ ነው። ሥልጣን የማቆያ ትርፍ የሚገኝበት ከሆነ ግን፥ ጦርነትም ቢቀሰቀስ የማይጠላ መንግሥት ነው ያለን።

በዮዲት ጉዲት ዘመን (ከ842 ዓ.ም. እስከ 882 ዓ.ም.) አያሌ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያናት ወድመዋል፤ ክርስቲያኖች እጅጉን ተሰቃይተዋል። ሆኖም፥ ከጥንትም በሮማ የነበሩ ክርስቲያናት ከመሬት ላይ ሕንጻ መሥሪያ ቦታ ቢከለከሉ፥ ካታኮምብ (ሰው ሰራሽ ዋሻ) እየሠሩ፤ በዚያ ይገለገሉ እንደነበር፤ በኢትዮጵያም ተመሳሳይ ችግር ቢያጋጥም፥ ውቅር ቤተ ክርስቲያናትን ከድንጋይ ውስጥ እየፈለፈሉ የሚገነቡ፥ መንፈሰ ብርቱ ክርስቲያኖች ባሉበት ሀገር፥ እነርሱን ሊያጠፋቸው የሚችል ምድራዊ ኃይል እንደማይኖር፥ ያ ክፉ ጊዜ አልፎ፥ በኢትዮጵያ ዙሪያ የተገነቡት፥ እና በብዛት እየተገነቡ ያሉት፥ ታላላቅ ቤተ ክርስቲያናት ምስክሮች ናቸው።

እግዚአብሔር እኛን ፈጥሮ እንዲሁ አልተወንም። እግዚአብሔርም የእርሱ የሆነውን እኛን ለመንግሥቱ ይፈልገናል። ስለዚህ፥ በእግዚአብሔር መንግሥት እና በሰይጣን መንግሥት መካከል ጦርነት ይኖራል።[64]

እግዚአብሔር በአምሳሉ የፈጠረውን የሰውን ልጅ ሰይጣን በእርሱ ልክ እንደገና ሊፈጥረው እቅድ አንዳለው በመካከላችን የሚመላለሱትን አንዳንድ ፈጽሞ የጠፉ ሰዎችን ሁናቴ መመልከት ይበቃል፤ እነኚህ በኢጋንንት አሽከላ (ወጥመድ) ተይዘው የሚያደርጉትን የማያቁ አሳዛኝ ፍጥረቶች ሁነዋልና። እርኩስ መንፈስ ለማንም የማይመለስ ስለሆነ፤ ከእያንዳንዳችን የማይጠፋውን ቢያንስ አንድ ድክመት እየተጠቀመ ኃጢአት ሊያሠራን ይሞክራል። ለሥጋም ለነፍስም የሚሆነውን መድኃኒት የምናገኘው ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ነው።

---

[64] *"መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆች እና ከሥልጣናት ጋር፥ ከዚህም ከጨለማ አለም ገዦች ጋር፥ በሰማያዊም ሥፍራ ካለ፥ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። " ኤፌ. 6*

የሰው ልጅ ሮቦት (robot) የሚባሉ ነፍስ አልባ ግዑዛን ፍጥረቶቹን (ማሺኖቹን) ተንቀሳቅሰው እንዲያገለግሉት እንደፈጠራቸው፤ ሰይጣን የሰጣቸውን ሥራ ከመሥራት ውጪ፥ የሰውን ልጅ (ልኩን መንፈሱን) ለይተው ማወቅ የማይችሉ ልክ እንደ ግዑዛን ማሺኖች የሆኑ አሉ በመካከላችን። ብዙ አይነት የሰው ሮቦቶች አሉ በአለማችን። ሃብታም የሰው ሮቦቶችም አሉ፤ ጭምልቅልቅ፥ ብክንክን በማለት፤ በማደንዘዢያ እጽ ራሳቸው እየሳቱ ለዛ የሌለው ኑሮ የሚኖሩ።

ይህ በዚህ እንዳለ፥ አንዳንድ ባለ ሃብቶች እና ኃያላን ሰዎች፥ አንዳንድ በሰው ልጅ አእምሮ አስጸያፊ የሚባሉትን ኢመንፈሳዊ ጉዳዮችን ልክ እንደ ሰብአዊ ዴሞክራሲያዊ መብቶች እያስመሰሉ በተባበሩት መንግሥታት መድረክ ለውይይት እና ለውሳኔ እንዲቀርቡ ይገፋፋሉ።

የሰውን ልጅ ለሳጥናኤል ለማስገዛት የተጀመረውን ፕሮጄክት በከፍተኛ ፍጥነት ለማንቀሳቀስ እና በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ፥ በቅድሚያ ሰው ክፉ እና ደጉን መለየት እንዳይችል የሚያደርጉ ስብከቶችን በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ያሰራጫሉ።

አለም አቀፍ ክርስቲያን እና ሌሎችም መንፈሳውያን ወገኖቻችን እና የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪዎች በየጊዜው በተባበሩት መንግሥታት ውስጥ፥ በምሥጢር እና በግላጭ እየተመከረ ስላለው ጠቅላይነት (globalization) እና ለወደፊት ስለሚያስከትለው አለም አቀፋዊ “አንድነት” ይወያያሉ።

ከቅርብ ጊዘ ወዲህ፥ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እና በኤጀንሲዎቹ ውስጥ አንዳንድ የአለም አቀፍ ጤና እና የጋራ የሆኑ ጉዳዮችን ለመቆጣጠር የሚያመቹ የጠቅላይነት ፖሊሲዎችን ለማውጣት እየተሰባሰቡ መመካከር ተጀምሯል። እነኚህ ፖሊሲዎች ረቀው ሲወጡ፥ ለወደፊት አለምን ለመቆጣጠር እንዲያመች፥ በሰዎች አእምሮ አንድ አይነት አለም አቀፋዊ አስተሳሰብ እንዲሰርጽ በማሰብም እንደሆነ፥ አንዳንድ ሁኔታዎች ያመላክታሉ።

የሀገር መሪዎችን “ዋነኞቻቸው” በሞተር እንደሚንቀሳቀሱ ሮቦቶች ስላደረጓቸው፥ ከእነርሱ ፈቃድ ውጪ ምንም ማድረግ አይቻላቸውም። ለእነርሱ አፈ ቀላጤዎች እየሆኑ እንዲያገለግሉ ለሚመረጧቸውም፥ ደጎስ ባለ ገንዘብ እየደለሉ ያቆዩአቸዋል።

ሰይጣን በምድር ላይ ለመንገሥ ካለው ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ፥ የሰውንም ጠባይ እንደርሱ ሰይጣናዊ ማድረግ አስፈልጎታል። ስለዚህ፥ የአለምን ሕዝብ የእርሱ ተከታይ (አገልጋይ) በመሆን፥ የእርሱን ፈቃድ እንዲፈጽምለት፥ አዲስ እና ረቂቅ በሆነ ምድራዊ ሥልጣኔ አእምሮውን ጠፍንጎ ይዞታል። እኛም ትኩረታችን በቀን ተቀን

ኑሮአችን ላይ ስለሚሆንብን፥ ስለወደፊቱ የሰው ልጅ "በገዛ ፈቃዱ ለሰይጣን እጅን መስጠት ጉዳይ" በቂ ጊዜ ሰጥተን አላሰብንበትም።

ለወደፊት የሰው አእምሮ ወደ አንድ ገንዘብ እና ወደ አንድ ወጥ እውቀት ቢሰባሰብ፥ ሰይጣን የሰውን ልጅ እንደ ልቡ ለመቆጣጠር ይቀለዋል። የአለም ሕዝብ የኑሮው ዝንባሌ በፍቅረ ነዋይነት ላይ የተመሠረተ ይሆናል፤ በሰዎች መካከል ፍቅር እና መተሳሰብ ይቀንሳል፤ አብሮ በመሆን ፋንታ፥ ግለኝነት እና ክፋቶች የኑሮ ዘይቤ ይሆናሉ።

ሰይጣን የሰውን ልጅ ከተፈጥሮአዊ ፍጥረቱ አጨናግፎ በራሱ ባህሪአዊ መልክ፥ ለራሱ እና እንደራሱ መልሶ ለመፍጠር ይረዳው ዘንድም፥ አለም አቀፋዊ ድርጅቶች እንዲተባበሩት ያደርጋል (አንዳንድ አገሮች ይቃወማሉ)።

የሰው ልጅ በራሱ ፈቃዳዊ ፍላጎት ጾታውን እንዲወስን፤ የወንዶች እና የሴቶች ልጆቻችንን ጾታ በመድኃኒት እና በቀዶ ጥገና መቀያየር እንደ አንድ የሰብአዊ መብት እንዲቆጠር፤ ሌዝቢያን እና ግብረ ሶዶማውያንም ማህበራዊ እና መንግሥታዊ ተጽእኖ እንዳያድርባቸው፤ ተመሳሳይ ጾታ ያላቸውም ተጋብተው እንዲኖሩ በሕጋዊ መንገድ እውቅና እንዲሰጣቸው ተደርጓል።[65]

የሕዝብ ቁጥር የሚቀንስበትን ማንኛውንም (ግልጽ እና ድብቅ መንገዶች) እንዲተገበር የሚያደርጉ እርምጃዎች በአንዳንድ አህጉራት የወሰዳሉ።

ልጆቻችን ለሰይጣናዊ ምልከታዎች አእምሮአቸውን እንዲከፍቱ የሚያደርጉ የትምህርት አይነቶች እንዲሰጡ፤ አለም አቀፋዊ የሥርዓተ - ፆታ ትምህርት እንዲዋቀር እና ልጆች ሁሉ እንዲማሩት እየተደረገ ነውና፤ ልጆቻችንን እንዳንቀማ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት እየተማሩ በሃይማኖት እንዲያድጉ ማድረግ ይገባል። የሃይማኖት ትምህርት እና ግብረገብነት በዘመናዊው ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ቢካተት፥ ሊመጣ ካለው ከወደፊቱ ጥፋት መዳኛ ሊሆን ይችላል።[66]

ታላላቅ አህጉራት በታናናሽ አህጉራት ውስጥ መንፈሳዊ እና ሞራላዊ እምነቶቻቸው፥ በትውፊታዊ አኗኗራቸውም ላይ ተጽእኖ ሲያደርጉ፤ ይህ አካሄድ

---

[65] በዚሁ ዓመት (2016) ውስጥ የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ በ36 የተባበሩት መንግሥታት አባል ሀገራት በሕጋዊ መንገድ እውቅና እያገኘ ተፈጻሚ ሆኗል።

[66] አጠቃላይ የፆታ ትምህርትን የሚደግፉ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኤጀንሲዎች (UNESCO, UNICEF, WHO, UNFP, WHO) አጠቃላይ የጾታ ትምህርት ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ለማድረግ መመሪያዎችን፣ ግብዓቶችን እና ድጋፍን ለአገሮች ይሰጣሉ።

ምናልባት ለወደፊት ምድሪቷን ወደ አንድ ምድራዊ ስርዓት እንድትመራ የሚያስገድድ ሊሆን እንደሚችል መጠርጠር ይገባል።

ያ የተፈለገው አለም አቀፋዊ ስርዓት ጥሩ ቢሆን ባልከፋ ነበር። ነገር ግን፥ በመንግሥታዊ መዋቅሮች አማካኝነት አንዳንድ ከሰው ልጅ ሞራላዊ ግንዛቤ ውጪ የሆኑ መጥፎ ሃሳቦች ሲሰራጩ፥ የሕዝቦችም ሃይማኖታዊ እና መንፈሳዊ አኗኗር ሲናጋ፤ ያ የተፈለገው ስርዓት የአለምን ሕዝብ ከፈጣሪው የሚያርቅ፥ የሰውንም ልጅ ለእርኩስ መንፈስ ተገዢ እንዲሆን የሚያደርግ ሲሆን፤ ይህንን እንዴት እንደ ጥሩ መቁጠር ይቻላል?

ሰይጣን የራሱን እውቀት ለሰው ልጅ ሁሉ በማጋራት በአንድ ሉላዊ እውቀት እንዲመራ፥ በቤቱ ቁጭ ሲል የሚያየው ቴሌቪዥን፥ የሚከፍተው ኮምፒተር፥ ከቤቱ ወጥቶ ሲሄድም ከእጁ የሚያስረው ሰአት፤ በኪሱም የሚይዘው ሞባይል፣ የሚወለዱትም ሕጻናት አይፓድን እንደ ጡጦ።

ሁሉም ጥሩ ቢመስልም፥ ጥሩ የሚመስል ሁሉ መጨረሻው ጥሩ እንዳይሆን አላወቅንም። ጥሩ ጥሩውን እያየን ከዚህ እንደደረስን፥ “ከዚህ በኋላስ ምን ይመጣ ይሆን? ወደፊት ሊፈጠር ያለው ምድራዊ ስርዓት መጥፎ ከሆነ፥ ያ መጥፎነት ምን ያህል ነው መጥፎ የሚሆነው? ሰይጣን የሰውን ልጅ ወደ መጥፎ እየመራ፥ ሰውም እየተከተለው ሲሄድ መጨረሻው ምን ይሆን? እግዚአብሔርስ እርሱ የፈጠረው ፍጥረቱ ጭልጥ ብሎ ሲጠፋ እያየ የሚታገሰው ምን እስኪፈጠር ድረስ ነው?” ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል።

በተጠቀሱት ቁሳዊ ዘመናዊ መገልገያዎች ተማርኮ ያልተወሰደ፤ አንድ በእድሜው ከ60 ዓመታት በላይ የኖረ ሰው፥ የሚጨመርልን እንዳለ፥ የሚቀነስብንም እንደሚኖር ያስተውላል። እንቡጥ ጽጌረዳ አብቦ ሲያዩት እና ሲያሸቱት ደስ እንደሚል፤ ትንሽ ቆይቶ መርገፉ እንደማይቀር፤ የኛም ነገር እንደዛ ሆኖ እንዳይቀር፥ በአሁኑ እና በመጪው ትውልድ ላይ ብዙ መሥራት ያለባቸው ጉዳዮች ይኖራሉ።

በግልጽ በሚታይ አለም ውስጥ ስላለን፥ የሚታየንን እናውቀዋለን። የሚያስጨንቀንን ድብቁን፥ የበለጠ እንዳይታይ  እኛው እየደበቅን፥ መድኃኒት ፍለጋ እንሄዳለን። በሁላችንም ውስጥ ያለውን ክፋት እየመራ መስመር የሚያስይዝ ቢኖር፥ ያንን ክፉ ኃይል ለይተን ካላወቅን፥ በሽታው አይድንም።

በኢትዮጵያችን በግልጽ ግፍ እየተፈጸመ እናያለን። ለሚፈጸመው ግፍ ሁሉ ምክንያቱ አንድ እና አንድ ብቻ እንደሆነ፤ እርሱም “ክፋት” መሆኑን እናውቃለን።

ይህንን "ክፋት" ማስወገድ ይቻል ነበር። ነገር ግን፥ እስከ ዛሬ ይህንን ክፋት ተባብረን ያለማስወገዳችን ምሥጢር ምን እንደሆነ እናስበው።[67]

ከሚታየው ከምድራዊ ከንውን እንኳን ተነስተን፥ ትንሽ ጠለቅ ወዳለ ምርምር ውስጥ ብንገባ፥ ያንኑ ከንውን ምድራዊ ባልሆነ መንገድ ለመግለጽ ብንሞክር፥ የሚገለጽልን ይኖራል። ስለዚህ፥ አሁንም ከምድራዊነታችን ባሻገር ስለ መንፈሳዊነታችን ነገር በጥልቀቱ እናስተውል። "አቤቱ አምላኬ ስለ መጥፎ ሃሳቦቼ ይቅር በለኝ" በማለት፥ ክፉና ደጉን ለመለየት የሚያስችል ጥበብ እንዲለግሰን አምላካችንን እንለምነው።

በክፉ መንፈስ አጋርነት የሚገኝ ድሎት ኃጢአትን ወደ መሥራት ይመራል። ለጊዜው ነው እንጂ ሥጋ አይጠቅምም። ምድራዊ ኑሮ ሲያስመርር አየን እንጂ፥ መንፈሳዊ ኑሮ ጸጸት ሲሆን አላየንም። ከምድራዊነታችን ባሻገር ሰማያዊ እና ዘለአለማዊ አለም ውስጥ የሚከተን፥ ቀድሞ ከእግዚአብሔር የመጣ፥ በኋላም ወደ እርሱው የሚመለሰው ጥሩው ሕያው መንፈሳችን ነው።

በአጠቃላይ ሲታይ፥ ማንኛውም በምድር ላይ የሚሠራ ሥራ ሁሉ፥ እስከሞት የሚያደርስ ቢሆንም፥ ሰብአዊነትን እስከ ተወሰነው ደረጃ ድረስ ለማድረስ ስለሆነ፥ ወደ መጨረሺያው ገደማ፥ በአንድ ሀገር የሕይወት ታሪክ ውስጥም እንዲሁ ነው የሚሆነው።

በኢትዮጵያችን ውስጥም ከአለማዊ ድርጊቶች ትይዩ መንፈሳዊ ድርጊቶች እየተካሄዱ ነው። በመንግሥታዊ አስተዳደር በኩል የተጨቆኑ ሕዝቦች ለፈጣሪ አቤቱታ ያቀርባሉ፤ ምላሹም በየጊዜው ይሰጣል። ይህንን የማያይ የሀገር መሪ፥ መንፈሳዊ አይኑ የታወረ፥ በምድራዊነቱ ብቻ የሚንቀሳቀስ፥ ለራሱም የሚበጀውን የማያውቅ ሞኝ ነው። ሞኝነቱን እንደ ብልጠት እየቆጠረ፥ ከውጪ ኃይላት ፍራንክ እየለቀመ፥ የእነርሱን አላማ የሚያሳካ፤ ይህ እንዲህ ያለውን የሀገር መሪ ምን ስም እንሰጠዋለን?

በየወቅቱ የሚከሰተውን በመንፈስ አርቅቆ በመመልከት፥ የእግዚአብሔር ክብር ይገለጣል። የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ "ማየት የሚችል" ይማራል፤ የተማረውም ያስተምራል። የእግዚአብሔርን ሥራ "ማየት የማይችል" ደግሞ አይማርም፤ ስለይማርም ያልተማረውን ያደናቁራል።

---

[67] *"እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤ ..." ሮሜ. 2፥28*

ኢትዮጵያ የመጀመሪያው የሰው ዘር ተፈጥሮ የተዘራባት፥[68] ጥንታዊ የመንፈሳዊ ሥልጣኔ ምንጭ ስለሆነች፤ የሰይጣን ትኩረት በተለይ በእርሷ ላይ ሆኗል። ይህም ካለ ምክንያት አይደለም። ከብሉይ ኪዳን እስከ አዲስ ኪዳን የተጠቀሰው የኢትዮጵያኖች መንፈሳዊ ቅንአት፥[69] በዘመናችንም የኢትዮጵያውያን ሃይማኖተኞች ቁጥር መብዛት እና መንፈሳዊ ጥንካሬአቸውም እጅጉን ሊያሳስበው ይችላል። የአለም አቀፋዊ ሂደቶች አለምን ወደ ክፋት ሲለውጡ፥ ኢትዮጵያ የጥፋት መሪ ብትሆን፥ ሌላውንም አለም (በተለይ አፍሪካን) ወደ ክፋት ለመምራት እንደሚቀለው ይገነዘባል። ስለዚህ፥ የኢትዮጵያችንን መንፈሳዊ ገጽታዋን ለማጥፋት እስካሁን ብዙ ተሞክሯል። ነገር ግን፥ የሙከራዎቹ ሁሉ ሂደት መጨረሻው ሽንፈት እንደሚሆንበት ከታሪክ እንረዳለን። ለምሳሌ፡-

ዘጠኝ ጳጳሳት በሃይማኖት ክርክር ጭንቅ ቢላቸው፥ ከአውሮፓ ምድር ወደ ኢትዮጵያ ገቡና ተረጋጉ፤ ከአውሮፓ ያላገኙትንም ሰላም ከዚህ አገኙ።[70]

የእስላም ሃይማኖት ከወደ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቢገባ፥ ግራኝ መሃመድ እስከተሸነፈበት ጊዜ ድረስ ለ900 ዓመታት አንጻራዊ ሰላም ነበር። ከዚያም በኋላ የሁለቱም ሃይማኖት ተከታዮች አብረው ተረጋግተው እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው፥ በሌሎች አለማት ያልታየ ሰላም እስካሁን ድረስ አልጠፋም።

በብዙ አህጉራት ውስጥ መንፈሳዊነት በምድራዊነት እየተለወጠ መምጣቱን ስናስተውል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ግን፥ ከጊዜ ወደ ጊዜ የምናስተውለው ተቃራኒውን ነው። በዚህም ምክንያት፥ ዲያቢሎስ አለምን እንደ እቅዱ አጠቃሎ ፍጹም ምድራዊ አድርጎ እንዳይገዛ ኢትዮጵያ ሳታስቸግረው አልቀረችም። ስለዚህ፥ በአንዳንድ ምድራውያን (ፖለቲከኞች እና መንፈሳዊ ነን ባይ አታላዮች) አማካኝነት፥ በኢትዮጵያችን ላይ ክንዱን አበርትቷል። ለምሳሌ፡-

በአንዳንድ የማህበራዊ ገጾች ላይ "የታላቁ ሉሲፈር ምዝገባ...አሁኑኑ ይቀላቀሉን፤..." እየተባለ፥ ይለጠፋል። ይህ እና የመሳሰሉ ሰይጣናዊ ድርጊቶች በተለይ

---

[68] ዘፍ. 2፡13

[69] መዝ. 68፡31፤ ኤር. 3፡ 23፤ አሞጽ 9፡7፤ የሐዋ. ሥራ 8፡ 27 - 39፤ ወ.ዘ.ተ.

[70] አባ ጎርጎርዮስ፥ 1978፤ **የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፥** ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

በኢትዮጵያችን ላይ እንዲፈጸሙ የሚያደፋፍር ኃይል ምድሪቱን በጠቅላላ ለዲያቢሎስ ተገዢ ለማድረግ ይቀለዋል። ይህንን የእርኩስ መንፈስ አላማ የሚያሳኩ ክፉዎችን “ተው” ለማይል መንግሥት ምን ስም እናውጣለት?

ዛሬ እና ወደፊት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረግ ምድራዊና መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ከወደፊቷ አለማችን መጻኢ ጋር ምን አይነት ቁርኝት ሊኖር እንደሚችል እያሰብን ብንቆይ፤ እስካሁን ያልተገለጹልን አያሌ ወሳኝ መንፈሳዊ ክስሰቶች የበለጠ ይገለጹልናል። ለምሳሌ፡-

የውጭ ጠላት ኢትዮጵያን ሊወር ሲመጣ፥ ዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያን ሕዝቦች በቀሰቀሱበት አዋጅ ውስጥ አንድ እውነት ስላለ ነበር ሁሉንም የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች በአንድነት ማስነሳት የቻሉት። ይኸውም፡- “ሀገሬን ኢትዮጵያን እወዳለሁ የሚል ኢትዮጵያዊ ሁሉ በአስቸኳይ ይነሳ፤ መስቀለ ሞቱንም ተመልክቶ ይከተለኝ፤ እግዚአብሔር የወሰነልንን የባሕር ወሰን አልፎ ሀገር የሚያጠፋ፥ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት መጥቷልና...” በሚል አዋጅ ውስጥ አንድ እውነት ነበር።

ይህ የነበረ እና እውነት ሆኖ የሚቆይ እውነት  ሕዝቡ እና ሀገሩ የእግዚአብሔር መሆናቸውን፤ መስቀለ ሞቱም ሕዝቡን ለማዳን መሆኑን ይገልጻል። በዚህም እውነት ምክንያት፥ ሕዝቡ፥ ሀገሩ፥ እና መስቀሉ በአንድ እንደተጣመሩ፤ ሕዝቦችም በመንፈሳዊ አንድነት ተሳሰሩ።

እኛ ኢትዮጵያኖች በመስቀለ ሞቱ ላይ የሙጥኝ ብለን፥ ሃይማኖታችንን እና መንፈሳዊነታችንን ከምድራዊ ሕይወታችን አስቀድመን መኖራችን ለሰይጣን ምቾትን አይሰጠውም። ስለዚህ በዚህ ሁኔታ ጦርነት ቢቀሰቀስ፥ ጦርነቱ በሥጋም በመንፈስም እንደሆነ፥  ከታሪካችን መማር ይቻላል።

ቀሳውስቱ ታቦቱን ተሸክመው ወደ አድዋ ዘመቱ፤ ቅዱስ ጊዮርጊስም፥ እንደ ልማዱ ፈረሱ ላይ ተቀምጦ፥ ኢትዮጵያውያን ተዋጊ አርበኞችን ሊራዳ መጣ። ተዋግቶ ማሸነፍ ልማዱ ነውና፥ ፋሺስት ኢጣልያን በዚያኑ እለት (የካቲት 23፥1988 ዓ.ም.) ሽንፈቱን ተከናንቦ በእፍረት እንዲመለስ ሆነ።

ኢትዮጵያውያን እስከ ዛሬ በታሪካቸው፥ በቅዱስ ጊዮርጊስ ታቦት ታጅበው፥ በወራሪ ጣልያን ላይ ሲዘምቱ፥ “ከሚታየው የሰው ኃይል ሌላ ተጨማሪ ኃይል ከሰማይ ተልኮልን (ቅዱስ ጊዮርጊስ አብሮን ተዋግቶ) አሸነፍን” አሉ እንጂ፥ እኛ ብቻችንን ተዋግተን አሸነፍን አላሉም (አይሉምም)። ይህም፥ ከሚታየው የማይታየው፥ ከሚታወቀው የማይታወቀው እጅጉን እንደሚልቅ የተረዱ ኢትዮጵያውያን፥ በአስተሳሰባቸው እና በእምነታቸው ከሥጋዊ ኑሮአቸው መንፈሳዊ ሕይወታቸውን እንደሚያስቀድሙ ያመላክታል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱ በሃማኖቱ ካለው ጽናት ጋር የተያያዘ መሆኑን ሰይጣን ስለሚያውቅ፥ “የሰማይ መላእክት ኢትዮጵያን ለማጥቃት ከአውሮፓ የሚዘምቱትን ነጫጭ ሰዎች ነው የሚያዩት እንጂ፥ ከውስጥ ያለሁትን እኔን አያገኙኝም” በማለት፥ ታክቲኩን ለውጦ በኢትዮጵያ ሕዝቦች (ከሊቅ እስከ ደቂቅ) አእምሮ ውስጥ እየተደበቀ ክፉ ሥራውን ቀጠለ እንጂ፥ ዝም ብሎ አልተቀመጠም።

በፖለቲካም፥ በሃይማኖትም እየገባ፥ እርስ በርስ አናክሶ፥ እርሱ ከበላይ ሆኖ ለመንገሥ ሲል የከፋት ወጥመዶችን ዘርግቶብናል። እርሱ የሚፈልገው ሥልጣን ስለሆነ፥ በቅድሚያ ተቀናቃኝ የሆኑትን ኃይላት ያጠፋል፤ ወንበሩን በኢትዮጵያችን ላይ ለማስቀመጥ፥ በቅድሚያ እርሱ በእጁ የያዛቸውን ሰዎች ለከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን እንዲበቁ ያደርጋል። እንዲሁም፥ የሃይማኖት አባቶችን (እስላም/ኦርቶዶክስ/ፕሮቴስታንት....) በጥቅማ ጥቅሞች ይይዛቸውና፤ እነርሱ እውነትን እንዳያዩ፥ የተቀረውም ሃይማኖተኛ ሕዝብ በሃይማኖት ግራ እንዲጋቡ ያደርጋል። ይህንን እና የመሳሰለውን ሴራ እየተጠቀመ ነው ሰውን ሁሉ ወደራሱ ካምፕ የሚስበው።

በቀደሙ ዘመናት ሁሉ፥ በኢትዮጵያኖች ዘንድ ከሥጋዊ አንድነታቸው ይልቅ ጎልቶ የሚታየው መንፈሳዊ አንድነታቸው ነበርና፤ ኢትዮጵያን ለመግዛት፥ የተጠናከረውን የመንፈስ አንድነታቸውን መሰባበር እንደሚያስፈልግ የተረዳው ሰይጣን ከአርባ ዓመታት በኋላ ይህንን የከፉ መንፈስ ሴራ (ልክ አሁን እንደሚደረገው አይነት መከፋፈል) ሲያውጠነጥን ቆይቶ፥ ተመልሶ መጣ።

መስከረም 1928 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ.) ከፋፍሎ ሊገዛ የተመለሰ ፋሺስት ጣሊያን ለጊዜው ሆነለት፤ በዚሁ ዓመት ውስጥ አዲስ አበባ ገብቶ ብዙ ሰው ፈጀ። ለጊዜው አሸናፊ ሆኛለሁ ብሎ ቢመጻደቅም፥ በሕዝቡ አንገዛም ባይነት፥ በአርበኞች ትግል፥ በንጉሡ በኃይለ ሥላሴ በሚመራ ጦር እና በእንግሊዞችም እርዳታ፥ ጣሊያን እንደገና ተሸንፎ፥ ሚያዚያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም. ውዷቷን ሀገራችንን ለቆ ሄዷል።

ስለዚህ፥ ታሪካዊ ምድራዊ ኩነቶችን ከመንፈሳዊ እሳቤዎቻችን ጋር እያገናዘብን ብናስተውላቸው፥ ጦርነቶች በተካሄዱባቸው የአለም አህጉራት ሁሉ፥ ጦርነቶቹ በሥጋም በመንፈስም ነበሩ ማለት እንደሚቻል፤ ይልቁንም፥ በኢትዮጵያችን የነበሩ ጦርነቶች ሁሉ፥ አሁንም ቢሆን በመካሄድ ላይ ያለው የውስጥ ጦርነት ምድራዊ ይዘቱ ከመንፈሳዊ ይዘቱ ተለይቶ እንደማይታይ እንገነዘባለን።

ኢትዮጵያ ሰማያዊ መሆኗን ማረጋገጪያ የሚሆኑ ገዳማት እና አድባራት፥ የቤተ ክርስቲያናት እና የምእመናን ብዛት፥ ሁሉም እንደ ሰማይ ከዋክብት ብርሃናቸውን በደማቁ እየፈነጠቁ ባሉበት ሰዓት፥ ጥቂት ግለሰቦች ተነስተው “እናንተ

ሁላችሁም ጥፉ፤ እኛ ብቻ ብርሃናችንን እናብራ” ብለው የሚሰብኩ፥ አመጣጣቸው ከየት እንደሆነ፥ ተልእኮአቸውም የማንን አላማ ለመስፈጸም እንደሆነ ይገባናል። እና፥ “የኢትዮጵያ ምድራዊ እና ሰማያዊ ልዕልና” ሲነካ፥ እኛ ሁሉን እያየን እንዳላየ ሆነን አንቀመጥም፤ ቅዱሳን መላእክትም ዝም ብለው አይመለከቱም።

ምድራዊና መንፈሳዊ ሂደቶች የራሳቸው ምክንያቶች ቢኖራቸውም፥ እኛ በእነዚህ ሂደቶች ውስጥ የወደፊቱን የማናውቅ በመሆናችን፥ በውዴታ እና በግዴታ የምንንቀሳቀስ ፍጡሮች ሆን እንጂ፥ “ሁሉም” አለ (ይታያል) ካጠገባችን።

ጥበብ ማለት የሚታየውን ብቻ ማወቅ አይደለም፤ የማይታየውንም ጭምር ነው እንጂ። በግልጽ ከሚታየው ጦርነት በስተጀርባ የማይታይ ጦርነት ስለሚኖር፥ ወደድንም ጠላንም፥ ያ ጦርነት ሁላችንንም በጦርነቱ እንድንሳተፍ ያደርገናል። በግልጽ ከሚታየው ጦርነት እጅጉን የባሰ ይሆናል የምንለው ያ ጦርነት፥ የአለምን ሕዝብ በጠቅላላ የሚያሳትፍም ሊሆን ይችላል። እኛም ድኅነትን እስክናገኝ ድረስ እጆቻችንን ወደ ሰማይ እንዘረጋለን።[71]

እያንዳንዱ ግለሰብ የፈጣሪውን እውነት የሚያገኘው፥ ከእውነት ጎን በመሰለፍ፥ ለእውነት ሲጋደል ነው። እውነቶች እና ውሸቶች ለየብቻቸው ሆነው፥ መሃል ሠፋሪዎችም ጎራ ለይተው፥ ምድሪቱን ለመውረስ እርስ በርስ ከመፎካከር አልፈው ጦርነት ውስጥ ገብተዋል።

አንዳንድ ሰዎች “የታል ጦርነቱ?” በማለት ይጠይቃሉ። በእርግጥ ለእነርሱ ላይታያቸው ይችላል እንጂ፥ ሰውን ከሰው በመሳሪያ ከሚያጨራርሰው ሌላ፥ ሰውን ከሰው በሃሳብ የሚለያይ - በሃሳብ የሚያቆስል፥ በሃሳብ የሚያደማ፥ በሃሳብ የሚያሳምም ጦርነት በአለም ሁሉ ላይ እየተካሄደ ነው ያለው።

አለም ታሟል፤ ኢትዮጵያም ታማለች። በሽተኛን በሽተኛ አያክመውም። ጻድቃን እውነቶቻቸውን አንግበው፥ በአለም ዳርቻ ሁሉ መንፈሳዊ ተጋድሎ ያደርጋሉ። አንድ ሀገር ራሱን አክሞ ቢድን፥ የተቀረውንም አለም አክሞ ማዳን ይችላል። ኢትዮጵያም፥ ብቻዋን ሳይሆን፥ ከሌሎች የአለም ጻድቃኖች ጋር ሆና፥ እንደ ሀገር ራሷን ማከም ብትችል፥ የተቀረውንም አለም ለማከም አቅም ይኖራታል። ነገር ግን፥ እንዲህ ያለው ነገር እጅጉን የሚያሳስበው ሰይጣን ኢትዮጵያ ራሷን እንዳታክም፥ ይልቁንም ሕመሟ (በሽታዋ) እጅጉን እንዲጸናባት እያደረገ ነው። ስለዚህ፥ ይህ ነገር

---

71 *“መልእክተኞች ከግብጽ ይምጡ፤ ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።” መዝ. 67፡31*

እኔንም ይመለከተኛል የሚል፥ ከምድራዊነታችን ባሻገር ለሚኖር ታላቅና ወሳኝ መንፈሳዊ ታጋድሎ እራሱን ያዘጋጅ።

የሼክስፒርን አባባል (*There is nothing either good or bad, but thinking makes it so.")* ተከትለን፥ ይህቺን አለም እንደ ትያትር ቤት በመቁጠር፡- "የገዛ አስተሳሰባችን በሚፈጥረው እየተመራን ነው እንጂ፥ ጥሩም ሆነ መጥፎ ነገር የለም" በሚል እሳቤ ከተመራን፥ እንደ ጥቁርና እንደ ነጭ ቁልጭ ብሎ የሚታየውን ከፋትና ደግነት መኖሩን እየካድን፤ "መጥፎውንም፥ ጥሩውንም፥ ጥሩ ነው ማለት መጥፎውን ይደመስሳል" ከሚሉ  በውሸት አለም ውስጥ ከሚኖሩ ጋር ተደምረን፤ መጥፎውንም እንደ ጥሩ እየቆጠርን፤ በምንሠራቸው መጥፎ ሥራችን ሁሉ የማንጸጸት ኃጢአተኞች እንሆናለን።[72]

የሰው ልጅ በችሎታውና በባህሬው ከቅዱሳን መላእክት ዝቅ ይላል ከሚል መነሻ ነጥብ ብንነሳ፥ እነርሱ ካሉበት ለመድረስ እና እውነትን ለማግኘት፥ ብዙ አንጻራዊ እውነቶችን አልፈን፤ የሚያጋጥሙንን አንጻራዊ የእውነት እርከኖችንም እየደረስንባቸው እና እያለፍናቸው መሆን አለበት።

በእርግጥ እግዚአብሔር የሰው መንፈሱን እንዲሁም ሥጋውን እንዳይጎዳ ያስብለታል። ለነፍሳችን ሲያስብልን፥ ለሥጋችንም ያስብልናል። ይኸንን ነው እኛ በየጊዜው የምናየው፤ የሀገራችንም ታሪክ የሚያትተው (ከመጽሐፍ ቅዱስም የተማርነው)።

በአንድ በኩል የአሁኑን የሕብረተሰቡን ጭንቀትና ውጥረት፤ ለወደፊት የታቀደለትንም ተስፋ አስቆራጭ ሰይጣናዊ ሴራ እያሰብን ብናዝንም፥ "የሰማይ መላእክት (ጻድቃን፥ ቅዱሳን፤ ሰማእታትም፤ ቅዱስ ጊዮርጊስም ከእነርሱው ጋር) በምድር እና በሰማይ እንደሚመላለሱ፤ እውነት ወዳለበትም እንደሚመጡ ስለምናውቅ እንጽናናለን።

በጊዜ ውስጥ ያለፍናቸውን ጊዜያቶች፥ አንዱን ከሌላው በማወዳደር፥ በውስጡ ፖለቲካዊ/ታሪካዊ ትንተናዎችን በማቅረብ ሳይሆን፥ "አጠቃላይ ሂደቱ ምን ይመስላል?" እያልን እራሳችንን ስንጠይቅ፥ ለጥያቄዎቻችንም አጥጋቢ መልሶችን ስናጣ፥ በእውነት "ይህች ድንቅ ኢትዮጵያችን በውስጧ ሰዎች ብቻ ናቸው ያሉባት? እኛ ሥጋውያን ብቻ ነን በውስጧ የምንመርመሰመሰው?" እያልን እና እራሳችንን በመደጋገም በመጠየቅ፥ የጠበቅነውን እና የምንችለውን ያህል፥ የተገለጡልንን እውነቶች ይዘን እንጓዛለን።

---

[72] "የማይገለጥ የተሸፈነ፣ የማይታወቅ የተሰወረ ምንም የለም።" ሉቃ. 12፡2

## የስውራን ኃይላት ተጽእኖ በኢትዮጵያችን ላይ

በአለም ሕዝቦች ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያለው፥ ከሰው ውጪ መንፈስ መኖሩን እና ሥራውን በዝርዝር ለመናገር አቅም ያላቸው ጥቂቶች ቢሆኑም፥ በምድራችን ላይ ተሳታፊዎቹ፥ ሃሳብ አመንጪዎቹና አስፈጻሚዎቹ ምንጊዜም ሰዎች ብቻ አለመሆናቸው ከብዙዎቻችን የተሰወረ ሃቅ አይደለም።

የሰው ልጅ የሕይወት ፍልስፍናውን የሚያዛምደው ለራሱ ምድራዊና ሰማያዊ ሕይወቱ ነው። ሰይጣን ግን፥ ሰማያዊ ሕይወቱን ያጣ በመሆኑ፥ ለምድራዊ ሕይወቱ አጋር ይፈልጋል። ስለዚህ ጥሩ አስተሳሰብ ባላቸው ጥሩዎች ውስጥም ቢሆን፥ የእርሱን አላማ የሚያሳካ ባይተዋር ምልከታ ይከትባቸዋል። እነርሱ ግን፥ ጥሩ ያሰቡ እየመሰላቸው በሠሩት ሁሉ ሲያዝኑና ሲጸጸቱ፥ "ማን ምን መከሮኝ ነው?" ብለው አያስቡም።

ጥሩ ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ሲጓዙ የእግዚአብሔር መላእክት፥ በሥጋ የሞቱ የጻድቃን መንፈሶችም ደስ አይላቸውም። ስለዚህ ለጥሩ ሰዎች ፈቃዳዊ ፍላጎት ምክርን ለመለገስ ሲሉ በምልክት (በሕልምም ቢሆን) ይመክሯቸዋል። አንዳንዶቹ ወደ ጥፋት እንዳይገቡ ውስጣዊው የጥሩነታቸው ኃይል ይመለሳቸዋል፤ ሌሎችም፥ በጥፋት ጎዳና ይቀጥላሉ እንጂ፥ አይመለሱም።

የታሪክ ተንታኞች እና ፖለቲከኞች የኢትዮጵያችን ስቃዩአ በዝቶባታል (ቆይቶም ተራዝሞባታል) ይላሉ። ነገር ግን፥ ለማንም ሰው ገሃድ ከሆኑ ፖለቲካዊ ሃተታዎች ባሻገር፥ ብዙውን ጊዜ መንግሥታት እና ደጋፊዎቻቸው፥ ወደውም ሆነ ሳይወዱ፥ የሰይጣንን አላማ በማሳካት፥ ከክፉ መንፈስ ጋር እንደሚያብሩ አልተመለከቱም።

በእርግጥ፥ ምድራችን የአንድ "ድርጅት አላማ" ማስፈጸሚያ ትሆን ዘንድ፥ በጥብቅ የፈለጋት የክፉው መንፈስ ኃይል በውስጣችን ገብቶ እንደሚያተራምሰን፤ ይህንን ጉዳይ በዝምታ እንዳናልፈው ስንል ብቻ ወዳልተለመደ ሃተታ ውስጥ እንገባለን እንጂ፤ የተቀረውማ (ምድራዊ ፖለቲካው)፥ በሌሎች በብዙ መጻሕፍት ተጽፈዋል፤ በልዩ ልዩ የሕዝብ መገናኛ መድረኮችና ሚዲያዎችም ተገልጸዋል። ጋዜጠኞችም በሚቻላቸው መጠን የምድራዊ ክንውኖችን ሂደት አሳውቀውናል።

አንድ የሕዝብ ቡድን ወይንም የሀገር መሪ፥ ከእግዚአብሔር ወገን ካልሆነ፤ ከዲያቢሎስ ወገን ሊሆን እንደሚችል፥ ተቃራኒውን በማረጋገጥ (Argumentum e contrario) ማገናዘብ ይቻላል፡-

ከእውነተኛ ሰው የምትመነጭ እውነት ምንጊዜም አንድ ናት። የእውቀት አይነቱ ብዙ ቢሆንም፤ የእውነት ግን፥ አይነቱ አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም እውነት ነው።

እውነትን ለማግኘት የምንሄድበትም የሃሳብ መንገድ፥ ወይንም ስነ አመክንዮ (logic) አንድ አይነት ነው የሚሆን። ስለዚህ፥ አንዱ ሰው በአንድ ጊዜ ጥሩ መስሎ መጥፎ፥ ደግ መስሎ ክፉ፥ ታማኝ መስሎ አታላይ፥ እውነተኛ መስሎ ሃሰተኛ፥ ርህሩህ መስሎ ጨካኝ፤ በአጠቃላይ ጻዲቅ መስሎ ኃጢአተኛ (ነፍሰ ገዳይ) መሆን የሚቻለው አመጣጡ ከእግዚአብሔር ሊሆን አይችልም። ታዲያ እንዲህ ያለ ሰው አመጣጡ ከእግዚአብሔር ካልሆነ፥ በተቃርኖ (ተቃራኒውን በማረጋገጥ) ከማን እንደሆነ ይረጋገጣል።

"ጥሩ" የሚባል ሥራ የሚሠሩትን ደጋግ ሰዎች እንደ ክፉዎች የሚቆጥራቸው፥ ከእስር ቤትም የሚወረውራቸው፤ "ክፉ" ሥራ የሚባለውንም እየሠራ፥ በክፉ ሥራዎቹ ደስ የሚሰኝ መንግሥት፥ አመጣጡ ከሰይጣን መሆን አለበት እንጂ፥ ከእግዚአብሔር ሊሆን አይችልም።

ፍጹም እውነት ወደሚገኝበት ወደ ሰማያዊ አለም ይመሩናል ባልናቸው የሃይማኖት አባቶች መካከልም፥ አንዳንዶቹ በምድራዊ ጥቅማ ጥቅሞች፥ በክብር እና በሥልጣን ስለተጠመዱ፥ እነርሱ እውነትን ሲያዛቡ፥ ተከታዮቻቸውም ግራ ይጋባሉ። በዚህን ጊዜ፥ ክፉ መንግሥት በሃይማኖት አባቶች መካከልም ከፋፍሎ መግዛትን ይለማመዳል።

ሁሉም የሃይማኖት አባቶች ስለ ምድራዊ አገዛዝ አያውቁም አይባልም። ትምህርታቸው ሰማያዊ ቢሆንም፥ በፖለቲካውም የበሰሉ አባቶች አሉን። አንዳንድ አባቶች በየቀኑ የሚያዩት እና የሚሰሙት የሕዝባቸው ስቃይ እና ሰቆቃ እነርሱንም ይሳዝናቸዋል፤ ያስለቅሳቸዋልም። እነርሱ በመንፈሳዊ አይናቸው ሲያዩ ቁልጭ ብሎ የሚታያቸውን ግን፥ እኛ ሁላችንም ላናይ እንችላለን።

እነርሱ የእርኩሳን መናፍስትን አሠራር በጥሞና የማስተዋል ብቃት፤ ከክፉው መንግሥት ጋርም በማነጻጸር፥ የሁለቱን ዝምድና እና ልዩነት በበለጠ እንዲያውቁት የሚያስችል ትምህርት ይኖራቸዋል። የሁለቱ (የመንግሥት እና የሰይጣን) አሠራር አንድ ሆኖ የታያቸው አባቶች ሲታገሉ (በግላጭ እየተናገሩ፥ እየገሰጹ፥ ከልጆቻቸው ጋር ሰላማዊ ሰልፍ እየወጡም ቢሆን፤ ወይንም በድብቅ በጸሎት እና በስውር ትግል ሲታገሉ) ከአምላካቸው መንፈስ ጋር ሆነው ነው እንጂ፥ ብቻቸውን አይደለም። ከጥንቱም መስቀላቸው አንድም በበጎ የመጣውን ሊባርኩበት፥ አንድም በክፉት የተጠጋቸውን ሊጓጉጡበት፥ ነውና፤ እርኩሳኑ ልጆቻቸውን ሊወጉ እየተንደረደሩ ሲመጡ፥ በመስቀላቸው ይከላከላሉ እንጂ ዝም ብለው አያዩም።

ለእነኚህ አባቶች (ለእኛም ቢሆን) እውነት የሚገለጥላቸው፥ ስለተማሩ፥ ስላወቁ እና ስለተመራመሩ ብቻ አይደለም፤ በውስጣቸው ፍቅር እና ሰላም ስላለም ጭምር ነው እንጂ። እንዲህ የሚል የእንግሊዝኛ ጥቅስ አለ፦

"The manifestation of truth is a mystry of Love, just as conversly the content of love is a mystry of truth።"

ትርጓሜውም፦ "የፍቅር ይዘት የእውነት ምስጢር እንደሆነ ሁሉ፥ የእውነት መገለጫም የፍቅር ምስጢር ነው።"

እውነት እና ፍቅር አመጣጣቸው አንድ ስለሆነ፥ እነርሱ ይዛመዳሉ፤ እርስ በርሳቸውም ይደጋገፋሉ። የሀገሩን ሕዝብ የሚወድ፥ በራሱ ላይ ስቃይ ባይደርስበትም፥ በውስጡ ፍቅር ስላለው፥ የሕዝቡ ስቃይ ይሰማዋል፤ በዚያውም እውነት ይገለጥለታል። ብዙ የሚያውቁ፥ በውስጣቸው ግን ፍቅር የሌላቸው እውነት አይገለጥላቸውም።[73]

አንዳንድ በውስጣቸው ፍቅር ሳያጡ፥ ዝምታን የሚያበዙ አባቶች፥ አንድም በምድራዊው ፖለቲካ ውስጥ በመግባት መስመር ማስያዝ የኛ ሥራ አይደለም ስለሚሉ፤ ወይንም ጊዜያቸውን ሁሉ በጸሎት፥ በቅዳሴ እና እኛን በማስተማር ስለሚያጠፉትና የጊዜውን ሁኔታ ለመረዳት በቂ ጊዜ ስለማይኖራቸው ይሆናል።

ሌሎች አንዳንዶች ግን፥ በመንፈሳዊ ምግባራቸው ስንወዳቸው፥ በአላዋቂ የፖለቲካ ተቋማቸው ሲዘባርቁ፤ ወይንም በገንዘብ እየተደለሉ፥ ወይንም በፍርኃት፥ ያልሆኑትን እየሆኑ፥ የዋሁን ሕዝብ ወደ ተሳሳተ ምድራዊ ፖለቲካ ሲመሩት ሰምተናል፤ አይተናልም።[74]

---

[73] *"በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሽዋሽዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ። ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ፥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፥ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ፥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም።" 1ኛ ቆሮ. 13፡ 1- 3*

[74] *"ብዙ ጊዜ ተዘልፎ አንገቱን ያደነደነ፥ ድንገት ይሰበራል፤ ፈውስም የለውም፤ ጻድቃን በበዙ ጊዜ ሕዝብ ደስ ይለዋል። ኃጥእን በሠለጠኑ ጊዜ ግን፥ ሕዝብ ያለቅሳል።" ምሳ. 29፡ 1፥2*

እንደ ዮሐንስ መጥምቅ ያለ፥ ለገንዘብ የማይገዛ፥ ነገሥታትን የሚገስጽ ደፋር ባህታዊ ማነው? እንደ አባታችን እንደ ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ያለ ደፋር አባትስ ከወዴት ይገኛል?[75]

በእምነታቸው የምንመስላቸውን ስንመርጥ በጥንቃቄ መሆን እንዳለበት ጊዜ አሳውቆናል።[76]

ጥቂት የማይባሉ ምሁራን፥ ጥልቅ ከሆነው የታሪክ እና የፖለቲካ ትንታኔዎቻቸው ባሻገር፥ አውርተው፥ አውርተው፥ ጽፈው ጽፈው፥ በሥራቸው መርካት ሲያቅታቸው፡- "ግን የሰው ልጅ እንዴት በራሱ ብቻ፥ ካለ ምንም የውጪ ተጽእኖ፥ ያን ያህል ክፉ ሊሆን ይችላል?" ብለው ይጠይቃሉ። የደረሰብን ክፉው ምን ያህል የከፋ እንደሆነ በጥልቀቱ ሲረዱ፥ የክፋቶች ሁሉ ምንጭ ስለሆነው ስለ ዲያቢሎስ አሠራር እና ስለ መንግሥታትም የሥራ ፍሬ[77] - የሁለቱን ዝምድና እና ልዩነት ማወቅ ይፈልጋሉ።

ክፉ መንግሥት በጣም ሲከፋ፥ መንግሥቱን ለሰይጣን አስረክቦ ይጠፋል። እንዲህ ያለውን ምድራዊ ሂደት በአይነ ልቦና የሚመለከቱ የወደፊቱን ሲተነብዩ፥ "ለወደፊት ሰይጣን አለምን በሙሉ ይቆጣጠራል። እርሱ የአለም ገዢ ሆኖ ከቆየ በኋላ ነው የሰማይ መንግሥት ወደ ምድራችን የሚመጣውና ሰላም በምድራችን የሚሰፍነው" ይላሉ።

በአለማችን ዙሪያ (በኢትዮጵያም) ምድራዊ ሂደቶችን ስንመለከት፥ በተለይ ይህ ኢትዮጵያን የሚያስተዳድረው መንግሥት እየተጣደፈ ያለው ከእርኩሳን መናፍስት ጋር አብሮ ለመግዛት፥ ወይንም በጊዜአዊነት የጨበጠውን መንግሥቱን ለሰይጣን አስረክቦ ለመጥፋት ይመስላል።

---

75 በገድለ ተክለ ሃይማኖት እንደተገለጸው፥ እርሳቸው የቅዱስ መንፈስ ኃይል ስለተሰጣቸው፥ ከተራ ሰው በላይ ኃይል ነበራቸው። እርሳቸውን የሚገዳደር እርኩስ መንፈስ ቢያጋጥማቸውም፥ ቅዱስ ሚካኤል እንደ ታማኝ ጓደኛ እየመጣ ይረዳቸው ነበር።

76 *"የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሯችሁን፥ ዋኖቻችሁን አስቡ፤ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ፥ በእምነታቸው ምሰሏቸው።" ዕብ. 13፡7*

77 *"...ከፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ።" ማቴ. 7፡20*

*".....መልካም ፍሬ የሚያፈራ ክፉ ዛፍ የለም።" ሉቃ.6፡43"*

*"ዛፍ ሁሉ ከፍሬው ይታወቃል። ከእሾህ በለስን አይለቅሙም፤........" ሉቃ.6፡44*

አዎ! የአለም አህጉራት "ሁሉ" በታሪካቸው ውስጥ ሰይጣናዊ ሰዎች እና ሰዋዊ ሰይጣኖች፥ ሰላማዊውን ሰው ሲያናውጡት እና የመኖርን ለዛ ሲያሳጡት፥ ይህ ያየነውና የምናውቀው፥ የማይታበል ሃቅ ነው። አለመታደል ሆነና፥ ከንጉሡ ከኃይለ ሥላሴ ቀጥሎ ኢትዮጵያችንን ያጋጠሟት መንግሥታት፥ የጠቀስናቸው ሰይጣናዊ ሰዎች፥ እና ሰዋዊ ሰይጣኖች ሁነው ተገኝተዋል። የማንኛው መንግሥት የትኛውን እንደሆነ፥ ወይንም ወደየትኛው እንደሚያደላ አእምሮ ያለው ሁሉ አስቦ ያገኘዋል።

## ትንበያ እኩይ ተግባር ማስፈጸሚያ ሲሆን

እርኩስ መንፈስ ምንጊዜም ቢሆን የተንኮል ሥራውን አይተውም። ስለዚህ፥ ሰይጣንም፥ እርሱ የአለሙ ገዢ[78] ስለሆነ፥ ለራሱ ሰዎች አስቀድሞ ለማድረግ የሚያስበውን ይነግራቸዋል። የሀገር መሪዎች ትንቢት እንዲነገርላቸው የሚፈልጉት ሌሎችን ሰጥ ለጥ አድርገው ለመግዛት እንዲመቻቸው ነው። ለአንዳንድ የተመረጡ አህጉራትም፥ በተለይ ራሳቸውን በጣም የሚወዱ ሰዎች ተመርጠው ይዘጋጃሉ። ከልጅነት እስከ እውቀት ኮትኩቶ የሚያሳድጋቸውንም፥ እርሱ የሚፈልገውን ሁሉ እንደሚፈጽሙለት ያሰናዳቸዋል፤ አለዚያም እርሱ ራሱ በእነርሱ ውስጥ ገብቶ ያሻውን ያደርጋል። ጠንቋዮች ይዘጋጃሉ፤ ሰላዮችም እንዲሁ።

እርሱ ለወደፊት ማድረግ የሚፈልገውን ስለሚያውቅ እና በችሎታውም ስለሚተማመን፥ "ለወደፊት ይህ ይሆናል፤ ይህም ይፈጸማል..." እያለ የሚነግራቸው ምድራዊ ጠቢባን (ጠንቋዮች) ይኖራሉ። በተለይም አንዳንድ እርሱ አጥብቆ የሚፈልጋቸውን ሰዎች ከልጅነት ጀምሮ ያሰለጥናቸዋል። ለምሳሌ፡-

በእነ እስታንሊንግ ጊዜ፥ የፖላንድ ተወላጅ የሆነ፥ አንድ ዉልፍ ጋንግ ሜሲንግ የተባለ፥ በጣም የታወቀ ጠንቋይ ነበር። ይህንን ጠንቋይ ቤተሰቦቹ ገና ከልጅነቱ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ዲያቆን እንዲሆንላቸው ነበር የሚፈልጉት። እርሱ ግን የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት አልፈለገም። ሰይጣንም ይህንን ብልጣ ብልጥ እና ብልህ ልጅ ለራሱ ሊጠቀምበት ስለፈለገ፥ ከቤተሰቦቹ ኮብልሎ ወደሌላ ሀገር እንዲሄድ መከረው።

ወጣቱም ምንም ገንዘብ ሳይኖረው፥ መሳፈሪያ ቲኬትም ሳይቆርጥ ከአውቶብሱ ተሳፈረ። ረዳት ሹፌሩ እያንዳንዱን ተሳፋሪ የያዙትን ቲኬት ሲጠይቅ፥ ወጣቱ የተሳፋሪዎቹን እግር ከለላ በማድረግ፥ ከአንድ ሰው መቀመጫ፥ ከወንበሩ

---

[78] *"....የዚህ አለም ገዢ ይመጣልና፤......." ዮሐ.14፡30*

ሥር ተደበቀ። ዳሩ ግን ረዳት ሹፌሩ አይቶት ኖሮ፥ ከተደበቀበት ጎትቶ አወጣው። ቲኬቱን ካላመጣ እንደሚያስወርደው በቁጣ እና በማስፈራራት አስጠነቀቀው። ወጣቱም የሆነ ብጣሽ ወረቀት ከኪሱ አውጥቶ ሰጠው። ወዲያውም ረዳት ሹፌሩ፥ “ታዲያ ይህ ቲኬት እያለህ ለምንድነው የምትደበቀው? በል ወንበር ያዝና ተቀመጥ” አለው በቁጣ። ወጣቱም እንደማንኛውም ተሳፋሪ ወንበር ይዞ ተቀመጠ፤ ከሚፈልገውም ሥፍራ ደረሰ፤ ከወላጆቹም ተሠውሮ የሚፈልገውን ሁሉ አደረገ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዉልፍ ጋንግ ሜሲንግ እና ሰይጣን አብረው መሥራት ጀመሩ። ብጣሹን ወረቀት ከወጣቱ ተቀብሎ እውነተኛ ቲኬት ለረዳት ሹፌሩ ያቀበለው ሰይጣን ራሱ በሥውር እጁ ይሆናል። ወጣቱ ግን ይህንን እንደራሱ ሰውን የማሳመን ችሎታ ስለቆጠረው፥ በዚያው እንዲሰለጥንበት ተገፋፋ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፥ የሰዎችን አእምሮ መቆጣጠርን እየተለማመደው መጣ (ሰይጣን በእርሱ ውስጥ የፈለገውን ሠራ)።

እስታንሊን እና ጄኔራል ቤሪያ የተባለው የምስጢር ፖሊሶች አለቃ ይህንን ዉልፍ ጋንግ ሜሲንግ የተባለውን ጠንቋይ ችሎታ ስላመኑበት፤ ካጠገባቸው እንዳይለይ አደረጉት። እርሱም ከፉ ከፉውን እየመከራቸው፤ እነርሱም እርሱ የሚለውንም ሁሉ በጥሞና እየሰሙ ብዙ ሰው ገደሉ። ያሳዝናል! ያ ደም ቀለቡ የሆነ ሰይጣን፥ እርሱ ባሰለጠናቸው ሰዎች አማካኝነት በብዙ ሚሊዎን የሚቆጠሩ ሕዝቦች አለቁ (ሰይጣን የፈለጋቸው ሥራዎች ሁሉ ባግባቡ ተፈጸሙለት)።

እንዳው ልዩነቱ ያልታወቀለት፥ በመምሰል እና በማስመሰል ‘ሚኖርበት፥ የሰላምና የጦርነት፥ የፍቅር እና የጥላቻ፥ የደስታና የሃዘን፥ የቅዠት እና የህልም ቅልቅል፥ በአንድ አለም፥ ሁለት አለም። ይህንን ለሁላችንም አንድ አይነት ያልሆነ አለም እንዴት እናጥናው? ብዙ አጥንተን ቡዙ ብናውቅ፥ የማይገባን ከሚገባን እንደሚልቅ ሲገባን፥ በማወቅና ባለማወቅ መካከል ልዩነቱ ይጠፋናል።

በሀገራችንም ምንጊዜም ቢሆን፥ እርኩስ መንፈስ የተንኮል ሥራውን አይተውም። ስለዚህ፥ ሰይጣንም ለራሱ ሰዎች አስቀድሞ ለማድረግ የሚያስበውን ይነግራቸዋል። ከልጅነት እስከ እውቀት ኮትኩቶ የሚያሳድጋቸው ሰዎች እርሱ የሚፈልገውን ሁሉ እንደሚፈጽሙለት፤ አለዚያም እርሱ ራሱ በእነርሱ ውስጥ ገብቶ ያሻውን ማድረግ እንደሚችል ስለሚያውቅ፥ “ለወደፊት ይህ ይሆናል፤ ይህም ይፈጸማል...” እያለ የሚነግራቸው ሰዎች ይኖራሉ። እነርሱም ትንቢት ተናጋሪዎች ይባላሉ።

ሰይጣን የእርሱን ሥራ ያከናውኑለት ዘንድ የሚመለምላቸው ሰዎች በሌሎች ሰዎች ዘንድ “ጥሩ መስለው ከሚታዩ” መካከል ነው። ለምሳሌ፥ በውስጠ ጠባዩ እጅግ

መጥፎ ሆኖ፥ መጥፎነቱን የመደበቅ ብቃት ያለውን (የተለሰነ መቃብር) "ይህ ሰው ጥሩ ለውጥ ያመጣል" ተብሎ ቢተነበይለት፥ ብዙ ሰው ሊያምነው ይችላል። በሰዎች ዘንድ በመጥፎነቱ የሚታወቅን ሰው ግን፥ "ይህ ሰው ጥሩ ለውጥ ያመጣል" ተብሎ ቢተነበይለት፥ ተቀባይነት አይኖረውም።

ሼክ ሁሴን ጂብሪል ከጻፉት የግጥም መጽሐፍ ውስጥም "ኢትዮጵያን አንድ የሚያደርግ ሰው ከዚህ አካባቢ ይወጣል" ተብሎ የተነገረለትን ሰው "ያ ሰው እገሌ ነው፤ አይ፥ እሱ አይደለም፤ ይኸኛው ነው" በማለት፥ ሁሉም እንደየስሜቱ ይመራበታል። ይህ ትንቢት መሳይ ነገር ለምን ተነገረ? ከማን የመጣ ትንቢት ነው? አላማውስ ምንድነው?" ብሎ መጠየቅ ይገባል፤ ይህንን እና የመሳሰሉ ትንቢት መሳይ ነገሮችም ሕበረተሰቡን ወደተሳሳተ ጎዳና የሚከቱት ናቸው።

የሼክ ሁሴን መጽሐፍ በተለያዩ መንገዶች ተተርጉሟል። በ2011 ዓ.ም. ለአስራ ሁለተኛ ጊዜ ታትሟል።[79] በዚህ በሼክ ሁሴን መጽሐፍ ውስጥ፡-

"አይነቀንቁትም ሴራ ቢገምዱ፥ ከሰማይ አውርዶ፥ ወንበሩን የሰጠው፥ አላህ ነው ዘመዱ።"[80] የሚል ስንኝ ተጠቅሷል። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሸፍጥ የሠራ ቢኖር፥ "ሰይጣን ነው ዘመዱ" የሚያሰኘውን ሥራ የሠራውን ሰው ታሪክ መዝግቦታል። ስለዚህ፥ "ያ ሰው እገሌ ነው፤ አይ፥ እሱ አይደለም፤ ይኸኛው ነው" እያሉ ሰዎች የተከራከሩበት ማን እንደሆነ - ብዙዎች የሚስማሙበት አሁን ተለይቷል። ይልቁንስ፥ ሼክ ሁሴን ጂብሪል ታመው ሊሞቱ ሲሉ፥ እንዲያ በበሽታ እንዲሰቃዩ፥ ያደረጋቸው አንድ የርሳቸው ጣውንት እንደሆነ፥ ከእርሳቸው ግጥም ውስጥ ተከትቧል። ከጥቅሳው ሼክ ጋር ጠባቸው ይፋ ከሆነ ጀምሮ፥ በሽታቸው ጠናባቸውና፣ የሚከተለውን ግጥም ገጠሙ ይባላል።

"በጎጃም፣ በትግሬ፣ በሸዋ፣ በጎንደር ሳገሳ ሳገሳ፥

ስብርብር አረገኝ የጥቅሳ አንበሳ።"[81]

ታዲያ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረበት የጥቅሳው ሼክ ወይንስ ሼክ ሁሴን ጂብሪል? እንዲህ ልዩ ችሎታ የተሰጣቸው ሰዎች፥ ችሎታቸው በሥራ ሲተረጎም ምን እንደሚያስከትልም መመርመር ያስፈልጋል።

---

79 ከቦጋለ ተፈሪ በዙ።

80 https://konjoethiopia.com/

81 ttps://zelalemkibret.files.wordpress.com/2011/03/gelaye4.pdf

የጥንቆላውና የትንቢቱ ጋጋታ ወደጥሩው የሚመራ ቢሆን ባልከፋ ነበር። ግን፥ በሰዎች ስነ አእምሮ ውስጥ ለተወሰነ ቡድን ተስማሚ የፖለቲካ እሳቤ እንዲሰርጽ የሚፈለግ መሆኑን በሚያስከትለው ውጤት ማገናዘብ ያስፈልጋል።

በኢትዮጵያችን ውስጥ ሰላሙን እና ብልጽግናውን ከመጪው 2014 ዓ.ም. ጀምሮ የምናገኘው ነው ሲባል፥ ሳይሆን ሲቀር፤ እንደገናም፥ ሰላሙን እና ብልጽግናውን ከመጪው ከ2015 ዓ.ም. ጀምሮ የምናገኘው ነው ሲባል፥ ሳይሆን ሲቀር፤ በ2016 የደረስንበት ዓመት ካለፉት ዓመታት ሁሉ የባሰ እጅግ ከፉውን ያየንበት ዓመት ሆነ።[82]

እነኛ እንደ ትንቢት የተነገሩት ሁሉም አንድ የሠሩት ሥራ ቢኖር፥ በሕዝቡ አእምሮ ውስጥ የማይጨበጥ አጉል ተስፋ በመጫር፥ ሕዝቡ መራራውን እውነት እንዳይመለከት አድርገዋል። ሕዝቡ በአጉል ተስፋ ሲጠመድ፥ መንግሥት የፈለገውን ለመሥራት ፋታ አግኝቷል። አሁንም ሕዝቡ የትንቢት ተናጋሪዎችን አፍ ከመጠባበቅ ይልቅ፥ ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ፥ በማንኛውም የኢትዮጵያ ምድር በሰላም እንዲኖር የሚያደርግ ሁኔታ እስኪፈጠር ድረስ፥ ጦርነት እንደማይቀርለት፥ ይህንን መራራ እውነት ተከትሎ፥ ማድረግ ያለበትን ቢያደርግ ነው የተሻለ ጊዜ የሚመጣው።

ምድራዊ ሂደቶችን እየተመለከቱ መተንበይ ለብዙዎቻችን ከባድ አይደለም። ከፊት ለፊታችን መጪው ከፉ ጊዜ እየታየን፥ "አይዟችሁ፥ ማር ይዘንባል ከደጃችሁ" እያሉ የሚተነብዩት ግን፥ ከፉውን ጊዜ ለመቋቋም እና ተዘጋጅተን እንዳንጠብቅ ነው የሚያደርጉን።

## የሰውራን ድርጅቶች ወሳኝ ተሳትፎ በአለማችን ላይ

ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ፥ የእግዚአብሔርን ሕግጋት እና እርሱ ያስቀመጠልንን ስርዓት በምንጥስበት ጊዜ ሁሉ፥ መጠኑ ይለያይ እንጂ፥ በተለያዩ ቀውሶች ውስጥ አልፈን፥ የሚያስከትለውንም ፍዳ መከራ ስንቀበል ቆይተናል። ለወደፊትም ታላቅ እልቂት እንደሚጠብቀን እናውቃለን።[83]

ሰይጣን አላማውን የሚያስፈጽመው በተደራጀ መዋቅራዊ አስተዳደር ነው እንጂ፥ እንዲሁ በዘፈቀደ አይደለም። የሰው ልጅም ሕይወቱን ሙሉ የዛን

---

[82] *"በዚህ ፈንታ፡- ጌታ ቢፈቅድ፥ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን፤ ማለት ይገባችኋል።" ያዕ. 4፡15*

[83] የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24ን ይመለከቷል።

የማይታየውን "የድርጅት አላማ" በመቃወም ይታገላል። መጥፎ መንግሥት ስውሩን "የድርጅት አላማ" ወዶም ሆነ ሳይወድ ይፈጽማል።

የሰው ልጅ አሁን ከደረሰበት ምድራዊ ሥልጣኔ የደረሰው፥ "ከምድራዊ ኑሮው ካገኘው ልምድ ተነስቶ፥ በራሱም ተፈጥሮአዊ እድገቱ ያገኘው ነው" እንዳንል፥ አንዳንድ መንፈሳዊ ክስተቶች በሰዎች ኑሮ ውስጥ ጣልቃ ገብተው እንደነበር አስተውለናል። የጥፋት መላእክትም ወደ መሬት ገብተው ክፉ ሥራን እንደሠሩ፥ እኛም እነርሱን ተከትለን የተማርናቸው ብዙ ጥፋቶች መኖራቸውን የአለማችን ታሪክ ያመላክታል። ከግለሰብ እስከ ማሕበረሰብ እና መንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ የእርኩስ መንፈስ ጣልቃ ገብነት በመኖሩ እና፥ እስከ ምጽአት ድረስም ቢሆን፥ ሰይጣን እውነትን እየታገለ እንደሚቀጥል ነው ከመንፈሳዊ ታሪካችን የተማርነው።[84]

ከታላላቅ "**መቅሰፍቶች**" በስተጀርባ እጅግ ክፉ ሥራዎችን የሚያሠሩ የጥፋት መላእክት ክፋትን በሕብረት ሊያመጡብን ሲሉ፥ የእነርሱን ድርጅታዊ አሰራር ለማሳካት በቅድሚያ እርስ በርሳቸው በመማማል ነበር።

*"ይህቺን ምክር እንዳንለውጣት፥ ይህቺንም ምክር ቁም ነገር እንድናደርጋት፥ ሁላችን መሓላ እንማማል፤ እርስበርሳችንም እንወጋገዝ" ብለው ሁሉም መለሱለት። ያን ጊዜም ሁሉም አንድ ሆነው ማሉ፤ እርስ በርሳቸውም በነገሩ ተወጋገዙ፤ ሁሉም ሁለት መቶ ሆኑ።" (ሄኖክ 2፡ 5፥ 6)*

በኢትዮጵያችን ላይም ጥፋትን በሕብረት ሊያመጡብን፥ አሁንም ሠፊውን ሕዝብ በሥጋ እንመራለን ብለው የተነሱ፥ "የሥውራን እርኩሳን መናፍስት" አገልጋዮች፥ ሁሉም በየበኩላቸው ተማማሉብን። ከተለያዩ የበይነ መረብ አውታሮች እና ዩቱቦች (youtubes) ብዙ የፖለቲካ ወሬዎችን እንሰማለን፤ እርስ በርስ የተማማሉብንን ግን አንሰማም። ለምሳሌ፡- የአኖሌ ሃውልት ተገትሮ እናየዋለን፤ ምናልባት በወረቀት ላይ የተጫረውን ንድፉን ደርሰንበት ይሆናል እንጂ፤ የተማማሉብንን ምሥጢራዊ አድማ የነገረን የለም።

የአሁኖቹም ልክ እንደ ጥንቶቹ ጦረኞች እንድንሆን፥ በሃሳብም በመሳሪያም እርስ በርሳችን እንድንተላለቅ አደረጉ። እኛ ግን፥ የአሁኖቹም ዝርያዎች (ልጆቻቸው)

---

84 *"አንተ በንጋት የሚወጣ የአጥቢያ ኮከብ ሆይ፥ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ፤ ወደ አሕዛብም መልዕክትን የላክህ አንተ ሆይ፥ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቀጠቀጥህ!.." ኢሳ. 14፡12*

ልክ እንደ ጥንቶቹ ዝርያዎች (ልጆቻቸው) እርስ በርሳቸው ተላልቀው እንደሚጠፉ፥ ይህንን እናውቃለን።[85]

የአለማችን አካሄድ እና የሰው ልጅ የወደፊት እድሉ፤ ኢትዮጵያችንም ዛሬ ያለችበት ሁናቴ እና የወደፊት መጻኢ እድሏ ያሳስበናል። በተለይም፥ "ትልቋ ኢትዮጵያ ትፈርሳለች፤ ሌሎች ትላላቅ አህጉራት፥ እንደ ዩጎዝላቪያ እና ሶቪየት ሕብረት፥ እርሷም በትናንሽ ሀገራት (አማራ፥ ትግራይ፥ ኦሮሚያ፥ ወ.ዘ.ተ.) መከፋፈሏ አይቀርም.." እየተባለ መሰበኩ፥ በሕዝቦች መካከል ፍርኃትን እና ጭንቀትን ስላመጣ፤ ምናልባት "የውጪ ኃይላት ስውራን ድርጅቶች" በኢትዮጵያ መጻኢ ላይ ወሳኝ ተሳትፎ ሊኖራቸው ስለሚችል፥ የሩቁን ወደፊት በአይነ ልቡና ማየት ያስፈልጋል፤ "በደረቅ አይናችን ከምናያቸው አንጻባራቂ ተቋሞች በስተጀርባ ምን ይኖር ይሆን?" እያልን እራሳችንን እንድንጠይቅ የሚያደርገን፥ የሁኔታዎች በአንድ አቅጣጫ መቀነባበር ነውና።

በተጠመደብን ወጥመድ ልጆቻችንም እንዳይገቡበት፥ አስቀድመን ጠላቶቻችንን እንለያቸው። አወቅን የሚሉ ሁሉ በራሳቸው ሎጂክ (logic - ስነ አመክንዮ) ይመራሉ፤ የሰው ሎጂክ ከሚያየውና ከሚሰማው አያልፍም። በአንድ ወቅት፥ ጊዜው ሲለወጥ፥ ክፉው መንፈስ መሸነፉ ሲረጋገጥ፥ ቅን እና የዋህ በመሆናቸው ያወቁ የመሰላቸው፥ አለማወቃቸውን ሲገነዘቡ፥ የአስተሳሰብ አቅጣጫቸውን ይለውጣሉ። የዛን ጊዜ፥ በእውነትም ኢትዮጵያ እጅጉን የተጎዳችው፥ በሥጋዊ አይናችን የምንመለከተው፥ በሥጋዊ ጆሮአችንም የምንሰማው ውሱን በመሆኑ፥ የኢትዮጵያን ሁለመናዋን (ምድራዊ እና መንፈሳዊ ገጽታዋን) ልናይላት ባለመቻላችን ምክንያት መሆኑ ይገባቸዋል።

እኛ'ኮ! በነጭ አልተገዛንም" እያልን በራሳችን ስንኩራራ ቆይተናል፤ ከጥንትም እንዳንገዛ ያደረገን የቅዱስ መንፈስ ኃይል በመካከላችን እንዳለ እና እንደሚራዳን ሁሉ፤ አሁንም እንደጥንቱ እርኩስ መንፈስ ኢትዮጵያን ሊያጠቃ ሲመጣ፥ ከሀገር ውስጥ ካሉ፥ ከውጪም በሚመጡ በሰዎች ውስጥ አድሮ፥ ሰው መስሎ ነው እንጂ፥ ጅብ ወይንም ሌላ አስፈሪ አውሬ መስሎ አይደለም።

አንድ ጤነኛ ሰው ብቻውን ሜዳ ላይ እንደቆመ፥ አንድ እብድ እየገሰገሰ ወደ እርሱ ሲቀርበው፥ ሰውዬውም የእብዱን ሥጋዊውን ሰውነት እንጂ፥ ከዛ እብድ ጋር ያሉትን የመናፍስት ግሪሳ አይመለከትም። "እብድ ሲማታ አይን የለውም" ሲባል፥

---

[85] ለኛ በአካል የሚታዩትን በአካል ከማይታዩ፥ ተወራራሽ ከሆኑ ከውስጠ ጠባዮቻቸው ጋር እያወዳደርን፥ በአይነ ሕሊና እንቃኛቸው። በዚያውም፥ መጽሐፈ ሄኖክን በመመልከት፥ ከአሁኑ እና ከመጪው ዘመን ጋር ያለውን ዝምድና በማወዳደር እናስተውል።

ኃይሉ ከሰው ኃይል የላቀ መሆኑን ያመላክታል። ስለ እብድ ጉልበት ስንገረም፤ “ተቅበዝባዥ” የሆኑ የሀገር መሪዎችም እንዲሁ፥ ሕዝቡን ሲጨፈጭፉ፥ “ያንን ሁሉ ኃይል ከየት አመጡት?” ብለን መጠየቃችን አይቀርም።

የእብደትም አይነት አለው’ኮ! አንድ ሰው አብዶ የሚጎዳው እራሱን ብቻ ሲሆን፥ እንዲህ ያለው እብድ በአለባበሱ በአመጋገቡ እና በአኗኗሩ በቀላሉ ይለያል። አንድ ሰው አብዶ የሚጎዳው ሕብረተሰቡን ሲሆን ግን፥ እንዲህ ያለው እብድ በቀላሉ አይለይም። ኦሮሞው በኦሮሞው (ወንድም በወንድሙ) ላይ እንዲዘምት፤ አማራውም በአማራው (ወንድም በወንድሙ) ላይ እንዲዘምት የሚመክር፤ ለእንዲህ አይነቱ መንግሥት ምን ስም እናውጣለት? ለእንዲህ ያለው ክፉ ሃሳቡና ክፉ ሥራው የሚመጥነው ስም የትኛው ነው? ብዙዎች ግን፥ “ሰይጣን ወይንም ሰይጣናዊ” እያሉ ነው የሚጠሩት።

ብዙውን ጊዜ፥ በአለም ላይ በመጥፎነታቸው ታዋቂ የሆኑ የሀገር መሪዎች ከተራው ሰው በላይ ቁጠኞች፥ እልኸኞች፥ ተናዳጆች፥ ኃይለኞች እንዲሁም ተናጋሪዎች ሲሆኑ፤ ምናልባት ለእንስሳት እንጂ፥ ለሰው ልጅ ርኅራኄ የላቸውም፤ ጸጸትን አያውቁም፤ የሚታመኑ አይደሉም፤ ጠበኞች፥ ጨካኞች እና ተንኮለኞች ናቸው። በተፈጥሮ ጠባያቸው የተገለጹትን ጠባያት ተደምሮ ከዛም በላይ ሌሎች ሰይጣናዊ ክፋቶችን ያካተቱም ይኖራሉ።

የተጠቀሱት ጠባያት (narcissist, psychopath, sociopath) በሚባሉ ጠባያት ውስጥ ይገኛሉ። የአንድ ሰው ጠባዩ የተገለጹትን ሦስት ጠባያት ተደምሮ ከዛም በላይ ሲሆን፤ እንዲህ አይነቱ ምን ተብሎ ይጠራል? “እብድ፥ ድብቅ እብድ፥ ሰይጣን ወይንስ ሌላ?[86]

በደርግ፥ በኢሕአዴግ እና በአሁኑ መንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያላየው አይነት ጠባይ የለም። እስከዛሬ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሁሉ በአንድም ሆነ በሌላ ያዳረሱ የግፍ አይነቶች በኢትዮጵያ ሰማይ ሥር የተፈጸሙት፥ ሁላችንም አይተናቸው እንድንማርባቸው ስለተፈለገ ይሆናል። ጥሩ አድርጎ የሚያስተምር ሁልጊዜ ጥሩ ሰው አይደለምና፤ ከመጥፎዎችም መማር ይቻላል። እስካሁን መማር ያለብንን ካልተማርን ምንጊዜም ላንማር እንችላለን። ከሰውም ይሁን ከሌላ፥ በተጠመደብን ወጥመድ

[86] Psychopaths tend to be the most violent and dangerous because they lack empathy, conscience, and respect for authority. Sociopaths are similar but often use manipulation and deceit over violence. Narcissists can also be selfish and cruel but are less likely to engage in illegal or violent behaviors.

ልጆቻችንም እንዳይገቡበት፤ መማር ያለብንን በደንብ እንማር፤ ማወቅ ያለብንን በደንብ እንወቅ። መጥፎ እየሠሩ ጥሩ የሠሩ የሚመስላቸው፥ በውስጣቸው እርኩስ መንፈስ ያደረባቸውን ባለ ሥልጣኖችን እያወቅናቸው፥ ለእነርሱ ስንገዛ፥ በፈቃዳችን ከክፉዎች ጋር እንደተባበርን ይቆጠራል። ቢያንስ፥ "እራስን ይቅርታ በሚያሰጥ ክበብ" ውስጥ ማቆየት - ለክፉ ሥራ ተበባባሪ አለመሆን ይሻላል።[87]

## መደራጀት ከእውነት እስከ እውነት

የሰው ልጅ የአስተሳሰቡ እድገት በከፍ እና ዝቅ (ወይንም በክፋት እና በደግነት) ስለሚለያይ፥ በአንድ ሀገር ውስጥ ፍጹም ሰላምን ማምጣት ቀላል አይሆንም። ለዚህ ነው፥ አንድ ሕዝብ ማሕበራዊ የሕሊና ንቃቱን በየጊዜው እንዲያሳድግ፥ ለዴሞክራሲያዊ ውይይቶች በር የሚከፍት መንግሥት የሚያስፈልገው። ሕዝቦችም ከመሪያቸው የሚሰጣቸውን መመሪያዎች ካልሰሙና ካልተከተሉ በስተቀር፥ በሰላም አብሮ መኖር አስቸጋሪ ይሆናል። በሕዝብ እና በመንግሥት መካከል ልዩነቶች የሚጠቡት በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ነው።

እኛ ኢትዮጵያኖች፥ ከደርግ እስከ ኢሕአዴድ፥ ከኢሕአዴግም እስከ አሁኑ ግራ አጋቢ መንግሥት ድረስ፥ በብዙ መሰናክሎች አልፈን ነው ከዚህ የደረስን። ከእንግዲህ፥ የምድራዊ ፖለቲካ ጨቅላነት የለብንም። ከኢሕአዴግ ጀምሮ በአንድነታችን እንዳንዘልቅ ያደረገንን የክፉ መንፈስ ሴራ አሁን ተገንዝበነዋል። "ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኚያ አንቀው ጣሏት እንዲሉ፥ "ትበለጽጋላችሁ" እያሉ ሊያታልሉን የሞከሩበት መንገድ ሁሉ፥ አንዱም ውሃ አልቋጠረላቸውም።

ኢትዮጵያችን በከፋ የፖለቲካ ውጥረት መግባቷን ያዩ ግለሰቦች ቆጣ ብሎ ከሚነሳ ትውልድ ስለተፈጠሩ፥ አቅማቸው በፈቀደ መጠን ተንቀሳቅሰዋል። ሆኖም፥ ከየግል ፍላጎታቸው አልፈው የማሕበረሰቡን ችግር የሚያዩበት ስነ ልቦና በብልጭ ድርግም ተስፋ ተቆራረጠባቸው (ምድራዊነታችው አንቆ ያዛቸው?) በጋራ መመልከት እንዳይችሉ፥ ቆጣ ብለውም በሕብረት እንዳይነሱ "የሚገታ ኃይል" ገታቸው።

"አዲሱ" መንግሥት ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ፥ መሠረታዊ የአገዛዝ ስልቱ ከወያኔዎች የአገዛዝ ስልት አልተቀየረም፤ የኢትዮጵያም ሕዝብ ቃሉን የሚሰማለት

---

87 *"ከሌባ ጋር የሚካፈል ነፍሱን ይጠላል።" ምሳ. 29፡24....."ብዙ ሰዎች የሹምን ፊት ይፈራሉ፤ የሰው ፍርድ ግን፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።" ምሳ. 29፡29*

መንግሥት አላገኘም። የፖለቲካ ፓርቲዎች የሙበዛታቸውን ያህል፥ ኢትዮጵያዊ በሆነ የጋራ ርዕዮተ አለም (ideology) መግባባት እና አብሮ መሥራት አልቻሉም።

ኢትዮጵያችንን የጎዳት በዘር የተዋቀረ የመንግሥት ስርዓት እና አስፈጻሚዎቿ ሲሆኑ፥ ጠላቶቿም ይህንን ስርዓት የሚደግፉት ናቸው። እኛ ግን፥ አይነ ሕሊናችንን በራሳችን ስላጨለምን፥ "አያያዙን አይቶ ጭብጦውን ቀማው" እንዲሉ፥ ካጠገባችን ሆነው ሊጨርሱን ሲማማሉብንም፥ እያወቅን ችላ አልናቸው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የደረሰበትን በደል ተሸክሞ እንደቆየ ሁሉ፥ በአንድ ወቅት በቃኝ ብሎ መነሳቱ አይቀርም (ተነስቷልም)። የዛን ጊዜ፥ በእጁ ሊገባ ያለውን ለውጥ ለመቀማት የሚነሳ ኃይል ይጠፋል።

የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፎች ሲደረጉ በአረንጓዴ፥ ቢጫና ቀይ ባንዲራችን ላይ ምንም ሌላ ተጨማሪ ምልክት የሌለውን በመያዝ የሆነበትም ዋናው ምክንያት፥ የዘረኛውን አገዛዝ መልሶ ላለመድገም፥ ከአዲስ መንግሥት አዲስና መሠረታዊ መዋቅራዊ ለውጦችን ከመሻት አንጻር ነው እንጂ፥ ጠቡ ከኮከቡ ብቻ አልነበረም።

ቀኑም ቢጨለም - እጅግ ቢበዛም ስቃይ፥

ተስፋችን አይጠፋም፥ ጥሩ ቀን ሳናይ።

ዛሬ በቀለሙ ቢታከልበት ሌላ ምስል፥

ዝም ቢልም - ዝም ማለትን ለማይችል፥

አንድ ናት ሀገሬ ለሚል፥

ቀና ብሎም ለሚያስተውል፥

ያውና አርማው - ከሰማዩ ላይ፤

ይኸው! ይታያል፤

ቀስተ ደመና ነው እንጂ፥ ሌላም አይደል።

በወያኔዎች እና በመንግሥት መካከል ጦርነት የተቀሰቀሰበት ምክንያት ምን እንደሆነ፥ ጦርነቱንም ለምን በቶሎ መቋጨት እንዳልተፈለገ (ወይንም ለምን እንዳልተቻለ)፤ መንግሥት የአማራ ፋኖችን ብቻ መርጦ ትጥቅ ፍቱ ማለቱ፤ ይህንን እና የመሳሰሉትን ፖለቲካዊ እውነታዎች፥ ለፖለቲከኞች፥ ለጋዜጠኞች፥ ለታሪክ ተመራማሪዎችና ለእውነት ፈላጊዎች እንተወው።

በእርግጥ፥ ለአንድ ሀገር የሚያስፈልገው አንድ መከላከያ ጦር ብቻ ነው። ስለዚህ፥ "እናንተ የራሳችሁን ጦር ገንብታችሁ በያለበት የምትንቀሳቀሱ ሁሉ፥ ኑ፥ ከእኛ ጋር ተቀላቀሉ" ማለት፥ ለሀገር በማሰብ፥ ከቅንነት የተነሳ ቢሆን ጥሩ ነበር። ነገር

ግን፥ የአማራ ግድያና ማፈናቀል በሆነበት ወቅት፤ መንግሥት የአማራ ፋኖችን ብቻ ለይቶ ትጥቅ እንዲፈቱ ለማስገደድ መሞከሩ፤ ፋኖ ሥልጣኔን ይቀማኛል ብሎ ስለሚፈራ መሆኑን ነው የሚያመላክተው። በተደጋጋሚ መንግሥት ከሚወስዳቸው እርምጃዎች ያየነው፥ መንግሥት የራሱ ሥልጣን እንዲራዘምለት እንጂ፥ ጦርነቱ እና የሕዝቡ እልቂት አይሰማውም፤ እርቅ እና ሰላሙ አይገደውም። ስለዚህ፥ የሚወስዳቸው እርምጃዎች ሁሉ "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" በሚል የተንኮለኞች እና የክፉዎች እሳቤ የተቀሰቀሰ መሆኑን ማንም ባለ አእምሮ ይረዳዋል።

ይገርማል፤ ይደንቃል፤ ልክ በደርግ ዘመን እንደተፈጸመው፥ አሁንም ወጣቶች (በብዛት የኦሮሞ ተወላጆች) ከየገጠሩ እየተሰበሰቡ፥ ለውትድርና ይሰለጥናሉ። የቀድሞዎቹ የሚዘምቱት በኤርትራ ላይ ነበር፤ የአሁኖቹ ደግሞ በአማራ ላይ። አሁንም እንደ በፊቱ፥ ሚስቶች፥ እናቶችና እህቶች ያለቅሳሉ፤ "ክቡሬ - ክቡሬ የኢትዮጵያ ባላገር፥ በል ደህና ሁን፥ ካውቶብሱ ተሳፈር፤ ልትዘምት ነውና፥ ወደ አማሮቹ - ወደ ዘመዶቼ ሀገር.." እያሉ። እናቶች፥ ልጆቻቸውን "ሂድ፤ ግደልና ሙት" ሲባሉ፥ እነርሱ ከበስተጀርባ ያለውን ሰይጣናዊ ተንኮል ያውቃሉ። ነገር ግን፥ ይህንን መከላከል ባለመቻላቸው እጅጉን ያዝናሉ። ኢትዮጵያን ካስለቀሳት የውጭ ጠላት ይልቅ፥ ኢትዮጵያን ያስለቀሳት የውስጥ ጠላት በለጠ።

በወሳኝ የጊዜ ጠርዝ ላይ ስንደርስ፥ መንግሥት እና ግብረ አበሮቹ፥ ሠፊውን ሕዝብ ከመጥፎ ወደ በጣም መጥፎ ሲመሩት፤ ነገሮች ከቀን ወደቀን እየከፉ ሲሄዱ፤ መንግሥታዊ ሴራ የምንለው ሁሉ፥ ድብቅ መሆኑ ቀርቶ፥ አለም ያወቀው ሲሆን፤ ከሰው የተፈጠረ የሰው ልጅ የተፈጠረባትን ኢትዮጵያን የማይወድ፥ በሕዝቦቿም አንድነት የሚቀና፤ ሰው ሲገደል፥ ሕዝቦች ሲሰደዱ፥ መጠጊያ ሲያጡ፥ ሲጨነቁ፥ የሚበሉትና የሚጠጡት አጥተው ሲቸገሩ የማያዝንላቸው መንግሥት፤ እርሱ በሰይጣናዊ ልባምነት የሚመራ መሆኑን ያረጋግጣል።

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፥ በአንድ ብሔር ላይ (እየመረጠ በየተራ) ያነጣጠረ፥ መንግሥታዊ ጥቃቶች ተፈጽመዋል። "ኢትዮጵያን እናፍርሳት!" የሚል የክፉው መንፈስ ድምጽ አስተጋብቷል። ክፉዎች እና ዘረኞችም ወደ ጦርነት ገብተዋል። ታዲያ፥ በዚህን ጊዜ፥ ኢትዮጵያ በብዙ ሺህ ዓመታት እድሜዋ እናታቸውን ከውድቀት የሚያነሱ ጀግኖች የሏትም? አላት እንጂ።

ከጥንት ጀምሮ መንፈሳቸውን ከኢትዮጵያ መንፈስ መለየት ያልቻሉ፥ በጀግንነት ታሪካዊ እውቅና የሚሰጣቸው ኢትዮጵያውያን ታጋዮች፥ ቅን አሳቢዎች እና ሀገር ወዳዶችም "ኢትዮጵያ አትፈርስም" በማለት፥ ለሰላም እና ለሕልውና ሲሉ ተነስተዋል (ተነስተናል)። ከአማራው ውስጥ የበቀሉ ፋኖ የሚል ስም የተሰጣቸው

ለዘላቂ ሰላም እና ለጋራ ሕልውና ሲሉ ጦራቸውን አንስተዋል። ከእውነት ተነስተው ለእውነት የቆሙ ጥቂት የእውነት ሰዎችን የእግዚአብሔር መንፈስ ይመርጣቸዋል፤ ይረዳቸዋልም።[88]

ፋኖ የሚል ስም የተሰጣቸው ጦር ያላቸው (ጠብ መንጃያ፥ መትረየስ...) ያላቸው፥ እነኚያ በትጥቅ ትግል የተሠማሩትን ቢሆንም፤ እኛም ዝም ብሎ መቀመጥን ያልወደድን፥ በአካልም ባይሆን በመንፈስ ከእነርሱው ጋር ነን።

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ይህ መንግሥት የሀገራችንን ችግር ሊፈታው እንደማይችል ገብቷቸዋል። ስለዚህ፥ "ኢትዮጵያችን ስትፈርስ ዝም አንልም" በማለት፥ የሕብረተሰቡ ክፍሎች (ገበሬዎች፥ ወታደሮች፥ ነጋዴዎች፥ ተማሪዎች፥ ወ.ዘ.ተ.) የትጥቅ ትግሉን በሃሳብም በአካልም በመደገፍ ተነስተዋል። ድል እውነትን ለሚከተሉ ታጋዮች እንደሚሆን አያጠራጥርም።

ደረቅ እውነትን ይዞ በሃሳቡ የሚታገል፥ በአንደበቱ የሚጸልይ ብዙ ነው በየቤቱ። እውነት እውነተኞችን ስለሚያቀራርብ፥ ፋኖ የተባለውንም ስም፥ እውነትን ፈላጊዎች ሁሉ፥ ከሌሎች እንደ መለያ ስም ተቀብለው ወደ ትግሉ ተቀላቅለዋል።

አንድ ወንዝ እንዳይፈስ ምንጩን ማድረቅ እንደሚያስፈልግ፥ የፋኖንም ትግል ለማቆም፥ የቆመለትን እውነት ማድረቅ ያስፈልጋል (ከተቻለ)። ነገር ግን፥ ማንም ሰው (ትግሬ፥ አማራ፥ ኦሮሞ፥ ወ.ዘ.ተ.) የእውነትን ማተብ ካነገተ (እውነትን የሕይወቱ መመሪያ ካደረገ)፥ ከቆመለት አላማው ሊያደናቅፈው የሚችል ኃይል አይኖርም። እውነትን ከምንጩ ማድረቅ የሚቻለው ማነው?

መንግሥታዊ መዋቅሩ ሀገር የሚከፋፍል መሆኑን የተረዱ ጀግኖች የትጥቅ ትግል መጀመራቸውና ለሀገራቸው መስዋዕት በመሆን የሚታገሉት፥ ይህንን ክፉ መንግሥት በኃይል ገርስሶ፥ በምትኩ በሕዝብ የሚወደድ መንግሥት ለመመሥረት ነው እንጂ፥ በመፈንቅለ መንግሥተኝነት መንግሥታዊ ሥልጣንን ለሌላ አምባገነን መንግሥት ለማስረከብ አይደለም። የፋኖ አላማ፥ ሕገ መንግሥቱን በመቀየር እና በሥራ ላይ በማዋል፥ መሠረታዊ መዋቅራዊ ለውጥን ለማምጣት እንጂ፥ ሌላ ውዝፍ ወይንም ቅምጥ መንግሥት በመሆን፥ ሌላ ቀውስ (ሕብረተሰብአዊ አለመረጋጋት) ለመፍጠር አይደለም።

የሀገርን ሰላምና አንድነት፥ የሕዝቦችንም ሕልውና ለመጠበቅ እና ነጻነታቸውን ለማረጋገጥ፥ ይህንን የፋኖን አስተሳሰብ ለመጋራት፥ ጥሩ ሰው መሆን ብቻውን በቂ ነው።

---

88 ለደካማ ኃይልን ይሰጣል፤ ጉልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል። ኢሳ. 40፡29

በጥቂት የፋኖ ጀግኖች የተቀጣጠለው ትግል አሁን አለም አቀፋዊ መልክ ይዟል። ሰላማዊ ሰልፎችም በአለም ታላላቅ ከተማዎች ተካሂደዋል። ሃቀኞች ኢትዮጵያኖች ባሉበት ሥፍራዎች ሁሉ፥ ሃቀኞች ዲያቆናት፥ ቀሳውስት፥ ጳጳሳት እና ሌሎችም አባቶች ስለ እውነት በአንድነት ቆመዋል። ከጥንት ከአባቶቻችን የወረስነውን ፋኖነት ይህ ትውልድ ለመረከብ መብቃቱ እንደ አንድ ትልቅ ጸጋ ይቆጠራል። ለወደፊትም፥ ፋኖነት የእውነት መገለጫ በመሆን፥ ከትውልድ ትውልድ እየተሻጋገረ ይቀጥላል እንጂ፥ በዚህ ትውልድ ብቻ የሚያበቃ አይደለም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ላለፉት 50 ዓመታት ሲመኘው የነበረውን ከዘረኛነት የጸዳ፥ ነጻነትና እኩልነት የሰፈነበት፥ ለዘለቄታው አስተማማኝ የሆነ ሕዝባዊ መንግሥት ለመመሥረት፥ በቁርጠኛነት እና በቆራጥነት የተጀመረ ትግል በእግዚአብሔር ፈቃድ እስኪጠናቀቅ ድረስ፥ የአለም መጨረሻ ቢሆንም አያቆምም። በሕዝብ የተጠላ መንግሥት ይሰናበታል፤ ቀሪው ሕዝብ ተስማምቶ እንዳይኖር የሚያድርግ ኃይልም እንዲሁ።

የሰው ልጅ ሰማያዊ ተፈጥሮ ስላለው፥ ጠፈር አቀፍ ሃሳቡን በአንድ ሥጋዊ አንጎሉ እንዳሻው ሊያዘዋውረው ይችላል። ስለዚህም፥ በሃሳቡ ከመቀመጫያ ቤቱ ወጥቶ፥ አለምን ሁሉ ዞሮ ጎብኝቶ፥ ምድሪቱንም ለቆ ሠፊውን ጠፈር እንደ መዝናኛ ሥፍራው መመላለሺያና መዝናኚያ ሥፍራው ሊያደርገው ይችላል። አንዳንድ ሰዎች ግን፥ "ከምድራዊነት" እሳቤ ስለማይላቀቁ፥ ፖለቲካዊ ምልከታቸውም እንደዛው ጥብብ ይላል። በዚህች መሬት "የእኔ ልኑር፥ እኔ ልኑርባት" ንትርክ እስከ ጠብ እና መገዳደል የሚደርሱትም፥ በዚሁ ውሱን ምልከታ እና እራስን ከመጠን በላይ ከመውደድ የተነሳ ነው።

በአሁኑ ወቅት (2016) ኢትዮጵያን እየመራት ያለው መንግሥት በማይጨበጥ የአመራር ብስለቱ፥ ሕዝቡን በማታለል፥ የሥልጣን ዘመኑን ለማራዘም የሚቻለውን ሁሉ አደረገ። ካሁን በፊት ጨካኝ፥ ከፉ፥ ዲክቴተር፥ ወ.ዘ.ተ. እየተባሉ መጥፎ ስሞች የተሰጣቸው መሪዎች እንደስማቸው ቀላል የማይባል ጥፋት አጥፍተው ሄደዋል። መጪው የሀገር መሪ እነሱን ባለመምሰል ብቻ ውስጣዊ ጥሩነቱን ያስመሰክራል። ጥሩ የሀገር መሪ "ሕዝቡ ካልፈለገኝ ልሂድ አሰናብቱኝ፤...." ይላል እንጂ፥ "እኔ ካልነገሥኩ፥ ኢትዮጵያ ትፍረስ" በማለት፥ ሕዝቡን አይጨፈጭፍም። ስለዚህ፥ የምንጠብቀው መልካም መሪ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት፥ መንፈሳዊ ጥንካሬ የሚታይበት፤ ራሱን ከመጠን በላይ በመውደድ ለሥልጣን እና ለሥጋዊ ክብር የማይንገበገብ፤ ክፋት የሌለበት፤ ውዳሴ ከንቱን የማይፈቅድ፤ ከራሱ ክብር የሀገሩን ክብር የሚያስቀድም፤ ቀጥተኛ ርዕዮት ያለው፤ ፈጽሞ የማይዋሽ፤ እውነትን ብቻ

በመከተል፥ በአቋሙ የሚጸና እንጂ፥ የማያወላውል፤ የሀገሩን እና የሕዝቡን ታሪክ ጠንቅቆ የሚያውቅ እና ለማንኛውም የሕዝብ ወገን የማያዳላ (ዘረኛ ያልሆነ)፤ ትእቢትን እና መታጀልን የማይወድ፤ ለተጎዱና ለተበደሉ የሚያዝን የርኅራሄ ልብ ያለው፤ የራሱን ሀገር የመምራት ኃላፊነት በሚገባ የሚወጣ - በሥሩ ላሉ ሥራ አስኪያጆች ትክክለኛ መመሪያ እየሰጠ፥ ሥራቸውን ከመቆጣጠር አልፎ፥ የሌሎችን ሥራ ለራሱ የማያደርግ፤ ሕዝቡ የሚለውን የሚሰማ፤ ሀገራችን የሚያስፈልጋትን እና የጎደላትን አግባብ ካላቸው የሕዝብ ተወካዮች እየሰማና እያስማማ - እየተመካከረ እንጂ፥ በራሱ ፍላጎት እየተመራ የፈለገውን የማያደርግ፤ ለሀገር ሕልውና ቅድሚያ የሚሰጥ፤ በአጠቃላይ ሠፊውን ሕዝብ በቅንነት ለማስተዳደር በቂ ስብእና ያለው፤ የሁሉንም ሃይማኖት የሚያከብር፤ ስግብግብነት፥ ትምክህተኛነት፥ እብሪተኛነት፥ አክራሪነትና ጀብደኛነት እና ጠበኛነት፥ በአጠቃላይ ፍጹም ምድራዊነት የማንነቱ መገለጫ ያልሆነ መሆን አለበት።

የፋኖ ድል መንሳት የትግላችን መጨረሻው ባይሆንም፥ ለቀጣዩ ተስፋችን ፈር የቀደደ፥ ውሸት በእውነት ላይ ምንም ሥልጣን እንደሌለው፤ እምነትን፥ ሃይማኖትን አጥብቆ፥ እግዚአብሔርን ይዞ ሽንፈት እንደሌለ፥ ሁሉም በእግዚአብሔር እንደሚቻል የምናረጋግጥበት በመሆኑ ለደስታችን ወሰን የለውም። የፋኖ ድል መንሳት እስከ ዛሬ ድረስ የተራማጅ ኢትዮጵያውያንን እውነተኛ የትግል መንፈስ ተከትሎ የመጣ እንጂ፥ እንዲሁ ድንገት የተገኘ አይደለም።

ከጥንትም በኢትዮጵያ ላይ የሚሰነዘር ጥቃት፥ በተለይም ባለፉት ጥቂት ዓመታት ያሳለፍነው የትግላችን መንስኤ፥ ጸባችን እና ጦርነቱም ከእርኩስ መንፈስ ጋር ስለሆነ፤ የአሁኑ ድል፥ ምድራዊት ኢትዮጵያችንን ከፍ የምናደርግበት፥ ሰይጣን የጋረደባትን የክፋት መጋረጃ የምንቀድበት፥ ሰማያዊ መልኳም እንዲታይ የምናደርግበት በመሆኑ ለደስታችን ወደር የለውም።[89]

ሰዎች ስለየግል እውነቶቻቸው ስለ ማንነታቸው (ስለ ኢትዮጵያዊነታቸው፥ ስለ ሉዓላዊነታቸውም) ብዙ ያወራሉ፤ ነገር ግን፥ "በሕዝቦች መካከል ገብቶ የሚያተራምሰውን ሰይጣን እንዴት አድርገን በሕብረት እናስወግደው?" ብለው አይወያዩም። ስለየግል እውነቶቻቸው ይጨነቃሉ እንጂ፥ የጋራ እውነቶቻቸውን እንዴት በሕብረት ወደ አንድ መስመር አምጥተው፥ እውነትን እስከ እውነት እንዴት ማድረስ እንደሚቻል አይመካከሩም። በስሜቶቻቸው እየተናጡ፥ እውነቶቻቸውን እየለቀቁ፥ በብኸርታ መንፈስ ወደአልፈለጉት አቅጣጫ ያመራሉ። የፖለቲካ ፓርቲዎችን

[89] *"ሞት ሆይ መውጊያህ የታለ? ሲኦል ሆይ ድል መንሳትህ የታለ?" 1ቆሮ 15፡55*

አብዝቶ፥ እርስ በርስ ተለያይቶ፥ እስከ መቼ? ያለቺን አንድ ኢትዮጵያ ናት፤ በውስጧም አንድ እውነት።

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የነጻነት ጉዞ፥ እውነትን የጋራ አድርጎ፥ በሕብረት እና በአንድነት እስካልሆነ ድረስ፥ ይኸ እውነትን የግል አድርጎ የብቸኝነት ጉዞ፥ በተለያዩ አህጉራት ተሞክሮ እንደታየው ሁሉ፥ ውጤቱ አያምርም፤ አይሳካም (አይሆንም)። እኩል የማንነቃ ሆነና፤ የአሁኑ ክፉው፥ ከመጪው ክፉ ጋር ያለውን ዝምድና ባለመገንዘባችንም ምክንያት፥ ስቃይ በዛብን። ስቃይም አስተማሪ ሆኖ ሊያስተምረን ይሞክራል፤ እኛ ግን፥ የማንማር እምቢተኞች ሆንን። በመካከላችን እየገባ ስለሚያፋጀን ኃይል ማወቅ ስላልፈለግን፥ የራሳችንን ውስጣዊ ኃይል በአግባቡ መጠቀም አልቻልንም።

ባለፉት 50 ዓመታት ታሪካችን ውስጥ በተደጋጋሚ እንዳየነው፥ ሰዎች ለአንድ አላማ ሲደራጁ፥ ከሞላ ጎደል እውነትን በማስቀደም ይሆንና፥ ትንሽ ቆየት ሲል፥ መስመራቸውን እየለቀቁ እንዲሄዱ የሚያደርጋቸው ምድራዊ ስግብግብነትን የሚፈጥር ሁኔታ ይፈጠርና ከቀዳማይ አላማቸው ሸርተት ማለት ይጀምራሉ። ለምሳሌ፡- ዳግማይ ወያኔዎች፥ የቀዳማዊ ወያኔዎችን እውነት በማስታከክ፥ በከፊልም የኤርትራውያንን እውነት ተገን በማድረገው ተነሱ፤ ሻቢያና ዳግማይ ወያኔ በአንድላይ ሆነው ኢትዮጵያን በያዙበት ወቅት፥ በሁለቱም መካከል፥ ትንሽ፥ ትንሽ አንጻራዊ እውነት ነበር። ትንሽ ቆየት ሲል፥ መስመራቸውን እያለቀቁ ሄዱና፤ በመካከላቸው የነበረው የአንድነት አንጻራዊ እውነት ተሸረሸረ፤ ውሸት ገነነ፤ እርስ በርስ እስከ መገዳደልም የሚያደርስ ጥላቻ ተፈጠረ።

ኤርትራውያንም ከጊዜ በኋላ፥ በሁለት ተከፍለዋል። ከእነርሱ መካከል እውነት ያላቸው፥ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውንም የአንድነት እውነት ተገን አድርገው ሊነሱ ይችላሉ (እውነቶች ከእውነቶች ጋር ሲደጋገፉ፥ ዘርና ብሄር አይመርጡም)። ለወደፊት “ከእንግዲህስ፥ የሕዝብ አይነቱ የሚታወቀው በዘር ማንነቱ ሳይሆን በክፉ እና በደግ መሆኑ አይቀርም” የሚያስብሉ ክስተቶችን ማየታችን አይቀርም።

ፖለቲካዊ ድርጅቶች በያለበት፥ እውነትን ይዘው መነሳታቸው ጥሩ ሆኖ ሳለ፥ በዛው በእውነቶቻቸው ቢቀጥሉበት ጥሩ ይሆናል። ለምሳሌ፡- ፋኖዎች ትግላቸውን ሲጀምሩ፥ እውነትን መከታ አድርገው ነው፤ በዚያው በእውነቶቻቸው እንዳይቀጥሉበትና አላማቸውን እንዳያሳኩ የሚያደርግ ጠላት ይተናነቃቸዋል።

ይህንን መራራ እውነት ካለፉት ታሪኮቻችን መማር ይቻላል። ለምሳሌ፡- በኢሕአፓ አመራሮች ውስጥ የነበረውን እውነት እንዲሸረሸር ያደረገው፥ በመቀጠልም አንጃዎች ተፈጥረው፥ እርስ በርስ እስከ መገዳደልም የሚያደርስ ጥላቻ እንዲፈጠር

ያደረገው ምን እንደሆነ ከታሪክ መማር ይቻላል። በፋኖዎችም ውስጥ ተመሳሳይ ችግር ይኖራል። ሆኖም፥ ኢትዮጵያችንን በማስቀደም ማንኛውንም ችግር በቀላሉ መፍታት ይቻላል። አሁን እና ለወደፊት ለሚፈጠሩ ችግሮች መፍትሄ የሚሆነው፥ ስለየግል እውነቶች በመጨነቅ ፋንታ፥ የጋራ እውነቶችን እንዴት በአንድ አጣምሮ፥ እንዴት በሕብረት ወደ አንድ መስመር አምጥቶ፥ እንዴት እውነትን እስከ እውነት ማድረስ እንደሚቻል በመመካከር ነው።

"በዘራችን ተጠቃን" ማለት የተጀመረው ካለፉት ስድስት ዓመታት በፊት ቢሆንም፥ በተለይ በአሁኑ ጊዜ ነው የዘር ፖለቲካ እጅግ የተካረረው። የብልጽግናው መንግሥትም አንዱን ካንዱ እያጋጨ፥ የራሱን የሥልጣን ዘመን ያራዝምበታል። በዚህ አንጻር፥ መሠራት ያለበት ኃጢአት ሁሉ እየተሠራ፥ የኃጢአት እድገቱ (በኢአማናዊነት፥ በድንቁርና፥ በውሸት እና በክፋት) ከፍተኛ ደረጃ ላይ ተደርሰ።

"የትግላችን ጅማሮ በአማራነታችን ስለተጠቃን እንደሆነ፥ ይኸው ትግላችን ሲቀጥል፥ በማንነታቸው የተጠቁትንም ነጻ እናወጣበታለን፤ ኢትዮጵያም ለኢትዮጵያውያን ሁሉ እኩል እስክትሆን ድረስ ትግላችን አያቋርጥም" የሚሉ፥ ከእውነት ተነስተው በእውነት የሚጨርሱ ናቸው።

የዘር ፍጅትን ያስከተለው ዘር ተኮር አስተሳሰብ መሆኑ እየታወቀ፥ አሁንም ከዚያ አስተሳሰብ የማይላቀቁ ይኖራሉ። ስለዚህ፥ እንደአጀማመሩ መጨረሻውም እንዲያምር፥ ፍቅር እና አንድነትን የሚሰርጹ አስተሳሰቦቻችንን (እርቅ እና ሰላምን፥ እኩልነት እና ነጻነትን) ከሚጻረሩ ኃይላት ጋር ትንንቁ ይቀጥላል። ትግሉ በትንሹ የሚቋጭ አይደለም። የደፈረሰው እስኪጠራ ብዙ ጊዜ ሊፈጅ ይችላል።

በአሁኑ (2016 ዓ.ም.) የኢትዮጵያ ሕዝብ በሁለት ጎራ ተከፍሏል (እየተከፈለም ነው)። አንዱ ወገን ወደ እውነት ይጠጋል፤ ሌላውም ወገን ከእውነት ርቋል። ተገፍቶ ተገፍቶ ከገደል አፋፍ ላይ የቆመውን ሕዝበ አዳም የተመለከተ፥ አይቶም ፈዞ መቆምን ያልወደደ ታጋይ - ብዙ የሰማ፥ ብዙም ያየ አርበኛ፥ እውነትን እየሸሸ በውሸት አለም ውስጥ የሚኖር ጠላትን ከጠላትነቱ እንዲወጣ በአንደበቱ ይመክራል፤ አልመከር ያለውንም በጦሩ ይማርካል፤ ማርኮም ያስተምራል።

በአንድ ሥፍራ ፈዞ መቆምን ያልወደደ ታጋይ፥ የእውነት መገኛ ከእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን አውቆ፥ መስቀሉን በአንገቱ፥ ጦሩን በእጁ ይዞ እግዚአብሔር ወደመራው ይሄዳል። በኢትዮጵያ ዳርቻዎች ሁሉ እውነት እስኪሰፍን ድረስ፤ የኢትዮጵያም ሕዝቦች ሁሉ በኢትዮጵያ ምድር ሁሉ በሰላምና፥ በፍቅር በእኩልነት እና በነጻነት እስኪኖሩ ድረስ፥ ከሞቀ ቤቱ ቁጭ ብሎ፥ የራሱን ግለኛ ኑሮ መኖርን ባለመምረጥ፥ ማድረግ ያለበትን ሁሉ ያደርጋል።

የእግዚአብሔርን መንገድ ትተን የመረጥነው መንገዳችን እንደ ቅጣት ሆኖ፥ ጨካኝ እና ክፉ መንግሥታት ላይ ስንወድቅ ስንነሳ እንደቆየን፤ ያለፈውስ አልፏልና፥ አሁንም፥ ካለፈው ተምረን፥ ለቀጣዩ ምድራዊ ኑሮአችን ሰላምን እንድናገኝ ጥሩዎች፥ ብልጦችም እንድንሆን ጊዜ አስተምሮናል።

ከጥንት ከአባቶቻችን የወረስነውን ፋኖ የተባለ መጠሪያ፥ ዛሬ ልጆቻችን ይዘውልን ብቅ ብለዋልና፤ ከእንግዲህ ይህ ስማችን ሁላችንም አንጻራዊ እውነቶቻችንን ይዘን የምንቆምበት የነጻነት መድረክ ነው። ከእንግዲህ ይህ ስማችን የሀገር ፍቅር፥ የጀግንነት፥ የክብር፥ የአብሮነት እና የአንድነት መገለጫ፣ በማንም የማንደፈር መሆናችንን የሚያረጋግጥ እውነተኛ መጠሪያችን ነው።

ታጣቂ ፋኖዎች ስለራሳቸው ማንነት ያሻቸውን ቢናገሩ፤ በመካከላቸውም ውስጥ ልዩነቶችና የእርስ በርስ ሽኩቻዎችም ቢታይባቸው፤ እነርሱ ሁሉም እንዳሉ ሆነው ለኢትዮጵያችን አስፈልገዋታል። ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ ብዙ እውነቶች ከኢትዮጵያ ሰማይ ርቀዋል። ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉም የእኩልነት መንፈስ እንዲሰማው የሚያደርግ ጊዜ እስኪመጣ ድረስ፥ ያለፍንባቸውን ስህተቶች እያረምን የምንጓዘው መንገድ ረጅም ነው።

የፋኖዎች በዚህን ጊዜ ውስጥ የመገኘታቸው ምስጢር፥ የደረቀን መሬት የዝናብ ነጠብጣብ እንደሚያረሰርሰው ይቆጠራል። ኢትዮጵያችን ከመፈራረስ ድና አንድነቷ ተጠናክሮ የምናየው ቆይቶ ቢሆንም፥ በየጊዜው የምንወጣበትን አቀበት፥ የምንደርስበትንም እርከን በጸጋ በመቀበል፤ በቦንብ፥ በመድፍ፥ በመትረየስ፥ ፋኖ ሥልጣን ሲይዝ፥ ለኢትዮጵያችን የውሃ ዝናብ እንጂ የእሳት ዝናብ እንዳይሆን፤ የፋኖን ትግል ያልተቀላቀለ፥ ወይንም የፋኖን ትግል ለማክሸፍም የታገለ፥ ሁሉም እንደየ ምልከታው በኢትዮጵያዊነቱ ሰላሙ እንዲበዛለት መጸለይ ያስፈልጋል።

የምርጫ ጊዜም በደረሰ ጊዜ፥ አንድን ሰው ለፖለቲካ መሪነት (ለማንኛውም ሕዝባዊ ኃላፊነት) እጩ ሆኖ ሲቀርብ፥ ስለ አስተሳሰቡ (ስለ ብቃቱ፥ ስለ እውቀቱ እና ስለ ችሎታው) ብቻ ሳይሆን፥ ስለ ውስጠ ጠባዩ ማንነትም (በልቡ የነገሠውን መንፈስ) ማወቅ - በእውነት ያ ሰው የእርኩስ መንፈስ ተጽእኖ የሌለበት መሆኑንም ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

እግዚአብሔር ለነፍሳችን ሲያስብልን፥ ለሥጋችንም እንደሚያስብልን ይገባናል (ይኸንን እናውቃለን)። ክፉውን መንፈስ የሚያሸንፍ ከብዙዎቻችን የሚሰርጽ የጥሩ መንፈስ ኃይል ነውና፤ ልዩነቶቻችንን እንደ አንድ የጋራ ኃይል መጠቀም የሚያስችል ጥበብ እና ኃይል እግዚአብሔር ይለግሰን።

ጸሎታችን ብርቱ ነው፤ እግዚአብሔር የኢትዮጵያችንን ሁኔታ ተመልክቶ፥ ለችግሮቻችን ሁሉ መፍትሄ እንዲሰጠን፤ ጥሩውን ጊዜ ፈጥኖ እንዲያመጣልን፤ ፍቅሩን ሰላሙን ሕብረት እና አንድነቱን እንዲያድለን፤ ኢትዮጵያን እንዲጠብቃት፤ ሕዝቡንም እንዲባርከው ቤተ ክርስቲያናት ይጸለያሉ፤ እኛም በየቤታችን እንጸልያለን።

ለምክንያት ተቀምጣለችና፤ ይህቺ ታቦተ ሕጉን ታቅፋ የቆየች፥ ግማደ መስቀሉም የሚገኝባት ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ፥ ምድራዊት ብቻ አይደለችም፤ ሰማያዊትም ናት እንጂ። ለዚህም እንደ ምሥክር የሚቆጠሩ፥ አያሌ ምድራዊ ያልሆኑ "ነገሮች" ይገኙባታል። ለምሳሌ፡- በሌሎች አህጉራት ያልታዩ አያሌ መንፈሳዊ መጻሕፍትን በየአድባራቱ ይዛለች። የክርስቲያኑም ሕዝብ አኗኗር ከዚያው በመነጨ እውቀት ይመራል። እና፥ እኛም ልክ እንደ አካላዊ ዘረ መል (gene)፥ ከጥንት አባቶቻችን የወረስነው መንፈሳዊነታችን በውስጣችን እስካለ ድረስ (በአስተሳሰባችንና በአኗኗራችን ሁሉ ከምናመልከው ከእግዚአብሔር መንፈስ እስካልራቅን ድረስ)፥ ተራዳኢ መላእክትን አምላካችን ይልክልናል፤ እናት አድርጎ ለኛ የሰጠን እመቤታችን ማርያም አለችልን፤ ስለዚህ አንፈራም።

በመካከላችን ገብቶ የሚጫወትብን የእርኩስ መንፈስ ኃይል ከእንግዲህ እርሱ እንደ ሻማ ቀልጦ ይጠፋል፤ እንደ ጨው ሟምቶ ይፈሳል፤ እርሱ አውሎ ነፋስ ነቅሎ እንደጣለው እንደ የቤት ጣሪያ ይጣላል እንጂ፥ እኛን ወደ ገደሉ ሊከተን አይችልም። ከእንግዲህ ኢትዮጵያችንን ደፍሮ የሚጣላት ይመን እንደሚሸነፍ። በአንድ ወቅት፥ የመጨረሻው ዋዜማ ሲቃረብ፥ የሕዝቦች ማእበል ይነሳል፤ ክፉው መንግሥት ይፈርሳል፤ ጠላቶቿ ሊያፍርሷት ቢነሱ፥ እነርሱ ቀድመው ይፈርሳሉ፤ ኢትዮጵያችን ትዘልቃለች። የአለም መጨረሻም ቢሆን፥ ከሞት ይፈልቃል አዲስ ሕይወት፤ ሰይጣን ይሸነፋል፤ በምድር ይነግሣል የእግዚአብሔር እውነት።

አንድን የሀገር መሪ ለመምረጥ፥ ከሰው እና ከመንፈስ ቅዱስ ውጪ እርኩስ መንፈስም እጁን እንደሚያስገባ፤ እስካሁን ባየነው እጅግ አስከፊ እና ዘግናኝ ድርጊቶች ሁሉ ተምረናል። ከአሁን በኋላ ግን፥ የእርኩስ መንፈስን ሴራ የሚያከሽፍ አምላክ ዝም አይልም። ጊዜ ባነገሣቸው ኃያላን ምትክ በእርሱ የሚያምኑትን እና በሕዝቡ ፍላጎት የሚመሩትን ጠቢባን ይሾማል።[90]

---

[90] *"እሱም ጊዜያትን እና ዘመናትን ይለውጣል፤ ነገሥታትን ያስነሳል፤ ነገሥታትንም ይሽራል፤ ጥበብን ለጠቢባን፥ ዕውቀትንም ለአስተዋዮች ይሰጣል።" ዳን.* 2፡21

ተገፍተን ተገፍተን ከገደል አፋፍ የደረስነው አንድም ከፉውን ቀድመን ሳናይ በመቅረታችን እና "ብልጽግና" በሚል አጉል ተስፋ በመቆየታችን ምክንያት ስለሆነ፥ አሁንም እናስተውል። ከሕብረተሰባችን ጭንቀት አንጻር፥ የኢትዮጵያችንንም ወሳኝ ወቅት ከግምት ውስጥ በማስገባት፥ ሁሉም በየቤቱ ስለ ምድራዊ ኑሮው፥ ስለ ነፍሱም እንዲያስብበት፥ እርስ በእርሱ እንዲወያይ (እንዲመክር)፤ ሃሳባዊ አቋም ወስዶ፥ ወገን ለይቶ ይጠባበቅ። እንግዲህስ፥ ማየት ያለብንን አይተናልና፤ መቅመስ ያለብንንም ቀምሰናልና፤ አእምሮአችንን እና ልቦናችንን ለሰላም፥ ለፍቅር እና ለአንድነት ክፍት እናድርገው። ለወደፊት ሀገራችንን ለመምራት የሚነሱትም ሕሊናቸውን ይሰብስቡ። ሁሉንም ሰው በሰውነቱ ይመልከቱ። ሁሉን በእኩልነት ይዩት እንጂ፥ አንዱን ከአንዱ በማስበለጥ አይሁን።[91]

ከገደል አፋፍ ቆሞ፥ ጀሮ ያለው ማዳመጥ የሚችል ያዳምጣል፤ በአይነ ሥጋ የምናያቸው የዛሬዎቹ እና ወደፊት የሚመጡትም ጦርነቶች ልክ እንደ ብርሃን እና እንደ ጨለማ የሚለዩ፤ በእውነት እና በውሸት መካከል የሚካሄዱ ጦርነቶች ስለሆኑ፥ ሰው ሁሉ ወገን ለይቶ ይቁም።[92]

ያለፉት መንግሥታት የተጠቀሙት የአመራር ስልት ከእንግዲህ የአንዳቸውም ለኢትዮጵያ አያዋጣትም። ቀጣዩም መንግሥት በደንብ ቢያስብበት እና "ኢትዮጵያ ምድራዊ ብቻ አይደለችም፤ ሰማያዊም ናት" ብሎ ቢነሳ ነው ደጉ። የኛ

---

[91] *"የሐሰት እንጀራ ለሰው የጣፈጠ ነው፤ ከዚያ በኋላ ግን፥ አፉ ጭንጫ ይሞላል።" ምሳሌ 20፡17*

[92] *"እግዚአብሔር ተዋጊ ነው፤ ስሙም እግዚአብሔር ነው።" ዘጸ.. 3፡15*

*"የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይወጣል፤ ኀይለኛውንም ያጠፋል፤ ቅንአትንም ያስነሳል፤ በጠላቶቹም ላይ በኀይል ይጮሃል።" ኢሳ. 42፥ 13*

*"በአንተ ጠላቶቻችንን እንወጋቸዋለን፤ በስምህም በላዮቻችን ላይ የቆሙትን እናዋርዳቸዋለን።" መዝ. 43፡(44)፡5*

*"ልጆች ሆይ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ፤ አሸንፋችሁማል፤ በዓለም ካለው ይልቅ፥ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና።" 1ኛ ዮሐ. 4፡4*

*"ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና፤ ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው።" 1ኛ ዮሐ. 5፡4*

*"ነገር ግን፥ በወደደን በእርሱ ሁሉን ድል እንነሳለን።" ሮሜ. 8፡37*

ትግላችን ሁሉም ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ መኖሪያ መሆኗን የሚያረጋግጥ መንግሥት መመሥረት ነው። ቀጣዩም ትውልድ፥ እስከዛሬ ኢትዮጵያ ያስተናገደችውን፥ በግልጽ የሚታየውን ሥጋዊ ታሪኳን፥ በግልጽ ከማይታየው መንፈሳዊ ታሪኳ ጋር አብሮ ይመልከት። ሰው ሆኖ ከተፈጠረ (ንጉሥም ቢሆን ጳጳስ) ከውስጡ ክፋት ሊኖር ስለሚችል፥ ከክፉው ጋር እንዳንቆም ተመክረናል።[93]

አብሮ በመሆን ተቻችሎ በመታገል እንጂ፥ እርስ በርስ በመነቃቀፍ ሀገር ወደፊት አትቀድምም። የአንድ ግለሰብ ወይንም የአንድ ፓርቲ የትግል ውጤት በአንድ ትውልድ ውስጥ ላይታይ ስለሚችል፥ በየአቅጣጫው የሚደረገውን የሰውን ሁሉ ተሳትፎ ማክበር የሚያስፈልግበት ጊዜ ላይ ነን። ከተሳታፊ እንጂ፥ ከተቀማጭ ምንም አይገኝም።

እያንዳንዱ ሰው፥ በመልኩ እንደሚለያይ ሁሉ፥ በውስጣዊ ጠባዩም ይለያያል። እንዳው በጥቅሉም ስንመለከት፥ ብዙ አይነት ሰው አለ፤ በዛውም መጠን ብዙ አይነት ጠባይ አለ። የሰውን ጠባዩን ለውጦ ወደ አንድ ለማስጠጋት መሞከር፥ ሰውን ዳግመኛ ለመፍጠር እንደ መሞከር ይቆጠራል። ሆኖም፥ ከልጅነት እስከ እውቀት ሰዎች በጋራ የሚያዩት እና በጋራ የሚሰሙት፥ በሃሳብ ያቀራርባቸዋል። ስለዚህም፥ ክፉውን በክፋቱ፥ ደጉንም በደግነቱ የሚመለከቱበት ፍጥረታቸው (አይነ ልቡናቸው) ሰዎችን በአስተሳሰብ የጋራ አመለካከት እንዲኖራቸውና እንዲቀራረቡ ያደርጋቸዋል።

ወደድንም ጠላንም፥ አለምን በሁለት ማሕበራዊ ንቃተ ሕሊና በመከፈል ላይ ያለ ክስትት፥ የኢትዮጵያንም ሕዝብ እንዲሁ በሁለት እየከፈለ ነው ያለው። ለጊዜው ይህ ክስተት ጎልቶ ላይታይ ይችላል። ነገር ግን፥ ቀስ በቀስ፥ ግልጥ እየሆነ ይመጣል። ይኸም ክስተት እስከ አለም ጦርነት ድረስ ይዘልቃል እንጂ፥ እንዲሁ ተዳፍኖ የሚቀር አይደለም። የሰው ልጅ ሕይወት በውሸት እና በእውነት ትንንቅ ሲጨናነቅ፥ ጦርነት እና የሰው እልቂትም አብሮ እንደሚዘልቅ እንወቅ። ስለዚህ፥ ማንም ሰው ነፍስና ሥጋውን ለማዳን ጠላቱን ይለይ፤ ሀገርን ወገንን ለማዳን ይወግን፤ ነቅቶም ይጠብቅ።

እስከዚህ፥ ምድራዊ ፖለቲካን ከመንፈሳዊነትም ጋር እያነካካን (እንዳሻን) ሁሉን እንደመሰለን ተናገርን። አንዳንዶች ግን፥ “የአብሮነት እና የአንድነትን መንፈስ የሚያርቅብን፥ ነጻ ውይይትን የሚያስጠላን የእኛው የራሳችን ውስጣዊ ጠባይ ሆኖ ሳለ፥ እንዲህ ድክመቶቻችንን ሁሉ በሌላ (ዲያቢሎስ፥ ሰይጣን፥ ክፉ መንፈስ፥

---

93 *“በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፥ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ፥ እሱ የተመሰገነ ነው።” መዝ.1፥1*

ገለመሌ) እያሉ ማደባበስ፤ ምድራዊ የሆነ ፖለቲካን ከመንፈሳዊ እሳቤዎች እና ከእምነቶች (ከሃይማኖቶች) ጋር ማደባለቅ አይገባም...” የሚሉ ይኖራሉ።

አዎ! ማንነታችንን የሚገልጸው ምድራዊነታችን ብቻ ቢሆን ኖሮ፥ እነርሱ ልክ ናቸው ይባላል። ነገር ግን፥ የእኛ ማንነት በምድራዊነታችን ብቻ አይገለጽም (አይለካም)። እኛ በእግዚአብሔር አምሳያ የተፈጠርን ሰዎች መንፈሳዊነታችንም የማንነታችን መገለጫ ስለሆነ፥ የተፈጥሮ ማንነታችን (መንፈሳዊ ተፈጥሮአችን) አይለቀንም። ለዚህ ነው ሁሉንም በአንድ ገበታ ያቀረብነው።

የክፉ መንፈስ ክፉ ሃሳቦችን በመካከላችን የሚያሰራጭ ሰይጣን እውነትን ከሚከተሉ ሰዎች ላይ አይኑን አያነሳም። ስለዚህ፥ የጋራ እውነቶቻችንን በአንድ መስመር ለማምጣት ከፍተኛ መንፈሳዊ ተጋድሎን (ጾምና ጸሎት) ማድረግም እንደሚጠቅም እናስበው።

አለም የሰውን የእውቀቱን ምንጭ፥ አወጣጡ፥ አካሄዱ፥ ኃይሉና ብርታቱ እንዴት እንደሆነ ባለማወቁ (የሰውን እውቀቱን ከሰይጣናዊነት ለይቶ መመልከት ባለመቻሉ)፥ ይኸው እርስ በርስ እየተገዳደልን ከዚህ ደረስን። ይህም፥ ምድራዊነታችንን ከመንፈሳዊነታችን በማስቀደማችን የደረሰብን ፍዳ ነው።

ከእንግዲህስ፥ ምድሪቱ በሚጠላለፉ ሁለት አለም ውስጥ፥ እውነተኛ ሕይወት የሚኖሩት ሲያለቅሱ፥ ትያትረኞቹ የሚስቁበት ሁለት አይነት ሰዎችን እያስተናገደች አትቆይም።

ምጽአት እስኪቃረብ ለማይሰሙ፥ መሬት ሲንቀጠቀጥ፥ ተነስቶ መራመድ፥ ጋደም ብሎ፥ ተንጋሎ መተኛትም እስኪያቅት - የተቀመጥንበት፥ የቆምንበት፥ የሄድንበት፥ መሬቱ ሲያነጥር - አትቀመጡ፥ አትሂዱ፥ አትተኙ የሚያስብል - ከመቀመጫችን ቁጭ ብድግ የሚያደርግ - የምድሪቱ አመጽ ጅማሬ - እየገደለ ሙታንን የሚበላ፥ ኃጥአንን ከሙታን ሳይለይ ሁሉንም በጅምላ። አዎ! ለመጪው አዲስ ሕይወት ስትል፥ ለጊዜው ምድሪቱ ወንፊት መሆንን ትመርጣለች (ክፋውን ከደጉ ትለያለች)።

*ክፉ አድራጊዎች ይጠፋሉና፤ እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን፥ እነርሱ ምድርን ይወርሳሉ።” መዝ. 37፡9*

**ህልውናችን፥ አንድነታችን፥ ኢትዮጵያዊነታችን**

ሀገራችን (ያቺ) ለረጅም ዓመታት በአለም ታውቃና ተከብራ የቆየችው፥ በሰላም ወዳድ ሕዝቦቿ ፍቅር እና አንድነት መሆኑ፤ ህልውናችን፥ አንድነታችን እና ኢትዮጵያዊነታችንም እርስ በርስ እንደሚተሳሰሩ ይታወቃል።

በኢትዮጵያ/ኤርትራ የወደፊቱን መንግሥት ጥሩ የሚያደርገው - ለሕዝቦች የሚጠቅም መንግሥት መመሥረት የሚቻለው - በከፍተኛ የመንፈሳዊነት እድገት ስለሆነ፤ ሕዝቡ ለወደፊት አንድ ቅዱስ ሕዝብ ይሆን ዘንድ በጠባዩ፥ በአመለካከቱና በእምነቱ ጠንክር - ቀና ማለትን እንዲያውቅበት ሁኔታዎች ተስተካክለውለታል።

የወያኔ መንግሥት መምጣት ግዴታ እንደነበረ፥ ሕዝቡ ሁሉ በቃችሁ (ሲጋያ፤ ይአክለኩም፥ ወ.ዘ.ተ.) እያለ በተለያዩ ቋንቋዎች ሲመክርና ሲገስጽ፥ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ፍላጎት ተለይቶ ለወያኔዎች የማይገባቸውን ጊዜ እንዳልሰጣቸው ሁሉ፥ ለአሁኑ ግፈኛ መንግሥትም የመሰናበቺያ እንጂ፥ የመቆያ ጊዜ አይሰጣቸውም።

ከእንግዲህ የወደፊቱ የኢትዮጵያ መንግሥት የሕዝቦች ሁሉ የአንድነት ምልክት ይሆናል። ሕዝቡም የራሱን ኢኮኖሚ ለማዳበር ተስማምቶ፥ ተከባብሮና ተቻችሎ፥ አብሮ ይሠራል ተግቶ።

በኢትዮጵያ/ኤርትራ ብዙ መሠረታዊ ለውጦች ይከናወናሉ። የተበላሸው ይስተላከላል፤ በጥላቻ የታነጸ አእምሮ በፍቅር ይታደሳል።

አንዱን ከፍ አድርጎ ሌላውን ዝቅ ሳያደርግ፥ ካለ ምንም አድልኦ የሚያስተዳድር መንግሥት ይመጣል። የዛን ጊዜ ኢትዮጵያ (ከኤርትራ እና ከጎረቤት አገሮች ጋር) በቀናው ጎዳና እስከ አለም መጨረሺያ ድረስ ወደ ፊት ትጓዛለች።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች ተፎካካሪ (ተቃዋሚ/ተቀናቃኝ) ኃይላት አንዱ የሌላውን ጉድለት (ድክመት) በማስተጋባት (እርስ በርስ በመነቃቀፍ) እስከዛሬ ያጠፉት ጊዜ ውጤት አልባ ሆኖ አልቀረም። የእርስ በርስ ፍትጊያቸው የበለጠ እንዲተዋወቁ ስላደረጋቸው፥ ካሁን በኋላ በጋራ መሥራት የሚችሉበት ሁኔታ ተመቻችቶላቸዋል።

መላ የኢትዮጵያ ሕዝቦች (ኦሮሞ፥ ትግራይ፥ አማራ፥ አፋር፥ ወ.ዘ.ተ.) በጋራ የቀመሱት የከፋው ስርዓት ጦስ - ችግር፥ መከራ እና ስቃይ - በሃሳብም በስሜትም ከበፊቱ የበለጠ እንዲቀራረቡ አድርጓቸዋል። ደጋግ ሕዝቦች ባሉበት የከፋት መርዞችን እየነሰነሱ ያለፉት፥ እነርሱ ባልጠበቁት መስመር፥ አንድነታችን እንዲጠናከር ምክንያት ሆነውልናል።

ፈረንጆች፥ blessing in disguise/ድብቅ በረከት እንደሚሉት አይነት፥ ክፋቶች ደግነትን ባይወልዱም፥ በኢትዮጵያችን የክፋቶች እድገት ልክ አባ ጨጓሬ ወደ ቢራቢሮ እንደሚለወጥ ሆኖልናል።

ዛሬ ውስጣዊ ማንነታችን ብቅ ብሏል። ሼኩና ቄሱ አክራሪ ባለመሆን፥ “በሃይማኖት ብንለያይም፥ ሁላችንም የአንድ እግዚአብሔር ልጆች ነን” የሚል እሳቤ ሕዝቡን የበለጠ እንዲቀራረብ አድርጎታል። አኗኗሩም መንፈሳዊነትን የተላበሰ በመሆኑ፥ እርስ በርስ የሚተሳሰብ፥ በፍቅር ሰንሰለት የተሳሰረ ሆኗል።

*“ስርዓትህን እማር ዘንድ ያስጨነቅኸኝ፥ መልካም ሆነልኝ።”መዝ. 118(119)፡71*

የጥንት ኢትዮጵያውያኖችን/ኤርትራውያኖችን ሕብረተሰብአዊ አንድነት በሚመለከት የውጪ ጸሐፊዎች እንደሚከተለው ብለውላታል፦

"…Men are united by infinity of ties which would count for nothing in Europe. They live together in a reciprocal dependence and solidarity which they value highly and consider a matter of pride, and which influences all they do…” Davidson Basil, 2005 (Page 115)

*ወደ አማርኛ ሲተረጎም፦ “ሰዎችን እርሰበርስ አገናኝቶ አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ተቆጥሮ አያልቅም። በአውሮፓ እንዲህ ያለ ነገር የለም። ሕይወታቸው እርስበርስ በመረዳዳትና በመደጋገፍ የተጠናከረ ስለሆነ፥ የሚያደርጉት ሁሉ አንድነታቸውን የሚያጸና ነው። እነርሱም ይህን አብሮ መኖር እንደ አንድ ታላቅ ጸጋ ስለሚቆጥሩት ይኮሩበታል፤ የሚያደርጉት ሁሉ ከዚሁ የአብሮነት ጠባይ ጋር የተያያዘ ነውና።”*

እንዲህም ሲነገርላት የቆየች ሀገራችን በድህነትና በረሃብተኛነት ብትታወቅም፥ ያ ሰማያዊ ጠባይ ከሕዝቡ ዘንድ አልጠፋም - ድሃና ረሃብተኛ ሁሉ እንዳይሞት፥ ተረዳድቶ የሚኖር አንድ ቅዱስ ሕዝብ።

አንድ በተባበሩት መንግሥታት የእርዳታ ሰጪ ቡድን ውስጥ የሚሠራ ሰውዬ፥ በረሃብ ለተጎዱ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ምግብ ሲያድል፦ “አምላኬ! አምላኬ! እያለ ጸሎቱን የማያቋርጥ ሕዝብ፥ እኛ ከምንሰጠው ዳቦ ውጪ ሌላ ምን እያገኘ ነው እንዲህ ጤነኛ መስሎ የሚንቀሳቀሰው? ለመጸለይስ የሚያበቃውን አቅም ከየት ነው የሚያገኘው?” በማለት በአግርሞት ይጠይቃል።

ወደ ኢትዮጵያችን በየጊዜው የሚገቡ የውጪ ሀገር ጋዜጠኞችም በጦርነት እና በረሃብ የተጎዱ ወገኖቻችንን እያዩ ይጽፋሉ። ሁሉም ግርም የሚላቸው ግን፥

የሕዝቡ የመንፈስ ጥንካሬ ነው። “ኢትዮጵያ እየሞተች ብትሆንም፥ እንደገና ትወለዳለች” ብለው የሚያምኑ የውጪ ሀገር ጋዜጠኞችም አሉ።[94]

ለሰው ልጅ የሃይማኖት ትምህርት ብቻውን መንፈሳዊ አያደርገውም፤ በመከራ ውስጥ ሲያልፍ፥ መንፈሳዊነቱ ጎልቶ ይታያል። ኢትዮጵያም በፈተናዎች እና በተለያዩ መከራዎች ውስጥ ብትዘፈቅም፥ መንፈሳዊ እድገቷ አልተጨናገፈም። ይልቁንም፥ የበለጠውን በመንፈሳዊነቷ ከፍ ብላ በመታየቷ፥ ለተቀረውም አለም የምታስተምር ሆናለች።

በአሁኑ ዘመን፥ ምድራዊነት (ፍቅረ ነዋይ፥ በብልጭልጭ ነገሮች መማረክ፥ በአጠቃላይ ውጫዊነት) በግለሰቦች ሚዛናዊ አስተሳሰብ ላይ ከባድ ተጽእኖ ስለሚኖረው፥ አለም አቀፋዊ አስተሳሰቡም በዛው መጠን ከምድራዊነት እምብዛም የተላቀቀ አልሆነም። አለም አቀፋዊ አስተሳሰብ ከአህጉራዊ ወይንም የቡድን (የዘር) አስተሳሰብ ሲተልቅ፥ የዛን ጊዜ፥ እያንዳንዱ ግለሰብ በዙሪያው ያሉትን ሰዎች የሚመለከታቸው በውጫዊ መልካቸው ሳይሆን፥ በውስጣዊ ጠባያቸው ይሆናል።

ሰፊው ሕዝብ በሥጋዊ - ምድራዊ ሕይወቱ፥ ሃብት ንብረት አፍርቶ፥ በልጽጎ፥ ደስ ብሎት መኖርን ይመኛል። በሕይወት ለመኖር የሚያበቃ ሰላም ሲታጣ ግን፥ የመንፈሳውያን (የምእመናን) ጸሎት፥ የቤተ ክርስቲያን ደወል፥ የቅን ሰዎች ጩኸት ይበረታል። ምላሹም የእውነት አምላክ ከሆነው ከእግዚአብሔር የሰጣል።

በኃይለ ሥላሴ ዘመን የሕዝቦች መንፈሳዊ ጤንነት የተጠበቀ ስለነበር፥ በመጠኑ የሚኖር ሰው ደስተኛ ነበር። የሚያጠግብ እንጀራ ብቻ ቢሆን ኖሮ፥ ገዳማት በኢትዮጵያ እንዲህ እንዳሁኑ አይበዙም ነበር። ጊዜው መንፈሳዊነትን የትግል መሳሪያ ማድረግን ይጠይቃል። ሥጋዊና መንፈሳዊ ሆኖ ለተፈጠረ ሕዝብ የሚበጀው፡- እስላም ክርስቲያን ሳይል፥ ሁሉንም በእኩልነት የሚመለከት - የጠቅላላ ሕዝቦችን ሁሉ ሥጋዊ እና መንፈሳዊ ሕይወት በአንድነት የሚንከባከብ መንግሥታዊ አስተዳደር ነው። ትግላችንም እንዲህ ያለውን መንግሥት ለመመሥረት ነው።

እኛ የኢትዮጵያችን አንድነት ይመጣል ብለን ተስፋ የምናደርገው፥ በክፉው መንፈስ ዙሪያ ሊፈጸም ዘንድ ያለውን አውቀን፥ ክፉውን በሕብረት ስንታገል፤ በጋራ ስናዝን፥ በጋራ ስንጾም እና ስንጸልይ ነው። የክፉ ዘመን ማብቂያው አይታወቅም። ተረጋግቶ መቀመጥ ግፉን እንዲቀጥል ነው የሚያደርገው።[95]

---

[94] Francene Dufresne, 1985: L'Ethiopie se meurt! Mais renaîtra

[95] *“በልቅሶ የሚዘሩ፥ በደስታ ይሰበስባሉ።” መዝ. 125፡5*

አንድነታችን በመንፈሳዊነታችን ከተገነባ፥ በጋርዮሽ መበልጸግ እና ማደግ ቀላል ይሆናል። የዚያን ጊዜ ብቻ ነው የእኛም እድገት የጋርዮሽ ደስታን የሚያሰጠን። የዚያን ጊዜ ነው ምድራዊት ኢትዮጵያችንም ሰማያዊት የምትሆን።

ብሔረሰቦች ሁሉ ተጠራርተው፥
እናቶች፥ አባቶች፥ ከነልጆቻቸው፥
ቄሶችም፥ ሼኮችም አጀብ አጀብ አድርገው፥
ሁሉም ከንፈሮቻቸውን ከፍተው፥
ጥርሶቻቸውን ገልጠው፥
አብሮ በመሆን ብቻ ተደስተው፥
ሰው ምን ይለኛል በማይባልበት
በታላቅ አዳራሽ ተሰባስበው፥
በዘፈን፥ በእልልታ፥ በእስክስታና በሽጎዬ፥
ወደላይ - ወደላይ ጮቤ ረግጠው፥
አቤት ማማራቸው፥
እንዲህ ሲጎላ ጥሩነታቸው።
ግሩም ነው፥ ድንቅ ነው፥
የሰው ማንነቱ - ሁለንተናው፥
አዎንታዊነቱ እና እውነታው፥
መንፈሳዊነቱ ውስጣዊነቱን ሲገልጠው፥
በግላጭ ሲታይ ቁንጅናው፥
በመንፈሳዊ ኃይል ውዝዋዜው፥
ተዋዶ ለሚኖር ሰው
ለደስታውም ወሰን የለው።

እንዲህ የልዩነትን፥
የአሉታዊነትን ጉም የሚያባርር፥
በአዎንታዊ ብርሃን የሚቀይር፥
ሃብት፥ እድሜ፥ ጾታ፥
ጎሳና ሃይማኖትን የማይለይ፥

ይህ እንጂ'ኮ ነው፥
በበጎ ፈቃድ የሚመጣ መከባበር፥
የእኩልነት፥ የነፃነት፥
የሕብረት እና የአንድነት ምሥጢር፤
በመንፈሳዊነት የሚገኝ፥
እውነተኛ ፍቅር።

በምድራዊ አስተሳሰብ የተገነባ የሰው ልጅ ከሥጋዊነቱ ጋር መንፈሳዊነቱንም ካላዋሃደ፥ ችግሮቹን ሁሉ ከምድራዊነቱ ባገኘው ጥበብ ብቻ ለመፍታት እንደማይችል ችግር እና መከራ አስተምሮናል።

አንድ ግለሰብ ዘወትር ስለ ራሱ ሕይወት ብቻ ቢያስብ እና ኑሮ ቢያስከፋው፥ ምድራዊ ከፋቶች ወደእርሱ ብቻ እያነጣጠሩ የሚመጡ እየመሰለው ጭንቀት ውስጥ ሊገባ ይችላል። ከራሱ ወጣ ብሎ ለሌላውም ማሰብ ሲጀምር እና ማሕበራዊ ንቃተ ሕሊና ውስጥ ሲገባ፥ ከራሱ አልፎ፥ ለሌሎችም ርህራሄ ይሰማዋል። ከራሱ ችግር አንጻር በሌሎች ላይ የሚደርሰውን እየተመለከተ ይጽናናል እንጂ፥ በከንቱ አይጨነቅም። ለዚህ ነው፥ በርህራሄ እና በበጎ አድራጎት ላይ የተመሠረቱ ተግዳሮቶች፥ የገዛ ሕይወትን ለሌሎች አሳልፎ እስከ መስጠት ሲደርሱ የምናየው።

በአንዳንድ የአካባቢ ሁኔታዎች ምክንያት ሰዎች በአብሮነት ይኖሩ ዘንድ ግዴታ ይሆንባቸዋል። አብረውም ሲኖሩ አብሮ ማሰብ፥ አብሮ መሥራትን ይለምዳሉ። በዚህም ምክንያት፥ የሰውን ልጅ (ወዶም ሆነ ሳይወድ) እያንዳንዱ በግላዊ ሃሳቡ እየተመራ እንዳይበታተን፥ እርስ በርሱም እንዲቀራረብ የሚያደርገው እንደ ማሕበራዊ እውቀት የሚቆጠር ማሕበራዊ ንቃተ ሕሊና (social conceousness) ተሰጥቶታል።

ማሕበራዊ ንቃተ ሕሊና፥ አንድ ሰው (ክፉ ሰውም ቢሆን/ደግ ሰውም ቢሆን) ዙሪያውን ሲመለከት፥ ከሚያየውና ከሚገነዘበው፥ ወደ አእምሮው ዘልቆ በመግባት ስሜቱን የሚቀሰቅስ፥ የአስተሳሰቡን ዝንባሌ ወደ ርህራሄ ወይንም ወደ ጭካኔ የሚወስድ፥ ወደ ፍቅር ወይንም ወደ ጥላቻ የሚመልስ፤ በአጠቃላይ፥ ውስጣዊ ማንነቱን የሚያጎላ፥ በትምህርትም፥ ካለ ትምህርትም የሚገኝ ነው።

አንድ ግለሰብ በራሱና ለራሱ (ለሥጋውና ለነፍሱ) የሚበጀውን ሁሉ ቢያደርግ፥ ግን ከራሱ አልፎ ከጎኑ ላለ ሰው እንግዳ ሆኖ ብቻውን ቢቀመጥ፥ ይህ ምን ትርጉም አለው? የመንፈሳዊነት ግቡ ምንድነው? ጥቅሙ ለራስ ብቻ ከሆነ፤

ለሕብረተሰብ፥ ለሀገር ለወገንም ካልጠቀመ። ግለሰብ ለራሱ የሚያደርጋቸው ሁሉ አብረውት ይሞታሉ፤ ለሌላው የሚያደርጋቸው ግን ዘለአለማውያን ናቸው።

ምንጊዜም እውቀት እና እውነት ከታላቁ ሥፍራቸው ተነስተው ወደ አናሳው ወደ አንድ ግለሰብ ሲዘዋወሩ፥ ሁለቱም ኩስስ ይላሉ፤ ከብዙዎች ዘንድ ሲገኙ ግን፥ ታላቅነታቸው ይረጋገጣል። ለዚህ ነው በአንድነት እና በሕብረት ማሰብ እና መሥራት አስፈላጊ የሚሆነው።

በማሕበራዊ ንቃተ ሕሊና፥ እያንዳንዱ ሰው ከግላዊነቱ እየወጣ፥ ችግሩን፥ ደስታና ሃዘኑን ሕብረተሰብአዊ ቢያደርገው፥ የሰዎች ስሜት መንፈሳዊ ዝንባሌ ይኖረዋል። በጋርዮሽም ሲተሳሰር፥ ደስታም ሆነ ሃዘን የጋራ ይሆናል። ሃዘኑም ቢሆን ተስፋና ደስታን አዘል ይሆናል እንጂ፥ ፍጹማዊ ሃዘን አይሆንም።

ኢትዮጵያችንን ከተዘረጋባት ክፉ ወጥመድ ልናድናት የምንችለው፥ ከምድራዊ እይታዎች ባሻገር፥ በሃሳብ እና በመንፈስ አንድነታችንን የምናጠናክርበትን ዘዴ በመፈለግ ስለሆነ፤ "እኛ እንዴት ከጥፋት እንዳን? የሀገራችንን መንፈሳዊ አንድነትስ የምንመልሰው እንዴት ነው?" እያልን እራሳችንን ስንጠይቅ፥ ከምድራዊ እና ሰማያዊ የማንነታችን እውነቶች ጋር እንገናኛለን።

በማንኛውም ጊዜ (ለክፋም ሆነ ለደግ)፥ ሰዎች እርስ በርስ፥ ሃሳብ ለሃሳብ ሲለዋወጡ፥ ትንሽ - ትንሽ አንዱ ሌላውን ይመስላል። በዚህን ጊዜ ክፋቶችና ደግነቶች ሁሉ ካንዱ ወደ ሌላው ይዛመቱና ሁለት አቢይት ማዕበሎች ይፈጠራሉ። የክፋት ማዕበሎች ሲደማመሩ ሰው እርስ በርሱ ይጨራረሳል። የደግነትም ማዕበሎች ሲደማመሩ ማሕበራዊ ግንባታ ይሆናል፤ ሁለቱ ተቃራኒ ማዕበሎች ሲደነቃቀፉ ደግሞ ምንም ሳይሠራ እድሜ መፍጀት ብቻ ይሆናል።

የሰው ልጅ በምድራዊ ሥልጣኔ ጠፈር ቢዳስስ እንኳን፥ ከሥጋዊነቱ ጋር መንፈሳዊነቱንም ካላዋሃደና፥ በምድራዊ ሕይወቱ ብቻ ተወስኖ ከቀረ፥ በዚች ጠባብ ምድር ውስጥ፥ እንደ ቁጫጭ፥ ከመርመስመስ የተለየ ዘለአለማዊ ሕይወት አይኖረውም። ሥጋ ሥጋ ነውና፤ ግኝት፥ ጥፍት እያለ ነው ከዚህ የደረሰው፥ ልክ እንደ ዘመሚት - እንደ ጉንዳን፥ ወ.ዘ.ተ.።

የሰው ልጅ ከጠባብ ሥጋዊ - ምድራዊ ርዕዮት እየተላቀቀ፥ ጠፈራዊ ንቃተ ሕሊና ይኖረው ዘንድ ተፈጥሮአዊ ግዴታ (እድገት) ነው። ከጠባቡ ሥጋዊ - ምድራዊ

ሕይወታችን (በአስተሳሰብ - በእምነት) እየተላቀቅን ወደ ሰፊው እንገባለን፤ በሰማይ ያለው በምድር ካለው ይበልጣልና።[96]

ሕያዋን ከሕያዋን ጋር መኖርን ይሻሉና፤ እኛም ከሰማያዊ ሕያዋን ጋር ለዘለአለም እንደምንኖር፥ ይህ ነው እምነታችን። የሰው ልጅ ምድራዊ ቢሆንም፥ በእግዚአብሔር እስትንፋስ ከሰማይም የመጣ እንጂ፥ ከዚሁ ከምድር ብቻ እንደ ሳር ያልበቀለ ስለሆነ፥ ያንን ሰማያዊነቱን (ዘለአለማዊነቱን) ለመቀጠል ጠፈራዊ ንኪኪ ይኖራል (አስፈልጓልም)። ይህ እውነት ስለሆነ፥ ነፍሱ ከብርሃን ፍጥነት በበለጠ በመጓዝ፥ ጥልቅ የሚልበት ሥፍራ ተዘጋጅቶለታል።[97]

እስከዛሬ በአንድነታችን ጸንተን እንድንቆይ ያደረገን፥ በእግዚአብሔር ላይ ያለን ጽኑ እምነታችን ለወደፊትም ይቀጥላል። ስለሀገራቸው ያለቀሱ የነነዌ ሰዎችን ልቅሶ የሰማ አምላካችን፥ የእኛንም ልቅሶ እንደሚሰማ በየጊዜው ያየነውና የምናውቀው ስለሆነ፥ የእኛ እምነት የጸና ነው። ስለዚህ፥ የጥንቱን ማሕበራዊ ኑሮአችንን፥ በአንድነታችን ስለሚገኘውም የጋራ ጥቅም እያሰብን፥ ሀገራችንን፥ ሃይማኖታችንን እና ጠቅላላ የሰውን ዘር ከጥፋት ለማዳን የምንችለውን ሁሉ እናድርግ፤ በጸሎትም እንትጋ።

አብሮነታችን (አንድነታችን) ከሌለ፥ በምድራችን ተደላድለን መኖር ያቅተናል። የሰው ልጅ ክፉ የሚሆነውና አብሮነትን የሚጠላው፥ ምድራዊ መንፈስ አንቆ ስለሚይዘው ነው። እኛ ሁላችንም ምድራዊያን ብቻ ብንሆን ኖሮ፥ ምንም ሳናጉረመርም፥ ጥሩና መጥፎውንም ሳንለይ፥ በምድራዊነታችን ብቻ "ተደላድለን" እንኖር ነበር፤ ክፉውን ሁሉ እየሠራን። ነገር ግን፥ በተፈጥሮአችን የጥሩነት መንፈስ ስላለብን፥ መጥፎውን አይተን በቸልተኝነት ማለፍ ያቅተናል።

ከእንግዲህስ፥ ኢትዮጵያችንን የሚያተራምሷትን ጥቂት የማይባሉ እርኩሳን መናፍስትን በሕብረት ለማጥፋት ተማምለን እንነሳ። ሁላችንም በአዎንታዊነት ተባብረን ውዲቷን ሀገራችንን በማስቀደም በአንድነት ከተነሳን፥ ይህች በመንፈሳዊ ጎኗ

[96] *"እነሆ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይሆናልና፤ የቀደሙትም አይታሰቡም፤ ወደ ልብም አይገቡም።" ኢሳ. 65፥17*

[97] *"በአባቴ ቤት ብዙ ማደሪያና ማረፊያ አለ፤..." ዮሐ. 14፥2*

ቆንጆ የሆነች ሀገር በሥጋዊ ጎኗም አምራና ደምቃ የምትታይበት ወቅት መምጣቱ አይቀርም።[98]

ምንጊዜም ሰማያዊ መፍትሄ መኖሩንም አንርሳ። የመንፈስ ቅዱስ አሰራር ከምድራዊ ስነ አመክንዮ (logic) በላይ፥ እጅጉን የላቀ መሆኑን አንዘንጋ። በምድራዊ ትምህርት (ሳይንስና ሌላም) የጠለቀ እውቀት ያላቸውም የመንፈስን ሥራ አይናቁ፤ የማናውቀው ከምናውቀው ይበልጣልና። የመንገዳችን አቅጣጫ ወደ ፍጹሙ የሚያደርስ ካልመሰለን፥ ረጋ ብለን እናስብ። ተስፋችንም ሕልም ብቻ ሆኖ እንዳይቀር፥ እንደጋገፍ፤ እንተባበር፤ ለኢትዮጵያችን ብርሃን የሚሆን ማንም የለም፥ ከኛ በቀር።

በሳቅና ፈገግታ ፋንታ
ልቅሶ እና ትካዜም ቢሆን የኛ ፋንታ፥
በዘፈን እና ጭፈራ ፋንታ
ሙሾ ማውረድም ቢሆን የኛ ደስታ፥
በመዝሙር እና በውዳሴ ፋንታ
መርዶ መስማት ቢሆንም የኛ ትውስታ፥
ከአካላዊ ማማር እና ከቁንጅና ፋንታ
ሰንበር እና ጠባሳም ቢሆንም የኛ ትዝታ፥
ሁሉንም እንማርበታለን በቀስታ።
አይን ባየው፥ አእምሮ ባሰላው፥
ለሃዘን መጠን፥ ለግፍም ምላሽ አለው።
ከእንግዲህ ማነው የሚያይለት? የሕዝቡን ጉዳቱን፥
እንግሊዝ፥ ፈረንሳይ ወይንስ አሜሪካን?
እባክህ አምላካችን በቃችሁ በለን፤
የሃዘን እንጉርጉሮ በሽታ ሆነብን፤
ኢትዮጵያን/ኤርትራን ጠብቃት፤

[98] *"አቤቱ! ቅጣን፤ ነገር ግን ፈጽመህ እንዳታጠፋን በፍርድህ ይሁን እንጂ፥ በቁጣህ አይሁን።"ትንቢተ ኤርምያስ 10፡24*

እባክህ ተመልከተን - አትሰውር ፊትክን።

በሰው ልጅ መከፋት ማርያም ታለቅሳለች፤
ሃዘን አልቀረላት፥ ኢትዮጵያን እያየች።
እመቤቴ ማርያም አታቋርጪ ጸሎትሽን፥
እባክሽ ለምኚው አስራት የሰጠሽን - ልጅሺን፥
ምህረቱን እንዲያወርድልን፤
ደጉን መንግሥት እንዲያመጣልን።
እግዚአብሔር ይሰማል - ፈጣሪያችን፥
ሕዝቦቹንም ይጠብቃል - አምላካችን፥
የአለማችን (ያገራችን) አየሩን፥ አፈሩን ድንጋዩን፥
ሁሉንም እንዲባርክልን፥
እንለምነው፤ አያቋርጥ ጸሎታችን፤
እግዚኦ ማለታችን - እግዚኦ ማለታችን።

ዳገቱን ስንወጣ የቆሳሰልንበትን ትኩሱን ቁስላችንን ስናየው ያስፈራናል። በየመንገዱ እያለቀስን፥ በእንባ እየተራጨን ከዚህ ደረስን። እግዚአብሔር እንደሚያየን እናውቃለን። ቁስሉ ይድናል፤ ጠባሳው ግን፥ የሕዝቦችን ጩኸት፥ ልቅሶና ዋይታ የማይሰሙ ክፉዎች ያደረሱብንን ጉዳት ስለሚናገር፥ ለምልክትነት ይቀራል። የወደፊቱም ትውልድ እንደ ታሪክ የተቀመጠለትን፥ ይህንን ምንጊዜም የማይጠፋ ጠባሳ እያየ ይማርበታል።

ነፋስ ሲያፏጭ፥ ጠላት ሲዘምር፥
የሙታን ጩኸት ሲሰማ ከመቃብር፥
የዛን ጊዜ ይሆናል መጨረሻው፤
የጨለማ ግርዶሽ መገፈፊያው።
ሰይጣን ከምድር ገጽ ይጠፋል፤
የአምላካችን ፈቃድ በምድር ላይ ይሆናል፤
ጻድቃን ምድርን ይወርሷታል።

እንግዲህ የሁላችንም ምኞትና እና ጸሎት፥ አሁን ካለንበት አስቸጋሪ ሁኔታ ወጥተን በብርሃን እንድንመላለስ ከሆነ፥ በሀገሪቱ ያለው የተበታተነ/የጎሳ ፖለቲካ ወደ ሰላማዊ አብሮነት እና አንድነት ወደሚያመራው ንቃተ ሕሊና ከተመለስን ሊፈታ

ይችላል። ሕዝቡ ፈሪሃ እግዚአብሔር ሲያድርበትና የንቃተ ሕሊናውም እድገት ይህንኑ ተከትሎ ከሆነ፥ ኢየሱስ ሐዋርያትን *"እስከ ዓለም ፍጻሜ በዘመኑ ሁሉ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ"* እንዳላቸው፥ እግዚአብሔር በመካከላችን ይገኛል። እንግዲህ እኛ ኢትዮጵያዊያን ሁላችንም በማንቸውም እንቅስቃሴዎቻችን ውስጥ የእግዚአብሔርን መንፈስ በመካከላችን እንዲገኝ በጎ ፈቃዳችን ከሆነ፥ የሁላችንም እውነቶች ተደጋግፈው ኢትዮጵያችንን ከወደቀችበት ቀና ያደርጓታል። ከዚያም ቀጥሎ፥ ሁሉም ጥሩ ይሆናል።[99]

በእውነት ፈጣሪ አምላካችን እግዚአብሔር ፍጹምና ኃያል፥ ስሙ ክቡር ለዘለአለምም የተመሰገነ ነው።

ቸሩ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ኢትዮጵያችንን ይጠብቃት። መሆን ያለበት ይሆን ዘንድ፥ ሁሉን የሚያውቅ እግዚአብሔር ነውና፤ ምድራዊ ያልሆነውን የመንፈሳዊነታችንን ነገር እግዚአብሔር ይገልጥልናል።

በሃሳብ አንድ ብንሆን፥ በመንፈስ አርቅቀን እንኄዳለን፤ ምድራዊ ኃይል አይበታትነንም።[100]

ለመሠረታዊ ለውጥ፥ ለአዲስ ስርዓት እና ለአዲስ መንግሥት በሕብረት እና በአንድነት እንነሳ። ለዚህም፥ እግዚአብሔር ይርዳን።

እግዚአብሔር የብዙሃኑን አእምሮ ይከፈትልን። መልካሙን እንድናይ፥ ቀናውንም መንገድ እንድንከተል፥ አይነ ልቦናችንን ያብራልን።

የእመቤታችን እና የእናታችን የማርያም ጸሎት እና ምልጃ አይለየን።

አስጀምሮ ላስጨረሰን ለፈጣሪ አምካችን ታላቅ ምስጋና ይድረሰው።

አሜን።

---

99 *"ያዘዝኋችሁንም እንዲጠብቁ አስተምሩአቸው፤ እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ በዘመኑ ሁሉ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ።" ማቴ. 28፡20*

100 *"እግዚአብሔርንም ለሚወዱት፥ እንደ አሳቡም ለተጠሩት፥ ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ፥ እናውቃለን።" ሮሜ 8፡28*

**ኢትዮጵያ ልጆችሽ ያንቺው ናቸው (መዝሙር መንፈሳዊ)**

አዝማች

ኢትዮጵያ ልጆችሽ ያንቺው ናቸው፥
አይለይም ከሕዝብ ልቡናቸው፥
አይርቅም ከወገን መንፈሳቸው።
አንቺ ቅዱስ ሀገር፥ ትዝታዬ፥
ሳልምሽ አድራለሁ ባይምሮዬ፤
ሳልምሽ አድራለሁ ባይምሮዬ።

ምድራዊ ችግሮች -- ከሩቅ በተናቸው፥
በአካል ተለዩ -- ወጡ ካገራቸው።
ይህ ችግር ጊዜያዊ -- ከቶም ይበቃዋል፥
ሁሉም ከሄደበት -- ፈጥኖ ይመለሳል።

አዝማች

እናንት ያገር ልጆች -- ትጉ በያለበት፥
መልካሙን አስቡ -- አትራቁ ከእውነት፤
በብልጭልጭ ነገር -- መታለሉ ይቅር፥
ለሕዝቦች እናስብ -- ለራስ ማሰብ ሳይቀር።

አዝማች

ለማግኘት አንጓጓ -- ለመስጠት እንሩጥ፥
ከቶ ምንም የለም -- ከመንፈስ የሚበልጥ፤
ችግር የሚረሳው -- ደስታም የሚገኘው፥
ለሌላው በማሰብ -- በእምነት በመኖር ነው።

አዝማች

ኢትዮጵያ ሀገራችን ሰብስቢን በአንድ ላይ፥
እርስ በርስ ተፋቅረን ክብርሽን እንድናይ፤
ለአንቺም ቀን ይውጣልሽ - እግዜር ይለመንሽ፤
የእናታችን ማርያም ፍቅሯ አይለይሽ።

## ጸሎት

**አቤቱ ፈጣሪአችን አምላካችን ቸሩ እግዚአብሔር ሆይ!**

እኛ ሰዎች አብረን ስንኖር በፖለቲካ፥ በሃይማኖት እየተለያየን እርስ በርሳችን ከመጣላት የሚያድነንን፥ ሰላማችንን እና አንድነታችንን የምናገኝበትን መንገድ አንተ ታሳውቀን፥ አንተም ትመራን ዘንድ እንለምንሃለን።

ቅዱስ መንፈስህን ከአለም ሕዝቦች አታርቅ። ሕዝቦች ሁሉ ለፍቅር፥ ለሰላምና ለአንድነት የሚቻኮሉ፥ በጽድቅ ጎዳና በአንተ ፈቃድ የሚመላለሱ እንዲሆኑ፥ በነውንም መንገድ እንዲሹ አንተ እርዳቸው።

ያንተ የሆኑ ሕዝቦች ሁሉ በያሉበት የእውነት ሰዎች ለመሆን በሚያደርጉት ጥረት ቅዱስ መንፈስህ እንዳይለያቸው እንለምንሃለን። የሕዝቡን ጉዳቱን ተመልከት፤ እባክህ አምላካችን በቃችሁ በለን፤ የሃዘን እንጉርጉሮ በሽታ ሆነብን፤ ኢትዮጵያን/ኤርትራን ጠብቃት፤ እባክህ ተመልከተን - አትሰውር ፊትክን።

ኢትዮጵያን ሀገራችንን ጠብቅልን፤ ለሕዝቦቿም ሰላም፥ ፍቅር፥ ሕብረት እና አንድነትን ስጥልን።

**አሜን**

**ተፈጸመ**

# ዋቢ መጻሕፍት

## (ለአራቱም መጻሕፍት)


Abdullah Yusuf Ali (Translation by), 2002: **The Qur'an**, Published by Asir Media.

Bartusiac Marcia (edited and with Introduction), 2006: **Archives of the Universe**, Vintage Books, A Division of Random House, INC. New York.

Bhaktivedanta Swami Prabhupada A.C (His Devine Grace), 1972, 1983: **Bhagavad Gita As it is,** The Bhaktivedanta Book Trust.

Charles Darwin, 1958: **The Origin of Species**, Signet Classics.

Close Frank, 2009: **Anti Matter,** Oxford University Press.

Coogan Michael D., 2003: **World Religions,** Duncan Baird Publications, London.

Davidson Basil, 2005: **Africa in History**; Touchstone, Rockfeller Center, New York, N.Y.

Drage Hale Rosemary, 2004: **Understanding Christianity**, Duncan Baird Publishers, London.

Ehrlich Carl S., 2003: **Understanding Judaism**, Duncan Baird Publishers, London.

Elain Murray Stone, 2004: **A Saint and His Lion, the Story of Tekla of Ethiopia,** Paulist Press.

Francene Dufresne, 1985 : **L'Ethiopie se meurt!** Mais renaîtra, Louise Courteau éditrice

Hammond, 2002: **Concise Atlas of World History**, 6th Edition, Map Makers for the 21st Century; HarperCollins Publishers.

Hausman Gerald, 1997: **The Kebra Nagast**: St. Martin's Press, New York

Hawking W. Stephen And Leonard Mlodinow 2010: **The Grand Design**; Bantam Books, New York.

Hawking W. Stephen, 1988: **A Brief History of Time**, From The Big Bang to Black Holes; Bantam Books, New York.

Hawking W. Stephen, 2005: **The Theory of Everything**, Fate of The Universe; Phonix Books.

Houston Drusilla Dunjee, 2007: **Wonderful Ethiopians of The Ancient Empire**; Nuvision Publications, LLC, Sioux Falls, SD, USA.

Jackson G. John, 1939 And 1985: **Ethiopia and the Origin of Civilization**; Nuvision Black Classic Press, Baltimore, MD. USA.

John Brockman (Editor), 2010: **This Will Change Everything**, Ideas That Will Shape The Future; Harper Collins Publishers, New York, NY. 10022.

Laszio Ervin, 2006: **Science and The Enchantment of The Cosmos**; The Rise Of The Integral Vision Of Reality, Inner Traditions, Rochester Vermont.

Leslau Wolf, 1976: **Concise Amharic Dictionary**, Amharic - English, English - Amharic, Otto Harrassowitz – Wiesbaden, Commercial Printing Press, Adds Ababa, Ethiopia

Mary And John Gribbin, 2003: **From Atoms to Infinity**; Icon Books.

Muhaiyaddeen Bawa M.R., 1987, revised 2004: **Islam and World Peace, Explanations of a SUFI,** The fellowship Press, Philadelphia, PA.

Oldstone Moore Jennifer, 2003: **Understanding Confusianism**, Duncan Baird Publishers, London.

Rana Fazal & Ross Hugh 2004: **Origin of Life**; Navpress, Colorado Springs, CO80920.

Ross Hugh 2010: **Beyond the Cosmos**, **What Recent Discoveries in Astrophysics Reveal About the Glory and Love of God,** 2010:Signalman Publishing, Orlando, Florida.

Southwood, Richard 2002: **The Story of Life**, Oxford University Press.

Steinberg Milton, 1975: **Basic Judaism**, Harcourt Brace Jovanovich, Publishers. San Diego, New York, London.

Vorilhon Claude, 1983፡ **Le Livre Qui Dit La Verite**

Wallis Budge (1932): **The Kebra Negast,** Oxford University Press, London, Humphrey Milford.

ልዑለ ቃል አካሉ (መምህር)፥ 1994፤ ***ሥርአተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ***፥ አትላንታ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፥ ዩ ኤስ ኤ፥ አታሚ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።

ልዑለ ቃል አካሉ (መምህር)፥ 1994፤ ***ሥርአተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ***፥ አትላንታ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፥ ዩ ኤስ ኤ፥ አታሚ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።

መሪራስ አማን በላይ፥ 2007፤ **ሕይወት እንደገና በሦስት አለሞች**።

ሰሎሞን ይርጋ፥ 1992፤ **ህልውና**፥ አታሚ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ቦጋለ ተፈሪ በዙ፥ 2011፤ **ትንቢት ሼህ ሁሴን ጂብሪል**።

ተስፋ ገብረ ሥላሰሴ (አዘጋጅ)፥ 1978፤ **ገድለ አቡነ አረጋዊ**፥ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ (1951)፤ ***የኢትዮጵያ ታሪክ*** 2ኛ መጽሐፍ።

ትንሳኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት (አሳታሚ)፥ 1990፤ **ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው**፥ ትንሳኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ።

አቡነ ሽኑዳ 3ኛ የግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ (ውርስ ትርጉም በዲያቆን ታደሰ ወንድም አገኘሁ)፥ 1993፤ **የንስሐ ሕይወት፥** ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት፤ አዲስ አበባ።

አባ ኤልያስ ሊቀ ጳጳስ፥ 2009፤ **በአዲስ መሠረት ላይ የነበረው ጥረት፥** Washington D.C. 20018 USA.

አባ ጎርጎርዮስ፥ 1978፤ **የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፥** ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

አባ መልከጼዴቅ፥ ሊቀ ጳጳስ፥ 2011፤ **የቅዳሴያችን ይዘት፥** ኦክላንድ፤ ካሊፎርኒያ-አሜሪካ፤ ጣና ማተሚያ ቤት፥ ቶሮንቶ፥ ካናዳ።

አንዱ ዓለም ዳግማዊ (መምህር)፥ 1998፤ **ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት፥** ኅትመተ ብራና ማተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ።

አንዱ ዓለም አባተ (የአጸደ ልጅ)፥ 2010፤ **ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ፥** እና ሌሎች ግለ-ወጎች።

አንዱ ዓለም አባተ (የአጸደ ልጅ)፥ 2010፤ **ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ፥** እና ሌሎች ግለ-ወጎች።

አባ ፊሊጶስ፡ 1992፡ **ገድለ ክርስቶስ ሠምራ፡** ተስፋ ገብረ ሥላሰሴ (አዘጋጅ)

ብሩህ ዓለምነህ፥ 2010፤ **የኢትዮጵያ ፍልስፍና የዘርርዓ ያዕቆብና የወልደ ሕይወት ሐተታዎች ትንታኔ (ከነሐተታቸው)**

ዓባይነህ አስፋው፥ 2012፤ **መጽሐፈ ሔኖክ ግዕዝ እና አማርኛ ከአንድምታ ማብራሪያ ጋር።**

ዐቢይ አሕመድ፥ 2012፤ **መደመር፥**

ኢንተርናሺናል መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር፥ 2001፤ **መጽሐፍ ቅዱስ፥** አዲሱ መደበኛ ትርጉም፥ International Bible Society.

ዓሥራት ገብረ ማርያም፤ 1991፤ **ትምህርተ መለኮት፥** ሁለተኛ እትም፥ ንግድ ማተሚያ ቤት ድርጅት፥ አዲስ አበባ።

ዓባይነህ ካሴ፥ 1992፤ **የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥** ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አንደኛ መጽሐፍ፥ አሳታሚ ማሕበረ ቅዱሳን፥ አዲስ አበባ።

ኤፍሬም አሰፋ ወረደወርቅ፥ 1992፤ **አዲሱ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፥** ሁለተኛ እትም።

ኤፍሬም አሰፋ ወረደወርቅ፥ 1995፤ **ሚሊንየም እንግሊዝኛ-አማርኛ መዝገበ ቃላት፥** Revised Edition.

እሸቱ ታደሠ ወንድም አገኘሁ (ዲያቆን) እና ደጀኔ ሽፈራው በላቸው (ዲያቆን)፥ 1991፤ **ወላዲተ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ፥** ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት፤ አዲስ አበባ።

ወሰኔ ይፍሩ፤ አዘጋጅ፤ 1990፤ **ሄኖክ**፤ በየዓመቱ የሚታተም የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር መጽሔት፥ 1101 S.W. Washington St. Suite 129 Portland, OR 97205

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር (አሳታሚ)፥ 1980፤ **መጽሐፍ ቅዱስ**፥ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፥ መጀመሪያ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ፥ United Bible Societies Africa Regional Centre, Nirobi, Kenya

የጥንት ሊቃውንት እንደ ጻፉትና እንደተረጎሙት፥ 1983፤ **ተአምረ ማርያም፥** አንደኛ መጽሐፍ፥ አዘጋጅና አከፋፋይ ተስፋ ገብረ ሥላሰሴ፥ አዲስ አበባ።

የጥንት ሊቃውንት እንደጻፉትና እንደተረጎሙት፥ 1946፤ **ገድለ ተክለ ሃይማኖት፥** ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

ዲበኩሉ ዘውዴ፥ 1986፤ **ፍትሐ ነገሥት ብሔረ ሕግ ወቀኖና**፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

ዘበነ ለማ (መምህር/ዶክተር)፥ 2019፤ **ምንትኑ ውእቱ ሰብእ ሰው ምንድን ነው? የማንነትን ትርጉም ፍለጋ፥** አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ

ጥዑመ ልሳን ካሳ (ሊቀ ካህናት - ርዕሰ ደብር)፥ 1981፤ **ያሬድና ዜማው፥** ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።